# መጽሐፈ ምስጢር

## ክፍል አንድ

ደራሲ፦
አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ተርጓሚ፦
መምህር
ኃይለ ማርያም ላቀው

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን

አዲስ አበባ
፳፻ (2000) ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

© ማኅበረ ቅዱሳን ፳፻ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ALL RIGHTS RESERVED

ይህ መጽሐፍ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
በማኅበረ ቅዱሳን
ኤዲቶሪያል ቦርድ ታርሞ ተስተካክሎ የተፈቀደ ነው፡፡

አድራሻ፡-

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ
በሰ/ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
ፖ.ሳ.ቁ 80078
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- lemat@eotc-mkidusan.org
Website;-www.eotc-mkidusan.org

የኮምፒውተር ጽሑፍና ቅንብር

የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ዋና ክፍል



# ማውጫ

ገጽ

መግቢያ ..........

ምዕራፍ አንድ

፩. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና ሥራዎቹ .......... 1
፩.፩ ዜና ሕይወቱ ለአባ ጊዮርጊስ .......... 1
፩.፩.፩ ልደት .......... 1
፩.፩.፪ ትምህርት .......... 2
፩.፩.፫ ምንኩስናና ተጋድሎ .......... 5
፩.፪. ሥራዎቹ .......... 12
፩.፪.፩ አርጋኖን .......... 12
፩.፪.፪ እንዚራ ስብሐት .......... 12
፩.፪.፫ ውዳሴ ሐዋርያት .......... 13
፩.፪.፬ ሕይወተ ማርያም .......... 13
፩.፪.፭ ተአምኖ ቅዱሳን .......... 13
፩.፪.፮ ጸሎት ዘቤት ቤት .......... 13
፩.፪.፯ ፍካሬ ሃይማኖት .......... 14
፩.፪.፰ ሰዓታት ዘመዓልት ወዘሌሊት .......... 14
፩.፪.፱ ቅዳሴያት .......... 16
፩.፪.፲ ውዳሴ መስቀል .......... 16
፩.፪.፲፩ ኆኅተ ብርሃን .......... 17
፩.፪.፲፪ መጽሐፈ ብርሃን .......... 17
፩.፪.፲፫ መጽሐፈ ምስጢር .......... 18
፩.፫. መደምደሚያ .......... 19

ምዕራፍ ሁለት
- የጊና ምንባብ .......... 21

ምዕራፍ ሦስት
- ስለ ብርሃን የሚናገር ምንባብ .......... 37

ምዕራፍ ዐራት
- የኖላዊ ምንባብ .......... 47

www.ethiopianorthodox.org

**ምዕራፍ ዐምስት**
- የገና ምንባብ ........................................ 61

**ምዕራፍ ስድስት**
- የልደት ምንባብ ........................................ 79

**ምዕራፍ ሰባት**
- የጥምቀት ምንባብ ........................................ 102

**ምዕራፍ ስምንት**
- የቃና ዘገሊላ ምንባብ ........................................ 108

**ምዕራፍ ዘጠኝ**
- ሦስተኛ የጥምቀት ምንባብ ........................................ 114

**ምዕራፍ ዐስር**
- የስምዖን ምንባብ ........................................ 117

**ምዕራፍ ዐስራ አንድ**
- የደብረ ዘይት ምንባብ ........................................ 124

**ምዕራፍ ዐስራ ሁለት**
- የትስብእት ምንባብ ........................................ 141

**ምዕራፍ ዐስራ ሦስት**
- የሆሣዕና ምንባብ ........................................ 146

**ምዕራፍ ዐስራ አራት**
- የጸሎተ ሐሙስ ምንባብ ........................................ 157

**ምዕራፍ ዐስራ አምስት**
- የስቅለት ዓርብ የነግህ ምንባብ ........................................ 164

**ምዕራፍ ዐስራ ስድስት**
- የስቅለት ዓርብ የሦስት ሰዓት ምንባብ ........................................ 177

**ምዕራፍ ዐስራ ሰባት**
- የስቅለት ዓርብ የስድስት ሰዓት ምንባብ ........................................ 183





**ምዕራፍ ዐስራ ስምንት**
- የስቅለት ዓርብ የዘጠኝ ሰዓት ምንባብ ........................................ 191

**ምዕራፍ ዐስራ ዘጠኝ**
- የስቅለት ዓርብ የሠርክ ምንባብ ........................................ 209

**ምዕራፍ ሃያ**
- የስቅለት ዓርብ የንዋም ምንባብ ........................................ 215

**ምዕራፍ ሃያ አንድ**
- የፋሲካ ምንባብ ........................................ 238

**ዋቢ መጻሕፍት** ........................................ 261


www.ethiopianorthodox.org

# መታሰቢያነቱ



ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ ዘሸዋ /፲፱፻፵፪-፲፱፻፹፬/ ካረፉበት
ጊዜ አንስቶ የብፁዕነታቸውን ዓላማ አንግበው በነዮዶ ሐመረ ብርሃቁም
ቅዱስ ገብርኤል ገዳም እና የካህናት ማሠልጠኛ ት/ቤት ሆነው ከማ
ታኩትና ከማገልገል በላይ በአብነት ትምህርት ገፍተው በመም
ነት መዓርግ ለመመረቅ ፍላጎት እያላቸው በችግር ምክንያት የ
ያቋርጡትን ከምእመናን እየለመኑ በማስተማር ብዙ ተተኪ መም
ንን ለቤተ ክርስቲያን ሳበረከቱት፣ በዚሁ አገልግሎት ጸንተው አሁን
ቤተ ክርስቲያን ሰው እንዲታጣ በቁርጥ ኅሊና ለሚወጡት ለሚወርዱ
ለአባ ማርቆስ ተፈራ ይሁንልን።

ማኅበረ ቅዱሳውም



# አኰቴቶሙ

ከሁሉ አስቀድሜ የኢትዮጵያዊውን ሊቅና ጻድቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ዘነኛ መጽሐፍ ተርጉሜ ለንባብ ለማብቃት የረዳኝን አምላኬን አመሰግናለሁ። «ፈጣሪዬ እግዚአብሔር ሆይ! ከዚህ ያደረስከኝ እኔ ማነኝ» ከማለት በስተቀር ምን ሌላ እላለሁ።

በግእዝ የተጻፉ የሃይማኖት፣ የክብረ ኅሊና (የግብረ ገብ) የሞራል፣ የፍልስፍና፣ የታሪክ፣ የየዘመኑን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕንስ ሐሳቦችን የሰነዱ መዛግብትን በመተርጐም ለንባብ ለማቅረብ በነበረኝ የረጅም ዘመን ምኞት በፍቅር ተነሣሥቼ የበኩር የሆነውን የትርጉም ሥራዬን አቅርቤያለሁ። ወደ ፊትም እግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ በስፋትና በጥልቀት እቀጥልበታለሁ።

«መጽሐፈ ምስጢርን»፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ያነበብኩት በ፲፱፻፺፫ ዓመተ ምሕረት ነው። ወቅቱ የኮሌጅ ትምህርቴን አጠናቅቄ ዕረፍት ላይ ስለነበርኩ ተረጋግቶ ለማንበብ ምቹ አጋጣሚ /ጊዜ/ ነበር። አንብቤ ከጨረስኩ በኋላ የተወሰኑ ማስታወሻዎችን ወሰድኩ፤ ከመጽሐፉ ያገኘሁት ነገር አስደነቀኝ ቤተ ክርስቲያን ለካስ ይኸን የመሰለ መጽሐፍ አላት? እስከ ዛሬ ከትርጓሜ ጀምሮ የተወሰኑ መንፈሳዊ ይዘት ያላቸውን መጻሕፍት የማንበብ ዕድል አጋጥሞኛል፤ ነገር ግን እንደ መጽሐፈ ምስጢር ዘንድ የመደበኛ ሥራዬ ውጭ ያሉትን ጊዜያት በአብዛኛው አሳልፌበት በእጅጉ የሳበኝ የለም።

መጽሐፈ ምስጢር እስከ ዛሬ ተተርጉሞ ለንባብ ሳይበቃ ለምን ቀረ? ለኅሊናዬ ያቀረብኩት የመጀመሪያ ጥያቄ ነበር። በዚህ የጥያቄ ውጥረት ላይ ሳለሁ በወቅቱ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ክፍል ሐላፊ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን አማከርኩት። እርሱም ለምን አትተረጉመውም አለኝ። እኔም በፍቅር የትርጉም ሥራውን ወዲያውኑ ጀመርኩ፤ የትርጉም ሥራው የመጀመሪያዬ ስለሆነ በየዕለቱ የምተረጉመውን ሳነበው

www.ethiopianorthodox.org

ትርጉሙ እጅግ እየመሰጠኝ መጣ። ከዲያቆን ዳንኤል ክብረትም ተገናኝተን ስላምታ ስንለዋወጥ «ኃ/ማርያም እንደምነህ አይለኝም፣ አባ ጊዮርጊስ እንዴት ናቸው?» ይለኛል። የትርጉም ሥራው ከምን ደረሰ ለማለት ፈልጎ ይመስለኛል። የትርጉም ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላም መጽሐፉን አንብቦ በግርጌ ማስተዋሻ ሊብራሩ የሚገባቸውን ቃላት በመጠቆም ገንቢ አስተያየት ሰጥቶኛል። ሐሳቡንም በደስታ ተቀብዬ ማስተካከያ አድርጌያለሁ። ስለዚህም የትርጉም ሥራ ተፀንሶ እስከሚወለድ ድረስ ከጎኔ ባለመለየቱ ላመሰግነው እፈልጋለሁ።

መጽሐፈ ምስጢርን በምተረጉምበት ወቅት በስመ ጥሩ ኢትዮጵያዊ የጥንታውያን ጽሑፍ ተመራማሪ /philologist/ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ከግእዝ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ የተዘጋጀውን «ደቂቀ እስጢፋኖስ በሕግ አምላክ» የተሰኘውን መጽሐፍ አነበብኩ። ይኸን መጽሐፍ ማንበቤ ለትርጉም ሥራው ትልቅ መነሣሣትን ፈጥሮብኛል፣ ፕሮፌሰር በማስከተል ያሳተሙት «የአባ ባሕርይ ድርሰቶች አሮሞዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋር» የሚለውም እንደዚሁ። በሚዛናዊነቱ በምርምሩ ጥልቀት ለጥንታውያን ጽሑፍ ጥናት መለኪያ፣ አብነት የሚሆን ሥራ ሠርተው የውስጥ መነሣሣት ስለፈጠሩብኝ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌንም የዕድሜ ጸጋ ያድልልኝ እላለሁ።

ይኸን መጽሐፍ ስተረጉም በአባታዊ ምክራቸው ማበረታቻ በመስጠት ያልተለዩኝን ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳምና የካህናት ማሠልጠኛ ት/ቤት የበላይ ሐላፊም ከልብ አመሰግናለሁ።

በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለአምስት ዓመታት ያህል የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ ትምህርት ስከታተል አጠቃላይ ወጪዬን ሸፍነው ያስተማሩኝ አባ ማርቆስ ተፈራ ለውጥኔ ስኬት ከጎኔ በመሆናቸው ከልብ አመሰግናቸዋለሁ።

መጽሐፉን የጻፈችልኝና ያረመችልኝ ወ/ት በዳሉ ሁንዴሳን የመጽሐፉ የገጽ ቅንብርና የሠራችልኝን ወ/ት ርብቃ ኃ/ማርያም አመሰግናለሁ።

ይህ መጽሐፍ ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ ብዙዎች ደክመውበታል። በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳምና የካህናት ማሠልጠኛ ት/ቤት የግእዝ ቋንቋ ምንነትን በመተንተን ከገባኤ ቃና እስከ እማነሞገር ከዚያም ሌሎችን ማስተጸል እስከ ምችልበት ድረስ ያስተማሩኝን



መጋቤ ሐዲስ እሸቱ ዓለማየሁን መጽሐፉን በማንበብ፣ በማርታት ጥቅሶችን በማሟላት የትርጉም ሥራው አሁን ካለበት ደረጃ እንዲደርስ ከበስተጀርባ የነበሩ የትርጉም ሥራው ሞተር በመሆናቸው ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

መ/ር ደሴ ቀለብ መጽሐፉን ተርጉሜ ከጨረስኩ በኋላ የዐማርኛውን ትርጉምና የግእዙን ቅጂ በማይክሮ ፊልም ከተቀረጹ ሌሎች ቅጂዎች ጋር በማስተያየት አንብቦ አስተያየት ሰጥቶኛል ማስተካከያም አድርጌአለሁ። በተለይ ከእኔ ጋር አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኬኔዲ ላይብራሪ አብሮ በማደር የጎደለውን በመሙላት የተዛባውን በማቅናት ያደረገልኝ እስከመቼም አልረሳውም ምን ልል እችላለሁ? ይኸው የድካም ፍሬ ከማለት በስተቀር።

ባልደረባዬ አቶ አለሳ ጥላሁን መጽሐፉን ለመተርጎም ካሰብኩበት ዕለት ጀምሮ ወደ ማተሚያ ቤት እስከሔደበት ዕለት ድረስ ከጎኔ ነበር፣ ባለው የአርትኦት ሙያ በመቀመር የተጻፈውን እንዲያርምልኝ ሰጥቼው የመጀመሪያውን የአርትኦት ሥራ ከፊደል ለቀማ እስከ ርእሰ ነገር ጥቆማ በመሥራት በግርጌ ማስተወሻ (footnote) ሊብራሩ የሚገባቸውን በመጠቆም ለመጽሐፉ እዚህ መድረስ የደከመልኝን አልዘነጋውም። በመሆኑም ከልብ አመሰግነዋለሁ። ዲያቆን መርሻ አለኸኝ ከሀገረ ጀርመን በስልክና በኢሜል ለመጽሐፉ ጥንካሬ የተለያዩ ምክረ ሐሳብ ስለሰጠኝ ላመሰግነው እወዳለሁ።

የመጨረሻውን ሥራ ያዩልኝን፣ በጎ ሐሳባቸውን የለገሱኝን እና ለሥራው መፋጠን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉልኝን አቶ ዐሥራት ከበደ የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት ሓላፊን፣ ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ የሐመር መጽሔት ዋና አዘጋጅ እና ዲ/ን ታደሰ ወርቁ የመጽሐፍ ዝግጅት ክፍል ሓላፊን አመሰግናለሁ። መምህር አበበ ደሴ መጽሐፉን በማንበብ የበኩሉን አስተያየት ስለሰጠኝ አመሰግነዋለሁ። በመጨረሻ የሐመር መጽሔት አዘጋጅ የሆነው ዲ/ን ማለደ ዋሲሁን ጥቅሶችን በማሟላት ለግርጌ ማስታወሻ የተመረጡ ታሪኮችን በመጻፍ ስለረዳኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡ በተለይ የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት አባላት የሥራ ባልደረቦቼ ከጐኔ ሳይለዩ ስላበረታቱኝ ውለታቸውን አልረሳውም። ስለዚህም አምላከ አባ ጊዮርጊስ ዋጋችሁን ይክፈላችሁ እላለሁ። በዚህ አጋጣሚ በቅርብ ቀን መጽሐፈ ምስጢር ክፍል ሁለት ትርጉምን እንደማቀርብ ለመግለጽ እወዳለሁ።

ተርጓሚው



www.ethiopianorthodox.org

# ይደልወከ

የትርጓሜ ስልቱና ዐይነቱ ብዙ ነው። ከዐሥራ ሦስቱ የትርጓሜ መንገዶች የዚይቤ አወጣጥ፣ የምስጢር አገላለጥ፣ የዚይቤ ማቃናትና፣ ጸያፉ መከተት፣ የውጥን አፈራረስ፣ የአርእስት መመልከትም ከማስማማት ጋር ተጠብቆ ቤተ ክርስቲያኒቱን በሚወክል ማዕከላዊ በሆነ ዐማርኛ ተስተካክሎ ከወጣ አንድ የትርጉም መጽሐፍ ሙሉ ይሆናል። በዚህ ረገድ ይህ የትርጉም መጽሐፍ ተደላድሎ እንዲቀርብ በጎ ሐሳባቸውን በመስጠት እና የፊደልና የስዋስው፣ የንግግርና የጽሕፈት አገባብ እንዲጠበቅ የተቻላቸውን ምሳሌ በመጠቆም መጽሐፉ ለአንባብያን በሚገባ ግልጽ እንዲሆን በማድረጋቸው ሊቀ ትጉሃን ኃይለ ጊዮርጊስ ዳኘ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የሕትመትና ልማት መምሪያ ም/ሓላፊን እናመሰግናለን።

እግዚአብሔር አምላክ ረጅም ዕድሜን ከሙሉ ጤንነት ጋር ይስጥልን ዘንድ መልካም ምኞታችን ነው።

ማኅበረ ቅዱሳን



# መግቢያ

ቅዱሳት መጻሕፍትን በአገራቸው ቋንቋ ተርጉመው ተጠቃሚ ከሆኑ አገሮች ኢትዮጵያ ከመጀመሪያዎቹ ረድፍ ትሰለፋለች። ቀደም ባሉት ዘመናት እንደዛሬው ሁሉ ዘመናውያን የኅትመት መሣሪያዎች ሳይፈ በረከ፡ አበው ሊቃውንት፣ነገሥታት፣ የበጎ ሥራ ተባባሪ ምእመናን ቅዱሳት መጻሕፍትን፣ ዜና መዋዕሎችን የተለያዩ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን የያዙ ሌሎች መጻሕፍትንም በመጻፍ በማስተርጐም አገራችንና ቤተክርስቲያናችንን የቅርሳ ቅርስ ባለቤት አድርገዋታል።

እነዚህ ቀዳሚዎቻችን ሊቃውንቱ፣ ነገሥታቱ ምእመናኑ በባህል ግንባታ በኩል ያበረከቱትም አስተዋጽኦ የላቀ በመሆኑ ለአፍሪካውያን ኩራት ሊሆን የሚችል ሁለገብ የዕውቀት ዕሴት በየትውልዱ ሳይቋረጥ ካለንበት ዘመን ሊደርስ ችሏል።

በቤተ ክርስቲያን የትርጉም ሥራ ሲወሳ ብሉይ ኪዳንን ከሰባ ሊቃናት ትርጉም ጋር በማዛመድና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በመጨመር በ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ ግእዝ የተረጎሙ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት እና እንደ አዝማች ተደርጎ የሚጠራው ቅዱስ ፍሬምናጦስ /አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን/ ሲሆኑ በ፭ኛው ምእት ዓመትም ተሰዓቱ ቅዱሳን ታላቅ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን የተለያዩ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ። በመሆኑም በዚህ የተቀደሰ ተግባር የኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ተሳትፎ ሁል ጊዜ ተቀዳሚውን ቦታ ይዞ ይታያል።

ሰላማ መተርጉም /ሰላማ ዘአዜብ/ ከአረብኛም ጭምር መቶ ክፍለ ዘመን ትርጉም በማቅናት የጥንቱን (Classical Geez) መጽሐፍ ቅዱስን በመካከለኛው ዘመን ግእዝ ተርጉመዋል።

በተለይም «የሥነ ጽሑፍ መንሰራራት ዘመን» ተብሎ በሚጠራው ከ፲፪፻፸ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ በርካታ የሃይማኖት፣ የታሪክና የፍልስፍና መጻሕፍት ተርጉመዋል። የዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት /፲፬፻፴፫-፲፬፻፷፰/ ተአምረ ማርያም እና ተአምረ ኢየሱስ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ መተርጎማቸው ይነገራል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዐማርኛ የብሔራዊ ቋንቋ መንበርን እስከተቆናጠጠበት እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ /፲፰፻፵፯/ ዘመነ መንግሥት ድረስ የነገሥታቱ ታሪክ ሳይቀር በግእዝ ይጻፍ ነበር። በቴዎድሮስ ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ የንጉሡ ታሪክ በዐማርኛ በደብተራ ዘነብ ተጽፏል።



www.ethiopianorthodox.org

አማርኛ የንግግርና የጽሑፍ ቋንቋነትን በስፋት ሲይዝም በግእዝ የተጻፉ መጻሕፍት አብዛኛዎቹ ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው በመሆናቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስትገለገልባቸው ቆይታለች:: እነዚህ በግእዝ የተጻፉ የሃይማኖት፣ የታሪክ፣ የፍልስፍና፣ የሥርዐትና የሕክምና መጻሕፍት በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ ጦርነቶች ከፊሎቹ ተዘርፈው ወደ ምዕራቡ ዓለም ሲጓዙ ከፊሎቹ የመቃጠልና ከአያያዝ ችግር የተነሣ የመጥፋት ዕድል አጋጥሟቸዋል::

የመዛግብቶቻችንን በዝርፊያ መወሰድ፣ ከአያያዝ ጉድለት መበላሸት የነገረ ሃይማኖት ትምህርታችንን ታሪካችንን ባህላችንን ለማወቅና ለመመርመር በአብዛኛው «የበይ ተመልካች ሆነን» የምዕራባውያን ጥገኛ እንድንሆን አስገድዶናል:: ዛሬ ዛሬ በመዛግብታችን በብራና መጻሕፍታችን ዙሪያ ጥናትና ምርምር በማድረግ አኩሪ ሥራ የሠሩ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ቢኖሩም በአብዛኛው ግን በእኛ ብራናዎች ተምረው ስለመዛግብታችን ይዘት፣ ቅርጽና አጠቃላይ ጭብጥ የሚነግሩን ምዕራባውያን ናቸው::

ከታሪካዊ ምርምርና ፍለጋ ውጪ የተለየ ዓላማ የነበራቸው አንዳንድ ምዕራባውያን የብራና ጽሑፋችንን ወለላ በመቅመስ ማሩን ወደ ዕሬት የመቀየር ሥራ ሠርተዋል:: ለምሳሌ በዐፄ ዘድንግልና በዐፄ ሱስንዮስ ዘመን የነበሩ ኢየሱሳውያን በመዛግብታችን ላይ የታሪክና የሃይማኖት ብረዛ አድርገው ሕዝቡን በመከፋፈላቸው ምእመናን፣ ሊቃውንት ለሕልፈተ ሕይወት እንዲዳረጉ ምክንያት ሆኗል:: ዛሬ የምንጠቀምበት መጽሐፍ ቅዱስ ሳይቀር ትክክለኛው ያልተበረዘው ያልተከለሰው ቅጂ ከእኛ ተወስዶ በእነርሱ ሙዚየም ተቀምጦአል:: የእነርሱን ሐሳብ ሊጎላ በሚችል መልኩ የተዘጋጀውን ሰጥተውን አንዲት እምነት የነበረን ክርስቲያኖች ወደ ተለያዩ ቅርንጫፍ (Denomination) እንድንከፋፈል ይደክማሉ::

ከእንግዲህ የመጀመሪያዎቹ ደገኛ አባቶቻችን ቀንና ሌሊት በጸሎት ተወስነው ዐይናቸው እስኪፈዝ ክንዳቸው እስኪዝል ድረስ ነገረ ሃይማኖትን፣ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን እና ፍልስፍናቸውን የቀረጹባቸውን መጻሕፍት በአስተርጓሚ ሳይሆን በራሳችን ሀገር ቋንቋ መተርጎምና መመራመር ግድ ይላል:: በዚህ ረገድ በቅርቡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በአገራችን የመጀመሪያ የሆነው የጥንታውያን ጽሑፎች ጥናት(philology) በድኅረ ምረቃ ደረጃ ከፍቶ ተመራማሪዎችን ተቀብሎ ማሠልጠኑ ዐይነ ጥላችንን የሚገፉ ምሁራንን ያፈራልናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን:: በተለይ





ከቤተክርስቲያኒቱ ልጆች በግእዝ የተጻፉ ሀገር በቀል ዕውቀቶችን በመተርጎም ሌሎች ያዛቡትን በማስተካከል ተቸግረው ላስተማሩን ምእመናን ብሎም ለዓለም ሕዝብ ከማሳወቅ አኳያ ብዙ የቤት ሥራ እንዳለብን ሳንጠቁም አናልፍም::

## የትርጉሙና የአርትኦቱ ዓላማ

ይህ መጽሐፍ ከተጻፈ ስድስት መቶ ዓመታትን አስቆጥሯል:: መጽሐፈ ምስጢር ተብሎ እንደመሰየሙ ምስጢርን ይዟል:: የግእዙን ቅጅ አግኝተው ያነበቡ ሰዎች ያውቁታል፤ ለእነርሱ አዲስ አይደለም:: ግእዝን ለማያውቁ ምእመናን እና የሃይማኖት ተመራማሪዎች ግን ምስጢር እንደሆነ እስከዛሬ ቆይቷል:: ከእኛ ይልቅ ፈረንጆቹ ተርጉመውና አስተርጉመው በመጽሐፈ ምስጢርና በሌሎችም የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ሲመራመሩ ኑረዋል:: አንዳንዶች ባህሉንና ነባራዊውን ሁኔታ ተርጉመዋል አስተርጉመዋል ሃይማኖቱንና ሥርዐቱን ባላገናዘበ መልኩ ቢሆንም በራሳቸው መንገድ የዚህ ትርጉም የግል ሐሳባቸውን በመጨመር እና የአርትኦት ሥራ ዓላማ ግእዙን የማያውቁ ምእመናን እና ሌሎችም፣ ኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክሳዊ ትምህርተ ሃይማኖት መኖሩን ማሣየት፤ የእኛው ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ለመናፍቃን መልስ የሰጡበትን ዘዴ ለትውልዱ ማስነበብ፤ በጥራዝ ነጠቅነት ቤተ ክርስቲያንን ለሚተቹ ትምህርተ ሃይማኖቷን ለሚያጣጥሉ መናፍቃንም መልስ ይሆን ዘንድ ነው:: ለወደ ፊቱም በዚህ ዓይነት የትርጉምና የአርትኦት ሥራ ለሚሰማሩ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች መነሣሣትን መፍጠር ጭምር ነው::

## የትርጉሙና የአርትኦቱ ውሱንነት

ኢትዮጵያዊው ጻድቅና ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ የጻፏቸው መጻሕፍት እስከዛሬ በተደረጉ ጥናቶች ቁጥራቸው በትክክል ያልተቀመጠ ቢሆንም ከ፴/፵/ በላይ መጻሕፍትን እንደጻፈ ይነገራል:: አንዳንድ አጥኚዎች ደግሞ የመጻሕፍቱን ብዛት ወደ አርባ ያደርሱታል:: የጽሑፍ መረጃቸው በሚገኙ የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ድርሰቶች ላይ እስከዛሬ የተወሰኑ የዲግሪ ሚሚዮ ጽሑፎች፣ የጥናት ወረቀቶች ቀርበዋል:: ይሁንና የዚህ ሊቅ ሥራ በስፋት አለመዳሰሱን መረዳት ይቻላል:: በመሆኑም በተጨማሪ ለቀጣይ ጥናትና ምርምር የሚጋብዙ ሁኔታዎች አሉ::

www.ethiopianorthodox.org

የዚህ መጽሐፍ /መጽሐፈ ምስጢር/ ትርጓሜና አርትኦት አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ጽፈዋቸዋል ከሚባሉት መጻሕፍት የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት፣ የወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን ዘለዓለማዊ ድንግልና ከሚሰብከውና ከሚተነትነው በመጽሐፈ ምስጢር ክፍል አንድ ላይ ብቻ ያተኩራል።

ቤተ ክርስቲያን ዓለማቀፋዊት እንደ መሆኗ በሃይማኖተ አበው፣ በስንክሳር በታሪክ መጻሕፍት በዓለም ሳሉ በደገኛ ሃይማኖትና ምግባር በመኖራቸው የተመሠከረላቸውን ከልሒቅ እስከ ደቂቅ ያሉት ቅዱሳንን ገድላቸውን፣ ቅድስናቸውን፣ ታሪካቸውን መዝግባ ዕለተ ዝክር /የመታሰቢያ ዕለት/ እንደምታስታውሳቸው ሁሉ በዓለም ውስጥ ከልዩ ልዩ ክህደት ልጆቿን ትጠብቅ ዘንድ በዓለም አቀፍ ጉባኤያት በተሳሳተ ትምህርታቸው የተወገዙ መናፍቃንን ከግለሰባዊ ማንነታቸው እስከ ተሳሳተ ትምህርታቸው በሰላ ብዕሩ የተቸበትን፣ መልስ የሰጠበትን፣ ማበራሪያዎችና ትምህርቶችን ያካተተ ይሆናል። በአጠቃላይ ነገረ ድኅነትን የሰበከበትን ወርቀ ንባብ ማሳየት ነው።

## የመጽሐፉ ገለፃና የተዛማች ጽሑፍ ዳሰሳ

መጽሐፈ ምስጢር እናቱ /በብራና የተጻፈው/ በምዕራፍ ሳይሆን በአርእስት የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው ክፍል አርእስት በምዕራፍ ሲከፈሉ ሃያ ምዕራፎች ሆነዋል። መጽሐፈ ምስጢር የግእዝ ቅጅ በወረቀት በሃያ ምዕራፎች ተከፍሎ አግኝቼዋለሁ። ይህ በወረቀት ተጽፎ ያገኘሁትን መጽሐፍ በምዕራፍ ከመከፈሉ በስተቀር በይዘት በኩል ከብራናው የተራራቀ አይደለም። «ወይገብሩ ስሞ ለበዓለ መጽሐፍ ቅድመ፡ በመጀመሪያ የመጽሐፉን ባለቤት ያስታውሱ» በሚለው መሠረት በዚህ የትርጉም ሥራ የመጽሐፉ አዘጋጅ ሥራዎች በተወሰነ ደረጃ ተብራርተው አንድ ምዕራፍ ስለተሠጣቸው የምዕራፉ ብዛት ወደ፳፩ /ሃያ አንድ/ ተሸጋግሯል። የሊቁ አባ ጊዮርጊስ ታሪክና ሥራ በተርጓሚው እና በአርተዒያኑ 6የተካተተ እንጂ የመጽሐፉ አካል አልነበረም።

ለመጽሐፉ የተሰጠው ምዕራፍና ሌሎችም አንባብያን ግር ያሰኛሉ ተብለው የሚታሰቡ ቃላትን በአርትኦት የተጨመሩ መሆናቸውን ለማመልከት የሚከተለው ዓለም አቀፍ ምልክት [ ] ጥቅም ላይ ውሏል።

መጽሐፉ ረጅም ዘመን የቆየ እንደመሆኑ ከአንዱ ብራና ወደሌላ ብራና እንዲሁም ወደ ወረቀት ሲገለበጥ ግድፈት እንዳጋጠመው ግንዛቤ ተወስዷል።



www.ethiopianorthodox.org



የደረሰውንግድፈትናአንድነትበጥቂት ናሙናዎች መመልከት ይቻላል። የሚከተሉት የእንግሊዝኛ ፊደላት እና ምልክቶች የሚከተሉት ትርጉም እንዳላቸው እግረ መንገድ ትርጉማቸውን ተናግሮ ማለፍ ማለፊያ ነው።

(OM.) = የማይገኙበት መጽሐፍ /ማይክሮ ፊልም/ የተቀነሰ

(ADD.) = የተጨመሩበት መጽሐፍ ማይክሮ ፊልም

EMML = በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር የሚገኙ ማይክሮ ፊልሞች (I.I:II….X)

P = ፓሪስ የሚገኙ

M = በሞንደት የሚገኙ

B = ቦድሊያን የሚገኙ

[ ] = በአርተዓያኑ የተጨመረ መሆኑን ያመለክታል

በእነዚህ ምልክቶች አጋዥነት በጽሑፉ ላይ የተደረገ የናሙና ጥናት ለመመልከት ይቻላል። ለምሣሌ፦ የመሠረተ ጥናቱ ቅጅ «፩ ውእቱ ሥምረተ አብ ወወልድ የሚለው በልዩ ልዩ ቅጆች +መንፈስ ቅዱስ። አጠቃላይ ምርመራው ውእቱ ሥምረተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» ይሆናል። የመሠረተ ጥናቱ ቅጅ ወተወልደ እም ብእሲት ሲል በልዩ ልዩ ቅጂዎች M፣PII፣ I፣ III፣ IV፣ VI፣VIII + ተዋሕዶ ይላል። አጠቃላይ ምርመራው ወልድ ዋሕድ። የመጨረሻ አንድ ለማከል የመሠረተ ጥናቱ ቅጅ እንተ ይእቲ ንጽሕት ሲል M -ንጽሕት ይላል። አጠቃላይ ምርመራው እንተ ይእቲ ንጽሕት ይላል። ይህ እንግዲህ በመሠረተ ጥናቱ ቅጅ እና በልዩ ልዩ ቅጂዎች መካከል ያለውን መጠነኛ ልዩነት ያሳያል። ተርጓሚውና አርተዓያኑ የሊቁ ሐሳብ በምልዐት ሊገልጹ ይችላሉ ያላቸውን ከተለያዩ ቅጂዎች ጋር በማመሳከር የትርጉም ሥራው ተሠርቷል።

መጽሐፈ ምስጢር ከመጀመሪያው ምዕራፍ እስከ መጨረሻው ምዕራፍ ድረስ አጀማመሩ በምስጋና ነው። አጨራረሱ ደግሞ የተሳሳተ ትምህርት ያስተማሩትን በመተቸት የራሱን ድካም በመግለጽ ምእመናን በጸሎታቸው እንዲያስቡት በማሳሰብ ይቋጫል። ይኸም ሥራን በምስጋና መጀመሩ ከቅዱስ ጳውሎስ የመልእክት አጻጻፍና ከመጽሐፈ ቅዳሴ አጻጻፍ ጋር ይመሳሰላል።

በመጀመሪያው ምዕራፍ ከምስጋና በመለጠቅ «መጽሐፈ ምስጢር ለምእመናን እንጂ ለኢአማንያን የማይነገር» መሆኑን ይተርካል። በማስከተል

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ገጽ የሚል የሰባልዮስ /ሰባልዮስን/፣ አቡሊናሪዮስን፡ ወልድ ከነቢያት አንዱ ነው የእግዚአብሔር ልጅ በዮርዳኖስ ባገኘው ጊዜ የጸጋ አምላክ ሆነ፡ የሚል ንስጥሮስን፡ የእግዚአብሔር ልጅ [ኢየሱስ ክርስቶስ] ሀልውና ከማርያም ወዲህ ነው ጥንት አይደለም የሚል ፎጢኖስን፣ ወልድ ከአብ ያንሳል አያየውም፣ መንፈስ ቅዱስም ከወልድ ያንሳል እርሱን መመልከት አይቻለውም የሚል አርንጌንስን፣ ወልድ ያለ አባቱ ለኃጥአን ሊፈርድባቸው ለጻድቃን ዋጋቸውን ሊሰጥ ይመጣል፡ የሚል ቢቱን፣ የክርስቶስ ሥጋ እንደኛ ሥጋ ደክሞ አልታመመም የሚል አውጣኪን፣ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ልጅ ያለፈቃዱ ሞተ የሚሉ ታኦዶስዮስና ሳዊሮስን፣ የክርስቶስ ሥጋ ምትሐት ነው፡ የሰው ሥጋ አይደለም፡ የሚል መንክዮስን፣ የክርስቶስን ትስብእቱንና መለኮቱን ሁለት ገጽ ነው፡ የሚል ፍላብያኖስን፣ እመቤታችን ጌታን ከወለደች በኋላ ከዮሴፍ ጋር በልማደ ብእሲ ወብእሲት ኖራለች የሚሉ አንጢዲቆ ማርንጦስን፣ [ሀረ ማርያም] ወልድ ፍጡር ነው የሚል አርዮስን፡ ትስብእት ከመለኮት ያንሣል የሚል ልዮንና ሌሎችንም መናፍቃንን በመተቸት የተሳሳተ ትምህርታቸውን በማስተዋወቅ ይጀምርና በቅደም ተከተል ለእያንዳንዱ መናፍቅ ትምህርት መልስ ይሰጣል።

ከላይ የተዘረዘሩት መናፍቃን በተነሡበት ዘመን የነበሩ አበው ሊቃውንት እነ ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቄርሎስ፣ ባስልዮስ ዘቂሳርያ ወዘተ በሃይማኖተ አበው የተለያዩ ትምህርተ ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው መጻሕፍት በመጻፍ መልስ መስጠታቸው ይታወቃል። የሚያስደንቀው ግን ኢትዮጵያው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እነዚህ ቀደምት ሊቃውንት መልስ ከሰጡበት ዘዴ ወጣ በማለት ትምህርተ ሃይማኖቱ ሳይዛባ የራሱን ስልት በመቀየስ የቀደሙትን ባለማፋለስ መልስ ሰጥቷቸዋል።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በአብዛኛው ከአዋልድ መጻሕፍት ይልቅ በስፋት የተጠቀመው መጽሐፍ ቅዱስን ነው። የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚ እና በሥራው የተሳተፉ አርታዒያን ሊቁ የተጠቀማቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንዳለ ነቅሶ በማውጣት በግርጌ ማስታወሻ (footnote) ለማሣየት ሞክረዋል።

የተጠቀምነው መጽሐፍ ቅዱስ ሰማንያ አሐዱ ተብሎ የሚጠራውን ነው አንዳንድ ጥቅሶችም አሁን በቤተ ክርስቲያን ከምንጠቀምበት መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሊቁ የተጠቀመበት መጠነኛ የቃላት ልዩነት እንዳላቸው





ግንዛቤ ተወስዷል። ሊቁ የተጠቀመበት የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ በቅርብ የማይገኝ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት መናፍቃን የተነሡበትን ዘመን እና የትምህርታቸ ውን ምንነት የሚገልጽ የግርጌ ማስታወሻም ተደርጓል። ከዚህ ውጪ ማብራሪያ ለሚፈልጉ አንዳንድ ሐረጋትና በግርጌ ማስታወሻ ላይ መጠነኛ ማብራሪያ ለመስጠት ተሞክሯል። ከዚህ ባሻገር ከመጽሐፈ ኪዳን፣ ከተአምረ ማርያም ከወንጌል አንድምታ የተወሰዱ መጻሕፍቱን እንዳለ በመጥቀስ ለማመላከት ጥረት ተደርጓል።

የትርገም ሥራው የአርትኦት ሥራ እየተሠራ የተተረጎመ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለሁ። ይህ ሥራ የመጨረሻ የተዋጣለት ነው ለማለት አይቻልም። በዳግም ኅትመት ወቅት እየተሻሻለ እየተራቀቀ እንደሚሔድ ባለ ሙሉ ተስፋ ነን። ለዚህም የብዙዎችን ደግ አንባቢያን አስተያየት ይፈልጋል። በመሆኑም አንባብያንም ሊቃውንትም የሚሠጡንን ገንቢ አስተያየት ለመቀበል ዝግጁ ነን።

**የመጻሕፍት ዝግጅት ክፍል**



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፩

## ፩. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫና ሥራዎቹ

### ፩.፩ ዜና ሕይወቱ ለአባ ጊዮርጊስ

#### ፩.፩.፩. ልደት

የወርቅማው ዘመን ወርቃማ ደራሲ፣ መናኝ፣ ጻድቅ፣ ሊቅ፣ የሕዝብ መምህር እና የሥነ ምሕንድስና ባለሙያ የሆነው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ የተወለደው በ፲፫፻፶፯ ዓመት ምሕረት በወሎ ክፍለ ሀገር በዛሬው ቦረና በጥንቱ ወለቃ ወረዳ ሸግላ በተባለ ቦታ ነው። አባቱ ሕዝበ ጽዮን እናቱ እምነ ጽዮን ይባላሉ። ስለ አባቱ ሕዝበ ጽዮን ሁለት የተለያዩ ታሪኮች ይተረካሉ። የስኗ ድርሳነ ዑራኤል ምንባብ አባቱ በመጀመሪያ የትግራይ በማስከተል የሰግላ /ጋሥጫ/ አገረ ገዥ እንደነበር ያወሳል። ገድሉ ደግሞ ጠቢብ ወማእምረ መጻሕፍት፡ ወአበሁኒ መፍቀሬ እግዚአብሔር እምኑልቈ ካህናተ ደብተራ ዘውሳጤ ዓጸደ ቤተ ንጉሥ፡- አባቱም የእግዚአብሔር ወዳጅና በቤተ መንግሥት በነበረችው ድንኳን /ሥዕል ቤት/ ከሚያገለግሉ ካህናት ወገን ነበረ ይላል። እንደ ገድሉ ገጸ ምንባብ ትርጉም ሕዝበ ጽዮን ከንጉሡ ሥዕል ቤት በቅዳሴ ወይም በማሕሌት ከሚያገለግሉ ካህናት አንዱ ነው። ..ወእሙኒ እም ሥዩማነ ወለቃ፡ እናቱም ከወለቃ ሹማምንት ወገን ነች.. ይላታል። ይኸውም የጥንቱ ወለቃ /የዛሬው ደቡብ ወሎ፣ ቦረና ከላላ/ ከነበሩ መኳንንት ወገን መሆኗን ያመለክታል።

የአባ ጊዮርጊስ ወላጆች ልጅ ሳይወልዱ ለረጅም ዓመታት ቆይተዋል። የልጅ ፍላጐታቸው እንዲሠምር ለሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ተሳሉ። ስለታቸው ሠምሮ በመልአኩ ቅዱስ ዑራኤል አብሣሪነት ወንድ ልጅ ወለዱ፡ ልጃቸውን ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስን በመማጸን ስለወለዱ ስሙን ጊዮርጊስ ብለው ጠሩት። ወላጆቹ የታላቁን ሰማዕት ስም ለልጃቸው

1. ፕሮፌሰር ያዕቆብ በየነ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና አባ ጊዮርጊስ ሰግላዊ ሁለት የተለያዩ ሰዎች መሆናቸውን አስረድተዋል ነገር ግን አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና አባጊዮርጊስ ሰግላዊ የአንድ ሰው ስም መጠሪያ ነው።
The location by yaqob Beyene … that Giyorgis of Casecca and Giyorgis of sagla were dwo different people by proved. But, according to the the hagiography and oral tradition, the Giyorgis who was born in sagla and the one who founded Dabra Bahary in Gasecca was one and the same person, (Encyclopidia Ethiopa V. II P II)

www.ethiopianorthodox.org

ያወጡት ወደፊት በዓላውያን ነገሥታት ፊት ምስክር፣ አዕራሪ እምነትን አሳፋሪ፣ ካህናትንና ምእመናንን በየዘመናቱ ከሚነፍሱ የኑፋቄና የክህደት ነፋሳት በወንጌል ብርሃን ነፃ የሚያወጣ ሲሉ ይህን ስም እንዳወጡለት ድርሳነ ዑራኤል እንዲህ ይተርካል:: «ዘይከውን መምህረ ኩሉ ዓለም ወበጸሎቱ ዘያድኅን እሞተ ሲኦል ፍቁረ ድንግል ማርያም ወላዲቱ ለዐማኑኤል:: ወመገሥጾሙ ለነገሥት:: ወፀሮሙ ለዐላውያን ሃይማኖት በሰይፈ ቃሎሙ ለሐዋርያት ዘያጠፍአሙ እም ብሔረ ኢትዮጵያ፡ ወለካህናተ ጽድቅ ዘይመርሆሙ እምጽልመተ ኑፋቄ መንገለ ብርሃነ ቃለ ወንጌሉ ለክርስቶስ በትምህርተ ሕጎሙ ለሐዋርያት» ይላል::

## ፩.፩.፪. ትምህርት

አባ ጊዮርጊስ የመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርቱን ከወላጅ አባቱ ሕዝበ ጽዮን እንደተማረ ይገመታል:: አባቱ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ካስተማሩት በኋላ መዐርገ ዲቁና እንዲቀበል ማድረጋቸውን ገድሉ ይነግረናል:: ወሶበ ልህቀ ሕቀ ወሰዶ ኀበ ጳጳስ ወሴሞ ዲያቆነ:: ባደገም ጊዜ ከጳጳስ ዘንድ ወሰደው ጳጳሱም በዲቁና አሾመው» ይላል ገድሉ:: ዲቁና መቀበሉን እንጂ መዓርገ ዲቁና የሰጡትን ጳጳስ ስም አይገልጽም:: ዳሩ ግን መዓርገ ዲቁናን በ፲፫፻፵፩ ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እስከ ዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ አካባቢ ከነበሩት ብፁዕ አቡነ ሰላማ መተርጉም እንደተቀበለ ይገመታል::

መዓርገ ዲቁና ከተቀበለ በኋላ የአባ ጊዮርጊስ ወላጆች ለታላቅ ሐላፊነት የተመረጠውን ልጃቸውን በዘመኑ የታወቀ የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ሊያስተምሩት ለሚችሉ መምህራን መስጠት እንዳለባቸው ወሰኑ:: በወቅቱ ጥልቀት ያለው የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ለመማር የሚመረጠው ትምህርት ቤት ሐይቅ እስጢፋኖስ ነበር::

ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ በዐፄ ዳዊት /፲፫፻፸፫-፲፫፻፺፫/ ዘመነ መንግሥት እንደገባ ገድሉ ይገልጣል:: ሐይቅ እስጢፋኖስ የተለያዩ ሊቃውንት የሚገኙበት፣ በብዙ መጻሕፍት የተሞላውና ዙሪያውን በሐይቅ በመከበቡ የተማሪን ሐሳብ ለማሰባሰብ አመቺ የሆነ ቦታ ነው:: አባ ጊዮርጊስ በሐይቅ እስጢፋኖስ ትምህርት አልገባው ብሎ ለሰባት ዓመታት ተቀምጦ ነበር:: የትምህርት ቤት ሕይወቱም ከቅዱስ ያሬድ ይመሳሰላል:: ቅዱስ ያሬድ ትምህርት አልገባው ብሎ ሰባት ዓመት እንደተቸገረው እንደዚሁ አባ ጊዮርጊስም አብረውት የሚማሩት ተማሪ ዎች ይህ ትምህርት የማይገባው ስለ ምንድን ነው? በእርሱ ኃጢአት ነው ወይስ በወላጆቹ? ብለው እስከ ሚጠይቁ ድረስ ትምህርት አልገባ ብሎት ነበር:: በዚያ ጊዜ የሐይቁ መምህር የነበረው ዐቃቤ ሰዓት ሠረቀ ብርሃን ለአባቱ «ልጅህ ትምህርት አይገባውምና የቤተ መንግሥት ነገር አስተምረው» ብሎ መለሰው:: አባቱ ሕዝበ ጽዮን ግን «አንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር ሰጥቼዋለሁ፡ አልቀበልህም እዚያው ገዳሙን ያገልግል» ብሎ እንደ ገና ላከው::[2]

በዚህ ዓይነት መምህሩ ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ መልሶ ወሰደውና በጥበበ እድ ሥራ ላይ ተመደበ:: በጥበበ እድ ባከበተው ዕውቀትም እንደ ቅዱስ ላሊበላ ከዐለት ፈልፍሎ ቤተ ክርስቲያን ለማነጽ ችሏል:: ዛሬ ከዘመን ርዝማኔ የተነሣ ጥገና ባይደረግለትም አባ ጊዮርጊስ ፈልፍሎ ያሠራው ዋሻ ቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስት እና መቅደስ ያለው ቤተ ክርስቲያን ብዙ የትሩፋት ሥራ በሠራበት በጋሥጫ ገዳም ይገኛል:: የወለቃን ወንዝ ለመሻገር ያገለግል ዘንድ ከዓለት ፈልፍሎ የሠራው ድልድይም የሥነ ምሕንድስና ሙያው የታየበት አሻራ ነው::

አባ ጊዮርጊስ ዕውቀት ስለ ተሠወረው ሁልጊዜ በሥዕለ ማርያም ሥር እየተንበረከከ ይጸልይ ነበር:: የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳምንም እህል በመፍጨት ያገለግል ነበር:: አባ ጊዮርጊስ ይፈጭበት የነበረው የድን ጋይ ወፍጮ አሁንም በገዳሙ ውስጥ ይገኛል::[3] አንድ ቀን እመቤ ታችን ተገለጠችለትና አይዞህ ዕውቀት የተሠወረብህ ትምህርት ስለ ማይ ገባህ ሳይሆን የእግዚብሔር ድንቅ ሥራ እንዲገለጥ ነውና ታገሥ አለ ችው:: ከዚያም ጽዋዐ ልቡና አጠጣችው::[4]

ከዚህ በኋላ በሐይቅ እስጢፋኖስ ትምህርቱን በሚገባ ተምሮ አጠና ቀቀ:: በዕውቀቱም ቀድሞ የሚያውቁት ሁሉ ይደነቁበት ጀመር::

አባ ጊዮርጊስ የያሬድንም ዜማ ተምሯል:: የተማረውም ከአቡነ ሳሙኤል ዘጋርማ እንደ ሆነ ገድሉ ይገልጣል:: ሊቁ በዚያ ዘመን በዐፄ ዳዊት አማካኝነት በሰሜን ኢትዮጵያ የያሬድ ድጓ ዋና ማዕከል በሆነው

2 ድርሳነ ዑራኤል
3 ዳንኤል ክብረት የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች ገጽ ፩፻፶፱
4 ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ [illegible]


www.ethiopianorthodox.org

በደብረ ነጎድጓድም ተሾሞ አስተምሯል። ምክንያቱም በኢትዮጵያ የድጓ ሊቃውንት ዝርዝር አባ ጊዮርጊስ ይጠቀሳልና። በትርጓሜ መጻሕፍትና በቅኔ የጠለቀ ዕውቀት እንዳለውም ድርሰቶቹ ይመሰክራሉ።

የማስተማር ሥራውን የጀመረው በዚያው በሐይቅ እስጢፋኖስ መሆኑን ገድሉ በሚከተለው መልኩ ይገልጠዋል «ወአብርሃ ለቤተ ክርስቲያን እንተ ተሐንጸት በሐይቅ ባሕር፣ ወእም አሜሃ አኀዙ ይስአሉ እምኔሁ ኩሉሙ ሰብአ ሀገር ቃለ መጻሕፍት ወትርጓሜሆሙ፣ ወኩሉ ቃለ ማሕሌት፤ በሐይቅ የታነጸችውን ቤተክርስተያን እንድታበራ አደረጋት /አደመቃት/። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከእርሱ ዘንድ የአገሪቱ ሰው ሁሉ የመጻሕፍትን ቃል ትርጓሜና ሁሉንም የማሕሌት ቃል ይጠይቁ ጀመር።»

ከሐይቅ በኋላ በዚያ ዘመን ሸዋ በመባል ትጠራ ወደ ነበረችው ወደ ትውልድ ሀገሩ ወደ ጋሥጫ ተጓዘ። በዚያ ጊዜ የነገሥታቱ መቀመጫ በዚያ የነበረ ይመስላል። ለዚህ ሦስት ምልክቶች አሉ። የመጀመሪያው በነገሥታቱ መቀመጫ አካባቢ አብያተ ክርስቲያናት እንደሚበዙት ሁሉ/ አክሱምን፣ ላሊበላን፣ ጎንደርን፣ እንኮበርንና አዲስ አበባን በምሳሌነት ማንሣት ይቻላል።/ ጋሥጫም በዚያ ዘመን ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ። ሁለተኛው ደግሞ በገድሉ ላይ አባ ጊዮርጊስ ወደ ሸዋ በመጣ ጊዜ ወደ ቤተመንግሥት እንዳስገቡት የሚገልጥ ታሪክ መኖሩ ነው። ሦስተኛው መረጃ ጋሥጫ የዐፄ ይስሐቅ የክረምት ጊዜ ማረፊያ እንደነበረች ገድሉ መግለጡ ነው።[5]

አባ ጊዮርጊስ ወደ ሸዋ ሲመጣ አባቱ በጣም አርጅቶና መንኩሶ ነበር። ስለዚህም በአባቱ እግር ተተክቶ በቤተመንግሥቱ ያለችውን ሥዕል ቤት እንዲያገለግል ወደዚያው አስገቡት። አባ ጊዮርጊስ በቤተ መንግሥቱ የንጉሡን ልጆች ከማስተማሩም በላይ በቤተ መንግሥቱ [illegible] ከነበሩት ሊቃውንት መካከል አንዱ ነበር። በአንድ ወቅት ግብፃዊው ጳጳስ አቡነ በርተሎሜዎስ ሥላሴን አንድ ገጽ ብለው ያምናሉ። ተብለው በተከሰሱ ጊዜ ነገሩን እንዲያጣሩ ከተመረጡት ከቄስ ሐጼ ተክሥተ ብርሃንና ከሐይቁ መምህር ከዐቃቤ ሰዓት የሴፍ ጋር አብሮ ተልኮ ነበር።

5. ዳንኤል ክብረት የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች ገጽ ፩፻፶



እነዚህ ሦስት አበው ጳጳሱን ካነጋገሩ በኋላ ክሱ ሐሰት መሆኑን በማረጋገጥ ስለ ምስጢር ሥላሴ የሚገልጠውን የጳጳሱን እምነት በጽሑፍ ይዘው መጡ።[6]

በቤተ መንግሥቱ በነበረ ጊዜ የንጉሡን ልጆች ይስሐቅን፣ ቴዎፍሎስን፣ እንድርያስን፣ ሀብተ ኢየሱስን፣ ሕዝቅያስን፣ ኢዮስያስን፣ዘርዐ ያዕቆብንና ሴት ልጁን እሌኒን በምግባርና በሃይማኖት ቀርጿቸዋል። ወደ ዙፋን ከወጡት ቴዎድሮስ፣ ይስሐቅ፣ ዘርዐ ያዕቆብና እንድርያስ በስተቀር ሌሎቹ ታዋቂ አይደሉም። በእነዚህም የአባ ጊዮርጊስ የሕይወት ፍልስፍና ተንጸባርቋል። ዘርዐ ያዕቆብ በድርሰቱ ሲመስለው ቴዎድሮስ ደግሞ ለቅድስና ማዕርግ በቅቶ በሕይወት መስሉታል፣ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ተብሎ ጽላት ተቀርፆለታል፤ በዓሉ ሰኔ ፳፱ ቀን ይከበራል። ይስሐቅም በዘመኑ ፖለቲካዊና ባህላዊ እመርታ አሳይቷል።

## ፩.፩.፬. ምንኩስናና ተጋድሎ

ዐፄ ዳዊት የአባ ጊዮርጊስን ሊቅነትና መልካም ሥነ ምግባር በሚገባ ስላወቀ በጋብቻ ሊዛመደው ወዶ ስለ ነበር ልጁን እንዲያገባ ዘወትር ይጠይቀው ነበር። አባ ጊዮርጊስ ግን በድንግልና ጸንቶ ለመኖር እንደ ሚፈልግ ከመግለጽ አልተቆጠበም ነበር። የዐፄ ዳዊት ጥያቄ ስለበዛበት ከአካባቢው በመሸሽ ከአባ በጸሎተ ሚካኤል መቃብር ደረሰ። አባ በጸሎተ ሚካኤልን ከልጅነቱ ጀምሮ ይወዳቸው ስለነበር እርሳቸው በመሰረቱት ገዳም በመልካም ሥነ ምግባራቸው ከታወቁት ከአባ ቴዎድሮስ ዘንድ የምንኩስና ልብስ ለብሶ መነኮሰ።[7]

ከመነኮሰ በኋላ ወደ ሸዋ በመምጣት « ወእምድኅረዝ ኮነ አቡነ ጊዮርጊስ መምህር ለነገሥት ወለካህናት ዘደብተራ ወለኩሉ ዐበይተ ቤተ መንግሥት፣ ለንቡራነእድ ወለመኳንንት፣ ለመሳፍንት ወለኩሉ ተዐይነ ቤተ መንግሥት፡ ከዚህ በኋላ ለነገሥታትና በቤተ መንግሥቱ ለነበሩ ካህናት እንዲሁም በቤተ መንግሥቱ ታላላቆች ለነበሩ፣ ለንቡራነእድ ለመኳንንት፣ ለመሳፍንትና በቤተ መንግሥቱ ለነበሩ ባለሚሎች ሁሉ መምህር ሆነ።»

6. Sergew Hable Sellassie, 1975, J.E.S.V.8 No. 1
7. ዶ/ር ስርግው ሀብለ ስላሴ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት በሚለው ሥራቸው አባ ጊዮርጊስ የት እንደመነኮሰ ገድሉ አይገልጽም ይላሉ። ነገር ግን ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋ ስጫ Folio 28 Recto. A ላይ / ወበእንተዝ ግብር ሖረ እምህየ ወበጽሐ ኀበ መቃብሪሁ ለአባ በጸሎተ ሚካኤል ድንግል ወሰማዕት እስመ ፈድፋደ ያፈቅሮ እም ንዑሱ ወለብሰ በህየ አልባሰ ምንኩስና እመ ነበ አበምኔት አባ ቴዎድሮስ ዘፍጹም በኩሉ ምግባረ ሠናይ ይላል።

www.ethiopianorthodox.org

አባ ጊዮርጊስ በሽግላ በነበረ ጊዜ በወባ በሽታ ታምሞ ሊሞት ደርሶ እንደ ነበር ገድሉ ይናገራል። ታምሞ በነበረ ጊዜ አንድ ሌሊት ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ ተገልጠውለት ከእኛ ጋር ትኖር ዘንድ ልንወስድህ መጣን አሉት። እርሱም የድርሰት ሥራዬን ሳልሠራና እግዚአብሔርንም አብዝቼ ሳላመሰግነው አሁን አትውሰዱኝ ሲል ለመነ። እነርሱም ልመናውን ተቀብለውት ከሕመሙ ፈውሰውት ሔዱ። ለዚህም ይመስላል ከበሽታው እንደ ተፈወሰ ወዲያው የድርሰት ሥራውን የጀመረው።

የመጀመሪያ መጽሐፉን ጽፎ እንደ ጨረሰ ጠፍቶበት እንደ ነበር ገድሉ ይተርካል። በቤቱ ውስጥ የነበሩትን መጻሕፍት ሁሉ እየገላበጠ ቢፈልገውም ሊያገኘው አልቻለም። አንድ ቀን በቤተክርስቲያን ሌሊት በአገልግሎት ላይ እያለ እመቤታችን ተገልጣ «ለምን አስቀድመህ ሳትነግረኝ ጻፍክ?» ስትል ጠየቀችው። እርሱም «አንቺን ደስ ያሰኘሁ መስሎኝ ነውና ይቅር በይኝ» ሲል መለሰላት። ከዚህ በኋላ የድርሰት ሥራውን ፈቅዳለት ተሰወረች።[8]

የድርሰት ሥራው አባ ጊዮርጊስ በበርካታ ሃይማኖታዊ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ እንዲኖረው አድርጓል። ይህ በጎ አገልግሎቱ ለበርካታ ጊዜያት ለመከራ አጋልጦት ነበር። በተለይም ለተራው ሕዝብና ለመኳንንቱ የሚሰጠው ከበሬታ አንድ አይነት በመሆኑ ይህ አድራጎቱም በሹማምንቱ ዘንድ አልተወደደለትም።

በመምህርነት እንደተሾመ እቴጌዎች /የነገሥታት ባለቤቶች/ ቁጭ እንዳሉ ሥጋ ወደሙ የመቀበላቸውን ልማድ ማስቀረት ፈለገ። «የነገሥታት ንጉሥ የሆነው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነውና እቴጌዎቹ ወደ ቁርባኑ ቦታ መጥተው መቀበል አለባቸው እንጂ እነርሱ ወንበር ላይ ቁጭ ብለው ቁርባኑ ወደ እነርሱ ሊሔድ አይገባም» ብሎ በመጽናቱ ንግሥቲቱ ወደ ካህናቱ ቀርበው መቁረብ ጀመሩ።

ይሁን እንጂ ንግሥቲቱ አባ ጊዮርጊስ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ይከበር ማለቱን እንደ ድፍረት ስለቆጠሩት ጉዳዩን ወደ ንጉሡ ዘንድ አቅርበው ከሰሱት። ንጉሡም በጉዳዩ ውሳኔ ለመስጠት አጣብቂኝ ውስጥ ገቡ። ንጉሡ የአባ ጊዮርጊስ ተማሪ እንደ መሆናቸውና እንደ መንፈሳዊ

8. ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ F. 18 Roa.



www.ethiopianorthodox.org



ሰውነታቸው የአባ ጊዮርጊስ ውሳኔ ትክክል እንደሆነ ልቦናቸው ቢያውቀውም ለንግሥቲቱ ያሳየውን አመለካከት ስላልወደዱለት እርሱን የንቡረ እድነት መዓርግ ሰጥተው ዳሞት ውስጥ ለሚገኝ ቤተ ክርስቲያን አለቃ አድርገው ላኩት። ይህን በማድረግ ንጉሡ ጉዳዩን በፊሊጥ በፈቱም። ውሳኔው ግን ለንግሥቲቱ ፍላጐት ያደላ ነበር።

አባ ጊዮርጊስ እና አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ የተገናኙት አባ ጊዮርጊስ ወደ ዳሞት በሚጓዝ ጊዜ ነበር። ከዚህ በኋላ የአባ ጊዮርጊስ ዋናው ትኩረቱ በድርሰቱ ላይ ሆነ። ወደ ጳጳሱ ወደ አቡነ በርተሎሜዎስ ዘንድ በመሔድ የቅዳሴ ድርሰት ለመድረስ እንዲፈቀድለት ከጠየቀ በኋላ የቅዳሴ ድርሰት ማዘጋጀቱን ገድሉ ይገልጻል። ይህም የኢትዮጵያ ቅዳሴያት ደራሲያቸው ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ፍንጭ የሚሰጠን ይሆናል። ገድሉ እንደሚተርከው አንዳንድ ካህናት የአባ ጊዮርጊስን ቅዳሴ ተቃውመው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር አርዮስን በቀጣበት መንገድ ቀጥቷቸዋል።

አባ ጊዮርጊስ ነገረ ሃይማኖትን ጠንቅቆ የተረዳና የሚያስረዳ ስለነበር በዘመኑ የተነሡ የሃይማኖት ክርክሮች ሁሉ እርሱ ከሌለ አይሳኩም ነበር። በዚያ ጊዜ በሸዋ በይፋት ራሳቸውን ቤተ እስራኤል እያሉ የሚጠሩ አይሁድ ነበሩ። ከአቡነ ዜና ማርቆስ ጀምሮ ብዙ መምህራን ወደነዚህ ሕዝቦች እየተሠማሩ ወንጌልን አስተምረዋል። አቡነ ዜና ማርቆስ ወደ ክርስትና ለተመለሱት ቤተ እስራኤላውያን በእመቤታችን፣ በቅዱስ ሚካኤል፣ በአባ ኖብና በሰማዕቱ በጊጋር ስም አራት አብያተ ክርስቲያናትን አሠርተው ነበር። ሁለቱ የመጀመሪያዎቹ አሁንም አሉ። ይህ ሁሉ ቢሆንም ቤተ እስራኤላዊያኑ ሙሉ በሙሉ ወደ ክርስትና አልተመለሱም ነበር።

ከእነዚህ አይሁድ መካከል አንዱ ከክርስቲያኖች ጋር በነገረ ሃይማኖት ለመከራከር ጥሪ አቀረበ። «ክርስቲያኖች ከረቱኝ ወደነርሱ ሃይማኖት እገባለሁ እኔ ከረታኋቸውም ወደኔ ሃይማኖት ይገባሉ» ሲል ነገሩን ጥብቅ አደረገው። ዐፄ ዳዊት ይህን ጉዳይ ሲሰማ በጣም ስለተናደደ ሊቃነ ካህናቱን፣ ንቡራነእዶቹንና የመጻሕፍት ዐዋቂዎችን ሁሉ ከየሀገሩ እንዲሰበሰቡ አዘዘ። አይሁዳዊው በአንድ ወገን መምህራኑ

9. ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ F 21 V B

በአንድ ወገን ሆነው ክርክሩን ጀመሩ። የመጀመርያው እድል የተሰጠው ለአይሁዳዊው በመሆኑ ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ አቀረበ፡- «እናንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የምትሉት ይኸ ክርስቶስ እውነት የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነ፣ ወደ ቢታንያ በመጣ ጊዜ አልዓዛር የተቀበረበትን ቦታ ሳያውቅ ቀርቶ አልዓዛርን የት ቀበራችሁት? ብሎ እንደ ጠየቀ በወንጌላችሁ ተጽፏል። ለዚህ መልስ ስጡኝ፣ እኔንም ከመጽሐፈ አሪት ጠቅሳችሁ ጠይቁኝ?» ሲል የመከራከሪያ ነጥቡን አቀረበ።

በዚህ ጊዜ አባ ጊዮርጊስ ታሞ አልጋ ላይ ነበር። ሊቃውንቱም እንዲህ ያለው ነገር ያለ እርሱ አይሆንምና አባ ጊዮርጊስ ይምጣ ሲሉ ለዐፄ ዳዊት አመለከቱት። አባ ጊዮርጊስም በአልጋ ላይ እያለ እንዲመጣ ተደረገ። ሊቁም በአልጋም ላይ ሆኖ በጉባኤው ላይ ተገኘ። ጉባኤተኞቹ የቀረበውን ጥያቄ ነገሩት። አባ ጊዮርጊስ የሰጠውን መልስ ገድሉ በሚከተለው መንገድ ይገልጥልናል «እኔ ግን በወንጌል ሳይሆን በኦሪት እከራከርሃለሁ። የምኩራብ መጻሕፍት ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን የታወቁ ናቸውና። ምኩራብ ዘራች ቤተክርስቲያንም አጨደችው፤ ምኩራብ ፈተለችው ቤተ ክርስቲያን ለበሰችው፤ አዳምን በገነት ሳለ አዳም ሆይ! ወዴት ነህ ብሎ የጠየቀው ማነው? አብርሃምንስ ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት ብሎ የጠየቀው ማነው? እስቲ መልስልኝ፤ ስይጣንንስ ከወዴት መጣህ ብሎ የጠየቀው ማነው? እግዚአብሔር አብ አይደለምን?» በዚህ ጊዜ አይሁዳዊው መልስ አጥቶ ዝም አለ። ንጉሡ፣ ሊቃውንቱና መኳንንቱም እጅግ ተደሰቱ።

አባ ጊዮርጊስ ሌላው ያጋጠመው ክርክር ቢቱ ከተባለው ሰው ጋር ያደረገው ክርክር ነበር። ቢቱ በምጽአት ጊዜ የሚመጣው ወልድ ብቻውን እንጂ አብና መንፈስ ቅዱስ አይመጡም የሚል ኑፋቄ ማስተማር ጀምሮ ነበር። ቢቱ ከዚህ ኑፋቄው በተጨማሪ የጥንቆላ ሥራም ይሠራ ነበር። ቢቱ በጥንቆላ ሥራው የተነሣ በቤተ መንግሥቱ ተቀባይነት የነበረው ሰው እንደ ነበረ ገድሉ ይናገራል። ይህን መሰሉን ተግባር አጥብቆ የተዋጋው ዘርዐ ያዕቆብ እስኪመጣ ድረስ ነገሥታቱ ምንም ክርስቲያኖች ቢሆኑ በዚህ መሰሉ ስንኩል ሕዐ ይዋጡ ነበር።





ቢቱና አባ ጊዮርጊስ ወደ ዐፄ ዳዊት ቀርበው በጉዳዩ ላይ መነጋገር እንደሚፈልጉ ገለጡ። ዐፄ ዳዊትም ጳጳሱና ሊቃውንቱ ባሉበት እንዲነጋገሩ ስለወሰነ ጳጳሱ እንዲመጡ አዘዘ። በዚህ ጊዜ ተንኮለኛው ቢቱ ከአባ ጊዮርጊስ ጋር ከተከራከረ እንደሚረታ ስላወቀ ንጉሡ የአባቶቻችንን ሃይማኖት ክዷልና አትስማ የሚል ደብዳቤ በአባ ጊዮርጊስ ስም ጽፎ ጳጳሱን ሊጠሩ በሔዱት መልእክተኞች እጅ ላከ። ወዲያውም ለዐፄ ዳዊት ይህንን ነገር አሳበቀ። ዐፄ ዳዊትም ፈጣን መልእክተኞች ልኮየፈተኞቹ መልእክተኞች እንዲመለሱ አደረገና ደብዳቤው ተነበበ። የቢቱ ተንኮል ያልገባው ዐፄ ዳዊት ይህን ደብዳቤ ሲመለከት አባ ጊዮርጊስ በደም እስኪነከር ድረስ እንዲደበደብ አድርጎ ወደ እስር ቤት አስገባው። ቅዱሱም ዐፄ ዳዊት እስኪሞትና ልጁ ቴዎድሮስ እስኪነግሥ ድረስ በዚያ ቆየ። ቢቱ ግን በመልአክ ተቀስፎ ሞተ።

በአባቱ ዙፋን በተተካ ጊዜ አባ ጊዮርጊስን ከወኅኒ ቤት አውጥቶት በጥንቱ ቦታው አስቀመጠው። አባ ጊዮርጊስ ግን የቤተ መንግሥትን ነገር ለመሸሽ ስለ ፈለገ በጋሥጫ ከመቀመጥ ይልቅ ርቆ ጥንት ወደ ነበረበት ወደ ዳሞት በመሔድ ማስተማር ጀመረ። ወደ ዳሞት ሲሔድ እግረ መንገዱን ወደ ደብረ ሊባኖስ ገብቶ የአቡነ ተክለሃይማኖትን መቃብር ተሳልሟል። በዚያ ጊዜ የደብረ ሊባኖስ አበምኔት ዕጨጌ ዮሐንስ ከማ /ስባተኛው የደብረ ለባኖስ ዕጨጌ/ እንደ ነበሩ ገድሉ ይናገራል።

ነገር ግን በዕውቀቱ የሚቀኑበት፣ በችሎታው የሚመቀኙት ሰዎች ነገር ሠርተው ከንጉሥ ቴዎድሮስ ጋርም ስላጣሉት ሰው ሊኖርበት ወደ ማይችል በረሃ እንዲጋዝ ተደረገ። አባ ጊዮርጊስ ከዚህም ግዞት የወጣው ዐፄ ቴዎድሮስ ሲሞት ነበር።

የአባ ጊዮርጊስ ሌላው ተማሪ የነበረው ዐፄ ይስሐቅ በ፲፫፻፺፱ ዓ.ም መንግሥቱን ሲይዝ አባ ጊዮርጊስ ከግዞት አውጥቶ ወደ ጋሥጫ መለሰው። በዚያ ጊዜ አባ ጊዮረጊስ ዕድሜው ፶፪ ዓመት ሲሆን በስደትና በጤንነት መታወክ የተነሣ ጉዳት ደርሶበት ነበር። ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜውን በጾም፣ በጸሎትና በድርሰት ያውለው ነበር።[11]

10. ወሶቤሃ ፈነው እግዚአብሔር መልአከ ወተሰፎ ለቢቱ ወሞተ ሞተ እኩየ ወአእረፈት ቤተ ክርስቲያን ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ F 26 Rb.

11. ዳንኤል ክብረት የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች ገጽ ፷፪።



www.ethiopianorthodox.org

አባ ጊዮርጊስ መከራ ያልተለየው አባት ነበር። ገድሉ እንደሚተርከው በቤተ መንግሥቱ የነበሩ ሰዎች የርሱን መከበርና መወደድ አይፈልጉትም ነበር። በተለይም ፍካሬ ሃይማኖት የተሰኘውን መጽሐፍ በመጻፉ የተነሣ መከበሩ አልተዋጠላቸውም። ስለዚህም ነገር ሠርተውም ከዐፄ ይስሐቅም ጋር አጣሉት።

ከዕለታት በአንድ ቀን የአባ ጊዮርጊስ በሥጋ ዘመዱ የሚሆን አባ ጊዮርጊስ በሰውና በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ክብርና ሞገስ አይቶ በመቅናት ወደንጉሡ በመሔድ በሐሰት ከሰሰው ዐፄ ይስሐቅ አባ ጊዮርጊስን አሳስሮ ውሃ ወደማይገኝበት አለታማ ቦታ አጋዘው። በዚያም በመከራ ለብዙ ጊዜ ኖረ። በዚያ እያለ ዘወትር በጸሎት አበዝቶ ይተጋ ነበር። እግዚአብሔርም ዐፄ ይስሐቅ ወደ ልቡናው እንዲመለስ አደረገ። ንጉሡም በአባ ጊዮርጊስ ላይ የፈጸመው ነገር ሁሉ ፀፀተው። አገልጋዮቹንም ጠርቶ አባ ጊዮርጊስን እንዲያመጡት አዘዘ። ነገር ግን እነዚያ ተንኮል ሠሪዎች የአባ ጊዮርጊስ መምጣት ተንኮላቸውን ስለሚያጋልጠው አባ ጊዮርጊስ ሞቷል ብለው አስወሩ። ይህንን ሲሰማ ዐፄ ይስሐቅ ፈጽሞ አዘነ።

አባ ጊዮርጊስ ሞቷል እየተባለ መወራቱን ከደቀ መዛሙሩ ስለሰማ በሕይወት የመኖሩን ዜና ጽፎ ለዐፄ ይስሐቅ እንዲያደርስለት አውሎ ነፋስን ላከው። አውሎ ነፋሱ ደብዳቤውን ተሸክሞ በመሔድ ዐፄ ይስሐቅ በድንኳን ተቀምጦ ስለ ጉልበቱ ላይ አስቀመጠው። ንጉሡ ምትሐት የተሠራበት ስለመሰለው ደነገጠና መኳንንቱንና ሕዝቡን ሰብስቦ ጉዳዩን ገለጠ። ወዲያውም እሳት አስነድዶ ቢጥለው ሊቃጠል አልቻለም። ወደ ውሃም ቢጨምረው አልጠፋም።[12] በዚህ ተደንቆ ወረቀቱን ከፍቶ አነበበው። ደብዳቤው ከአባ ጊዮርጊስ የተላከ መሆኑን ሲያውቅ ዐፄ ይስሐቅ ደነገጠ። እነዚያን መልእክተኞች ይዞ ወደ ወኅኒ ጨመራቸው። አባ ጊዮርጊስንም ከግዞት ያወጡት ዘንድ ላከ።

አባ ጊዮርጊስ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲመጣ ንጉሡ በደስታ ተቀበለው። ደብዳቤውን በማን እጅ እንደ ላከውም ጠየቀው። አባ ጊዮርጊስም ደብዳቤውን በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ በነፋስ እንደ ላከው አስረዳ።

12. በጥንት ዘመን የቅዱሳት መጻሕፍት አማናዊነት የሚረጋገጠው በእሳትና ውሃ ውስጥ ተፈትኖ ሲያልፍ እንደነበር በትውፊት ይነገራል።





ዐፄ ይስሐቅ ለአባ ጊዮርጊስ ምድረ ሰዎን የተባለውን የጳጳሳት መቀመጫ የነበረውን ሀገር በርስትነት ሰጥቶት ነበር። ይህ ቦታና ጋሥጫ ቅርብ ይመስላል። ምክንያቱም ገድለ አባ ጊዮርጊስ ስለ ምድረ ሰዎን ሲናገር በዚያ የአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም እንዳለ ይተርካል። የአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ያለው ከአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገዳም ሥር ነው። አባ ጊዮርጊስ በግዞት በነበረ ጊዜ በራእይ እመቤታችን ተገልጣ ዕረፍቱ በአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም እንደሚሆን እንደነገረችው ገድሉ ይተርካል። አባ ጊዮርጊስ በምድረ ሰዎን ንጉሥ ይስሐቅ ክረምቱን ያሳልፍበት በነበረው ቦታ ላይ ቤተክርስቲያን ሠራ። በዚያም በማስተማርና በጾም በጸሎት ይተጋ ነበር። በጋሥጫ እያለ ዐፄ ይስሐቅ አስጠራው። በዚያ ጊዜ ንጉሡ የመናገሻ ማርያምን ቤተክርስቲያን አሠርቶ ስለ ነበር እንዲባርክለት ፈልጎ ነበር። አባ ጊዮርጊስ ምንም እንኳን በዚያ ጊዜ ታምሞ የተኛም ቢሆን ወደ ንጉሡ ተጓዘ። እዚያ ሲደርስ በጣም ተዳክሞ ነበር። ሥርዓቱን ለመፈጸምም ዐቅም አልነበረውም። ስለዚህም ንጉሥ ይስሐቅ በአልጋ ተሸክመውት እንዲዞሩ ቤተክርስቲያኗን እንዲባርክት አደረገ።

ቡራኬውን ከፈጸመ በኋላ ደቀ መዛሙርቱን ሰብስቦ ከሞትኩ አባቴ በጸሎተ ሚካኤል መከራ ወደ ተቀበለባትና እኔም ቤተ ክርስቲያን ወደነጽኩባት ቦታ ወስዳችሁ ቅበሩኝ ሲል አዘዛቸው። ለደቀ መዛሙርቱ የመጨረሻ የስንብት ትምህርቱን እያስተማራቸው እነርሱም በአልጋ ተሸክመውት ወደ ጋሥጫ እየመሩ ሳለ በመንገድ ላይ ሐምሌ ሰባት ቀን ፲፬፻፳፯ ዓ.ም በ፷ ዓመቱ ዐረፈ።

በገድሉም ላይ በዘመዶቹና በደቀመዛሙርቱ መካከል የት ይቀበር በሚለው ጉዳይ ላይ ክርክር መነሣቱንና ንጉሡ በገዳሙ እንዲቀበር መወሰኑን ይገልጣል። ከዚህም በላይ ደግሞ ክርክሩ አልቆ ዐፅሙ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እስኪገባ ድረስ በሌላ ቦታ ዐፅሙ ዐርፎ መቆየቱን ገድሉ ጨምሮ ይገልጣል። በመሆኑም ያረፈበት ቦታ ጉንደ መስቀል ሳይሆን አይቀርም።

**የጻድቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን።**

www.ethiopianorthodox.org

## ፩.፪ ሥራዎቹ

በርካታ የድርሰት ሥራዎችን በማበርከት አባ ጊዮርጊስን የሚተካከል ሰው በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ውስጥ የተፈጠረ መሆኑ ያጠራጥራል። በዚህም የተነሣ የኢትዮጵያ ብርሃን የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። የመጻሕፍቶቹ ብዛት በትክክል ባይታወቅም በገድሉ ውስጥ የተጠቀሱት ዘጠኙ በሌሎች የጥናት ወረቀቶች የሰፈሩት የሚከተሉት ናቸው።

### ፩.፪.፩ አርጋኖን

አርጋኖን የተሰኘው መጽሐፍ ሊቁ እመቤታችንን በቅኔ ያመሰገነበት መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ እንደ ውዳሴ ማርያምና እርሱ እንደ ጻፈው ሰዓታት ብርሃን በሰባት ቀን የተከፋፈለ ነው። ይህ መጽሐፍ አብዛኛውን ጊዜ በነግህ ጸሎት የሚደርስ ነው። ገዳማውያን አባቶች በስፋት ይገለገሉበታል /ይጸልዩበታል/ በዚህ መጽሐፍ እምቅነት እና ይዘት የተደሰቱት ዐፄ ዳዊት መጽሐፉ በወርቅ ቀለም እንዲጻፍ አዘው እንደነበር ይነገራል።

ስለ አርጋኖን ድርሰቱ እንደሚከተለው በገድሉ ተጽፏል። «ወሰመየ በሠለስቱ አስማት ዘውእቶሙ አርጋኖን ውዳሴ ወመሰንቆ መዝሙር ወእንዚራ ስብሐት፤ በሦስት ስሞችም ሰየማቸው እነርሱም አርጋኖን ውዳሴ፣ መሰንቆ መዝሙርና እንዚራ ስብሐት ይባላሉ።» ይህ አገላለጥ አርጋኖን አንድ ሆኖ ሦስት መድብሎች ያሉት እንደሆነ ያሳያል።

### ፩.፪.፪ እንዚራ ስብሐት

እንዚራ ስብሐት የተሰኘው መጽሐፍ ከአርጋኖን ጋር በአንድ ጥራዝ የተዘጋጀ ሲሆን ከ«ሀ» እስከ «ፐ» ያሉትን ፊደላት በመከፋፈል በመልክዕ የተዘጋጀ ነው። «ወሰመየ ሠለስቱ አስማት ዘውእቶሙ አርጋኖን ውዳሴ ወመሰንቆ መዝሙር ወእንዚራ፣ በሦስት ስሞች ሰየማቸው እነርሱም አርጋኖን ውዳሴ፣ መሰንቆ መዝሙርና እንዚራ ስብሐት ይባላሉ።» ይላል ገድሉ። ይህ አገላለጥ ሁለት ነገሮችን ይጠቁራል። አንደኛው ስለ አርጋኖን ይዘት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሊቁ በዘርፉ በግጥም የሚደርሳቸው መጻሕፍቶቹ ከዜማ መሣሪያዎች ጋር ለማገናኘት ጥረት ማድረጉን ያመላክታል።





### ፩.፪.፫ ውዳሴ ሐዋርያት

ይህን መጽሐፍ አባ ጊዮርጊስ በእስር ቤት ሳለ እንደጻፈው ይነገራል። በተለይ በወኅኒ ተጥሎ ሳለ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ እየመጡ ያጽናኑት ስለ ነበረ «ውዳሴ ሐዋርያት» የሚለውን የመጽሐፉን ስያሜ ከግብራቸው አይደይዞ የሰጠው ነው። ይህ መጽሐፍ በሌላ አጠራሩ ገድሉ ይህን መጽሐፈ ፍጽም ብሎ እንደጠራው ይናገራል።

### ፩.፪.፬ ሕይወተ ማርያም

ከሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬምና ከኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ ለጥቆ እንደ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በእመቤታችን ሕይወት ዙሪያ በስፋት የጻፈና የተቀኘ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። ምንጮቻችንም አይጠቁሙም። በጥቅሉ ሕይወተ ማርያም ስለ ነበረ ድንግል ከቀደምት ነቢያት ትንቢትና ምሳሌ ጀምሮ እስከ ሐዋርያት ስብከት ድረስ የተጻፉ መጻሕፍትን መሠረት ያደረገና የሊቁ የጽሑፍ ክሂሎት የታየበት መጽሐፍ እንደ ሆነ ለመገመት አያዳግትም።

### ፩.፪.፭ ተአምኆ ቅዱሳን

የዚህም መጽሐፍ ቅጂ በአሁኑ ጊዜ አልተገኘም። ስለይዘቱ ግን ከስያሜው ተነሥቶ ግምት መስጠት ይቻላል። መጽሐፉ «ተአምኆ ቅዱሳን» ተብሎ እንደመሰየሙ የቅዱሳንን የገድል እና የትሩፋት ሕይወት የሚያሳይ መሆኑን መጠቆም ይቻላል። ምክንያቱም የሊቁ ሕይወት በገድልና በትሩፋት የተሞላ እንደመሆኑ የሌሎችን ቅዱሳን ሕይወት ያሳየበት መጽሐፍ ሳይሆን አይቀርም።

### ፩.፪.፮ ጸሎት ዘቤት ቤት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እና አልአዛር በምእመናን ቤት በመገኘት ያስተምር እንደነበረ ሐዋርያትም ይህንን አብነት አድርገው በምእመናን ቤት ትምህርትና ጸሎት ያደርጉ ነበር አባ ጊዮርጊስም ይህንን ትውፊት በመጠበቅ ካህናት በምእመናን ቤት ለማስተማርና ለማጥመቅ በሚዘዋወሩበት ጊዜ በምእመናን ቤት የሚጸልዩትን ጸሎት አዘጋጅቷል። ይህም መጽሐፍ ካህናት ለማጥመቅ ለማስተማር በሚዘዋወሩበት ጊዜ በየሰዓቱ የሚጸልዩት እና በምእመናን ቤት የሚደርስት የጸሎት መጽሐፍ ሊሆን እንደሚችል ከስያሜው ተነሥቶ መገመት ይቻላል።



www.ethiopianorthodox.org

## ፩.፪.፯ ፍካሬ ሃይማኖት

ገድሉ ላይ እንደተጻፈው [illegible] መጽሐፉ ስም መረዳት እንደሚቻለው ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው [illegible] ዳዊት ጦር አዛዥ የነበረው ቴዎድሮስ ስለ ቀናች ሃይማኖት /ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ/ በጠየቀው ጊዜ መልስ [illegible] ዘንድ የጻፈው መጽሐፍ ነው። ገድሉ ነገሩን ሲገልጽ «ወበአሐቲ [illegible] ተስእሎ አሐዱ መስፍን ዘስሙ ቴዎድሮስ ዘይሰመይ ካዕበ [illegible] በእንተ ሃይማኖት ርትዕት ወጸሐፈ ሎቱ መጽሐፈ ዘይሰመይ ፍካሬ ሃይማኖት ወሶበ ርእዮ [illegible] ለውእቱ መጽሐፍ [illegible] ሎሙ ካህናተ ምስጢር ይቤሉ [illegible] የሐንስ አፈወርቅ ወቄርሎስ [illegible] በረከት ተንሥኡ በመዋዕሊሁ ኢትዮጵያ ተመሰለት በቴዎድሮስ [illegible] ወተአረየታ ለእስክንድርያ፡ አንድ ቀን ቴዎድሮስ የተባለ መስፍን [illegible] ተኛው የጦር አዛዥ፣ አባ ጊዮርጊስን ስለ ርትዕት ሃይማኖት ጠየቀው። አባ ጊዮርጊስም ፍካሬ ሃይማኖት የተባለውን መጽሐፍ ደርሶ ሰጠው። ንጉሡና የምስጢር ሊቃውንት [illegible] ካህናት ይህንን በተመለከቱ [illegible] በእውነት የሐንስ አፈወርቅ [illegible] በረከት የሆነው ቄርሎስ [illegible] ተነሥተዋል፤ ኢትዮጵያም [illegible] መሰለች፡ ከእስክንድርያም [illegible] ከፍ ከፍ ብላለች ብለው አደነቁ [illegible]። ይህ መጽሐፍ ንጉሡን [illegible] በዘመኑ የነበሩትን ሊቃውንት እጅግ ማስደሰቱን ከገድሉ መረዳት ይቻላል።

በገድሉ በስፋት የተወደሰው ኢትዮጵያ እስክንድርያን በልጣ [illegible] ንጥንዩ በአቻነት ለመቆም [illegible] የተደረሰላት መጽሐፍ [illegible] ባሬትና በገዳማት ተሠራጭቶ [illegible] ላይ ሲውል አይታይም። [illegible] ርብ ትልቅ ትምህርተ ሃይማኖት [illegible] ቢኖረው እንደሚችል [illegible] መት አያዳግትም:

## ፩.፪.፰ ሰዓታት ዘመዓልት ወዘሌሊት

መጽሐፈ ሰዓታት ከስያሜው መረዳት እንደሚቻለው የሌሊት [illegible] የቀን ምስጋና ተብሎ በሁለት ይከፈላል። የዚህ መጽሐፍ ሊቃውንት [illegible] «መጽሐፈ ስብሐት» እንደሚባል በሊቁ ሥራ ላይ ጥናት ያደረጉት ዶ/ር ሥርገው ሀብለ ሥላሴ [illegible] በብራና ላይ በሚገኙ ቅጂዎች [illegible]





«መዝሙር» እየተባለ ይጠራል። መጽሐፉ ሰዓታት የተባለበት ምክንያት በየሰዓቱ የሚጸለይ ምስጋናን የያዘ በመሆኑ ነው። ለአብነት ያህል የሰዓ ታቱን የምስጋና አከፋፈል እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

በዚህ መልክ ለሃያ ሁለት ሰዓታት ያገለግል ዘንድ የተቀመረ ነው። በስ ፋት አገልገሎት ላይ የሚውለው ሰዓታት ዘሌሊት /የሌሊት ምስጋና/ ሲሆን የመዓልቱ ግን በታላላቅ ገዳማትና አድባራት በዐቢይ ጾም አገልግ ሎት ላይ ይውላል። በሊቁ የተዘጋጀው ይህ መጽሐፍ በትምህርተ ሃይማ ኖት የበለጸገ መሆኑን ከሚከተሉት ጥቅሶች መረዳት ይቻላል።

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር አረፋተ ጽርሑ ዘንድ ወጸፍጸፈ ቤቱ በረድ ኅብረ ህላዌሁ ዘኢይትበአድ ሎቱ ለባሕቲቱ ይደሉ ሰጊድ፡ የአዳ ራሹ ግድግዳ እሳት፡ የቤቱ ወለል በረድ፣ በአኗኗሩ [በባሕርዩ] የሚይለይ አንድ የሆነ እግዚአብሔር የተመሰገነ ነው፡ ለእርሱ ለብቻው ስግደት ይገባል።»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘእምቅድመ ዓለም ህሉ ወይሄሉ እስከ ለዓለም ፡ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እየተባለ የሚመሰገን እግዚ አብሔር ከዓለም በፊት የነበረ እስከ ዘለዓለም ይኖራል።»

✡

«ማርያም እግዝእትነ ወላዲተ አምላክ ሰአሊ በእንቲአነ እስመ ረከብኪ ሞገስ በኀበ እግዚአብሔር፡ አምላክን የወለድሽ እመቤታችን ማርያም ሆይ! በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን (ባለሟልነትን) አግኝተሻልና ለምኝልን።»

✡

«ሚካኤል ሊቀ መላእክት ሰአል በእንቲአነ ወቅዱስ ገብርኤል አዕርግ ጸሎተነ፡ የመላእክት አለቃ ሚካኤል ስለ እኛ ለምንልን ቅዱስ ገብርኤልም ጸሎታችንን አሳርግ።»

እነዚህ ለአብነት ከመጽሐፈ ሰዓታት የተወሰዱ መዝሙሮች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ሥርዐተ እምነት የሚያንጸባርቁ ናቸው። እዚህ ላይ ስለ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊነት ስለ ድንግል ማርያም እና ስለመላእክት አማላጅነት እንደተገለጸ መረዳት ይቻላል። በዚህ መልክ የተዘጋጀው መጽሐፈ ሰዓታት በተለያዩ አሳታሚዎች ታትሞ በስፋት ገበያ ላይ ይገኛል።



www.ethiopianorthodox.org

### ፩.፪.፱ ቅዳሴያት

አባ ጊዮርጊስ እመቤታችን ልጇን ይዛ ወደ ግብፅ በተሰደደች ጊዜ በወርኃ ጽጌ የሚቀደስ የእመቤታችንን ቅዳሴ መድረሱ ይነገራል። ይህ ቅዳሴ በወርኃ ጽጌ በአንዳንድ ገዳማት ይቀደሳል። ሌሎችም ያልታተሙ ወይም በብራና የተዘጋጁ ስድስት የቅዳሴ ቅጂዎች እንዳሉት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትውፊትና መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ጥናት ያደረጉ ስዊዛዊቷ ክርስቲን ሻዮ ያስረዳሉ።[13] እነዚህ በአባ ጊዮርጊስ የተዘጋጁት ቅዳሴያት አገልግሎት የሚይሰጡት በእመቤታችን ስም በሌሎች ቅዱሳን ስም የተዘጋጁ የመጀመሪያ ቅጂዎች በመኖራቸው መሆኑን አጥኚዎች ይስማማሉ።

አባ ጊዮርጊስ ቅዳሴያትን ይደርስ ዘንድ ሊቀ ጳጳስ አቡነ በርተሎሜዎስን ማስፈቀዱን የሚናገሩ አጥኚዎች አሉ። ሌሎች ደግሞ ቅዳሴን ይደርስ ዘንድ ያዘዙት ሊቀ ጳጳሱ አባ በርተሎሜዎስ ናቸው ይላሉ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዐሥራ አራት ቅዳሴያት እንዳሏት ይታወቃል። ይህ ሁኔታ ሌሎች አገራት ካላቸው ቅዳሴያት ጋር ሲነፃጸር የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በርካታ ቅዳሴያት ካላቸው አገራት ተርታ ያሳልፋታል።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዳሴያት መብዛት በይዘት መመሳሰል ምክንያት ደራሲው አባ ጊዮርጊስ በመሆኑ ነው የሚሉ አጥኚዎች አሉ። ይህ አስተያየት ብዙ የሚያስኬድ አይመስልም። በስማቸው ቅዳሴ የተሰየመላቸው ሊቃውንት ተቆጥሮ በሚታወቅ ዘመን የነበሩና ቅዳሴን ለመድረስ ብቃት ያላቸው አበው ሊቃውንት በመሆናቸው ነው። ከላይ እንደተገለጸው ግን አባ ጊዮርጊስ ተጨማሪ ቅዳሴያትን ደርሷል የሚለው ለእውነት የቀረበ ነው። አባ ጊዮርጊስ በቅዳሴ ዙሪያ የሠራው ሥራ ለቀጣይ ጥናት የሚጋብዝ ነው።

### ፩.፪.፲ ውዳሴ መስቀል

ይህ መጽሐፍ መገመት ይቻላል። በመጽሐፉ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንደሚያስረዱት መጽሐፉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ መስቀልን የሚያወድስ ነው። የአጻጻፍ ስልቱም ከሊቁ ሌሎች ሥራዎች ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ አለው። አጀማመሩ እንደ ሆኅተ ብርሃን እንደሆነ የአጥኚዎቹ

13. ክርስቲን ሻዮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት እና መንፈሳዊ ሕይወት ገጽ 120





ምልከታ ይጠቁማል። ይህ መጽሐፍ በሰዓታት መጽሐፍና በመጽሐፈ ምስጢር ስለ መስቀል ከገለጸበት ገጸ ምንባብ ጋር ተዛምዶ አለው። በሰዓታት «ጸልዩ ቅድመ መስቀል እንዘ ትእህዝዎ በየማን ወትክህድዎ ለሰይጣን እስመ ተቀደሰ በደመ ክርስቶስ መድኅን፡ ሰይጣንን ክዳችሁ በቀኝ እጃችሁ ይዛችሁ በመስቀል ፊት ጸልዩ በመድኅን ክርስቶስ ደም ተቀድሷልና» የሚል ክፍል አለና። ይኸውም የሊቁ ሥራ ለመሆኑ ፍንጭ ይሰጣል።

### ፩.፪.፲፩ ሆኅተ ብርሃን

በዚህ መጽሐፍ አባ ጊዮርጊስ የመጽሐፍ ቅዱስ ምጡቅ ዕውቀቱ እንዳንጸባረቀበት ከሥራው መረዳት ይቻላል። ለምሳሌ ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬም ትንቢተ ሕዝቅኤልን መሠረት አድርጎ «ርኢኩ ሆኅተ በምሥራቅ ኅቱም፡ በምሥራቅ የተዘጋ በር አየሁ» «ሆኅትስ ድንግል ይእቲ እንተ ወለደት ለነ መድኅነ፡ ደጁም መድኅንን የወለደችልን ድንግል ማርያም ናት ብሎ» እንዳመሰገነ አባ ጊዮርጊስም በጠቀሰው ሊቅ አደራረስ መሠረት ለድንግል ማርያም አጠር ያለ ውዳሴ ያቀረበበት መጽሐፍ ነው።

ይህ መጽሐፍ በሰባት ዕለታት በመከፋፈሉ ከውዳሴ ማርያም ጋር ይመሳሰላል። በይዘቱም ከላይ ከተጠቀሰው ውዳሴ ማርያም አንቀጸ ብርሃንና ቅዳሴ ማርያም ጋር ይዛመዳል። ሆኅተ ብርሃን ከአርጋኖን ጋር ታትሞ ለተጠቃሚዎች ቀርቧል። ይህ መጽሐፍ ሆኅተ ብርሃን የአባ ጊዮርጊስ የመጀመሪያ መጽሐፍ ስለ መሆኑ ገድለ አባ ጊዮርጊስ እንደሚከተለው ያስረዳል። «ወውእቱ ሶበ ተፈስሐ በመንፈስ ቅዱስ ወደረሰ ላቲ መጽሐፈ ዘይሠመይ ሆኅተ ብርሃን።» የዚህ መጽሐፍ የብራና ቅጂ በሰሜን ሸዋ በሚገኙ ገዳማት እና አድባራት እንደሚገኝ የምንረጫቻችን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

### ፩.፪.፲፪ መጽሐፈ ብርሃን

አባ ጊዮርጊስ ይህን መጽሐፍ የእግዚአብሔርን መንገድ እና ክብረ ድንግልን ለመግለጽ ያዘጋጀው መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ «መጽሐፈ ብርሃን» ብሎ የሰየመበትን ምክንያት በገድሉ ላይ በዚህ መልኩ ተጽፎ ይነበባል። «እስመ ውእቱ ያበርህ ወያስተርኢ ፍናወ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር ወፍናወ ስብሐቲሃ ሆሙ ለትጉሃን ወለኩሎሙ ማኅበረ ቅዱሳን ልዑላነ ብርሃን ወዓዲ ይነግር እንዘ ያስተሐውዝ ውዳሴሃ ለድንግል ንጽሕት፡ የእግዚአብሔር የምስጋ


www.ethiopianorthodox.org

ናውን መንገድ አብርቶ ያመላክታልና፡ የእመቤታችንንም የምስጋናዋን ባሕም ይገልጣልና» ይላል። ከእርሱ በኋላ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በዘመኑ ሥር ሰዶ የነበረውን ባዕድ አምልኮ /አጉል እምነት/ ለመዋጋት ያዘጋጀው መጽሐፍም «መጽሐፈ ብርሃን» የሚል ስያሜ እንደተሰጠው ጥናቶች ይጠቁማሉ። ሁለቱ መጽሐፍት በስያሜ አንድ ቢሆኑም በይዘት እንደሚለያዩ መገመት ይቻላል።

### ፩.፪.፲፫ መጽሐፈ ምስጢር

ይህ መጽሐፍ የአባ ጊዮርጊስ የነገረ ሃይማኖት ዕውቀት በስፋትና በጥልቀት የተንጸባረቀበት መጽሐፍ ነው። መጽሐፈ ምስጢር የትርጓሜ ዕውቀቱ መለኪያ ነው የሚሉም አሉ። መጽሐፉን ኢትዮጵያዊ ትምህርተ ሃይማኖት የተንጸባረቀበትና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዐውደ ጥበብ ብለውታል።

መጽሐፈ ምስጢር የመናፍቃንን ትምህርት ለመቃወም የተጻፈ ነው። የመጽሐፉ ዓላማ የካቶሊካውያንን እምነት ለመቃወም የተደረሰ ሲሆን ይዘቱ በአንድ ኢትዮጵያዊና በአንድ ፈረንጅ መካከል የተደረገ የሃይማኖት ክርክር ውጤት ነው። የፈረንጁ ስም ብራንካሌዎኔ ነው የሚሉ አጥኚዎች አሉ።[14] ነገር ግን ይህ አባባል አያስኬድም ገድሉ ደግሞ ስለ መጽሐፈ ምስጢር አደራረስ ሲገልጥ፡፡

ከግዞት ከተመለሰ [ከተለቀቀ] በኋላ እመቤታችን ተገልጣለት መከራው ሁሉ እንደሐዋርያት መሆኑን ገለጠችለት። አእምሮውን ብሩህ፣ ልቡናውን ትጉህ፣ የሚያደርግ እጅግ ብዙ ምስጢር ነገረችው። ተሰናብታው ከሔደች በኋላ እጅግ ብዙ መብራት አቅርቡ አምስት ፈጣን ጸሐፊዎችንም አምጡ ብሎ አዘዘ። እርሱ እየነገራቸው እነርሱ እየጻፉ እረፍት ሳያደርጉ ሦስት ቀን ሙሉ አስጽፎ መጽሐፈ ምስጢር የተሰኘውን መጽሐፍ ፈጸመ። ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ይህን ዘዴ የተጠቀመው በስደትና በመከራ ከመድከሙ የተነሣ ዐረፍተ ዘመኑ መድረሱን ተረድቶ ይሆናል። አምስቱ ጸሐፊዎች የየድርሻቸውን ጠንቅቀው ጽፈው በአንድ አደረጉት አባ ጊዮርጊስም ጽሑፉን ተመልክቶ አደነቀ «እኔ የዚህን መጽሐፍ ቃል አልተናገርኩም፣ መንፈስ ቅዱስ በእኔ አፍ ተናገረ እንጂ» ሲል መመስከሩን ገድሉ ይገልጣል።

14. አምሣሉ አክሊሉ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍ ቅኝት ገጽ 40





ይህንም መጽሐፍ መጽሐፈ ምስጢር ሲል ሰየመው። የጻፈው በ፲፬፻፶፱ ዓ.ም እድሜው ፺፱ በደረሰ ጊዜ ሲሆን የዚህ መጽሐፍ ቅጅ በነጋድያን እጅ እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ በወቅቱ ሄዶ እንደ ነበር ገድሉ ያስረዳል።

መጽሐፈ ምስጢር የተጻፈበትን ዘመንና ምክንያት የዐፄ ዘርዐ መጽሐፈ ምስጢር የተጻፈበትን ዘመንና ምክንያት «በመዋዕሊሁ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ከዚህ በተለየ ነው የሚያስቀምጠው። «በመዋዕሊሁ ለዘንቱ ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ኮነ ተቃሕዎ በእንተ ሃይማኖት ወተዋ ሥአ አባ ጊዮርጊስ ምስለ አሐዱ አፍርንጅ ወሞዖ እስከ ከሠተ ወጻሐፈ በሃይማኖት መጽሐፈ ምሥጢር።» በዚህ በንጉሥ ዘርዐያዕቆብ ዘመን በሃይማኖት ምክንያት ክርክር ሆነ። አባ ጊዮርጊስም ከአንድ ፈረንጅ ጋር ተከራክሮ ረታው። መጽሐፈ ምሥጢር የተባለውንም መጽሐፍ ደረሰ።» ይላል። ይህ ግን የሚያስኬድ አይመስልም። ምክንያቱም አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ዐርፎ ነበርና።

ይህ መጽሐፍ በታወቁ ገዳማትና አድባራት ይገኛል። የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ከመጽሐፉ እየጠቀሱ ይጠቀሙበታል። የመጽሐፉ ጥንታዊ ቅጂ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ይገኛል። በአዲስ አበባም የመጽሐፉ የቅርብ ጊዜ ቅጂ በማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም ደብረ መድኃኒት ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። ይህን ቅጂ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። ሌሎች ለቤተ ክርስቲያኑ እንደሰጡ በብራናው ቅጂ ላይ ተጽፎ ይገኛል። ሌሎች በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ተቀምረው የተዘጋጁ የግእዝ ቅጂዎች አሉ።

በኢትዮጵያ ጥናት ላይ ብዙ ምርምር ያደረገው ኮንቲሮሲኒ ከመጽሐፈ ምስጢር ሁለት ምዕራፎች ወደ ጣልያንኛ ተርጉሞ አሳትሟል። ለዚህ መጽሐፍ ከእኛ ይልቅ የውጪ ሰዎች ምን ያህል ትኩረት እንደሰጡት መገመት አያዳግትም።

### ፩.፫ መደምደሚያ

አባ ጊዮርጊስ የወርቃማው ዘመን ስመጥር ደራሲ መምህር እንደ ነበር እሰጥ አገባ አያስገጥምም። ከቅዱስ ያሬድ ቀጥሎ በጽሑፍ ሥራው በመም ህርነቱ በሥነ ምህንድስና ሙያው በገድልና በትሩፋቱ የኢትዮጵያን



www.ethiopianorthodox.org

ቤተክርስቲያን ያበለጸገ ሊቅ ነው። እስከ ዛሬ ድረስ ለቤተክርስቲያኒቱ አውርሶ ያለፋቸው የዜማ እና የነገረ ሃይማኖት ድርሰቶቹ ምእመናን በጸሎት እንዲተጉ ከእምነት ተቃራኒዎቻቸው እንዲጠበቁ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

የዚህ ሊቅ ሥራዎች በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያና በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ የነበረውን የሥነ ጽሑፍ ብልጽግና ፍንትው አድርገው ያሳያሉ።

እንግዲህ በስፋት የሚጠኑት የአባ ጊዮርጊስ ሥራዎች እስከ ዛሬ ተተርጉመው ለሕዝበ ክርስቲያኑ አልቀረቡም። ስለዚህ በዚህ ሊቅ ሥራዎች የሕይወት ፍልስፍና ዙሪያ ብዙ ሊጠኑ የሚችሉ ነገሮች አሉ። ሊቁ በመጨረሻ ዘመን የጻፈውና ጥልቅ የነገረ ሃይማኖት እሴት ያለው የመጽሐፈ ምስጢር እነሆ!!!





# [ምዕራፍ ፩]

## የጌና ምንባብ

በሰማይ በምድር በባሕርና በጥልቅ ለዘላለም ክብር ይግባውና የማይታይ የተሸሸገ፡ ሙሉ ሆኖ የማይነካ፡ የማይቆረጥ የሃይማኖት ግንድ፥ በምእመናን ልብ ውስጥ የሚቀመጥ የሚገባ የበረከት መዝገብ፥ አንድ ስግደት የሚሰገድለት፡ አንድ ምስጋና የሚመሰገን፡ አንድ ጸሎት በሚጸለይለት፥ /የሚቀርብለት/ በማይለይ በአካል ሦስት በሚሆን በሚመሰገን በእግዚአብሔር ስም እንጀምራለን። አሜን።

መጽሐፈ ምስጢር ለምእመናን የሚነገር ሲሆን ለኢአማንያን የሚነገር አይደለም።[1] ዳታንና አቤሮንን ምድር ተከፍታ እስከምትውጣቸው ድረስ የሙሴ መስፍንነት ደስ አላሰኛቸውምና፡ እሳት ከማዕጠንታቸው ወጥታ እስከምትበላቸው ድረስ የሙሴ መስፍንነት በቆሬ ልጆች ዐይኖች ፊት መልካም አልነበረምና፡ ውሾች በድናቸውን እስኪበሉና ዘማዎች በደማቸው እስኪታጠቡ ድረስ ለአክአብና ለኤልዛቤል የነቢዩ የኤልያስ ተግሣጽ የሚያስጠይፍ ነበር።[2] ሶርያ ደርሶ ቆስሎ እስከሚሞት ድረስ ዳግመኛ በሴዴቅያስ ትንቢት ተምሯልና የሚክያስ ትንቢት ልቡን አሳመመው።[3] ጌታችንንም «ባለመድኀኒት ሆይ ራስህን አድን» አሉት። ዳግመኛም «በአጋንንት አለቃ አጋንንት ያወጣል» አሉት።[4] እንደገናም «ይህን የምታደርግ በማን ሥልጣን ነው?» አሉት።[5] እንደዚሁ ለሞት አድርሰው በመስቀል እንዲቸነከር አሳልፈው ሰጡት።[6] በሚያሳስቱ አጋንንት ኀይል ወደ አየራት የወጣ የሰማርያ ጠንቋይ ሲሞን መሠርይ የጴጥሮስን ትምህርት ተቃወመ። በጴጥሮስ ላይ ባደረ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ከወደ ጠፈረ ሰማይም ወደቀ። ጳውሎስንም «ይኽ ወሬኛ ምን ይላል?» ብለውታል።[7] እርሱም «እንዲህ ብለን ስናስተምር ለአይሁድ የምንሰንፍ ይመስላቸዋል፡ ለአረሚያም የምንበድል፣ ይመስላቸዋል፡ ለእኛ

1. ዘኁል ፲፮ ፥ ፩-፴፫፡ ዘዳግ ፲፩ ፥ ፮፡ መዝ ፻፮ ፥ ፲፯-፲፰።
2. ነገሥ ፳ ፥ ፳፱። ፳፪ ፥ ፴፬-፴፰።
3. ማር ፲፬ ፥ ፳፱።
4. ማቴ ፲፱ ፥ ፳፫።
5. ማቴ ፳፯ ፥ ፳፫።
6. ማቴ ፳፯ ፥ ፲፰።
7. ፩ቆሮ ፩ ፥ ፳፫።



www.ethiopianorthodox.org

ላመን የእግዚአብሔር ኀይል ነውና::»[8] ሰው ግን ከብርሃን ይልቅ ጨለ ማን ይወዳልና ኃጢአታቸው ይገለጣልና ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃ ንን ይጠላልና ብሎ ጌታችን እንደ ተናገረው እኛ ግን የማይለያይ በድ ምር የማይጨመርበት ሦስትነትን እንሰብካለን::

አብ ብርሃን እንደ ሆነ ወልድም ለዓለም ሁሉ የሚያበራ ብርሃን ነው:: ወልድ ብርሃን እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም በአንድ ብርሃንና ጸዳል /ውጋጋን/ የሚያበራ ብርሃን ነው:: አብ የማይዳሰስ እሳት እንደ ሆነ ወል ድም የማይነካ እሳት ነው:: ወልድ የማይነካ እሳት እንደ ሆነ መንፈስ ቅዱ ስም በሃይማኖት ባለ ነበልባል እሳት ቤተ ክርስቲያንን የሚያሞቅ የሚያደ ምቅ እሳት ነው:: አብ የማይታይ ኀይል እንደሆነ ወልድም በሥጋዌው እንጂ የማይገለጥ ኀይል ነው፤ ወልድ የማይገለጥ ኀይል እንደ ሆነ መንፈስ ቅዱስም ከሐዲዎች ቢነሱም ቤተ ክርስቲያን እንዳትገፋ ቤተ ክርስቲያንን የሚሸከም ኀይል ነው:: አብ ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ ወልድም ፍጹም አምላክ ነው፤ ወልድ ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ በአንድ ነቱ ለየ ገጽ ያለ መንፈስ ቅዱስም ፍጹም አምላክ ነው::

የዘንጉአንን ዘለፋ እንናገራለን:: ሰባልዮስ፡- «አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ገጽ ናቸው» አለ:: እኛ ግን ሦስት ገጽ አንድ ባሕርይ፣ ሦስት አካል አንድ አምላክ ሦስት ስሞች አንድ እግዚአብሔር እንላለን:: አቡርዮስ፡- «አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ለየራስ ናቸው» አለ:: አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ አንድ ባሕርይ አንድ መንግሥት አንድ ፈቃድ ናቸው እንላለን:: አርዮስ ክርስቶስ ፍጡር ነው አለ እኛ ግን ፈጽሞ ያልተፈጠረ ከአባቱ ህላዌ ያልተለየ ያላነሰ ነው እንላለን:: ንስ ጥሮስ፡- «ወልድ ከነቢያት እንደ አንዱ ነው:: የእግዚአብሔር ልጅ በዮ ርዳኖስ በተገናኘው ጊዜ የጸጋ አምላክ ሆነ» አለ:: እኛ ግን በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር አምላክ ነው እንላለን:: ፎጢኖስ፡- «የእግዚአብሔር ልጅ ህልውና ከማርያም ወዲህ ነው፤ ጥንት አይደለም» አለ:: እኛ ግን ህልውናው ከዘመናትና ከዓመታት ከዕለታትና ከሰዓት አስቀድሞ ነው እንላለን:: በኋለኛው ዘመን ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ ከቅድስት ድንግል ማርያም ስለ እኛ ደኅንነት ሰው ሆነ [ተዋሐደ] እንላለን::

8. ዮሐ.፫፥፲፱::





አርጌንስ፡- «ወልድ ከአብ ያንሳል አያየውም፣ መንፈስ ቅዱስም ከወልድ ያንሳል እሱን መመልከት አይቻለውም» አለ:: እኛ ግን በሥላሴ መዓርግ፣ የሚበልጥም ሆነ የሚያንስ ነገር የለም:: በአንድነት የተያያዙ በመለኮት አንድ ወገን ናቸው እንጂ እንላለን:: «የመለኮት ቃል ሰው ለመሆን ተለወጠ» የሚሉ አሉ:: እኛ ግን የመለኮት ቃል ከህልውናው /ከባሕርዩ/ አልተለወጠም እንላለን:: ባለመለወጥ ባለመጨመር አንድ ሆኖ ተዋሐደ እንላለን እንጂ:: «የመንፈስ ቅዱስ ህልውና ከክርስቶስ ጥምቀት ወዲህ ነው» የሚሉ አሉ:: እኛ ግን መንፈስ ቅዱስ ቅድመ ዓለም የነበረ ለዘላለም የሚኖር ነው እንላለን::

ቢቱ፡- «ወልድ ያለ አባቱ ለኃጥአን ሊፈርድባቸው ለጻድቃን ዋጋቸውን ሊሰጣቸው ይመጣል» አለ:: እኛ ግን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በሙታንና በሕያዋን ይፈርድ ዘንድ በአንድ አደባባይ በአንዲት መቀመጫ ይመጣል እንላለን:: እንጢዲቆማርያመስ እነዚህም አዕራሩ ማርያም /የማርያም ዐሮች/ ናቸው:: «ማርያም መድኃኒታችንን ከወለደች በኋላ ከዮሴፍ ጋር ተደመረች» [በልማደ ሰብእ (በሰው ልማድ) ኖረች] ይላሉ:: እኛ ግን የአምላክ እናት እንላታለን:: እርሷም ከወለደችው በኋላ እስከ ዘላለም በድንግልና ጸንታ ኖራለች እንላለን::

አውጣኪ፡- «የክርስቶስ ሥጋ እንደ እኛ ሥጋ ደክሞ አልታመም» አለ። እኛ ግን ከሕገ ሰብእ [ሰብአዊ ጠባይ] በተፈጥሮ ሕግ የቀረው የለም፤ ክርስቶስ በሥጋ መከራ ተቀበሎ ሞተ እንላ ለን::
ደከሞት አላበው፤ ተራበ፤ ተጠማ፤ መከራ ተቀበሎ ሞተ እንላ ለን::

የእስክንድርያው ታኦዶስዮስና የህንድኪያ ጳጳስ ሳዊሮስ፣ «በመጀመ ሪያ የእግዚአብሔር ልጅ ያለ ፈቃዱ ሞተ» አሉ:: እኛ ግን በፈቃዱ መከራ ተቀበሎ ሞተ፤ በፈቃዱ በመለኮቱ ኀይል ተነሣ እንላለን:: ዳግመኛ አቡርዮስ፡- «ለክርስቶስ ትስብእት ልብና ነፍስ የለውም መለኮቱ እንደ ነፍስና ልብ ሆነው አለ። እኛ ግን ሰብአዊ ነፍስና ጠባዐያዊ ልብ አለው:: ዳግመኛም እግዚአብሔራዊ ችሎታና [አምላካዊ ችሎታ] መለኮ ታዊ ክብር አለው እንላለን::

አፍቲክስ፡- የክርስቶስ ሥጋ ከሰማይ ወረደ» አለ። እኛ ግን የክርስቶስ ሥጋና ነፍስ ከገሊላዊት ብፅዕት ንጽሕት ከሆነችው ድንግል ማርያም ዘር ምክን ያት ሳይሆነው ከአዳም ጠባዐያዊ ፍጥረት የተነሣው ነው እንላለን::

መንክዮስ፡- «የክርስቶስ ሥጋ ምትሐት ነው፤ የሰው ልጅ ሥጋ አይደለም» አለ:: እኛ ግን የክርስቶስ ትስብእት ፍጹም ነው፤ የሚዳሰስ ሥጋ፥ የሥጋን



www.ethiopianorthodox.org

ማደሪያ የሚያጸና አጥንት፥ የሚፈስ ደም፥ ሥጋውን የሚያስር ደምስርና ጅማት፥ የራስ ፀጉር ቅንድብ፥ የማትታይ ነፍስ፥ የምታስተውልና የም ትናገር የሕይወት መንፈስ፥ በጣቶችና በእግሮች የበቀለ ጥፍሮች አለው እንላለን። አርሲስና መናፍቃን፦ ክርስቶስ በሥጋና በነፍስ ወደ ሲኦል ወረደ» አለ። እኛ ግን የመለኮት ቃል ከብፅዋ ነፍስ ጋር ወደ ሲኦል ወረደ እንላለን። ሥጋን ግን ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ከመስቀል ላይ አውር ደዋት በከፈን ጠቅልለው ከመቃብር ውስጥ ጨመርዋት። ሥጋም ያለ ነፍስ እስከ ትንሣኤው ዕለት ለብፅዋ ተቀመጠች። መለኮቱ ግን ከነፍሱ እና ከሥጋው አልተለየም። በአብ ቀኝም እንደ ቀድሞ ህልውናው ግልጽ ሆነ፤ በሁሉ ምሉዕ ሁኖ በሁሉ ቦታ ይኖራልና።

የሮሚ ሊቀ ጳጳሳት ልዮን ትስብእት ከመለኮት ያንሳል» አለ። እኛ ግን አንድ ከሆነ [ከተዋሐደ] በኋላ የክርስቶስ ትስብእት ከመለኮቱ አያ ንስም [አይጐድልም] እንላለን። የኬልቄዶን ማኅበርተኞች፦ «መለኮትና ትስብእት በሁለት ጉዳናና ሥርዐት ያሉ ናቸው» አሉ። እኛ ግን ከድንግል ማርያም ሰው የሆነ አንድ አምላክ አንድ ባሕርይ /ፈቃድ/ ነው እንላለን። «አምሳያው መስቀል ላይ ወጣ፤ የተቸነከረው እርሱ አይ ደለም» የሚሉ አሉ። እኛ ግን ለቤዛ ብዙኀን በካህናት አለቆች ዘንድ የተደበደበ፤ በጲላጦስ አደባባይ የተገረፈ፤ በችንካር የተቸነከረ፤ በሌንጊ ኖስ ጦር የተወጋ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እንላለን። ዳግመኛም፦ «በሕ ፃናት ሰውነት ውስጥ የሕይወት መንፈስ /ነፍስ/ እንዲሆን፤ በአዳም ላይ እንደ ሆነ ከእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው» የሚሉ አሉ»። እኛ ግን የነፍስና የሥጋ መውጣት ከወንድ አብራክ በመራቢያ አካል በኩል ወደ ሴት ማሕፀን ይቋጠራል (ይፀነሳል) ከእርሷም የባሕርይ መደባለቅ (መጨመር) ይሆናል፤ በእግዚአብሔር ትእዛዝ በወንድና በሴት ፈቃድ የወን ድም ሆነ የሴት ሥዕል ይሆናል።

አርጌንስ፦ «እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ያለበሳቸው [ልብስ ብርሃን] በላያቸው ላይ ያለውን ሥጋ ነው» ይላል። እኛም የምንመላለስበት የተሰፋ ቆዳ አይደለም። እኛ ግን በፈጠራቸው ጊዜ ሥጋ ነበራቸው እንላለን። እግዚአብሔር ትእዛዙን በማፍረሳቸው ያለበሳቸው የቅጣት ልብስ ቆዳ ነው እንላለን።

በሰው እጅ በተሠራች ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰማያት [ጽርሐ አርያም] ሊሸከመው የማይችለው የመለኮት ኃይል እንዴት ሊያድር ይችላል?» የሚሉ አሉ። ዳግመኛም ኅብስቱ ተለውጦ የክርስቶስ ሥጋ ወይኑም ተለውጦ የክርስቶስ ደም እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚሉ አሉ። እኛ ግን የመለኮት ኀይል ቤተ ክርስቲያንን በደሙ ይቀድሳት ዘንድ በህል ውናው ከጽርሐ አርያም ሳይለይ በቤተ ክርስቲያን ያድራል። በርደተ መንፈስ ቅዱስ በተቀደሰ ጊዜ ኅብስቱም ከኅብስትነት የክርስቶስ ሥጋ ወደ መሆን ይለወጣል፤ ወይኑም ከወይንነት የክርስቶስ ደም ወደ መሆን ይለወጣል እንላለን።[9]

«አሪት በወንጌል መምጣት ታጐለች፤ የነቢያት ትንቢትም በሐዋር ያት ስብከት ተሻረች ተበጠሰች፤ ሰንበትም በእሑድ ትንሣኤ ተሻረች» የሚሉ አሉ። እኛ ግን ኦሪት በስብከተ ወንጌል ከበረች፤ ነቢያትም በሐ ዋርያት ትምህርት ክፉ አለ፤ ዓለምን በመፍጠር ያረፈበት ዕለተ ሰንበት በመድኀኒ ዓለም ትንሣኤ ሰንበት ተከበረች እንላለን።

ዳግመኛም እመቤታችንን ድንግል ማርያምንና ስለ መስቀሉ ክብር የሚክራከሩ ሰዎችን ዜና ሰምተናል። አንዳንዶች «አምላክን የወለደች ድንግል ማርያም ከዕፀ መስቀል ትበልጣለች» ይላሉ፤ ሌሎች ደግሞ በክርስቶስ ደም የተጠመቀ መስቀሉ ይበልጣል» ይላሉ። እኛ ግን ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ እንደ ሆነች እናምናለን። በክርስቶስ ደም በተቀደሰውና የብርሃን ምልክት በሆነ በመስቀሉ እናምናለን።

ፍልብዮናስ፦ ለዮዩቶ «የክርስቶስ ትስብእቱና መለኮቱ ሁለት ገጽ ነው» ይላል። እኛ ግን የአምላካችን ህላዌ ትስብእቱና መለኮቱ በገጽና በአካል አንድ ነው እንላለን። መቅዶንዮስ፦ «መንፈስ ቅዱስ ፍጡር ነው። አብና ወልድ ግን እኩል ትክክል ናቸው» ይላል። እኛ ግን መንፈስ ቅዱስ ፍጹም ያልተፈጠረ፤ ከአብና ከወልድ የማይለይ፤ አንድ ግብር አንድ ባሕርይ ነው እንላለን።[10]

ሰዱቃውያን «ትንሣኤ ሙታን የለም» ይላሉ።[11] እኛ ግን ለጻድቃን ዋጋ ለኃጥአን ፍዳ የሚከፈልበት ትንሣኤ አለ እንላለን። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ገጽ ናቸው የሚለውን ሰባልዮስን እንዘልፈው ዘንድ ወደ

9. በቅዳሴ ጊዜ ካህኑ ሕብስቱንና ወይኑን «ልክ እንደዚያን ጊዜው ሥጋህና ደምህ አድርግ ብሎ ሲባርከው ውሳጤ ኅብስት ወወይን ይሆናል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ «የክርስቶስ ሥጋና ደም» እየተባለ እንጂ ኅብስትና ወይን እየተባለ አይጠራም።
10. አንድ ግብር ናቸው ሲባል ሦስቱንም አንድ የሚያደርጋቸውን መለኮታዊ ግብር ለመግለጽ ተፈልጎ ነው።
11. ማቴ ፳፪ ፥ ፳፫-፴፫ የሐዋ ፳፫ ፥ ፰።



www.ethiopianorthodox.org

ቀድሞ ነገራችን እንመለስ።[12] መጻሕፍት በየወገናቸው ስለ ሥላሴ ህልውና እየተናገሩ «የሥላሴ (የእግዚአብሔር) ገጽ አንድ ነው» እንዲት ይባላል። ከሁሉ አስቀድሞ የጸናች ኦሪት፦[13] «እግዚአብሔር አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር» ትላለች።[14] አብ ብቻውን በመልኬና በምሳሌዬ አላለም። አብ በመልክህ በምሳሌህ ወልድን አላለውም። እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን ብቻውን በመልክህና በምሳሌው/ህ/ አላለውም፡ በመልካችን እንደ ምሳሌ አችን አለ እንጂ። የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሳል እንደ ተፈጠረ ዕወቅ፤ ዳግመኛም የመለኮትን የሦስትነትን ገጽ ዕወቅ። ዳዊት፦ «አቤቱ፥ ፊትህን ማየት እፈልጋለሁ» አለ[15]። አስቀድሞ ወደ አብ ያመለክታል። ፊትህን ማየት እፈልጋለሁ ማለቱ ወደ ወልድ ያመለክታል። ፊትህን ከባሪያህ አትመልስ ያለው ደግሞ መንፈስ ቅዱስን ሲሆን ሦስትነትን ያመለክታል። እንግዲህ ነቢዩ የሥላሴን ፊት ለማየት ተጨነቀ። ነገር ግን እግዚአብሔርን አንድ ገጽ ብሎ የሚያስተምር ያልተጠመቀ፣ ያልተቀባ፣ ክርስቲያን ያልሆነ ነው። ዳግመኛም በመዝሙረ ዳዊት፦ «የእግዚአብሔር ቀኝ ኀይልን አደረገች» ተብሏል።[16] ይህም ስለ አብ ነው። «የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገኝ» ያለው ስለ ወልድ ነው፡ የክርስቶስ የመለኮቱ ትስብእት ለሰው ልጅ ክብሩ ነው። መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ «የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ነውና» ብሏልና። እንደገና በወንጌል «የእግዚአብሔር ቀኝ ኀይልን አደረገች» ማለቱ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተነገረ ነው። ይኸውም ሦስትነትን ያመላክታል። ኀይል ግን በእግዚአብሔር ያለ የመለኮት ጽናት ተብሎ ይተረጐማል። ይኸውም የማይታይ የማይታይ፣ የሚዳሰስ የማይዳሰስ፣ የሚገባ የማይገባ ነው። እንግዲህ የሥላሴን ህልውና [አናዎር] ተናገርን። የሰባልዮስ ትምህርት ሲኦል ያመጣችው ገሃነም የተሳው ነው። ይኸውም ከሰይጣን እስትንፋስ ወጥቶ በጠማማዎች ልቡና ተዘርቶ በቀለ፡ አደገም፡ የኃጢአትን እሾህ አፈራ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ከልጆቿ ጋር ታወከች።

12. ሰባልዮስ በ፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ የሊቢያ ሰው ነው። ወደ ሮም ሄዶ በዚያ ይኖር የነበረ የክህደት ፍልስፍና ውስጥ እግዚአብሔር አንድ አካል አንድ ገጽ ነው የሚለውን ትምህርት ወደ አገሩ መጥቶ ለማስፋፋት የሞከረ መናፍቅ ነው። አባ ጎርጎርዮስ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ አዲስ አበባ፣ ፲፱፻፹፰ ዓ.ም ገጽ ፸፱።
13. ቅድስት ኦሪት የሚለው የጸናች ኦሪት ተብሎ ተተርጉሟል። የኦሪትን አለማለፍ እና ኦሪት በራሷ ቅድስት መሆኗን ያሳያል።
14. ዘፍ.፩፥፳፮
15. መዝ.፹፥፫።
16. መዝ.፻፲፯፥፲፮።





ሰባልዮስ ሆይ! በልብህ ውስጥ መርዙን የጨመረው አባብ ነው ወይስ አፋኝት? በአፍህ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እያልክ ዳግመኛ አንድ ገጽ ትላለህና። አንድ ገጽ ካልክ አብ የትኛው ነው ወልድስ ማን ነው? መንፈስ ቅዱስ የትኛው ነው? አብም ነው፣ ወልድም ነው፣ መንፈስ ቅዱስም ነው የምትል ከሆነ ማን ላኪ ማንስ ተላኪ ይሆናል።

መድኃኒታችን ስለ ራሱና ስለ አባቱ እንዲህ ብሎ ተናግሯል፦ «የላከኝ አብ ከሁሉ ይበልጣል»።[17] ስለ መንፈስ ቅዱስም ዳግመኛ ጰራቅሊጦስን እልክላችኋለሁ» ብሏል።[18] እንግዲህ መንፈስ ቅዱስን ሁለተኛ ብሎታል። ዳግመኛም ስለ አባቱ ምስክሬ ሌላ ነው ይኸውም አብ ነው» ብሏል። ዳግመኛም «የላከኝ አባቴ ካልሳበው በስተቀር ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም» ብሏል።[19] ስለ ራሱም፦ «በእኔ ካልሆነ ማንም ወደ አብ መምጣት አይቻለውም» ሲል ተናግሯል። ዳግመኛ፦ «ብቻዬን ትታችሁኝ ትበተናላችሁ ነገር ግን ብቻዬን አይደለሁም፡ አብ ከእኔ ጋር ነውና።»[20] ዳግመኛም» «የሚወደኝን አባቴ ይወደዋል፡ ወደ እርሱ መጥተን እናድራለን፣ ዕረፍትም እናደርጋለን።»[21]

እንደዚሁም ስለ ሁለቱ ተናገረ እንጂ ስለ አንዱ አይደለም። ወደ እርሱ መጥተን እናድራለን ባለ ጊዜ ዳግመኛ ስለ መንፈስ ቅዱስ፦ «እኔ አብን እለምናለሁ እርሱም ዓለም ሊቀበለው የማይቻለውን የእውነት መንፈስ ጰራቅሊጦስን ይልክላችኋል።»[22] በዚህም የሥላሴን (የእግዚአብሔርን) ሦስትነት ያመለክታል፡ ወልድ አብን ጰራቅሊጦስን ይልክ ዘንድ ለመነ /ጠየቀ/፡ ጰራቅሊጦስም ወደ ሐዋርያት ተላከ። ዳግመኛ፦ «የነገርኋችሁን ሁሉ ልትሸከሙት አትችሉም፡ ያንጊዜ አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፣ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል» ብሏል።[23] ዳግመኛም ስለ አባቱና ስለ ራሱ እንዲህ ይላል፦ «የሁለት ሰው ምስክር እውነት ነው፡ እውነት እንደ ሆነ በሕጋችሁ ተጽፏል። ስለ ራሴ የምመሰክር እኔ ነኝ፡ የላከኝ አባቴ

17. ዮሐ.፲፬፥፳፰።
18. ዮሐ.፲፭፥፳፮።
19. ዮሐ.፲፬፥፯። ፰፥፲፱
20. ዮሐ.፲፮፥፴፪።
21. ዮሐ.፲፬፥፳፫።
22. ዮሐ.፲፬፥፲፯።
23. [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

ስለ እኔ ይመሰክራል።»[24] [illegible] ስለ ጰራቅሊጦስ፦ «እኔ [illegible] የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም [illegible] የሚወጣ የእውነት መንፈስ [illegible] ዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል [illegible] እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ [illegible] ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ [illegible] ይላል።[25] ስለ ራሱና ስለ [illegible] በማለት ይናገራል፦ «ከአባቴ [illegible] የሰማሁትን እናገራለሁ፤ [illegible] ከራሴ አይደለም። የላከኝ የአብ [illegible] ነው።» ስለ ጰራቅሊጦስም፦ [illegible] መንፈስ ጰራቅሊጦስ መጥቶ [illegible] መንገድ ይመራችኋል [illegible] ውን ይናገራል እንጂ ከራሱ [illegible] የሚመጣውንም [illegible] እርሱ ከእኔ የሰማውን ተቀብሎ [illegible] እኔን ያከብረኛል [illegible] የሆነው ሁሉ የእኔ ነውና ስለዚህ የሚነግራችሁ ከእኔ ተቀብሎ [illegible] እነግራችኋለሁ።»[26]

ጳውሎስም አንድ እግዚአብሔር አለና፤ በእግዚአብሔርና [illegible] መካከል ያለው መካከለኛው [illegible] አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነ [illegible] ኢየሱስ ነው «ራሱን ለሁሉ [illegible] ይላል።»[27]

ዳግመኛ «ሁላችሁም በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ኢየሱስ [illegible] ያደረገውን ይህን አስቡ» [illegible] ጳውሎስ ክርስቶስን [illegible] አርአያ እንዳለው አስተውል። እግዚአብሔር አንድ ገጽ [illegible] ወልድን የእግዚአብሔር አርአያ [illegible] ነበር፤ ወልድ የእግዚአብሔር [illegible] የመልኩ አርአያ ነውና ልጅ [illegible] አባቱን ይመስለዋልና [illegible] ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመናገሩ፦ «እኔን ያየ አብን [illegible] ስለዚህ ነው[28]። ዮሐንስ፦ «ልጆቼ [illegible] ይህን እጽፍላችኋለሁ [illegible] ሰው ቢኖር በኢየሱስ ክርስቶስ [illegible] ጰራቅሊጦስ አለን» ብሏል።[29] [illegible] አብሔርን ነቢያት የሰባልዮስ [illegible] በማጣጣል የኢየሱስ [illegible] ቶስን ተከታዮች ያስተምሯቸው [illegible] እንጥራቸው። የጸናች አሪት [illegible] አብሔር፤ አዳም ከእኛ እንደ [illegible] ክፉውን ደጉን የሚያውቅ [illegible] ለች።[30] ያን ጊዜ እጁን ከፍ [illegible] ከዕፀ ሕይወት በልቶ ለዘላለም [illegible] ነበር። የሥላሴ ገጽ አንድ [illegible] አዳም እንደ እኔ ሆነ [illegible]

24. ዮሐ.፰፥፲፯-፲፱።
25. ዮሐ.፲፭፥፳፮-፳፯።
26. ዮሐ.፲፮፥፲፭።
27. ፩ኛጢሞ.፪፥፭።
28. ዮሐ.፲፬፥፱።
29. ፩ኛዮሐ.፩፥፩።
30. ዘፍ.፫፥፳፪።



እንደ እኛ ሆነ ያለው ግን ስለ ክርስቶስ ሰው መሆን ነው። ይኸውም በአብ ቀኝ የተቀመጠው በአዳም ሥጋ ስለሆነ ነው። ዳግመኛ የጸናች አሪት እግዚአብሔር አለ፦ «ኑ እንውረድ፤ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው።» ትላለች።[31] ዳግመኛ፦ «እግዚአብሔር በሰዶምና በገሞራ ላይ እሳትና ዲን ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ አወረደ።» ትላለች።[32] «እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ እሳት አወረደ» ባለ ጊዜ ከሁለት አንድ እንደ ሆነ ያጠይቃል።

ዳግመኛም እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፦ «የእስራኤልን ልጆች እንዲህ በላቸው፤ ዛሬና ነገ ራሳቸውን ያንጹ ዘንድ ነገ ልብሳቸው ያጥቡ ዘንድ ተዘጋጁ ባላቸው፤ በሦስተኛው ቀን እግዚአብሔር ወደ ደብረ ሲና ይወርዳልና አለው።» ትላለች።[33] በዚህን ጊዜ ለሙሴ ሕግን ይሰጠው ዘንድ እንደ ወረደ ወልድ ተናገረ ዳግመኛ የጸናች ኦሪት፦ «በቀትርም ጊዜ እርሱ በድንኳን ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት። ዐይኑንም አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው ዐየ፤ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ሮጠ፣ ወደ ምድርም ሰገደ፤ እንዲህም አለ፦ አቤቱ፤ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ ባሪያህን አትለፈኝ ብዬ እለምናለሁ፤ ጥቂት ውሃ ይምጣላችሁ፤ እራሳችሁን ደግፉ፤ ከዚያም በኋላ ትሔዳላችሁ፤ ስለዚህ ወደ ባሪያችሁ መጥታችኋልና። እነርሱም እንዳልህ አድርግ አሉት።»[34]

ዳዊትም እንዲህ ይላል፦ «ጌታ ጌታዬን በቀኝ ተቀመጥ ከእስራኤል ቅዱስ ሌላ ለዳዊት ጌታው ማነው?» ይህን የተናገረው በአብ ቀኝ በክብር ስለ ተቀመጠው ስለ ወልድ ነው። ከዚህም በማስከተል «ጠላቶችህን ለእ ግርህ መረገጫ እስከአደርግልህ ድረስ...» ይላል።[35] ይኸውም ስለ ሰቃልያን [አይሁድ] የተናገረው ነው። «እግዚአብሔር የኀይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል።» ይኸውም የዕፀ መስቀልን የሃይማኖት ኀይል የሚያመለክት ነው። «በጠላቶችህ መካከል...» ለጻድቃን ዋጋን ለኃጥአን ፍዳን ለመስጠት በክበበ ትስብእት በግርማ መለኮት የሚቆምበትን የፍርድ አደባባይ ነው። ከአንተ ጋር ቀድሞ በኀይል ቀን ግን በእግዚአብሔር ስም የሚመጣውን መንግሥት ነው።

31. ዘፍ.፲፩፥፯።
32. ዘፍ.፲፱፥፳፬።
33. ዘፀ.፲፱፥፲፩።

www.ethiopianorthodox.org

ዳግመኛም ኃይል ሃይማኖታቸውን የተላለፉትን የምትገፋ ኃይል ነች። በቅዱሳን ብርሃን የሚለው ሥነ ብርሃን የጻድቃንን ዋጋ መግለጫ ነው፤ የጻድቅ መልካም ግብሩ ያበራለታልና ነው። «ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድኹህ» የሚለው በመለኮት ፈቃድ እንደ ሆነ ይተረጉማል። ሆድ ለሰው ልጅ የልብ መዝገብ ነው፤ ወልድም ለአብ ኅሊናው ነው፤ በወልድ የሌለ ኅሊና በአብ ላይ የለም። ስለዚህ «በአፍአዊ ባልሆነ በውስጣዊ ልደት ወለድኩኽ» ይላል። ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ የሚለው ግን ስለ ብርሃን ተፈጥሮ የተነገረውን የሚያመላክት ነው። ጽባሕ የመዓልት የመጀመሪያ ሰዓት ናትና። ብርሃንና ሌሊት የሥራ ሁሉ መጀመሪያ ናቸው።

ዳግመኛም ኮከበ ጽባሕ ሰይጣን ነው ተብሎ ይተረጐማል። ምክንያቱም ከፍጥረት አስቀድሞ በዕለተ እሑድ ተፈጥሮ በዕለተ ረቡዕ ወድቋል። ነቢዩ ኢሳይያስም፦ «በነጋ ጊዜ የወጣ ይህ የአጥቢያ ኮከብ ለምን ወደቀ?» ይላል።[36] እስከ ሰማይ ወጥቼ መንበሬን በአርያም አደርገዋለሁ፣ ከልዑል ጋርም እተካከላለሁ ብሏልና። ዳዊትም በማስከተል እንዲህ ይላል፦ «እንደ መልከ ጼዴቅ ክህነት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ እግዚአብሔር ማለ፤ አይጸጸትም።[37] ይኸውም በወንጌል ስለ ተነገረ ስለ ኅብስትና ወይን የሚያመለክት ነው። የቀናች አሪት እንዲህ ትላለች፦ «መልከ ጼዴቅም እንጀራንና የወይን ጠጅን አወጣ፣ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር።»[38]

ዳግመኛ በወንጌል፦ «ባረከ፣ እንጀራውንም ቆርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋውንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው ነገር ግን እላችኋለሁ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከ ምጠጣበት ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሬ አልጠጣውም።»[39] ጳውሎስም ስለዚህ ነገር እንዲህ ይላል፦ «በመሐላ ለሾመው ለእርሱ ግን እንደ መልከ ጼዴቅ ባለ ሹመት ተሹመህ የዘላለም ካህን አንተነህ ብሎ ማለለት ብሎ ተናገረለት፤ እንደ አሮን ክህነት ግን አላለም።»[40]

ዳግመኛ «እግዚአብሔር በቀኝህ» ወደ ሚለው ወደ መዝሙሩ ቃል እንመለስና ይኸውም የመንፈስ ቅዱስ መቀመጥ በወልድ ቀኝ እንደ ሆነ ያጠይቀናል። በመጀመሪያው መዝሙር «ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን ለእግርህ

36. ኢሳ. ፲፬፥፲፪።
37. መዝ. ፻፱፥፬።
38. ዘፍ. ፲፬፥፲፰።
39. ማቴ ፳፮፥፳፮-፳፱።
40. ዕብ. ፯፥፳፩።



www.ethiopianorthodox.org



መረገጫ እስከአደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ» ያለው የወልድ ማረፊያ በአብ ቀኝ እንደ ሆነ ያመለክታል። ከዚህም በማስከተል በዚህ መዝሙር «እግዚአብሔር በቀኝህ» ይላል። በዚህም የሥላሴ (የእግዚአብሔርን) በአካል ሦስትነት በመለኮት አንድነት መኖር አሳይቷል። በዚያ ያልተገነዘበ በዚህ አይገነዘብምን? በዚያ የካደ በዚህ ይክዳልን? ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ይላል፦ «ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ዐየሁት፣ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር፤ ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር፣ ለእያንዳንዱም ስድስት ክንፍ ነበረው፤ በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር፣ በሁለቱም ክንፍ እግሩን ይሸፍን ነበር፤ በሁለቱ ክንፍ ይበር ነበር። አንዱም ለአንዱ ..ቅዱስ፤ ቅዱስ፤ ቅዱስ፤ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምስጋናህ በምድር እና በሰማይ የሞላ»[41] ቅዱስ፤ ቅዱስ፤ ቅዱስ ማለታቸውስ አንድ ገጽ ቢሆን ኑሮ አንድ ጊዜ ብቻ ቅዱስ ማለት በበቃቸው ነበር፤ ቢበዛም ከዚያ በበለጠ ነበር ለማለት ነው። ነገር ግን ሥላሴ በገጽ ሦስት እንደ ሆኑ ለማጠየቅ ሦስት ጊዜ ቅዱስ፤ ቅዱስ፤ ቅዱስ አሉ። አንድ ጊዜ ብቻ የሰራዊት ጌታ ጸባኦት ማለታቸው በመለኮት አንድ መሆናቸውን ያመለክታሉ።

ነቢዩ ዳንኤልም እንዲህ ይላል፦ «ዙፋኖችም እስኪዘረጉ ድረስ ዐየሁ፣ በዘመናት በሸመገለውም [ዘመናትን በሚያስረጅ] ዘንድ ተቀመጠ፣ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ የራሱም ጠጉር ጥሩ ጥጥ ነበረ፣ ዙፋኑም የእሳት ነበልባል ነበረ፤ መንኰራኩሮቹም የሚነድድ እሳት ነበሩ። የእሳትም ፈሳሽ ከፊቱ ይፈልቅና ይወጣ ነበር። በእግዚአብሔር ፊት መጽሐፍ አምጥተው ከፈቱ፤ የሕይወትንም መጽሐፍ ለብቻዋ ገለጿት፤ የሰው ልጅም መጥቶ በሸመገለው [ዘመናትን በሚያስረጀው] ዘንድ ተቀመጠ።»[42] ይኸውም የአንዱ በሁለተኛው ዘንድ መቀመጥ ትርጓሜ ወልድ በአብ ዘንድ ህልው መሆኑን ያስገነዝባል። በዚህ እንኳን ልብህ የታወረ አታስተውልምን?

ዳግመኛም «እንደ ሰው ልጅ ያለ ከንፈሬን ዳበሰኝ፣ እኔም አፌን ከፍቼ አናገርኩት።» ይህንም ያለው ስለ አብ ነው። የሰውን ልጅ የሚመስል አለ እንጂ የሰው ልጅ አላለም። የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ምሳሌ ተፈጥሯልና ዳግመኛ ለሦስተኛ ጊዜ በሰው አምሳል አንድ ሰው ዳሰሰኝ፣ አጸናናኝ ይላል።

የወልድን ትስብእት ሰው መሆን ሲያመለክት መዋቲ «ሥጋን የተዋሐደ»

41. ኢሳ.፮፥፩-፬።
42. ዳን.፯፥፱-፲፫።

ይላል:: ስለ አብም ሲናገር «የእጓለእመሕያው አምሳል» ይለዋል፡ ስለ መንፈስ ቅዱስም ሲናገር «የሰው አምሳል» ይላል:: «እነሆ! አብንና ምንፈስ ቅዱስን ሰው ከመሆን አራቃቸው» ይላል:: ስለ መንፈስ ቅዱስ ግን አርአያውንና ምሳሌውን ተናገረ፤ በመጀመሪያ እንዳል ነው «ሕዝቅኤልም በወገቡ ሙዳየ ቀለም እንደ ዝናር ታጥቆ ልብሰ ተክህኖ የለበሰ ይህ ሰው መጣ» ይላል»:: «እንደ አዘዝከኝ አደረግኹ» በማለት ይመልስለታል::[43] ይኸውም ወልድ ለአባቱ ትእዛዙን መፈጸሙን ሲናገር ነው:: ልብሱ ጸደሬ [መጐናጸፊያው] ያሳደፈች ንጹሕ የሆነች ሥጋ ነች፡ ጸደሬ ልብስነቱ ንጹሕ የሐር ልብስ ማለት ነውና:: ዳግመኛ ሕዝቅኤል መጐናጸፊያ የለበሰውን ሰው እንዲህ ይለዋል:- «ከኪሩብ በታች ወዳለው ሠረገላ ግባ፤ በእጅህ የእሳቱን ፍሕም ይዘህ በሀገሩ ሁሉ በትነው፡፡» የወልድ በኪሩብ መካከል መቀመጥ በአባቱ ዘንድ ያለው ህላዌ ነው:: የእሳቱ ፍሕም መበተን በሐዋርያት ላይ እንደ እሳት [በእሳት አምሳል] የወረደውን መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ነው::

ሦስቱም በዘፈቀደ በኪሩቤል ሠረገላ ይቀመጣሉ:: ዳግመኛ እሳት የተባለው አብ ነው:: «አምላካችን የሚባላ እሳት ነው» በማለት ሙሴ እንደ ተናገረ አብ እሳት ነው::[44] ነቢዩ ኢሳይያስ «ከሱራፌል አንዱ እየበረረ ወደ እኔ መጣ፤ በእጁም ከመሠዊያው በጉጠት የወሰደው ፍሕም ነበረ፤ አፌንም ዳሰሳት» ብሎ እንደ ተናገረ::[45] ወልድም እሳት ነው:: ዳግመኛ በጽርሐ ጽዮን በእሳት አምሳል ወርዷልና መንፈስ ቅዱስም እሳት ነው::[46]

እነሆ ከኦሪት ቃልና ከነቢያት ከወንጌል ቃል ከሐዋርያት ምስክር አቀረብኩላችሁ:: ስለዚህ ትጠራጠራላችሁ፤ ትከዳላችሁ፡ ስለፊትና ስለ መልክ ያዕቆብ:- «እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ተመለከትሁት፣ ነፍሲም ዳነች::» ይላል ዳግመኛ የጸናች ኦሪት እግዚአብሔር በአሮንና በእኅቱ በማርያም እንደ ተቆጣ ስትናገር እንዲህ ትላለች:: «እነርሱም ቃሊን ስሙ፥ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ፣ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ። ባርያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም፡ እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው:: እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ::»

43. ሕዝ.፱፥፲፮፤ ሕዝ.፲፥፩::
44. ዘዳ.፬፥፳፬::
45. ኢሳ.፮፥፮::
46. የሐዋ. ፪፥፫::





ቅዱስ ዳዊትም:- «አቤቱ፥ ፊትህን እሻለሁ፡ ፊትህን ከእኔ አትሰውር::» ይላል ዳግመኛም «ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ» ይላል፡ ዳግመኛ:- «ፊትህን ከእኔ አትሰውር» ይላል:: ዳግመኛም «የጌታ ፊቱ ግን ክፉ በሚያደርጉ ላይ ነው::» ይላል:: እንዲሁም «ከፊትህ አትጣለኝ» ይላል:: ዳግመኛም «ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?» ይላል:: ጌታችንም:- «በወንጌል በሰው ፊት የሚክደኝን እኔም በሰማያዊ አባቴ ፊት እክደዋለሁ፡ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ እኔም በአባቴ ዘንድ እመሰክርለታለሁ» ይላል::[48]

ዳግመኛም «ሕፃናትን ወደ እኔ እንዲመጡ አትከልክሏቸው፤ መላእክቶቻቸው በሰማይት ያለውን የአባቴን ፊት ዘወትር ያያሉና::» ይላል:: ጳውሎስ፡ «እግዚአብሔርን በመልክ የሚመስለው በባሕርይ የሚተካከለው የለም» ይላል::[49] እንደዚሁ ዳንኤል ስለ እርሱ እንዲህ ይላል፦ የራሱ ፀጉር እንደ በረዶ ነጭ ነው::»[50] ሰሎሞንም እንዲህ ይላል:- «ራሱ ዝምዝም ወርቅ ነው» እንዳለው የተዘረፈረፈ ነው::[51] ሰንተሎ ጥቁረቱም ጥቁር ነው:: ስለ ዐይን እንናገር፤ ዳዊት የእግዚአብሔር ዐይኖች ወደ ጻድቃን ጆሮዎቹም ወደ ጩኸታቸው ናቸውና»[52] ዳግመኛ «ዐይኖቹ ወደ ድኻ ይመለከታሉ፤ ቅንድቦቹም የሰው ልጆችን ይመረምራሉ»[53] ኢሳይያስም እንዲህ ይላል «በዐይኔ ዐሳይምን በጆሮዬስ አልሰማሁምን ነገር ግን ኃጢአታችሁ በእኔና በእናንተ መሐከል ይቆማል ይላል::[54] እግዚአብሔር፡ ዳግመኛ እንዲህ ይላል፥ ቤትን ከቤት ለሚያያይዙ የራሳቸው ያልሆነውን የጓደኞቻቸውን ይቀስጡ ዘንድ እርሻን ከእርሻ ለሚያቀራርቡ ወዮላቸው፡ በአሸናፊ በእግዚአብሔር ጆሮ ይህ ነገር ተሰማ::» ዳግመኛ ዳዊት:- «አቤቱ፥ ጆሮህን ወደ እኔ ዘንበል አድርገህ ስማኝ፡ ዳግመኛም ጆሮህ የስእለቴን ቃል የሚያዳምጥ ይሁን» ይላል::[55] እነሆ! እግዚአብሔር፥ ዐይን ቅንድብ ጆሮ እንዳለው ታወቀ:: ዳግመኛም መጻሕፍት እጆች እንዳሉት ይናገራሉ:: የቀናች ኦሪት እንዲህ ትላለች

47. ዘኁ. ፲፪፥፰፤ መዝ. ፵፬፥፲፩፤ መዝ.፻፴፰፥፯::
48. ማቴ. ፲፥፴፪:: ማቴ.፲፱፥፲፬::
49. ፊል. ፪፥፮::
50. ዳን. ፯፥፱::
51. መኃ. ፭፥፲፩::
52. መዝ. ፴፫፥፲፭::
53. መዝ. ፲፥፬::
54. ኢሳ. ፩፥፲፮::
55. መዝ. ፲፯፥፮::

www.ethiopianorthodox.org

«እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ሰጠው::»[56] ዳግመኛ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎታል «እኔ ፊቴን በአለት ስንጥቅ ውስጥ አደርጋለሁ፣ በእጄም እሸፈናለሁ::»[57] ዳግመኛ በነቢዩ ኢሳይያስ ሰማይ ዙፋኔ [መኖሪያዬ] ነው፣ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ ምን ዓይነት ቤት ትሠሩልኛላችሁ ይላል እግዚአብሔር ዳግመኛ፤ ሁሉን የሠሩ እጆቼ አይደሉምን?»[58] ዳግመኛ ዳዊት:- «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የእጁን ሥራ ይናገራሉ:: «ዳግመኛ በመዝሙር:- «እጆችህ ሠሩኝ አበጃጁኝ» ተብሏል::[59]

ዳግመኛም:- «አቤቱ÷ እጅህን ከአርያም ላክ ተብሏል::[60] ዳግመኛም ክንድህ ከኃይል ጋር ጸናች÷ ቀኝ እጅህም ከፍ ከፍ አለች::»[61] ዳግመኛም «እጅህ ጠላቶችህን ሁሉ ታገኛቸዋለች» ተብሏል:: ዳግመኛ «እጅህ ተመራኛለች÷ ታኖረኛለችም::» ዳግመኛ ቀኝህም ተብሏል:: «አቤቱ÷ አንተ ረዳቴ ነህና/ ነፍሴን በእጅህ እሰጣለሁ፤ እጅህ ጠላትን አጥፍታ ሌሎችን ተከለች:: አሕዛብን አሠቃይተህ አሳደድካቸው፥ ምድራቸውን? በጦራቸው ወረሷት? ክንዳቸውም አላዳናቸውም ያለ ቀኝ ክንድህና ያለ ፊትህ:: ብርሃን» ዳግመኛ:- «አንተ ፈጠርከኝ÷ እጅህንም በላዬ አኖራት» ተብሏል::[62] አቤቱ፡ ለምን እጅህን /ቀኝህን/ ለረጅም ጊዜ ከእቅፍህ መሐል ትመልሳለህ::» ዳግመኛ:- «አንተ አስቀድመህ ምድርን መሠረትህ÷ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው::»[63] በኢሳይያስ እንዲህ ይላል:- «እጅህ ምድርን መሠረተች፡ ቀኝህም ሰማይን አጸናቻት:» ለእግዚአብሔር እጆች ክንዶች ጣቶች እንዳሉት እመኑ /ኗ/ ስለአፍንጫም የጸናች አሪት እንዲህ ትላለች:- «እግዚአብሔር የኖኅን የመሥዋዕቱን መዓዛ አሸተተ::»[64] ስለ ደረትም እንዲህ ትላለች:- «በደረቱ ተሸከማቸው÷ እግዚአብሔር::» ብቻውን መራቸው::»[65] ስለ ወገብና ጐኖችም ነቢዩ ኢሳይያስ:- «በወገቡ ጽድቅን እንደ ዝናር የሚታጠቅ እውነትን በጐኑ የተጐናጸፈ» ይላል::[66]

56. ዘፀ. ፴፩፥፲፰::
57. ዘጸ. ፴፫፥፳፪::
58. ኢሳ. ፷፮፥፩::
59. መዝ. ፲፰፥፩:: መዝ. ፻፲፰፥፸፫::
60. መዝ. ፺፫፥፯::
61. መዝ. ፹፰፥፲፫::
62. መዝ. ፻፴፰፥፰::
63. መዝ. ፻፩፥፳፭::
64. ዘፍ. ፰፥፳፩::
65. ዘጸ. ፴፪፥፲፪፡ የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ «በክንፎቹም» የሚለውን ሊቁ ደረት ብሎ ተርጉሞታል::
66. ኢሳ. ፲፩፥፭





ዳንኤልም:- «ወገቡን ከወርቅ በሚበልጥ የወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ» ይለዋል::[67] አቡቀለምሲስም፣ «ወገቡን በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ» ይለዋል::[68] ዳግመኛ «በወገቡ የነገሥታት ንጉሥ÷ የጌቶች ጌታ» የሚል ጽሑፍ አለ ይላል:: ስለ እግሮችም የጸናች ኦሪት ትናገራለች:- «እግዚአብሔርም ሙሴን፡ ከአዳራሽ ድንኳን በትርን ውሰድ የእግዚአብሔር እግሮች በሥራየው የሚቆሙበትን አለት ምታ::»[69] ዳግመኛ የጸናች ኦሪት:- «እስራኤልም ከእግሩ በታች እንደ ሰማን ማፈኪያ ድንጋይና እንደ ጸናች ሰማይ በተጐበኘች ጊዜ እግዚአብሔር የሚቆምበትን ቦታ ተመልከቱ::» ትላለች::[70] ዳዊትም:- «የጌታችን እግር ከቆመበት ቦታ እንሰግዳለን:: ይላል::[71] ዳግመኛም «ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን ለእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው» ይላል::[72] እንደገና ዘካርያስም፡ «ስማያትን ዝቅ አደረገ፡ ደመናም ከእግሩ በታች ነው::» ዘካርያስም: «የእግዚአብሔር እግሮች በደብረ ዘይት ይቆማሉ» ይላል::[73] ጌታችንም በወንጌል:- «በሰማይ አትማሉ፡ ሰማይ የእግዚአብሔር መቀመጫ ነውና፡ በምድርም አትማሉ ምድር የእግሩ መረገጫ ናትና» ብሏል::[74]

እንግዲህ ወደ እግዚአብሔር አብ አፍ እንመለስ፡ የጸናች ኦሪት፡ «ሰማያት ስሙ፡ ምድርም የአፌን ቃል አድምጪ»[75] ብሎ እግዚአብሔር እንደ ተናገረ ትመሰክራለች:: ዳግመኛ በመዝሙር:- «ከአእላፋት ወርቅና ብር ይልቅ የአፍህ ሕግ ይሻለኛል::» ይላል::[76] እንደገና ስለ ዳዊት እንዲህ ይላል፡ «ለዳዊት እንዳላጐድለው ከአፌ እንደ የወጣውን ለባሪያዬ የማልኩትን አላጐድልም» እንግዲህ የአፉ ሕግ ያደረገውን ተአምር ምክሩን አስታውሱ:: እንደገና ነቢዩ ኢሳይያስ:- «የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሯል» ይላል:: የመዝሙሩም ቃል እንዲህ ይናገራል:- «በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ጸኑ፡ ሠራዊታቸውም ሁሉ የአፉ እስትንፋስም ሁሉ[79] እንደ ገና «አቤቱ፡ የምድር ነገሥታት ሁሉ የአፍህን ቃል ሰምተዋልና::» እነሆ!

67. ዳን. ፯፥፱::
68. ራእ. ፯፥፱::
69. ዘጸ. ፲፯፥፯::
70. ኢሳ. ፷፮፥፯::
71. መዝ. [illegible]፥፯::
72. መዝ. ፻፱፥[illegible]::
73. ዘካ. ፲፬፥[illegible]
74. ማቴ. ፭፥[illegible]::
75. ኢሳ. ፩፥፪::
76. መዝ. ፻፲፰፥[illegible]::
77. መዝ. ፹፰፥[illegible]::
78. ኢሳ.፩፥፳::
79. መዝ. [illegible]፥፮::



www.ethiopianorthodox.org

ለእግዚአብሔር ፍጹም የሆነ የሰው ልጅ መልክ እንዳለው ከቅዱሳት መጻሕፍት ምስክር አቀረብንልህ::

እንግዲህ አንተ ተጠራጣሪ [መናፍቅ] ክህደትን ትተህ በሥላሴ እመን:: ለመለኮት መገለጫ ተገዛ:: በጥርጥርህ ከጸናህ ዕድል ፈንታህ ጽዋ ተር ታህ ካልተጠመቁና አረማውያን ጋር ይሆናል:: ከክርስቶስ መንጋ ጋርም አትቆጠርም:: እንግዲህ ልጁን ወልድን ወደ ድንግል ማሕፀን ለላከ ለአብ ምስጋና ይገባዋል፥ ከድንግልም ሰው ለሆነ ለወልድም ስግደት ይገባ ዋል:: ለለያት፥ ላጸናት ለጠበቃት ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይሁን::

ዳግመኛ እንዲህ እንላለን:- ለልጁ ለወልድ በዮርዳኖስ ምስክር ለሆነ ለአብ ምስጋና ይገባል:: በዮርዳኖስ ለተጠመቀ ለወልድ ስግደት ይገባል:: በርግብ አምሳል በወልድ ላይ ለተቀመጠ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል:: እንደገና እንዲህ እንላለን:- በልጁ ሞት ይቅር ላለን ለአብ ምስጋና ይገባል:: ለደኅንነታችን ለእኛ መድኃኒት ሊሆን የሞትን ጽዋ ለቀመሰ ለወልድ ስግደት ይገባል:: በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የሞትን ሥልጣን ላሻረ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል:: ወልድን በሥጋ ከሞት ላስነሣ ለአብ ምስጋና ይገባል:: በአብ ቀኝ በክብር ለተቀመጠ ለወልድ ስግደት ይገባል:: በጽርሐ ጽዮን በሐዋርያት ላይ ለወረደ ለመን ፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል:: ከዚህም ቀጥለን እንዲህ እንላለን:- በግርማ መንግሥቱ ለሚወርድ ለአብ ምስጋና ይገባል:: በጉቶችን በቀኙ፣ ፍየሉ ችን በግራው ለሚያቆም ለወልድ ስግደት ይገባል:: ለሁሉም እንደየ ሥራው ለሚከፍል ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል::

አኰቴተ ሥላሴ ላስጀመረን፥ አስጀምሮ ላስፈጸመን ለዘላለም ክብር ምስጋና ይሁን:: አሜን:: ለሰባልዮስ ከአሪት ከብለይ ኪዳን፣ ከሐዲስ ኪዳን ስለሥ ላሴ ምስክርነት የሚናገረው መልስ ተፈጸመ::

ቅናተ መንፈስ ቅዱስን የለበሳችሁ ደካማ ሆኜ መናገር ለተሳነኝ ለእኔ ጊዮርጊስ ስለ ሃይማኖቴ ጸልዩልኝ፡ ባርኩኝ::





[ምዕራፍ ፫]

# ስለ ብርሃናት የሚናገር ምንባብ

ፍጥረትን ኹሉ ለሚገዛ ለእርሱ ምስጋና ይግባውና የሙብረቅ ብል ጭታ ሲከማችና የነጐድጓድ ድምፅ ሲሰማ ከደመናዎች ሆድ የዝናብ ጠብታዎችን በሚቀዳ፡ የፀሐይ ነበልባል ሲገበገብ በብርሃን ቀን ጠን ቀቆ እስኪመላ ድረስ በጠዋት በጨረቃ ክበብ ብርሃንን በሚመላ፣ የነፋስ ኀይል ሲነፍስ በሰማይ መስኮቶች ፀሐይን በሚያወጣ፣ በፀሐይ ክበብ በነፋሳት ሠረገላ በሚያደርግ [በሚያኖር] አንድ ምስጋና በሚመ ሰገን፡ አንድ ስግደት በሚሰገድለት፣ በማይለይ በማይጨመር፣ በማይቀ ላቀል በባሕርይ በአኗኗር አንድ በሚሆን በአካል ሦስት በሚሆን ቅዱስ፥ ቅዱስ፡ ቅዱስ ተብሎ በሚመሰገን በእግዚአብሔር በሥሉስ ቅዱስ ስም እንጀምራለን::

እንግዲህ «አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ለየራሳቸው ናቸው::» የሚለውን የአቡርዮስ ዘለፋ እንጽፋለን:: አቡርዮስ ሆይ፥ አብ በግዛቱና በሥርዐቱ፥ ወልድም በግዛቱና በሥርዐቱ፡ መንፈስ ቅዱስም በግዛቱና በሥርዐቱ አለ ትል ዘንድ እንዴት ደፈርኽ? አስቀድመህ በራስህ ላይ ፍረድ፡ ሥላሴ በሥርዐት ሦስት ከሆኑ ማንኛው ፈጠረህ? ማንኛውስ ሠራህ? «አብ ጭንቅላቴን ፈጠረ፡ ወልድም እጄን ፈጠረ፡ መንፈስ ቅዱስ እግሬን አጸናው» ትላለህን? እንግዲህ በመልክህ ውስጥ ልዩነት ፈጠርኽ::

ዳግመኛ «አብ የሥጋዬ አምላክ ነው፥ ወልድም የነፍሴ አምላክ ነው፥ መንፈስ ቅዱስ የዐፅሞቼና የደም ስሮቼ አምላክ ነው» ትላለህን? እንግ ዲህ የሥላሴን (የእግዚአብሔርን) አንድነት ዝርው እንዳደረግህ ራስህን ዝርው አደረግኽ:: አብ ሰማያትን እንደ ፈጠረ፣ ወልድ ምድርን እንደ ፈጠረ መንፈስ ቅዱስ ባሕርን እንዳጸና ትናገራለህን? ይህን የምትል ከሆነ የነማርያን ትምህርት ተሳታፊ ሆንኽ::

1 አቡሊናርዮስ ከ፫፻፲፡፫፻፺ ዓ.ም በታናሽ እስያ በሎዶቅያ ተወለደ:: በምሥጢረ ሥጋዌ አምላክ ሰው በሆነ ጊዜ የተዋሐደው ሥጋን እንጂ ነፍስን አይደለም:: ስለነፍስ ፈንታ መለኮት ለሥጋ ነፍስ ሆነው ሁለቱ ማለት ነፍስና መለኮት ለመዋሐድ አይችሉምና በሌላ አነጋገር «ህየንተ ነፍስ ወልቡና ኮነ መለኮቱ» ይላል ይህ ትምህርቱ በ፫፻፸፪ ዓ.ም በእስክንድርያ ሲኖዶስ ተወግዟል:: ሁለተኛ በአንጾኪያ ሲኖዶስ በ፫፻፸፱ እና በመጨረሻ በቁስጥንጥንያ ተወግዟል:: አባ ጎርጎርዮስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ ፻፳፰



www.ethiopianorthodox.org

የአረማውያን ነገሥታት የእግዚአብሔርን ምርጥ ጊዮርጊስን፡- «አጵሎን ሰማያትን እንደ ፈጠረ፣ ኤራቅሊስ ምድርን እንደ ፈጠረ ስቀመደርሽና አቴና ፀሐይን እንደሠሩ እንደ ፈጠሩ፣ አርቴሞስና ሰፎ ባሕርን እንደ አጸኑ ዕወቅ ጊዮርጊስ ሆይ! ይሉታል።

እንግዲህ የዝንጉአን ትምህርት ተከታይ ኾነሃል፤ ምክንያቱም የሥላሴን (የእግዚአብሔርን) አንድነት እንደ አሕዛብ አማልክት ከፍለሃልና። ሰብልዮስ ባለማወቅ በሥላሴ ላይ ጨመረ፤ አንተ ደግሞ ባለማስተዋል ሥላሴን ለያየህ [ዝርው አደረግኸ]፤ ሰብልዮስ ከአረማውያን ሥርዐት ጋር ተባበረ፤ አንተ ደግሞ አምላኮቻቸው ብዙ አጋንቶቻቸው ብዙ ከሆኑ ከጣዖት አምላኪዎች ሥርዐት ጋር ተባበርክ።

የጸናች አሪት «እግዚአብሔር ሰውን በመልካችንና በምሳሌያችን እን ፍጠር አለ»፡- ብላ በተናገረች ጊዜ ሰብልዮስን ዘለፈችው፤[2] አንተንም እንደዚህ ብላ በተናገረች ጊዜ ዘለፈችህ፡ እስራኤል ሆይ ስማ፡ አምላክህ እግዚአብሔር አንድ ነው። ሁለት ወይም ሦስት አይደለም።»[3] ይህን ሲል መለኮትን ሦስትነትን ያስቀር ዘንድ አይደለም። የሥላሴን አንድነት ያዋሕድ ዘንድ ነው እንጂ። ሰብልዮስን እንደበቱን አስያዝነው። በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ በየገጹ ባልን ጊዜ በአኗኗሩ አንድ አምላክ ነው ባልን ጊዜ አፍህን አሰርነው። የመለኮትን ክብር እንዳያጎድል ሰብልያኖስን ዘለፍነው። አንተንም ሥላሴን እንዳትነጣጥል ከለከልንህ።

አቡርዮስ ሆይ! የማይከፈለውን እንዴት ትከፍለዋለህ? የማይለያየውንስ እንዴት ትለያየዋለህ? የማይበተነውን እንዴት ትበትነዋለህ? አቡርዮስ ሆይ! የማይለያየውን እንዴት ትለያየዋለህ? የማይርቀውን ለምን ታርቃለህ?

አቡርዮስ ሆይ! «አንዱ ከአንዱ እንዴት ልዩነት አለው፡ ሁለቱ ከሦስቱ ይለያል» እንዴት ትላለህ? ራስህን በመለኮት ሰይፍ ስነጠቅኸ፡ አንደበትህንም በወንጌል ቢላዋ ቆረጥኸ። ስለ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት፣ ውሃ እና ነፋስ ናቸው ትላለህን? እሳት ብለህ ከሰየምካቸው የመሃይምናንን? የኃጢአት እሾኸ የሚያቃጥል አንዱ እሳተ ሕይወት ነው። በነፋስም ብትመስላቸው ህልውናቸው የማይዳሰስ አንድ መንፈስ ናቸው።

በባሕር ውሃ ብትመስላቸው በስሙ የተጠመቅንበት አንድ የምሕረት

2. ዘፍ. ፩፥፳፮።
3. ዘዳ. ፮፥፬።



www.ethiopianorthodox.org



ባሕር ነው። በሦስት ጠባዮት በወሰናቸው በሥላሴ ሥርዐት ላይ አንዱ የሚቀዘቅዝ፡ አንዱ የሚያቃጥል፣ አንዱ የሚረጥብ ብለህ አታስብ። አብ ዘወትር የሚያበራ ፀሐይ እንደ ሆነ ወልድም ዘወትር በቅዱሳን ላይ የሚያበራ ፀሐይ ነው፡ ወልድ ዘወትር በቅዱሳን ላይ የሚያበራ ፀሐይ እንደ ሆነ መንፈስ ቅዱስም ቤተ ክርስቲያንን የሚያስጌጣት ፀሐይ ነው። አብ በኪሩቤል ሠረገላ እንደሚቀመጥ ወልድም በክብር በአርባዕቱ እንስሳት ይቀመጣል፡ ወልድ በአርባዕቱ እንስሳ እንደ ሚቀመጥ መንፈስ ቅዱስም በሦስትነት በክበር ዙፋኑ ይቀመጣል።

አብ አዳምን እንደ ፈጠረ፡ ወልድም በአርያውና በአምሳሉ ፈጥሮታል፤ ወልድ አዳምን በአርያውና በአምሳሉ እንደ ፈጠረው መንፈስ ቅዱስም በራሱ መልክ ፈጥሮታል።

አብ በነቢያት አንደበት «ከንጋት ኮከብ መውጣት አስቀድሞ ወለድኩህ» ብሎ ተናገረ።[4] ዳግመኛ በኢሳይያስ አፍ «እነሆ፡ ወዳጄ ያስተውላል፡ ከፍ ይላል፡ ይከብራል፡ አሕዛብም ስለ እርሱ ያደንቃሉ» ይላል። ዳግመኛም እንዲህ ይላል፡- «እኔ አባት እሆነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።»[5] በዖዝያን አንደበት «ልጄን ከግብጽ ጠራሁት» ይላል።[6] ይህን ምስክርነት ነው አብ ስለ ልጁ በነቢያት ያናገረው። ዳግመኛ ወልድም በነቢያት አፍ ስለ አባቱ እግዚአብሔር፡- «ልጄ ነህ አለኝ፡ ዛሬም ወለድኩህ፡ ከእኔ ለምን፡ አሕዛብን ለርስትህ እሰጥሃለሁ፡ ግዛትህ እስከ ዓለም ዳርቻ ነው» ብሎ ተናገረ።

ስለ ራሱ ሕማማት ሲናገር እንዲህ ይላል፡- «በልብሶቼ ላይ ዕጣ ተጣጣሉ፡ ልብሶቼንም ተካፈሉ።» ዳግመኛ፡- «እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ፡ አጥንቶቼን ቆጠሩ።» ዳግመኛ፡- «በመብሌ ውስጥ ሐሞት ጨመሩ፡ መጻጻ ሐሞት አጠጡኝ።»[7] በኢሳይያስ አፍ፡- «ጀርባዬን ለግርፊያ፡ ፊቴን ለጥፊ፡ ፊቴንም ምራቅን ከማፈር አልመለስኩም።» ይህ የወልድ የቃሉ ምስክርነት ነው። ይኸውም ስለ አባቱና ስለ እርሱ በነቢያት አፍ የተነገረ ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስም እንዲህ እያለ ይናገራል፡- «የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድኾች ወንጌልን

4. መዝ. ፻፱፥፫።
5. ፪ኛ ሳሙ. ፯፥፲፬፤ ዕብ. ፩፥፭።
6. ሆሴ. ፲፩፥፩፤ ማቴ. ፪፥፲፭።
7. [illegible]

እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛል፣ ለታሰሩትም መፈታትን።»[8] ይህ የትንቢት ቃል የተነገረው፥ በርግብ አምሳል በእርሱ ላይ ስለ ወረደው መንፈስ ቅዱስ ነው። «ለድኾች እሰብክ ዘንድ ላከኝ» ማለቱ ለአሕዛብ መምህር እሆን ዘንድ ማለቱ ነው። ምክንያቱም በጥንት ዘመን አሕዛብ ከሕገ ኦሪት፥ ከቃለ እግዚአብሔር ርቀው ነዳያን ስለነበሩ ነው። «ለታሰሩ ትም መፈታትን እሰብክ ዘንድ» ማለቱ ደግሞ ከአምልኮተ እግዚአብሔር ወደ አምልኮተ ጣዖት የተማረኩትን ነው። ዳግመኛ ስለ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ። ድንቆችን በላይ በሰማይ ምልክቶችንም በታች በምድር።»[9] ይህ የኢዩኤል ቃለ ትንቢት፣ መንፈስ ቅዱስ በጽርሐ ጽዮን በሐዋርያት፣ የጌታ እናት በተገኘችበትና ጌታን በገንዘባቸው ያገለግሉ በነበሩ ቅዱሳት አንስት ላይ ስለ ወረደው ስለ መንፈስ ቅዱስ የተነገረ ነው። መንፈስ ቅዱስ በነቢያት አፍ አናገረ። «የነቢያትን ራእይ አበዛሁ በነቢያት እጅም ተመሰልኩ» ይላል።

ዳግመኛ፦ «ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ በደረታቸውም እጽፋለሁ፤ እነሱ ሕዝቤ ይሆኑኛል፥ እኔም አምላካቸው እሆናቸዋለሁ» ይላል።[10] ዳግመኛ በኢሳይያስ አፍ እንዲህ ይላል፦ «ከማን ዘንድ ዐርፋለሁ? ከየዋህና ከትሁት በስተቀር አላዋቂም ከቃሌ የተነሣ የሚንቀጠቀጥ አይደለምን?» ስለ ራሱ ይህን ተናገረ።[11] ስለ አብም እንዲህ ይላል፦ እግዚአብሔርን ፈልጉት፥ ቀርቦም ሳለ ጥሩት፤ ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛ ሐሳቡን ይተው።» ዳግመኛም እንዲህ ይላል፦ «እግዚአብሔርን የሚፈሩት ጭንቀት የለባቸውም፤ ቅዱሳኑ ሁላችሁም እግዚአብሔርን ፍሩ።»[12] ስለ ወልድም እንዲህ ይላል፦ «በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ በሩክ ነው።»[13] ዳግመኛም ነቢዩ ዕንባቆም እንዲህ ይላል»፦ «እግዚአብሔር ከቴማን፣ ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ይመጣል። ክብሩ ሰማያትን ከድኖአል፥ ምስጋናውም ምድርን ሞል ቶአል።»[14] ዳግመኛም እንዲህ ይላል፦ «በምድር ላይ እንደሚንጠባጠብ ነጠብጣብ እንደ ጠል ወደ ፀምር ውስጥ ይወርዳል።» ዳግመኛ በኢሳይያስ አፍ እንዲህ

8. ኢሳ. ፷፩፡፩፤ ሉቃ. ፬፡፲፯-፲፱።
9. ኢዩ. ፪፡፳፰፤ የሐዋ. ፪፡፲፯-፳፩።
10. ኤር. ፴፩፡፴፫።
11. ኢሳ. ፶፯፡፲፩።
12. መዝ. ፹፱፡፯።
13. መዝ. ፻፲፯፡፳፮፤ ማቴ. ፳፩፡፱።
14. ዕንባ. ፫፡፫።





ይላል፦ «እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፤ የበግ ጠቦትም በሸላቾቹ ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁ አፉን አልከፈተም፤ በመከራ በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልድ ማን አስተዋለ?»[15] ስለ ትንሣኤውም እንዲህ ይላል፦ «እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደ ሚነቃ ተነሣ፤ የወይን ስካር እንደ ተወው እንደ ኃያልም ሰው።»[16] ስለ ዕርገቱም እንዲህ ይላል፦ «ምድርን የሚገዛት ክፍ አለ።»[17] እነሆ ሦስትነትን በየህልውናው እየሳየ የምስጢርን ጉዳና በነቢያቱ እንደበት አናገረ።

«አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ለየቅል ናቸው» የምትል አቡርዮስ ሆይ፥ ታፍራለህ፤ ደንቆሮው! [የማታስተውለው] እስኪ ጆሮ ካለህ ጌታችን በወንጌል፦ «እኔን ያየ አብን አየ» ያለውን ስማ።[18] እነሆ አንድ ናቸው። ዳግመኛም፦ «እኔና አብ አንድ ነን» ይላል።[19] እንግዲህ በህልውና አንድ ናቸው።

ዳግመኛ እነሆ ስለ አብ አንድ ሕይወት፦ «አብ ሕያው እንደ ሆነ እኔም ሕያው ነኝ» ይላል።[20] እንደ ገና እንዲህ ይላል፦ «አብ በልጁ ይመ ሰገን ዘንድ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ያደርግላችኋል፤ በአባቴ ስም የምትለምኑትን [ብትለምኑኝ] አደርግላችኋለሁ።» እነሆ አንድ ፈቃድ ናቸው። እንደገና እንዲህ ይላል፦ «እኔ አባታችሁ ነኝ፥ አባቴም አባታችሁ ነው።» ስለ መንፈስ ቅዱስም፦ «ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር መግባት አይቻለውም።» ይላል።[21] ስለዚህ በአ ንድነት ተገኝተዋል። እንደገና አብ ሙታንን እንደሚያሥነሳቸው ሕይ ወትም እንደሚሰጣቸው ወልድም የወደደውን ያድነዋል። እነሆ አንድ ሥልጣን ናቸው። እንደገና፦ «የአባቴ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው» ይላል። አባቱንም፦ «የእኔ የሆነው ያንተ ነው፤ የአንተም የሆነው የእኔ ነው።» ይለዋል።[22] እነሆ! አንድ ጌትነት አላቸው። ዳግመኛ «አብ እንደሚ ያውቀኝ እኔም አብን አውቀዋለሁ» ይላል።[23] እነሆ! አንድ ዕውቀት አላቸው። እንደ ገናም የላከኝ አብ ካልሳበው በስተቀር ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይቻለውም» ይላል። እነሆ አንድ መጠሪያ [ጥሪ] አላቸው።

15. ኢሳ. ፶፫፡፯።
16. መዝ. ፸፯፡፷፭።
17. መዝ. ፶፱፡፰።
18. ዮሐ. ፲፬፡፱።
19. ዮሐ. ፲፡፴።
20. ዮሐ. ፭፡፳፮።
21. ዮሐ. ፫፡፫-፬።
22. ዮሐ. ፲፯፡፲።
23. ዮሐ. ፲፡፲፭።



www.ethiopianorthodox.org

አይሁድንም እንዲህ ይላቸዋል፡- «እኔን ብታውቁ ኑሮ አባቴን ባወቃችሁ ነበር፡ እኔንም አባቴንም አታውቁም።» እነሆ! አንድ መታወቅ አላቸው። እንደ ገናም እንዲህ ይላል፡- «እኔ የላኩትን የሚቀበል እኔን ተቀበለ፡ እኔን የተቀበለ አባቴን ተቀበለ።»[24] እነሆ! አንድ መቀበል [መታመን] አላቸው። እንደ ገና እንዲህ ይላል። «የሰው ልጅ ከፍ ባለ ጊዜ ያን ጊዜ እኔ እንደ ሆንኩ፣ የምናገረው ከእኔ እንዳልሆነ አብ ያስተማረኝን እንደምናገር ታውቃላችሁ። የላከኝ አብ ከእኔ ጋር አለ። ፈቃዱን አደርጋለሁና ለብቻዬ አይተወኝም።» እነሆ በትምህርት አንድ ናቸው።

ዮሐንስም ለደቀ መዛሙርቱ፡- «ያን ጊዜ አብ በእኔ ህልው እንደ ሆነ፡ (እንዳለ-እንዲኖር) እኔም በአብ ህልው እንደ ሆንኩ፣ እናንተም በእኔ ህልውና እንዳያጸናችሁ እኔም በእናንተ ህልው እንደ ሆንኩ ታውቃላችሁ» ይላቸዋል። እነሆ! አንድ ኅብረት ናቸው።

ዮሐንስ ስለ ደቀ መዛሙርቱ ሲለምን እንዲህ ብሏል፡ «አባት ሆይ! በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፣ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ እንዲሆኑ ዓለም አንተ እንደ ላከኸኝ እንዲያምን።»[25] እንዳለ እነሆ! በተዋሕዶ አንድ ናቸው። ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ ይላቸዋል፡- «እናንተን የሰማ እኔን ሰምቷል፡ እኔን የሰማ የላከኝን ሰምቷል።» ስለዚህ አንድ ዕውቀት አላቸው። እንግዲህ ስለ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ተዋሕዶ ፈጸምን።

ስለ መንፈስ ቅዱስ እንናገራለን። ወልደ እግዚአብሔር የራሱን ህልውና ከአባቱ ጋር አስናስሎ እንዳያየዘ ሁሉ ቅዱስ ጳውሎስም እንደ እርሱ የመንፈስ ቅዱስን ህልውና ከአብና ከወልድ ጋር አስናስሎ አየይ ዟል። ጳውሎስ በመልእክቱ «በንጹ ሰው ልብ ያለውን የሚያውቅ የለም፡ እኛ ግን የተሰወረውን የሚገልጽ፡ የተደበቀውን የሚመረምር የእግዚአብሔር ልብ አለን።»[26] የእግዚአብሔር ልብ ማለት የተሰወረውን የሚያውቅ ማለት ነው። በወልድ የሌለ ኀሊና በአብ የለም፡ በመንፈስ ቅዱስ የሌለ ኀሊና በወልድ የለም፡ ምክንያቱም በአንድ ልብ ያስባሉ፡ በመለኮትም አንድ ናቸው።

ዮሐንስ ቅዱስ ጳውሎስ፡- «መንፈስ ቅዱስ ካላደረበት በስተቀር ኢየሱስ

24 ማቴ. ፲፥፵።
25 ዮሐ. ፲፯፥፳፩። ዮሐ. ፲፫፥፳።
26. ፩ቆሮ. ፪፥፲፩፤ ፩ቆሮ. ፲፪፥፫።





ክርስቶስ ጌታ ነው ብሎ መናገር የሚችል የለም» ይላል። «ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሰይጣን የተወገዘ ነው» የሚልም የለም ይላል።

ጌታችን በወንጌል፡ «የምነግራችሁ ብዙ ነገር አለኝ፡ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም፡ ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፡ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና የሚመጣውን ይነግራችኋል። እርሱ ያከብረኛል። ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል።»[27]

ሰነፉ ሆይ! ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል ባለጊዜ የወልድ የትምህርቱ ቃል የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ቃል እንደ ሆነ አስተውል። ስለ አባቱ ግን «በአባቴ ዘንድ የሰማሁትን እናገራለሁ» ይላል። ስለ መንፈስ ቅዱስ «ለእኔ ካለኝ ወስዶ ሁሉን ይነግራችኋል።» ይላል። እነሆ የሥላሴ አንድነት በአንዲት ሥርዓት የጸና ነው። በሐሳብና በንግግር መለየት የለም። በገጽ እና በክብር መለዋወጥ የለም።

ዘንጊው ሆይ! በመንፈስ ቅዱስ የሌለ ክብር በወልድ እንደሌለ፡ በወልድ የሌለ ክብር በአብ እንደሌለ አስተውል። የዘንጊዎች የሃይማኖታቸው መታሰቢያ በእግዚአብሔር ዘንድ የተሸነቆረ ነው። በአንደበታቸው የተመላው ስድብ ጥምቀታቸውን [ልጅነታቸውን] ያረከሰ ነው። የትምህርታቸው ድምፅ ቤተ ክርስቲያንን ያውካታል፡ የእግራቸው እንቅስቃሴም ምድርን ያረክሳል።

ሰብልዮስ በመለኮት ባሕርይ ላይ ጨመረ። አቡርዮስ የሥላሴን አንድነት በተነ። ሁለቱም የገሃነም ልጆች ሆኑ። ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ቦታ የተሰጡ ናቸው። በሃይማኖታቸው የሚያምነውን ወደ ቤትህ አታስገባ፡ ፈጽሞ ሰላም አትበለው። ገደል ውስጥ እየጣደፈህ ወደ ዐዘቅት ውስጥ እንዳያጥምህ ከጠላትህ ጋር አብረህ አትቀመጥ። እንዳ ያውክህ ከተከሉ ጋር አትዛመድ፡ አትወዳጅ እንዳይተናኩልህ እባብን ከወገብህ አትታጠቅ፡ በመርዙ እንዳያሳምምህ፡ በአንገትህ ውስጥ እፉኝትን አታንግተው፡ በጅራቱ እንዳይነድፍህ፡ ጊንጥን ከብብትህ አትጨምረው፡ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጥ፡ ዕንቁህንም በእሪያዎች ፊት አትጣል፡ ጨለማውን ተጸልሎ ወጥመዱን እንዳይጥልብህ ንጹሕ ልብስ ካለህ ወደ ተጻለ ለበት አትቅረብ።

በርኩሰቱ እንዲያደምነው የከበረ ዕንቁ ከገዛህ በመሬትውስጥ

27. ዮሐ. ፲፮፥፲፪።



www.ethiopianorthodox.org

አታስቀምጠው:: በአሪት እንደ ተጻፈው የኲነኔ ፍርድ በእነርሱ ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥቷልና ከከሐድያን ስለ መራቅ ይህን ምዕዳን መሰልንልህ::

አባቱ ግብፃዊ የሆነ የእስራኤላዊት ልጅ ተወለደ:: የዚህችን እስራኤላዊት ልጅ ራሱን ወልደ እግዚአብሔር ብሎ ሰየመ:: የልጁ እናት ከነገደ ዳን የሆነች የዳቤር ልጅ ሰሎሚት ትሰኛለች:: የተረገመውን ልጁንም ከሙሴ ዘንድ አቀረቡት፤ ሙሴም በእግዚአብሔር ትእዛዝ እስከ ሚቀጣው ድረስ ከእስር ቤት አኖረው:: እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው:- «የተረገመውን ልጅ ከከተማ ውጭ አውጣው፥ የሰሙትም የከተማው ሕዝብ ሁሉም ወጥተው እጃቸውን ያሳርፉበት፥ በድንጋይም ይውገሩት»[28] አለው::

ሙሴም የተሰደበውን ልጅ ወደ አደባባይ አውጥተው፣ በድንጋይ ወግረው መግደላቸው በያዕቆብ አምላክ ትእዛዝ እንደ ሆነ ለእስራኤል ልጆች ነገራቸው:: ጌታችንም በወንጌል እንዲህ ሲል ተናግሯል:- «ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር:: በብሉይም በሐዲስም ሃይማኖትን በሚተላለፉ ሰዎች ላይ የሞት ትእዛዝ ተላልፏል [ወጥቷል]:: በነቢይስ ስለ ቅናተ ሃይማኖት [በሃይማኖት ስለ መቅናት] ሲናገር እንዲህ ይላል:- «ማረሻችሁን ሰይፍ ማጭዶቻችሁንም ጦር ለማድረግ ቀጥቅጡ፥ ደካማውም እኔ ብርቱ ነኝ» ይላል::[29]

ዳዊትም እንዲህ ይላል:- «ጠላቶችህን ፍጹም መጥላትን ጠላኋቸው፥ ስለ ጠላቶችህም ማሰንኩ፤ ጠላት ሆነውኛልና ፈጽሞ ጠላኋቸው::»[30] የሐዋርያት አለቃ ጴጥሮስ ቀሌምንጦስን እንዲህ ብሎ ስለ ቀናች ሃይማኖት ገልጿል:: «በክርስቶስ በማያምኑ፥ ሃይማኖትን በሚተላለፉ ከሐዲያን ላይ ሰይፍህን ምዘዝ፤ ተጋደል::»

ጳግመኛ ሰሎሞን እንዲህ ይላል:- «የንጉሥ መንበሩ የጸዳ [ንጹሕ] ይሆን ዘንድ በንጉሡ ፊት ዝንጉዎችን አርቅ::»[31] ከሐዋርያት የተቀበሉትን አምልኮተ እግዚአብሔርን ረስተው ሃይማኖትን ከሚተላለፉ

28. ማቴ. ፲፰፥፲፯::
29. ኢሳ. ፪፥፬::
30. መዝ. ፻፴፰፥፳፩::
31. ምሳ. ፳፭፥፭::





ወዲህ ዝንጉ ማነው? ንጉሥም ቢሆን በሃይማኖት ጉዳይ መታገሥ የለበትም፡ ምክንያቱም ቆስጠንጢኖስ በአርዮስ ስደት ምክንያት ፫፻፲፰ ሊቃውንት በተሰበሰቡበት በኒቂያ ጉባኤ ከእነርሱ አንድም ሳያውቁት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘበት ተመስግኗልና ለራሱም በየትውልዱ የሚታወስበትን መታሰቢያም አኑሯል:: በዘመኑ የሃይማኖት ሥርዓት ተመሥርቷል:: የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀልም ተገልጧል:: እንደዚሁም የከሐድያን ማዕበልና የመናፍቃን ትንሣኤን የሚተላለፉ ሞገድም ጸንቷል፡ የቤተ ክርስቲያን ምሰሶዋ ጸንቶ ቆሟል::

በኢየሱስ ክርስቶስ እስትንፋስ የተመረጡ የበጐች እረኞች ሊቃነ ጳጳሳት ተደሰቱ:: የቆስጠንጢኖስ መንግሥት በሥርዐተ ማኅበር እንደ ተመሰገነች በታስሮስና ዲድሮስ የተጀመረ የንስጥሮስን ሃይማኖት የወደደ የሮሜ ንጉሥ የመርቅያን መንግሥት የተዘለፈች ሆናለችና [ተዘለፈች]:: እግዚአብሔር የንስጥሮስን ሞቱን በማፋጠን ሃይማኖቱ እንዳትጸና ከልክሏል::

ከዚህም በኋላ ወደ ልዩን ሃይማኖት ተመልሶ ለዚህችም ሃይማኖት ፯፻፴፮ ኤጲስ ቆጶሳትን ከኒቅያ ማኅበር የተለየች ትሆን ዘንድ በልቡ አስቦ ሠይሚል [ሾሚል] ተከሳዎች በዙ፡ ሃይማኖትም ጐደለ፥ ተከሳዎች በዝተው የምስጢር በጐች [ምእመናን] ተበተኑ::

የሐሰት ሰባክያን በጉተቱት ከጉባኤያቸው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ራቀ:: ስለ ቀናች ሃይማኖት ጥርሱ ከተሰበረውና ጽሕሙን ከተነጨው ከዲዮስቆሮስ ዘንድ ቀረች:: እንግዲህ መርቅያን ስለ ተጠላች እምነቱና ስለ ከፋች ሃይማኖቱ በምእመናን ዘንድ የተነቀፈ ነው:: የዝንጉዓን መታሰቢያ ከዘለፋና ከቁጣ ጋር ይኖራል:: እነሆ! የቆስጠንጢኖስ የሃይማኖቱ መታሰቢያ ከምስጋና እና ክብር ጋር ለዘላለም ይኖራል:: ምክንያቱም የጻድቅ መታሰቢያ ከፍጹም ምስጋና ክብር ጋር ለዘላለም ይኖራል:: ስለዚህ በኒቂያ የተሰበሰቡ አባቶች የጸናች ሃይማኖትን ለክርስቲያን ሁሉ አጽንተው መሠረቱ:: በኑበረትም ሆነው ግፋም ከሆነ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ቤተ ክርስቲያንን እናጸና ዘንድ ሥልጣን አገኘን አሉ:: ይህን የሚተላለፉ ከሰይጣን ጋር ይተባበራሉ:: ለዘላለም ይሁን ይደረግ:: አሜን::



www.ethiopianorthodox.org

የሰይጣን አገልጋይ አቡርዮስን ለመዝለፍ የተጻፈችው ይህች ድርሳን ተፈጸመች። ስለ ጥምቀቴ የሐዋርያት ልጅ በቅብዐ በለሳን[32] (ሜሮን) የታተምኩ፥ በሃይማኖት ሃይል የታጠቅኩ፥ ክቡር ክርስቲያን ነኝ፡ እምነቴም ከናዝ ራውያን ወገን ሲሆን ስለ ኃጢአቴ የተናቅሁ ምስኪን እኔ ጊዮርጊስ አጻፍኳት።

32. ሽቱ፤ የሽቱ ዕንጨት ስም፣ በይሁዳና በገሊላ ይልቁንም በኢያሪኮ፥ የሚበቅል፡ ከዕፀው ዕጣን አንዱ መገርመሪያው፣ ሽታው ከሽቱ ዕንጨት ኹሉ የሚበልጥ ጳጳሳት ቅብዐ ቅዱስ ሜሮን የሚያደርጉት፤ ሊቃነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ ፪፻፸፬።/





# [ምዕራፍ ፬]

## የኖላዊ ምንባብ

ዓለም ሳይፈጠር ሦስት ሲሆን አንድ የሆነ፥ ያለ መቀሳቀል በመለኮት አንድ የሆነ ፍጹም ያልተፈጠረ፡ መለየየት የሌለበት፥ ያለምሰሶ ሰማይን የፈጠረ፡ የረጋች መሬትን በባሕር ላይ ያስቀመጠ፥ የፀሐይንና የጨረቃን ዑደት እንደ መስታዮት የቀመረ፥ በሰማይ ላይ ለፀሐይና ጨረቃ መሽከሚያዎች የነፋሳት ሠረገላን የሠራ፣ በሰማይ ላይ መመላለሻን የሠራ [የፈጠረ] ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ መላእክት ያዘዙዋቸው ከዋክብትን ይመራሉ፡ ለብርሃናት ጌታ ክብር ለዘላለሙ ይግባው። አሜን።

እንግዲህ አርዮስ[1] «በዲቁናው» ክሕደትን አብቅሎ በ«ቅስናው» የነጢአት እሾክን አፈራ። የአርዮስን ዘለፋውን እንናገር። አርዮስ የሰይጣን ሠረገላው የኢጋንንትም ማኅበርተኞቻቸው ነው። አርዮስ ሃይማኖቱ የከፋ ልቡ የጨለመ፡ ከነሊናው ማስተዋል የጠፋበት ነው። አርዮስ በማዞት መርዝ እንደበቱ [ከንፈሮቹ] የታመሙ፣ የቆሰሉና የረከሱ ናቸው። እባቡን፡- ይህን ስላደረግኽ ከእንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ፡ በሆድህም ትሔዳለህ፥ አፈርንም በሕይወት ዘመንህ ሁሉ ትበላለህ። በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነት አደርጋለሁ፡ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፡ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።» ብሎ እባብን በረገመ በሰራዊት ጌታ በእግዚአብሔር አፍ አርዮስ የተረገመ ነው።[2]

የአርዮስ ልጆች ከየዋሃን ወገን ካገኙ ወደ ክሕደታቸው [ግዛታቸው] ይመልሱ ዘንድ የየዋሃንን ተረከዝ [እግር] ይጠባበቃሉ። እኛም ከመምህሮቻችን ወገን ካገኘን አንገታቸውን ቆርጠን ምላሳቸውን እንቀርጥፋቸው። ዘንድ እንጠብቃለን። አርዮስ ከመላእክት ወገን ተለይቶ ከወደቀ ዲያብሎስ ፈጽሞ አይለይም። አርዮስ ሔዋንን ካሳታት እባብ ፈጽሞ አይለይም።

1. አርዮስ በ፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በ፫፻፴፮ ዓ.ም ገደማ በአፍሪካ ሰሜን ክፍል በምትገኘው በሊብያ የተወለደ ሲሆን በዘር ግን ግሪካዊ ሳይሆን አይቀርም። የኑፋቄ ትምህርቱን በአንፆኪያ ትርጓሜ ት/ቤት ሆኖ ከሉቅያኖስ ያገኘው ሲሆን በእስክንድርያ በዲቁና ሲያገለግል «ወልድ ፍጡር ነው» የሚለው የኑፋቄ ሐሳቡ በጊዜው የእስክንድርያ ሊቀጳጳስ ለነበረው ተፈጻሚነት ሰማዕት ጴጥሮስ ተገልጦለታል። አባ ጎርጎርዮስ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ ፹፰

2. ዘፍ. ፫፥፲፬።



www.ethiopianorthodox.org

**አርዮስ** ከኢየሱስ ክርስቶስ አንደበት በወጣ የእሳት ሰይፍ የተቆረጠ ነው። መራራ ሥር አርዮስ በእስክንድርያ በቅሎ ሃይማኖታቸው በጸናች በ፫፻ ፲፰ ሊቃውንት ተነቅሏል።

ጥንተ ነገሩ እንደምነው ቢሉ፥ አብያተ ክርስቲያናት ተዘግተው አብያተ ጣዖታት ይከፈቱ ዘንድ ባዘዘው በከሐዲው ዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት ይህ ሰው ለጣዖት ሠውቶ ለአጋንንት ተገዝቷል። በኤጲስ ቆጶሳት ላይ ስደትን አዝዞ በየዋሃን ምእመናን ላይ ግፍ አምጥቷል። ወደ ከፋች ሃይማኖቱ የተመለሱትም ለአጋንንት ሠውተዋል። መከራውን ፈርተው የተሰደዱት በየተራራውና በየዋሻው ውስጥ ተደብቀዋል። በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተረፉ ጥቂቶቹ ሃይማኖታቸውን ክደው እንደ ፈቀዱት ተናገሩ፥ እንዳሰቡትም አስተማሩ።

ከዚህ በኋላ ገና «ዲያቆን» ሳለ የአርዮስ የክሕደት ድምፅ ተሰማ። «ክርስቶስ ፍጡር ነው፤ የዓለም መድኃኒት የተፈጠረ ነው» አለ። የስማዕታት መጨረሻ ጴጥሮስ ይህን በሰማ ጊዜ አውግዞ ከቤተ ክርስቲያን ለይቶ አባርሮታል። አርዮስ ወደ እለስክንድሮስና አኪላስ ዘንድ ሔዶ ሊቀ ጳጳሳት ጴጥሮስ ከግዝቱ እንዲፈታው ያማልዱት ዘንድ ለመናቸው። ጴጥሮስም አላቸው፦ «ከክሕደቱ ወደ ጸናች ሃይማኖት የሚመለስ መስሏቸው ስለ አርዮስ ልመናቸውን አጽንተው ሊቀ ጳጳሳት ጴጥሮስን አብዝተው በዘበዘቡት በማለዱት ጊዜ ሕዝቡን እንዲረቱና [እንዲሔዱ] እለእስክንድሮስና አኪላስ እንዲቆዩ አዘዘ። እለእስክንድሮስና አኪላስን እንዲህ አላቸው። በሀች ሌሊት ጌታዬ ኢየሰሱ ክርስቶስ በብሩህ ሕፃን አምሳል ከነዘን የተነጣ ፊቱን ቋጥሮ የተቀደደ ልብስ ለብሶ የተቀደደውን ልብስ በሁለት እጁ ይዞ ታየኝ።

እኔም ጌታዬ ሆይ! ልብስህን ማን ቀደደብህ? አልኩት፡ ልብሴን የቀደደው አርዮስ ነው፤ እንዳትቀበለው ተጠንቀቅ አለኝ። በጠዋት ስለ እርሱ የሚለምኑህ አሉ። ከአባቴ መለኮት የከፈለኝን አርዮስን የአባቴ መለኮት በመንግሥቱ አይቀበለውም። ከዚህ በኋላ ሁለቱ ቀሳውስት ሊቀ ጳጳሳት ጴጥሮስን መለመናቸውን ተዉ። ከዚህ በኋላ የመርሞትቴን ምርኮ ስለተቤዣቸው ገላት የተባሉ ጠርባናሳትና ሚትራይቱይ ራሱን ይቆርጡት ዘንድ በከሐዲው በዲዮቅልጥያኖስ ትእዛዝ ተላኩ። ብፁዕ ጴጥሮስ ምስክርነቱን አጽንቶ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በሰይፍ ተሰይፎ ከዚህ ዓለም ዐረፈ።





ከእርሱም በኋላ አኪላስ ተሾመ። አርዮስ ከአኪላስ ዘንድ ሔደ። ሊቀ ጳጳሳት ጴጥሮስ የገዘተውን ግዝት አንሥቶ ከግዝቱ እንዲፈታው ለመነው። እርሱም ከግዝቱ ፈትቶ ቄስ አድርጎ ሾመው። ከዚህ በኋላ አርዮስ ወደ ጥንት ክሕደቱ ተመለሰ።

እግዚአብሔር ዲዮቅልጥያኖስን ከዙፋኑ አወረደ፤ በወርቅ ወፍሮም ኹለት ዐይኑን አሳወረው፤ መላ ሰውነቱ ተልቶ ቆሰለ። ልሳኑም ተዘግቶ ከመንግሥቱም ተሽሮ በአንጾኪያ አውራ ጐዳና ምጽዋት እየለመነ ተቀመጠ።

በእርሱ ፈንታ ከሮሜ ሥርወ መንግሥት ቆስጠንጢኖስ ነገሠ። የከሐድያን ሞገድ ጸጥ አለ፡ የኃጢአት ማዕበልም ጸጥ አለ፡ ቤተ ክርስቲያንም ዐረፈች። በኒቅያ አደባባይ፥ ይህችውም የአህጉር እናት ቢታንያ የሚላት ናት፡ በዚያ ፫፻፲፰ ሊቃውንት ግሩምና አሸናፊ ከሆነ ከቆስጠንጢኖስ ጋር ተሰብስበው ፈጣሪውን ፍጡር ያለውን አርዮስን አወገዙ። ያንጊዜ የክርስቶስም ሃይማኖት ገሀድ ሆነ። የአርዮስን እምነት የሚከተሉትን ሁሉ ከክርስቶስ መንጋዎች ለይተው አባረሩ።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ አርዮስ ከሌላ ንጉሥ ዘንድ ሔደ። «እለእስክንድሮስ» የእስክንድርያ ካህናት በጸሎትና በቊርባን ያሳትፉኝ ዘንድ ስለ እኔ ካህናትን ለምንልኝ፡ እኔም በሃይማኖት ከእነርሱ ጋር እተባበራለሁ» ሲል ተማፀነ። ንጉሡም አርዮስ በሃይማኖት ከእናንተ ጋር ተባብሮ በጸሎተ ቊርባንም ስለሚሳተፍ የጥንት ጥፋቱን ይቅር በሉት ሲል መልእክተኛ ላከ። እለእስክድሮስም ወደ ንጉሡ ዘንድ እንዲህ ሲል መልእክተኛ ላከ።

«አርዮስ በየተሰደደበት ክፋቱን በልቡ ደብቆ በየዕለቱ እመለሳለሁ እያለ ይለማመጣል ነገር ግን ክዶ ወደ ቀደመ ጥፋቱ ይመለሳል፤ ጴጥሮስ አውግዞ ከቤተ ክርስቲያን ለየው። አኪላስ ግን ተቀብሎ በተለማመጠው ጊዜ በቅስና ሾመው። ከዚህም በኋላ በክርስቶስ ላይ ስድቡን አብዝቷል። በጣዖት አምላኪዎችም ዘመን ምእመናንን አሳድዷል።

እለእስክንድሮስ አወገዘው፡ ቢለማመጠው ፈታው። እንደ መጀመሪያው ሃይማኖቱን ዳግመኛ አስፋፋ፡ ፫፻፲፰ ሊቃውንት አወገዙት፤ ሲለማመጥ ይህ ሦስተኛው ነው። ንጉሡ ግን ብዙ ጊዜ በመልእክቱ ያሳትፉት ዘንድ ለመናቸው። እነርሱ ንጉሡን በመፍራት «እግዚአብሔር የወደደውን ያድርግ» አሉ። እነርሱም፦ «ለሰባት ቀን ይጹም፥ ይጸልይ፥ እኛም እንደ



www.ethiopianorthodox.org

እርሱ እናደርጋለን» ብለው እስከ ዕለተ እሑድ ድረስ በጾምና በጸሎት ሊፈት ኑት የሰባት ቀን ዕድሜ ሰጡት።

በዕለተ እሑድ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከእነርሱ ዘንድ ያማረ ልብስ ተክህኖ ለብሶ ሔደና ለጸሎት ጥቂት ሰዓት ቆመ። ከዚህ በኋላ ሆዱን ታሞ (የወገብ ሕመም ተሰምቶት) ወደ መጸዳጃ ወደ ንጽሕና ቤት፣ /አንበሳ መደብ/ ቤት ይጸዳዳ ዘንድ ሔደ፥ ተቀመጠም፡ አንጀቱ ወጥቶ ሆድቃው ተዘረገፈ። አርዮስ ወደ ውጭ ወጥቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሳይመለስ በዘገየ ጊዜ ካህናቱ፡- «በቅዳሴ ሰዓት ዐይተነው ነበር፤ አሁን ግን ወዴት ሔደ?» ተባባሉ። ንጉሡ እንዳይቆጣን ቊርባን ይቀበል ዘንድ ሒዱና ጥሩት ተባለ። ሊጠሩት በሔዱ ጊዜ አንጀቱ ወጥቶ ሆድቃው ተዘርግፎ መጸዳጃ ቤት ውስጥ ሞቶ አገኙት። ከመናፍቅ ሃይማኖት ኀብረት ያዳናቸውን እግዚአብሔርን አደነቁ፡ አጽን ተውም አመሰገኑት። «የኃጥእ ሰው ሞቱ የከፋ ነው» የተባለው ትንቢት ቃል በአርዮስ ላይ ተፈጸመ።

ዳግመኛ «በኃጥአን ላይ የቁጣህ መቅሰፍት የሚያስፈራ ነው።» ይላል[3]። ጳውሎስም እንዲህ ይላል፡- «ልብህን ባደነደንክ ቁጥር እና ንስሐ ካልገባህ መቅሠፍትን ትሰበስባለህ።»[4] እንደዚህም የአርዮስ አሟሟቱ የከፋ ሆነ።

አርዮስ ክርስቶስን ፍጡር ነው እንዴት ይላል? እርሱ ግን የመለ ኮትንና የትስብእትን ህላዌ መገኛ በአንድ አደረገ። ምክንያቱም የመለኮት ህልውና ከተፈጠሩት ፍጥረታት ከሰዓትና ዕለት እንዲሁም ከዘመናት አስቀድሞ ነው። አብ በአባትነቱ ህልው ነው፡ ጸንቶ ይኖራል እንጂ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ወደ መሆን አይመለስም። ወልድም በወል ድነቱ ህልው ነው፤ ጸንቶ ይኖራል እንጂ አብና መንፈስ ቅዱስ ወደ መሆን አይመለስም። መንፈስ ቅዱስም በመንፈስ ቅዱስነቱ ህልው ነው ጸንቶ ይኖራል እንጂ አብና ወልድ ወደ መሆን አይመለስም። አብ በህልውና ከወልድ የሚቀድምበት የዐይን ዕይታና የዐይን ጥቅሻ ታህል ጊዜ የለም። ወልድም በህልውና ከመንፈስ ቅዱስ የሚቀድምበት የሙብረቅ ፍጥነትን ያህል፥ የንስር ክንፍ ንዘረትን ያህል ጊዜ የለም።

አብ ለብቻው አብ ተብሎ ከመጠራት በስተቀር በወልድ የሌለ ክብር በአብ የለም። ወልድም ለብቻው ወልድ ተብሎ ከመጠራት በስተቀር ከአባቱ በክብር የሚያንስበት ጉድለት የለበትም። መንፈስ

3. መዝ. ፴፫፥፳፩።
4. ሮሜ. ፪፥፭።



www.ethiopianorthodox.org



ቅዱስም ለብቻው መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ከመጠራት በስተቀር ከአብና ከወልድ ማነስ የለበትም።

አብን ለልጁ አባት ተብሎ አገኘነው። እኛ የዚህ ዓለም ፍጡራን እንዴት እንደወለደው አናውቅም። ምክንያቱም ያን ጊዜ ለመወለድ ሥጋዊ ዘርና እናት አልነበረም። ያን ጊዜ የሁላችን አባት አዳም አልተፈጠረም። የሁላችን እናት ሔዋንም ከጐኑ አልወጣችም። እንደገ ናም በባሕርየ መለኮቱ አባትና ልጅ የሌለውን መንፈስ ቅዱስን መንፈስ ቅዱስ ተብሎ አገኘነው። ነገር ግን እኛን በመለኮታዊ ባሕርዩ በጥምቀት ወለደን፡ አብ ወለደን፡ ወልድም ወለደን፥ መንፈስ ቅዱስም ወለደን [ፈጠረን]። ስለ ራሱና ስለ አባቱ ግን እንዲህ ይላል። እኔ አባ ታችሁ ነኝ፡ አባቴም አባታችሁ ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስም እንዲህ ይላል፡- «ሰው ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚ አብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው።»[5]

አብ በቸርነቱ ብዛት እንደ ወለደን ሁሉ ወልድም እንደ ምሕረቱ ብዛት ወልዶናል፡ መንፈስ ቅዱስም በይቅርታውና በቸርነቱ ብዛት ወልዶናል።

አብ ሕያው እንደ ሆነ ወልድም ስለ አብ ሕያው ነው፡ ወልድ ስለ አብ ሕያው እንደ ሆነ መንፈስ ቅዱስም ስለወልድ በጐች [ምእመናን] ሕያ ውና የሚያድን ነው። አብ እኛን በመውደዱ ከእኛ ይልቅ የሚወደውን ልጁን አራራለትም ወልድም እኛን ወዶ ስለ በጐቹ ቤዛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷል። ወልድ በጐቹን [ምእመናንን] ወዶ ነፍሱን ስለ በጐቹ ቤዛ እንደ ሰጠ፡ መንፈስ ቅዱስም እኛን ወዶ ከምእመናን ዘንድ በመው ረዱ አልራቀም።

በሥላሴ ገመድ ወይም በማይለይ [ሰንሰለት] ፍጹም ታስረናል። ከልባችን በማይነቀል [በማይመዘዝ] በቅንዋተ ፍቅሩ ተቸንክረናል። እሱ ወዶናል፡ አይጠላንም። እኛም በእምነት ይዘነዋል አንተወውም።

በሃይማኖት ወደ እርሱ ተሰብስበናል። ከእርሱ ዘንድ ግራና ቀኝ አንልም [አንሸሽም]፡ እንደ ቀለበት ከልባችን ውስጥ እንደ ማዕተብ ከክንዳችን ውስጥ አስቀምጠነዋል። እንደ ዕንቊ ከልባችን ሣጥን፣ እንደ ወርቅ መክሊት ከልባችን መዝገብ ውስጥ ጨምረነዋል።

5. ዮሐ. ፫፥፮።

እንደ ልብስ ለበስነው፤ እንደ ወርቅ መጐናጸፊያ ተጐናጸፍነው፡ እንደ ነገሥታት ወታደር ሰይፍ ታጠቅነው። ለጦርነት እንደ ተዘጋጀ ጀግና ጋሻ መከትንበት፤ ከልባችን ውስጥ ፍቅሩ በኤሉል[6] ወር እንደ ተከዜና ግዮን፣ በእርሻ ወቅት እንደ ተከዜ ዮርዳኖስ፣ በክረምት ወቅት እንደ ተከዜና ኤፍራጥስ ስንዴ እንደ ሚያሸትበት ወቅት ሞላ። ልባችንን በወንጌል ወንዞች አጠጣ። በሃይማኖት ባሕር ውስጥ ጀልባችን ታጠበች። ከሊባኖስ ዕፀዋት ጀልባን ሠራ የሊባኖስ ዕፀዋት የተባሉት ነቢያት፥ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ ቅርንጫፎች ናቸው። ዝርዋን ከሆኑት ከ፲ሥራ ኹለቱ ነገድ በዓለም ባሕር ውስጥ እየቀዘፉ የሚመላለሱትን ዐሥራ ኹለቱን ዋናተኞች መረጠ። ከብንያም ወገን የሆነ የጠርሴስ የቄልቅያን ወጣት ለአገልግሎት ጠራ። ይኸውም የሐዋርያትን ዜና ከምትይዝ ዕብራክሲስ[7] በተሰኘች መጽሐፍ ውስጥ ዜናው የተጻፈለት ጳውሎስ ነው። በቀዘፋም ጀልባዋን ለማፋጠን የሚረዱ ፸፪ /ሰባ ኹለት/ አርድዕትን መረጠ።

ክርስቶስን ፍጡር የሚለውን አርዮስን ወደ መዝለፍ እንገባ። ልብሀ የታወረ አርዮስ ሆይ! በነቢይ «ከፀሐይ መውጣት በፊት ስም አለው» ተብሎ ስለ እርሱ የተነገረለትን ክርስቶስን ፍጡር ትላለህን?[8] ዳግመኛ «ከአጥቢያ ኮከብ መውጣት በፊት ከሆድ ወለድሁህ» አለ።[9] ራሱ ጌታችን በወንጌል፡- «አባት ሆይ! ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ አለ።[10] ከሰማይም አከበርኩህ፡ እንደገናም አከብርሃለሁ» የሚል ቃል መጣ። ክርስቶስ ፍጡር ቢሆን ኖሮ ከፍጥረተ ዓለም በፊት ክብሩ ከየትም ባልተገኘ ነበር። ዓለም ሳይፈጠር በፊት ባይመሰገን ኑሮ አባቱ፡- «አከበርኩህ እንደገናም አከብርሃለሁ» ባላለው ነበር። ስለ መለኮት ህላዌ ግን በነቢይ አንደበት፡- «ተራሮች ገና ሳይ መሠረቱ፥ ሰማያት ገና ሳይዘረጉ ከዓለም አስቀድሞ ወለደኝ» ብሎ ተናግሯል።[11] የጸናች አሪት ስለ ትስብእት ህላዌ እንዲህ ትላለች፡- «እግዚ. አብሔር አለ፥ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ።»[12] ከአብ ስለ መወለዱ

6. ኤሉል የወር ስም ሲሆን በዕብራውያን ከሚያዝያ - መስከረም ያለው ስድስተኛው ወር ነው። መጽሐፈ ሰዋስው ወመዝገበ ቃላት አዲስ ገጽ ፪፻፲፭
7. ዕብራክሲስ ያላት የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን ሳይሆን አይቀርም።
8. መዝ. ፸፩፥፲፯።
9. መዝ. ፻፱፥፫።
10. ዮሐ. ፲፯፥፭።
11. ምሳ. ፰፥፳፭።
12. ዘፍ. ፫፥፳፪።





ወንጌላዊው ዮሐንስ፡- «በመጀመሪያ ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ያም ቃል እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚ. አብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።» ስለ መለኮት ይናገራልና ይህን የወንጌላዊውን ቃል ስማ፡- «በመጀመሪያ ቃል ነበረ» በማለት ያስቀድማል።[13] የአብን ትእዛዝ ስለሚናገር ወልድን ቃል ይለዋል። ምክንያቱም ጌታችን ራሱ እንዲህ በማለት ተናግሯልና «በአባቴ ዘንድ የሰማሁትን ሁሉ እናገራለሁ» ከዚህ አስከትሎ፡- «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ይላል።[14]

ይህ የሚናገረው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። በሦስተኛነት «ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» ይላል። ወንጌላዊው ዮሐንስ ከፍ ያለውን ነገር «ሁሉ በእርሱ ሆነ፡ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» የሚለውን ይናገር ዘንድ ንጹሕ የሆነ የልቡናውን ራስ አነማ።[15]

እነሆ አብ ያለ ወልድ አንዳች እንዳልፈጠረ አስረግጦ አጽንቶ አስ ረዳ። ከአብ ጋር ቅድመ ዓለም እንደ ነበረ ተናገረ። የዓለም ፍጥረት ያለ ወልድ እንዳልሆነ አስረገጠ [አስረዳ]። የዮሐንስ ሰይፍ አንደበቱ በአምላካችን ላይ የስድብን ቃል የሚናገረውን የአርዮስን ልሳን ቆረጠ።

የአርዮስ ወገን ሆይ! እስኪ አይሁድ ጌታችንን፡- «ገና ሐምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃምን ዐይተሃልን?» ብለው፡- ይደበድቡት ዘንድ ድንጋይ አንሥተዋል።[16] ከአንተ ስንፍና ይልቅ የእነርሱ ስንፍና ይሻላል። /ከአንተ ድንቁርና ይልቅ የእነርሱ ድንቁርና ይሻላል/። ስለ ትስብእቱ እውነት ተናግረዋል። ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ተሰቀለበት ዕለት ድረስ ዕድሜው ፴፫ ዓመቱ ነበርና ከማርያም የተወለደበት ዓመት ቁጥር እስከ ተሰቀለበት ሲቆጠር በእርግጥ ፴፫ ከ፶ ያንሳል። ከአብ ዘንድ መወለዱን ስለማያውቁ የዮሴፍ ልጅ መሰላቸው። ምክንያቱም ምድራዊት እናቱን ዐይተው ሰማያዊ አባቱን ዐላዩም። በሥጋ ማደጉን [ሥጋዊ ዕድገቱን] ተመለከቱ። ቅድመ ዓለም የነበረውን ህላዌውን ግን አላወቁም። ከኃጥአን ጋር ሲቀመጥና በዘማዊት ሴት እጅ ሲዳሰስ ተመለከቱት። በኪሩቤል ላይ ተቀምጦ በሱራፌል ሲቀደስ አልተመለከቱም።

በመለኮቱ ክብሩ ተገልጾ እንዳያውቁትና እንዳያስተውሉ በትሕትና

13. ዮሐ. ፩፥፩።
14. ዮሐ. ፲፭፥፲፭።
15. ዮሐ. ፩፥፫።
16. ዮሐ. ፰፥፶፯።



www.ethiopianorthodox.org

ከእነርሱ ዘንድ መጣ:: ነገር ግን «አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ» ባለ ጊዜ በስሑል የተሳለ ቃሉ ወግቶአቸዋል:: እንደ ዋሸ ሰው፥ እንደ አበደ ሰው መስሎአቸው ተጠራጥረውታል::[17] ስለዚህ ይወግሩት? ዘንድ ድን ጋይ አነሡ:: አርዮስ ሆይ! እንግዲህ አንተስ የተጠመቅኸ ክርስቲያን ነኝ ትላለህን? ክርስቲያን ከሆንክ በማን ስም ተጠመቅህ? ያለወልድ በአብ ስም ነውን? እነሆ! ጥምቀትን ያለ ሥላሴ መጠመቅ አይገባም:: በወንጌል፡- «ስታጠምቋቸው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ» ተብሎ ተነግሯል::[18] "በፍጡር ወልድ ስምና በአብ ፈጣሪ ስም ተጠ ምቂያለሁ" ያልክ እንደ ሆነ እነሆ ጥምቀትህን አበላሸህ [አከፋህ]፡ ምክን ያቱም ጸጋ የምታገኝበትን ጥምቀትህን በፍጡር አድርገሃል:: ቊርባን ስለ መቊረብስ የሰውን ልጅ ሥጋ ያለ መለኮት ኀይል እበላለሁ፡ የሰውን ልጅ ደምስ መንፈስ ቅዱስ ሳይጨመር እጠጣለሁ ትላለህን? ይህን የምትል ከሆነ፡- «በድን [ሬሳ] የዳሰሰ ሰው እስከ ሠርክ ድረስ የረከሰ ነው» የምትለውን ሕግ ተላልፈሃል [ተላለፍክ]::[19] የሰው ሥጋ መብላትስ እንዲህ እንዴት ይሆናል? የቅዱሳን ሥጋ መብላት ለሰዎች ተገቢ ቢሆን ኖሮ፥ እስራኤላውያን የሙሴን ሥጋ በበሉ ነበር፡ ምክንያቱም እርሱ ኦሪትን ተቀብሎ ሥርዐቱን ያስፈጽም ነበርና:: እኛም የሐዋርያትን ሥጋ በበላን ደማቸውንም በጠጣን ነበር:: በፍጡራን ደም የፍጡር ሥጋ የሚቀደስ ቢሆን ኖሮ በአቤል ደም አባቶች በአዳም ከተፈረደው ፍርድ በዳኑ ነበር::

ከእግዚአብሔር ዘንድ አብርሃም ልጁን ይስሐቅን ይሠዋው ዘንድ ትእዛዝ መጣ:: አብርሃም ሰይፉን መዝዞ ሊሠዋው በተዘጋጀ ጊዜ የእግዚ አብሔር ቃል ከለከለው:: በሥርዐትና በሕገ መጽሐፍ የሰውን ሥጋ መብ ላት አልተፈቀደምና በይስሐቅ ምትክ የሚሠዋውን በግ አወረደለት:: በግ አርዶ ሥጋውን መብላት የተለመደ ነው::

ለመብልም ቢሉ ለመሥዋዕት እግዚአብሔር ይፈትነው ዘንድ አዘዘው:: «የምትወደውን ልጅ ይስሐቅን ሠዋልኝ» አለው:: ዳግመኛም «እንደ ምት ወደኝ ዐውቄአለሁና በልጅህ ላይ እጅህን አታውርድ» አለው:: እግዚ አብሔር አስቀድሞ አብርሃም እንደሚወደው አያውቅምን? ያውቃል:: ነገር ግን አብርሃም እግዚአብሔርን እንደሚወደው እኛ እናውቅ ዘንድ ለእኛ ምልክት ተወልን:: እግዚአብሔር አብርሃምን በምን ምክንያት

17. ዮሐ. ፰፥፶፰::
18. ማቴ. ፳፰፥፲፱::
19. ዘሌ. ፲፩፥፳፬::





ወደደው:: ድንግል ስለሆነ ነው? ሰማዕት ስለሆነ ነው? መነኩሴ ስለሆነ ነው? መስተጋደል ስለሆነ ነው? መከራስ በመቀበሉ ነው? አንበል:: በአብርሃም ዘንድ የሁሉንም ቅዱሳን ገድል አግኝተናል:: ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀንቶ የአባቱን የጣዖት ቤት ከጣዖቶቹ ጋር አቃጥሏል:: ስለዚህ «ምድር ተከፍታ ትውጣቸው ዘንድ ከቆሬ ልጆች አጥንት ውስጥ እሳት ላወጣው ሙሴ አባት ሆነ::»[20] ዳግመኛ ከእግዚአብሔር ዘንድ እሳት አውርዶ ፫፻፲፰ መምለክያነ ጣዖታትን ላቃጠላቸው ለኤል ያስም አባት ሆነ::[21]

ከእግዚአብሔር ዘንድ አብርሃም ከአባቱ ቤትና ከተወለደበት መንደር እንዲወጣ ትእዛዝ መጣ:: እርሱም በእግዚአብሔር ደስ ተሰኝቶ ወጣ:: ስለዚህ ርስታቸውን አገመራቸውን፥ እርሻቸውን አባታቸውን እና ልጆቻቸውን ትተው የመውጣት ትእዛዝ ያላቸው የመነኮሳት አባት ሆኖ ተሾመ:: በሚስቱ በሣራ መጠለፍ ምክንያት ከጌራራ ንጉሥ አቤሜ ሌክና ከግብጻዊ ንጉሥ ፈርኦን ዘንድ ተፈተነ::[22] ስለዚህም ለሚገፉ ሰዎች አባት ሆነ:: እግዚአብሔር አብርሃምን በዘጠና ዘጠኝ ዓመቱ ይገዘር ዘንድ አዘዘው:: እሱም እንደ ሕፃናት እርቃን ሥጋውን ሁኖ ለመገዘር አላ ፈረም:: ስለዚህም የሕፃናት አባት ተባለ:: ሽማግሌ ሲሆን የግርዛት ሕመ ምንም አልፈራም:: ስለዚህም የሰማዕታት አባት ተሰኘ:: ምክንያቱም ከሕፃናት ግርዛት ይልቅ የሽማግሌዎች ግርዛት ሕመም ይጸናልና፡ ከሚወደው ልጁ ይስሐቅ ይልቅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያደርግ ዘንድ ወደደ:: ፈጽሞ ያርደው ዘንድ አጋደመው:: በአብርሃም ልጅ ይስሐቅ ምትክ እግዚአብሔር ነጭ በግን አሳረደ:: እግዚአብሔርም የሚወደው ልጁን ከአብርሃም ልጅ ከይስሐቅ ዘር ሰው ይሆን ዘንድ ሲልከው አላዘነም:: ይኸውም በዮሐንስና በኢሳይያስ ዘንድ በግ፥ በመልከ ጼዴቅ ዘንድ የመሥዋዕት ስንዴና የወይን ዘለላ በሉቃስ ዘንድ የሚታረድ ላህም በሁሉም ሐዋርያት ዘንድ የአሕዛብን ኃጢአት ለማስተሰረይ ከሰሜን ጽንፍ እስከ ደቡብ ጽንፍ ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ ድረስ የታዘዘ ንጹሕ መሥዋዕት ነው::

20. ዘኍ. ፲፮፥፴፫::
21. ኩፋ. ፲፫፥፵::
22. ዘፍ.፳፥፪::



www.ethiopianorthodox.org

ከሰው ልጅ በተዋሐደ በእግዚአብሔር ልጅ መሥዋዕትነት እንጂ የሰው ልጅ በዕሩቅ ብእሲ ሥጋ መሥዋዕትነት እንደማይቀደስ ፈጣሪ ያችን ያውቃል። ሕያው በሆነ የማይሞት ሕያው [እግዚአብሔር] የሰው ልጅ ከሰው ልጅ በተዋሐደው በአምላክ ልጅ የደሙ ቁርባን እንጂ በዕሩቅ ብእሲ የደሙ ቁርባን እንደማይቀደስ ተረዳ፣ ዐወቀ። ይህ የማይሞተው የሚሞተውን ሥጋ ለበሰ። ይህን የሚሞተውን ሥጋ የማይሞት ሕያው አደረገው። ይህ የማይጠፋ ኃይል የሚጠፋ ሥጋን ለበሰ። ይህ የሚጠፋውን ሥጋ የማይጠፋና የሚናገር አደረገው። በ፶፱ተኛው ትውልድ የአዳም ፈጣሪ በአዳም ልጅ አደረ። ሰው ይሆንባት ዘንድ ንጹሕ ሥጋን ከሰማየ ሰማያት ለራሱ ያመጣ አይደለም። ኀያል የሆነ እርሱ ከህላዌው ሳይጐድል ያለ ድምፅ [ያለሞገድ ድምጽ] ወረደ። በቦታ ሳይወሰን በድንግል ማርያም ማኅፀን አደረ። ከምልዑ ሳይጐል በማኅፀን ሰው ሆነ [ተወሰነ]። አንዱ ባነጻው ሕንፃ ሲያድር ለእርሱ አይደንቀውም፤ ፈጣሪ የፈጠረውን ሥጋ መልበሱ እሱን አያዋርደውም [አያጐሳቁለውም]።

አርዮስን ወደ መዝለፍ እንግባ፤ የክሕደት አብቃይ አርዮስ ሆይ! ፈጣሪን «እኔና አብ አንድ ነን» የሚለውን የፍጥረታትን ፈጣሪ ፍጡር ነው ትላለህን?[23] ዳግመኛ፦ «እኔን ያየ አብን ዐየ» ያለው ፍጡርን ነውን? እንደገና «እኔን የሰማ የላከኝን ይሰማል፤ እኔን የካደ የላከኝን ይክዳል» ያለውን ፍጡር ነው ትላለህን? እንደገና «ያለ እኔ ወደ አብ መቅረብ የሚቻለው የለም» አለ። ዳግመኛም «የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው፤ የአንተ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው» አለ። እንደገና «አብ ሕያው እንደ ሆነ እኔም ስለ አብ ሕያው ነኝ ሥጋዬን የበላ ስለ እኔ ይድናል።[24]

እነሆ! ሥጋውን በመብላት በሚያድን ድኅነት ከመለኮቱ ጋር አሳተፈን። የሕይወቱም ተካፋይ አደረገን። ዮሐንስ ወንጌላዊ በመጀመሪያ መልእክቱ እንደ ተናገረው፦ «አንድ መሆናችንም ከአብ ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው።» እንዳለ።[25] እኛም የክርስቶስ ሥጋው ከአዳምና ከሔዋን ሥር የተገኘ ፍጡር እንደ ሆነ እናምናለን። መለኮቱ ግን አዳምንና ሔዋንን የፈጠረ ነው። ሥጋ መልበሱ ከፍጥረት ወገን ባይሆን ኖሮ በማኅፀን ባልተወሰነ ነበር። መለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ኖሮ ከልደቱ በኋላ የእናቱ ማኅተመ ድንግልናዋ ባልተገኘ ነበር። ሥጋው ከፍጥረት

23. ዮሐ. ፲፬፥፱።
24. ዮሐ. ፮፥፶፯።
25. ፩ዮሐ. ፩፥፫።





ወገን ባይሆን ኖሮ በከንድ ባልታቀፈ በእጅም ባልተዳሰሰ ነበር። በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ወንድ ከማታውቅ እናቱ የድንግልና ወተት ከጡቷ ባልፈለቀ ነበር። ሥጋን መዋሐዱ ከሰው ወገን ባይሆን ቀስ በቀስ ባላደገ ነበር። መለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ኑሮ፦ «አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነበርኩ» ባላለ ነበር።[26] ሥጋ መሆኑ ከሰው ወገን ባይሆን ኑሮ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተዳሶ ባልተጠመቀ ነበር። በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ኑሮ ከአብ ዘንድ፦ ይህ የምወደው ልጄ ነው፤ እርሱን ስሙት» ተብሎ ባልተመሰከረ ነበር።[27]

ደግሞም መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ በራሱ ላይ ባልተቀመጠ ነበር። ሰው መሆኑ ከሰው ወገን ባይሆን ኑሮ ለጥማቱ ውሃን ከሳምራዊት ሴት ባልጠየቀ ነበር።[28] መለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን በቃና ዘገሊላ ውሃን ወደ ወይን ባልለወጠ ነበር። ሰው መሆኑ ከሰው ወገን ባይሆን ኑሮ ደም የሚፈሳትን ሴት ልብሱን ኃጢአተኛዋ ሴት እግሩን ባልዳሰሰችው ነበር። በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ኑሮ ልብሱ ስለ ተዳሰሰ፦ «ከእኔ ኀይል እንደ ወጣ ዐወቅኹ» ባላለ ነበር።[29] የደሚን ምንጭ በመለኮቱ ኀይል ስላደረቀ መለኮቱን ኀይል ይለዋል። ዳግመኛ ኃጢአተኛዪቱን ሴት እግሩን ስትዳስስ፦ «ኃጢአትሽ ተሰርዮልሻል» ባላላት ነበር።[30]

ያለ እግዚአብሔር ብቻ በቀር ኃጢአትን ይቅር ማለት ለማን ይቻለዋል? ሥጋን መዋሐዱ ከሰው ወገን ባይሆን ኖሮ የኢያኢሮስን ልጅ ልጄ [ማቢታ] ብሎ ባልጠራ ነበር። በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ኑሮ ከሞተች በኋላ በሕይወት ባላስነሣት ነበር። ሥጋን መዋሐዱ [ሰው መሆኑ] ከሰው ወገን ባይሆን ምራቁን ከአፈር ላይ ባላደረገ ነበር። በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ምራቁን በመቀባት ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የሆነውን ሰው [በርጤሜዎስን] ዐይን ባላበራ ነበር። ሥጋን መዋሐዱ ከሰው ወገን ባይሆን ማዕበል ሲነሣ በጀልባ ውስጥ ባልተኛ ነበር። በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ባሕሩን ነፋሳትን በመገሠጥ ጸጥ ባላሰኘ ነበር። ሥጋን መዋሐዱ ከሰው ወገን ባይሆን መንገድ በመሔድ ባልደከመ ነበር። በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን መሔድ የተሳናቸውን [እግረ ሰባሮችን] ባላዳናቸው እንደ

26. ዮሐ. ፰፥፶፰።
27. ማቴ. ፲፯፥፭።
28 ዮሐ. ፬፥፯።
29. ዮሐ. ፱፥፩-፯፤ ማር. ፭፥፴።
30. ሉቃ. ፯፥፵፰።



www.ethiopianorthodox.org

ጉበዝ ተራማጅ ባላስኬዳቸው ነበር። ሰው መሆኑ ከሰው ወገን ባይሆን ባልተ ራብ፥ በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን አምስት ሺሕ ሮኑባንን በአምስት ኅበስትና በኹለት ዓሣ ዐራት መቶ ሮኑባንን በሰባት እንጀራና በጥቂት ዓሣ ባላጠገበ ነበር። ሥጋን መዋሐዱ ከሰው ወገን ባይሆን ስለ አልዓዛር ሞት ባላለቀሰ፥ በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ከቀብር ውስጥ ጠ ርቶ ባላወጣው ነበር። ሰው መሆኑ ከሰው ወገን ባይሆን በአህያና በአህያ ውርንጫ ባልተቀመጠ፥ በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን በሕፃናት አፍ ባልተመሰገነ፥ ሥጋን መዋሐዱ ከሰው ወገን ባይሆን በሊቃነ ካህናት ጭፍሮች ባልተጻፈ [በጥፊ ባልተመታ]፥ በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ጴጥሮስ ጆሮውን የቆረጠውን ሰው ጆሮውን ወደ ቦታው ባላስገባ፥ ሥጋን መዋሐዱ ከሰው ወገን ባይሆን በጲላጦስ ፊት ባልቆመ፡ በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ጲላጦስን፦ «መንግሥቴ ከዚህ ዓለም ቢሆን አገልጋዮቼ አይሁድ ወደ አንተ ዘንድ እንዳይወ ስዱኝ በተከላከሉልኝ» ባላለው ነበር።

ሥጋን መዋሐዱ ከሰው ወገን ባይሆን የጲላጦስ ወታደሮች ልብሱን ባልገፈፉት፥ በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ዐሐይ ዓለምን በማጨለም ብርሃ ኑን ሰውሮ ዕርቃኑን ለማየት ባላፈረ ነበር። ሰው መሆኑ [ሥጋዊው] ከሰው ወገን ባይሆን «አምላኬ፣ አምላኬ ስለምን ተውኸኝ?» ባላለ ነበር። በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ዳግመኛ «አባት ሆይ፡ ነፍሴን በእጅህ እሰጣለሁ» ባላ ለም ነበር። ሰው መሆኑ ከሰው ወገን ባይሆን በሥጋ ሞትን ባልተቀበለ ነበር። በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ምድር ባልተናዋወጠች የቤተ መቅደስም መጋረጃ ባልተቀደደ ነበር። ሰው መሆኑ ከሰው ወገን ባይሆን በሌንጊኖስ ጦር ባልተወጋ ነበር። በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን በደሙ ነጠብጣብ ከአለት ውሃ ባላፈለቀ ነበር። ከጐኑ የፈሰሰው ጠለ ምሕረቱ ሙታንን ባላስነሣ ነበር። ሰው መሆኑ ከሰው ወገን ባይሆን እንደ ጥንት በድን መቃብር ውስጥ ባልተኛ ነበር። በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን ነፍሱን ሥጋውን ለማንሣት ወደ ሥጋው ባልመለሰ ነበር። «ነፍሴን በፈቃዴ እሰጣለሁ። ነፍሴን ላኖራት ሥልጣን አለኝ። ዳግመኛም ላስነሣት ሥል ጣን አለኝ። ይህንም ትእዛዝ ከአባቴ ዘንድ ተቀበልኩ።» ብሎ ራሱ እንደ ተናገረው ሥጋ ሰው መሆኑ ከሰው ወገን ባይሆን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በተነሣበት ዕለት ምግብ ለመመገብ ባልተቀመጠ ነበር። በመለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን፦ «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡





ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ይቀርላቸዋል፡ የያዛችሁባቸው ይያዝባቸዋል» ብሎ በደቀ መዛሙርቱ ፊት እፍ ባላለባቸው ነበር። ሰው መሆኑ ከሰው ወገን ባይሆን በሐዋርያት ላይ እጁን ባላኖረ ነበር። መምህራን በደቀ መዛሙርታቸው ላይ እንደ ሚያደርጉት ሥርዐት በሐ ዋርያት ላይ እጁን ባላኖረ ነበር። መለኮቱ ፈጣሪ ባይሆን በደመና እሳት ተጭኖ ወደ ረጅሙ አርያም ከፍ ባላለ ነበር። በአባቱም ቀኝ ባልተቀመጠ ነበር።

ከሥጋዌ በኋላ ስለ ትስብእትና መለኮት ህላዌ እንናገር። ወልደ እግዚአብሔርን በመለኮቱ የሰው ልጅ አንለውም። በትስብእቱም ድን ግል «የራሷን መለኮት በራሷ ሥጋ ከራሷ ሥጋ ወለደች» አንለውም። አብም የራሱን ሥጋ በራሱ መለኮት በአምላክነት ካለ ከራሱ ኃይል ወለደ አንለውም፡ ቀዳሚ ልደት ግን ብቻው እግዚአብሔር ከብቻው እግዚአብሔር፡ የተገኘ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፡ ከሕይወት እሳት፣ የተገኘ የሕይወት እሳት፡ [ከእሳት ሕይወት የተገኘ እሳተ ሕይወት] ከሕያው አብ የተገኘ ሕያው ወልድ፡ ከተፈጠረ ነገር ያልተፈጠረ፣ በመለ ኮቱ የማይታይ፡ የማይነካ፡ የማይዳሰስ፡ የማይደኸይ፡ የማያረጅ፡ የማይ ቸገር፡ የማይፈርስ፡ የማይተኛ፡ የማይንቀሳፋ፡ የማይጨልም የማይ ሳለም፡ በፈቃዱ ካልታወቀ የማይረዳ ልብ የሚያደርግ፡ የማይመ መር፡ የማይለይ፡ የማይለወጥ፡ የማይደክም፡ የማይሰለች፡ የማይ ቀየም፡ የማይተበል፡ የማይጐድልበት፡ የማያድፍ፡ የማይረክስ ነው።

ስለ መንፈስ ቅዱስ በክብር በአካል በልክ ከአብና ወልድ እንደ ማያንስ እንናገራለን። ከአብና ከወልድ ህልውና ፈጽሞ ያልተለየ ነው፡ ክብሩም እንደ ክብራቸው ነው፡ መልኩ እንደ አርአያቸው፡ በጽም ራት፡ በአንድነት፡ በተዋሕዶ፡ በነደ እሳት የተሸፈኑ፥ በመሰወሪያ የተከ ደኑ፡ በመጋረጃ የተደበቁ፡ በሐሳብ የማይገኙ፥ በምስጢር የተሸሸጉ፥ ከሰማየ ሰማያት ከፍ ያሉ፡ ከባሕር ባሕር/ከውቅያኖስ ውቅያኖስ የጠ ለቁ/ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ የሰፉ፡ በመከፈል ያይደለ በአንድነት፥ በመለ ያየት ያይደለ በህልውና ጥምረት [አንድነት] የሰፉ [ምሉዓን] ናቸው።

ለማይበተን ሦስትነታቸው ምስጋና ይገባል። ለማይጨመር አንድነ ታቸው ምስጋና ይገባል። ለዘላለም ለማይከፈል ህልውናቸው ክብር ይገ ባል። አሜን። ይሁን ይደረግ።

በሸንጋይ ልቡ የከፋ፣ የሰይጣንን መንገድ የሚከተል፣ ለውሾች መንጋ እረኛ፡ በገሊላው ኢየሱስ መለኮት ላይ ስድብን የተናገረ የአር



www.ethiopianorthodox.org

የስ በለፋው ተፈጸመ። በሃይማኖቱ ክርስቲያን፣ በሙሴ ሕግ አራታዊ፣ በክርስቶስ ወንጌላዊ፣ በማኅተሙ መስቀላዊ፣ በተጋረደ በአሸበረቀ በተጌጠ አዳራሽ ቤት የሚኖር፣ በቅብዐ ቀምቀት ናዝራዊ፣ በምግባር ኃጢአተኛ ዘማዊ [ስብአዊ ምኞት ያለው][31] ጊዮርጊስ ይህን አለ። ለዘላለም ሕያውና የሚያድን ለሆነ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን ለዘላለም። አሜን።

31. ቅዱሳን ከብዙዎቹ ከመግለጥ ራሳቸውን ማግለል ወይም ዝቅ ማድረግ ስለሚመርጡ ሌቱ ራሱን በግግ እያለ እንደሚጠራ ልብ ይሏል።





# [ምዕራፍ ፫]

## የገና ምንባብ

ጥንት አናፍሩ የማይደረስበት፣ በቁጥር የማይሰፈር፣ በማይገኝ፣ በእግዚአብሔር አብ ስም፣ የከዋክብት ገጽታ ሳይታይ ውሃዎችን ወደ ራስ የሚሰበስብ፣ የናጌብ ባሕር ሳይጸና ከአብ ጋር የነበረ፣ በኋላኛው ዘመን እንበለ ዘርዐ ብእሲ ከድንግል ማሕፀን በተገኘ በአንድ ልጅ [ወልድ] ስም፣ የሰማይ ስፋቱ ሳይዘረጋ በነበረ፣ የምድር ስፋት ሳይሰፋ፣ የምሥራቅና ምዕራብ የሰሜንና ደቡብ ንእሳን ማእዘናት የመሰዕና የአዜብ ትይዩ ሳይታወቅ በነበረ፣ በራሱ ጥበብ በሚያውቅ ልብን በሚመረምር የጽድቅ መንፈስ በሆነ፣ በጰራቅሊጦስ ስም፣ ይህ ቀዳማዊ ነው ይህ ደግሞ ሁለተኛ [ተከታይ] ነው በማይባል፣ በአንድ ምክርና ቃል፣ በአንድነት በሦስትነት ዓለምን ሁሉ በፈጠረ እግዚአብሔር ስም እንጽፋለን።

እንግዲህ ‹ወልድን ከነቢያት አንዱ ነው የሚለውን የንስጥሮስን[1] ዘለፋ እንጽፋለን። የክሕደቱም ምክንያት ይህ ነበር። ታስሮስና ሂድሮስ የተባሉ ኤጲስ ቆጶሳት፦ ‹አንዱ ወልድ የባሕርይ ልጅ፣ አንዱ ወልድ የጸጋ ልጅ የምትል የክሕደት መጽሐፍ በጥንት ዘመን አስተምጠውለት ነበር። ንስጥሮስም ወልደ እግዚአብሔር [ቃል] በዮርዳኖስ የማርያምን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ባገኘው ጊዜ የጸጋ አምላክ አደረገው ይሉታል የሚለውን ይህን የክሕደት መጽሐፍ ከእነዚያ ኤጲስ ቆጶሳት ከስሕተት ማጥናቸው ውስጥ አገኘ፤ መጽሐፉንም በልቡ ወደዳት፤ በነሲናውም አፈቀራት፤ ነገር ግን የቁስጠንጥንያ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ እስከሚሾም ድረስ ግልጽ አላደረጋትም።

በአንድ ወቅት ምእመናን በዕለተ ዐርብ ቍርባን ይቀበሉ ዘንድ ለም እመናን ጉባኤ ተደረገ። ያን ጊዜ ከመር አበባዋ ያልነጻች አንዲት ሴት

1 ንስጥሮስ ‹ኤፍፐፖርቴርየስ› በሚባል የአንጾኪያ ገዳም የሚኖር ግብፃዊ መነኩሴ ነበር። ዲቁናና ቅስናም የተሾመው በአንጾኪያ ነበር። ድምፀ መልካምና ንግግር አዋቂ እንደነበር ይነገርለታል። ከፍተኛ ትምህርቱን የተማረው በአንጾኪያ ት/ቤት ከመርስስ ሊቀጳጳስ ከዲዮድሮስ ነው። ዲዮድሮስ እምነቱ በምሥጢረ ሥጋዌ ክርስቶስን ከሁለት ከፍሎ አንዱን ወልደ ዳዊት ሌላውን ወልደ እግዚአብሔር ነው ይል ነበር። ተማሪው ንስጥሮስ በዚሁ በአንጾኪያ የተማረውን በደፋ ይመጣው የቁስጥንጥንያ ሊቀጳጳስ ሆኖ ሀገረ ሀገረ ሄዶም ከሆነ በኋላ ነው። /አባ ጎርጎርዮስ፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፤ ገጽ የ፵፩/



www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያንን በመውደድ ቍርባን ትቀበል ዘንድ መጣች። ሕዝቡም የመንፈስ ቅዱስ ጥላ እንደ ፀሐይ ብርሃን ሲሸሽ ተመለከቱ። ንስጥሮስ ፓትርያርክ ስለነበረ ሴቲቱን ከፊቱ አምጥተው አቆሟት። ንስጥሮስ፡- «አንቺ ሆይ! ከአንቺ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እስከሚነጥፍ ድረስ ርኩሰትሽ ምንድነው? ምንስ አድርገሻል? ንገሪኝ» አላት። ሲትየዋም፡- «የፈጸምኩት በደል የለም። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያንን በመውደዴ ከወርኀዊ ግዳጄ ሳልነጻ ከምእመናን ጋር ቍርባን ልቀበል እዚህ መጥቻለሁ» አለችው። ሊቀ ጳጳሳቱም ተቆጣ፤ ዕርቃን ሥጋዋን ገልጸው ቁልቁል ወደ መሬት ዘቅዝቀው እንዲሰቅሏት አዘዘ። «እግዚአብሔር በሥጋ ከማርያም ቢወለድ ኖሮ መንፈስ ቅዱስ ከዚህች ሴት ባልራቀ ነበር።» እግዚአብሔር ከሴት ተወልዶ ቢሆን ስለ ማርያም ሴቶች ሁሉ ከርኵሰታቸው በተለዩ ነበር።» አለ። ሊቀ ጳጳሱም ሕዝቡ ወደ እርሷ ቀርበው ምራቃቸውን በንፍረተ ሥጋዋ ላይ "በዚህ ሥጋ እግዚአብሔር ተወልዷል ብሎ የሚያምን የተወገዘ ይሁን" እያሉ ይተፉ ዘንድ አዘዘ። «እግዚአብሔር በማኅፀን ተወስኖ እንደ ተወለደ የጡት ወተት በመጠባት ከሕፃናት ጋር ተሳትፏል። በማንኛውም በሴቶች ልማድ አልፏል። የሚል የተወገዘ ይሁን።» አለ ሕዝቡም እንዳዘዛቸው አደረጉ።

ዮሐንስ የሚባል ጠርዝቢጠር /ትርጉሙም ካህን ወይም ቄስ ማለት ነው/ ወደ ተፈረደባት ሴት ቀርቦ «እኔ እግዚአብሔር ከሴት በዚህ ሥጋ እንደ ተወለደ አምናለሁ» ብሎ የወር አበባ የሚፈሳትን ሴት ንፍረተ ሥጋ ሳመ። «እኔ እግዚአብሔር በድንግልና ወተት እንዳደገ፤ በሕፃናት ሥርዐት እንደ ተሳተፈ ከኃጢአት በስተቀር የሰውን ሕግ እንደ ፈጸመ አምናለሁ።

ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትው ሥዕለ ማርያም «አፈ ወርቅ ብላ ጠራችው። ስለዚህ «ዮሐንስ አፈ ወርቅ» ተባለ። ያዕቆብ በእግዚአብሔር አፍ እስራኤል ተብሎ እንደተጠራ ዮሐንስም እንደ እርሱ በአፈ ሥዕለ ማርያም አፈ ወርቅ ተባለ። እኔም ስለ እርሱ በእውነት አምላክ ከድንግል ስለ መወለዱ ፍቅር የወር አበባ የሚፈሳትን ሴት ንፍረተ ሥጋ ለመሳም ያላፈረ አፈ ዕንቍ፣ አፈ ወርቅ እለዋለሁ። በእርግጥ በድርሳናቱ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስጌጥ አፈ ዕንቍ አፈ ወርቅ ነው። እውነት ነው፤ በማርና በስኳር አፉ [እንደበቱ እውነትም] ቢቃሉ

2 ተአምረ ማርያም ገጽ [illegible] ተስፋ ገብረ ሥላሴ፡ የ[illegible]::





ጣዕም ምእመናን የሚያጠጣ ነው። በትምህርቱ መና የምስጢር በጐችን [ምእመናንን] የሚያስደስት አፈ ሹቱ፤ አፈ መዓዛ ነው። በመዝሙሮ ሥልጣኑ ከሐድያንን የሚቆራርጥ አፈ ሰይፍ፤ አፈ ቢለዋ ነው። እውነትም የማይነዋወጥ ምስሶ የማይፈርስ መሠረት ነው፤ ከምገድና ማዕበል መነዋወጥ የተነሣ የማይሰበር መርከብ ወደ ሃይማኖት ባሕር ጠልቆ የሚገባ ዋናተኛ ነው፤ በጠላት ፊት የማይፈርስ ግንብ የጸና ቤት ነው።

እንግዲህ የንስጥሮስን ዘለፋ እንናገራለን። ምክንያቱም ንስጥሮስ የስንፍና መምህሩን የሆኑ የታስሮስና የዲድሮስ የክህደት መጽሐፍን ገሀድ አደረገ እንጂ ከስንፍናው አልተመለሰም። በአትሮንስ ላይ ተዘርግቶ የሚነበብ ድርሰት ደረሰባት። እርሱ እንደሚለው እናገር ዘንድ እፈራለሁ። የከፋች ሃይማኖቱን ከማሰብ የተነሣ ጉልበቶቼ ይንቀጠቀጣሉ። እንደ ሬት ደም ለአፌ ነገሩ መራራ ሆነብኝ። ሞተው እንደ ተጣሉ ውሾች በድን አፍንጫዬን ሸተተኝ። ለጕሮሮዬ እንደ ጋለ የብረት ችንካር ሆነብኝ። ለእግሮቼም የተንተረከከ ፍሕም እሳት መርገጥ ሆነብኝ። ስድብን የተመላ የአንደበቱ ቃል ልቤን አስደነገጠው። በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስጠይፍና በሰው ዘንድ የተናቀ ትምህርተ ሃይማኖቱ የሚስተጥጥ ነው፤ እኔስ ደሟ ይፈስ የነበረ ሴትን ንፍረተ ሥጋ የሳመ የአፈ ወርቅ የዮሐንስን አፍ እስም ዘንድ በወደድኩ። የወላዲተ አምላክ የማርያም ድንግልን ቅድስና አስቦ የግዳጅ ደም ርኩሰትን አላሰበም። የመለኮትን ሥጋዊ አስቦ ስለ ራሱ አበሳ አላሰበም።

በሕግ መጽሐፍ እንዲህ የሚል ጽሑፍ አለ፡- «ሴት ፈሳሽ ነገር ቢኖር ባት በሥጋዋም ያለው ፈሳሽ ነገር ደም ቢሆን፡- በመርገምዋ ሰባት ቀን ትቀመጣለች። የሚነካትም ሁሉ እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው። መርገም ስትሆን የምትተኛበት ነገር ሁሉ ርኩስ ነው። መኝታዋን የነካን ሁሉ፤ የጸናች አረት ታረክሰዋለች።[3] የደሟን ምንጭ የነካውንማ ንፍረተ ሥጋዋን በመሳም የተሳለመውን እንዴት ይሆን? ዮሐንስ ይህን ያደረገው ስለ ሃይማኖቱ በመቅናት ነው እንጂ የሙሴን ሕግ በማቃለል አይደለም። ንስጥሮስን ከግዳጅ ደማቸው የተነሣ ሴቶችን አረከሳቸው። የሴቲቱን ንፍረተ ሥጋ ስለሳመ የተስፋ ዋጋ አልጐደለበትም።

ደም የሚፈሳት ሴት በዳሰሰችው ጊዜ የኢየሱስ ክርስቶስ ልብስ

3 ዘሌ. ፲፭፥፲፱::



www.ethiopianorthodox.org

እንዳልረከስ፡ ከእርሱ ኃይል ወጥቶ የደሟን ምንጭ እንዳደረቀ፣ እንደዚሁም ደም የሚፈሳት ሴት ኀፍረተ ሥጋን መሳሙ የሐንስን አላረከሰውም:: ከአፉ የሃይማኖት ኀይል ወጥቶ የጥፋት ምንጭ ውሃን አድርቋልና:: ይኸውም የከሐዲው የንስጥሮስ ትምህርት ነው::

ወደ ንስጥሮስ የስንፍና ነገር እንመለስ:: ብንነግረው ከአፉ ስለወጣው የስድብ ቃል እንፈራለን:: ብንተወው የክሕደት ትምህርቱ ሥር በደካሞች ልቡና ይጸናል:: የንስጥሮስን ዜና እንነግራችኋለን፡ ስሙ:: ንስጥሮስ የረከሰ፣ መርገምን እንደ ልብስ የለበሳት፡ እንደ መጐናጸፊያ የተከናነባት፡ ኃጢአትን እንደ ቀበቶ የታጠቃት፡ ዘወትር የማዝት መርገ እንደ ውሃ፡ ከአንጀቱ እንደ ቅባት ከአጥንቶቹ የገባ ነው::

ከዚህ በኋላ ስለ እርሱ ፪፻ ኤጲስ ቆጶሳት በኤፌሶን ተሰብስበው ስለ ስሕተቱ ወደ ጉባኤ ጠርተው ገምጉት:: ልቡን አደንድኖ ከክሕደቱ አልተመለሰም:: «ያለ ፍርንት አንዱ ወልድ የባሕርይ፣ አንዱ ወልድ የከበረ የጸጋ ልጅ ነው» አለ:: «የእግዚአብሔር ልጅ በዮርዳኖስ በተገናኘው ጊዜ የጸጋ አምላክ ሆነ:: ኢየሱስ ክርስቶስን የጸጋ አምላክ አለው:: ከስሕተቱ ይመለስ ዘንድ ለመኑት፣ እሺ፡ አልፈረኝ አላቸው::

በኀብረት በመንፈስ ቅዱስ አፍ አውግዘው ከቤተ ክርስቲያን አስወጡት:: በእርሱ ሃይማኖት የሚያምኑና በክፉ በከረፉ አምልኮቱ የሚኑ ዘውን ሁሉ አወገዙ:: በእርሱ መንበረ ጵጵስና ላይ ለቤተ ክርስቲያን ጠበቃና ለሃይማኖቱ የሚቀና መክስምያኖስን አስቀመጡ [ሾሙ]::

ንስጥሮስ ከሞተ በኋላ ንጉሡ መርቅያን መንግሥቱ የእርሱ አልነበረም፡ ብርክልያ የንጉሡ ልጅ ስለወደደችውና በአባቷ በአርቃድዮስ ፈንታ ስላነገሡችው እንጂ:: እናቷ አውዶክስያም በማኅተ ውስጥ በስደት የሞተ ዮሐንስ አፈወርቅን ያሳደደችው ናት::

ንጉሡ የከሐዲውን ንስጥሮስን ሃይማኖት ወደደ፡ የረከሰ ሃይማኖቱን ያጸና ዘንድ ማኅበርም ያቋቁም ዘንድ ፈቀደ:: እግዚአብሔር ግን የወደደውን ያደርግ ዘንድ አላውለሰነውምና ንስጥሮስን ፈጥኖ ገደለው:: ንጉሡ በማፈሩ በንስጥሮስ ሞት ወደ ልዮን ሃይማኖት ገብቶ ፳፻፴፮ ኤጲስ ቆጶሳትን ሰበሰበ:: ልዮን ግን በሚሞትበት በሽታ ውስጥ ነበር:: ሃይማኖቱ የረከሰችና ከንፈሮቹ የረከሱ የንስጥሮስ ሃይማኖት ይህ ነው:: በስንፍና ቃል እንዲህ ይላል፡- «ከማርያም የተወለደው የዮሴፍ ልጅ

4. ማር. ፩፥፳፩





ነው:: የእግዚአብሔር ልጅ ግን በዮርዳኖስ ባገኘው ጊዜ የጸጋ አምላክ አደረገው::» ንስጥሮስ ሆይ! ወንጌላዊው የሚለውን ስማ::

«የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት እንዲህ ነበረ:: እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ በመንፈስ ቅድስ ፀንሳ ተገኘች:: እጮኛዋ የሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ:: እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፡ እነሆ! የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም ታየው፡ እንዲህም አለ፡- የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ! ከእርሷ የሚወለደው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህ ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ:: ልጅም ትወልዳለች፡ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ:: በነቢይ ከጌታ ዘንድ፡- እነሆ! ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም (ወልድን) ትወልዳለች፡ ስሙንም ዐማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፡ ትርጓሜውም፡- እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው የሚል ነው»::[5]

ሉቃስም እንዲህ ይላል፡- «በስድስተኛው ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደ ምትባል ወደ ገሊላ ከተማ፡ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፡ የድንግሊቱ ስም ማርያም ነበረ:: መልአኩም ወደ እርሷ ገብቶ፡- ደስ ይበልሽ፡ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ! እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው፡ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት፡ ከቃሉ የተነሣም ደነገጠች፡ እንዲህ ያለውን ሰላምታ እንዴት ሊቀበሉት ይገባል? አለችው:: ማርያም ሆይ! በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሻልና አትፍሪ፡ እነሆም! ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፡ ስሙን ኢየሱስ ትዪዋለሽ:: እርሱ ታላቅ ነው:: የልዑል ልጅም ይባላል፡ እግዚአብሔር አምላክም የአባቱ የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል:: በያዕቆብ ወገን ለዘላለም ይነግሣል፡ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም:: ማርያምም መልአኩን፡- ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው:: መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፡ የልዑልም ኀይል ይጸልልሻል፡ ስለ ዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል::»[6]

ከሐዲው ንስጥሮስ ሆይ! ስማ፡ አንተ ክርስቲያን ነኝ የምትል ከሆነ በወንጌላውያን እመን:: በከረፋች «ሃይማኖትህ» የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ከምታረክስ ክርስቲያን ባትሆን ባትጠመቅ ይሻልህ ነበር:: ቅዱስ ጳውሎስ

5. ማቴ. ፩፥፲፰::
6. ሉቃ. ፩፥፳፮



www.ethiopianorthodox.org

ስለ ዕብራውያን ሰዎች እንደ ተናገረው፦ «ልቡናቸው በሃይማኖት አንድ ስላልሆነ ለእነዚያ የሰሙት ቃል አልጠቀማቸ ውም፡፡» በወልደ እግዚአብሔር ሳያምኑ የሙሴን ሕግ መጠበቅ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ካልጠቀማቸው ፍጥረትህ ከአረማውያን ሥር ከሐዲና ያልተገዘርክ ሮማዊ፣ ያለ ክርስቶስ ሃይማኖት ክርስቲያን ብቻ መባል እንግዲህ እንዴት ይጠቅምሀል? «የሕግ ፍጻሜው በክርስቶስ ማመን ነው» እን ዳለ ቅዱስ ጳውሎስ፡፡ አንተ ግን ተክልን ያለ ፍሬ፣ ዛፍን ያለ ቅጠል፣ ወንዝን ያለ ፈሳሽ፣ ጉድጓድን ያለ ውሃ፣ ንጉሥን ያለ ዘውድ፣ መንግሥትን ያለ ወታደር (ያለ መሣሪያ)፣ ደመናን ያለ ዝናም፣ እሸትን ያለ ዘለላ፣ አባትን ያለ ሁብት ሲሳይ እናትን ያለጡቶች፣ ማንብን ያለ ማር፣ በርን ያለ መዝጊያ እና ሙሽራን ያለ አክሊል፣ ሙሽራይቱን ያለ ቀለበት ካህንን ያለ ልብስ ተክህኖ፣ መሠዊያን ያለ ቊርባን [መሥዋዕት] መርከበኛን ያለ ጀልባ ሥርዐት፣ ገቢያን ያለ ገንዘብ ባለሥረገላን ያለ ብረት ቁር (ጥሩር) ፈረሰኛን ያለ ጦር መሰልክ፡፡

በክርስትና ማኅተም ሳትቀደስ እንዴት ለጽጽስና ተመረጥክ? በእምነት ሳትጌጥ እንዴት ለክህነት ተመረጥክ? ንስጥሮስ ሆይ! ታስሮስ ክሕ ደቱን ተወልህ፣ ሂድሮስ በስንፍናው አሳተፈህ፡፡ ንስጥሮስ ሆይ! ሲኦል በጡቶቿ አሳደገችህ፣ ገሃነምም በጥፋት ወተቶቿ አሳደገችህ፣ ሰይጣን እንደ ልብስ ለበሰህ፣ አንተም እንደ ልብስ ተጐናጸፍከው፡፡ ሐምጥን ያሳተ አባብ መርዙን አፍህ ውስጥ ጨመረ፣ አንተም እንደ መቃጠቢያ [ቀበቶ] ታጠቅኸው፡፡ የታስሮስና የሂድሮስ ቃል ሆድህን እንደ ሕመምተኛ አወከው፣ በጣር ሀንስህ ኃጢአትንም ወለድህ፣ ጉድጓድ ቆፍረህ ገባህ፣ በውስጡም ወድቀህ አልተነሣህም፡፡ ከአባትህ ወገብ የእፉኝት መርዝ መነጨን ወደ እናትህ ማኅፀን አባብ ገባን? በረከስ ወተትና ውሾች አሳደጉህን? የአሳማዎች መንጋ በእዛባ ማጥ ውስጥ በግርግታ በሚተራ መሰብት (በሚንከባለሉበት) አሳደጉህን እናትህ በአራስነት ሳለች ተበርዎች ወይስ የዐረብ ተኩላዎች በልደትህ ዕለት በዓል አደረጉን? የተፀነስክበትና የተወለድክበት ዕለት የተረገሙ ናቸ፡፡ ንስጥሮስ ሆይ! የእግዚአብሔርን ልጅ የዮሴፍ ልጅ ለማለትና የነቢያትን አምላክ ከነቢያት አንዱ ለማለት እንዴት ደፈርክ? ይህን በተናገርክ ጊዜ የምትረግጣት ምድር ትውጥህ ዘንድ ባለመሰንጠቋ የእግዚአብሔርን ትዕግሥት አደንቃለሁ፡፡

7. ዕብ. ፬፥፪፤ ሮሜ. ፲፥፬፡፡





ይህንን ስትናገር ምጽናኑተ ሰማያት ያልፈረሱ የከረብቶች መሠረቶችስ ያልተነዋወጡ እንዴት ነው? ያሠጥመህ ዘንድ የገሃነም ባሕሮች እንዴት አልፈለቁም? የሲኦል ምንጮችስ እንዴት አልወጡም? የእሳት ሰይፎች አንተን ለመሰየፍ እንዴት አልተ መዘዙም? የመብረቅ ነጐድጓድ ሳይቃጥልህ እንዴት ዝም አለ? ይህን በተናገርክ የቤተ ክርስቲያን ጠባቂ ሚካኤል እንዴት ዝም አለ? ማርያምን፦ «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኀይል ይጸልልሻል፡፡ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡፡» ያላትን ስብከቱን ስታስተባብል ገብርኤል እንዴት ዝም አለ?[8] አንተ በጠባይህ ወደ መወለጃህ [ልደትህ] መለስከው፣ መወለጃህ ከገጸ ምድር ትጥፋ [ትሻር] ስምህም ከሕይወት መጽሐፍ ይደምሰስ፡፡ ይህ እርግማን ለአንተ ብቻ አይደለም፣ የአንተንም ሃይማኖት ለሚያምኑ ሁሉ ነው እንጂ፡፡

ማርያምን የአዳኝ እናት እንደሚሏት የአምላክ እናት እንደ ማይሏት የልጆችህን ዜና ሰምተናል፡፡ ልጇንም ነቢያት እንደ አንዱ ነው ይሉታል በማን መስለው ነው? የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላልፎ ከገነት በወጣው በአዳም ነውን? ወይስ በደሙ መፍሰስ ለብዙኃን ቤዛ ባልሆነ በአቤል ነውን? ስሟ እድኒ[9] የተሰኘች ከእርሷ በፋካቤ ሥጋ ማቱሳላን የወለደች ሴትን ባገባ በሄኖክ ነውን? ወይስ የጥፋት ውሃን ፈርቶ መርከብን ሠርቶ በዳነ በኖኅ ነውን? በበኵርነቱ ከሚስቱ ከልጆቹ ከልጅ ልጆቹ ጋር ዳነ እንጂ ኃጢአተኞችን ክርስቶስ እንዳዳናቸው አላዳናቸውም፡፡

ዳግመኛ በማን ይመስሉታል? በግራ ምክንያት የግብፅ ንጉሥን ፈርቶ ሣራን ሚስቱ እንዳልሆነች በካደ በአብርሃም ነውን? ወይስ በርብቃ ምክንያት የጌራራ ንጉሥን ፈርቶ ርብቃን ሚስቱ እንዳልሆነች በካደ በይሥሐቅ ነውን?

እንደገናም ከነቢያት አንዱ ብለው በማን ይመስሉታል? ሁለቱን የላባን ልጆች ልያንና ራሔልን ባገባ ባላንና ዘለፋን ዕቅባት ባደረገ በያዕቆብ ነውን? ወይስ ለአልዮጳሲስ[10] የሚሰዋ የአማልክት ካህን የሆነ ልጁ የጲስፋራን ልጅ ባገባ በዮሴፍ ነውን?

እንደገናም ከነቢያት አንዱ ብለው በማን ይመስሉታል? እግዚአብሔር የሞአብ ክፍል ወደ ሆነው ደብረ ናባው ሂድና በሕዝብህ ዘንድ ወጥተህ

8. ሉቃ. ፩፥፴፭፡፡
9. እድኒ የሄኖክ ሚስት ስም ነው፤ EMML III 9M እድና ይላል፡፡
10. አልዮጳሲስ ግብጽ ውስጥ ያለች የጣዖት ከተማ ናት፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ተቀሳቀል። በቀስት ውሃ አልቀደሳችሁኝምና በዚያ ሙት ባለው በሙሴ ነውን?[11] ወይስ የጥጃ ምስል ሠርቶ «እስራኤል፥ እነሆ አማልክቶቻችሁ»[12] ባለ በአሮን ነውን?

እንግዲያውስ ከነቢያት አንዱ ብለው በማን ይመስሉታል? አርዮንን ያስገደለ በአርዮ ሚስት ምክንያት በደልን በድሎ በሞተ በዳዊት ነውን? ከአባቶቻቸው አማልክት በኋላ እስኪያስከትሉት ድረስ ከአሕዛብ ነገሥታት ሁሉ ፫፻ ዕቁባትን በወሰደና ፯፻ ሚስቶች በነበሩት በልጁ በሰሎሞን ነውን?

እንደገና ከነቢያት አንዱ ብለው በማን ይመስሉታል? ወይስ ከኤልዛቤል ፊት ሸሽቶ፦ «ይበቃኛል አሁንም፥ አቤቱ፥ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥም ነፍሴን ውሰድ ብሎ በለመነ በኤልያስ ነውን?»[13] ወይስ ንጉሡ የኤልሳዕ ራስ ዛሬ በላዩ ያደረ እንደ ሆነ እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ ይጨምርብኝ» ብሎ ስለ ነበር ከእስራኤል ንጉሥ መል እክተኛ ፍርሃት የተነሣ አገልጋዩ የቤቱን በር በዘጋ በኤልሳዕ ነውን?[14]

እንደገና ከነቢያት አንዱ ብለው በማን ይመስሉታል? «እኔም ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፥ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል እኖራለሁ»[15] ባለ በኢሳይያስ ነውን? ወይስ ከማጥ ውስጥ እንዳይመልሰው ሲዴቅያስን በተማፀነ በኤርምያስ ነውን? እንደገናም ከነቢያት አንዱ ብለው በማን ይመስሉታል? ስልምናሶር በማረካቸው በፋርስ ነቢያት ነውን? ወይስ በአባቶቻቸው ኃጢአት ምክንያት በምርኮ በአሕዛብ ርኵሰት መካከል በወደቁ ናቡከደነፆር በገዛቸው በባቢሎን ነቢያት ነውን? /እንደገና/ ከነቢያት አንዱ ብለው በማን ይመስሉታል? «ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፥ የጫማውን ጠፍር ለመፍታት አይገባኝም። «እነሆ! የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ። አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል፥ ከእኔም በፊት ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል» ብሎ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር በሆነ በመጥምቁ ዮሐንስ ነውን? በሥጋዊ ልደት ዮሐንስ ኢየሱስ ክርስቶስን

11. ዘጸ. ፴፬፥፳፱::
12. ዘጸ. ፴፪፥፬::
13. ፩ኛ ነገ. ፲፱፥፬::
14. ፪ኛ ነገ. ፮፥፴፩::
15. ኢሳ. ፮፥፭::





በስድስት ወር ይበልጠዋል፥ ከአብ ስለ ተወለደው ልደት፦ «ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔም በፊት ነበር» አለ።[16]

ትእዛዝን በመተላለፋቸው ያነሳናቸውን ስለ ነቢያት ልዩ ልዩ በደልም ያሳሰብነው ትእዛዝን በማፍረስ የበደሉ አሉ። በጋብቻ ሕግ ውስጥ የኖሩ አሉ፥ በዝሙት የወደቁ አሉ። ራሳቸውን ሲያድኑ ሌሎችን ያላዳኑ አሉ፥ ፍርድን [ኩነኔን] በመፍራት የኖሩ አሉ፥ ስለ ኋጥኡ ነቢያት ይህን ሁሉ ያስታወስነው እንዝለፋቸው ዘንድ አይደለም፥ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ምሕረት ከእነርሱ ጋር ነውና። ከኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ በቀር ልቡናው ውስጥ ሽንገላ፥ በሥጋው ውስጥ መጉደፍ፥ በእጁ ውስጥ በደል፥ በአንደበቱ ሐሰት ያልተገኘበት ከኃጢአት የተለየ ሰው ነቢይ ሐዋርያ እንደሌለ እናውቅ ዘንድ ነው እንጂ «ጥፍርና ቀንዱ ካልዘረዘረ ላህም ይልቅ እግዚአብሔርን አገለግለው።»[17] ተብሎ በመዝሙር እንደ ተነገረው «እግዚአብሔርን አገለግለው /ደስ አሰኘው/» የሚል ቃል በአብ ፈቃድ ወልድ ለመሥዋዕትነት የቀረበ ላህም ነው ተብሎ ተተርጉሟል «ቀንድና ጥፍሩ ያልዘረዘረ» የሚለው በጭንቅላቱ ትዕቢት በእጁ በደል የሌለበት ተብሎ ይተረጐማል። እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፥ «የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁ አፉን አልከፈተም»።[18] በእውነት ኢየሱስ ክርስቶስ ዐመፃ የሌለበት አምላክ፥ ኃጢአት የሌለበት ሰው ነው፥ ነውር የሌለበት ላህም እድፍ የሌለበት ንጹሕ በግ ነው። ያላረረ (ሳያር) የተሰጠ ኅብስት፥ ዝቃጭ (አተላ) የሌለው ንጹሕ የወይን ጭማቂ፥ ተወዳጅነት ያለው እጣን፥ የሚያንፀባርቅ ዕንቁ ነው።

የሕዝብን ኃጢአት የሚያስተሰርይ በደል የሌለበት ካህን፥ ለድኾና ለሀብታም ፊት ዐይቶ የማያዳላውን ንጉሥ እንዴት በጸጋ የከበረ አምላክ ይሉታል? ከነቢያት ምኑን አስበለጡት ምክንያቱም እግዚአብሔር ሙሴን «ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ፥ ወንድምህ አሮን ነቢይ ይሁንህ» ብሎታልና።[19] ስለ ነቢያትም እንዲህ ብሏል፦ «እኔ ግን አማልክት ናችሁ፥ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ ብያለሁ።» ስለ ሐዋርያትም እንዲህ ብሏል፦ «እግዚአብሔር በአማልክት ማኅበር ቆመ፥ በአማልክትም መካከል ይፈርዳል።»[20] ይህን ያለው በተነሥኦት እሑድ ምሽት በዝግ በር ገብቶ በደቀ መዛሙርቱ መካከል ስለ ቆመው ወልድ ነው። በጸጋ የእግዚአብሔር

16. ዮሐ. ፩፥፳፯::
17. መዝ. ፷፰፥፴፩::
18. ኢሳ. ፶፫፥፯::
19. ዘጸ. ፯፥፩::
20. መዝ. ፹፩፥፩::



www.ethiopianorthodox.org

ልጅ ስለ መባል እግዚአብሔር ፈርኦንን «ሕዝቤን ልቀቅ፥ እስራኤል የበኵር ልጄ ነውና» ብሎታል። እነርሱን አልለቅም ብለህ ከታበይክ የበኵር ልጅህን እገድላለሁ።

ጌታችንም በወንጌል፦ «እኔ አባታችሁ ነኝ፥ አባቴም አባታችሁ ነው» ብሏል። ዮሐንስም እንዲህ ይላል፦ «ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፥ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድና ከሴት ፈቃድ አልተወለዱም።»[21] ጴጥሮስም እንዲህ ይላል፦ «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በመነሣቱ በቸርነቱ ብዛት ለምንድንበት ተስፋ እንደገና የወለደን የጌታችን ኢየሱስ አባት እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን።»[22] ጳውሎስም እንዲህ ይላል «የእግዚአብሔር መንፈስ የሚወደውን ሥራ የሚሰሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ዳግመኛም በምትፈሩ ግዛት የመገዛትን ሀብት የተቀበላችሁ አይደለም፥ ወልድም መምሰልም የማሰጣችሁን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ፥ እርሱንም አባ አባቴ ብላችሁ ትጠሩታላችሁ እኛ የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ለልቦናችን ምስክሩ እርሱ መንፈስ ቅዱስ ነው። እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆን ወራሾቹ ነን፥ የእግዚአብሔር ወራሾች ከሆንም የክርስቶስ ወራሾቹ ነን»።[23]

ዮሐንስም በመልእክቱ እንዲህ ይላል፦ «ወንድሞቻችን እርስ በርሳችን እንዋደድ ፍቅር ከእግዚአብሔር የተገኘ ነውና የሚዋደድ ሁሉ እርሱ ከእግዚአብሔር ተወለደ፥ እግዚአብሔርን ያውቀዋል።»[24] እነሆ በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ ስለ ተባሉትና በህብተ መንፈስ ቅዱስ አማልክት ስለ ተባሉት ነገርናችሁ። ዳዊትም እንዲህ ይላል፦ «የአማልክት ልጆችን ለእግዚአብሔር አምጡ፥ የጊደር ልጅ ለእግዚአብሔር አምጡ፥ የጸናች አራት እንዲህ ትላለች አማልክትን [ነቢያትን] አትንኳ፥ የሕዝብ ህንም መሪ ክፉ ነው አትበለው። ጌታችንም በቃል ኪዳን ከሰዎች ዘንድ አማልክት ይሆኑ [ይባሉ] ዘንድ ለሚያምኑብህ ትሰጣለህ፥ የቀና ልቡናን የምትፈጥር ነህ።

21. ዮሐ. ፩፥፲፪።
22. ፩ኛ ጴጥ. ፩፥፫።
23. ሮሜ. ፰፥፲፬-፲፯።
24. ፩ኛ ዮሐ. ፬፥፯።
25. መዝ. ፹፪፥፩።





ስሉ ሆይ! በብሉይም በሐዲስም በጸጋ አማልክት ስለ ተሰኙትና በህብተ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ[26] ስለ ተባሉ፥ እነሆ ነገርን ስለዚህ በባሕርይ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንን ለኢየሱስ ክርስቶስ ተውለት፥ የእግዚአብሔርን ልጅ የዮሴፍ ልጅ የምትለው ንስጥሮስ ሆይ! አፈር፣ አፈር እንጂ እነሆ፥ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው።»[27] እያለ አባቱ ይጠራዋል። «የአምላክን ልጅ በፋኪቤ ተወለደ» የምትለው ንስጥሮስ ሆይ! አፈራ! አፈር።

ኢሳይያስ ስለ ልደቱ ምስክር ሆኖ አስምቶ ይጮኻል። እንዲህ ይላል፦ «እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ [ወልድን] ትወልዳለች፥ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።»[28] «ዐማኑኤልን በወንድ ዘር ተፀነሰ» የምትል ንስጥሮስ ሆይ! አፈር (ኩም) በል! እነሆ፥ ነቢዩ ዳዊት ስለ እርሱ እንዲህ ይናገራል። «እንደ ዝናም ጠብታ መስክ ላይ /በምድር ላይ/ እንደ ሚንጠባጠብ ጠብታ ይወርዳል። በዘመኑም ጽድቅ ይገኛል። ጨረቃም እስኪያልፍ ድረስ ሰላም ይበዛል። ብዙ ከባሕር እስከ ባሕር ድረስ ከወንዞችም እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ይገዛል። በፊቱም ኢትዮጵያ (የኢትዮጵያ ሰዎች) ይሰግዳሉ። ጠላቶቹም አመድንም ይቅማሉ።»[29] እንደ ዝናብ በታጨደ መስክ ላይ በምድር እንደሚንጠባጠብ ጠብታ ይወርዳል ማለቱ ግን ወደ ድንግል ማርያም የወልደ እግዚአብሔርን መውረድ ያመለክታል።

እግዚአብሔር በአራት ዘዳግም እንደተናገረው። «ሰማይት ሆይ! አድምጥ እኔም እናገርሃለው፥ ምድርም የአፌን ቃል ትስማ፥ ትምህርቴንም እንደ ዝናብ ተስፋ ታድርገው፥ ነገሬ እንደ ጠል ይውረድ።»[30] ፀምር ግን በቅድስት ድንግል ማርያም፣ ጠልም በማሕፀኗ ባደረ በእግዚአብሔር ቃል ይተረጐማል። ጌድዮን ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክት እንዲህ ሲል ጠየቀ። «እነሆ፥ በአውድማው ላይ የተባዘተ የበግ ጠጉር አዘረጋለሁ፥ በጠጉሩ ብቻ ላይ ጠል ቢወርድ ምድሩም ሁሉ ደረቅ ቢሆን እንደ ተናገርህ የእስራኤልን ልጆች በእኔ እጅ እንደምታድናቸው ዐውቃለሁ አለ። እንዲሁም ሆነ፥ በነጋውም ማልዶ ተነሥቶ ሄደ፥ ጠጉሩንም ጨመቀው፥ ከጠጉሩም የተጨመቀው ጠል ቆሬ ገንዳ ሙሉ ውሃ ሆነ። ጌድዮንም

26. ዘጸ. ፳፱፥፳፰፤ የሐዋ. ፳፫፥፳።
27. ማቴ. ፫፥፲፯።
28. ኢሳ. ፯፥፲፬።
29. መዝ. ፸፩፥፮-፲።
30. ዘዳ. ፴፪፥፪።



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔርን፦ እኔ ይህን አንድ ጊዜ ስናገር አትቈጣኝ፤ እኔ ይህን አንድ ጊዜ በጠጕሩ፤ እባክህ፤ ልፈትን፤ አሁንም በጠጕሩ፤ እባክህ ልፈትን፤ አሁንም በጠጕሩ ብቻ ላይ እባክህ ደረቅ ይሁን፤ በምድሩም ሁሉ ላይ ጠል ይሁን» አለው። እግዚአብሔርም በዚያ ሌሊት እንዲሁ አደረገ፤ በጠጕሩ ብቻ ላይ ደረቅ ነበር፤ በምድሩም ሁሉ ላይ ጠል ነበር።»[31]

ዐይነ ኅሊናው የታወረ ሰው የመጻሕፍት ሆድ ውስጥ የተከበበውን የተሸሸገ ምስጢር አይመለከተውም። ከነቢያትና ከሐዋርያት አፍ የከበሮ ከል [ቆዳ] ያስተጋባል፤ ይጮሐል፤ አገዛ ልቡናው ወደ ደነቆረ ሰው ግን አይገባም። የብረት መወርወሪያ ቢጸና በአንጥረኛ ይከፈታል። ጠንካራ ብረት በእሳት መጋረጃ ይቀልጣል። የሰነፍን ልብ ግን በመጻሕፍት ቃልና በጥበባዊ ቃል መክፈት የሚቻለው የለም። እንደ ነፋስ ቀቅሽ መጻሕፍትን በአፍ በማንበቡ ሰነፍ ይመካል። በውስጡ ያለውን ግን አያውቀውም። ወደ ተዘጋው ንጉሥ ቤት ሳይገባ በንጉሥ ቤት ያለውን መዝገብ የሚያይ ሰውን ይመስላል። ስለ ንጉሥታት ገንዘብ ለሚጠይቅ ሰው ምን ይመልስለታል? እነሱ ግን መጻሕፍትን ከመመርመር ከማወቅ የራቁ ሲሆን መምህራን ተብለዋል። በወርቅ ቅጠል የተለበጡና በፈርጥ የተሸለሙ የአረማውያን ነገሥታት አጽሎችን ከሚከተሉ የእባ ጠን ሰዎች የማይተናነሱ ናቸው። ምንጣፍ ላይ የሚቀመጡ በምትሐት የተሸፈኑ ናቸው። ውስጣቸው ግን በረከሰ የእንስሳት ዐፅምና ከተቀረጠ ግንድ የተመላ ነው። የሸቱ ዕጣን አያሳረ ጉላቸው የዕጣኑ መዓዛ ከአፍንጫቸው አይደርስም። ከመሥዋዕታቸው ስብ አይበሉም። ከወይናቸው ጠጅ አይጠጡም። በሚገፉቸው ላይ አይከፋም፤ የሚታመኑባቸውንም አይረዷቸውም። በሆነቱ [በጥዛ] አማልክት ይባላሉ። እነዚህም መምህራን ከቃለ እግዚአብሔር የተጠሙ ሲሆኑ በሆነቱ መምህራን ይባላሉ። እንግዲህ ወደ እነሱ የመጣውን እንዴት ያረኩታል?

ከነቢያትና ከሐዋርያት አፍ ያልተቀዳ፣ የደፈረሰና የተበላሸ ውሃ ያጠጧአቸዋል። ምክንያቱም ነቢያት ያለ መንፈስ ቅዱስ ሥልጣን በራሳቸው ፈቃድ መምህራን አልሆኑም። ሐዋርያትንም መንፈስ ቅዱስን ሳይቀበሉ ለማስተማር አላሰለጠናቸውም። መንፈስ ቅዱስን እንደ ጠል በጽድቅ አስተማሩ፤ በጽናትም ሰበኩ፤ ዛሬ ግን የክርስቶስን መንጋ ይበትኑ ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ጡት ሳይደጉ ቃለ እግዚአብሔርን ሳይቀምሱ መምህራን መባልን ይፈቅዳሉ።

31 መሳ. ፮፡፴፮-፵።





የጌዴዎን ፀምርን ወደ መተርጐም እንመለስ። ጌዴዎን ያልተሸመተ ንጹሕ ፀምርን ዘረጋ። ከእግዚአብሔር ዘንድ ጠል ወደ ፀምሩ ይወርድ ዘንድ ምልክት ጠየቀ፤ ምድር ሁሉ ከዝናም ነጠብጣብ ደርቃ ሳለች እግዚአብሔር ጌዴዎን እንደ ጠየቀው አደረገ። ስለዚህ ዳዊት በትንቢት እንዲህ ሲል ተናገረ፦ በምድር ላይ እንደሚንጠባጠብ ጠብታ ይወርዳል። ምድር ሁሉ ደርቃ ሳለች የጠል ብቻዋን ወደ ፀምር መውረድ የጠል ወደ ፀምር መውረድ በመለኮት ወደ ድንግል ማሕፀን መውረድ ይተረጐማል። ሌሎች ሴቶች ቢኖሩም በአርያም ነጠብጣብ ኀይል ያልተነኩ ናቸው።

ዳግመኛ ጌዴዎን ጠል ወደ ምድር ሁሉ ይወርድ ዘንድና ፀምር ብቻዋን የደረቀች ትሆን ዘንድ ለመነ። እንደገና ጌዴዎን እንዳለው እግዚአብሔር አደረገ። ይህ በዓለም ላይ ባሉ ሴቶች ማኅፀን የሚሆን በልማድ ዘር ወደ መዋለጃ መውረድ ተብሎ ይተረጐማል። ድንግል ግን ከዚያ የዘር ነጠብጣብና ከርስሐት ተከልክላ በሥጋ ጥልቀት ንጽሕት ነች።

በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ከብቻው እግዚአብሔር እንደ ተወለደ ዳግመኛ የእግዚአብሔር ልጅ ከብቻዋ የዳዊት ልጅ ብቻውን ተወለደ። በመጀመሪያ የማይታየው ከማይታየው ተወለደ። በኋላኛው የማይዳሰሰው የሕይወት እሳት ከምትዳሰስ ሥጋ ተወለደ። በመጀመሪያ ጥንተ ህላዌው የማይታወቅ ተወለደ። በኋለኛው የዘመናት ፈጣሪና የዓመታት ወሰኝ፤ ዕድሜዋ ፲፫ ዓመት ከሆነ ከትንሽ ልጅ ተወለደ። የመጀመሪያ ልደቱን ምስጢር አደረገ [ሰወረ] የኋለኛ ልደቱን አስደነቀ። የመጀመሪያ ልደቱን ፍጡራን እንዳናውቀው በመሰወሩ መግነዙ ጠቀለለው። ኋለኛ ልደቱን ለአረኞች ገለጸ፤ ለጥበብ ሰዎችም ዐሳየ። ያለ ወንድ ዘር ከሴት የሰው መወለድ ከዚያ አስቀድሞ አልሆነም፤ ከዚህ በኋላም አይሆንም።

ከብቻዋ ሴት ፍጹም ሰው ሆነ እንጂ፤ በምድር ላይ አባት ስለሌለው ሰው የመሆን ሥርዐትን ያኈደለ አይደለም። እናት ሳይኖራት ከአዳም ጐን ፍጽምት ሴት እንደ ወጣች ፍጹም ሰው ሆነ። የሔዋንን ሥጋ ለማነጽ ከአዳም ጐን አንዲት ዐፅም ብትነሣ የአዳም የጐኑ አጥንት እንዳልጐደለ ከበስተኋላዋ የሴቶች ጠባይ የትስብእት ጐዳና አልተጓደለም። እንደዚሁም



www.ethiopianorthodox.org

ስለ ወለደችው የድንግል ማርያም ማኅተመ ድንግልናዋ አልጐደለም:: አዳም የጐኑ ዐፅም ሲነቀል የጻዕር ሕማም አልተሰማውም፡ (አላገኘውም) እግዚአብሔር ከባድ እንቅልፍን ሰጥቶታልና (ጥሎበታልና):: እንደዚሁም የድንግል የሥጋዋ ማኅተም የተዘጋ ሲሆን ድንግልን የወሊድ ሕመም አላገኛትም:: ሰይጣን እግዚአብሔርን ተፎካክሮ የራሱን ክብር ያጸና ዘንድ ወደደ::

የማይመጥነውን አሰበ፡ የማይገባውንም ፈለገ:: ይህን ያህል ለ[illegible] በእውነት መከራ ይገባዋል:: ይህን ያህል የዓመፃ መክንን ለሆነ በእውነት መንጸፈ ደይን ይገባዋል:: ለእንደዚህ ያለ የሐሳብ ትእቢተኛ የእሳት እስር ቤት ይገባዋል:: ከዚህም በኋላ ወደ እባብ ገባ:: በሔዋን ጆሮ እያንሾካሾከ ፈተናት:: ዕፀ ሕይወትን በልታ ከገነት እንድትሰደድ አግባባት:: አምላክ እንደምትሆን ተስፋ ሰጣት:: ትእዛዙን በሰማች ጊዜ የፈጣሪዋ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ታጐለ፤ አዳምም የሚስቱን የሔዋንን ትእዛዝ በሰማ ጊዜ የእግዚአብሔር ጸጋ ከእርሱ ላይ ራቀ::

የእግዚአብሔር የፍርዱ ውሳኔ ድንቅ ነው:: ምክንያቱም፡- «አዳም ሆይ! ወዴት ነህ ያለኸው?» ብሎታልና:: እርሱም አለ፡- «በገነት ስትመላለስ ድምፅህን ሰማሁ፡ ራቁቴንም ስለሆንሁ ፈራሁ፤ ተሸሸግሁም::» «እግዚአብሔርም አለው ራቁትህን እንደ ሆንህ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን? አዳምም፡- ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ:: እግዚአብሔር አምላክም ሴቲቱን፡- ይህ ያደረግሽው ምንድን ነው? አላት:: ሴቲቱም አለች እባብ አሳተኝና በላሁ:: እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው፡- ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ፡ በሆድህም ትሄዳለህ፤ አፈርንም በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ትበላለህ::»[32]

እግዚአብሔር እንደ አዳምና ሔዋን እንደጠየቃቸው እባብን በደኋን ሳይጠይቅ እርግማንን አስቀደመ:: ምክንያቱም የኃጢአት መሠረት ከእባብ እንደ ወጣ ያውቃልና እንደገና እግዚአብሔር ሰይጣንን ተቃወመው:: ሰይጣን እናታችን ሔዋንን በመምከር ሞትን እንዳመጣ እንደዚሁ እግዚአብሔር በእናታችን ድንግል ማርያም ሕይወትን አመጣ:: ስለ ሴት

32. ዘፍ ፫፥፱-፲፱::





እንደ ተሰደድን ስለ ሴት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተጠጋን ሆነን:: ዲያብሎስ አዳምና ሔዋን አምላክ እንደሚሆኑ ተስፋ እንደ ሰጣቸው እንደዚሁ ገብርኤል ማርያምን በሥጋዋ አምላክን እንደ ምትወልድ ተስፋ ሰጣት:: እግዚአብሔር ዕፀ በለስን በመብላታችን እንደነቀፈን፤ እንደዚሁ በዕፀ መስቀሉ ይቅር አለን:: በገነት ዛፎች መካከል የአዳም ዕርቃን ሥጋ እንደ ተገለጠ እንደዚሁ የመድኀኒታችን እርቃን ሥጋው በእስራኤል ጭፍሮች ጉባኤ መካከል ተገለጠ:: «አዳም ሆይ! መጀመሪያ መሬት ነህ፡ ተመልሰህ ወደ መሬት ትገባለህ፡ የሞት ፍርድ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ወጣ እንደዚሁ ከሐናና ቀያፋ ዘንድ በመድኀኒታችን ላይ የሞት ፍርድ ወጥቷል፡ ምክንያቱም «እኛ ሕግ አለን፤ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጓልና በሕጋችን ሊሞት ይገባል ብለዋል::[33] እግዚአብሔር ኪሩቤልንና ሱራፌልን የዕፀ ሕይወትን መንገድ አዳም ወደ ርስቱ እንዳይገባ ይጠብቁ ዘንድ እንደሾማቸው እንደዚሁ ጠባቂዎች ደቀ መዛሙርቱ መጥተው በሌሊት እንዳይሰርቁት ከሙታን ተነሣ እንዳይሉ ከጲላጦስ ወታደሮችና ከሊቃነ ካህናት መቃብር ጠባቂዎች ተሰበሰቡ:: እግዚአብሔር በልጁ ሞት አዳምን ይቅር ባለው ጊዜ ሱራፌልና ኪሩቤል አዳምን ወደ ገነት እንዳይገባ መከልከል አልቻሉም:: እንደዚሁ የጲላጦስ ወታደሮችና ሊቃነ ካህናት ጌታችን ከሙታን ተነሥቶ በአባቱ ቀኝ መቀመጥን መከልከል አልቻሉም::

ወንጀለኛው (በደለኛው) ንስጥሮስ ሆይ! ፈጣሪን የዮሴፍ ልጅ ባልከው ጊዜ ልሳንህ ከጉሮሮህ ተጣብቆ እንደበትህ እንዴት አልተዘጋም? ይህን ካልክ በኋላ የአፍህን [እንደበትህን] እስትንፋስ ያልዘጋው የእግዚአብሔር የትዕግሥቱና የዝምታ ክብሩ ምን ያህል ቢረዝም ነው? እኔስ ከአንተ የሥቃይ ፍርድ ይልቅ የሰቀሉት የሥቃይ ፍርድ ያነሰ ይሆን ዘንድ በፈረድኩ ነበር:: እነሱስ ለእግዚአብሔር መንግሥት የቀኑ መስሏቸው ባለማወቅ መከራ አጸኑበት፡ በመከራው ዕለት ነፍሱ ከሥጋው በተለየች ጊዜ፡- «አባት ሆይ! የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» ብሎ ራሱ እንደ ተናገረ::[34] ጳውሎስም እንዲህ ብሏል «አውቀውስ ቢሆን የክብር ጌታን ባልሰቀሉት ነበር::[35] አሪትም እንዲህ ትላለች፡- በሚመጣው ዘመን ሳይወቁት ያውቁት ዘንድ አላሰቡትም::» ንስጥሮስ ሆይ! አንተ ግን

33. ዮሐ. ፲፱፥፯::
34. ሉቃ. ፳፫፥፴፬::
35. ፩ኛ ቆሮ. ፪፥፰::



www.ethiopianorthodox.org

የነቢያትን ቃል በውቀህ ለሐዋርያት ትምህርት በመምህርነት ተሹመሃል። በልብህ ውስጥ ስንዴ ተዘርቶ በልብህ ክፉት እንክርዳድ አደረግኸው። በጓሮህ ውስጥ የወይን ሐረግ በቅሎ በትምህርትህ ቃል እሾህን አፈራ። ሁሉንስ ካድክ የወንጌላዊውን ቃል ትክዳለህን? ኢየሱስም ሲያስተምር ሲጀምርም ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ሆኖት ነበር። እንደ መሰላቸው የኤሊ ልጅ የዮሴፍ ልጅ ቢሆን ኖሮ ኢየሱስ «የዮሴፍ ልጅ እንደ መሰላ ችው።»[36] አይልም ነበር።

ዳግመኛ ወንጌላዊው እንዲህ ይላል፡- «የዐሥራ ሁለት ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ እንደ በዓሉ ሥርዐት ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ፤ ቀኖቹንም ከፈጸሙ በኋላ ሲመለሱ ብላቴናው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር፤ ዮሴፍም እናቱም አላወቁም ነበር። ከመንገደኞች ጋር የነበረ ስለ መሰላቸው የአንድ ቀን መንገድ ሔዱ፤ ከዘመዶቻቸውም ከሚያውቋቸውም ዘንድ ፈለጉት፤ ባላገኙትም ጊዜ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። ከሦስት ቀን በኋላ በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸውም ሲጠይቃቸውም በመቅደስ አገኙት፤ የሰሙትም ሁሉ በማስተዋሉና በመልሱ ተገረሙ። ባዩትም ጊዜ ተገረሙ፤ እናቱም፡- ልጄ ሆይ፤ ለምን እንዲህ አደረግህብን? እነሆ፤ አባትህና እኔ እየተጨነቅን ስንፈልግህ ነበር አለችው። እርሱም፡- ስለምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን? አላቸው።»[37]

ይቺስ እውነተኛ እናቱ ናት። ዮሴፍ ግን በሥጋዊ ዝምድና እንጂ በዘር በመወለድ አባቴ አይደለም። የእመቤታችን የአባቷ አባትና የዮሴፍ የአባቱ አባት ወንድማማቾች ናቸው። ስለዚህ ማርያምን በንጽሕና ይጠብቃት ዘንድ ሰጡት። ከአባቶቻቸው ነገድ ርስት ከአንዱ ነገድ ወደ ሌላው ነገድ እንዳይፋለስ የአባቶቻቸውን ርስት ይወስዱ ዘንድ ከትርብ ከአባ ቶቻቸው ነገድ እንዲያገቡ በአራት የሰለጳአድ[38] ልጆች እስከሚደ ርጋቸው ድረስ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደታዘዘላቸው። እመቤታችን ማርያም ወንድምና እኅት የላትም። ምክንያቱም የእመቤታችን ማርያም

36. ሉቃ. ፫፥፳፫።
37. ሉቃ. ፪፥፵፩-፵፱።
38. ሰለጰአድ አምስት ሴቶች ልጆች የነበሩት የምናሴ ነገድ ሰው ነው። (ዘኁ. ፳፮፥፴፫፤ ኢያ. ፲፯፥፫) ሰለጰአድ አምስት ሴቶች ልጆች [illegible] ሴቶቹ ልጆች ርስት እንዲወርሱ ብለው ሙሴን ለመኑት ተሰጣቸውም። ዘኁ. [illegible] ሴቶቹ ልጆች ርስት [illegible] እመቤታችን ድንግል ማርያምም በልበ ሥጋሴ የተመረጠች በመሆኗ ከአባቷ ነገድ የሆነ ዘመዷ ዮሴፍ እንዲጠብቃት መሰጠቷን በንጽጽር ለመግለጥ ሴቱ የሰለጰድን ልጆች በንጽጽር እንድናቀርብ ልብ ልብ ይሏል።





እናትና አባት ከእርሷ ሌላ ልጅ አልወለዱም። ስለዚህ የአባቷ ርስት ወደ ሌላ ነገድ እንዳይፋለስ እርሷን ለዮሴፍ ሰጡ። እመቤታችንና ዮሴፍ ሁለቱም የዳዊት ዘር ናቸው። ስለዚህ «እነሆ! አባትህና እኔ እየተጨነቅን ስንፈልግህ ነበር» አለችው። «በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን?» ብሎ ወልደ እግዚአብሔር በአባቱ ሰማያዊ መሆኑን አሳወቀ፡- እግዚአብሔር በአባቴ ሰማያዊ እንደ ሆነ አስረዳ። ወንጌላዊው እንደ ተናገረው፡- «ኢየሱስም ጅራፍ አዘጋጅቶ ወደ መቅደስ ገባና በመቅደስ የሚሸጡትን የሚገዙትን ሁሉ አስወጣ፤ የገንዘብ ለዋጮችን ገበታዎች የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠ። ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፏል አላቸው። እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችኋት አላቸው።»[39] ብሎ ወንጌላዊው እንደ ተናገረ ቤተ መቅደስ የአባቱ ቤት ናት።

ወደ ወንድሜ አረጋዊና ወደ ንጽሕት ድንግል ጥንተ ዜና እንግባ። የዳዊት ሴት ልጅ ከዳዊት ልጅ ዘንድ ገባች። ንጽሕት ርግብ ከየዋህ በግ ዘንድ ገባች። የታተመች መጽሐፍ ማንበብ ለማይችል ሰጡት። እርሱም ማንበብ አልችልም አለ። የታተመ መጽሐፍ በቅድስት ድንግል ማርያም ይተረጐማል። የተሰጠች ሀብት ከቤተ መቅደስ ወደ ዮሴፍ ቤት በመሰጠቷ ይተረጐማል። «ማንበብ አልችልም» የሚለው ዕንቍን ባለማወቅና በሥጋ ባለመቅረቡ ይተረጐማል። «እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች።»[40] ብሎ ወንጌላዊው እንደ ተናገረ። ቅርንጫፉ ሳይቋጠል እሳቱ ሳይጠፋ እሳተ መለኮትን የወለደች ዕፀ ጳጦስ ይህች ናት።

ነቢዩ ኢሳይያስ፡- «ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፤ ከሥሩም ቁጥ ቋጠ ያፈራል። የእግዚአብሔር መንፈስ ያርፍበታል።»[41] ብሎ ስለ እርሷ የተናገረላት የሃይማኖት በትር ይህች ናት። ሰባት ማብረያ ያላት የወ ርቅ መቅረዝ ይህች ናት። ይኸውም ሰባት የተባለው አምስቱ የሙሴ መጻሕ ፍት ከመለኮት ወንጌልና ከሐዋርያት የትምህርታቸው ቃል ጋር ተደምሮ

39. ዮሐ. ፪፥፲፬-፲፮።
40. ማቴ. ፩፥፲፰።
41. ኢሳ. ፲፩፥፩።



www.ethiopianorthodox.org

ነው። በላይ ያሉት ሰባቱ ቅርንጫፎች የሰባቱ ሥዩማን ቤተ ክርስቲያን ምሳሌዎች ናቸው። የዚይቱ ቅባት ግን የሃይማኖት ኀይል ነው። የመብራቱ ፈትል የክርስቶስን ብርሃን የሚቀበል ልብ ነው። ስለዚህ ዮሐንስ አበቀለምሲስ በእጆቹ ሰባቱን ከዋክብት አጽንቶ በሰባቱ የወርቅ ማብራያ መካከል የሚቀመጠው እንዲህ ይላል፡- «የመንፈስ አባታችን የማን በራችን አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የእምነታችን ሥር፥ የሃይማኖታችን ምሰሶ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በመለኮቱ የእግዚአብሔር ልጅ በሥጋው የሰው ልጅ ነው።[42] በክብር በምስጋና ከወለደው አባቱ ጋር እኩል ትክክል ነው። ከሁላችንና ከሁላችሁ ጋር ዘላለም ይኑር። አሜን።

የክርስትናውን ጥምቀት ያፈረሰ ጽጽስናውን ያረከሰ ልቡናው የጠፋ የንስጥሮስ ዘለፋው ተፈጸመ። የቤተ ክርስቲያን ምስኪኗ፥ በውስጧ ተወልዶ በዓለም ያደገ፥ በየማእዝኗ ሃይማኖትን የሚሰብክ፥ ስለ ማርያም ምም፣ አምላክን በድንግልና እንደ ወለደች ዜናን የተሸከመ ነው። በሀገራችንም ይህችን መጽሐፍ ያሳመራት በልቡናው ደካማ ሲሆን ጊዮርጊስ በገና ዕለት ትንበብ ዘንድ አዘዘ፥ በብርሃት ደመና /በባሕርይ ክብሩ/ ለሚመጣ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል። ለዘለዓለሙ አሜን።

42. እመቤታችን ወላዲተ አምላክነቷ በምሥጢረ ሥጋዌ በዳግራዊ ልደቱ እንጂ በምሥጢረ ሥላሴ በቀዳማዊ ልደቱ አይደለም። እኮ ወልደ ማርያም በመለኮቱ በእንበለ ዳዕሙ በሥርዐተ ትስብእቱ ያለማ አብ። ራእ ፲፬፡፲፬።





# [ምዕራፍ ፯]

## የልደት ምንባብ

በሦስትነቱ አንድ የሚሆን፣ በአንድነቱ ሦስት የሚሆን በመለኮት የተካከለ በህልውና አንድ የሆነ አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት የማይባሉ በአንዲት ፈቃድ የተዋሐዱ በጥምረት (በተዋሕዶ) የተያያዙ በመብረት ምስጋና የተጋረዱ በእሳት የተሸፈኑ፥ አንዱ ከሁለተኛው ሁለተኛው ከሦስተኛው የነፋስ ፋጫ ያህልና የዐይን ጥቅሻ ያህል የማይ ቀድም፥ ከመላእክትና ከሰው ዘንድ በአንድነት ለሚሰገድለት ለእግዚ አብሔር ስም በመጀመሪያው ያለ ጥንት ለኋለኛው ያለ ፍጻሜ ለዘላለም ምስጋና ይሁን። አሜን።

«የክርስቶስ ህልውና ከማርያም ወዲህ ነው። ከዚያ ከአብ ህልውና አይደለም» የሚል የፎጢኖስን[1] ዘለፋ ከእንግዲህ እንጽፋለን። የሰብል ያኖስ (ሰባልዮስ) የአርዮስ፥ የፎጢኖስ የልባቸው ፍላጐት አንዲት ናት። የወልድን ከአብ መሆን ለማጉደልና ህልውናውን ለማክፋፋት በአፋቸው የሃይማ ኖት አተረጓጐም ባይተባበሩም በዐይነ ልቡና ግን ይናበባሉ (ይተያያሉ)። አርዮስ፡- «ስለ ድኅነታችን ከማርያም የተወለደው ክርስቶስ ፍጡር ነው» ይላል። «አዳም ከመሬት አፈር እንደ ተፈጠረ፣ ሔዋንም ከአዳም የጐን አጥንት እንደ ተፈጠረች ልቡናው እየታዘበው፣ እንዲሁም ክርስቶስም ከድንግል ማሕፀን ተፈጠረ፥ ስለ ድኅነታችንም ተወለደ» ይላል። እነሆ! በአብ ትእዛዝ ከድንግል ማርያም እንደ ተፈጠረ የነገሩን መንገድ ዐሳየ።

ሰብልዮኖስ፣ «አብ እንደ ሰው፥ ወልድ እንደ አንደበቱ ንባብ (ቃል)፥ መንፈስ ቅዱስ እንደ አፉ እስትንፋስ ነው።» ይላል። ስለዚህ አንድ ገጽ ይላል። ገጹን ግን ብቻውን በአብ አጸና፥ ወልድንም ለዐይን የማይታይ በጆሮ እንደሚደመጥ ንባብ አደረገው፥ መንፈስ ቅዱስንም ወዲት እንደሚሔድ የማይታወቅ ለእይታ በማይቻል እንደ አፍ እስትንፋስ አደረገው።

ለወልድ መልክ እንዳለው ለመንፈስ ቅዱስም እንደ አብ መልክ እንዳለው ከመጻሕፍት ምስክር አቀረብን [አደረስን]፥ በፎጢኖስ በዘለፋ መጽሐፍ

1 ፎጢኖስ በአራተኛው መቶ ክ/ዘመን የነበረ ሲሆን የጳውሎስ ሳምሳጢን የኑፋቄ ትምህርት አድሶ «ወልድ ወይም ቃል በአካል የተገለጠው ከማርያም በተወለደ ጊዜ ነው» በማለት ያስተምር ነበር። አባ ጎርጎርዮስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ ፫፱።



www.ethiopianorthodox.org

ለእርሱም ኅሊናው እየታዘበው /እየወቀሰው/ «የወልድ ህልውና ከማር ያም ወዲህ ነው፡፡» ታገበ «የአብ መልእክት እንደ ገብርኤል ቃል ከማ ርያም ተፀነሰ» አለ፡፡ ከአብ ጋር ህልው የሆነ ወልድ በመልአኩ በገብርኤል ብሥራት ከማርያም ሰው ሆነ አይልም፡፡ እነሆ! የሁሉም፡ የሃሳቱም፡ የስንፍናቸው ሐሳብ አንድ ሆነ፡፡ በኅብረት ተካክለው በደሉ፡፡

ፎጢኖስ ሆይ! ከሴት የተወለደው እርሱ ፍጹም የእግዚአብሔር ልጅ ካልሆነ ወልድን ብታመልከው ምን ትጠቀማለህ?[2] እርሱ ቅድመ ዓለም እንዳልነበረ ልብህ እየታዘበ ፍጡርን ብታመልክ ምን ትጠቀማለህ? ፎጢኖስ ሆይ! ፈጣሪን ፍጥረት የሚል የከሐድያን አለቃ የአርዮስን አሥር የውሻ ጅራት የተከተልክ ነህ፡፡ አንተም «የወልድ ህልውና ከማርያም ወዲህ ነው» ትላለህ፡፡ አርዮስ በክሕደት ቀደመህ፡ አንተም በስድብ ተከተልከው፡፡ አርዮስ በጥፋት ትምህርት አለቃ ሆነህ፡ አንተም በጥፋት ልብህ ጅራት ሆንክ፡ ምክንያቱም አንገት ወደ ገባበት ጅራት ይከተላል፡፡

የሐሰት ተክል ፎጢኖስ ሆይ! የተተከልክበትን ሥር ወደታች አትስ ደድ፥ ወደላይም አታብብ፥ ለዘላለም ፍሬ አይገኝብህ፡፡ ፎጢኖስ ሆይ! መርዝ የተመላ የጥፋት ጽዋን ከወዴት ጠጣህ? የስሕተት ስካር ልብ ህን አዞረው፡ የኃጢአት እንቅልፍ ቅንድቦችህን ከደናቸው፡፡ ፍጢኖስ ሆይ! ክፉ አውሬ ከወዴት አገኘህ? መራራ አጻኝ ልብህን ሰደበን በተመላ በስሕ ተት ጦሩ /ቀስት/ ልብህን ነደፎ በልብህ ውስጥ መርዝ ጨመረ፡፡ ከዚህ በኋላ የምትናገረውን አላወቅህም፡ የምታወራውንም አላሰብክም፡፡ በዓመፃ ነገርህ «የክርስቶስ ህልውና ከማርያም ወዲህ ነው» ትላለህ፡፡ ይህን ከምትናገር እንደበትህ ድዳ ቢሆን ከንፈሮችህ ቢዘጉ በተሻለ ነበር፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ይሁዳ፡- «ይህ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር፡፡»[3] ብሎ እንደ ተናገረው ይህን ከአባትሕ ወገብ ባትወጣ ከእናትህ ማሕፀን ባትረጋ

2. EMML III ፎጢኖስ ሆይ የፈጠራችን ባሕርይ ብታመልክ ጥቅሙ ምንድነው፤ ፎጢኖስ ሆይ ከእርሷ የተወለደው ፍጹም የእግዚአብሔር ልጅ ካልሆነ ሴትን ብታመልካት ጥቅሙ ምንድን ነው?
EMML VII,VIII፡- ፎጢኖስ ሆይ የፍጡራችን ባሕሪያቸውን ብታመልክ ጥቅሙ ምንድን ነው? ፎጢኖስ ሆይ የተወለደውን እግዚአብሔር ብታመልከው ጥቅሙ ምንድን ነው?
EMML IX, X፡- ፎጢኖስ ሆይ የፍጡራችን ባሕርያቸውን ብታመልክ ጥቅሙ ምንድነው፤ ፎጢኖስ ሆይ የምታመልከው ከሴት የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ ካልሆነ ጥቅሙ ምንድ ነው?
EMML I, IV add፡- ፎጢኖስ ሆይ የፍጡራችን ባሕርያቸውን ብታመልክ ጥቅሙ ምንድን ነው? ይላል ... የሚለው ባሕርይ ተብሎ ተተርጉሟል፡፡
3. ማቴ ፳፮፡፳፬፡፡





ይሻልህ ነበር፡፡ ይህን ከምትናገር እንደ ናቡከደነፆር አውሬ ብትሆን፡ እንደ ሎጥ ሚስት የጨው ሐውልት ብትሆን ይሻልህ ነበር፡፡ ይህን ከምትናገር ከመኖር አለመኖር ይሻልህ ነበር፡፡

ፎጢኖስ ሆይ! ሰይጣን በአፉ እስትንፋስ አፍህ ውስጥ ተነፈሰ፡ አንተም የሰይጣን ዕንዚራ ሆንክ፡፡ ሰይጣን በማስናከያው መታህ፡ አንተም ለሐሰት መንፈስ መሰንቆ ሆንክ፡፡ አጋንንት እንደ ወደዱ መጫወቻ እንዲ ያደርጉህ የአጋንንት አርጋኖን ሆንክ፡፡ ሰይጣን በአንገትህ ላይ ቀንበሩን አስተምሮ እንደ እንስሳ ጠመደህ፡፡ በመጫወቻ ልጓሙ ገዝቶህ በላይህ ተቀመጠ፡ አንተም የሰይጣን ሠረገላ ሆንክ፡፡ ሰይጣን በክርስቶስ ደም ከመገዛት አውጥቶ የራሱ ባሪያ አደረገህ፡፡ ሰይጣንም የክርስቶስን የቅድመ ዓለም ልደት ክደህ «ህልውናው ከማርያም ወዲህ ነው» በል አለህ፡፡

እንደ ገብርኤል ቃል ከማርያም ሰው እንደ ሆነ ትጠራጠራለህን? የገብርኤል ጌታስ ከእርሷ ሰው እንደ ሆነ አታውቅምን? የሥጋዌውን ብሥ ራት ያበሠራት ዘንድ አገልጋዩን ወደ አገልጋዩ ላከ፡፡ መልአኩ፡- «ደስ ይበልሽ፡ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው፡ እነሆ! ትፀንሻለሽ፡ ወንድ ልጅ ንም ትወልጃለሽ» አላት፡፡ «ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?» አለችው፡፡ እነሆ! የዳዊት ልጅ እውነት ተናገረች፡፡ ምክንያቱም ከዚህ አስቀድሞ እንደዚህ ያለ ዕንስ አልሰማችም፡ ስለዚህ መልአኩ «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል» አላት እንጂ ዘካርያስን እንደ ነቀፈ አልነቀፋትም፡፡ እነሆ! የመለኮት ማደሪያ ትሆን ዘንድ የሚቀድሳት ከሥላሴ ወገን አንዱ ነው፡፡ እነሆ! የልጁ እናት ትሆን ዘንድ የሚያ ጸናት ከሥላሴ ወገን ሁለተኛው ነው፡፡ ዳግመኛ መልአኩ «የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል» አላት፡፡ እንደገና መልአኩ መልሶ «ስለዚህ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡፡ እግዚአብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፡»[4] እነሆ! ይህ ከድንግል የተወ ለደው ሦስተኛ [ወገን] ነው፡፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር ወደ አንቺ ይመጣል» አለ እንጂ ከአንቺ ሰው ይሆናል አላለም፡፡ ስለ ወልድ ሲናገር ግን፡- «ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡ እግዚአብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፡፡ ከአብ ስለ ተወለደው ልደት የልዑል ልጅም ይባላል፡፡» አለ፡፡ ከድንግል ስለ ተወለደው ልደት፡- «እግዚአብሔር

4. ሉቃ ፩፡፳፮ ፴፩፡፡



www.ethiopianorthodox.org

አምሳክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል።» አለ፡ ምክንያቱም ድንግል ማርያም ከዳዊት ዘር ናትና።

ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዩ /የተለየ/ ጳውሎስ፦ በነቢያቱ አፍ በቅዱሳት መጻሕፍት አስቀድሞ ስለልጁ የተናገረ፡ በሥጋዊ ሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ በኀይሉና በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ዐሳየ» ብሎ እንደ ተናገረው።[5]

እነሆ! ጳውሎስ ከዳዊት ወገን ሰው ሆኖ መጣ ባለ ጊዜ ጥንት ሰው ያልሆነ ቅድመ ዓለም የነበረ የዳዊትን ቤት ጐብኝቷልና ከዳዊት ልጅ [ከእመቤታችን] ሰው እንደሆነ ያመለክታል። ስለዚህ «በሥጋ ከዳዊት ዘር መጣ። በኀይሉና በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ዐሳየ።» አለ። ዳግመኛ ነቢዩ ዕንባቆም እንዲህ አለ፦ «እግዚአብሔር ከቴማን፡ ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ይመጣል።»[6] ፋራን በግዕዝ [በጥጃ] ይተረጐማል። ግዕዝም በንጽሕት ድንግል ይተረጐማል፡ ክብሩ ሰማያትን ከድኖአል ይህም፡ በመለኮቱ ኀይል ከአባቱ ጋር እኩል ትክክል በመባል ይተረጐማል «ምስጋናውም ምድርን ሞልቶአል» ይህም በአጽናፈ ዓለም ቤተ ሰበከው ገቢረ ተአምራቱ ይተረጐማል። «በምድር ሁሉ ነገራቸው ወጣ። እስከ አጽናፈ ዓለም ንግግራቸው ደረሰ» ተብሎ በነቢይ እንደ ተነገረ።[7] ዳግመኛ በነቢይ፦ «በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።» ተብሎ እንደ ተነገረ።[8] ዳግመኛም ከእግዚአብሔር ቤት መረቅናችሁ» ጌታ እግዚአብሔር ተገለጠልን። እንደገና «በኪሩቤል የሚቀመጥ ተገለጠ» ተብሎ እንደ ተነገረ።[9] ያለ ሥጋዌ እግዚአብሔርን ያየ ማነው? ሙሴን፦ «ፊቴን ዐይቶ በሕይወት የሚቆይ የለም።» እንዳለው።[10]

ዳዊት ስለ መለኮት ወደ ድንግል ማርያም መውረድ እንዲህ ይላል፦ እንደ ዝናብ በመስክ ላይ በምድር ላይ እንደሚንጠባጠብ ጠብታ ይወርዳል፡ በዘመኑም ጽድቅ ይሰፍናል ጨረቃም እስኪያልፍ ድረስ ሰላም ብዙ ነው። ከባሕር እስከ ባሕር ድረስ ከወንዝም እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ይገዛል። በፊቱም ኢትዮጵያ (የኢትዮጵያ ሰዎች) ይሰግዳሉ። ጠላቶቹም ዐመድም

5. ሮሜ. ፩፥፫, ዕብ. ፩፥፩።
6. ዕንባ. ፫፥፫።
7. መዝ. ፲፰፥፬።
8. መዝ. ፻፲፯፥፳፮-፳፯።
9. መዝ. ፸፱፥፩።
10. ዘጸ. ፴፫፥፳።





ይቅማሉ። የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ። የዓረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ።»[11]

እነሆ የመዝሙሩ ቃል፦ «እንደ ጠል በፀምር ላይ፣ እንደ ነጠብጣብም በምድር ላይ የሚያንጠባጥብ ይወርዳል። ባለ ጊዜ የወልደ እግዚአብሔርን ወደ ድንግል ማርያም መውረድ ግልጽ አደረገ። እንዲህ በማለት ያስከትላል፦ «በዘመኑም ጽድቅ ይሰፍናል።» ቅዱስ ጳውሎስ፦ «የሕግ ሁሉ ፍጻሜ በክርስቶስ ማመን ነው» ብሎ እንደ ተናገረ።[12]

የመስቀል ግንድ በቀለ፡ ቅርንጫፎቹም ለመለሙ፡ የጣዖት ግንድ ተሻረ፡ የአማልክት ምስል ተቀጠቀጠ፡ የወንጌል በረከት በቀለ፡ የአራት መር ገም ታጐለ፡ ምእመናን በቀሉ፡ ሰቃልያን ተበተኑ፡ የምስጢር ካህናት በቀሉ፡ ጣዖት አምላኪዎች ተደመሰሱ፡ «ጨረቃም እስኪያልፍ ድረስ ሰላም ብዙ ነው፡ ምክንያቱም ወሮቹም የሰላም ወሮች ናቸው። ዓመታቱም የይቅርታና የምሕረት ዓመታት ናቸው። ከባሕር እስከ ባሕር ድረስ ከወንዝም እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ይገዛል። ይህም በዓለም ሁሉ ስፈ ስለሆነች መንግሥቱ የተነገረ ነው። «በፊቱም ኢትዮጵያ (የኢትዮጵያ ሰዎች) ይሰግዳሉ።» ይህም ያለሐዋርያ ስለ አመኑት ሃይማኖታቸው ነው።

የሮሚ ሰዎች ጴጥሮስንና ጳውሎስን በመከራ አሠቃይተው ገደሉአቸው። ከዚያም በስብከታቸው አመኑ። እግዚአብሔር ይቅር ብሎ እን ዳልታመመ ሰው እስከሚፈወሰው ድረስ የሕንድ ሰዎች የቶማስን ቆዳ ገፈው ሥጋው ቀልጦ ነፍሱ እስክትቃጠል ድረስ በቁስሉ ውስጥ ወይ ንና ጨው ጨመሩ። በአራት ጦሮች ወግተው በተራራ ላይ ገድለውታል። ከዚ ህም በኋላ በስብከቱ አመኑ።

ወንጌላዊው ማርቆስ በግብጽ አውራጃዎች ሰበከ። የእስክንድርያ ሰዎች የላም አውራን እንስባለን እያሉ በዐለት ላይ ጐተቱት፡ ደሙ በየመን ገዱ፡ በየመስኩ ፈሶ ተጨንቆ ሞተ። ከሞተ በኋላ በስብከቱ አመኑ። ሐዋ ርያው እንድርያስ ሰው ከሚበሉ ሰዎች አገር ገባ። በአንገቱ ላይ ገመድ አድርገው በሾሉ ድንጋዮች ላይ ሥጋው እስኪላጥ ድረስ ጐተቱት። ከዚህም በኋላ በስብከቱ አመኑ። ከዚህም ወደ ሌላ አገር ገባ። እነሱም መስቀል ላይ አውጥተው በጽኑዕ ቅጣት ቀጡት። ነፍሱ እስከ ምትወጣ ድረስ ቀጡት። ከዚያም በኋላ በስብከቱ አመኑ። ሐዋርያው ማትያስ ወደ

11. መዝ. ፸፩፥፮።
12. ሮሜ. ፲፥፬።



www.ethiopianorthodox.org

ሀገረ ደማስቆ ገባ። የብረት አልጋ አዘጋጅተው በላዩ ላይ አስተኙት። ነበልባሉም ፲፰ ክንድ ከፍ እስኪል ድረስ በላዩ ላይ እሳት አነደዱ። እንደዚህ እያነደዱ እስከ ፳፰ ንጋት ድረስ ተቀመጡ። የነካውም የለም፤ ከዚህም በኋላ በስብከቱ አመኑ።

ወንጌላዊው ዮሐንስ ወደ እስያ ገብቶ ከሮምና ቤት አደረ፤ በከፋም አገዛዝ አስጨነቀችው፤ ለማእድ ቤት [የምግብ ማዘጋጃ ቦታ «ኩሽና»] ሲገ ዛላት፤ እርሷም ያለ ምሕረት እየ ደበደበች የባርነት መጽሐፍ በእርሱ ላይ አጽፋ አስጨነቀችው። በየ ዕለቱም በግርፋት በመቅሠፍት እያስጨነቀ ችው ተቀመጠች። ከዚህም በኋላ ተአምራቱን ባየች ጊዜ አመነች። የሀገሩ ሰዎች በእርሱና በስብከቱ ባመነ ዲዮስቆሬዶስ በተባለ መኰንን ላይ ሞረድ አነሡ። የሰይጣን ምክር ያሰራቸው ሰዎች በእስር ቤት በመዘጋት አስጨነቋቸው። ከዚህም በኋላ በስብከቱ አመኑ።

ሐዋርያው ፊልጶስም ወደ አፍሪቅያ አገር ገብቶ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰበከላቸው። የአገሬው ሰዎች በቁጣ ልባቸው ነዶ መስቀል ላይ አውጥተው ቁልቁል ሰቀሉት። ነፍሱ እስክትወጣ ድረስ ጽኑዕ ቅጣት ቀጡት። እንደገና በሥጋው ላይ እሳትን ያነዱ ዘንድ ወደዱ፤ የእግዚአብሔር መልአክ ነጠቀው። ከዚህም በኋላ በስብከቱ አመኑ፤ ወንጌላዊው ሉቃስ ከመምህሩ ከጴጥሮስ ጋር ወደ ሮሚ ገባ። ከጴጥሮስ ሞት በኋላ ስብከቱን አጽንቶ ምእመናንን እያጸና ተቀመጠ። ከዚህም በኋላ ንጉሡ ኔሮን ይህ ደሙ እንደ ውሃ እስከ ሚፈስ ድረስ በጅራፍ ገረፈው። እግዚአብሔርን ድንቅ ሥራና የሐዋርያትን ተአምራት የሚ ጽፍባት ቀኝ እጁን ይቆርጡ ዘንድ አዘዘ። የሚሰየፍበት ዕለት አንገቱን በሰይፍ ቆረጡ። ከዚህም በኋላ በስብከቱ አመኑ።

ወንጌላዊው ማቴዎስ ወደ ክነዶት አገር ገባ። ወደ አጽንጊ ከገባ በኋላ በበትርያ አገር ውስጥ አዙረው አንገቱን በሰይፍ ቆረጡ። ከዚህ በኋላ በስብከቱ አመኑ። ሐዋርያው ታዴዎስ ወደ ሶርያ አገር ገብቶ ተአምራት አደረገ። ገንዘብን በመናቅ እንጂ በገንዘብ ብዛት መጽደቅ እንደማይቻለው ለአንድ ጐረምሳ በነገረው ጊዜ ጐረምሳው ተቆጥቶ አነቀው። በመታነቁ የተነሣ ዐይኑ ለመውጣት እስክትፈቅድ ደረሰች። ባለጸጋውን ለመዘለፍ በዚያን ሰዓት ግመልን በመርፌ ቀዳዳ ሁለት ሦስት ጊዜ አሳለፈ። ከዚህም በኋላ በስብከቱ አመኑ።

ከነቢዩ ከኢሳይያስ ደም እስከ በራክዩ ልጅ ዘካርያስ ድረስ እንደገና





የነቢያት ፍጻሜ እስከ ሆነ መጥምቁ ዮሐንስ ደም ድረስ የብዙ ነቢያት ደም በኢየሩሳሌም ፈሰሰ። ምድር እንደገና ደማቸውን እስክትተፋና ከእናታቸው ወተት ነጠብጣብ የተነሣ ነጭ እስክትሆን ድረስ የዚህን ዓለም ርኵሰት የማያውቁ የገሊላ ሕፃናት ደም በእርሷ ላይ ፈሰሰ።

በአባቱ ዘንድ ደሙን ያፈሰሰትን እየከሰሰ የሚጮኽና የሚናገር ከሁሉ የሚበልጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በእርሷ ላይ ፈሰሰ። በእምነት ለሚቀበሉትም ኃጢአታቸውን የሚያስተሰርይ ደም ነው። እንደገና በድንጋይ ተደብድበው የሞቱት የእልፍዮስ ልጅ፤ የያዕቆብ ደምና የእስጢፋኖስ ደም፤ ከቤተ መቅደሱ ጣራ በማጣደፍ የጌታችንን ወን ድም የያዕቆብና የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብ፣ የቀለዮጳ ልጅ የስምዖን ደም በእርሷ ላይ ፈሰሰ። ሀገራቱ የደም ጉድጓድ ስለሆነች በዚህ ሁሉ የፈሰሰው የቅዱሳን ደም ምላሺ መልካም፤ አጸፋዋ መልካም አይደለም።

በርቶሎሜዎስም በባሕር ማዶ ወደ ታናሹ ታላላቅ አገሮች ወደ ማያንና ኒአን ድስ ደረሰ። ወደ ከሐድያን አገር ገብቶም የክርስቶስን የወንጌል ጸጋ ሰበከ። በማቁ ውስጥ አሸዋ መልተው በውስጥ ንጹሑን ሐዋርያ ጨምረው ባሕር ውስጥ ወረወሩት። በእግዚአብሔር ሰላም ምስክርነቱን ፈጸመ። ከዚህ በኋላ በስብከቱ አመኑ።

እንግዲህ ከሁሉም አገሮች አንዳንዶቹ ከእነርሱ የሰበኩላቸውን ከገ ደሉ፤ ካሠቃዩ በኋላ በውስጣቸው የተደረገውን ተአምራት በተዘከሩ ጊዜ በትምህርታቸው ወይም በሐዋርያው ሥጋ ላይ ተአምር በተመለከቱ ጊዜ ያምናሉ።

አገራችን ኢትዮጵያ ግን በላዩዋ ላይ የሐዋርያት እግር እንደ እነርሱ የተመላለሰባት አይደለም። የጌታ ተአምራትም በውስጧ አልተደረገም። በዜና አምና ድምፁን ተቀበለች እንጂ። ስለዚህ ነቢዩ እንዲህ ይላል፦ «የኢ ትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ ዐየሁ።»[13] [ኢትዮጵያውያን] ለእምነት ይደነግ ጣሉ፤ ሳለማመን ልባቸውን አያደነድኑም። የእግዚአብሔርን ቃል ለመ ስማት ይደነግጣሉ። ትእዛዙን ከመስማት ጆሮአቸውን አይመልሱም። ከጥንት የጣዖት ቤቶቻቸው በንስሐ ይመለሱ ዘንድ ይደነግጣሉ። ክርስቶ ስን ወደ ማምለክ ይሮጣሉ።

በሊላም በኩል፦ «አንተ የከይሲን ራስ በውሃ ውስጥ ሰበርከ።» ይላል።[14] የከይሲ አንገት የሰይጣንን ኀይል በመስበር ይተረጐማል።

13. ዕንባ. ፫፥፯
14. መዝ. ፸፫፥፲፫።



www.ethiopianorthodox.org

አንተ የከይሲን ራስ ቀጠቀጥክ፡፡ የከይሲ ራስ መቀጥቀጡ ግን ዳግመኛ እንዳይነሣና እኛም ወደ አምልኮቱ እንዳንመለስ፥ እንደ ሞተ አስበን እን ዳናስታውሰው ነው፡፡ «ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንጀራቸውን ሰጠሃቸው፡፡»[15] ይህም ስለ ወልደ እግዚአብሔር ሥጋ ወደሙ ቍርባንነት የተነገረ ነው፡፡ ይኸውም የጻድቃን የዘላለም ምግባቸው ነው፡፡ በጥምቀት ውሃ ሳይረጭ በቅብዐ በለሳን /በቅብዐ ሜሮን/ ሳይታተም ቍርባን መቀበል የሚቻለው የለም፡፡ በሃይማኖት ኀይል የሰይጣንን ራስ ቀጥቅጦ ሰይጣንን ሳያወግዝ ጥምቀትን መቀበል የሚችል የለም፡፡

በሌላ በኩል «አማላጆች /አስታራቂዎች/ ከግብጽ ይመጣሉ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች፡፡» ይላል፡፡[16] ይህ ትንቢት የኢ ትዮጵያ ጳጳሳት ሹመት ከመንበረ ማርቆስ እንደሆነ የሚናገር ነው፡፡ የኢ ትዮጵያ ሰዎች የእምነታቸው ምክንያት እንደዚህ ነው፡፡

ከዘንዶው መንግሥት እስከ ንግሥተ አዜብ የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ ዘንድ ወደ ዳዊት ልጅ ወደ ሰሎሞን እስከ ምትወርድ ድረስ በጣዖት ቤት እያመለኩ በአሕዛብ ሕግ ኖሩ፡፡[17] ንግሥተ አዜብ በተመለሰች ጊዜ ከኢየሩሳሌም የኦሪትን ዜና አምጥታለች፡፡ ከዚያን ዕለት ጀምሮ እስከ ምጽአተ ክርስቶስ [እስከ ክርስቶስ ልደት] ድረስ ለሕግና ሥርዐት በትእዛዝ እየተገዙ የእግዚአብሔርን ሰንበታት በመጠበቅና እያገለገሉ በአይሁድ ሕግ ኖሩ፡፡» «ከሌላ ወገን ተወልደው ወደ እግዚአብሔር የተመለሱትን የተገዙለትንም የእግዚአብሔርንም ስም የሚወዱትን ወንዶች ባሮችና ሴቶች ባሮች የሆኑትን ሰንበቶቼን የሚጠብቁትን የማይሽሩትን በሕጌም ጸንተው የሚኖሩትን ሁሉ ወደ መመስገኛዬ ወደ ኢየሩሳሌም አገባቸዋለሁ፡፡ ጸሎት በሚደረግባት ቤቴም ደስ አሰኛ ቸዋለሁ ቍርባናቸውና መስዋዕታቸውም የተመረጠ ይሆናል እግዚአ ብሔር ለአሕዛብ ሁሉ ቤተ ጸሎት የሚደረግበት ቤት ይባላል አላቸው፡፡»[18] በሆሴዕም እንዲህ አለ፡- «ሕዝቤ ያልሆነውን ሕዝቤ አደርገዋለሁ፡ ያልተወ ደደችውንም የተወደደችው ብዬ እጠራለሁ፡፡ እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም የተባላችሁም ስፍራ በዚያ የሕያው እግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉ፡፡»[19]

15. መዝ. ፸፫፥፲፬፡፡
16. መዝ. ፷፯፥፴፩፡፡
17. ፩ኛ ነገ. ፲፥፩፡፡
18. ኢሳ. ፶፮፥፱፡፡ (አስመራ የታተመው)
19. ሆሴ. ፪፥፩፡፡





የእምነታቸው ምክንያት ግን ሕንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት ጃንደረባ ለፋሲካ በዓል ይሰግድ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም በወረደ ጊዜ በጊታ ሆነ፡፡[20] በአሕዛብ ውስጥ በአይሁድ ሕግ ያመነ ሰው ቢኖር በፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይወርዳል፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ስም ባልተሰማበት ቦታ የፋሲካን ሥርዐት ማድረግ አይቻልምና ነው፡፡

ስለዚህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እንዲህ የሚል ጽሑፍ አለ፡ «በበዓ ሉም ሊሰግዱ ከወጡት አንዳንዶቹ የግሪክ ሰዎች ነበሩ፡ እነርሱም ከገሊላ ቤተ ሳይዳ ወደሚሆን ወደ ፊልጶስ መጥተው ጌታ ሆይ! ኢየሱስን ልናይ እንወዳለን ብለው ለመኑት፡ ፊልጶስም መጥቶ ለእንድርያስ ነገ ረው፡ እንድርያስና ፊልጶስ መጥተው ለኢየሱስ ነገሩት፡ ኢየሱስም መለሰ ላቸው፡ እንዲህ ሲል፡- የሰው ልጅ ይከብር ዘንድ ሰዓቱ ደርሶአል፡፡ ይህም አሕዛብ በእኔ አምነው ያመሰግኑኝ ዘንድ ጊዜው ደረሰ ማለት ነው፡፡[21]

በሐዋርያት ሥራ እንደ ተጻፈው፡- «በዚህ ነገር ምክንያት ሕንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት ጃንደረባ ለፋሲካ በዓል ይሰግድ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ወረደ፡፡ የጌታ መልአክ ፊልጶስን፡- «ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደ ሚወርደው ምድረ በዳ ወደሆነ መንገድ ሒድ አለው፡፡ ተነሥቶም ሔደ፡፡ እነሆም፡ ሕንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘብዋም ሁሉ የሠለጠነ አንድ ኢትዮጵያዊ ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር፡፡ ሲመለስ በሠረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን፡- ወደዚህ ሠረገላ ቅረብና ተገናኝ አለው፡፡ ፊልጶስም ሮጦ የነቢ ዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰማና፡- በእውኑ የምታነበውን ታስተ ውለዋለህን? አለው፡፡ እርሱም፡- የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለ ኛል? አለው፡፡ ወጥቶም ከእርሱ ጋር ይቀመጥ ዘንድ ፊልጶስን ለመ ነው፡፡ ያነበውም የነበረ የመጽሐፉ ክፍል እንዲህ ይላል፡፡ «በግ በሚሸ ልተው ሰው ፊት እንደ ማይናገር እንደዚሁ በመከራ ጊዜ አልተናገረም፡፡ ሞትን ድል ነስቶ መግነዙን ፈቶ ተነሣ፡ መነሣቱን ግን ይናገራል፡ ነፍሮው ከምድር ተፈጽሚልና፡፡»

ጃንደረባውም ለፊልጶስ መልሶ፡- እባክህ፡ ነቢዩ ይህን ስለማን ይናገራል? ስለ ራሱ ነውን ወይስ ስለ ሌላ? አለው፡፡ ፊልጶስም አፉን ከፈተ፡ ከዚህም

20. የሐዋ. ፰፥፳፯፡፡
21. ዮሐ. ፲፪፥፳፡፡



www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌል ሰበከለት። በመንገድም ሲሔዱ ወደ ውሃ ደረሱ። ጃንደረባውም፦ እነሆ ውሃ፤ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው? አለው። ፊልጶስም፦ በፍጹም ልብህ ብታምን፥ ተፈቅዶልሃል አለው። መልሶም፦ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ አለ። ሰረገላውን ይቆም ዘንድ አዘዘ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውሃ ወረዱ፥ አጠመቀውም። ከውሃውም ከወጡ በኋላ የእግዚአብሔር መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው፥ ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም። ደስ ብሎት መንገዱን ይሔድ ነበርና።»[22]

በእርሱም ዜና የኢትዮጵያ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌል ጸጋ አመኑ። ጠንካራ ክርስቲያን መሆን ግን ተሳናቸው። ምክንያቱም ጃንደረባው ያጠምቃቸው ዘንድ ካህን አይደለም። ከብዙ ዓመታትና ከጥቂት ወራት በኋላ አንድ ነጋዴ ከሁለት ልጆቹ ጋር ከጢሮስ መጣ። የአንደኛው ስም ፍሬምናጦስ የሁለተኛው ስም ሲድራኮስ ይባላል። ከዚህ በኋላ ነጋዴው በኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍ ወደብ ላይ ታሞ ሞተ። ፍሬምናጦስና ሲድራኮስን አምጥተው ከኢትዮጵያ ንጉሥ ፊት አቆሙአቸው።

ንጉሡም ወደዳቸው፥ ከቤተ መንግሥት ልጆች ጋር ደመራቸው። የኢትዮጵያን ሕዝቦች ነጻነት እየደነቁ ተቀመጡ። ለስመ ሥላሴ ይሰግዱ ዘንድ መሕለያ [ጸሎት ቤት] ሲሠሩ ስለ ተመለከቱ «እንዴት አመኑ?» ይባባሉ ነበር። በሴቶቻቸው ግንባር ላይ የመስቀል ምልክት አይተው ፈጽሞ ተደንቀው እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ምክንያቱም ያለ ሐዋርያ ሃይማኖትን፥ ያለ ስብከት እምነትን ከፍሎ ሰጥቶአቸዋልና ነቢዩ ኢሳይያስ እንደ ተናገረው «ያላስተዋሉት ይጠይቁት ዘንድ አላቸው።» ስለ እርሱ ያልተነገራቸው ሕዝቦች ያውቁታል።[23] ጌታችንም በወንጌል፦ ቶማስን «ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው።» አለ።[24]

ወደ ፍሬምናጦስና ሲድራኮስ ጥንተ ነገር እንመለስ። ንጉሡ በሕይወት ሳለ ቤተ መንግሥት ውስጥ ተቀመጡ። ንጉሡ ሊሞት በደረሰ ጊዜ ነጻ አውጥቶ ወደ ፈቀዱት ይሔዱ ዘንድ አሠለጠናቸው። ሲድራኮስ ወደ ሀገሩ ጢሮስ ገባ። ፍሬምናጦስ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የድኅነታቸውን ምክንያት ይፈልግ ዘንድ ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ዘንድ ሔዶ ያለሐዋርያት ትምህርት ያመኑትን ፍጹም እምነት ነገረው። ያለ ስብከት የሆነውን

22. ሐዋ. ፰፥፳፮-፵።
23. ሐዋ. ፳፩፥፩፡ (በአስመራ የታተመው መጽሐፈ ኪዳን)
24. ዮሐ. ፳፥፳፱።





ሃይማኖታቸውን አድንቆ እግዚአብሔርን አመሰገነ። ሊቀ ጳጳሱም፦ «እግዚአብሔር አንተን አሳድጉሃልና ወደ እነርሱ ተመልሰህ አንተ እረኛ ሁናቸው።» አለው። ሊቀ ጳጳሱም እጁን በፍሬምናጦስ ላይ አድርጉ፦ ጸሎተ ተክሌዝ ዘሚመተ ምጥሮቢሊጥ፣ ለሚመተ ጵጵስና የሚጸለይ ጸሎትም ጸለየ። ፍሬምናጦ ስም ወደ ብሔረ አግአዚ [ኢትዮጵያ] ሔደ። በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠመቃቸው፥ ጳጳሳትን፣ ዲያቆናትን ሾመላቸው። እነርሱም እንደ አምላካቸው አከበሩት፥ እንደ አባታቸውም ወደዱት። ሰላምን አምጥቶ ላቸዋልና አባ ሰላማ አሉት። አወጣጡ ግን ዝናምን ደስ ብሏት እንደም ትጠየባ እንደ ተጠማች ምድር የጽድቅን ትምህርትን በተቀበሉ በአብርሃና አጽብሐ ዘመነ መንግሥት ሆነ።

ከብዙ ወራትና ከጥቂት ዓመታት በኋላ በርካታ የአክሱም ነገሥታት ካረፉ በኋላ የሮም ቅዱሳን ከንጉሣቸው ከመሳፍንቶቻቸውና ከመኳንንቶቻቸው ጋር ከካህናቶቻቸውና ከመሥዋዕቶቻቸው፥ ከንዋየ ቅድሳታቸውና ከመጻሕፍቶቻቸው ከሕዝቦቻቸው ጋር ወጡ። አወጣጣቸው ግን በሰል አደባ ልጅ በአልአሚዳ ዘመነ መንግሥት ነበር። ሀገራቸውን ለመውረስ ንጉሣቸውን ከእነርሱ ለማንገሥ የወጡ ስለ መሰላቸው ከመውጣታቸው ምድር ደንገጠች፥ የኢትዮጵያ አውራጃዎች ተነዋወጡ። እነርሱ ግን የሃይማኖታቸውን ኀይል አሳዩ። ተራራ ያፈለሱ አሉ። ባሕርንም ያፈለሱ አሉ። ጠዋት ስንዴ ዘርተው በሠርክ ጊዜ ወደ አውድማ የጨመሩ አሉ። ውድማውም በዕፀ ገራዩ /በግራር/ እንጨት ላይ ነበር።

የዛፎቹ ቅጠሎች ሳይረግፉ በሬዎቹ ሳይጣደፉ የስንዴ ፍሬ ወርዶ በአደባባይ ከምር ሆነ። ገለባው ግን ወደ ዱር ተጣለ። ስንዴውን ፈጭተው ለሠርክ መሥዋዕት ደረሰ። ጠዋት አባ ጉርባ ብርቱ እንጨት በሌለው ልሙጥ አለት ላይ ተከለ። በጊዜ በቅሎ ትልቅ ዛፍ ሆነ። ግንዱ በፈቃደ እግዚአብሔር ደረቀ። ፈልጠው እንድደው ፍሕሙን በስስ ልብስ የቋጠሩ፥ ለሠርክ ዕጣንም ያደረሱ አሉ። ሰው ከሞተ በኋላ ያናገሩ አሉ። ውሃን በወንፊት ቋጥረው ውሃው ሳይፈስ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ለቍርባን ሥርዐት ያስገቡ አሉ። ከእነርሱ በመላእክት እጅ የተገነዘም አለ። ርዝመቱ ከትልቅ ተራራ የሚበልጥ ትልቅ የድንጋይ ምሰሶ አዘነበለ። ፈጽሞ /ሀንቶ/ ቆሞ ሥጋውን ከወንዝ ዳር ተቀበለ። እስከ ዛሬ የቅዱሱ በድን በድንጋዩ ምሰሶ መሐል አለ። የተገነዘበትን ፍሊጋ አባ ጉርባ በሊለበት አለት ላይ በብልህ ሠዓለ.



www.ethiopianorthodox.org

እንደ ተገለጸ ሥዕል ባሬም ይታያል። ከእነርሱም ሀሥሩ የእጆቻቸው ጣቶችና ሀሥሩ የእግሮቻቸው ጣቶች በጸሎት ጊዜ ቆመው ሳሉ እንደ መብረቅ ብርሃን የሚያበሩ አሉ። ከእነርሱም በእግዚአብሔር ጸጋ ከሞት ፊት ደኅነው የተሸሸጉ አሉ። ከእነርሱም ወደ ሀገራችን ቀድመው የመጡና ተመልሰው የኢትዮጵያን የቸርነት ዜና ያለ ሐዋርያት ስብከት በክርስቶስ እንደ አመኑች የተናገሩ አሉ።

ከዚህም በኋላ የእነዚህ ቅዱሳን ሐዋሳት በክርስቶስ የሃይማኖት ወላፊን ነደው ከቁሳቁሶቻቸው ጋር ወደ ሀገራችን ወጡ። ምድር በእግሮቻቸው ከደት ተቀደሰች ታደሰች። በመመላለሳቸውም የምድር ቅጽሮቿ ታደሱ። የቃላቸውም መዓዛ በየአውራጃዋ ፈሰሰ። ከሰልአደባ ልጅ አል አሚዳ መንግሥት እስከ ታዜና ልጅ ካሌብ መንግሥት ድረስ በሰማይ ላይ እንደ ሚያበሩ ከዋክብት የጽድቃቸውን ክብር እያሳዩ ያለ መለያየት በትንሽ ቤት ውስጥ ተባብረው ተቀመጡ። የአበባቸው ውበት መዓዛቸው እንደሚገ እንደ ገነት ዛፎች ልዩ ልዩ ነበር። ፍሬያቸውም ልዩ ልዩ ነበር። ሥነ ሞገሳቸው [እንደሚያንጸበርቁ] የሕንድ ደንጋዮች ለየቅሉ ነው፤ መልካቸውም ለየቅሉ ነው።

እንደ ሽቱ መዓዛዎች ተጣፍጠ [ተቀምሞ] በጽዮን ቀርኑ ቅብዕ እንደ ተከብሮ ሚቀመጥ ይቀመጣል። በሰንፔር ድንጋይ ላይ ተመጣጥነው እንደ ተለኩ የዕንቁ ምስስዎች [ተሰፍረው]፤ ከፖፉሄም ይልቅ ንጹሕ በሆነ ወርቅ እንደ ወርቅ ድንጋይ ተጠምጉተው፤ በሙሽራት አንገት እንደ ሚደረግ ወርቅና በሙሽራ ራስ ላይ እንደሚደረግ አክሊል በነገሥታት ራስ ላይ እንደ ሚደረግ የዕንቁ ጌራ በመሳፍንት እጆች እንደ ሚደረጉ ቀለበቶች ለአክሱም ምድር ጌጥ ሆኗት።

የሕጋቸውንና የሥርዐታቸውን መጻሕፍት ሰጥተዋት በክርስቶስ ሐዋርያት ትምህርት አጸኗት። መጻሕፍተ ብሉያትን ከዕብራይስጥ ወደ ግእዝ ተረጐሙ። ከሰሎሞን ባገኘችው በንግሥተ አዜብ ዘመን መጻሕፍተ ብሉያት ከዕብራይስጥ ወደ ግእዝ ተተርጉመዋል። ስለዚህ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ[illegible] አይሁድ ስለ ነበሩ፤ በብሔረ አግዓዚት ውስጥ የሚገኙ መጻሕፍተ ነቢያት ትርጉማቸው የተጣራ ሆኗል።

[illegible]





ከክርስቶስ ልደት በኋላ ቢከዱትም ሲቃልያን የጽድቅን ቃል ወደ ሐሰት ምስክር መለሱ (ለወጡ)። የነቢያት መጻሕፍት ከዕብራይስጥ ወደ ግእዝ እንደ ተመለሱ በመጽሐፈ ነገሥት ውስጥ ምልክት ይገኛል። በዕብራይስጥ «ኢሉሂ» ማለት ወደ ግእዝ ሲተረጉም «አምላኪ» ማለት ነው። «አዶናይ» ማለት «ጌታ ጸባኦት» ማለት «ሰራዊት» ማለት ነው። ለአገራችን ኢትዮጵያ መጻሕፍተ ሐዲሳት፤ ጉባኤ ከሰባት ኢጳስ ቆጳሳት ከመሰብሰባቸው በፊት፤ የልዮን ሃይማኖት ሳይፈጠር የንስጥሮስ ሃይማኖት ሳይታይ ከሮማይስጥ ወደ ግእዝ ተተረጐሙ። ስለዚህ የብሔረ አግዓዚት የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ትርጓሜ እንደ ወርቅ የነጠረ፤ እንደ ብር የተፈተነ፤ እንደ ወተት የጎደ ምንም ያልተፈጠመረበት ሆኗል።

የኢትዮጵያ ንጉሥ ወደ ኢየሩሳሌም ቢሔድ፤ የሮሚ ንጉሥ ወደ ቁስጥንጥንያ ቢሄዝ፤ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ጋር ቢገዛ የሮማው ንጉሥ ከቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት ጋር መጥቶ በአባ ሲኖዳ ቤት ይገናኛሉ። የሮማው ንጉሥ ከቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ ጋር «የእኛ ሃይማኖት ይበልጣል» ይላል። ዳግመኛ የኢትዮጵያው ንጉሥ ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ጋር «የእኛ ሃይማኖት አሳምራ ትበልጣለች። እናንተ የሮሚ በምች በትስብእትና በመለኮት መካከል ልዩነት አድርጋችኋል። የማይከፈለውን ከፈላችሁ፤ የማይለየውን ለያችሁ» አሏቸው። ስለዚህ ስለ ተነገው ነገር በመጻሕፍት ቃል ጠብ የረዝማል። ምክንያቱም የብሉይ ኪዳን የተወፈት መጻሕፍቶች የአዜብ ንግሥት ከኢየሩሳሌም በመጣች ጊዜ ነበር። የሐዲስ ኪዳን የትውፊት መጻሕፍቶቻቸው የሮማ ቅዱሳን በወጡ ጊዜ ነበር። ስለዚህ የኢትዮጵያ መምህራን የሮማን መምህራን ይፈታቸዋል። ምክንያቱም መጻሕፍቶቻቸው በአጽናፈ ዓለም ካሉ መጻሕፍት በለጡ። ስለዚህ ነቢዩ ኢሳይያስ መጻሕፍትን «ከኢትዮጵያ ወንዞች ይመጣሉ» አለ። ከዚህም በኋላ ጉባኤ ሆናባቸው ክሕደትን ያበዛሉ። ለእናንተ ሊቃነ ጳጳሳት ሸንጎት ይሆን ዘንድ፡- «መንፈስ ቅዱስ የወረደው ከእኛ ሊቃነ ጳጳሳት መመዊያ ላይ ነው። ከዚህ በኋላ የሮሚ ሊቀ ጳጳሳት በአንድ መመዊያ ውስጥ ይቀድሳል፤ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት በአንድ መመዊያ ይቀድሳል። ይላሉ። በየዕቆባውያን እና በመለካውያን ፊት፤ በአረማውያን መኳንንትና በአይሁድ ፊት መንፈስ ቅዱስ በነጭ ርግብ አምሳል በእስክንድርያው ሊቀ



www.ethiopianorthodox.org

ጳጳሳት መሠዊያ ላይ በግልጽ ይወርዳል።[26] ጉኖቹ የወርቅ አመልማሎ፥ ክንፎቹ የፀሐይ ብርሃን፥ ጭራው የመብረቅ መጐናጸፊያ፥ ሆዱና ደረቱ የኢስጲድና የሰርዱኖ ዕንቍ አንገቱ እንደ ብርሃን ላንቃ፥ ራሱ የሚያንጸበርቅ፥ ዐይኖቹ የወርቅ፥ በአንገቱ ላይ የብርሃን ማዕተብ ትእምርተ መስቀል ያለ፥ በዚህ የብርሃን ማዕተብ ላይ በበጉ ሥዕል ፊት የናዝራውያን አምላክ «ናዝራዊው ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ ነኝ» እያለ ይጮኻል።[27]

ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ንጉሥ ተደሰተ። ከሕዝቡ ጋር በእልልታ ቃል ይጮኻል። የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ከግብጽ ኤጲስ ቆጶሳትና ከመምህራን ጋር በኢትዮጵያ ሰዎች ይደሰቱባቸዋል። በመጻሕፍታቸው ቃል የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኗልና። ስለዚህ ነቢዩ ኢሳይያስ ግብጻውያን «በኢትዮጵያ ይመካሉ» አለ። ምክንያቱም የግብጽና የኢትዮጵያ ሰዎች በሃይማኖትና በክህነት በአንድነት የሚሳተፉ ናቸው። ከዚህ በኋላ የሮሜ ሰዎች ከንጉሦቻቸውና ከጳጳሶቻቸው ከማኅበራቸው ጭፍሮች ጋር ኀፍረት ይለብሳሉ። ስለዚህ ዳዊት፦ «በፊቱም ኢትዮጵያ (የኢትዮጵያ ሰዎች) ይሰግዳሉ (ይገዛሉ) ጠላቶቹም አመድ ይቅማሉ።» የሮሚን ታላላቆች ያሳፍራቸው ዘንድ፥ የመጻሕፍት ቃል ማሸነፍን ስላደላቸው እውነትም ኢትዮጵያ (የኢትዮጵያ ሰዎች) በፊቱ ይሰግዳሉ (ይገዛሉ)። ጠላቶቹም አመድን ይቅማሉ ያለው እውነት ነው። ይህም ስለ መለካውያን ጉስቋላ ስብከታቸው የተነገረ ነው። ምክንያቱም መለካውያን የኢየሱስ ክርስቶስን ሳይሆን የንጉሥ ወገን የሆኑ ማለት ነው። ንጉሡ መርቅያን በፈቀደበት ሥፍራ መመለሳቸው ስደትንና ቅጣትን በመፍራት ነውና። ስለዚህ ንጉሣውያን ተብለዋል። ክርስቶሳውያን አይደሉም። ምክንያቱም በዐረብኛ ቋንቋ መሊኩ ማለት ንጉሥ ማለት ነው። የሃይማኖታቸው ስም ክሕደታቸውን ያሳውቃል፥ ለእግዚአብሔር ከማድላት ይልቅ ለንጉሥ አድልተዋልና።

ከረከሰች ሃይማኖታቸው ተመልሰው ይጸጸቱ እንደ ሆነ ወደ ሮሙ ንጉሥ፣ ወደ ቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳሳትና ወደ ማኅበራቸው ጭፍሮች ዜና እንመለስ። በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት መሠዊያ ላይ የመንፈስ ቅዱስን

26. የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት በሰዋው መሥዋዕት ላይ አነ ውእቱ ክርስቶስ ብሎ በርግብ አምሳል ወርዶ ይመሰክራል። ከዚህ በኋላ በሃይማኖት አንድ ይሆናሉ በግብ ይገናኛሉ እንደዚህ የሚል ከምን አለ ቢሉ ከገድለ ፊቅጦር ከራእየ ሲኖዳ ይገኛል። [የማቴዎስ ወንጌል እንድምታ ወይሰበክ ዝ ወንጌል መንግሥት ውስተ ኵሉ ዓለም፤ ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ ማቴ ፳፬፥፲፬ የሚለው ትርጓሜ ገጽ ፬፻፸፯
27. ራእ ፳፩፥፲፰





መውረድ በተመለከቱ ጊዜ መጽሐፎቻቸው ወደ ጥልቅ ባሕር ይገባሉ። ይጠልቃሉ። ይኸውም ሰይጣን በአፉ የተነፈሰው የሐሰት መጻሕፍት ናቸው።

እንደገናም ክሕደትን ያስተማሯቸውን አባታቸውን ልዮንን ይረግሙታል። ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ንጉሥና በሮም ንጉሥ መካከል ሰላም፣ ፍቅር፣ ስምምነት ይሆናል። ይኸውም የአንበሳ ልጅ ማለት ነው። የኢየሩሳሌም ግዛት ወደ ሮም ንጉሥ፣ የግብጽና የምሥር ግዛት ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ይገባል። ከዚህ በኋላ የመነኮሳት አለቃና የባሕታውያን አባት አባ ሲኖዳ እንደ ተናገረው ወደ የአገራቸው በሰላም ይገባሉ።

«ኢትዮጵያ በፊቱ ይሰግዳሉ፤ ጠላቶቹ ዐመድ ይቅማሉ።» ማለት እንደ ገና ትርጓሜ አለው። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ስደተኞች ኢየሩሳሌም ወርደው ክርስቶስ በተወለደበት ቤተ ልሔም ያመሰግናሉ። ይሰግዳሉ። ክርስቶስ ወደ ተጠመቀበት የዮርዳኖስ ወንዝና ወደ ተሰቀለበት ቀራንዮ ሰግደው ያመሰግናሉ። ዳግመኛ ክርስቶስ ወደ ተቀበረበት መካነ ጎልጎታ በልቅሶና በዋይታ አመስግነው ይሜላለሳሉ። እዚያ የነበሩ ሰዎች ምስክር ሆነዋል። በፋሲካ ብርሃን ከትንሣኤ አስቀድሞ በቀዳሚት ሰንበት በሰሙነ ሕማማት የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ይሆናል። በመካነ ጎልጎታ በየወገናቸው መብራት [ቀንዲል] ይሰቅላሉ። አስቀድመው የሮም ሰዎችና መለካውያን ይሄራሉ። በዐይኖቻቸው የመብራት ብርሃን አይታይም፥ አፍረው ይወጣሉ። ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ፥ ግብጽ፥ ሶርያ፥ አርማንያ ይሄራሉ። ከእነርሱ ጋር ኢትዮጵያዊ ከሌለ የመብራት ብርሃን በማብራያቸው ውስጥ አይታይም። ኢትዮጵያዊ ቢኖርም ያለ ኢትዮጵያ ቀንዲል የመብራት ብርሃን አይቀመጥም። ክሕደታቸውን በዓመፅ ወደ ሌላ ቦታ ቢያፈልሱት የእግዚአብሔር ፊት [ክብር] ተከትሎት በላዩ ላይ የመብራት ብርሃን ይታያል። እነሆም ስለ ኢትዮጵያ ክብርና ልዕልና ምስክር አደረስንላችሁ [አቀረብንላችሁ]፤ ምክንያቱም የግብጽ ሰዎች ከኢትዮጵያ ስደተኞች ተለይተው ብቻቸውን ዘረው እንዳጡ የነገሩን ሰዎች አሉ። የመብራታቸው ብርሃንንም አልታየላቸውም።

ከዚህም በኋላ የሚገዙአቸው መኳንንት አረማውያን እነሆ! ሃይማኖታችሁን



www.ethiopianorthodox.org

አከፋፋችሁ፡ እንግዲህ ወደ እኛ ሃይማኖት እንመልሳችኋለን፡ ምክንያቱም የአምላካችሁ ብርሃን አልታየላችሁም ይሏቸዋል። የግብፅ ሰዎች አምላካችንን እንድንጠይቅ ትንሽ ጊዜ ታገሡን እያሉ አለቀሱ። ከዚህም በኋላ በተዋቸው ጊዜ ከኢትዮጵያውያን ወገን ወደ ሆነ አንድ ስደተኛ መቃብር ሔደው መቃብሩን ቆፍረው ዐፅሙን አውጥተው በልብሳቸው ቋጥረው በየዓመቱ እንደ ለመዱት የጌታችንን መቃብር ሄዱ። በቀንዲል ውስጥም የመብራት ብርሃን ታየ። ከዚህም በኋላ የግብፅ ሰዎች በረዳቸው በእግዚአብሔር ተደሰቱ፤ አረማውያንም በሃይማኖታቸው እንዲኖሩ ተዋቸው።

ወደ ሌላ ነገር ውስጥ በመግባት ወደ ረሳነው ወደ ፎጢኖስ ዘለፋ እንመለስ። ፎጢኖስ ሆይ! ያበደ ውሻ የነከሰውን ያሳምማል፡ በጥርሱ የለ ከፈው በጽኑ ደዌ ይሞታል። እንደዚሁም ትምህርትህን የሚሰማ በስሕተትህ ሕማም ይታመማል። በልቡ ውስጥ አጥንትን የሚሰብር አንጀትን የሚበጥስ የግዝት መርዝ ይገባበታል። ፎጢኖስ ሆይ! «የክርስቶስ ህልውና ከማርያም ወዲህ ነው» እንዴት ትላለህ? አብ ስለ እርሱ በኦሪት [በሕግ መጽሐፍ] «አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፡»[28] ዳዊትም «ፀሐይ ሳይፈጠር አስቀድሞ ስም አጠራሩ አለ።» አለ። ወንጌላዊው ዮሐንስም «በመጀመሪያው ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። እንደዚሁም አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር። እነሆ! አስቀድሞ፡ ሁሉ በእርሱ ሆነ፡ ከሆነውም አንዳች እንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።»[29] ብሏል።

እነሆ! አብ በራሱ ህልውና ብቻውን ያለ ወልድ አንድነት ያደረገው ነገር እንደሌለ ግልጽ አደረገ። ስለዚህ ከሆነውም አንዳች እንኳ ያለ እርሱ አልሆነም አለ። ዳግመኛ ዮሐንስ በመልእክቱ፦ «ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዐይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እንናገራለን፡ ሕይወትም ተገለጠ፡ አይተንማል እንመሰክርማለን፤» አለ።[30]

28. ዘፍ. ፫፥፳፪።
29. ዮሐ. ፩፥፩-፫።
30. ፩ኛ ዮሐ. ፩፥፩።





ጳውሎስም ማርቆስም በነቢያት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ «የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ።» አለ።[31] ዳግመኛ በወንጌል «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው የለም፡ በአባቱ እቅፍ ያለ /እሪና ያለ/ አንድ ልጁ ወልድ ዋሕድ እርሱስ ከቶ ነገረን እንጂ ።»[32] ይሁዳም «ሁሉንም አሳስባችሁ ዘንድ ወደድኩ ኢየሱስ በመጀመሪያ ጊዜ ሕዝቡን ከምድረ ግብጽ እንዳዳነ በሁለተኛውም ጊዜ ያላመኑትን እንዳጠፋቸው ታውቃላችሁ።» አለ።[33] ዳግመኛ ዳዊትም፦ «ከአንተ ጋር ቀድሞ በኃይልህ ቀን በቅዱሳን ብርሃን አለ።»[34] አለ ራሱ ወልድም፦ «አባት ሆይ፡ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ።» አለ።[35]

ልቡናህ የታሰረ ፎጢኖስ ሆይ! «በዚህም አታስተውልምን? ቅድመ ዓለም የነበረውን ህልውና ትክዳለህን? የሐሰት ተክል ፎጢኖስ ሆይ! ከሕያዋን ሥር ተመዝዞ ሲኦልን በሚዘት ድንኳኖች ውስጥ ተተክለክ። እኛ ግን አብ ከልጁና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ህልው እንደ ሆነ እናምናለን። አብ ልጁን [ወልድን] የወለደው በሥራ እንዲረዳው አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ህላዌ ወደ ህላዌው የተደመረው [የተዋሐደው] ጥበብንና ተግባርን ለማሟላት አይደለም። በባሕርይ፡ በሐሳብ፡ በሥርዐት አንድ ናቸው እንጂ። ለፍጥረታዊ ጠባይ የማይገኙ፡ በእጅ የማይዳሰሱ፡ ለእይታ የማይታዩ፡ ለምልክት አይታሰቡም፡ የማይጨመሩ፡ የማይነዋወጡ፡ በልዩነት፡ የማይለዩ፡ በመብዛት የማይበላለጡ፡ በጉድለት የማይጎድሉ ናቸው። አብ፡ ለነቢያት በራእይ በትንቢት እንጂ ፍጹም በባሕርዩ የማይታይ የተለየ ነው። ወልድም ያለ ሰውነቱ በመለኮቱ የማይታይ የተለየ ነው።

ቅዱሳንን በሚረዳቸው ገንዘብ ለመታየት የሚፈቅድ ነው እንጂ. መንፈስ ቅዱስም በሌላ ግርማ የማይታይ የተለየ ነው። እግዚአብሔር የጻድቁ አቤል ደም በአዳም ዕዳ ላይ ለመሠልጠን እንዳልጠቀመ በተመለከተ ጊዜ፡ አባቱ ባሠራው መሠዊያ ላይ የይስሐቅ መኃደም ሳይሆን፡ ስለ ዐጸደ ወይኑ የተገደለ የኢይዝራኤላዊ ናቡቴ ደም ሳይሆን፡ በእንጨት መጋዝ በየክፍል የሰነጠቁት የኢሳይያስ ደም ሳይሆን፡ ስለ ጺዋዌ [ምርኮ] በተነበየ ጊዜ ረግረግ ውስጥ በጨመሩት በኤርምያስ ደም ሳይሆን፡ ከምርኮ መልስ በኋላ አምላክ ወልደ አምላክ ባለጊዜ የኢሳይያስ

31 ማር. ፩፥፩።
32 ዮሐ. ፩፥፲፰።
33 ይሁዳ ፩፥፭።
34 መዝ ፻፱፥፫።
35 ዮሐ. ፲፯፥፭።



www.ethiopianorthodox.org

የስንፍና ነገር ይህ ነው ብለው ገደሉት:: ዳግመኛ የሦስቱ ወጣቶች [ሠለስቱ ደቂቅ] በሙሴ በዱን ባፈሉት በባቢሎን እቶን እሳት ውስጥ ነበልባሉ ከማንደጃው አፍ ፵፱ [አርባ ዘጠኝ] ክንድ ከፍ እስኪል መጣላቸው ወይም የዳንኤል በተራቡ አንበሶች ጉድጓድ መጣል፥ ከልዑል ቅዱሳን ደም ሚዛንና፥ ከነቢያት ጽድቅ ሚዛን ይልቅ የአዳምና ሔዋን ኃጢአት ሚዛን [እንደያለ] ባሰበ ጊዜ የአዳምና የሔዋን ከገነት የመው ጣታቸው ምክንያት አምላክ ለመሆን በመፈለጋቸው ነውና:: አምላክ የመሆን ፍላጐት ዕዳ እንደሚያሠለጥን እግዚአብሔር ተመለከተ::

የሔዋን አባት ከሔዋን ልጅ ዘንድ አደረ:: የአዳም አባት ዳግመኛ አዳ ም ን ለመሆን ተጨነቀ:: እነሆ! የእግዚአብሔር በረከት ከሕዝብ ወደ ሕዝብ ሲናኝ ተስተዋለ:: የአቤልን መሥዋዕት ተቀብሎ የቃየልን መሥዋዕት ግን አልተቀበለም:: ስለዚህ ቃየል አቤልን በቅንአት ገደለው:: የደሙ በቀል ጮኸ ወንድሙን እግዚአብሔር ቃየል የሚያርሳትን ምድር እስከሚ ረግም ድረስ በእግዚአብሔር ዘንድ ከሰሰው::[36] ስለዚህ ጳውሎስ የክር ስቶስን ደም ከጻድቁ አቤል ደም ጋር አመሳሰለ::

ከአቤል ሞት በኋላ ሴት ተወለደ:: ትርጓሜው ቃየል የገደለው የአቤል ምትክ ማለት ነው:: ስለዚህ የአቤል በረከት በሴት ልጆች ላይ ዐረፈ:: የቃየል ዘር ግን ከምድረ ገጽ ለመርገምና ለድምሳሴ ሆነ:: ኖኅ- ሴም፥ ካምና ያፌትን እግዚአብሔር ምድርን ያስፋለት አለው:: ሴምን ግን ከያፌት በረከት አስቀድሞ «የሴም አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ» ይለ ዋል:: ከያፌት በረከት በኋላ «እግዚአብሔር በሴም ቤት ይደር» ብሎ አስከተለ::[37] እነሆ! እግዚአብሔር በቤቱ እንደሚያድር ታወቀው:: በረ ከቱም እጥፍ ድርብ ሆነ:: እነሆ! በረከት ወደ ሴም ቤት ፈለሰች:: አብርሃም ከግብጻዊቷ አጋር እስማኤልን ወለደ:: በስተእርጅና ከሣራ ይስሐቅን ወለደ::[38]

ከኬጡራ፡- ዮቃጤንን፣ ዘንባረንን፣ ያክሰንን፣ ማይዳንን፣ ኢዮዝባቅን፥ ሴሃንን ወለደ:: ከሣራ ልጅ ይስሐቅ ዘንድ በረከት ፈለሰች:: እግዚአብሔር አብርሃምን፡- «ከይስሐቅ ዘር ይሾምልሃል:: ብሎታልና::»[39] ይስሐቅ ዔሳውንና ያዕቆብን ወለደ:: እግዚአብሔር በነቢይ አፍ፡- «ያዕቆብን ወደድኩ ዔሳውን

36. ዘፍ. ፬፥፰-፲፥ ዕብ. ፲፪፥፬::
37. ዘፍ. ፱፥፳፮::
38. ዘፍ. ፲፮፥፩፥ ዘፍ. ፳፩፥፪
39. ሮሜ. ፱፥፯::





ጠላሁ አለ::[40] እነሆ! የእግዚአብሔር በረከት ከዔሳው ወደ ያዕቆብ ተሻገረ:: ያዕቆብ ዐሥራ ሁለት ልጆችን ወለደ:: ያዕቆብ ለእያንዳንዱ እንደ ጸጋው የሚገባውን በረከታቸውን አሳያቸው:: ይሁዳን ግን ይሁዳ ወንድሞችህ አንተን ያመሰግኑሃል:: እጅህ በጠላቶችህ ደንደስ ላይ ነው:: የአባትህ ልጆች በፊትህ ይሰግዱሉ:: ይሁዳ የአንበሳ ደቦል ነው:: ልጄ ሆይ! ከአደንህ ወጣህ፡ እንደ አንበሳ አሸመቀ፥ እንደ ሴት አንበሳም አደባ፡ ያስነሣውስ ዘንድ ማን ይችላል? በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይ ጠፋም፥ የኀይም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፥ ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ የአሕዛብ መታዘዝም /ተስፋ/ ለእርሱ ይሆናል:: ውርንጫውን በወይን ግንድ ያስራል፥ የአህያይቱንም ግልገል በወይን ሐረግ ልብሱን በወይን ያጥባል፥ መጐናጸፊያውንም በወይን ደም:: ዐይኑም ከወይን ይቀላል፥ ጥርሱም ከወተት ነጭ ይሆናል::[41]

እነሆ! በይሁዳ ቤት የክርስቶስን መንግሥት ምልክት ዐሳየ:: ይሁዳም ከትዕማር ፋሬስንና ዛራን ወለደ፥ ፋሬስም ኤስሮምን ወለደ፥ ኤስሮምም አራምን ወለደ፥ አራምም አሚናዳብን ወለደ፥ አሚናዳብም ነአሶንንና የካህኑን የአሮንን ባለቤት ኤልሳቤጥን ወለደ፥ ነአሶን ለይሁዳ ወገን ለነገዳቸው አለቃ ነው:: እሱም ሰለሞንን ወለደ፥ ሰለሞንም ከራኬብ የጋይ ከፍል ከሆነ ከኢያሪኮ ዘማ ባአሶን [ቦኤዝን] ወለደ፥ ቦኤዝም ከሞ አባዊቷ ሩት ኢዮቤድን ወለደ፥ ኢዮቤድም እሴይን ወለደ፣ እሴይም በኩ ሩን ኤልያብን ተከታዩን አሚናዳብን ሦስተኛ ሣማህን አራተኛ ናትና ኤልን፥ አምስተኛ ራዳይን ስድስተኛ አሳንን ሰማዕን ዳዊትን ወለደ::[42]

እግዚአብሔር ሳሙኤልን፡- «በተንደህ ዘይቱን ሞልተህ ሒድ ወደ እሴይም ቤት ግባ፥ ከልጆቹ የመረጥኩትን እኔ ዐሳይሃለሁ::» አለው:: ሳሙኤ ልም ወደ ቤተ ልሔም ደረሰ፥ ከእሴይ ግቢ ገቡና «ልጆችህን አቅርብ» አለው:: ኤልያብን ባሰለፈው ጊዜ ሳሙኤል «እግዚአብሔር የሚቀባው በፊቱ ነው» አለ:: እግዚአብሔርም የመረጥኩት ይህን አይደለም አለው::

ዳግመኛ ሳሙኤል አሚናዳብን አቀረበው፥ በእግዚአብሔር ፊትም አሳየው:: እግዚአብሔር «ይህንንም አልመረጥኩም» አለ:: እሴይ ስድስቱን ልጆቹን አሳለፈ:: የእግዚአብሔር ፊት በሳሙኤል ፊት ወደ እነርሱ አልተመለከተም:: ሳሙኤል እሴይን፡- «የቀረ ሌላ ልጅ አለህን?» አለው::

40. ሮሜ. ፱፥፲፫ ሚል. ፩፥፪::
41. ዘፍ. ፵፱፥፰-፲፩::
42. ማቴ. ፩፥፩::



www.ethiopianorthodox.org

እርሱም፦ «ታናሹ ገና ቀርቶአል፤ እነሆም በጎችን ይጠብቃል» አለ። ሳሙኤልም፦ «በፍጥነት ልከህ አስመጣው» አለው። ዳዊትን አምጥተው በሳሙኤል ፊት አቆሙት። እግዚአብሔር ሳሙኤልን፦ «ያልኩህ ይህ ነውና ተነሥተህ ቅባው» አለ።[43]

በሌላም በኩል፦ «ባሪያዬን ዳዊትን አገኘሁት፣ ቅዱስ ዘይትን ቀባሁት፣ እጄ ትረዳዋለች፤ ክንዴም ታጸናዋለችና ጠላት በእርሱ ላይ አይጠቀምም፣ የዓመፅ ልጅም መከራ አይጨምርበትም። ጠላቶቹን ከፊቱ አጠፋለሁ፣ የሚጠሉትን አዋርዳቸዋለሁ፣ እውነቴና ምሕረቴም ከእርሱ ጋር ነው። በስሜም ሥልጣኑ ከፍ ከፍ ይላል። እጁን በባሕር ላይ ቀኙንም በወንዞች ላይ አኖራለሁ። እርሱ አባቴ አንተ ነህ፤ እኔም በኩሬ አደርገዋለሁ፣ ከምድር ነገሥታትም ከፍ ይላል።[44] ዳግመኛ እኔ ለዳዊት ሥልጣንን እሰጣለሁ። ለቀባሁት መብራትን አዘጋጃለሁ፣ ጠላቶቹን ኀፍረትን አለብሳቸዋለሁ፣ በእርሱ ቅድስናዬ ያፈራል።»[45]

በሌላም በኩል፦ «ለቀባው ለዳዊትና ለዘሩ ለዘላለም ምሕረቱን ያደርጋል።» ይላል።

ነቢዩ ኢሳይያስ፦ «ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፤ ከሥሩም ቁጥቋጦ ያፈራል፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ያርፍበታል።» አለ።[46] እነሆ! የእግዚአብሔር በረከት ወደ ዳዊት ቤት ፈለሰች። የዘይት ቀንድ በራሱ ላይ ፈሳ። ከቤቱም በትረ መንግሥት ወጣች። እግዚአብሔር የድኅነታችን ከዘሩ አስነሥቶአልና ዳግመኛ ወደ ገሊላ ነገሥታት አውራጃ አልገባም። የሄሮድስን ልጅ አልመረጣትም። ከታላላቅ የይሁዳ ነገሥታት ይልቅ የድኻ ልጅን መረጠ። እርሱ እግዚአብሔር ሳለ በሴት ማሕፀን አደረ። ደም ግባቷን ወድዶ ባፈቀራት ጊዜ በጽርሐ አርያም እናት ትሆነው ዘንድ ወደ ሰማይ አላሳረጋትም። ራሱ ወርዶ ከጸራቢው ከዮሴፍ ቤት አደረ (ሰው ሆነ) እንጂ። በኪሩቤል ሠረገላ ላይ ትሆነው ዘንድ ወደ ኪሩቤል ሠረገላ ላይ አላወጣትም። ናዝሬት ገሊላ በምትባል አገር ሳለች ራሱ በማሕፀኗ አደረ (ሰው ሆነ) እንጂ። በሥጋዌው ጊዜ በክብሩ አላሰፋትም። ገብርኤልን ድንግሏን በሆዷ ዘጠኝ ወር ትሸከመኝ ዘንድ ወደዚህ አምጣልኝ አላለውም።

43. ፩ኛ ሳሙ ፲፮፥፩-፲፫።
44. መዝ ፹፰፥፳-፳፯።
45. መዝ ፻፴፩፥፲፯-፲፰።
46. ኢሳ ፲፩፥፩።





እርሱ ትሕትናዋን ተሳትፎ ከገብርኤል ጋር ወርዶ ወደ ድኻ ቤቷ ገባ። መልአኩ «መንፈስ ቅዱስ ወዳንቺ ይመጣል» ባላት ጊዜ የአምላክ እናት ለመሆን በመንፈስ ቅዱስ መውረድ ተቀደሰች። «የልዑል ኀይልም ይጋርድሻል» ብሎ በደገመ ጊዜ በሰማያዊ አባቱ ኀይል አንድ ወልድን በመሸከም ጸናች። «ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» ባላት ጊዜ ያን ጊዜ ከእርሷ የሚወለደው የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አስተዋለች። ወልድ ከአባቱ ጋር ወዳለበት ወደ ጽርሐ አርያም ኅሊናዋን አወጣች [አሳረገች]። እርሱም ሰማያትን ዝቅ አድርጎ ወርዶ ራሱን ወደ ማሕፀኗ መለሰ። ዳግመኛ ድንግል መልአኩን፦ «እንደ ቃልህ ይሁንልኝ» አለችው።[47] ያን ጊዜ ቃል ከእርሷ በተዋሕዶ ሰው ሆነ። ዐይታ እንዳትደነግጥ ተመልክታ እንዳትፈራ በሥጋዌ ጊዜ ዐርባዕቱ እንስሳ [ኪሩቤልን] ከእርሱ ጋር አላመጣም። ሰማያትን በሚጠብቁበት ሥርዐት ሰማያውያንን በዚያ ተወ። ለቅዱሳን መላእክት የሚበቃ ምድራዊ ሥርዐትን በዚህ ሠራ። እዚያ በአባቱ ቀኝ አለ። እዚህ በእናቱ በድንግል ማሕፀን አለ በዚያ [በሰማይ] የማይታይ ኀይል ነው። በዚህ [በምድር] ከሚዳሰስ ሥጋው ጋር የሚዳሰስ ኀይል ነው።

በዚያ የእሳት ሥዕል ዐርባዕቱ እንስሳት ይሸከሙታል። በዚህ በትስብእት ትዳና አራቱ ጠባዕያት ይሸከሙታል። በዚያ አባት ያለ እናት በዚህ እናት ያለ ምድራዊ አባት አለው። እዚያ ገብርኤል በፍርሀት ይቆማል። እዚህ በደስታ ያበሥራል። በዚያ በጽርሐ አርያም ከአብ የማይታይና የማይደነቅ የልደት ክብር አለው። በዚህ በቤተልሔም ከድንግል የሚደነቅ የልደት ክብር አለው። በዚያ ሰማያውያን ካህናት በወርቅ ጽንሐሕ የዕጣን መዓዛ ያቀርቡለታል። በዚህ ከሰብአ ሰገል ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ ይቀርብለታል።

በዚያ ከግርማው የተነሣ ሱራፌልና ኪሩቤል ይንቀጠቀጣሉ። በዚህ ድንግል ማርያም ታቀፈችው፤ ሰሎሜም ተላላከችው። በዚያ በፊት የመባርቅት ነጸብራቅ ያንጸበርቃሉ ከአዳራሹም የእሳት ወላፈን ይወጣል። በዚህ አህያና ላም በትንፋሻቸው ያሟሙቁታል።

በዚያ የእሳት መንበር በዚህ የድንጋይ በረት አለው። በዚያ የዕብነ በረድ ድንጋይ የሰማይ ምንጣፍ በዚህ የከብቶች ማደሪያ [ማረፊያው] ሆነ። በዚያ በትጉሃን ማደሪያ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት በዚህ በእንስሳት በረት ነበር። በዚያ የዕድሜ ርዝማኔው የማይታወቅ የዳንኤል ብሉየ

47. ሉቃ ፩፥፳፮-፴፱።



www.ethiopianorthodox.org

መዋዕል [ዘመናትን የሚያስረጅ] ነበር። በዚህ በሰው ልጅ የዕድሜ መጠን አረጋዊ ዮሴፍ ይታቀፈዋል። በጽርሐ አርያም ዐንሳው ቢሆን ኖሮ ክብርና ልዕልና ለብቻዋ በሆነ ነበር። እኛም በልዕልናዋ ጥቅምን ባላገኘን ነበር። በሰማያት የሚደረገውን ምስጢር ምን ዕናውቃለን? በአርያም ያለውን የተሰወረውን ምን ዕናያለን?

በኪሩቤል ሠረገላ ላይ በነበረ ጊዜ በምድር ባይመላለስ የጥምቀትን ፈለግ ለማንም ባላሳየ ነበር። «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው»[48] የሚለው የአብ ምስክርነት በማንም ላይ ባልሆነ፥ መንፈስ ቅዱስ በነጭ ርግብ አምሳል በማንም ራስ ላይ ባልወረደ፥ የሥላሴ ወገን ባይታይ ኖሮ በማን ስም በተጠመቅን ነበር? ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱን፦ «ሒዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው።» አላቸው።[49] አብ ማን ነው? ወልድስ ማን ነው? መንፈስ ቅዱስ ማን ነው? እንዳይሉ በዮርዳኖስ ወንዝ የሥላሴን ወገን ዐሳየ። በሰው ልጅ አምሳል ባይጐለምስ፥ በሰው ልጅ አምሳል ባይታይ ስለ ደኅንነታችን ማን በታመመ ነበር? እነሆ! የሰው ልጅ ከሰማይ መላእክት ይልቅ ከበረ፤ እግዚአብሔር ከሴት ተወልዷልና። ስለዚህ ጳውሎስ «የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም።» አለ።[50]

ስለዚህ የሮጦኖስን ዘለፋ ፈጽመን፥ የአምላክን ልጅ የሥጋዌ በዓል እናድርግ። ለተሸከመችው ማሕፀን ምስጋና እናቅርብ። ለታቀፈችው እንስገድ፤ ከእረኞች ጋር እናመስግን፤ ከሰብአ ሰገል ጋር እጅ መንሻ እናቅርብ። እንደ ዮሴፍ እናድንቅ፤ እንደ ሰሎሜ እንላላክ። ወደ ተኛበት በረት እንስገድ፤ ወደ ተጠቀለለበት በረት እናስፍስፍ /እናሸብሽብ/። ሰውን ለወደደ ለእግዚአብሔር በላይ በሰማይ ክብር ምስጋና፥ ሰላምም በምድር ይሁን እንበል። እግዚአብሔር ሰው ሆነ፤ የአዳም ልጅም የእግዚአብሔር እናት ሆነች። ለእርሱ ክብር ምስጋና ለእርሷም የክብር ስግደት ለዘላለም ይሁን። አሜን።

ቤተ ክርስቲያንን ያቀለለ፥ የወልድን መለኮት የለየ፥ የሚያምኖትን

48. ማቴ. ፫፥፲፯።
49. ማቴ. ፳፰፥፲፱።
50. ዕብ. ፪፥፲፮።





ገመድ የበጠሰ የገሞራ ሐረግ የሮጦኖስ ዘለፋ ተፈጸመ። የዐምሐራ አገር ሰው ጊዮርጊስ የቤተ ክርስቲያን ክህናት ትምህርት ልጅ፥ የማይመዋሩትን መንገድ የወደደ ይህን አለ። ድንግል ተቀዳሚ ተከታይ ከሌላው የበኩር ልጇ ዘንድ ኃጢአቱን ታስተስርይለት ዘንድ፥ በዚህ ዓለም ከመከራ ታድነው ዘንድ፥ በሚመጣው ዓለም ወደ ቤቷ ታስገባው ዘንድ፥ ከሚደነቅ የሕይወት ማዕድ ታበላው ዘንድ፥ ከምስጢር ወይን ታጠጣው ዘንድ፥ ለዘወትር መከራን እንዳያይ ከመከራ ደጃፍ ታርቀው ዘንድ ለምኑለት። ይህን መጽሐፍ ሥነ ምግባሯ በተከበረበት፥ የክብሯ ገናናነት በታየበት በመታሰቢያዋ ዕለት ታኅሣሥ ፳፱ ቀን እንዲነበብ አዘዘ። ለዘላለሙ። አሜን።



www.ethiopianorthodox.org

# [ምዕራፍ ፮]

## የጥያቄት ምንባብ

እንደ ናዝራውያን ሥርዐት በምንሠልሰው፤ እንደ ሱራፌል በምን ቀድሰው በጽርሐ አርያም አትሮንሱን ባስቀመጠ በእግዚአብሔር ስም የሚቸ ኀሊና የማይፈልገው፣ የሰው እጅ የማይዳስሰው፣ በተራሮች ጫፍ ላይ የጭጋግ ተንን የሚያጠፋው፤ ያለ ጨኸት የሚያሻሽለው፤ በአ የራት ውስጥ የሚያታግል ሰፊውና የሰማይን ፊት የደመና መጐናጸፊያ የሚያለብሰው ለእርሱ ክብር ምስጋና ለዘላለም ይገባል። አሜን።

«ወልድ አብን በእርሱ ላይ ስላለ ክብር ያየው ዘንድ አይችልም፣ መን ፈስ ቅዱስ ወልድ በእርሱ ላይ ስላለ ክብር ያየው ዘንድ አይችልም፣ መላእ ክት መንፈስ ቅዱስን በእርሱ ላይ ስላለ ክብር ያዩት ዘንድ አይችሉም፣ የሰው ልጆች በእነርሱ ላይ ስላለ ክብር የሰማይ መላእክትን ይመለከቷቸው ዘንድ አይችሉም፤» የሚልን የአርጌንስን ዘለፋ እንመለከታለን።[1]

አምስት ማዕርጋት ሥርቶላቸው አይመለከቱም ይላል። በጠባዩ አዋኪ፣ በአንደበቱ ሸንጋይ፣ ዋዛ ፈዛዛ የሚወድ፣ በዐይኑ ትዕቢተኛና ልበ የታበየ አርጌንስ በእስክንድርያ አብያተ ክርስቲያናት ሁከትን ይዘራል። በማብዕ አውራጃዎች እሾኽን ዘራ። ከሊጳስ ቆጶሳት የተለየ ትምህርት ያስተምራል። ክፋትን ሳያደርግ አይተኛም። አመለካከቱ ግን ከመና ፍቁ አርዮስና ሹመትን ከሚወድ ሚሊጢስ ጋር አንድ ነው። አርዮስ ስለ ክሕደቱ በንጉሥ ርዳታ ምእመናንን አሳድዶ ቤተ ክርስቲያንን በትኗል። ከዚህ በኋላ በርቱዐ ሃይማኖት በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዘመን ሊቃውንት በኒቅያ ጉባኤ በአደረጉ ጊዜ ጸንቶ ቆመች። ሚሊጢስ የቅ ዱስ ጴጥሮስን ጽጽስና በመንጠቅ ቤተ ክርስቲያንን ጨቁኗል። ትችቱ ግን ስለ ሃይማኖት ፍቅር አይደለም። ሹመትን በመውደድ እንጂ። አርጌንስ ግን ሃይማኖትን በመለወጥ ሁከትን በማድረግ ነው፤ የወልድን ከአብ ማነስና የመንፈስ ቅዱስን ከወልድ ማነስ ያስተምራልና።

1. አርጌንስ የተወለደው በ፻፹፭ ዓመተ ምሕረት በእስክንድርያ ነው። እናትና አባቱ ክርስቲያኖች ናቸው። አባቱ ሊዎንዳስ ይባላል። በ፪፻፪ ዓመተ ምሕረት ሴፕቲሞየስ ሳዊሮስ የጣለው ክርስቲያኖችን በመግደል በዚያ ጊዜ አባቱም በሰማዕትነት ሙቷል። አርጌንስ የመጀመሪያ ትምህርቱን የተማረው በእስክንድርያ ትምህርት ቤት ሲሆን በትምህርት ኰትኵቶ ያሳደገው ቀሌምንጦስ በእስክንድርያ ነው። የአርጌንስ የምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት እንደ መምሩ እንደ ቀሌምንጦስ ትምህርት የተዘበራረቀና የተምታታ ነበር። አባ ጎርጎርዮስ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ ገጽ፹፫-፹፬።





አርጌንስ ወልድ ከአብ ያንሳል እንዴት አለ? ከወንጌል ቃል ከወደዳችሁኝ በእኔ በተደ ስታችሁ እኔ ወደ አብ ዘንድ እሄዳለሁ።[2] አብ ይበልጠኛልና የሚለውን ምክንያት አደረገለት። እንደ ዐይን ጥቅሻ እና እንደ ንስር ክንፎች መርገብገብ ያህል በሰዓትና በዕለት ሳይቀድመው እንዴት አብ ወልድን ይበልጠዋል? አብ ይበልጠኛል የሚለው በእውነት [በእርግጥ] በአባቱ ቀኝ እስከሚቀመጥ ድረስ መለኮት ትስብእትን ይበልጠዋል በአባቱ ቀኝ ከተቀመጠ በኋላ ግን አብ ይበልጠኛል አይልም [አላለም]። እንደ ዋና [ዳግመኛ]፦ «ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ» አለ።[3] ከዕርገቱ አስቀድሞ «ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ» ማለቱ ግን የትስብእትን ትሕትና ጉዳና ሲያሳይ ነው። ለእነርሱ የጸጋ አባታቸው ነው። ለእርሱ ግን የባሕርይ አባቱ ነው። ለእነ ርሱ አምላካቸው ነው። ለእርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ነው። ከዕርገቱ በኋላ ግን ትስብእቱ ከመለኮቱ ጋር ትክክል ሆነ [ነው]። በኦሪት «አዳም መልካ ምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ»[4] የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ተፈጸመ። ስለ አብና ወልድ እኩልነት [ዕሪና] ጌታችን በወንጌል «እኔና አብ አንድ ነን» አለ።[5] ዳግመኛ ፊልጶስ ጌታችንን «አብን ዐሳየንና ይበቃናል» ያለውን ስማ። «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እኔን ያዩ አብን ዐይቷል።» [እኔን ያየ አባቴን ዐይቷል] አለው። እንደ ገና «እኔ በአብ እንዳ ለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምኑም?» አለ።[6] ዳግመኛ «አባት ሆይ፤ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ አለ። ከሰማይም አከበርኩህ ዳግመኛ አከብርሃለሁ የሚል ቃል መጣ።»[7]

አርጌንስ ሆይ! ወልድ በአባቱ ዘንድ እንደ ተከበረ ዕወቅ [አስተውል]፤ አባቱ ካከበረው እንዴት ያንሳል ትለዋለህ? አንተ ከክርስቲያን ክብር ትጐድላለህ እንጂ ወልድን ከአባቱ ዘንድ ጉድለት የሚያገኘው አይደለም። ስለ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ እንደ ሚያንስ ስትናገር አት ታዘብምን? [አታፍርምን] በወንጌል፦ «እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኙ እርሱም ከአብ የሚወጣው የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ

2. ዮሐ ፲፬፥፳፰።
3. ዮሐ ፳፥፲፯።
4. ዘፍ ፫፥፳፪።
5. ዮሐ ፲፥፴።
6. ዮሐ ፲፬፥፰-፲፩።
7. ዮሐ ፲፯፥፭።



www.ethiopianorthodox.org

እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤ እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ» የሚለውን ስማ::[8] «ከአብ ዘንድ ይወጣል» ባለ ጊዜ በዚህ እንኳ አታስተውልምን? ከእርሱ የሚወጣ ከሆነ እንግዲህ እንዴት አይመለከተውም? በማስከተልም፦ «እናንተም ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ከነበረው ጋር ምስክሮቼ ናችሁ» ይላል:: ከመጀመሪያ ከእርሱ ጋር ከነበረ እንዴት አይመለከተውም? እንዴትስ ከእርሱ ያንሳል? ቅዱስ ጳውሎስም፦ «እንዲህ ከሆነ የእግዚአብሔርን ልቡን ማን ያውቃል? መካሪስ ማነው? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን::[9] እኔም ወንድሞች ሆይ፤ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም» አለ:: እነሆ! ቅዱስ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን «የክርስቶስ ልብ» በማለት ሰየመው:: እርሱ የክርስቶስ ኅሊና ከሆነ እንዴት አይመለከተውም? ኅሊና ሐሳብን ከመመልከት ይበልጣልና፤ ልብን መመርመር የውጭን ከመመልከት ይበልጣልና፤ ደግመኛ ቅዱስ ጳውሎስ፦ «መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው ግን ኹሉን ይመረምራል:: እርሱን ግን የሚመረምረው የለም፤ እኛ ግን የተሸሸገውን የሚገልጥና የተደበቀውን የሚመረምር የእግዚአብሔር ልብ አለን» አለ:: ስሎሉ ሆይ! ወልድም አብን እንደ ሚመለከተው ዕወቅ [አስተውል]:: በወንጌል እንደተነገረው ወልድ አብ ካላሳየው በቀር ምንም ምን ሊያደርግ አይችልም እርሱ የሚያደርገውን እንደ እርሱ ያደርጋል ወልድም እንደ እርሱ ያደርጋል አብ ልጁን ይወደዋልና እርሱ የሚያደርገውን ያሳየዋል::

እናንተም ትደነቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል:: ስለ መንፈስ ቅዱስ አስቀድመን ነግረናችኋል:: እናንተ ዝንጉዎች ከእንግዲህ፦ «ወልድ ከአብ ያንሳል፤ አይመለከተውም» አትበሉ:: «መንፈስ ቅዱስም ከወልድ ያንሳል፤ አይመለከተውም» አትበሉ::

እኛ ግን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ባሕርይ፤ አንድ መንግሥት፤ አንድ መገለጥ፤ አንድ መለኮት፤ አንድ ሐሳብ፤ አንድ ፈቃድና ሥርዐት እንደ ሆኑ እናምናለን:: በባሕርይ፤ በአገዛዝ፤ በመገለጥ፤ በሐሳብ፤ በመፈቃቀድና በሥርዐት አንድ ናቸው:: ፈቃዳቸው ሕግና ሥርዐታቸው ችሎታቸው አንድ ነው:: እንደ አሕዛብ አማልክት በየሥርዐታቸው ሦስት አማልክት አይሏቸውም:: በሦስትነት ያለ፤ አንድ አምላክ ይሏቸዋል እንጂ:: እንደ አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ አንዱ ከአንዱ

8. ዮሐ. ፲፭፥፳፮-፳፯::
9. ፩ቆሮ. ፪፥፲፮::





ቀድሞ እንደ ነበረ አንዱ አንዱን፤ ሁለተኛው ሦስተኛውን አይከተለውም:: የዐይን ቅንድቦች አገላለጥ፤ የመብረቅ ብልጭታ ያህል አብ ከወልድ ወልድ ከመንፈስ ቅዱስ የቀደመ ህልውና የለውም:: እናታችሁ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ ትታመናለች:: «አቤቱ፤ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል? በተቀደሰውም ተራራህ ማን ይኖራል?» ተብሎ እንደ ተጻፈ[10] በሙሽራዋ ተደስታ በወልድ ክንድ ላይ ታርፋለች:: «ግራው ከራሴ በታች ናት፤ ቀኙም ታቅፈኛለች»[11] ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ «ቅዱስ መንፈስህ በጽድቅ ምድር ይመራኛል»[12] ተብሎ እንደ ተጻፈ በመንፈስ ቅዱስ ብርሃን መብራትነት ወደ ገነት ድንኳኖች ትመራለች:: ከዚህ በኋላ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቅ ፈልጋ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ትጓዛለች:: ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ወርዳ መጀመሪያ ከዮርዳኖስ ወንዝ ከወጣች በኋላ የክርስቶስ ባሪያ ትባል ዘንድ የትብዐ በለሳን [የትብዓ ሚሮን] ማኅተም ትቀበላለች:: ትብዐ በለሳን የሃይማኖት ኀይል ነውና:: ሐዋርያት በዲድስቅልያ ትምህርት እንደ ተናገሩት በጥምቀት መወለድ ግን ክርስቶስ ከድንግል የተወለደውን ልደት ይመስላል:: ክርስቶስ ከድንግል ማርያም እንደ ተወለደ ከእርሷ ከተወለደ በኋላ ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይፈታ በድንግልና ማኅተም ተገኘ:: እንደዚሁም ከጥምቀት ሆድ (ከጥምቀት) [ከማሕፀነ ዮርዳኖስ] ወጥተን የምንወለደው ይህ ልደት ከጥምቀት ሆድ (ማሕፀን) ከውሃ ወጥተን በመጠመቂያ ውስጥ የመግቢያና የመውጫ ፍለጋው አይገኝም:: በመዝሙር፦ «መንገድህ በባሕር ውስጥ ነው፤ ፍለጋህም በውሃ ውስጥ ብዙ ነው፤ ፍለጋህም አይታወቅም» ተብሎ እንደ ተነገረ::[13]

እንግዲህ ወደ ተውነው ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ነገር እንመለስ:: ከዚህ በኋላ ከቅዱስ ጳውሎስ ቃል፦ «በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው» የሚለውን ሰምታ አካሔዷን አሳምራ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ትወጣለች:: ዳግመኛ ቅዱስ ጳውሎስ፦ «በራሳችሁ፤ በእጃችሁም የመንፈስ ቅዱስን ሰይፍ ያዙ»[14] ብሎ እንደ ተናገረ በራሷ ላይ የዕንቍ ጌራ ትደፋለች:: ይኸውም የሃይማኖት አክሊል ነው::

10. መዝ. ፲፬፥፩::
11. መኃ. ፰፥፫::
12. መዝ. ፻፵፪፥፲::
13. መዝ. ፸፮፥፲፱::
14. ኤፌ. ፮፥፲፯-፲፰::



www.ethiopianorthodox.org

በእጆቿም የክብር ቀለበት ታጠልቃለች። ይኸውም የድኅነት ምልክት የጸጋ ማስተብ ነው።

ከዚህ በኋላ አብርሃም በሚቀመጥበት ዘንድ ይስሐቅም በተሠዋበት በተቤዠበት ዘንድ ወደ ሰርግ ቤት ዐጸድ ትገባለች። አባታችን ያዕቆብ፡- «የወርቅ መሰላል ከምድር እስከ ሰማይ ተተክላ የእግዚአብሔር መላእክት ሲወጡባት ሲወርዱባት በተመለከተበት ዘንድ፤ ሙሴ ስለ እስራኤል ልጆች ዘለዓ ምስክር ይሆኑ ዘንድ የትእዛዝና የሕግ ጽላትን በተሸከመበት ዘንድ፣ መልከ ጼዴቅ ኅብስትና ወይን ለቤተ ክርስቲያን ምሥጢር ሥርዐት ባወጣበት ዘንድ፣ ዳዊት በእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ፊት፡- «አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ፤ አንተና የመቅደስህ ታቦት»[15] እያለ በሚዘምርበት ዘንድ፣ አሳፍ በሚቀኝበት ዘንድ፤ የቆሬ ልጆች በመሰንቆ በሚያመሰግኑበት ዘንድ፣ ነቢዩ ኢሳይያስ ለወዳጄ ምስጋና እያለ በሚዘምርበት ዘንድ፡ ኤርምያስ ደንጋይ ሰንጥቆ ወደ ውስጧ የአዳራሽ ድንኳን መሥሪያ ዕቃ አስቀምጦ የድንጋዩን ስባሪ አተማት። እንደ ብረት መሸፈኛ ሆነችው፡ መከፈቻዋንም ለፀሐይ ሰጠ፡ ኤልያስ የእግዚአብሔር መልአክ የሰጠውን የተዘጋጀ እንጀራ በልቶ በዚያም ምግብ ኀይል አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በተጓዘበት ዘንድ፤ ዕዝራ ሱቱኤል ከዑራኤል እጅ የምስጋና ጽዋን ጠጣ። የትእዛዝና የሕግ መጻሕፍትን የምታስተውለው ልቡናው በደረቱ ውስጥ ከብዶ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት አፉ ሳይዘጋ በተቀመጠበት ዘንድ፣ ዘካርያስ ነጫጭና ዝንጉርጉር ፈረሶችን በተመለከተበት ዘንድ፣ ሕዝቅኤል የእሳት ሠረገላ ወደ ተመለከተበት፡ ዳንኤል ብሉየ መዋዕል [ዓለም ሳይፈጠር፡ ዘመን ሳይቆጠር፡ ቅድመ ዓለም የነበረ] ሲሆን ከሰው ልጅ ጋር ተቀምጦ መንበሮችን በተመለከተበት ዘንድ፣ ዕንባቆም በሁለት እንስሳት መካከል እግዚአብሔርን በተመለከተበት ዘንድ፣ ሁሉም ነቢያት በትንቢት አርጋኖን ስብከትን በሚያደምጡበት ዘንድ፣ የገሊላ ሕፃናት በማኅሌት ቃል ኅሊናን የሚመስጥ፡ ልቦችን [ኅሊናትን] የሚማርክ፡ አጥንቶችን የሚያለመልም ምስጋና በሚያመሰግኑበት ዘንድ፣ ጴጥሮስ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ በተቀበለበት ዘንድ፣ ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን ብርሃን ይሆን ዘንድ ወደ ተጠራበት፡ ዮሐንስ እንደ መለከት ቃል ምሥጢረ መለኮትን እየሰበከ በሚጮኽበት

15. መዝ. ፻፴፩፥፰





ዘንድ፣ ሁሉም ሐዋርያት በርደተ መንፈስ ቅዱስ የእሳት ልሳን በጠጡበት ዘንድ፣ ማኅበረ መላእክት የእግዚአብሔርን መሠዊያ ለመጐብኘት በሚጨፍሩበት ዘንድ፣ የሰማዕታት ማኅበር የሕማማቸው [የመከራቸውን] እና የድካማቸውን ዋጋ አክሊል በተቀዳጁበት ዘንድ፣ የደናግልና የመነኮሳት ማኅበርም የድካማቸውን ዋጋ አክሊል በተቀዳጁበት ዘንድ፣ ከዚህም በኋላ በሙሽራው የዙፋን አጐበር [መሠዊያ] ለምእመናን ምግብ ሙሽራው ይታረዳል።

መታረዱን ከማየት የተነሣ ጉልበቶቿ ይርዳሉ [ይንቀጠቀጣሉ] ደሙ በመሠዊያው ቀንድ ላይ ሲፈስ በተመለከተች ጊዜ አንጀቷ ይታወካል። ፍርሀት ሥጋውን ትበላለች በመንቀጥቀጥም ደሙን ትጠጣለች። ከዚህም በኋላ በልቧ ውስጥ የሚያምናት ላህብ [እሳት] ይቀጣጠላል። በሆዷ ውስጥም የፍቅሩ ሞገድ ይፈላል።

ዛሬም በሥላሴ መለኮት ላይ ስድብን የተናገረ የአርዮስን ዘለፋ ፈጽሞ፡ የሁሉም ፍጥረት ገዢ ለሆነ ለአብ ምስጋና ይገባል። የመንግሥትና የኀይላት ጌታ ለሆነው ለወልድ ምስጋና ይገባል። ልብንና ኩላሊትን ለሚመረምር ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል ለዘላለሙ አሜን።

ኅሊናው የእንስሳ ልቡናው ልምሾ የሆነ የአንርጊንስ ዘለፋ ተፈጸመ። ከአንድ የአብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ መለኮት ለአንዱ ጉድለት እንዳይሆን ለሥሉስ ቅዱስ ሃይማኖት ቀንቼ በአፈ ቃል ደርሼ [ጽፌ] የቀሲስ ሕዝበ ጽዮን ልጅ እኔ ጊዮርጊስ አጻፍኳት። ለእርሱ በባሕርና በየብስ በተራራ መሐል እንዳለ ረባዳ ሰፊ ምድርና በደሴቶች ምስጋና ይገባል። ለእርሱ ከሁሉም ፍጥረት ዘንድ ምስጋና ይገባል ለዘላለም አሜን።



www.ethiopianorthodox.org

# [ምዕራፍ ፰]

## የቃና ዘገሊላ ምንባብ

የማይደፍን ልዑል የማይታይ፡ በሦስትነት በአንድነት በሚኖር በእግዚ አብሔር ስም፥ የማይነኩት እሳት የማይዳስሱት መንፈስ፡ የማያስተ ውሉት ኀይል የማይሸሙት ንጉሥ ነው። በመለኮቱ አምላካችን በቸርነቱ አባታችን ለሆነ ለእርሱ ለዘላለም ምስጋና ይገባል። አሜን።

«የመለኮት ቃል ሥጋ፣ ደም፣ ዐፅም፣ ጸጉር፣ ደምሥር ወደ መሆን ተለወጠ።» የሚሉ የኀስፎሎችን (የዘንጉአንን) ዘለፋ እንጽፋለን። እናንተ ሰነፎች፡ የመለኮት ኀይል ሥጋ ወደ መሆን፡ ትስብእትም መለኮት ወደ መሆን እንደ ተለወጠ ይመስላችኋልን? የሎጥ ሚስት የጨው ሐውልት እንደ ሆነችው አይደለም።[1] የከለዳውያን ንጉሥ ናቡከደነጾር የዱር አውሬ እንደ ሆነ ዳግመኛ ሰው ወደ መሆን እንደ ተመለሰ አይደለም።[2] የቃና ውሃ ወይን እንደ ሆነ አይደለም።[3] እነዚህ ሦስቱም ከህልውናቸው ተለውጠዋል። በፈቃደ እግዚአብሔር እንጂ በፈቃዳቸው አይደለም።

የሎጥ ሚስት ወደ ሰዶምና ገሞራ እንዳትመለስ ያዘዛትን የእግዚ አብሔርን ትእዛዝ በመተላለፏ የጨው ሐውልት ሆነች። ለመመልከት በተመለሰች ጊዜ እንደ ምድጃ ጢስ ያለ ጢስን ተመለከተች። ከዚህ በኋላ ፍጹም የጨው ሐውልት ሆነች። ለማሽተት ትንፋሽ እና ለመንቀ ሳቀስ ነፍስ አልቀረላትም። እግዚአብሔር ድንጋይ አድርጓት ህልው ናዋን ወደ ሐውልትነት ለውጧታልና። ንጉሥ ናቡከደነጾርም በሥልጣኑ የዓለም ጌታ እንደ ሆነ አስቦ በአጽናፈ ዓለም ሁሉ ሥልጣንና ማሸነፍን ለሰጠው እግዚአብሔር አልተገዛም። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር የምድር አውሬ አደረገው። በአውሬነት አስቀምጦ በማመሳሰስ ገሥጸው። የአራዊት ፀጉርና የእንስሳ ጥፍር አደረገለት እንጂ የሰው ልጅ ፀጉርና ጥፍር አላስቀረለትም። ከአራዊት ጋር ተምሮ ሣር እየበላ በገዳም ውስጥ ሰባት ዓመት ተቀመጠ፤ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይበቀላልና።

ዳግመኛ እግዚአብሔር ኀሊናውን ሰውን ወደ ማስተዋል፡ መልኩንም

1. ዘፍ. ፲፱፥፳፮።
2. ዳን. ፬፥፳፩-፴፫።
3. ዮሐ. ፪፥፱-፲፩።



እንደ ሰው ልጅ መልክ መልሶ በመንግሥቱ ላይ አስቀመጠው። እግዚ አብሔር ለተነሳሒያን ይቅር ባይ ነውና ከዚህ በኋላ እርሱም ለእግዚ አብሔር ክብር ተገዛ። የመንግሥትና የነገሥታት ጌታ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ዐወቀ።

ወይን የሆነ የቃና ውሃም በወይን መርገጫ ረግጠው፡ በመጭመቂያ ውስጥ ጠምቀው የሠሩት የልማድ ወይን አይደለም። ሙሽራው እንዳ ያፍር ሰርገኞችም እንዳይረኩ የእግዚአብሔር ልጅ የተአምራቱ ወይን ነው እንጂ። የጌታችን እናት «የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም፡ ወይናቸው አልቆ አልና [ይህን አትልል]» ብላዋለችና። ጌታችን ኢየሱስም፦ «አንቺ ሆይ! ምን ትያለሽ፡ ጊዜዬ ገና አልደረሰም።» አላት። በልቡ ውስጥ ለተጻፈ ፍቅሯ የሚሻለውን መለሰ። እርሷ ስለ ምድራዊ ወይን ማለደ ችው፡ እርሱም አመስጥሮ ከጐኑ ስለ ሚቀዳው ወይን ደሙ ተናገረ። «ጊዜዬ ገና አልደረሰም» ማለቱ ግን «ከጐኔ በሚፈሰው በምስጢር ወይን ምእመናንን አረካቸው ዘንድ በጦር የምወጋበት ሰዓት አልደረሰም።» በሚለው ይተረጐማል።

ከኅቶአን ጋር በመቀመጥ፡ በመዳሰስ ከአንቺ በነሣሁት ሥጋ ሬኅበና ጥምን ማንኛውንም መከራ በመቀበል የአባቴን ተአምራት በምድር ላይ ዐሳይ ዘንድ ሦስት ዓመታት ቀርተውኛልና። ከላይ ስለ ተናገረው ስለ ተአምራቱ ወይን ይህን አለ። እኔም ጊዜው ደርሶ ሥራውን አላዘገየም አለዋለሁ። ያን ጊዜ ውሃ ቀድተው በስድስት የድንጋይ እንስሮች ይሞሉ ዘንድ አዘዘ። ውሃው ወይን ወደ መሆን ተለወጠ። ውሃውን ወደ ወይን የለወጡት እንስሮች አይደሉም። ወደ እንስሮች ውሃውን ይሞሉት ዘንድ ያዘዘው ውሃውን ወይን ወደ መሆን መለሰው እንጂ። እንስሮች ግን እነርሱ ውሃውን ወይን ወደ መሆን የመለሱት አይደለም። አይሁድ ዘወትር ሁለትና ሦስት እንስራ በሚይዙ ጋኖች ይጠምቃሉ። የቃና ወይን በሕገ ኦሪት ትመሰላለች። የጠሟትን አላጸደቀቻቸውምና፡ ነገር ግን በመዓዛዋ ጣዕም ልባቸውን አስደሰተች። እንደዚሁም ኦሪት አስተ ድመው የተቀበሏትን አላጸደቀቻቸውም። በመምጣቷ ልቡናቸ ውን አስደስታለች፡ የእግዚአብሔር ቃል ናትና። ስለዚህ ጳውሎስ «በሕገ ኦሪት መጽደቅ በተሳናቸው ጊዜ በኦሪት ያሉትን ወደ ወንጌል ይመል ሳቸው ዘንድ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደ ልጁን ላከ።[1] [አለ]።

1. ገላ ፬፥፬።



www.ethiopianorthodox.org

ውሃው በቃና ወይን ወደ መሆን እንደ ተለወጠ እንደዚሁም ሙሴ ፈርዖ ከፊቱ እስከሚሸሸ ድረስ የሙሴ በትር በደብረ ሲና እባብ ወደ መሆን ተመልሷል:: ዳግመኛም ሙሴ እስከ ሚያገኙበስ በትር ወደ መሆን ተመልሷል:: ሙሴ በትሩን አንሥቶ በፈርዖንና በመኳንንቱ ፊት በዚያ በትር ተአምራት አድርጓል::[5] የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወይኑ ደሙ በሕገ ወንጌል ተመስሏል፡ አውሬ ማድረግና ማጽደቅ ችሏልና::

መድኃኒታችን ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው ብሏልና፡ «ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፡ ሞትንም አይቀምስም::» ብሏልና[6] ስለ ወንጌሉም፡- «ያመነ የተጠመቀ ይድናል፡ ያላመነ ግን ይፈረድበታል::» አለ::[7]

እመ አምላክን ከልጇ ዘንድ፡- ወይን ስለመፈለጓ ዜና እንመለስ «ወይን አልቆባቸዋልና» ስትል ስለምን ለመነችው? ከውሃ ወይንን ይቀዳ ዘንድ ዐውቃ [ተረድታ] ይሆንን? ከዚያ ሰዓት በፊት እንደዚህ አላደረገምና:: «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የተአምራት መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፥ ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ»[8] ብሎ የሐንስ ወንጌላዊው እንደጻፈው ውሃውን ወደ ወይን እንደሚለውጠው ድንግል አላወቀችምን? ነገር ግን በአብ ጽላሎት እንደ ፀነሰችው በልዑል ኀይል እንደ ወለደችው ታውቃለች:: ስለዚህ ድንግል ስለ ወይን ትማልደው ዘንድ ደፈረች:: አባቱ ሰማያዊ እንደ ሆነ ከበሥራት መልአክ ዘንድ ተረድታለችና [ተገንዝ ባለችና]:: ስለዚህ በልቧ የተአምራት አድራጊ ልጅ እንደ አባቱ ተአምራትን ያደርጋል አለች:: ደቀ መዛሙርቱ ግን ስለ ወይን አልማለዱትም፡ አባቱን አያውቁምና እርሱም የዮሴፍ ልጅ ይመስላቸዋል:: መልአኩ ለእናቱ እንደ ተናገረ ለእነርሱ አልነገራቸውምና:: ተአምራትም ካደረገ በኋላ ከነቢያት አንዱ እንደ ሆነ እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አላመኑትም:: ስለዚህ በፊልጶስ ቂሣርያ አገር፡- «ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል?» ብሎ ጠየቃቸው:: እነርሱም «አንዳንዱ መጥምቁ

5. ዘፀ. ፯፥፳-፳፫::
6. ዮሐ. ፮፥፶፮-፶፱::
7. ማር. ፲፮፥፲፮::
8. ዮሐ.፪፥፲፩::





ዮሐንስ፣ ሌሎችም ኤልያስ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት:: እርሱም፡- እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው:: ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡- አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» አለ:: ጴጥሮስ ከወልድ ጋር በፊልጶስ ቂሣሪያ አገር ሲነጋገር የጴጥሮስ ልቡና ድንገት በመንፈስ ቅዱስ ክንፎች ከአብ ህልውና [እናምር] ደርሶ ተነጠቀ [ተመሠጠ]:: በዚያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በአብ ቀኝ ተቀምጦ አገኘው:: ስለዚህ፡- «አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለው:: እርሱም ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ አለው:: ጴጥሮስ፡- ከመንፈስ ቅዱስ ዘንድ ተመርቶ ከአብ ዘንድ ልቡናን አግኝቶ ከወልድ ዘንድ ኤጲስ ቆጶስነትን ተሾመ:: እኔም እልሃለሁ፡ አንተ ጴጥሮስ ነህ፡ በዚችም ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም:: «የመንግሥት ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፡ በምድር የምታስረው በሰማያት የታሰረ ይሆናል:: በምድር የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል::»[9] ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ ከነቢያት አንዱ እንደ ሆነ እንጂ በልቡናቸው እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምነ ውበት እንዳልተከተሉት ዐወቁ [ተረዱ]:: የመለኮት ትስብእት ግን ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ የሌጥ ሚስት የጨው ሐውልት እንደሆነች፣ ሙሴ በመመልከቱ እስከሚሸሽ ድረስ የሙሴ በትር እባብ እንደ ሆነች ዳግመኛ ፍርዖውን በመያዝ እስከሚያነሣ ድረስ እባቡ በትር ወደ መሆን እንደ ተመለሰ በመለወጥ አይደለም:: ዳግመኛ የመለኮት ትስብእት የጌታችን ህልውና የልማድ ኀይል ወደ መሆን አልተመለሰም [አልተለወጠም]:: ዳግመኛ የቃና ዘገሊላ ውሃ ወደ ወይን እንደ ተለወጠ አልተለወጠም:: የመለኮት ኀይል ሰው ለመሆን ቢለወጥ ኑሮ ያለ ሩካቤ ባልተፀነሰ ነበር:: ትስብእት መለኮት ወደ መሆን ተለውጦ ቢሆን በድንግልና ተፀንሶ ቀስ በቀስ አድጎ ባልታየ ነበር:: ዳግመኛ መለኮት ሰው ወደ መሆን ተለውጦ ቢሆን ከድንግል ማሕፀን ባልተወለደ:: ትስብእት መለኮት ወደ መሆን ቢለወጥ በክንድ ባልታቀፈ በስሎሚ

9. ማቴ. ፲፮፥፲፫-፳::



www.ethiopianorthodox.org

እጅ ባልተዳሰሰ። ዳግመኛ ግን የመለኮት ኀይል ሰው ለመሆን ቢለወጥ በድንግል ጡቶች ወተትን ባላመነጨ ነበር። ዳግመኛ የመለኮት ኀይል ሰው ለመሆን ቢለወጥ ግን የልደቱን ምልክት ከከብን ለሰብአ ሰገል ባላሳያቸው ነበር፤ ከዚህ አስቀድሞ የውልደተ ሥጋ መጀመሪያ በሆነ በቃየን ልደት ወይም በእስራኤል መንግሥት ቀዳማውያን በሚሆኑ በሳኦልና በዳዊት ልደት እንደዚህ አልታየምና።

ዳግመኛም የመለኮት ኀይል ሰው ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ግን በታናናሽ ሕፃናት ሥርዐት በበረት ተኝቶ ለእረኞች ባልታየ ነበር። ዳግመኛ መለኮት ሰው ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ስለ ራሱ፦ «አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነበርኩ» ባላለ ነበር።[10] ዳግመኛ ትስብእት መለከኮትን ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ቀስ በቀስ ባላደገ፤ በሰው መጠንም ባልጐለመሰ ነበር። ዳግመኛ የመለኮት ኀይል ሰው ለመሆን ተለውጦ ቢሆን በቃና ዘገሊላ ውሃውን ወይን ባላደረገ ነበር። ትስብእት መለኮትን ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ሳምራዊቷን ሴት ውሃ አጠጭኝ ባላላት ነበር። ዳግመኛም አይሁድ በዕፀ መስቀል ላይ በሰቀሉት ጊዜ በመስቀል ላይ ተጠማሁ ባላለ ነበር።

ዳግመኛ የመለኮት ኀይል ሰው ወደ መሆን ተለውጦ ቢሆን ግን ሞትን ባልቀመሰ ነበር። ሞትን ቀምሶ ቢሆን የሰማይ ጠፈር በፈረሰ፤ የምድርም መሠረት በተበተነ ነበር። ዓለምን የያዘው የመለኮት ኀይል ነውና። ትስብእት መለኮት ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ለሰቃልያን ባልተያዘ የመስቀልን ህፍረት ባልታገሠ ነበር። መለኮት ግን በእጆችም አይዳሰስምና ለዐይንም አይታይም ለልብም አይገኝም። ዳግመኛ የመለኮት ኀይል ሰው ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ግን፦ «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፤ በሦስት ቀን አስነሣዋለሁ» ባላለ ነበር።[11] ትስብእት መለኮት ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ሕማምና ሞትን ባልተቀበለ ነበር። «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት» ያለው «እኔ በሦስት ቀን አነሣዋለሁ» ብሏልና እነሆ! ባለመለወጥ የተጠበቀ፣ ባለመጨመር አንድ የሆነ፤ ባለመለየት በአንድነት ተዋሕዶ የተዋሐደ በድንን የሚያነሣ ነው፤

10. ዮሐ ፰፥፶፰።
11. ዮሐ ፪፥፲፱።



እርሱ በተዋሕዶ ተነሥቶ፤ በአንድ መልክ ወደ ሰማያት ዐርጐ በአንድ አካል በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ። ስለ እርሱ ከፈታችን በመለየት (ከኛ ተለይቶ) ላረገው ለትስብእቱ፣ ለፈጠረን ለመለኮቱ፣ ደግሞ እንስግዳለን ይባል ዘንድ አይቻልም። ለኢየሱስ ክርስቶስ ሰግደን እንገዛለን ይባላል እንጂ። ለእርሱ ለዘላለም ምስጋና ይሁን፤ አሜን።

«የመለኮት ቃል ወደ ትስብእት፤ ትስብእትም ወደ መለኮት ተለወጠ» ለሚሉ ዘለፋቸው ተፈጸመ። እነርሱ የሐሰት መጣግብት ናቸው፤ ከአጋንንት ይከፋሉ፤ ከውሾችም ይረክሳሉ። ሃይማኖቱ የጸና ጊዮርጊስ ተናገረ። በሥርዐት ደም የተቀደሳችሁ ለኃጢአቱ ስርየትን ለምኑለት። ለዘላለም አሜን።



www.ethiopianorthodox.org

[ምዕራፍ ፱]

# ሦስተኛ የጥምቀት ምንባብ

በችሎታና በሥልጣን የሠለጠነ፣ በአስራኤል የሚመሰገን አንድ አምላክ፡ በሚሆን፡ በኪሩቤል የሚመሰገን፣ በሱራፌል የሚቀደስ፣ በብርሃን ድን ኳኖች የሚሰወር፣ በመብረቅ ምስጋና የሚከለል፣ መንበሩን በሚንበለበል የእሳት ሠረገላ ላይ ያደረገ፣ ከሰማየ ሰማያት ከፍ የሚል፣ ከጥልቆች ጥልቅ የሚጠልቅ እና የፀዳልና የመልክ ኅብረት ያለው፣ በአካል የሚተካከል፣ በባሕርይ አንድ የሆነ፣ ምሉዕ ሆኖ የማይቀበል፣ በሦስትነት የማይከፈል በእግዚአብሔር ስም እንጀምራለን:: ለዘላለም አሜን::

«የመንፈስ ቅዱስ ክዋኔ ከክርስቶስ ጥምቀት ወዲህ ነው» የሚሉ ሰዎችን ዘለፋ [ትችት] እንጀምራለን:: ፈዘኞች እና ሰነፎች ሆይ! ከፍጡራን አፈፃር አስቀድሞ የነበረውን የአምላካችን የጰራቅሊጦስ መለኮትን እንዴት አዘገያችሁት? የክርስቶስ ጥምቀት ከፍጥረተ ዓለም ወዲህ በ፭ሺ፶፻፴ [በአምስት ሺሕ አምስት መቶ ሠላሳ] ሆኗልና:: ነገር ግን የመ ንፈስ ቅዱስ ክዋኔ ከክርስቶስ ጥምቀት ወዲህ ከሆነ ከእኛ የሚዘገየውን እንዴት እናመልከዋለን? እንግዲህ ከእኛ በሚከተል እንዴት እንቀደሳለን?

እኛ ግን ፍጻሜ የሌለው ኋለኛ፡ ጥንት የሌለው የመጀመሪያ እንለ ዋለን:: ከዓለም አስቀድሞ ከአብ ከወልድ ጋር የነበረውን ክዋኔውን [መገ ለጡን] «ከክርስቶስ ጥምቀት ወዲህ ነው::» እንዴት ትሉታላችሁ? ዓለም በተፈጠረ ጊዜም ፍጡራንን ያበጀ እርሱ ነው:: ነቢዩ፡- «መንፈ ስህን ትልካለህ፡ ይፈጠሩማል፡ የምድርንም ገጽ ታድሳለህ::» እንዳለ::[1] የጸናች አሪት፡- «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ:: ምድርም ባዶ ነበረች፡ አንዳችም አልነበረባትም፡ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፡ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር::»[2] እነሆ መንፈስ ቅዱስ በፍጥረተ ዓለም ጊዜ ከአብና ወልድ ጋር ህልው ነበር:: ሕዝቅ ኤልም «በራስ ጠጉሬም ያዘኝ የእግዚአብሔር መንፈስ በምድርና በሰማይ መካከል አቆመኝ::» አለ[3]:: እነሆ! ይህም የመንፈስ ቅዱስ

1. መዝ. ፻፫፥፴::
2. ዘፍ. ፩፥፪::
3. ሕዝ. ፰፥፫::





ህልውና ከክርስቶስ ጥምቀት እንደሚቀድም በነቢይ አንደበት [አፍ] የተነገረ ዜና ነው:: ዳዊትም፡- ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትው ሰድብኝ ማዳንህንና ደስታህን በሚአረጋጋ መንፈስም አጽናኝ::» አለ::[4] ጌታችንም፡- «እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣው የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራ ል፡ እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራ ላችሁ::»[5] አለ:: ጳውሎስም ስለ መንፈስ ቅዱስ፡- «ወንድሞች ሆይ፥ ሰነፎች ትሆኑ ዘንድ አንፈቅድም:: ጥንት እናንተ በአረማዊነት እንደ ነበራችሁ ታውቃላችሁ እንጂ:: መናገር የማይችሉ አማልክትን ማየት አድርጋችሁ እንደ ምታመልኩ ታውቃላችሁ ረክሳችሁ ተዋርዳችሁም ነበር::»[6]

ስለ መንፈስ ቅዱስም ህልውና ከወልድ ጥምቀት በፊት እንደ ሆነ ብዙ ጥቅስ አለኝ:: ነገር ግን ነገር በዝቶ ሰማዕያን እንዳይዘናጉ ተውኩት:: እንግዲህ ግን አብ ቅድመ ዓለም እንደ ነበር ወልድም ከዓለም አስቀድሞ ነበር:: ወልድ ከዓለም አስቀድሞ እንደ ነበረ መንፈስ ቅዱስም ከእነርሱ ጋር የነፋስ ፋጠት [ፍጥነት] ያህል ሳይዘገይ ነበር:: በኖኅ ርግብ አምሳል በመታየት በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ መውረድ ለዘላለም በወፍ አምሳል ይኖራል ብላችሁ አትታዘቡ:: [አታስቡ] እግዚአብሔር ግን ሰውን ይመስላል እንጂ ወፍ እና እንስሳን የሚመስል አይደለም:: የጸናች አሪት፡- «እግዚ አብሔር አለ፥ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር» እንዳ ለች:: ዳግመኛም የጸናች አሪት፡- «እግዚአብሔርም የሰውን ልጅ በመ ልኩ ወንድና ሴት አድርጉ ፈጠራቸው::» ት ላለች::[7] ዳግመኛም የጸናች አሪት «የሰውን ደም ያፈሰሰ ስለ ፈሰሰው ደም ፈንታ ደሙ ይፍሰስ::» ትላ ለች::[8] የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሮአልና::

መንፈስ ቅዱስ ዘወትር በወፍ ብቻ የሚመስል ቢሆን ኖሮ ግን በጽርሐ ጽዮን በሐዋርያት ላይ በእሳት አምሳል ለምን ወረደ? በኖኅ ርግብ

4. መዝ. ፶፥፲፩-፲፪::
5. ዮሐ. ፲፭፥፳፯::
6. ፩ኛ ቆሮ. ፲፬፥፩-፫::
7. ዘፍ. ፩፥፳፯::
8. ዘኁ. ፴፭፥፴፫::



www.ethiopianorthodox.org

አምሳል የታየውም እርግብ ከሁሉ አእዋፍ የዋህ ነው በግም ከሁሉ እንስሳ የዋህ በመሆኑ ነው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በየዋህ እርግብ አምሳል ተሰየመ [ተጠራ]፤ ወልድም በየዋህ በግ ተመሰለ። ስለ መንፈስ ቅዱስ፣ መጥምቁ ዮሐንስ፦ «መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ ዐየሁ፡ በእርሱ ላይም ኖረ። እኔም አላውቀውም ነበር፤ ዳሩ ግን በውሃ አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ፦ መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው፡ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ። እኔም ዐይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ መስክሬአለሁ።» ይህን በርግብ አምሳል በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ስለ ወረደው ስለ መንፈስ ቅዱስ ተናገረ። ከዚህም አስከትሎ፦ «እነሆ፤ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ አለ።»[9]

እነሆ! መንፈስ ቅዱስ በርግብ ወልድም በበግ ተመሰለ። የርግብና የበግ ምሳሌነታቸው የተመሰገነው በሐዲስ ኪዳን ብቻ አይደለም። ዕዝራም፦ «ከተፈጠሩት አእዋፍ ሁሉ ለራስህ አንዲት ርግብ መረጥክ። ከተፈጠሩት መንጋዎች ሁሉ ለራስህ አንድ በግ መረጥክ።» አለ።[10] ርግብና በግ በእነርሱ ላይ ስላለ የዋህነት መመስገናቸውን ተመልከት። እግዚአብሔርም የየዋሃን ወዳጅና የዋህ ነውና ተመሰለባቸው።

ለእርሱ ለዘላለም ምስጋና ይገባል። የመንፈስ ቅዱስን ህልውና «ክክ ርስቶስ ጥምቀት ወዲህ ነው» የሚሉና ህልውናው ቅድመ ዓለም እንደሆነ የማያምኑ። በሐሰት ነገር የሚከራከሩ የዝንጉዓን ዘለፋቸው ተፈጸመ። የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ልጅ ጊዮርጊስ አለ። ስለ ኃጢ አቱ ሥርየት እነርሱን ተስፋ ያደርጋል። ለዘላለም አሜን።

9. ዮሐ ፩፥፴፪-፴፬።
10. ዕዝ. ፫፥፳፯።





# [ምዕራፍ ፲]

## የስምዖን ምንባብ

ክርስቶስ አምላኬና ተስፋዬ ነው። ዕፀ መስቀሉም የሃይማኖቴ በትር ነው። የተወጋው ጐኑ የጥምቀት ፈፋቴዬ ነው። የግርፋቱ ደም የመ ክበሪያ ቅብዓቴ ነው። ሐዋርያቱ የመንገዴ መሪዎች ናቸው። እመቤቴ ማርያም የድኅነቴ በር ናት።

ጉኖቿ በወርቅ አመልማሎና ከንፈሯ በብር በተሠሩ [ስለ ተሠሩ] ነጭ ወፍ የሚናገር ድርሳን። ነቢያትን የዚህችን ወፍ መወለጃ አገርን ጠየ ቅኋቸው፡ ኢሳይያስም መልሶ፦ «ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፥ ከሥ ሩም ቍጥቋጦ ያፈራል።» አለኝ።[1] ዳግመኛ ልጅ እንዳላት ጠየቅኩት፡ «እነሆ፡ ድንግል ትፀንሳለች፡ ወንድ ልጅም [ወልድን] ትወልዳለች፡ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።» አለኝ።[2] ዳግመኛም ነቢያትን ክርስቶስ ከወዴት ቦታ ይወለዳል ስል ጠየቅኋቸው፡ ሚክያስ፦ «አንቺም ቤተ ልሔም የኤፍራታ ምድር ሆይ! ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሽም ሕዝ ቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና ሲል ምልክት ሰጠኝ።[3] እንዲህ ስል ነቢያትን ጠየቅኋቸው፡ በአካለ ሥጋ የሚታይ አይደለም፡ እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ አንዱ ከአንዱ በኋላ ሲከተል የሞቱታቸው ዘመናት ረዝሚልና መጻሕፍቶቻቸውን ፈለግሁ። በትንቢታቸው ቃል መለሱልኝ፡ በሥጋቸው ቢሞቱም [ዐረፍተ ዘመን ቢወስና ቸውም] የትን ቢታቸው ቃል አልሞተም። የትንቢታቸውን ቃል በመፈለግ በዳዊት አገር ድንግል ያለ ሩካቤ የወለደችውን ልጅ ተሸክማ አገኘኋት። በሃይማኖት ኀይል አገኘኋት። ለዚህ ዓለም ጥቅም በሚሮጡ የሥጋ እግሮች ግን አይደለም። ያዝኳት፡ አልለቀቅትም፡ ለኃጢአት ሥራ በሚገዙ በሥጋዊ እጆች አይደለም። ቅዱሳት ምስጢራትን በሚዳስሱ የኀሊና እጆች ነው እንጂ። ወደ እናቴ ቤት አስገባኋት፡ ይህችውም ቤተ ክርስቲያን ናት። ወደ መሠዊያው አትጣሚ አስቀመጥኳት፡ ጠረጴዛ እንድትሆን አዘጋ ጀኋት፡ ልጇን የሚሰዋ እንጦሬ[4] [ካህን] ቀረበ፡ በእጁ በተቀበለው ጊዜም

1 ኢሳ ፲፩፥፩።
2 ኢሳ ፯፥፲፬።
3 ሚክ ፭፥፩።
4 እንጦሬ በጽርዕ አናጦሬ የሚል ስያሜ ሲኖረው ትርጉሙም አኰቴት፣ ኅብስት፣ መሥዋዕት ማለት ነው። ጸሎት እንጦሬ እንዲል /መጽሐፈ ቅዳሴ/ ኪዳን ወልድ ክፍል መጽሐፉ ስዋስው ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ ፈ፻፱



www.ethiopianorthodox.org

ጽርስፎራ [መሶሶዋዕት] በመሆን ታየ። ሰማያዊ አባቱ ስለ ቤዛ ብዙኃን የተሠዋ የልጁን መታረድ ይመለከት ዘንድ አንገቱን አዘነበለ። መንፈስ ቅዱስ ከኪሩቤል ሠረገላ ላይ ዘለለ። በብርሃን ክንፎች ይጋርደው ዘንድ በነጭ ርግብ አምሳል [በመታየት] በላዩ ላይ ወረደ። ከወዲያ ወዲህ ኀይል [ተአምር] ተዘረጋ። በቤተ ክርስቲያን ጣራ ውስጥ እሳት ተተከለ። ኪሩቤል በጽርሐ አርያም የሚይዳስሰው ሲታረድ በተመለከቱ ጊዜ ተደነቁ፡ ሱራፌልም ያለ ጉጠት ካህኑ ፍሕሙን ሲፈትት በተመለከተ ጊዜ ፈሩ።

ነቢያት በትንቢታቸው ቃል ያነጋግሩኝ ዘንድ ጠራኋቸው። ዳዊትም «ምስጋናውን ሁሉ እናገር ዘንድ በጽዮን ልጅ በደጆችዋ» ብሎ ዘመረ።[5] ኢሳይያስም «የወደዱትን ለተወደደ መዝሙር እዘምራለሁ» እያለ [ዘመረ][6] አሳፍም፡- «ልጄ ሆይ! ስሚ እዪ፥ ጆሮሽንም አዘንብዪ፥ ወገንሽን የአባትሽን ቤት እርሺ፡ ንጉሥ ውበትሽን ወድዷልና፡ እርሱ ጌታሽ ነውና።» ብሎ ተቀኘ።[7] የቆሬ ልጆችም፡- «ወፍ ለእርስዋ ቤትን አገኘች፡ ዋኖስም ጫጩቶችዋን የምታኖርበት ቤት አገኘች። የሰራዊት አምላክ ንጉሤም አምላኬም ሆይ! እርሱ መሠዊያህ ነው» እያሉ መሰንቆ ገረፉ።[8] እነ ኋት በጥንት ድርሳን የፈለግናት ነጭ ወፍ ለመሠዊያ የሚሆን በሚሠዋበት ቦታ ቤት አገኘች። ጫጩቷንም ቊርባን ሆኖ አስቀመጠች።

የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁላችሁም ኑ ንጽሕት ድንግልን እንዲህ እያልን እንጠይቃት ዘንድ ኑ። ንጽሕት ድንግል ሆይ! ያቺ ዕለት ለአንቺ እንዴት ዕለተ ንጽሕ [ከርኩሰት መቀደሻ] ሆነችልሽ? ዕለተ ንጽሕን ትፈልጊ ዘንድ መቼ ረከስሽ? ያለ ሩካቤ ፀንሰሽ ያለ ርኩሰት ወልደ ሽዋልና። [በአራስነትሽ] አልረከስሽም፡ ለምን በዕለተ ንጽሕ ጊዜ የምስ ጋና ፍሬን ወደ ቤተ መቅደስ ወሰድሽው? አንቺ ከቤተ መቅደስ እየተቀ ደስሽ ልጅሽ በሰማይ ጽላት ታቦት ውስጥ ይከብራል፡ ልጅሽ ሁለት ጉኖች ባሏት፣ በዕብራይስጥ ፊደል በተቀረጸ በጽላት ሕግን ለሙሴ የሰጠ እርሱ ነውና ለአንቺ ለምን በወፍ ደም ርስሐትሽን በሚያነጻ ገንዘብ ለካህን አምኃ ታገቢ ዘንድ ሁለት የርግብ ጫጬት ዘውገ ማዕነቅ አስፈለገ? ልጅሽ የአዕዋፍ ወገኖችን ከናጌብ ውሃ አውጥቶአቸዋልና በንጹሕና በረ

5. መዝ. ፱፥፲፬::
6. ኢሳ. ፭፥፩ ::
7. መዝ. ፵፬፥፲::
8. መዝ. ፹፫፥፫::





ከሱ መካከል ለሙሴ ለይቶለታልና። «የሚበርም በአራት እግሮችም የሚሔድ ተንቀሳቃሽ ሁሉ በእናንተ ዘንድ የተጸየፈ ነው። ነገር ግን ከሚበርሩት፡ አራትም እግሮች ካሉአቸው፥ ከእግሮ ቻቸውም በላይ በምድር ላይ የሚዘልሉባቸው ጭኖች ካሉአቸው ተንቀሳቃሾች እነዚህን ትበላላችሁ።»[9]

ሉቃስ ወንጌላዊን፡ እንዲህ ያለውን ኑ፥ እንጠይቀው፡ «እንደ ሙሴ ሕግ የመንጻታቸው ወራት በተፈጸመ ጊዜ፥ በጌታ ሕግ፡- የእና ቱን ማሕፀን የሚከፍት ወንድ ሁሉ እግዚአብሔር የተቀደሰ ይባላል ተብሎ እንደ ተጻፈ እግዚአብሔር ፊት ሊያቆሙት፥ እግዚአብሔርም ሕግ፡- ሁለት ዋሊያ ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች እንደ ተባለ፥ መሥዋዕት ሊያቀ ርቡ ወደ ኢየሩሳሌም ወሰዱት። እነሆም፥ በኢየሩሳሌም ስምዖን የሚባል ሰው ነበረ፡ ይህም ሰው የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር፡ ጻድቅና ትጉህም ነበረ፡ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበረ። እግዚአብሔር የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር። መንፈስም ወደ መቅደስ አወጣው ዘመዶቹም እንደ ሕጉ ልማድ ያደርጉለት ዘንድ ሕፃኑን ኢየሱስን በአስገቡት ጊዜ፥ እርሱ ደግሞ ተቀብሎ አቀፈው እግዚአብሔርንም እየባረከ እንዲህ አለ፡-

አቤቱ! አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፡ ዐይኖቼ በወገንህ ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን /ትድግናነን/ ዐይተዋልና፡ ይህም ለአሕዛብ ብርሃንን፣ ለወገንህ ለእስራኤል ክብርን ትገልጥ ዘንድ።

ዮሴፍና እናቱም ስለ እርሱ በተባለው ነገር ይደነቁ ነበር። ስምዖንም ባረካቸው፡ እናቱን ማርያምንም እንዲህ አላት እነሆ! ይህ ሕፃን ከእስ ራኤል መካከል ለብዙዎች ለመነሣታቸውና ለመውደቃቸው በሚፈር ድባቸው ገንዘብ ለምልክት የተዘጋጀ ነው። በአንቺ ግን በልብሽ ፍላፃ ይገባል። የብዙዎቹን ሐሳብ ይገልጥ ዘንድ።[10]

ወንጌላዊው፡- «በኢየሩሳሌም ስምዖን የሚባል ሰው ነበረ። ይህም ሰው የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበረ። ጻድቅና ትጉህም ነበረ። መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበረ። እግዚአብሔርም የተቀባውን

9. ዘሌ. ፲፩፥፳::
10. ሉቃ. ፪፥፳፪-፴፭::



www.ethiopianorthodox.org

ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበረ::[11] በምን ምክንያት በነቢዩ ኢሳይያስ ዘመን የስምዖን የጉልምስና ዘመን ሆነ? ነቢዩ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ፥ ካህናትም በመብራት ማብሪያ መብራት አበሩ:: ቤተ መቅደስንም ባማሩ ልብሶች በወርቅ ፈትል በተሠሩ በሚላት መጋረጃዎች ውስጣቸው በሚያጽደለድል በጠሩ የብር ጸናጽሎች በተሞሉ በለመለሙ በተነጠፉ የሮማናት ወርቅ አማመሯት:: የአሮን ልጆች የበቀለ የተምር ዝንጣፊ ከወይራ ዛፍም ያማረውን አነሡ:: «በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው::» አሉ:: ነቢዩትን ለመቀበል ሥርዐት ነውና ጌታ ችን ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በተጓዘ ጊዜ በእንደዚህ ዓይነት ልማድ ተቀበሉት:: እነሆ! የነገሩ ምልክ ትም በማቴዎስ ወንጌል፣ «ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ መላው ከተማ ይህ ማን ነው? ብሎ ተናወጠ:: ሕዝቡም ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣ ነቢዩ ኢየሱስ ነው አለ::[12] ጌታችን ኢየሱስም ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ገባ::» የሚል ተጽፏል:: ነቢያት ወደ ቤተ መቅደስ በሚገቡበት ጊዜ እንደሚደረግላቸው የአቀባበል ሥርዐት ለጌታችንም የአቀባበል ሥርዐት ተደረገለት::

ወደ ስምዖን ዜና ነገር እንግባ:: እንግዲህ ካህናት ከነቢዩ ኢሳይያስ አንደበት የወጣውን የትንቢት ቃል ይጽፍ ዘንድ ቀለምና ብዕር ያዘጋጅ ዘንድ አዘዙት:: እርሱም እንዳዘዙት አደረገ፡ ብዕርና ቀለምም አዘጋጀ፡ ቃሉንም ለመጻፍ ተዘጋጀ፡ ከዚህ በኋላ የኢሳይያስ የትንቢት መንፈስ ወደ እርሱ መጣ:: «ድንግል ትፀንሳለች፡ ወንድ ልጅም ትወል ዳለች፥ ወልዳም ዐማኑኤል ትለዋለች» ብሎ ፃፈ::[13] ያን ጊዜ እኔ ይህንን የሐሰት ትንቢት ጻሐፊ አልሆንም ብሎ ከእጁ ውስጥ ብዕሩን ጣለ:: ድንግል ስትፀንስ ማኅተመ ድንግልናዋ የታተመ ሴት ስት ወልድ ያየ የሰማ ማነው?

የኢሳይያስ የትንቢት ቃል እንዳይታበል ኹለተኛ ቃል መጣ:: የትንቢት ቃሉንም ጻፈት:: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ስምዖንን በእግዚአብሔር የተቀባ ውን ሳያይ እንደማይሞት ገልጾ ነገረው:: ስለ እርሱ ነቢዩ ኢሳይያስ የተነበየለትን፥ ስሙ ዐማኑኤል የተባለውን ሕፃን፡ ለመታቀፍ አደረሰው እንጂ

11. ሉቃ. ፪፥፳፮::
12. ማቴ. ፳፩፥፲::
13. ኢሳ. ፯፥፲፬::





መጠራጠሩ እንደ በደል አልተቆጠረበትም:: ወንድሞቹን ያስካደ የቶማስ መጠራጠር ከበደል አልተቆጠረም፡ መጠራጠሩ [ጥርጥሩ] የመድኃኔዓለምን ቁስሎች ለመዳሰስ አደረሰው:: እግዚአብሔር የወደደው ምስጉን ነው አይነ ቀፍም፡ ቁስሉቹ አይሸቱም፡ ኃጢአቱም በእግዚአብሔር ፊት አይታሰብም::

በርስሐት ጊዜዋም ሆነ በመንጻት ጊዜዋ ላላደፈች ዛሬ ሐዋርያት እንደ አዘዙን በዓል እናድርግ ከዘመናት በፊት የነበረ ብሉየ መዋዕል [ዘመናትን የሚያስረጅ] ሲሆን ሕፃን ሆኖ በአረጋዊ ክንድ ታቀፈ ዛሬ በዓል እናድርግ:: ዛሬ አረጋውያን ምእመናን በዓልን አድርጉ፡ የአረጋ ውያን አባት እንደ ሕፃን ጡት ጠብቶ በአራት እንደታዘዘው መብዐ ለማግባት መጥቷልና::

ዛሬ ሕፃናት በዓል ያድርጉ፡ ሕፃናትን የሚሥል፥ ወደ ቤተ መቅደስ ከኹለት የርግብ ጫጩቶች ጋር መጥቷልና:: የጸናች ኦሪት እንደም ትናገረው «ሴት ብታረግዝ ወንድ ልጅም ብትወልድ ሰባት ቀን ያህል የረከሰች ናት:: እንደ ሕመምዋ መርገም ወራት ትረክሳለች፡ በስምን ተኛውም ቀን ልጁ ከሥጋው ሸለፈት ይገረዝ፡ ስለ ደምዋም መንጻት ሠላሳ ሦስት ቀን ትቀመጥ፡ የመንጻትዋ ቀንም እስኪፈጸም ድረስ የተቀደሰ ነገርን አትንካ፡ ወደ መቅደስም አትግባ፡ ሴት ልጅም ብት ወልድ እንደ መርገምዋ ወራት ኹለት ሳምንት ያህል የረከሰች ናት:: ከደምዋም እስከ ትነጻ ድረስ ስድሳ ስድስት ቀን ትቀመጥ:: የመንጻትዋ ወራትም በተፈጸመ ጊዜ ለወንድ ልጅ ወይም ለሴት ልጅ የአንድ ዓመት ጠቦት ለሚቃጠል መሥዋዕት የርግብም ግልገል ወይም ዋኖስ ለኃጢ አት መሥዋዕት ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ወደ ካህኑ ታምጣ ለት:: እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ያቀርበዋል፥ ያስተሰርይላትማል፥ ከደምዋም ፈሳሽ ትነጻለች:: ወንድ ወይም ሴት ለምትወልድ ሴት ሕጉ ይህ ነው:: ጠቦት ለማምጣት ገንዘብዋ ያልበቃት ኹለት ዋኖሶች ወይም ኹለት የርግብ ግልገ ሎች አንዱን ለሚቃጠል መሥዋዕት ሌላውንም ለኃጢአት መሥዋዕት ታቀር ባለች፥ ካህኑም ያስተሰርይላታል፥ እርሷም ትነጻለች::

ወዳጆቼ ሆይ! የሰማይና የምድር ሀብት በሕፃኑ እጅ ሳለ [ሲሆን] የእናቱንና የሕፃኑን የድህነታቸውን ጥልቀት ተመልከቱ:: የጸናች ኦሪት አስቀድማ ሴት «የመንጻትዋ ወራት በተፈጸመ ጊዜ ለወንድ ልጅ ወይም



www.ethiopianorthodox.org

ለሴት ልጅ የአንድ ዓመት ጠቦት ለሚቃጠል መሥዋዕት የርግብ ግልገል ወይም ዋኖስ ለኃጢአት መሥዋዕት ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ወደ ካህኑ ታመጣለች።»[14] ብላለች። የጸናች አራት አስቀድማ በግ ስላለት [ሴት] በጉ ለመሥዋዕት የርግብ ግልገሎች [ዋኖሶች] ለኃጢአት ሥርየት እንዲሆን ይህን ተናገረች።

ከዚህም በኋላ አራት በማስከተል ጠቦት ለማምጣት ገንዘብዋ ያልበቃት እንደ ሆነ ኹለት ዋኖሶች ወይም ኹለት የርግብ ግልገሎች አንዱን ለሚቃጠል መሥዋዕት ሌላውንም ለኃጢአት መሥዋዕት ታቀርባለች፥ ካህኑም ያስተሰርይላታል፥ እርሷም ትነጻለችም። አለች። እነሆ ከማርያም እጅ በግ ታጣ፤ በግ ለማምጣት [ለመግዛት] የማትበቃ ሆናለችና። ስለዚህ ኹለት የርግብ ጫጩቶችን አንዱን ለኃጢአት ማስተሥረያ አንዱን ለመሥዋዕት አመጣች። ከማርያም እጅ በግ ለምን ታጣ? የልጇ ፈቃድ በዚህ ምድር ከድሆች ወገን እንጂ ከሀብታሞች ወገን አይደለምና። ከዘመድ ነቀፌታ ትስብእቱን ያርቅ ዘንድ ከዳዊት ዘር በሥጋ ተወለደ። ራሱን ወደዚህ ዓለም ብልጽግናን አላስገባም። የዚህን ዓለም ብልጽግና ወድዶ ቢሆን ግን ከሄሮድስ ልጅ በተወለደ እርሱም [ሄሮድስም] ከዳዊት ወገን ነውና እንገታቸውን አግዝፈው በዐይኖቻቸው የሚጠቃቀሱ የሐር፣ የሲራይ፣ የወርቅ ልብሶቻቸውን ዘርፍ የሚስቡ የገሊላ ነገሥታት ሴት ልጆችን ወድዶ ወደ ቤተ መንግሥት አልገባም። እናትና አባቷ ከመሞታቸው አስቀድሞ የተዋትን የሙት ልጅ መረጠ። ከእናትና አባቷ ሞት በኋላ ወንድምና እኅት አልነበሩትም። በወለድዋት በሦስተኛ ዓመት ብጽአት አድርገው ለቤተ መቅደስ ሰጧት። ዐሥራ ኹለት ዓመት በሆናት ጊዜ በሕግ እስከ ሚያጣምሯት ደረስ በንጽሕና እንዲጠብቃት ለዮሴፍ ሰጧት። ዮሴፍ ወደ እርሷ ሳይቀርብ በዐሥራ አራት ዓመቷ ገብርኤል አበሠራት። ከዚህም በኋላ በተወለደች በዐሥራ አምስት ዓመቷ መድኃኒታችንን ወለደችው። ከእርሱም ጋር እስከ ዕርገቱ ድረስ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከአራት ወር ተቀመጠች። ከልጇ ዕርገት በኋላ ዐሥራ አራት ዓመት ተቀመጠች። ጳውሎስ ለወንጌል አገልግሎት በተማረከበት ዘመን [ዓመት] ከዚህ ዓለም ዐረፈች፤ ሐዋርያትም ከወንድማቸው ከጳውሎስ ጋር ገነዟት።

ስምዖን ሕፃኑን ከእናቱ ክንድ [እቅፍ] እንዴት ተቀብሎ በጭኑ ላይ

14. ሉቃ. ፪፥፳፬።





እንዳስቀመጠው እንናገር ዘንድ ወደ ጥንት ነገራችን እንመለስ። የወንጌልን መሥዋዕት የአራት ካህን ተሸከመው፤ ጊዜው አልደረሰምና መሠዋት አልተቻለውም፤ ቤተ መቅደስ ከገሊላ ሕፃናት እንደ አንዱ በሕጉ መጽሐፍ ይጸፍ ዘንድ እንዳለው [እንደሚገባው] አስመሰለችው። በበግ ደም መሥዋዕት ፋሲካን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የበላው [ኢየሱስ ክርስቶስ] ከአራት በኋላ ስለ ቤተ ክርስቲያን መታጨት [ለቤተ ክርስቲያን መታጫ] ሥጋውና ደሙን በቁርባንንት ሰጠ።

የካህናት ልጆች እንስሳትን የሚሠውበትን ክህነታቸውን አሳልፎ እንደ መልከ ጼዴቅ በስንዴ ኅብስትና በወይን ደም ንጹሕ የክህነት ሥርዐትን ለአሕዛብ ያደርግላቸው ዘንድ ያለውን ክርስቶስ በምክራቸው ዐጸድ አኖሩት። ከዚህ በኋላ ስምዖን በእቅፉ ውስጥ ያለውን ሕፃን ከዚህ ዓለም ያሳርፈው ዘንድ ለመነው። ከለመነውም በኋላ ለእናቱ ሰጣት፤ በዚያችም ዕለት በእግዚአብሔር ሰላም ዐረፈ። አሜን።



www.ethiopianorthodox.org

# [ምዕራፍ ፲፩]

## የደብረ ዘይት ምንባብ

ክርስቶስ አምላኬና ተስፋዬ፥ የአባቴ ስም የመድኃኒቴ ዘውድ፣ የመንፈስ ቅዱስ ስም የመቀደሻዬ ምንጭ ነው፤ የመስቀሉ ሞገስ የመመኪያዬ አክሊል፣ እመቤታችን ማርያም የገነት መግቢያ ቁልፌ፣[1] ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የጥምቀቴ ምንጭ፤ ሐዋርያት አጥማቂዎቼ፣ የበለሳን ቅባት [ሜሮን] የእምነቴ ማኅተም፣ የሁሉም ቅዱሳን ገድል የኃጢአቴ ማስተሥረያ ነው፡፡ ለዘላለም አሜን፡፡

እኔ ክርስቲያን እወዳለሁ፤ ክርስቲያን ተብዬ እኖራለሁ፡፡ ክርስቲያን እፈልጋለሁ፡፡ እንደ አባቶቼ ሐዋርያት ትምህርት በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን እገባለሁ፡፡ እንደ አባቶቼ ሐዋርያት በቤተ ክርስቲያን በመቃብር ውስጥ እተኛለሁ፡፡ ከአባቶቼ ሐዋርያት ጋር በመነሣቴ [በትንሣኤ] በቤተ ክርስቲያን እነቃለሁ፡፡ በተቀደሰች ደብረ ጽዮን በአባቶቼ ሐዋርያት እቅፍ ከክርስቲያን ጋር እቀመጣለሁ፡፡ የቅዱሳንን ዜና ለመናገር ፍቅር ያገብረኛል [ያስገድደኛል]፡፡ ከሐዲዎችን እዘልፋቸው ዘንድ ቅንዓት ያስገድደኛል፡፡ ሰይጣንን እወግዘው ዘንድ ቅንአት ያስገድደኛል፣ የክርስቶስን ሐዋርያት እከተላቸው ዘንድ ፍቅር ያስገድደኛል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን አመሰግነው ዘንድ ፍቅር ያስገድደኛል፡፡ ዝንጉአንን እሸሻቸው ዘንድ ቅንዓት ያስገድደኛል፡፡ ሰማዕታትን አመሰግናቸው ዘንድ ፍቅር ያስገድደኛል፡፡ ማርያውያንን[2] እዘልፋቸው (እጠላቸው) ዘንድ ቅንአት ያስገድደኛል፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ የሽቶው መዓዛ በፈሰሰበት በዚያ ቦታ መልካም መዓዛ ይሸታል፡፡ ሃይማኖታቸውን የካዱ ሰዎች ትምህርት በፈሰሰበት በዚያ የሰይጣን ክርፋቱ ይሸታል፡፡ ሽቱን የዳሰሰ [የነካ] ሰው ስለ ነካው ሽቱ እጁ ሽቱ ሽቱ ይሸታል፤ ክፉ ሽታ የነካ እጅ ስለ ነካው ክፉ ሽታ እጁ ያስጠይፋል፡፡

የመለኮትን ነገር በሚናገሩ ዘንድ በዚያ እግዚአብሔር አለ፡፡ የክሐድያንን ስሕተት በሚናገሩ ዘንድ በዚያ አጋንንት ይጨነቃሉ፡፡

1. መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት፤ ወደ መንግሥተ ሰማያት መርታ የምታስገባ ብለው ሊቃውንትና ምእመናን የሚጠሯት እመቤታችን ናት፡፡
2. የመናፍቃን ተከታዮች





ዛሬም የአብን መምጣት ከዶ፣ «ወልድ በኃጥአን ለመፍረድ ለጻድቃን ዋጋቸውን ለማስጠት ያለ አብ ይመጣል» የሚል የቢቱን[3] ዘለፋ እንናገራለን፡፡ እኔ፣ ስለ እርሱ ሥጋ የለበሰ ጋኔን ሰው እንደ ሆነ እታዘባለሁ፡፡ እንዴት የሰው ልጅ ይህን ያህል ስድብን በመለኮት ክብር ላይ ይናገራል? በወልድና በወላጁ [በአባቱ] መንግሥት ላይ ይህን ያህል ክፋሌ [መክፋፈልን] እንዴት ይናገራል፡፡ ቢቱ የነቢያትንና የሐዋርያትን መጽሐፍ የማያውቅ ይመስላችኋልን? ፈጽሞ ያውቃል፡፡ ነገር ግን ሰይጣንን በሚያስደስተው ግንዘብ ይተጋል፤ ሰይጣንም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የማያውቅ አይደለም፡፡ የኀሊናውን ራስ በማንሣት በልቡ ትዕቢት ትእዛዙን የሚቃወም ሆኖ እንጂ፤ ሰይጣን የሰው ልጆችን በሚያስታቸው መንገድ ይተጋል፤ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ እንደሚወድ ያውቃልና፡፡

ቢቱም በሰይጣን ይመስላል፡፡ እንደ አባቱ ሰይጣን ምእመናንን በሚያስታቸው ጎዳና ይተጋል፡፡ ከቢቱ ማሳሳት ይልቅ የሰይጣን ማሳሳት ይቀላል፤ ሰይጣን ከዘመዶችን ተለይቶ የፈጣሪው የእግዚአብሔር ክብር ጠላት ነውና፡፡ ቢቱ ግን ራሱን ክርስቲያን ያደርጋል፤ በልቡ ግን ክርስቲያን አይደለም፡፡ በልቡ እኔ የተጠመቅሁ ነኝ ይላል፤ በሃይማኖቱ ግን ያልተጠመቀ ነው፡፡ ስለ ቢቱ ምን እንላለን? እባብ እንበለውን? እባብም በክፋት ይለዝባል፤ እባብ ግን በጥርሶቹ ያልነከሰውን አያሳምመውም፡፡ ቢቱ ግን ወደ እርሱ የሚቀርበውን በአፉ አናግሮ በሰላም ነገር ውስጥ መርዝ ጨምሮ ማሳመም ይችላል፡፡ ስምምነትንም ወደ ጠብ ይለውጣል፡፡

ከመተኛት ቅንድቦቹን ያደረቀ ቢቱ ክፋት ሳያደርግ አይተኛም፡፡ ደምን ለማፍሰስ እግሮቹ ፈጣን ናቸው፡፡ ክፋትን ለመናገር አንደበቱ ሽንጋይ ነው፡፡ ከተማን ያለ እሳት ያቃጥላል፤ ነገሥታትን እንደ አንበሳ ግሳት ያስጮኻል፡፡ የዋን እንደ አራስ ድብ፣ አውሬ አድርጐ እንደ ዱር ከርከሮ ጠማማ ያደርገዋል፡፡ በሰይጣን ዘንድ ሞገስን አግኝቶአልና ይህን ዋሽህ ይህንንም አክፋፋህ የሚለው የለም፡፡ ንጉሥም ስለ እርሱ እንደ አንበሳ ያገሳል፥ በተመለከተውም ጊዜ በእርሱ ላይ መክፋት አይችልም፡፡

3. ቢቱ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ኢትዮጵያ ውስጥ አካባቢ የተነሣ መናፍቅ ነው፡፡ ትምህርቱም ዓለምን ለማገልፍ እና በፍርድ ቀን የሚመጣው ወልድ ብቻ ነው የሚል ነበር፡፡ በንጉሡ በዓፄ ዳዊት ፊት በማስመሰል እንደተከራከረው መጻሕፍትን ዐዋቂ ተደርጐ ይቆጠር ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አባ ጊዮርጊስ መረጃዎችን እያጣቀሰ ተከራክሮታል በገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ተጽፏል፡፡



www.ethiopianorthodox.org

የቢቱን የከፋቱን ነገር ፈጽሞ መናገር አይቻልም:: ስለዚህም የድንግል ማርያምን የቸርነቷን ክብር [ብዛት] ፈጽሞ መናገር እንደ ማይቻል የቢቱን የከፋቱን ነገር ፈጽሞ መናገር አይቻልም:: አባ ጊዮርጊስ ስለ ጠንቋዩ ቢቱ እንደዚ ያለበት ምክንያት አለው:: ነገሥታቱ ጥንቆላውን ስለወደዱለት ስሕተቱን ቢያውቁ እንኳን አይናገሩትም:: እንዲያውም ዐፄ ዳዊት ለቢቱ አድልቶ አባ ጊዮርጊስን አስገርፎ አሳስሮታል::

አሁንም ስለ ክፉ ሥራው ነገር ከማጠናቀቅ /ከመመረመር/ የማይማኖቱን ዘለፋ እንናገር:: ጳውሎስ:- «ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንመረምራለን፤»[4] እንዳለ የቢቱ የስንፍና ትምህርት ይህ ነው:: «ወልድ ያለ አባቱ» [አብ] ይመጣል» የሚል ነው:: አብን ግን እንደ ንጉሥ አደረገው፤ ወልድንም እንደ ኀያል መልአክ አደረገው:: ንጉሡም የሰራዊቱን አለቃ ጠላቶቹን ይበቀላቸው ዘንድ እንደ ሚልክ፣ ለሚወዱት ደግሞ ዋጋቸውን ይከፍ ላቸው ዘንድ እንደሚልክ የወልድን ምጽአት እንደዚህ አደረገ:: እንደዚህ ዓይነት ክሕደትን ከዚህ አስቀድሞ ከዚህም በኋላ በአይሁድ ዘንድም ከክርስቲያንም ዘንድ በእስላሞችም ዘንድ የሰማን የለንም:: አይሁድ ግን «እግዚአብሔር ለሙሴ ሕግን ሰጠ፤ ትእዛዞሪትን የማይጠበቁትን በፍርድ ቀን ዋጋቸውን ይከፍላቸዋል::» አሉ::[5] ንጉሞቸውና ነቢያቸው ዳዊት «እግዚአብሔር እንዲህ ተናገረ፤ እኔም ይህን ብቻ ሰማሁ፤ ኀይል የእግዚአብሔር ነው፤ አቤቱ ምሕረትህም ያንተ ነው፤ አንተ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ፍዳውን ትከፍለዋለህና::[6] ስለዚህ እግዚአብሔር ኃጥአንን ይበቀላቸዋል፤ ለጻድቃን ዋጋቸውን ይሰጣቸዋል::» አለ:: ወልድን ግን «ከዚህ በኋላ ይመጣል::» ይሉታል:: «የዳዊት ልጅ» ይሉታል እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ አይሉትም:: ሐሳዊ መሲሕን ይቀበሉት ዘንድ አላቸውና እስላሞችም:- እግዚአብሔር አልተወለደም አይወልድም [«እግዚአብሔር አይወልድም አይወለድም»] ይላሉ::

የእግዚአብሔርን ልጅ ግን በገብርኤል ቃል ከማርያም ተፀነሰ ይሉታል:: የእግዚአብሔርም ንባብ ይሉታል፤ የእግዚአብሔር ልጅ አይሉትም:: የእግዚአብሔርን ምጽአት ግን አይክዱም:: የአይሁድ እና የእስላሞች ክሕደት ግን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ

4. ሮሜ. ፲፬፥፲::
5. ዮሐ. ፭፥፲፰፡ ዮሐ. ፭፥፵፯፡ ዕብ. ፲፥፳፰-፳፱::
6. መዝ. ፷፩፥፩፥፲፩-፲፪::





እንዳልሆነ ነው:: እኛ ክርስቲያኖች ግን እግዚአብሔር ከልጁ [ወልድ] እና መንፈስ ቅዱስ ጋር እንደሚመጣ እናምናለን::

ዳዊት ስለ እርሱ «እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል::» ያለለት አብ ለምን ኢየመጣም ይባላል? ስለ ወልድም «አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም::» አለ::[7] የአብን የምጽአቱን ዜና አስቀድሞ ወልድም ዝም እንደማይል ሰቃል ያንን እንደሚፋረዳቸው አስከተለ:: ዮሐንስ አቡቀለምሲስ እንደ ተናገረው «እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ ታየዋለች፤ የወጉትም ያዩታል፤ የምድር ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ይላሉ:: አዎን አሜን ያለውና የነበረው የሚመጣውም እግዚአብሔር ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ:- አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ»[8] አለ::

መጽሐፍ፣ «ጉኑን የወጉትም ያዩታል::» እንዳለ አይሁድን ግን ንቀው ስለ ገረፋት ሰቅለው ስለወጉት ይፈርድባቸዋል፤ ክርስቲያኖችንም ወንድ ማቻውን የሚንቁትን እንዲህ ሲል ይፈርድባቸዋል:: [ይወቅሳቸዋል::] «ተርቤ አላበላችሁኝምና፣ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፣ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፣ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፣ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና:: እነርሱ ደግሞ ይመልሱና አቤቱ! ተርበህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም? ይሉታል:: ያን ጊዜ እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል:: እና ንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሒዱ ይላቸዋል::[9]

አብ ግን ከሰቃልያን [አይሁድ] ዘንድ ሕማማትን በሚቀበልበት ገን ዘብ ሥጋን አልለበሰምና አይፈርድባቸውም:: ጠላቶቹን ከእግሮቹ መረገጫ በታች ለልጁ ያስገዛለታል:: ነገር ግን ዳዊት እግዚአብሔር ጌታዬን:- ጠላቶችህን ለእግርህ መርገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው ብሎ እንደተናገረው::[10]

በዕርገቱ ጊዜ በቀኜ ተቀመጥ ይለዋል፤ ከዚህ አስከትሎ ጠላቶችህን ከእግሮችህ መረገጫ በታች እስከ ማደርግልህ ድረስ ብሎ ስለ ምጽአቱ ዕድሜ [ቀጠሮ] ሰጠው::

7. መዝ. ፵፱፥፫::
8. ራእ. ፩፥፰::
9. ማቴ. ፳፭፥፴፬-፵፮::
10. መዝ. ፻፱፥፩::



www.ethiopianorthodox.org

ዳግመኛም ጠላቶቹ ከእግሮቹ መቀመጫ በታች ተገዝተውለት በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ ይመጣል። አባቱ፣ ጠላቶችህን ከእግሮችህ መቀመጫ በታች እስከ ማስገዛልህ ድረስ ተቀመጥ አለው እንጂ መድኃኒት አድርጌ ጠላቶችህን እስከ ማስገዛልህ ድረስ በሌላ ቦታ ተቀመጥ አላለውም።

አብ ዘወትር በጽርሐ አርያም ህልው እንደሆነ ወልድም ዘወትር በአባቱ ቀኝ ህልው ነው። በሥጋዌው ከፍ ብሎ በቀድሞ ቦታው በተቀመጠ ጊዜ በመልክ ኹለትነት የለውም፤ በባሕርዮም አልተጨመረበትም፤ ዳግመኛም በወለደው አባቱ ቀኝ ተቀምጦ ይመጣል። ሊቃነ ካህናትን «የሰውን ልጅ በኀይል ቀኝ ተቀምጦ በደመና ሰማይ ሲመጣ ታዩታላችሁ»[11] እንዳላቸው እነሆ የአብ የምጽአቱ ዜና በቀኙ ከሚቀመጥ ከወልድ ጋር መሆኑ ታወቀ። «ኀይል ግን» በሚዳሰስ በማይዳሰስ በሚታይ በማይታይ ይጠራል [ይተረጐማል]። ያንጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ ጠላቶቹ ከእግሮቹ መረገጫ በታች ይገዛሉ። ጳውሎስ ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛለት። ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዝቶለት ያላስገዛለት የለም፤ አለ። ዳግመኛ ሁሉም ከተገዛለት በኋላ ራሱ ደግሞ ሁሉን ለአስገዛለት ይገዛል አለ።[12] እነሆ! የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ የፍርድ አደባባይ አንድ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ አብ በፍርድ አደባባይ ይቀመጣል አለ። ወልድም በወንጌል እርሱ ራሱ ፍርዴ እውነት ነው ብሎ እንደተናገረ ይፈርዳል። መንፈስ ቅዱስም ሐዋርያው ሁላችንም በመንፈስ ቅዱስ እንደ ምንመረመር አታውቁምን እንዳለ መንፈስ ቅዱስም ይፈርዳል።[13] እነሆ! የአብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የፍርድ አደባባይ አንድ ነው። ለእያንዳንዱ እንደየምግባሩ ፊት ሳይነሳ [ሳያዳላ] የሚፈርድ አብን ብትጠሩት ግን ሐዋርያው እንደ ተናገረው አብ በፍርድ አደባባይ ይቀመ ጣል።[14] እነሆ! የሥላሴ [መለኮታዊ] የፍርድ አደባባይ አንድ ነው። ወልድ አብ በማንም አይፈርድም ፍርድን ሁሉ ለልጁ ሰጠው ያለው ግን ይህንን አይሁድንና ክርስቲያኖችን ስለ ሚፈርድባቸው የፍርድ ቀስት [ወቀሳ] ነው። አስቀድመን እንደተናገርነው አይሁድን ስለሰቀሉት፣ ክርስቲያኖችንም ወንድ ማቸውን ስለናቁ ይፈርድባቸዋል። የፍርድና ወቀሳ ትርጓሜያቸው ኹለት ነውና

11. ማቴ. ፳፮፥፷፬።
12. ፩ኛ ቆሮ. ፲፭፥፳፯።
13. ፩ኛ ቆሮ. ፪፥፲፭።
14. ዮሐ. ፰፥፲፮።





በዚያን ዕለት ሄሮድስና ጲላጦስ ተስማሙ፡ አስቀድሞ ጠብ ነበሩና።[15] ብሎ ወንጌላዊው እንደተናገረው ይህንን ስለ ወቀሳ ፍርድ አለ።

ጌታችን በወንጌል የስቃይም ፍርድ ትርጉም ግን ሌላ ነው። «እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና፤ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል።»[16] ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል የሚልም አለ።[17] ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህ ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ የሚልም አለ።[18] ፍርድ የሚለውም ፈራጅ የሚለው ሦስተኛ ትርጓሜ አለው። ፈራጅ ማለት ግን አኀዜ ዓለም [ዓለምን የያዘ] ማለት ነው። ፍርድ ማለትም የኩሉም መንግሥት ሥሉጥ ሥልጣን ነው።

በመዝሙር እንደተነገረው እግዚአብሔር ፈራጅ ነው፤ ያንን ያከብራል ያንን ያዋርዳል አለ። ዳግመኛም እግዚአብሔር እውነተኛ ፈራጅ ኀያል ታጋሽ ነው፤ ዳግመኛ ዓለምን የሚገዛት ከፍ አለ።[19] ይላል።

ስለ ምድር ገዥዎችም ጳውሎስ «ለባለስልጣን መገዛትን ትእዛዝን የሚቃወም እግዚአብሔርን ይቃወማል።» አለ። የጸናች አሪትም የሕዝብህን አለቃ ክፉ ነው አትበል ትላለች።[20] ዳግመኛም መኳንንትን አትማ አለ።

ስለ ወልደ እግዚአብሔርም በመዝሙር፡- ለችግረኛ ሕዝብህ በእውነት ፍረድ የችግረኞች ልጆችህንም አድናቸው። አለ።[21] ዳግመኛም፡- «ከባሕር እስከ ባሕር ድረስ፤ ከወንዙ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ይገዛል።» አለ። ዳግመኛም፡ - «ዓለምን በእውነት አሕዛብንም በርትዕ ይገዛል።» አለ።[22] እነሆ በሦስት መንገድ ፈራጅን [መፍረድን]፣ መኰነንን፣ ፍርድን መፍረድ ማለት ወደ ሥልጣነ ሚመት፣ መኰነን ማለት ሥቃይ ፍርድ ማለት ወደ ወቀሳ እንደ ሚተረጐም ነገርኳችሁ። አመለከትኳችሁ። «ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ስንኳ አይፈርድም።» ያለው ግን የወቀሳ ፍርድ ነው።

ስለ አብ መምጽአት ግን ዳንኤል፡- ብሉየ መዋዕል [ዘመናትን ያሚያስረጀው፤ ዘመኑ የማይቆጠር፣ ዘመኑ ከእስከ የሌለው] የራሱ ፀጉሩ እንደ ፀምር ነጭ ነው፤ ዓይኖቹ እንደ ነደ እሳት ናቸው። በፊቱም የእሳት ወንዝ ይፈሳል። አለ። መጻሕፍትን አምጥተው በእግዚአብሔር ፊት ገለጿት [ከፈቷት]። የሕይወትን

15. ሉቃ. ፳፫፥፲፪።
16. ማቴ. ፯፥፩።
17. ማቴ. ፭፥፳፪።
18. ማቴ. ፲፪፥፴፯።
19. መዝ. ፸፬፥፯።
20. ዘጸ. ፳፪፥፳፰ የሐዋ. ፳፫፥፭።
21. መዝ. ፸፩፥፪።
22. መዝ. ፺፭፥፲፫።



www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፍ ብቻዋን ገለጿት [ከፈቷት]፡ የሰው ልጅ መጥቶ በዘመናት በሽመ ገለው [ዘመናትን በሚያስረጀው ዘንድ] ተቀመጠ፡ የዘላለም ግዛት ተሰጠው፥ መንግሥቱም የማያልፍ ነው [አያልፍም]።[23] አለ፡፡

ይህን ትንቢት ለመተርጐም ልባችንን እናንቃ፡፡ «ለብሉየ መዋዕል [ዘመናትን ለሚያስረጅ] ወንበሮችን አመጡ፡፡» ያለው በአብ ምጽአት ስለሚሆን የፍርድ አደባባይ ነው፡፡ «የእሳት ወንዝ በፊቱ ይፈሳል፡፡» የተባለው የኃጥአን የመከራ ወንዝ በፊቱ ስለሚፈስ የሚበቀላቸውን በቀል እንደ ተመለከቱ ይፈራሉ፡ አይተውም [ተመልክተውም] ያለቅሳሉ፡፡ ያን ጊዜ የሚያጠቅም ንስሐ፥ የማያድን ልቅሶ ይሆናል፡፡ በሕይወታቸው ንስሐ አልገቡምና፡ «መጻሕፍን አምጥተው በእግዚአብሔር ፊት፡ [ገለጧት] ከፈቷት» ያለው የኃጥአን የፍዳ መጽሐፍ ነው፡፡ የሥራት በዚህና በዚያ ይገኛል፡፡ በድብቅ የሠሩት በግልጽ ይነገራል፡ ያንጊዜ ኃጢአቱን መሸሸግ የሚችል የለም፡ የበደል መጽሐፍ ትዘልፈዋለችና፡፡

«የሕይወትን መጽሐፍ ግን ለብቻዋ ከፈቷት [ገለጧት]» የሚለው ግን የልዑል ቅዱሳን የድካማቸው መጽሐፍና ወደ ሕይወት መጽሐፍ የተላኩት ሥነ ምግባራቸው ናት፡፡ የሕይወት መጽሐፍ ለብቻዋ መከፈት ግን የጻድቃን የገድላቸው መጽሐፍ ከኃጥአን የፍዳ መጽሐፍ ጋር የምትደመር አይደለምና ነው፡፡ የኃጥአን መቆሚያቸው በስተግራ ነው፡፡ የምትዘልፋቸው የፍዳቸውም መጽሐፍም በስተግራ ናት፡፡ የጻድቃን መቆሚያቸው በስተቀኝ ነው፡፡ የምታመሰግናቸው የሕይወታቸው መጽሐፍም በስተቀኝ ናት፡፡ የሰው ዋጋው ከራሱ ጋር ነው፡፡ ምግባሩም በፊቱ ነው፡፡

የሰው ልጅ መጥቶ በብሉየ መዋዕል ዘንድ [ዘመናትን በሚያስረጀው ዘንድ] ተቀመጠ» የሚለው እነሆ! የወልድን መጽአትና በአባቱ ዘንድ መቀመጥን ሲናገር ነው፡፡ በዚህ ነገር አታስተውሉምን? እነሆ! የአብና የወልድን በአንድ አደባባይ መቀመጥ በመንፈስ ቅዱስ መርማሪነት አንጻት ወቀሳ ይሆናል፡፡ ጌታችን በወንጌል፡- «እርሱ ጰራቅሊጦስ መጥቶ ስለ ኃጢአት፥ ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል [ይፋረደዋል] ስለ ኃጢአት በእኔ ስለ ማያምኑ ነው፡ ስለ ጽድቅም ወደ አብ ስለ ምሄድ ከዚህም በኋላ ስለ ማልታይ ነው፡ ስለ ፍርድም የዚህ

23. ዳን. ፯፥፱-፲፬::





ዓለም ገዥ ስለ ተፈረደበት ነው»[24] ብሎ እንደ ተናገረ ዝንጉ ንጉሥ ሆይ! የሥላሴ አንድነት ከዛሬ እስከ ዘላለም መቼም መች እንደ ማይለያይ ዕወቅ፡፡

በወልድ መለኮት ትስብእት ጊዜ ገብርኤል ማርያምን ስለ መንፈስ ቅዱስ፡- «መንፈስ ቅዱስ ወደ አንቺ ይመጣል፡፡» አላት፡፡ ስለ አብም «የልዑል ኀይል ይጋርድሻል [ይጸልልሻል]፡፡» አለ፡፡ ስለ ወልድም፡- «ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡፡» አለ፡፡[25] እነሆ! ሥላሴ እዚህ አሉ፡፡ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ወልድ ሲጠመቅ አብ፡- «የምወደው ልጅ ይህ ነው፡፡» ብሎ ምስክር ሆነ፡ መንፈስ ቅዱስም እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ተቀመጠ እነሆ! ሥላሴ እዚህ አሉ፡፡[26]

ደግመኛም ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን፡- «እንግዲህ ሒዱና በዓለም ዳርቻ ሁሉ ወንጌልን አስተምሩ [ስበኩ]፡፡ አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው፡፡» አላቸው፡፡[27] መጠመቅን በማይለያዩ ሦስትነት [ስም] አዘዘ፡፡ ያስተማሩን የሥላሴን ስሞች አስጠብቀውን ከሥላሴ ዘንድ አማፀኑን በሥላሴ ስም በመጠመቃችን ግን በሥላሴ አደባባይ እንደምንመረመር ዕናውቃለን፡፡ እርሱም አይሁድን ሲወቅሳቸው፡- «በአብ ዘንድ እኔ የምከሳችሁ አይደለም፡ እርሱን ተስፋ የምታደርጉት የሚከሳችሁ ሙሴ አለ፡፡»[28] አብ ከልጁ ጋር ባይመጣ ሙሴ ሕዝቡን በአብ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመኑ አብ በሌለበት ለመክሰስ እንዴት ይችላል? የአብ መምጣት ባይኖር ኖሮ የሙሴ መክሰስ አይኖርም፡፡ የሙሴ መክሰስ ከሌለ በአይሁድ ላይ ዘለፋ የለም፡፡ አይሁድን መዝለፍ ከሌለ የማይታበለውን የእግዚአብሔርን ቃል ውሸት አደረጋችሁት፡፡ ጌታችን በወንጌል፡- «በሰው ፊት የሚያምነኝን እኔም በሰማያት በሚኖር አባቴ ፊት አምነዋለሁ፡ በሰው ፊት የሚክደኝን በሰማያዊ አባቴ ፊት እክደዋለሁ፡፡»[29] ብሏል፡፡

እነሆ! የአብ መምጣት በልጁ እንደበት ግሃድ ተደረገ፡፡ የአብ ምጽአት

24. ዮሐ. ፲፮፥፰-፲፩::
25. ሉቃ. ፩፥፴፭::
26. ማቴ. ፫፥፲፯::
27. ማቴ. ፳፰፥፲፱::
28. ዮሐ. ፭፥፵፭::
29. ማቴ. ፲፥፴፪-፴፫:: ማር. ፰፥፴፰::



www.ethiopianorthodox.org

ባይኖር ኑሮ፦ «በሰው ፊት የሚያምነኝን በአባቴ ፊት አምነዋለሁ፤ በሰው ፊት የሚክደኝን በሰማያዊ አባቴ ፊት እክደዋለሁ።» ባላለ ነበር። እነሆ! የእግዚአብሔር ልጅ በአባቱ ፊት፣ ከሚያምንበት ጋር በሰው ፊት፣ በሰማያት በሚኖር በአብ ፊት ሲያምነው፤ በሰው ፊት የሚክደውንም በሰማያት በሚኖር በአብ ፊት ሲክደው ፈጽሞ ዐሳየ። [አነጻጽሮ ዐሳየ]። ስለዚህ ቃል ሰማዕታት በሰማያት ባለው በአባቱ ፊት እንዳይ ክዳቸው ምስክር ለመሆን እሳቱንና ስዕለቱን ታግሠው ጨከኑ፤ ዕዝራም፦ «በፊትህ ሞገስን ካገኘሁ ጌታዬ ሆይ! አስረዳኝ [ንገረኝ] ዓለምህን በማን እንደምትጎበኝ ለባሪያህ ንገረው።» ብሎ ለመነው።[30] እርሱም «የመጀመሪያውን በሰው ልጅ ኋለኛውን ግን ራሴ» አለው። ነቢዩ ግን «ዓለምህን በማን ትጎበኛለህ» ያለው ወደ ዓለም ስለ እግዚአብሔር መምጣት ለማወቅ ፈልጎ ነው። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን በሰው ልጅ ያለው ግን ስለ ልጁ ሰው ለመሆን መምጣቱን ሲያመለክት ነው። «የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላልና።» ራሱም የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ነው።» እንዳለ።[31] ዳግመኛ «የሰው ልጅ ሊያገለግል እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።» ይላል።[32] እንደገናም «የሰው ልጅ ዓለምን ያድን ዘንድ እንጂ በዓለም ይፈርድ ዘንድ አልመጣም።» አለ።[33] እንደገናም «የሰውን ልጅ በኀይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይ ደመና ሲመጣ ታዩታላችሁ።» አለ።[34] ዳንኤልም፦ «የሰው ልጅ በዘመናት ወደ ሸመገለው [ዘመናትን ወደ የሚያስረጅ] መጣ።» ይላል። እነሆ! ሁሉም መጻሕፍት የሰውን ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ይሉታል። አብን ግን የሰውን ልጅ ሥጋ አልተዋሐደምና የሰው ልጅ አይሉትም። ስለዚህ ዕዝራን «የመጀመሪያውን በሰው ልጅ» አለው። ይህንም ስለ ወልድ መምጣት የተናገረው ነው። ኋለኛው «ራሴ ነኝ» ያለው ግን ስለ ራሱ መምጣት ነው።

እነሆ! የአብ የምጽአቱ ጉዳና ፈጽሞ ተገኘ። ጥንት ጌታ ክርስቶስ ዛሬም ጌታ ክርስቶስ በምጽአትም ጌታ ክርስቶስ [ዘላለማዊ] ነው አለ።[35] ፍጻሜው ግን እግዚአብሔር መንግሥቱን በተቀበለው ጊዜና ፍርድ ሁሉ በተሻረ ጊዜ ነው። ዳግመኛም ዮሐንስ አቡቀለምሲስ ስለ አብና ወልድ

30 መጽ. ዕዝ. ፫፥፶፩።
31 ዮሐ ፩፥፶፩።
32 ማር ፲፥፵፭።
33 ዮሐ ፫፥፲፯።
34 ማቴ ፳፮፥፷፬።
35 ዕብ ፲፫፥፰።





ምጽአት «ቅድስቲቱን አገር ኢየሩሳሌምንም አየኋት፤ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወረደች፤ ለባሏ እንደ አጌጠች ሙሽራም ተዘጋጅታ ነበር። ከሰማይ ታላቅ ቃል ሰማሁ፤ እንዲህ የሚል፤ እነሆ! የእግዚአብሔር ቅድስናው ከሰው ጋር በእነርሱ አደረች። እነርሱም ሕዝቡ ይሆኑታል፤ እሱም አምላካቸው ይሆናቸዋል። እግዚአብሔርም አብሮ አቸው ይኖራል። ከዐይናቸው እንባን ያርቃል። ከእንግዲህ ወዲህ ሞት የለም ሐዘንም ቢሆን ጭንቀትም ቢሆን ሕማምም ቢሆን እንግዲህ የለም፤ የቀድሞው ሥርዐት አልፏልና እነሆ ሁሉም ታደሰ።»

በዙፋንም ላይ የተቀመጠው፦ እነሆ! ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም ይህ ቃል የታመነና በእውነትም የሚሆን ነውና ጻፍ አለኝ። አልፋና ዖሜጋ፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውሃ ምንጭ እንዲጠጣ እኔ እሰጠዋለሁ። ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል፥ አምላክም እሆነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይሆነኛል። ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ፥ የርኩሳንም የነፍስ ገዳዮችም፣ የሴሰኞችም፣ የአስማተኞችም፣ ጣዖትንም የሚያመልኩ፣ የሐሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው። ይኸውም ኹለተኛ ሞት ነው።

ሰባቱም ኋለኞች መቅሠፍቶች የሞሉባቸው ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ፦ ወደዚህ ና፥ የበጉንም ሚስት ሙሽራዪቱን አሳይሃለሁ ብሎ ተናገረኝ። በመንፈስም ወደ ታላቅና ወደ ረጅም ተራራ ወሰደኝ። የእግዚአብሔር ክብር ያለባት ቅድስቲቱን ከተማ ኢየሩሳሌምን ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አሳየኝ፤ ብርሃንዋም እጅግ እንደ ከበረ ድንጋይ እንደ ኢያስጲድ ድንጋይ ሆኖ እንደ ብርሌ የጠራ ነበረ። ታላቅና ረጅም ቅጥር ዐሥራ ሁለትም ደጆች ነበሩአት በደጆቹም፤ ዐሥራ ኹለት መላእክት ቆሙ [አሉ] የዐሥራ ኹለቱም የእስራኤል ልጆች ነገዶች ስሞች ተጽፈውባቸው ነበር። በምሥራቅ ሦስት ደጆች ነበሩ። በምዕራብም፣ በሰሜንም፥ በደቡብም ሦስት ሦስት ደጆች ነበሩ። ለከተማዪቱም ቅጥር ዐሥራ ኹለት መሠረቶች ነበሩአት፥ በእነርሱም ውስጥ የዐሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ስሞች ተጽፈው ነበር።

እርሱ ከኔ ጋር ይነጋገር የነበረውም ከተማዪቱንና ደጆችዋን፣ ቅጥርዋንም የሚለካበት የወርቅ ዘንግ ተሸክሞ ነበረው። ከተማዪቱም አራት



www.ethiopianorthodox.org

ማእዝን ነበራት፡ ርዝመትዋም እንደ ስፋትዋ ልክ ነበር፡፡ ከተማዪቱንም በዘንግ ለካት ስፍሯም ዐሥራ ኹለት ሺሕ ሆነ፡፡ ርዝመትዋም እንደ ስፋትዋ ልክ ነበር፡፡ ግርግዳዎቿንም በዘንግ ለካ በሰው ክንድ 44,000 ሆነ ይኸውም በመልአኩ ክንድ አንድ ነው፡፡ ርዝመትዋና ስፋትዋ ከፍታዋም ትክክል ነው፡፡ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረች፡፡ የከተማዪቱም ቅጥር መሠረት በከበረ ድንጋይ ሁሉ ተጊጦ ነበር፡፡ ፊተኛው መሠረት ኢያስጲድ፣ ሁለተኛው ሰንፔር ሦስተኛው ኬልቄዶን፣ አራተኛው መረግድ፣ አምስተኛው ሰርዶንክስ፣ ስድስተኛው ሰርድዮን፣ ሰባተኛው ክርስቲሎቤ፣ ስምንተኛው ቢረሌ፣ ዘጠነኛው ወረወሬ፣ ዐሥረኛው ክርጵራሶስ፣ ዐሥራ አንደኛው ያክንት፣ ዐሥራ ኹለተኛው አሜቴስጢኖስ ነበር፡፡ ዐሥራ ኹለቱም ደጆቹ ዐሥራ ኹለት ዕንቍዎች ነበሩት፡፡ እያንዳንዱ ደጅ ከአንድ ዕንቍ የተሠራ ነበረ፡፡ የከተማዪቱም አደባባይ ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረ፡፡ አዳራሹን ዐላየሁም ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር አምላክ በጉና አዳራሿ መቅደስዋ ናቸውና፡፡»[36]

ስነፉ ሆይ! ከዚህም በኋላ በመጽሐፍ ገጽ ያለውን የአቡቀለምሲስ የተሰወረ ነገር አስተውልልኝ፡፡ «አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፡ ፊተኛዪቱ ምድርና ፊተኛዪቱ ሰማይ አልፈዋልና ባሕርም ወደ ፊት የለም፡፡ ቅድስቲቱን ከተማ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ ተመለከትኋት፡፡» አንድም ርደተ ኢየሩሳሌም ሲል የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስን በአንድነት ወደ ማዕከለ ምድር ወደ ኢየሩሳሌም መምጣትን ይገልጣል፡ እነሆ! ፊተኛዪቱ ሰማይና ፊተኛዪቱ ምድር አልፋ አዲስ ሰማይና ምድር እንደ ታየ ነገረህ፡፡ ኢየሩሳሌም ከሰማይ ወደ ምድር እንደ ወረደች ይህችውም የእግዚአብሔር የመቅደሱ አዳራሽና የእስራኤል ቅዱስ [ምስጉን] የምስጋናው አዳራሽ ናት፡፡ ከዚህ በኋላ የሕንፃዋን ውበትና ርዝመቷን፣ ስፋቷን፣ መጠኗን፣ የዕንቍም ድንጋይ በቅጽሯ ውስጥ እንዳለ ተናገረ፡፡

ሁሉንም የሚገዛ እግዚአብሔርን እና የበጉ የሆኑትን ተመለከትኩ በምስጋናው አዳራሽ ሀገራቱም ፀሐይና ጨረቃ ያበሩላት ዘንድ አትፈልግም፡፡ የበጉን መብራት እግዚአብሔር ይበራላታልና፡ የኢየሩሳሌምን ከአብና ከወልድ ጋር ከላይ እስከታች ተመልከት፡፡ መውረድ የተሰወረውን ራእይ አስቀድሞ የሥላሴን ሦስትነት ምስጢርን ሰማይና ምድርን

36. ራእ. ፳፩፥፩-፳፪፡፡





ገልጧልና ከዚህ በኋላ ከእግዚአብሔር አብና በጉ [ወልድ] ጋር የኢየሩሳሌም ሰማያዊትን መምጣት አስከትለ፡፡ ከአባቱ ህላዌ [ባሕርይ] ከማይ ለይ ከዐማኑኤል በስተቀርስ በጉ ማነው? ዝንጉው ሆይ! እፈር አፍህን በእጅህ ውስጥ አስገባ፡፡ መርዝ ትምህርትህ በልባቸው የተመለሰ [የተጨመረ] ምእመኖችህ በነበሩ ጊዜ «ቢቱ» ቢኖር ግን እሱም ከዚህ የበለጠ በተናገረ ነበር፡፡ እኔም ከመጻሕፍት ቃል ስለ አብ አለመምጣት የሚናገር ከሌለበት ለምን በሽንገላ ነገር አሰናከለኝ እላቸዋለሁ፡፡ በማገረከን ንጉሥ ዘንድ ዕድሜው አልረዘመም [አልቆየም] የመጽሐፉን ገጽ ትቶ በሽንገላ ነገር አደነኝ፡፡ እርሱ ግን ሞቷል [የሞተ ነው] አንተን ግን ሕያው ነህ ማን ይመልስልሃል፡፡ ብትለ እኔም ይህ የእግዚአብሔር የፍርዱ ውሳኔ ነው እላችኋለሁ፡፡ እግዚአብሔር የንስጥሮስን ሞት እንዳፋጠነ ቤተ ክርስቲያንን እንዳይጠወጋት የእርሱንም ሞት [ጥፋት] አፋጠነ፡፡ እኔን ግን ከነቢያትና ከሐዋርያት በተቀበልኩት የመጻሕፍት ቃል ምእመናንን አጽንቼ የሃይማኖቱን ዘለፋ [ትችት] እስከ ምናገር ድረስ እግዚአብሔር ጠበቀኝ [አቆየኝ]፡፡ አንተም እንደ እርሱ ትሞታለህ» ብትለኝ ምጽአቱን የካደውን ዘለፋ እስከምናገር ድረስ እግዚአብሔር ጠበቀኝ እንጂ እንደ መላእክት ሞትን እንዳልቀምስ ለእኔ ሕይወትን አልሠራም መቆየ ቱም ለዚህ ነው እላችኋለሁ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ግን እግዚአብሔር በዐይ ኖቹ ፊት የወደደውን ያድርግ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ፡- «በሕይወት ሆነን ብንኖር ለእግዚአብሔር እንኖራለንና፣ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን»[37] ብሎ እንደ ተናገረ እንግዲህ ግን እግዚአብሔርን ጠራሁት፥ መለሰልኝም ፈለግሁት፡ አገኘሁት፥ አንኳኳሁ፥ ተከፈተልኝ እላለሁ፡፡» ከዚህ ዓለም ብፈልስም ጉዞዬ እንደ ቢቱ የሚሆን አይደለም፡፡ እርሱ ግን ምጽአቱን በካደበት ዘንድ ይቆማል እኔም ባመንኩበት እቆማለሁ፡፡ እንግዲህ ከዚህ አስቀድሞ እንደ ቢቱ ያለ ከሐዲ የተነሣ የለምና፡፡

ሰብልዮኖስም በሥላሴ አንድነት ላይ ስለ ጨመረ ከሐዲ ተባለ፡፡ አቡርዮስም የሥላሴን አንድነት ስለ ለየ አርጌንስም የወልድን ከአብ ማነስ ስላስተማረ፣ ፎጢኖስም የወልድን መለኮታዊ አኗኗር ከአብ መለኮት ስላዘገየ፣ አርዮስ፣ ንስጥሮስ፣ መንክዮስ፣ አፍቲክስ ልዮንና የኬልቄዶን ማኅበርተኞች በእግዚአብሔር ልጅ ላይ የክሕደትን ቃል ስለ

37. ሮሜ. ፲፬፥፯-፰፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ተናገሩ ከሐድያን ተባሉ። ቢቱን ግን የአብን ምጽአት ስለ ካደ ከሐዲ አልነው። አብ መልክም ለሚሠሩ ሁሉ አባት እንደሚባል እንዲሁም ቢቱን የዘንጉአን አባትና የከሐዲያን አለቃ እንለዋለን። እንግዲህ የስሕተት አባት፣ የውሸት አባት፣ የሽንገላ አባት፣ የዐመፅ አባት፣ የክፋት አባት፣ የበቀል አባት፣ የቂምና የቅንዓት አባት፣ የሰይጣን ልጅ የአጋንንት ወንድማቸው፣ የከሐድያን አባታቸውና የመናፍቃን መምህራቸው እንለዋለን። ፍሬው መራራ ፍሬ ወይኑ የእፉኝት መርዝ፣ ዘለላውም መራራ እና መጥመቂያውም የሬት ደም ነው። የወይኑ ዐጸድ እንደ ሰዶም ዐጸድ ወይን ሲሆን ሐረጉም የገሞራ ነው።[38]

እንግዲህ ስለ ወልደ እግዚአብሔር የአመጣጥ ጉዳና እንናገራለን። እነርሱም ሦስት ናቸውና። በመጀመሪያው ሥጋ ለመልበስ ወደ ንጽሕት ድንግል ዳግመኛ ሐሳዊ መሲህንና በእርሱም ማኅተም የታተሙትን ለመበቀል ይመጣል። ከዚህ በኋላ ለልዑልን ቅዱሳን ምሳን ያደርጋል [ማዕድ ያዘጋጃል]። ዮሐንስ አቡቀለምሲስ «በደብረ ጽዮን ያ በግ ይቆምላቸዋል» እንዳለ።[39] የጥበብ ምንጭ ጳውሎስም ስለሦስቱ የምጽአቱ ጉዳና ተናገረ። ስለ መጀመሪያዋ ምጽአቱ «ከዳዊት ዘር በሥጋ መጣ።» አለ።[40] ዳግመኛም በሰላም ቃል ሲተረጉም፡ «ከመላእክትስ፡- አንተ ልጄ ነህ እኔም ዛሬ ወልጄሀለሁ።» ደግሞም፡- «እኔ አባት እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል። ለማን አለ? ይህን ቃል በማስከተልም «በኩርን ወደ ዓለም በላከው ጊዜ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይሰግዱለታል።» አለ።[41] ይህን ግን ስለ ደብረ ጽዮን መንግሥት ተናገረ። «የደብረ ጽዮን ምሳ የለም።»[42] ለሚሉት ግን ከሺሕ ዓመቱ ማዕድ ድርሻ እንደ ሌላቸው በኢየሱስ ክርስቶስ እጅ መልኩ አለ። በመዝሙር፣ «በረከትን ያቃለላት ከእርሱ ትርቃለች።»[43] እንደ ተባለ።

ጳውሎስም ስለ ደብረ ጽዮን መንግሥት እንዲህ ሲል ተናገረ፦ «በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥

38. ዘዳ. ፴፪ ፡ ፴፪::
39. ራእ. ፲፱ ፡ ፲፭::
40. ሮሜ. ፩ ፡ ፫::
41. ሳሙ ካልዕ ፯ ፡ ፲፬፡ ዕብ. ፩ ፡ ፭-፮::
42. ምሳሔ ደብረጽዮን ወይም የደብረ ጽዮን ማዕድ በመንግሥተ እግዚአብሔር ለቅዱሳን የተዘጋጀ ምሥጢራዊ ማዕድ ነው። በሌላ አነጋገር ቅዱሳን የሚያገኙትን ጸጋና የሚወርሱትን ክብር የሚገልጥ ቃል ነው::
43. መዝ. ፻፰ ፡ ፲፯::





ልዑልን ለመቀበል በደመና እንነጠቃለን። ሁልጊዜም ከጌታችን ጋር እንሆናለን።»[44] ጳውሎስ ስለምን «በክርስቶስ የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ» አለ። በአንደበቱና በኀሊናው ስሑል [የተሳለ] የሆነ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳ የሚገባቸውን በትንሣኤ እንደሚቀደሙ ተናገረ። ከዚያም በኋላ «እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ልዑልን ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን።» ያለው ግን ይህን የደብረ ጽዮን ምሳ ተሳታፊ ይሆኑ ዘንድ ይመስጡ ዘንድ ስላላቸው ሰዎች የተናገረው ነው። ጳውሎስ ሞትን የቀመሰ አይደለም። ነገር ግን የራሱን ሕይወት ሕያው ሆነው ይመሠጡ ዘንድ ላላቸው ሰዎች ሕይወት አደረገ። ራሱ «እናንተ ሕያዋን ትሆኑ ዘንድ እኛ እንሞታለን።» እንዳለ።[45] ጌታችንም በወንጌል «በዚያን ጊዜ ኹለት ሰዎች በአንድ አልጋ ይተኛሉ፤ አንዱን ይወስዳሉ አንዱን ይተዋሉ በአንድ አልጋ ላይ የሚተኙ ኹለት ሰዎች እነርሱ ከዓለም ድካም ያረፉ ባለጸጐች ናቸው። አንዱ የደብረ ጽዮን ምሳ ስለሚገባው ይወስዱታል። አንደኛውን ስለማይገባው ይተዉታል። መኝታቸው አንድ ቢሆንም ምግባራቸው አንድ አይደለም። ዳግመኛም «ኹለት ሴቶች በአንዲት ወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱን ይወስዳሉ ኹለተኛዋን ይተዋሉ።» የደብረ ጽዮን ምሳ የሚገባትን ይወስዷታል የማይገባትን ይተዉታል። ድካማቸው አንድ ቢሆንም ሥነ ምግባራቸው ትክክል አይደለም። እንደገናም «ኹለት ሰዎች በአንዲት እርሻ ይሆናሉ አንዱን ወስደው አንዱን ይተዉታል።»[46] ሁለቱም ገበሬዎች ናቸው። የደብረ ጽዮን ምሳ ስለ ሚገባው አንዱን ይወስዱታል፡ አንዱን ስለ ማይገባው ይተዉታል። እርሻ ለማረስ ድካማቸው [ልፋታቸው] እኩል ቢሆንም መልካም ሥራን ለመሥራት ድካማቸው እኩል አልሆነም።

ልዑልን ያገለገሉ ከደብረ ጽዮን ምሳ ተሳታፊ ይሆኑ ዘንድ በሕያውነት እንደሚወሰዱ ልብ ብላችሁ ዕወቁ [ተረዱ]። ጳውሎስ «ከዚህም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ልዑልን ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፡ ሁልጊዜም ከጌታ ጋር እንሆናለን» አለ። ከዚህም አስከትሎ «ይህን ነገር ለወንድሞቻችሁ አስተምሩ» አለ። ወንድሞች ሆይ! ስለ ዘመናትና ስለ ወራት ለእናንተ እንጽፍላችሁ ዘንድ

44. ፩ኛ ተሰሎ. ፬ ፡ ፲፯::
45. ፪ኛ ቆሮ. ፬ ፡ ፲፪::
46. ሉቃ. ፲፯ ፡ ፴፬:: ማቴ. ፳፬ ፡ ፵-፵፩::



www.ethiopianorthodox.org

አይፈቀድም። የጌታችን ቀን ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ ፈጽማችሁ ዕወቁ። ሰላምና ደኅንነት ነው ሲሉ ያን ጊዜ መጥቶ ርጉዝ ሴትን ምጥ እንደሚይዛት በድንገት ይመጣባቸዋል፤ ከቶም አያመልጡም። ይህንን ስለ ሦስተኛው ምጽአት ተናገረ። ይህችውም ኃጥአን ፍዳ የሚቀበሉባት ጻድቃን ዋጋቸውን የሚያገኙባት ናት።[47]

ዮሐንስ አቡ ቀለምሲስም፡- «ሰማይ ተከፍቶ አየሁ፥ እነሆም ነጭ ፈረስ ወጣ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል፤ በጽድቅም ይፈርዳል፥ ይዋጋልም። ዐይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ናቸው። በራሱ ላይም ዘውድ አሉ። በዘውዱ ላይም ከእርሱም በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተጻፉ ስሞች አሉ፤ በደምም የተረጨ ልብስ ተጐናጽፎአል፤ ስሙንም የእግዚአብሔር ቃል ይሉታል። በነጫጭ ፈረሶች ተቀምጠው ይከተሉታል። ከንጹሕ ብርሃን የተሠራ የሚላት ልብስም ለብሷል። አሕዛብንም ይመታበት ዘንድ ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል። እርሱም በበትረ ኀጺን ይገዛቸዋል። ይህም ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቁጣውን የወይን መጥመቂያ ይረግጣል። በጎኑም የተጻፈበት፡- የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ የሚል ስም አለው።

ከዚህም በኋላ አንድ መልአክ በፀሐይ ውስጥ ቆሞ በሰማይም መካከል ለሚበሩ ወፎች ሁሉ መጥታችሁ የነገሥታትን ሥጋና የሻለቃዎችን ሥጋ የብርቱዎችንም ሥጋ የፈረሶችንም በእነርሱም የተቀመጡትን ሥጋ የጌታዎችንና የባሪያዎችንም የታናናሾችንና የታላላቆችንም ሁሉ ሥጋ እንድትበሉ ወደ ታላቁ ወደ እግዚአብሔር ፊት ተከማቹ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ከዚህም በኋላ በነጭ ፈረስ ላይ የተቀመጠውንና ጭፍራ ዎቹንም ይወጉአቸው ዘንድ አውሬውና የምድር ነገሥታት ጭፍራ ዎቻቸውም ከእርሱ ጋር ተሰበሰቡ። ያን አውሬም ያዙት እነርሱን በሚያስታቸው መንገድ በእርሱ ፊት ተአምራትን ያደረገ ሐሰተኛው ነቢይም ከእርሱ ጋር ተያዘ የዛም አውሬ የስሙ ማኅተም ለተጻፉ ባቸው፤ ለርሱና ለምስሉም የሰገዱለትን ከነ ሕይወታቸው በዲን ወደሚቃጠል ወደ እሳት ባሕር ጣሉአቸው። የቀሩትንም በፈረስ ላይ ከተቀመጠው ከአፉ በምትወጣ ሰይፍ ገደሉአቸው። ወፎችም ሁሉ

47. ፩ኛ ተሰሎ. ፭፥፩-፫።





ከሥጋቸው ጠገቡ።[48] ከዚህ በኋላ የጥልቁንም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው። ሺሕ ዓመትም አሰረው ወደ ጥልቅም ጣለው። አሕዛብንም ወደ ፊት እንዳያስት ሺሕ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት። ከዚ ያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል።

ከዚህም በኋላ ዙፋኖች ተዘርግተው የሰው ልጅ በላያቸው ተቀምጦ አየሁ። ስለ ኢየሱስና ስለ እግዚአብሔር ቃል ስለ ሞቱ ሰዎች ነፍስ ቅን ፍርድን ፈረደላቸው። ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱት ምልክቱንም በግምባራቸው በእጆቻቸውም ላይ ያልጻፉት እነርሱ ይድናሉ። ከክርስ ቶስም ጋር ሺሕ ዓመት ኖረው ነገሡ።[49] እነሆ! በዚህ ዳግመኛ የቅዱሳን ማረፊያቸው ወደ ሆነችው ደብረ ጽዮን የወልድን መምጣት አሳወቀ።

ከዚህ በማስከተል «ፊተኛው ሰማይና ፊተኛዪቱ ምድር አልፈዋል።» አለ።[50] እነሆ! ከምጽአት ወደ ሥጋዌ የምትሠለስ፣ ከምጽአት ወደ ደብረ ጽዮን እጥፍ ድርብ የምትሆንና የምትመጣውን መንግሥት ዐሳየ። ወደ ሥጋዌ መምጣት ግን ለዓለም ድኅነት ሆነች። ኹለተኛዋም ምጽአት ለቅዱሳን ተድላ ሆነች። ሦስተኛዋ ምጽአት ግን ለኃጥአን ፍዳ ለጻድቃን ዋጋ ትመጣለች። ስለዚህ ሙሴ እግዚአብሔር ለዘላለም እስከ ፍጻሜ ይነግሣል።» አለ።[51] እንደገና «ስለ ምንኖርባት ስለ ዚያችዪቱ ዓለም እግዚአብሔር ለዘላለም ይነግሣል።» አለ። ይኸውም ስለ ደብረ ጽዮን መንግሥት ነው። እንደ ገናም በአብ የመንግሥቱ ግርማ ስለ ምትመጣውም ዓለም ተናገረ። የዘመን መከፈልና የዓመታት ዕድሜ የሌለባት በሐሳብ የማትቆጠር አለ። ጌታችንም በወንጌል «ስለ ስሜ ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል። የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል።» አለ።[52] «መቶ እጥፍ ይቀበላል የዘላለምንም ሕይወት ይወር ሳል።» ያለው ስለ ደብረ ጽዮን መንግሥት

48. ራእ. ፲፱፥፲፩-፳፩።
49. ራእ. ፳፥፩-፭። ሺህ ዓመት ዘመነ ሥጋዌ [ጌታ ሰው የሆነበት ዘመን] የሚለው ቃል ዘመነ ክርስትና፣ ዓመተ ምሕረት [የይቅርታ ዘመን] ነው። ምክንያቱም መጽሐፍ ብዙ ጊዜ ስለቁጥር ሲናገር ቁጥሮችን ሲያስተምጥ የጉደለውን ሞልቶ ያነሰውን አብዝቶ የተረፈውንም አጉድሎ ቀንሶ አጥፎ ከፍሎና ጠቅልሎ ስለሚናገር ነው። ሰቡሕ አጸምጤ፣ ሺህ ዓመትና ሐሳዊ መሲህ፣ ገጽ[illegible]።
50. ራእ. ፳፩፥፩።
51. ዘጸ. ፲፭፥፲፰።
52. ማቴ. ፲፱፥፳፱።



www.ethiopianorthodox.org

ነው። «ብዘላለም ሕይወት የሚመጣው» ያለው ግን ስለ መንግሥተ ሰማያት፥ ስለ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ምጽአት ነው። ለዘላለም ለእርሱ ምስጋና ይገባል። አሜን።

በትምህርቱ ሃይማኖቱን ያጠፋ፣ በትዕቢቱ የዲያብሎስ ልጅ የሆነ፣ አብን ስለ ምጽአቱ የካደው የቢቱ ዘለፋ ተፈጸመ። በኃጢአቱ ምግባሩ የሸተተ፣ በእምነቱ ሃይማኖትን ያጸና፣ በቅንአቱ ከከሐድያን ጋር የተጣላ [የሚጣላ]፣ በሚችለው መጠን ለዘለፋቸው የሚተጋና በአምልኮቱ በሥላሴ ስም የሚመኩታቸው እምነትና ተስፋ ፍላጻና ቀስቱ ነው። ለብፁው ስሙ ከፍ ላለ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል። ለዘላለም አሜን።





# [ምዕራፍ ፲፪]

## የትስብእት ምንባብ

በስም፥ በአካል፥ በገጽ ሦስት፥ በአኗኗር [በህልውና]፣ በባሕርይ አንድ በሆነ፥ በሐሳብ የማያገኙት፥ ምድራዊውን ዓለም በያዘ፥ ለመንግሥቱ ክብር ሰማያዊ ዓለምን ያደረገ ለእርሱ የቅድስተ ቅዱሳን ምስጋናን የሐዲስ ኪዳን ሥርዐት መሥዋዕትን እናቀርባለን። ለዘላለም አሜን።

እንግዲህ መድኃኒታችንን ከወለደችው በኋላ ከዮሴፍ ጋራ ተደመረች [በልማደ ሰብእ ኖራለች] የሚሉትን የአንጢዲቆማርያጦስን የስንፍና ዘለፋ እንጽፋለን። ከወንጌላዊው ቃል፣ «ዮሴፍ እስክትወልድ ድረስ ዐላወቃትም።» የሚለውን ምክንያት አደረጉ።[1] እነሱስ ይህን ቃል መድኃኒታችንን ከወለደች በኋላ ተደመረች [በልማደ ሰብእ ኖራለች] በማለት ተረጐሙት። አላወቃትም የሚለውን ግን በማወቅና ባለማወቅ፥ በሩካቤ ሥጋ በመተዋወቅ እና ባለ መተዋወቅ ይተረጐማል።

የጸናች አሪት በሩካቤ ሥጋ ስለ መተዋወቅ እንዲህ ትላለች፦ «አዳምም ሚስቱን ሔዋንን ዐወቃት፤ ፀነሰችም፥ ቃየንንም ወለደች። ስለ እግዚአብሔር ሰውን ገዛን» አለች። ዳግመኛም የጸናች አሪት፦ «ቃየን ሚስቱን ዐወቀ፤ ሄኖስን ወለደችለት።» ትላለች።[2] ዳግመኛም የጸናች አሪት፦ «አዳም ሚስቱን ዐወቀ፤ ሴትን ወለደችለት።» ትላለች። ይህ ግን በሩካቤ በመዋለጃ ዘር በመተዋወቅ ይተረጐማል። በእርጅና ስለ መተጣጣትና ሩካቤን ስላ ለማወቅም መጽሐፈ ነገሥት እንዲህ ይላል፦ «ንጉሡ ዳዊትም ሸመገለ፤ ዕድሜውም በዛ፤ ልብስም ደረቡለት፤ ነገር ግን አይሞቀውም ነበር። ባሪያዎቹም፦ ለጌታችን ለንጉሡ ድንግል ልጅን ይፈልጉለት በንጉሡም ፊት ቆማ ታገለግለው ዘንድ በጌታችንም በንጉሡ ብብት ተኝታ ታሞቀው ዘንድ ያምጧት አሉ። በእስራኤልም አገር ሁሉ የተዋበች ቆንጆን ፈለጉ። ሱናማይቱን አቢሳንም አገኙ፤ ወደ ንጉሡም ይዘዋት መጡ (ወሰዷት)። ቆንጆይቱም እጅግ ውብ ነበረች። ንጉሡንም ትረዳውና ታገለግለው ነበር። ንጉሡ ግን ዐያውቃትም ነበር።»[3] ይህም በሩካቤ ባለመተዋወቅ ይተረጐማል።

1. ማቴ. ፩፥፳፭።
2. ዘፍ. ፬፥፩-፳፭።
3. ፩ኛ ነገሥ. ፩፥፩-፬።



www.ethiopianorthodox.org

ወንጌላዊው፣ እስከትወልድ ድረስ ዮሴፍ ዐላወቃትም» ያለው ግን የድንግልን ጽንሷን ባለማወቅ፣ ከሌላ እንደ ሆነ ወይም በወጣቶች ሕግ [ልማድ] በጉ ሪምዕት ከጉብር እንላ እንደ ሆነ ታገኟት በመቀመጡ ይተረጐማል፤ ከዚህ አስቀድሞ በድንግልና መፅነስንና ያለ ሩካቤ መውለድን አልሰማምና። ስለዚህ የአብን ልጅ በድንግልና እንደ ፀነሰችው ልጁ ሰሎሜ ከወለደችው በኋላ የድንግልናዋ ማኅተም እንደ ተገኘ በነገረችው ጊዜ፥ ያን ጊዜ በድንግልና እንደ ፀነሰች ዐወቀ። የሰማይ ሰራዊት በተወለደበት በእት [ቤት] ውስጥ እየተጨኑቱ በተኛበት በረት ውስጥ ሲያመሰግኑ በተመለከታቸው ጊዜ፤ ያን ጊዜ እርሷ የእግዚአብሔር እናት እንደ ሆነች ዐወቃት። እረኞች ከመንጋዎቻቸው ጠቦት ሲያቀርቡለት በተመለከተ ጊዜ፥ ያን ጊዜ ከእርሷ የተወለደው የሰዎችና የእንስሳት ጌታ እንደ ሆነ ዐወቀ። ሰብአ ሰገል ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ ሲያቀርቡለት በተመለከታቸው ጊዜ፥ ያን ጊዜ ከእርሷ ሥጋ [የተዋሐደው] የነገሥታትና የመንግሥት ጌታ እንደ ሆነ ዐወቀ።

ዳግመኛ ሰሎሜ የድንግልን ሰውነት ዳስሳ ጣቶቿ በተቃጠሉ ጊዜ ያን ጊዜ እርሷ የእሳት እናት [የመለኮት እናት] እንደ ሆነች ዐወቀ።[4] ዳግመኛ ሰሎሜ ሕፃኑን በዳሰሰች ጊዜ ጣቶቿ በዳኑ ጊዜ ድንግል የማኅየዊና የሕይወት እናት እንደ ሆነች ያን ጊዜ ዐወቃት። «ዮሴፍ እስከ ትውልድ ድረስ አላወቃትም» የሚለው ትርጉም ይህ ነው። አስቀድመን ያስታወስነው ፅንሷን ባለማወቅ ይተረጐማል። ከወለደች በኋላ ግን የማይታይ ኀይል በማኅፀኗ ተወስኖ ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ በሥጋ ከእርሷ ተወልዶ እንደ ታየ ዐወቀ። መድኃኒታችንን ከወለደችው በኋላ ከዮሴፍ ጋር ተደምራለች [በልማደ ሰብእ ኖራለች] የሚሉ ከርኩሳን አጋንንትና ከጨለማ አበጋዞች ከቤልሆር ሰራዊት ጋር የተባበሩና የተደመሩ ናቸው።

አንጢዲቆማርያጦስ አዕራረ ማርያም [የማርያም ዐሮች] ከሚባሉት ስንፍና ይልቅ የአይሁድ ስንፍና በጥቂት ይሻላል። አይሁድ ባለማስተዋላቸው «አባቱንና እናቱን የምናውቃቸው የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ አይደለምን? እንግዲህ ከሰማይ ወርጃለሁ እንዴት ይለናል?» ይላሉ።[5] በገብርኤል ብሥራት

4 ሊቁ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ማኅደረ መለኮት መሆኗን ለመግለጽ የእሳት እናት ይላታል አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው አብ እሳት ወልድ እሳት መንፈስ ቅዱስ እሳት እንዲል። /ቅዳሴ ማርያም።/
5 ዮሐ. ፮፥፵፪።





ሰው እንደሆነ ስለማያውቁ በመወለጃ ዘር ከማርያም የተወለደ ይመስላቸዋልና። ስለዚህ በድንግልናዊ ፅንሷ ላይ ሐሜትን አደረጉ።

በእግዚአብሔር በጥበቡ መጋረጃ ምስጢሩ ከእነርሱ ስለተሰወረና መልአኩ በጉባኤ ፊት ስላላበሠራት በወገኖቿ መካከል ስላልነገራት በሆዷ ያለውን ፅንሱ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እስከ ኅልፈተ ዓለም ድረስ ልማድ በሆነው በሴትና ወንድ ፈቃድ ከሚገኘው ጋራ አመሳሰሉት። ልደት ግን ከብፅዕት ሴት በስተቀር ከዚህ አስቀድሞ አልሆነም፤ ከዚህም በኋላ አይሆንም። በእግዚአብሔርነቱ ለራሱ አዲስ ልደትን ፈጠረ። «ስለዚህ የእስራኤል ልጆች የእግዚአብሔርን ጥበብ ዐያውቁትም። በራሳቸው ጽድቅ ይቆሙ ዘንድ ፈቀዱ። ለእግዚአብሔር ሕግ ግን መገዛት አልቻሉም።»[6] ሲል ጳውሎስ እንደ ተናገረው ለአሪት ሕግ የቀኑ ሲመስላቸው አሪትን የሰጠውን ሰቀሉት። ለሙሴ ሕግ ሲቀኑ የሙሴን አምላክ ሰቀሉት። ዳግመኛም ለአምላኩ እግዚአብሔር ሲቀኑ የእግዚአብሔርን ልጅ ሰቀሉት።

ስለዚህም መድኃኒታችን፦ «አባት ሆይ! የሚያደርጉትን ዐያውቁምና ይቅር በላቸው» አለ።[7] እነዚህ አዕራረ ማርያም [የማርያም ዐሮች] የምንላቸው መናፍቃን «መድኃኒታችንን ከወለደችው በኋላ ከዮሴፍ ጋር ተደመረች [በልማደ ሰብእ] ኖረች» ይላሉ። ምን አፍ ይህን ስድብ ይናገር ዘንድ ደፈረ? ምን ልብ ይህን ያህል መጠን ያለው ስድብን አሰበ? ይህ የስድብ ነገር ከሴቶች የመርገም ጨርቅና በሚወልዱ ጊዜ ከሚፈሰው የኀርስ ደም ይረክሳል። ሴቶች ከግዳጃቸው በሰባት ቀን ይነጻሉና፤ ሴት ልጅ ቢወልዱ በሰማንያ ቀን፥ ወንድ ልጅ ቢወልዱ በአርባ ቀን ከኀርስ ደም ይነጻሉ።[8] መለኮትን በወለደች ድንግልናዋ ላይ የሚሳደቡ ግን በዚህም ዓለም ሆነ በወዲያኛው ዓለም ንጽሕና የላቸውም። ለኃጢአታቸውም በንስሐም ሆነ በጾም፥ በቁመትም ሆነ በጸሎት መደምሰስ [የኃጢአት ሥርየት] የላቸውም። ከሃይማኖታቸው ወደ ሃይማኖታችን የተመለሰ ቢኖር ዳግመኛ

6. ሮሜ. ፲፥፫-፬።
7. ሉቃ. ፳፫፥፴፬።
8. ዘሌ. ፲፪፥፩-፭።
ሊቁ ይኸን ሀሳብ በንጽጽር ያቀረበው በብሉይ ኪዳን በግዳጅ ላይ ያሉ ሴቶች ስለሚፈሳቸው ፈሳሽና ፈሳሹን የሚነካ ሁሉ እንደሚረክስ፥ በእመቤታችን ድንግልና ላይ የስድብን ቃል የሚናገሩ ሰዎች የረከሱ መሆናቸውን ለመግለጥ እንጂ ዛሬ በግዳጅ ላይ ያሉ ሴቶች የረከሱ ናቸው ለማለት አይደለም።
9. መለኮትም በወለደች ድንግልናዋ ላይ የሚሳደቡ ግን በዚህም ዓለም ሆነ በወዲያኛውም ዓለም ንጽሕና የላቸውም፤ ለኃጢአታቸውም በንስሐም ሆነ በጾም በቁመትም ሆነ በጸሎት መደምሰስ [ሥርየተ ኃጢያት] የላቸውም ሲል መናፍቃኑ የሃይማኖትን መሠረት ስለናዱ ነው እንጂ ንስሐ የሚያድን ነው ሃይማኖት ሲይዙ ስለሆነ ነው። ንስሐ ከገቡ ግን አይሰረይም ለማለት አይደለም ለእነርሱ የሚሰጠው ግን ከተኖና ቀኖናውን ከፍጾ ፍጻውን ማገባለጥ ነው። (ማቴ. ፲፪፥፵፰)፡ ትርጓሜ ወንጌል ይመልከቱ።



www.ethiopianorthodox.org

ያጠምቁት ዘንድ ይገባል፡ ጥምቀታቸው እንደ ክርስቶስ ጥምቀት አይደለምና [አልሆነምና]። በክርስቶስ እናት ስድብን ተናግረዋልና በመሠዊያቸው ላይ የልዑል ኀይል አይጸልልም። የልዑል ኀይል ስለ ጋረደው ድንግልናዋ ክሕደትን ተናግረዋልና፡ መንፈስ ቅዱስ የቀደሳትን ዜናዋን ያረከሱ የመንፈስ ቅዱስ ጽላሎት አይደርሳቸውም።

የእግዚአብሔርን ልጅ እስከ ፀነሰችው ጊዜ የካህናት አለቆች እስከ አስጠበቋት ድረስ ለመቃረብ መንፈስ ቅዱስ ያላሰለጠነው ዮሴፍ መድኃኒታችንን ከወለደችው በኋላ ከዮሴፍ ተደመረች [በልማደ ሰብእ ኖረች] እንዴት ይሏታል። ከወለደችው በኋላ ለመቃረብ እንዴት ያሰለጥነዋል? ምን ሥጋ የመለኮትን አዳራሽ ለመቅረብ ይችላል። ምን ሰው ወደ መለኮት ማደርያ መግባት ይችላል? ኢሳይያስ «መጽሐፍ ለማያውቅ ሰው መጽሐፍ ሰጡት» አለ።[10] «ነገር ግን ማንበቡን [ሊያነብበት] አይችልም» ይላል። የንጹሐ ሥጋዋ ዜናና የድንግልናዋ ማኅተም ወንድ ባለመቅረብ ይህ ነው። ሕዝቅኤልም «ድንቅ በሆነ ታላቅ ቁልፍ የተዘጋች ደጅ በምሥራቅ አየሁ። ከነያላን ጌታ በቀር ወደ እርሷ ገብቶ የወጣ የለም።» አለ።[11] ይህ የተዘጋ በር የድንግልናዋ ዜና ነው። ሰሎሞንም «የተዘጋች ገነት የታተመች ጉድጓድ [ያንቺ መንገዶች ናቸው] አለ።[12] በገነት አካባቢ ምን ይገኛል? የሚጣፍጥ ፍሬ አይደለምን? የሚጣፍጠው ፍሬ ምንድን ነው? የእናቱ የድንግል ማርያም ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን? የተዘጋች ገነት ማለትስ በድንግልና ቁልፍ በተዘጋች በአንቀጸ ሥጋዋ ይተረጐማል። ደግመኛ ከጉድጓድ ከሚጣፍጥ ውኃ በስተቀር ምን ይቸኝል? የሚጣፍጥ ውኃ ምንድን ነው? በወንጌል «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ»[13] ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የታተመች ጉድጓድ የተባለው የንጽሕት እናቱ የድንግልናዋ ኀይል ነው። ሁሉም ነቢያት ስለሥጋዋ በር «የተዘጋች፥ በድንግልና የታተመች» ብለዋታልና። ለቀደሳትና ላነጻት ለእግዚአብሔር ለዘላለም ምስጋና ይሁን።[14]

የርኩሳት መምህራን የአዕራረ ማርያም [የማርያም ዐሮች] የአንጢዲቆማ

10. ኢሳ. ፳፱፥፲፩-፲፪
11. ሕዝ. ፵፬፥፩-፪።
12. መኃ. ፬፥፲፪
13. ዮሐ. ፯፥፴፯።
14. ለቀደሳትና ላነጻት ሲል እመቤታችን ከዚህ በፊት ርኩሰት ኖሮባት አነጻት ለማለት አይደለም በልበ ሥጋዊ ለእናትነት ተለይታ መመረጧን ለመግለጥ ነው።





ርያጦስ ዘለፋቸው ተፈጸመ። የመንፈስ ቅዱስ ጽላሎት አልደረሳቸውም። የክርስቶስን እናት በአፋቸው ቃል እንዳረከሷት ሥጋ ከለበሱ ሁሉ ርኩሳን እንሳቸዋለን። በምድር ገጽ ከሚመላለሱት ውስጥ ከፈረሶችና ከአህዮች ጥንብ የሚከረፉ ናቸው። ለስመሥላሴ ማሕሌት የሚያቀርብ፡ ለቤተመቅደስ የሚዘምር፡ የሐዋርያት ትምህርት የጴጥሮስና የጳውሎስ ደቀ መዝሙር በምግባሩ በዳዩ ጊዮርጊስ አለ። የኢየሱስ ክርስቶስ የምስጢሩ በጎች ምእመናን ሆይ! እግዚአብሔር በአዲሲቷ የሰርግ ቤት ከአባቶቹ ሐዋርያት ዕቅፍ ውስጥ ያስቀምጠው ዘንድ ሥርየተ ኀጥያት ለምኑለት። ለዘላለም አሜን።



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፲፫]

## የሆሣዕና ምንባብ

አንድ በሆነ በናዝሬታውያን አምላክ በአብ ስም አምኜ አብን ወላዲ ብዬ፤ በወልድ ስም አምኜ ወልድን ተወላዲ ብዬ፤ በመንፈስ ቅዱስ አምኜ መንፈስ ቅዱስን ሠራጺ ብዬ፤ ምንም ለአጠይቆ አካላት ሦስት ብልም አንድ በሆኑ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንጀምራለን።

የህብቱ ክብደት የማይመጠን፤ የመንግሥቱ ስፋት የማይወሰን የመለኮቱ ተዋሕዶ ያለ መለየት የሚኖር፤ በሥልጣንና በስም የሠለጠነ፤ ከዘመናት አስቀድሞ በአንድነት አንድ የሆነ፤ የማይጨልም የመብራታቸው ብርሃን፤ የማይንገዳገድ የመርከቦችን አለቃ (መሪ) የማያዘነብል የሃይማኖታችን ምሰሶ ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን ጠዋት ማታ ካደጉ ከሁሉም ምእመናን አፍና ከትጉሃን መላእክት አፍ ምስጋና ይገባል። ለዘላለም አሜን።

በኢየሱስ ክርስቶስ የምስጋና ቃል የምእመናንን ሕንጻ ሥጋቸው በሚጸናበት ገንዘብ ሃይማኖታቸው አንዱ የደረሰው በዕለተ ሆሳዕና የሚነበብ ድርሳንን ለመናገር እንደበቴን ይደክመኛል። መንፈስ ለመናገር ያስገድደኛል። ወደ አስብኩት ቦታ ለመድረስ ልቡናዬን አቃተው። የመንፈስ ቅዱስ ሠረገላም ወደ ፈተደበት ነጥቆ አደረሰው። ሆዴም ለዚህ ዓለም ለማሰብ አዘነች። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ግን ልቤን ወደ ራሱ ማረከች። አፌ ከቃሉ ጣዕም የተነሣ አልጫ ሆነ። ታላቁ ሊቀ ካህናት በመለኮቱ ጨዋነት አጣፈጠው። እግሮቼ ለመውደቅ ተንገዳገዱ፤ እግዚአብሔር በቀኝ አኖረኝ። የዘመናት ሞገድ የልቤን መርከብ አወከው። የኖኅተኞች አለቃ በተበቡ መቅዘፊያ አዳነኝ። በእኔ ላይ ጠላቶች ተነሡ። የጽድቅ መኮንን በቃሉ ስይፍ ተቃወማቸው [ተጣላቸው]። መርዝን የተመላ እባብ አንደበቱን አውለ በለበ። እግዚአብሔርም በኃያሉ ልጓም ለጐመው። «ይህን ስላ ደረገልኝ ሁሉ ለእግዚአብሔር ምን እመልሳለሁ? ከዛሬ ጀምሮ እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ በፊቴ አየዋለሁ። እንዳልታወክ በቀኜ ነውና። ስለዚህ ልቤ ተደሰተ አንደበቴም ሐሴት አደረገ፤ እል ዘንድ ይገባኛል። ደግመኛም «ነፍሴ ሆይ፤ ለምን ታዝኛለሽ?



1 ርቱዐ ሃይማኖት ከአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በፊት የተነሳ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ነው «ርቱዐ ሃይማኖት የሚለው ስም የአመነት ስሙ ሳይሆን የብዕር ስሙ ነው። በጻፈው መጽሐፍ መግቢያ ላይ ስሙን ያልገለጠው «በእንተ ሕፀተ ሃይማኖት ይላል» ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ርቱዐ ሃይማኖት ስመ ደራሲ መሆኑን በሐገ አምላክ በተሰኘው መጽሐፋቸው ጠቁመዋል። በሐገ አምላክ ገጽ 27 እንዳሉት የአውሮፓ ሊቃውንት ርቱዐ ሃይማኖት የዮሐንስ አፈወርቅ ስም በመሆኑ መጽሐፉም የዮሐንስ አፈወርቅ ነው በማለት በስሕተት ጽፈዋል።

2 መዝ. ፲፮፥፰።



ለምንስ ታውኪኛለሽ? የፊቴን መድኃኒት አምላኬን አመሰግነው ዘንድ በእግዚአብሔር ታመኚ።»[3] እል ዘንድም ይገባኛል። ደግመኛም «እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፥ የሚያስፈራኝ ማን ነው? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው፥ የሚያስደነግጠኝ ማን ነው?»[4] እል ዘንድ ይገባኛል። አቤቱ! አሁንም በሕፃናት አፍ እንደ ተመሰገንክ፤ ምስጋናህን እናገር ዘንድ ዛሬም እዝነ ልቡናዬን ግለጥ። ካህናት [ነቢያት] «በእግዚአብሔር ስም የሚመጣው እርሱ ቡሩክ ነው»፤ «በእግዚአብሔር ስም መረቅናችሁ ጌታ እግዚአብሔር ለእኛ ተገለጠ»[5] ብለው ያመሰገኑት እነሆ! ወደ አንቺ መጣ፤ ኢየሩሳሌም ሆይ! ደስ ይበልሽ እልል በይ ብዬ በነቢያት ቃል ኢየሩሳሌምን እንዳበሥራት የልቤን በር ዛሬ ከፈትልኝ።

«ኢየሩሳሌም ሆይ! ኢሳይያስ ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ! ብርሃንሽ መጥቷልና የእግዚአብሔር ክብር በአንቺ ታይቷልና እነሆ ብርሃንሽ ይብራ ብሎ ስለእርሱ የተናገረው ብርሃን መጥቷልና ደስ ይበልሽ እልል በይ»

«ኢየሩሳሌም ሆይ! ዘካርያስ የጽዮን ልጅ ደስ ይበልሽ የኢየሩሳሌም ልጅ ሐሴትን አድርጊ እነሆ! ንጉሥሽ ጻድቅና የዋህ ሆኖ በአህያይቱና በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል» ብሎ ስለእርሱ ትንቢት የተናገረለት ንጉሥሽ መጥቷልና ደስ ይበልሽ እልል በይ[6]

ፈሪሳውያንም ተሰብስበው ሳሉ ኢየሱስ «ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው? ብሎ ጠየቃቸው። የዳዊት ልጅ ነው አሉት። እርሱም፦ እንኪያስ ዳዊት፦ ጌታ ጌታዬን፦ ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው። ሲል እንዴት በመንፈስ ጌታ ብሎ ይጠራዋል? ዳዊትስ ጌታ ብሎ ከጠራው እንዴት ልጁ ይሆናል? አላቸው። አንድም ቃል ስንኳ ይመልስለት ዘንድ የተቻለው የለም። ከዚያ ቀንም ጀምሮ ወደፊት ማንም ሊጠይቀው አልደፈረም።»[7] ስለዚህ የጌታ ቃል እንግዲህ ምን እንላለን? ከድንግል የተወለደውን ልደት ካደ እንላለን? ማርያምን ፍጹም ከዳዊት ዘር እንደ ተወለደች ዕናውቃለን።

«የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ነውና» አላለምን? ደግመኛም «የሰው ልጅስ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሔዳል። ነገር ግን የሰው ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት

3. መዝ. ፵፪፥፩።
4. መዝ. ፳፯፥፩።
5. መዝ. ፻፲፯፥፳፮-፳፯፣ ማቴ. ፳፩፥፲።
6. ኢሳ. ፷፥፩-፪ ዘካ. ፱፥፱።
7. ማቴ. ፳፪፥፵፩-፵፮፣ መዝ. ፻፱፥፩።
8. ዮሐ. ፫፥፳፰-፳፱።



www.ethiopianorthodox.org

ለዚያ ሰው ወዮለት።»[9] ዳግመኛ ስለ ዕርገቱ «የሰው ልጅ ቀድሞ ወደ ነበረበት ሲያርግ ታዩታላችሁ።» አለ።[10] ዳግመኛም «ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም። እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው።» አለ።[11]

የመለኮት መውረድ ከሰማይ ሳልወረደ ሥጋ እንደተቆጠረለት መለኮት በሥጋ መታመም የማይችለው ሲሆን የትስብእት ሕማማትን መቀበል እንዲሁ ለመለኮት ይቆጠራል። ሥጋ በሰማይ ሳትኖር የመለኮት ከሰማይ መምጣት ለሥጋ እንደተቆጠረ ተመልከት። ሥጋን ከመለኮት ጋር አንድ ያደረጋት ዘንድ ይኸን ተናገረ እንጂ። ስለ ምጽአቱም «የሰው ልጅ በሰማይ ደመና ሲመጣ በኀይል ቀኝ ሲቀመጥ ታዩታላችሁ» አለ።[12] በአባቱ ቀኝ እንደ ሚመጣ ሲያመለክት፦ «በዚህ አባቱን ኀይል ይለዋል» አለ። ራሱን የሰው ልጅ ብሎ በስየመበት ቦታ ራሱን ይሾማል።

የእግዚአብሔር ልጅ ማለቱ ግን በየጥቂቱ ህልውናው ይከደን ዘንድ በማመስጠር ለአይሁድ ኀሊና እንዳይታወቅላቸው ነው። ለሕማማቱ መስ ቀል ይተጋልና። ይሁዳን «እንግዲህ የምታደርገውን በፍጥነት አድርግ»[13] ብሎ እንዳሥለጠነው ስለ ራሱ የሰው ልጅ በማለቱ ሳያፍር እንዴት የዳዊት ልጅ በመባል ያፍራል። ከሰው ልጅ ወገንስ ችግረኛ አለ፣ አካል ጉዳ ተኛ አለ፣ ዐይነ ስውር አለ፣ በዳይ አለ፣ ባለጤና አለ፣ ድውይ አለ፣ ሀብታም አለ፣ ድኃ አለ፣ ክፉ አለ፣ ያማረ አለ፣ አይሁዳዊ አለ፣ አረማዊ አለ፣ ጻድቅ አለ፣ ኃጢአተኛ አለ፣ ጥበበኛ አለ፣ [ዐላዋቂ] አለ።

ዳዊትስ በመንግሥቱ ክብር [ልዕልና] የእስራኤል ንጉሥ ነው። በትንቢቱ ደግሞ የእግዚአብሔር ወዳጅ ነው። ስለ እርሱ በነቢይ «እንደ ልቤ የሚሆን ሰው ባሪያዬን ዳዊትን አገኘሁት» አለ።[14] ዳግመኛም፦ «በዚህ ለዳዊት [ሥልጣንን እሰጣለሁ] ለቀባሁትም ሰው መብራትን አዘጋጀለሁ። ጠላቶቹ ንም ኀፍረትን አለብሳቸዋለሁ። በእርሱ ግን ቅድስ ናዬ ያብባል።»[15] ቢያፍር የዳዊት ልጅ በመባሉ የበለጠ ባፈረ ነበር። ፈሪሳውያ ንን ግን «ዳዊትስ ጌታዬ ብሎ ከጠራው እንዴት ልጁ ይሆናል?» አላቸው። መድኀን ትስብእትን

9. ማቴ. ፳፮፥፳፬።
10. ማቴ. ፳፬÷፳፱።
11. ዮሐ. ፫፥፲፫።
12. ማቴ. ፳፬፥፴።
13. ዮሐ. ፲፫፥፳፯።
14. የሐዋ. ፲፫፥፳፪።
15. መዝ. ፻፴፩፥፲፯።





በመለኮት መዋሐድ ከፍ ሲያደጋት ለመልካም አምልኮ አንድ ትሆን ዘንድ ያለ አንዱ አካልና ያለ አንዱ መልክ ወደ ኹለት ባሕርይ እንዳያስቧት ነው። ፈሪሳውያን ክርስቶስን «የዳዊት ልጅ» ይሉታል።[16] ያለ መለኮት ተዋሕዶ የተለየ ሥጋዌን [ሰው መሆንን]ያስተምራሉ። የእግዚአብሔር ልጅ ከዳዊት ልጅ [ሰው ሆኖ] የዳዊት ልጅ እንደሚባል አያምኑም።

ስለዚህ ከወንድ ዘር እንደ ተወለደ እንዳያስቡ የኅሊናቸውን ሥር በሰ ይፌ ቃሉ ቆረጠ። እነሱ የዮሴፍ ልጅ እንደ ሆነ አስመስለውታልና፦ «አባቱ ንና እናቱን የምናውቃቸው እንግዲህ፦ ከሰማይ ወርጃለሁ እንዴት ይለናል? አሉ።[17] ዳዊትስ ጌታ ብሎ ከጠራው እንዴት ልጁ ይሆናል?» ባለ ጊዜ ዳግመኛ በዚህ ቃል የልባቸውን ሽለፈት ገረዘ። ከዳዊት ልጅ የነሳውን ሥጋ ግን ከመለኮቱ ጋር አዋሐዳት። በአንድ አካል እንዳትለይ እግዚአብሔር ለመሆን ነጠቃት። ፊልጶስን፦ «እኔን ያየ አባቴን ዐየ»[18] ባለው ጊዜ ትስብእቱን [ሰውነቱን] የተመለከተ የአባቱን መለኮት እንደ አየ ተቆጥሮ ለታልና። በዚህ የቃል ሰይፍ የዮሴፍ ልጅ እንደ ሆነ የሚያ ስቡ የፈሪሳውያንን የኅሊናቸውን ሸለፈት ቆረጠ። ይህ የቃል ሰይፍ «ከነቢያት አንዱ ነው» የሚለውን የንስጥሮስን ልሳን ቆረጠ።[19] በዚህ የቃል ሰይፍ አንድ ከሆኑ በኋላ «ትስብእት ከመለኮት ያንሳል» የሚል የልዮ ንን ልሳን ቆረጠ። በዚህ የቃል ሰይፍ «መለኮትና ትስብእት በኹለት ጉዳና በኹለት ሥርዐት ናቸው፣ ለመለኮት የመለኮት ሥራ ይገባል። ለትስብእት የትስብእት ሥራ ይገባል።» የሚሉ የኬልቄዶን ማኅበርን ልሳናቸውን ቆረጠ። በዚህ የቃል ሰይፍ «የመድኀኒታችን የሰውነቱና የመለኮቱ ገጽ ኹለት ነው።» የሚለውን የፍልብያኖስን ልሳን ቆረጠ።

ከዛሬ ጀምሮ ስለ ይሁዳ የተነገረውን ምርቃት ይነግረን ዘንድ እስራ ኤል ያዕቆብን እንጥራው። «ይሁዳ፣ ወንድሞችህ አንተን ያመሰግኑሃል፣ እጅህ በጠላቶችህ ደንደስ ላይ ነው፣ የአባትህ ልጆች በፊትህ ይሰግ ዳሉ። ይሁዳ የአንበሳ ደቦል ነው፣ ልጄ ሆይ! ከአደንህ ወጣህ፣ እንደ አንበሳ አሸመቅህ፥ እንደ ሴት አንበሳ አደባ፣ ያስነሣውስ ዘንድ ማን ይችላል? በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፣ የገዥም ዘንግ ከግሮቹ መካከል፣

16. ማር. ፲፪፥፴፭-፴፯።
17. ዮሐ. ፮፥፵፪።
18. ዮሐ. ፲፬፥፱።
19. ማቴ. ፲፯፥፲፬።



www.ethiopianorthodox.org

ኀኘር የሆነው እስኪመጣ ድረስ፡ የአሕዛብ ተስፋቸው እርሱ ይሆናል። ውር ንጫውን በወይን ዓፀድ መካከል ያስራል፡ አህያይቱንም በወይራ እን ጨት፡ ልብሶቹንና መጐናጸፊያውንም በወይን ደም ያጥባል፡ ዐይኖቹም ከወይን ይቀላል፡ ጥርሶቹም እንደ ወተት የነጹ ናቸው።» ስለ ይሁዳ የተናገ ረው የአባታችን ያዕቆብ ያ የትንቢት ቃል ዛሬ ተፈጸመ። የነገሩ ፍጻሜ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ይፈጸማል።

ለዳን እንደ ተናገረው፦ «ዳን በወገኑ ይፈርዳል፡ ከእስራኤል ነገድ እንደ አንዱ። ዳን በጐዳና ላይ እንደ እባብ ይሆናል፡ በመንገድም እንደ ቀንዳም እባብ፡ ፈረሱን ከስኮናው ይነክሳል፡ ፈረሰኛም ወደ ኋላው ይወ ድቃል። እግዚአብሔር ያድነው ዘንድ ተስፋ ያደርጋል እግዚአብሔርም ይጠብቀዋል።» «ዳን በወገኑ ይፈርዳል፡ ከእስራኤል ነገድ እንደ አንዱ።» የሚለው በሐሳዊ መሲሕ መንግሥት ይተረጐማል። ሙሴም በምርቃቱ «የአንበሳ ልጅ ዳን ከባሳን ይበራል» ይላልና።[20] ስለ ሰይጣናዊ መንግሥቱ አስፈሪነት ይህን አለ፡ አንበሳ ማለት በኹለት ይተረጐማልና።

ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ይተረጐማል፡ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ተአምራትን አድርጐ እንደ አባቱ ለድኅነተ ዓለም ይሠራልና። ዳግመኛ ዓለምን ለማሳት በአባቱ በሰይጣን ኀይል ተአምራትን በሚያ ደርግ በሐሳዊ መሲሕ መንግሥት ይተረጐማል። ያዕቆብ ስለ ኢየሱስ ክር ስቶስ መንግሥት፦ «ይሁዳ የአንበሳ ደቦል ነው። ልጄ ሆይ! ከአደንህ ወጣህ፡ እንደ አንበሳ አሸመቀ፡ እንደ ሴት አንበሳም አደባ፡ ያስነሣው ዘንድ ማን ይችላል?» አለ። ሙሴ ስለ ሐሳዊ መሲህ፦ «ዳን አንበሳ ነው፡ እንደ ከባሳን ያብራል» አለ። ዳግመኛም ዮሐንስ አቡቀለምሲስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መን ግሥት፦ «እነሆ፡ ከዳዊት ሥር ከይሁዳ ነገድ እነሆ አንበሳ አሸነፈ፡ አታ ልቅስ መልአክ አለኝ»[21] አለ። ጴጥሮስ ስለ ሐሳዊ መሲህ መንግሥት፦ «በመጠን ኑሩ፡ ንቁም፡ ባለጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጐ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና» አለ።[22] ያዕቆብ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት፦ «በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፡ የገዢም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፥ ገዢ የሆነው እስኪመጣ ድረስ፡ የአሕዛብ ተስፋቸው እርሱ ይሆናል።» አለ።

ስለ ሐሳዊ መሲሕ መንግሥት፦ «ዳን በጐዳና ላይ እንደ እባብ ይሆናል፥

20. ዘዳ. ፴፫ ፥ ፳፪።
21. ራእ. ፭ ፥ ፭።
22. ፩ኛ ጴጥ. ፭ ፥ ፰-፱።





በመንገድም እንደ ቀንዳም እባብ፣ ፈረሱን ከሰኮናው ይነክሳል፡ ፈረሰ ኛውም ወደ ኋላው ይወድቃል። እግዚአብሔርም ያጸናዋል፣ የሚወደውን ሁሉ ፈቃ ዱን እንዲያደርግለት ያውቃልና በደስታ ይቀበለው ዘንድ ወዳጁን በመንገድ ላይ ይጠብቀዋል። ሰይጣን «እኔ ክርስቶስ ነኝ» እንደሚል ሐሳዊ መሲሕንና፣ ፈጣሪውን እንደሸጠ ይሁዳ የሚወደው የለምና፡ ኹለቱም ከነገደ ዳን ናቸውና። እርሱ ፈቃዱን እንዲያደርጉለት በኢየሩሳሌም መንገድ ጠብ ቋቸዋል። ይሁዳን ከሊቃነ ካህናት ጋር ቃል ኪዳን ያደርግለት ዘንድ እነ ርሱም ቅዱሱን በማስቀል ሠላሳ ብር ይሰጡት ዘንድ እስም ክርስቶስን አሳልፎ ይሰጣቸው ዘንድ በኢየሩሳሌም ሜዳ ጠበቀው።

ከኃጢአት ሁሉ ፍቅረ ንዋይ የሚያስደንቅ ነው። እርሱ አስቀድሞ ከጌታው ሙዳዬ ምጽዋት ውስጥ ከሚገባው ብር ይሰርቅ ነበርና። ማርያም ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር አምጥታ የኢ የሱስን እግር በቀባች፣ በጠጉርዋም እግሩን ባበሰች ጊዜ። ቤቱ በናርዶስ ሽቱ መዓዛ በተመላ ጊዜ ግን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የስምዖን ልጅ የአስቆሮቱ ይሁዳ፦ «ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለምን ነው?» አለ። ስለዚህ ወንጌላዊው ዘለፈው፦ «ይህንም የተናገረ ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ ለድሆች ራርቶላቸው [ተጨንቆላቸው] አይደለም። ሙዳየ መባም ይዞ ከሚገባው ይወስድ ስለ ነበር ነው።»[23] በዚህ ሁሉ ፍቅረ ንዋይ አለመጥገብ ጌታውን እስከ መሸጥ ደፈረ።

እንግዲህ ሐሳዊ መሲሕ ጌታችን በወንጌል «በአንዲት አገር እግዚአ ብሔርን የማይፈራ ሰውን የማያፍር መኰንን ነበረ። በዚያችም አገር ከባላ ጋራዬ ፍረድልኝ እያለች ዘወትር የምትመላለስ አንዲት መበለት ነበ ረች። እርሱም ምንም እንኳን እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውን ባላፍርም ዘወትር እንዳታደክመኝ፣ እንዳታስቸግረኝና እንዳትመጣ ከእንግዲህ ለዚህች መበለት እፈርድላታለሁ» አለ። እንዳለው ለሐሳዊ መሲሕም እባብ እግዚአብሔርን እንዳይፈራ ሰውንም እንዳያፍር በልቡ ውስጥ መርዝን እስኪጨምርለት በኢየሩሳሌም በር ይጠብቀዋል። ጌታችንም በተንም በሌሊ ትም ጩኸታቸውን ለሚያሰሙት ለመረጣቸው አይፈርድላቸውም የሚለ ውን የዓመፃ ገዢን ቃል ስሙ።

23. ዮሐ. ፲፪ ፥ ፮።



www.ethiopianorthodox.org

የዓለም ገዢስ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውን የማያፍር ራሱን በወልድ ስም ሲጠራ እግዚአብሔርን የማይፈራ በቤተ እግዚአብሔር ውስጥ ማያትን ሲያስቀምጥ፡ ለጥንቱ አውሬ ምስል ይሰግዱ ዘንድ ሲያዝ ሰውን የማይፈራ ሐሳዊ መሲሕ ነው አላቸው።

የመጀመሪያውስ አባብ በመበደል ከሁሉ የሚቀድመው ሰይጣን ነው። የዓመፃ ገዢውን ከባላጋራቼ ተፋረደኝ እያለች የምትለው መበለትስ ከቤተ ክርስቲያን በፊት የታነፀችው የአይሁድ ምኩራብ ናት።[24]

በቤተ ክርስቲያንና በምኩራብ ልጆች መካከል አንድነት የለምና ክርስቶስ በእኛ በቤተ ክርስቲያን ልጆች እና በእነርሱ መካከል በሕማማተ መስቀሉ ልዩነትን አድርጓልና።

መበለቲቱስ በየማዕዘናቱ ልጆችን ለእስራኤል አምላክ ግን ከተመረጡት ከጥቂቶቹ በቀር አልወለደችለትም። ነቢዩ ኢሳይያስ እንደ ተናገረው፡- «የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር።»[25] ስለ ግልሙትናዋ ግን በነቢዩቱ እግዚአብሔር አስመስክሮባታል። «ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ዘርሽና ትውልድሽ ከከነዓን ምድር ነው። አባትሽ አሞራዊ ነበረ፡ እናትሽም ኬጢያዊ ነበረች። በተወለድሽ ጊዜ በዚያው ቀን እትብትሽ አልተቆረጠም፡ ንጹሕም ትሆኚ ዘንድ በውሃ አልታጠብሽ፡ በጨውም አልተቀባሽም፡ በጨርቅም አልተጠቀለልሽም። በተወለድሽበት ቀን ከሰውነትሽ ጉስቍልና የተነሳ በሜዳ ላይ ተጣልሽ እንጂ ከዚህ አንዳች ይደረግልሽ ዘንድ ዐይን አልራራልሽም፡ ማንም አላዘነልሽም።

በአንቺ ዘንድ ባለፍሁ ጊዜ፡ በደምሽም ውስጥ ተለውሰሽ ባየሁሽ ጊዜ በደምሽ እንዳለሽ በሕይወት ኑሪ አልሁሽ። አዎን፥ በደምሽ እንዳለሽ በሕይወት ኑሪ አልሁሽ። በእርሻ ላይ እንዳለ ቡቃያ አበዛሁሽ አንቺም አደግሽ፡ ታላቅም ሆንሽ፡ በእጅጉም አጌጥሽ፥ ጡቶችሽም አጐጠጐጡ ጠጉርሽም አደገ፡ ነገር ግን ዕርቃንሽን ሆንሽ ተራቁተሽም ነበርሽ። በአንቺ ዘንድ ባለፍሁና ባየሁሽ ጊዜ እነሆ! ጊዜሽ የፍቅር ጊዜ ነበር። እኔም መጐናጸፊያዬን በላይሽ ዘረጋሁ፡ ኀፍረተ ሥጋሽንም ከደንሁ፥ ማልሁልሽም፡ ከአንቺም ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። አንቺም ለእኔ ሆንሽ፡ በውሃም

24. ሉቃ. ፲፰፥፲።
25. ኢሳ. ፩፥፱።





አጠብሁሽ፡ ከደምሽም አጠራሁሽ፡ በዘይትም ቀባሁሽ፡ ወርቀ ዘቦም አለበስሁሽ፡ በአቆስታ ቁርበትም ጫማ አደረግሁልሽ። በጥሩ በፍታ አስታጠቅሁሽ። በሐርም ከደንሁሽ፥ በጌጥም አስጌጥሁሽ፡ በእጅሽም ላይ አምባር በአንገትሽም ላይ ድሪ አደረግሁልሽ። በአፍንጫሽም ቀለበት፡ በጆሮሽም ጉትቻ፥ በራስሽም ላይ የክብር አክሊል አደረግሁ። በወርቅና በብር አጌጥሽ፥ ልብስሽም ጥሩ በፍታና ሐር ወርቀ ዘቦም ነበር፡ አንቺም መልካሙን ዱቄትና ማርን ዘይትንም በላሽ፡ እጅግ በጣም ውብ ሆንሽ፥ ለመንግሥትም ደረስሽ። በአንቺ ላይ ካኖርኋት ከክብር የተነሣ ውበትሽ ፍጹም ነበርና ዝናሽ በአሕዛብ መካከል ወጣ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።

ነገር ግን በውበትሽ ታምነሻል፡ ስለ ዝናሽም አመንዝረሻል፡ ምንዝርናሽንም ከመንገድ አላፊ ሁሉ ጋር አበዛሽ። ከልብስሽም ወስደሽ በኮረብቶች ላይ በዝንጉርጉር ልብስ ያስጌጥሻቸውን መስገጃዎች ለራስሽ ሠራሽ፡ በዚያም ገለሞትሽ። እንዲህም ያለ ነገር ከአሁን በፊት አልነበረም፡ ከእንግዲህ ወዲያም አይሆንም። ከሰጠሁሽም ከወርቄና ከብሬ የተሠራውን የክብርሽን ዕቃ ወስደሽ የወንድ ምስሎች ለራስሽ አድርገሻል፡ አመንዝረሽባቸውማል። ወርቀ ዘቦውንም ልብስሽን ወስደሽ ደርበሽላቸዋል። ዘይቴንና ዕጣኔን በፊታቸው አኖርሽ። የሰጠሁሽንም እንጀራዬን ያበላሁሽንም መልካሙን ዱቄትና ዘይቱን ማሩን ጣፋጭ ሽታ አደረግሽ፥ በቤታቸውም አኖርሽ። እንዲህም ሆኖአል ይላል ጌታ እግዚአብሔር። ለእኔም የወለድሻቸውን ወንዶችና ሴቶች ልጆችሽን ወስደሽ መብል ይሆኑ ዘንድ ሠዋሽላቸው። ልጆቼን አርደሽ ለእነርሱም በእሳት በኩል አሳልፈሽ ሰጠሽ። በውኑ ግልሙትናሽ ሁሉ ዕርቃንሽን ሆንሽ፡ ተራቁትሽም ሳለሽ፥ በደምሽም ተለውሰሽ ሳለሽ የሕፃንነትሽን ወራት አላሰብሽም።

ውዮ ወዮልሽ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፥ ከክፋትሽም ሁሉ በኋላ የምንዝርናን ሥፍራ በየአደባባዩም ከፍ ያለ ቦታን ለራስሽ ሠራሽ። በየመንገዱ ራስ ከፍ ያለውን ቦታሽን ሠራሽ፡ ውበትሽንም አረከስሽ። ለመንገድ አላፊ ሁሉ እግርሽን ገለጥሽ፡ ግልሙትናሽንም አበዛሽ። ሥጋቸውም ከወፈረ ከጐረቤቶችሽ ከግብጻውያን ጋር አመነዘርሽ፡ እኔንም ታስቆጪ ዘንድ ግልሙትናሽን አበዛሽ። ስለዚህ እነሆ! እጄን በአንቺ ላይ ዘርግ



www.ethiopianorthodox.org

ቻአለሁ፡ ድርጕሽንም አጉድያለሁ፡ ለሚጠሉሽም ከክፉ መንገድሽ የተነሣ ለሚያፍሩ ለፍልስጥኤም [ለኢሎፍሊ] ሴቶች ልጆች ፈቃድ አሳልፌ ሰጥቼሻለሁ። አልጠገብሽምና ከአሦራውያን ጋር ደግሞ ገለሞትሽ። ከዚህም ጋር ገና አልጠገብሽም። እስከ ነጋዴዎች ምድር እስከ ከላውዴዎን ድረስ ግልሙትናሽን አበዛሽ። ከዚህም ጋር ገና አልጠገብሽም።

የማታፍረውን የጋለሞታን ሥራ ሁሉ ሠርተሻልና ልብሽ ምንኛ ደካማ ነው? ይላል ጌታ እግዚአብሔር። በየመንገዱ ራስ የምንዝርናሽን ሥራ ሠርተሻል። በየአደባባዩም መኖሪያሽ አድርገሽዋል። ዋጋዋን እንደ ምትንቅ እንደ ጋለሞታ አልሆንሽም። በባልዋ ፋንታ ሌሎችን ተቀብላ የምታመነዝር ሴትን ትመስያለሽ። ለጋለሞቶች ሁሉ ዋጋ ይሰጡአቸዋል። አንቺ ግን ለውሽሞችሽ ሁሉ ዋጋ ትሰጫለሽ። ከአንቺም ጋር ለማመንዘር በዙሪያሽ ይገቡብሽ ዘንድ ማመለጃ ትሰጫቸዋለሽ። ግልሙትናሽ የሚበልጥ [የሚብስ] ነው። ማንም ለግልሙትና የሚከፍልሽ የለም። ዋጋ ሳይሰጥሽ አንቺ ዋጋ በመስጠትሽ በዚህ ነገር ልዩ ሆነሻል።

ስለዚህ ጋለሞታ ሆይ! የእግዚአብሔርን ቃል ስሚ፡ ከውሽሞችሽ ጋር ባደረግሽው በግልሙትናሽ ርኵስትሽ ስለ ፈሰሰ ኀፍረተ ሥጋሽም ስለ ተገለጠ ስለ ርኵስትሽ፣ ጣዖታት ሁሉ ስለ ሰጠሻቸውም ስለ ልጆች ደም ስለዚህ እነሆ! ከእርሱ ጋር ደስ ያለሽን የወደድሻቸውንም ውሽሞችሽ ሁሉ ከጠላሻቸው ሁሉ ጋር እሰበስባቸዋለሁ። በአንቺ ላይ በዙሪያሽ እሰበስባቸዋለሁ ኀፍረተ ሥጋሽንም ሁሉ እንዲያዩ በፊታቸው ኀፍረተ ሥጋሽን እገልጣለሁ።»[26]

በሆሴዕም አስመሰከረባት። እናታችሁን ውቀሷት /ተካሰሷት/፡ እናታችሁ ሚስቴ አይደለችምና እኔም ባልዋ አይደለሁምና ተምዋገቱ፡ ከእናታችሁ ጋር ተምዋገቱ። ግልሙትናዋን ከፊትዋ ምንዝርናዋንም ከጡቶችዋ መካከል ታስወግድ። ራቁቷን እንደ ተወለደችበትም ቀን እንዳላደርጋት በጥማትም እንዳልገድላት የግልሙትናዋ ልጆች ናቸውና ልጆችዋን አልምርም። እናታቸው አመንዝራለች፡ የፀነሰቻቸውም እንጀራዬንና ውሃዬን፣ ጥጤንና የተልባ እግሬን ዘይቴንና መጠጤን ከሚሰጡኝ ከውሽሞቼ በኋላ እሄዳለሁ ብላ አስነወረቻቸው። ስለዚህ እነሆ! መንገድሽን በእሾህ እዘጋለሁ፡ መንገድዋንም እንዳታገኝ ቅጥርን እቀጥርባታለሁ። ውሽሞችዋንም ትከተላለች

26. ሕዝ. ፲፮፥፩-፶፰።





ነገር ግን አትደርስባቸውም፣ ትወጋቸውማለች ነገር ግን አታገኛቸውም። እርስዋም፦ ከዛሬ ይልቅ የዚያን ጊዜ ይሻለኝ ነበርና ተመልሼ ወደ ቀደመው ባሌ እሔዳለሁ ትላለች።

እርስዋም እህልንና ወይን ጠጅን ዘይትንም የሰጠኋት፥ ለበዓልም የተሠራውን በብርና ወርቅ ያበዛሁላት እኔ እንደ ሆንሁ ዐላወቀችም። ስለዚህ እህሌን በጊዜዋ ወይን ጠጄን በወራትዋ እወስዳለሁ። ራቁትነትዋንም እንዳትሸፍን ጥጤንና የተልባ እግሬን እገፍፋታለሁ። አሁንም ውሽሞችዋ እያዩ ነውርዋን እገልጣለሁ። ከእጄም ማንም አያድናትም። ይህን ምስክርነት በነቢዩ አስመሰከረ። ስለ ሥጋ ዝሙት ብቻ አይደለም። በግብጽ፣ በጢሮስና በሲዶና አማልክቶችና በላያቸው ላይ የእግዚአብሔር ስም ባልተሰየመባት [ባልተጠራባት] በሁሉም አሕዛብ አማልክት ስላመነዘረች እንጂ።[27] ከዛሬ ጀምሮ ግን ያዕቆብ፦ «ዳን በጎዳና ላይ የሚጠብቀው እንደ እባብ ይሆናል።» ወደሚለው ትርጓም ገብተን እንናገር። ይህ ግን ሰይጣን በሐሳዊ መሲሕ መንግሥት እንደሚገባ ይተረጐማል። በማስከተልም «በመንገድም እንደ ቀንዳም እባብ ፈረሱን ከሰኰናው ይነክሳል። ፈረሰኛም ወደ ኋላው ይወድቃል። እግዚአብሔርም ይጠብቀዋል። በመለኮቱ ኀይል እርሱ ተሸክሞአቸው ሦስትነቱን እንደ ሚሸከሙ ኪሩቤል ፈረሶቹ የሥላሴን ስም ከምትሸከም ያለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ፈረሱ ምንድን ነው? «ፈረሴንና የፈርዖንን ሠረገላ አስመሰልኩሽ» ተብሎ በመሐልየ መሐልየ እንደ ተነገረ ፈርዖን በሰይጣን ሠረገላዎቹም ለማሚረት በሚጫኑባቸው ይተረጐማል። በፈረሴ አስመሰልኩሽ የሚለው ቤተ ክርስቲያንን መጀመሪያ የሰይጣን ሰረገላ ነበርሽ ያላት የእግዚአብሔር ልጅ ቃል ዛሬ ግን መሸከሚያ /ማረፊያ/ ትሆኚ ዘንድ በኪሩባውያን ፈረሶቼ አስመሰልኩሽ በሚለው ይተረጐማል።

«ፈረሱን ከሰኰናው ይነክሳል» የሚለው ግን በሐሳዊ መሲሕ መንግሥት ሰይጣን ቤተ ክርስቲያንን ያሰናክላት ዘንድ ይወዳልና በጥርሱ መርዝም የምእመናን ሰኰናቸውን ይነክሳል። የሚድን አለ፥ የሚጠፋም አለ። ስለሚመጣውም «ፈረሰኛም ወደ ኋላው ይወድቃል» አለ፡ በእርሱ ላይ ያለውን ሃይማኖት ጥሏልና። ስለሚድነውም «እግዚአብሔር ይጠብቀዋል» አለ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፦ «ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉ፤ እስከ መጨረሻው የሚታገሥ እርሱ ይድናል።» ብሎ እንደተናገረ

27. ሆሴ. ፪፥፩-፳፫።



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ያጸናዋል፡ /ይጠብቀዋል/ የሚለው ግን እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን ፈጽሞ የሚጥላት አይደለም:: ከምእመናንም አምልኮተ ሥላሴን የሚያስታጉል አይ ደለም:: ወደ ግብፅ ምድር [ዋሻ] ፍርኩታዎች ተራ ሮች በመሸሸ የሚድኑ አሉ:: እነዚያን ቀኖች እግዚአብሔር ባያሳጥር ሥጋ የለበስ ሁሉ ባልዳነም ነበር:: ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡ ሰዎች ያጥራሉ::[28]

ዛሬም የኢየሩሳሌምን ሰዎችን እንናገራለን:: ጡት የሚጠቡ ልጆቻቸው፦ «ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ ንጉሥ ቡሩክ ነው:: ሆሳዕና በአርያም ለእግዚአብሔር በስማያት ክብር» አሉ:: «አንተ የእስራኤል ንጉሥ የተመሰገንክ ነህ» እያሉ በሮኹ ጊዜ ሕፃናት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑት ጌታችንን እነዚህ ሕፃናት ዝም ይሉ ዘንድ ገሥጻቸው ያሉትን የእነዚህን ሽማግሌዎች ስንፍና አድንቁ:: ሕፃን ሲያስተውል ማን ዝም ያሰኘዋል? እንደ ከበሮ ሲሮኹ ማን ስንፍናን ያስተምረዋል:: ከእናንተ ጎሊናችሁ ከነበዘ በስተቀር በእውነት ማንንም አያስደስተውም:: ሕፃናት ዝም ካሉ /ቢሉ/ ሕፃናትን ጥበበኛ ያደርጋቸዋል የተባለው የታመነ የእግዚአብሔር ምስክርነቱ በየት ይፈጸማል? ሕፃናት ዝም ካሉ /ቢሉ/ ጥበብ ደንቆሮ /መስማት የተሳነውን/ ጆሮን ከፍታ የሕፃናትን አንደበት ርቱዕ አድርጋለችና የተባለው በየት ይፈጸም ነበር::

ዛሬም በእልልታ ዓለም ሳይፈጠር ከአብ ለተወለደ ከቅድስት ድንግል ሥጋን የተዋሐደ [ሰው ለሆነ] ለዳዊት ልጅ «ሆሳዕና በአርያም ክብር ይገባል:: እያልን በዓል እናድርግ፡ ባለመለወጥ፣ ባለመደመርና ባለመጨመር በመለኮቱና በትስብእቱ የተባበረ [የተዋሐደ] ይኸው ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ነው:: ስለ ወይራ ቅርንጫፍ ፈንታ ለራሳችን መስቀልን እንውሰድ:: ስለ ዘንባባ ዝንጣፊ ፈንታ ወንጌላትን እንሸከም:: ስለ አይሁ ዳዊት ቤተ መቅደስ ፈንታ ቤተ ክርስቲያን እንክበባት:: በውሳጤ ሕግ [ኦሪት] ስላለባት ታቦት ፈንታ የበረከት ፍሬን የተሸከመች ማርያምን ሰላም እንበላት:: በክርስቶስ ሕያው እንሆናለን:: በክርስቶስ እንኖራለን:: በክርስቶስ ለዘላለም እንድናለን:: ለዘላለሙ አሜን::

28. ማቴ. ፳፬፥፳፪ ::





# [ምዕራፍ ፲፬]

## የጸሎተ ሐሙስ ምንባብ

ለሕዝቅኤል እንዳሳየው በምድር ላይ ሦስትነቱን የሚያጠፉ፥ በአንድ መብራትና ጸዳል የሚሸፈን፥ በሦስት አካል በኪሩቤል ሠረገላ ላይ የሚ ቀመጥ፥ በሦስትነቱ በማይከፈል በእግዚአብሔር ስም እንጀምራለን:: ዳግመኛም የዳንኤልን ከናፍር በመዳሰስ ሦስትነቱን እንዳመለከተ፥ ስለ ጥንት አኗኗሩ ከመቼ ዘመን እስከ መቼ [ከዚህ ዘመን እስከዚህ ዘመን] የማይባል፥ ስለ ኋላውም እስከ መቼ ይወከላል የማይባል ለእርሱ ከኪሩቤ ልና ከሱራፌል አፍ ምስጋና ይገባል:: ራሳቸውን ለወንጌል ቀንበር አስገዝ ተው በመስቀል ሃይማኖት ተመክተው በድንኳን አዳራሽ በቤተ መቅደስ ከሚሰበሰቡ ምእመናን ለእርሱ ስግደት ይገባል:: ለዘላለም አሜን::

በአገረ ቢታንያ በአልዓዛር ቤት ጌታችን የደቀ መዛሙርቱን እግር እንዳጠበ የሚናገር፥ የመጽሐፉስ ነገር ርቱዐ ሃይማኖት[1] አገሩ ኢትዮ ጵያ በሆነ አንድ ሰው የተደረሰው ድርሳን ይህ ነው::

ወንጌላዊውም «ፋሲካን ሊያርዱበት የሚገባው የቂጣ በዓል ደረሰ» አለ:: ጌታችን ኢየሱስም ጴጥሮስንና ዮሐንስን፦ «ፋሲካን እንድንበላ ሔዳችሁ አዘጋጁልን ብሎ» ላካቸው:: እነርሱም፦ ወዴት እናዘጋጅ ዘንድ ትወዳለህ? አሉት:: እርሱም አላቸው፦ እነሆ! ወደ ከተማ ስትገቡ ማድጋ ውሃ የተሸከመ ሰው ታገኛላችሁ ወደ ሚገባበት ቤት ተከተሉት:: ለባለቤቱም መምህሩ፦ ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ፋሲካን የምበላበት የእንግዳ ቤት ክፍል ወዴት ነው? ይልሃል በሉት:: ያም በደርብ ላይ ያለውን የተነጠፈ ታላቅ አዳራሽ ያሳያችኋል:: በዚያም በግ ፍስሀን [ፋሲካን] አሰናዱልን:: ወደ ተላኩበት ሀገር ገብተውም እንዳላቸው አልዓ ዛርን የውሃ ማድጋ ተሸክሞ አገኙት::[2] አልዓዛር ወደ ከተማ ያስገባው ዘንድ ውሃ ማድጋ በትከሻው መሸከሙ ስለምን ሆነ? እንግዲህ ለሐዋርያት እግር መታጠቢያ ማድጋ ውሃ ያስገባ ዘንድ ለተልእኮ ፈቃደ እግዚ አብሔር እንዳዘዘችው እንናገራለን:: አልዓዛር በትከሻው ማድጋ ውሃ መሸከሙ በኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ባይሆን ደቀ መዛሙርቱን «ማድጋ

1. አስቀድመን የገለጽነውን ርቱዐ ሃይማኖትን ደግሞ እናገው::
2. ሉቃ. ፳፪፥፯-፲፫፤ ማቴ. ፳፮፥፲፯-፲፱፤ ማር. ፲፬፥፲፪-፲፮፤ ዮሐ. ፲፫፥፩-፲::



www.ethiopianorthodox.org

ውሃ የተሸከመ ሰው ታገኛላችሁ ሔዳችሁ አዘጋጁልን» ከሚል አልዓዛርን፦ «ፋሲካን አዘጋጅልን በሉት አለ» እንጂ። ጌታችን ኢየሱስ የአልዓዛርን ስም ሀያውቅም ነበረን? ስለ እርሱ፦ «ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቶአል ነገር ግን ከእንቅልፉ ላስነሣው እሔዳለሁ» ያለ እርሱ አይደለምን? ደቀ መዛሙርቱ፦ «ጌታ ሆይ! ተኝቶስ እንደ ሆነ ይድናል አሉት። እነርሱ ግን ስለ እንቅልፍ መተኛት እንደ ተናገረ መሰላቸው። እርሱ ግን ከእንቅልፍ ሞት ማንቃት እንደ ሚችል ዐውቆ ሙታንን የሚያሥነሳ በመሆኑ ከእን ቅልፉ ላሥነሣው እሔዳለሁ አለ።

ወደ መቃብሩ አፋም ደርሶ አልዓዛር ሆይ! ወደ ውጭ ና ብሎ ጠራው። የሞተውም እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደ ተገነዙ ወጣ። ፊቱም በጨርቅ እንደ ተጠመጠመ ነበር። ፍቱትና ይሒድ ተዉት ብሎ አዘዘ።»[3] በአይሁድ ፊት እንዳልሞተ ከመቃብር ወጥቶ ይመላለስ ዘንድ እንዳዘዘ በምስጢር በኀሊናው ውስጥ በማኖር ለሥርዐተ ምስጢር የተፈቀደውን የማድጋ ውሃ ይሸከም ዘንድ አዘዘው። ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ተሠራ እንጂ በአልዓዛር ፈቃድ አይደለም።

እግዚአብሔር የግብጽ ምድርን በኩር ሁሉ ከቤተ መንግሥት ከሚቀመጠው ጀምሮ ወፍጮ እስከ ምትፈጨው ድረስ በገደለ ጊዜ[4] ለእስራኤል በግብጽ ምድር ፋሲካ እንደ ተሠራ [እንደ ተዘጋጀ] በመሸ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀምጦ የፋሲካውን በግ በላ። ፈርዖን በሰይጣን፣ ግብጽ በዓለም ይተረጐማል [ይመሰላል]። የፋሲካው በግ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማት [ጸዋትወ መከራ] ይተረጐማል። የእስራኤል ልጆች ከግብጽ በፍጥነት በሌሊት በወጡ በጭንቅ ሰዓት በበሉት በግ ደም እንደ ዳኑ እንዲሁ ሐዋርያት በእግዚአብሔር በግ ደም አሳልፈው ለአይሁድ በሚሰጡባት ሌሊት እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው ያላቸውን በልተው ድነዋል።

ዳግመኛ ጽዋንም አንሥቶ «ይህ ደሜ ነው፤ ጠጡ» አላቸው።[5] በኃጢአት እርሾ ያልተለወሰው ለፋሲካ የቀረበው እንጀራ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ይተረጐማል። ጳውሎስ «እናንተ በአዲሱ እንጀራ ተቀደሱ»[6] እንዳለ። ሙሴና አሮን በአልዓዛር ቤት ውስጥ ፋሲካን ለማዘጋጀት ለተላላከ

3 ዮሐ. ፲፩፥፲፩-፵፬።
4 ዘጸ. ፲፪፥፳፱።
5 ማቴ. ፳፮፥፳፯።
6 ፩ኛ ቆሮ. ፭፥፯-፰።





በተሸቀዳደሙ በጴጥሮስና በዮሐንስ ይተረጐማሉ። የሙሴ እኅት ማርያም ግን በኢየሱስ ክርስቶስ እናት በማርያም ትተረጐማለች። «በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር ዘምሩ»[7] እያሉ ያመሰገኑ ሌሎች የእስራኤል ሴቶች እነርሱ ደግሞ ሰባት አጋንንትን በአወጣላት በማርያም መግደላዊት፣ በጠራቢው ልጅ በሰሎሜ፣ በአልዓዛር እኅቶች በማርታና በማርያም ለትንሣኤው ክብር በሚተጉና በገንዘባቸው ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ባገለገሉ ሴቶች ሁሉ ይተረጐማሉ።

በሙሴ እጅ ያለው በትር በጴጥሮስ እጅ ባለው ቁልፍ [ሥልጣነ ክህነት] ይተረጐማል። ጴጥሮስ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገቡ ዘንድ ለሚገባቸው የመንግሥተ ሰማያትን በር ይከፍታልና፤ ይገቡ ዘንድ ለማይገባቸው ይዘጋባ ቸዋልና። ሙሴ የኤርትራን ባሕር ለእስራኤል ልጆች መተላለፊያን ትሰጥ ዘንድ በበትር መትቶአት እንደ ከፈታት ዳግመኛም የግብጽ ሰዎችን ታሰጥማቸው ዘንድ እንድትሰበሰብ በባሕሩ ላይ [እጁን] ዘረጋ።[8]

ዛሬም የደቀ መዛሙርቱን እግር ለማጠብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳገለገለ ወደሚናገረው ዜና እንግባ። ተራሮችን ኀይልን የሚያስታጥቃቸው፣ ለተልእኮ ማበሻ፣ [መወልወያ]፣ ታጠቀ። የባሕርን ውሃ እንደ አቁማዳ /ስልቻ/ የሚሰበስብና በውቅያኖስ እንስሮች የሚሞላ እግሮችን በማጠብ ያገለግልባት ዘንድ ከወዳጁ ከአልዓዛር ቤት የመታጠቢያ ውሃ ወስዶ በማድጋ አኖረ። ሙሴን የብረት ኩስኩስት ሠርቶ ወደ ድንኳን አዳራሽ እንዲያስቀምጥ ያዘዘው፤ ደቀ መዛሙርቱ እግሮቻቸውንና እጆቻቸውን በሚታጠቡት ኩስኩስት ውስጥ ውሃ ሞልቶ የደቀ መዛሙርቱን እግር ሊያጥብና በታጠቀበት ማበሻ ጨርቅ ሊያብስ ጀመረ። ወደ ስምዖን ጴጥሮስ መጣ። እርሱም፦ «ጌታ ሆይ! አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን? አለው። ኢየሱስም መልሶ እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም፤ በኋላ ግን ታስተውለዋለህ አለው። ጴጥሮስም፤ የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም አለው። ኢየሱስም ካላጠብሁህ ከእኔ ጋር ዕድል የለህም ብሎ መለሰለት።»[9] ይህም በአርአያ ገብር /በባሪያ አምሳል/ እግርህን ካላጠብኩህ አንተም ከበታችህ ላሉት ራስህን ዝቅ ማድ ረግ አትችልም ማለት ነው። ከበታችህ ላሉት ራስህን ዝቅ ካላደረግኸ በእነርሱ ላይ አለቃ ልትሆን አትችልም። በእነርሱ ላይ አለቃ መሆን ካልቻልክ እንግዲህ

7. ዘጸ. ፲፭፥፩።
8. ዘጸ. ፲፬፥፳፩-፴፩ ማቴ. ፲፮፥፲፱-፳።
9. ዮሐ. ፲፫፥፭-፰።



www.ethiopianorthodox.org

የመንግሥት ስማይት ተሳታፊ ልትሆን እንዴት ትችላለህ? «ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ይዋረዳል፣ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ይከብራል::»[10] የሚል አለ:: «ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲ ያገለግሉት አልመጣም::»[11]

ይህ የመለኮት ተግሣጽ ለሐዋርያት ለብቻቸው የተሠራ አይደለም:: ትምህርታቸውን በመከተል ለምንኖሀ ለእኛም እንጂ:: የሰው ልጅ የትሕትናው መስላል እስከ ስማይ ማረግ ያስችለዋል:: የትዕቢተኞች መሰላል ግን ለማዋረድ እንጂ ለማሳደግ ሥልጣን የለውም:: የሚታበይ ሁሉ የሰይጣን ልጅ ነው፡ ኢጋንንትም ወንድሞቹ ናቸው:: መንፈሱን ያዋረደ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስም ወንድሙ ነው::[12] ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበ በኋላ እንዲህ አላቸው:- «ያደረግኹላችሁን ታስተውላላችሁ? እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ:: እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል:: እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና:: ይህን ብታውቁ፡ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ:: ከዚህ በኋላ ለእራት ካመጡት እንጀራ አንዱን አንሥቶ ባረከ፡ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፡- «እንካችሁ፣ ብሉ፡ ይህ ሥጋዬ ነው» አለ:: ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖ ሰጣቸው እንዲህም አለ፡- «ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው» አላቸው::[13]

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በየተራው ዐሳየ እንጂ ከካህናት ማዓርግ አልተላለፈም:: ከሁሉ አስቀድሞ የሕዝባውያንን ሥርዐት ዐሳየ:: «ብላቴናው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር፣ ዮሴፍና እናቱም አላወቁም ነበር:: ከመንገደኞች ጋር የነበረ ስለ መሰላቸው የአንድ ቀን መንገድ ሔዱ፣ ከዘመዶቻቸውም ከሚያውቋቸውም ዘንድ ፈለጉት፡ ባጡትም ጊዜ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ:: ከሦስት ቀንም በኋላ በመምህራን

10 ማቴ. ፳፫፥፲፪::
11 ማቴ. ፳፥፳፰:: ማር. ፲፥፵፭::
12 የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግና ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ወንድም እንደሚባል ጌታችን በወንጌል ሐዋርያት በመልዕክታቸው ጽፈዋል:: ማር. ፫፥፴፫–፴፭፤ ዕብ.፪+፲፩::
13 ዮሐ. ፲፫፥፲፬–፲፰ ሉቃ. ፳፪፥፳::





መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸው ሲጠይቃቸውም በመቅደስ አገኙት::»[14] የመምህራንን ቃል መስማትና መጻሕፍትን መጠየቅ የሕዝባውያን ሥርዐት ነውና:: ዳግመኛም የአናጕንስጢስን ሥርዐት አሳየ:: ወንጌላዊው እንደ ተናገረው ወዳደገበቱም ወደ ናዝሬት መጣ፡ እንደ ልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኵራብ ገባ፥ ሊያነብም ተነሣ:: የነቢዩንም የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት፣ መጽሐፉንም በገለጠ /በተረተረ ጊዜ/፡- የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፡ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፡ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የእግዚአብሔር ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል::» ተብሎ የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ::»[15] በሮማውያን አባባል «አናጕንስ ጢስ» ማለት አንባቢ ማለት ነውና ኤጲስ ቆጶስ ማንበብ የሚችለውን «እን ጉስ» ብሎ ያዘዋል:: ትርጉሙም አንብብ ማለት ነው:: ስለዚህ ሐዋር ያት፡ - «አስቀድሞ የተፈተነ፣ ጆሮ የሚሞላ ንባብ ማንበብ የሚችል፣ አንደበቱ ያልተኮላተፈ አናጕንስጢስ ይሾምልን::» አሉ::

ጽሑፍ የሚችል በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ጽድቅ ይቆጠርለታልና ኅብስቱን በመባረክ በአምስት እንጀራ አምስት መቶ ሕዝብ ባጠገበ ጊዜና በሰባት እንጀራ ዐራት መቶ ሰው ባጠገበ ጊዜ የዲያቆናትን ሥርዐት ዐሳየ:: በመጽሐፈ ግብረ ሐዋርያት እንደ ተጻፈው ማዕድ ባርኮ ለምእ መናን መመገብ ለዲያቆናት የተሠራ ነው::

«በዚህም ወራት ደቀ መዛሙርት እየበዙ ሲሔዱ ከግሪክ አገር መጥተው የነበሩት አይሁድ በይሁዳ ኖረው በነበሩት አይሁድ አንጐራጐሩባቸው፥ በየቀኑ በተሠራው አገልግሎት መበለቶቻቸውን ችላ ይሉባቸው ነበርና:: ዐሥራ ኹለቱም ደቀ መዛሙርት ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉአቸው፡- የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም:: ወንድሞች ሆይ! በመልካም የተመሰከረላቸውን መን ፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፡ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፣ እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን:: ይህም ቃል ሕዝቡን ሁሉ ደስ አሰኛቸው፡ እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበትን ሰው እስጢፋኖስን ፊልጶስንም ጵርኮሮስንም ኒቃሮናንም

14. ሉቃ. ፪፥፵፮::
15. ሉቃ. ፬፥፲፯–፳::



www.ethiopianorthodox.org

ጢሞናንም ጳርሜናንም ወደ ይሁዲነት ገብቶ የነበረውን የአንጾኪያውን ኒቆላዎስንም መረጡ። በሐዋርያትም ፊት አቆሙአቸው፥ ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው።»[16] ጨርቅ ታጥቆ የደቀ መዛሙርቱን እግር ባጠበ ጊዜ በተዋረደ የንፍቀ ዲያቆን ሥርዐትንም አሳየ።

ከፍ የምትለው የክህነት ሹመት ግን ዝቅ ወዳለ ሥፍራ ትሕትናን አት ከለክልም። ዝቅ ስትደረግ ግን ባልሾሚት ዘንድ ትደፍር ዘንድ አይገባትም። ሙሴንና አሮንን ስለ መቃወማቸው የማይገባቸውን ዕጣን እንዳስገቡት እንደ ቆሬ ልጆች እንዳትሆን። «እሳት ከምስክሩ ድንኳን ውስጥ ወጥታ በላቻቸው፤ የአሮን ልጆች ግን ከወደዱ የሌዋውያንን ተግባር ያደርጉ ዘንድ የተገባቸው ናቸው።»[17] ሌዋውያን ግን እንደርሱ አይደሉም፤ የቆሬን ልጆች የበላች እሳት ከምስክሩ ድንኳን መውጣት እርም አስጎታቸዋለችና። እንደዚሁ ኤጲስ ቆጶስም በቅስና ሥርዐት ወይም በዲቁና ሥርዐት ያገለግል ዘንድ ይገባዋል። ለቄስ ግን ከርሱ በታች ወደሆነች ወደ ግብረ ዲቁና ዝቅ ብሎ ማገልገል ይገባዋል። ከፍ ብሎ ግን በጵጵስና ሹመት ማገልገል አይገባውም ጵጵስና ካልሾሙት በስተቀር። ወደ ኤጲስ ቆጶስነት ከፍ ይል ዘንድ ግን በተሾመበት ቦታ ሳለ አይገባውም። ዲያቆኑም ወደ ቄስ ተልእኮ እጁን ከፍ ያደርግ ዘንድ አይሆንለትም [አይገባውም]።

ስለዚህ ሐዋርያት እስጢፋኖስን አመሰገኑት እንዲህ እያሉ ይህን ያህል በጸጋ እግዚአብሔር የተሟሟቀና በኃይሉ ያለፈ በመንፈስ ቅዱስ ሀብት የሰባቱን ሰማያት ደጆች በር ተከፍቶ ዐየ።[18] የመለኮትንም ምስጢር ተመልክቶ ከራሱ አቅም በላይ አልተላለፍም /ተላልፎ አልሔደም።/ በእጁ ያስተመጠበት ሥፍራ መሥዋዕት የሠዋበት አልተገኘም። ዳግመኛም «ጌታችን እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ሁሉ ተይዞባቸዋል።»[19] ብሎ በራሳቸው ላይ እፍ ባላ ጊዜ የኤጲስ ቆጶስን ሥርዐት ዐሳየ። እነሆ! የእግዚአብሔር ልጅ በየወገኑ መዓርገ ሢመትን ፈጸመ።

ዛሬም በልባችን የክፋት መርዝ ሳለ ይህን ኅብስት ብንቀበል ዕጣ ፈንታችን ከይሁዳ ጋር እንዳይሆን ልቡናችንን ከክፋት እናንጻ። የበደለንም ቢኖር እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር እንዲለን እኛም የበደለንን

16. የሐዋ. ፮፥፩-፮::
17. ዘኁ. ፲፮፥፴፫::
18. የሐዋ. ፯፥፶፮::
19. ዮሐ. ፳፥፳፪-፳፫::





ይቅር እንበል። «እግዚአብሔር ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።» ብሎ በለውጥ [በልዋጭ] ምሕረትን ስጥቷልና። በምንጸልይበትም ጊዜ እንደ ዚህ እንድንል መምህራችን፦ «በምትጸልዩበት ጊዜ በደላችንንም ይቅር በለን፤ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደንል [እንል ዘንድ] በሉ» ብሎ አዘዘን።[20]

እንደዚህም ብንጸልይ ዳግመኛም የሚለማመጠንን አበሳውን ብንይዝበት ጸሎታችን በአለት ውስጥ እንደ ተዘራ ዘር ሆነች፥ የስንዴ ቅንጣት በአለት ውስጥ ብትዘራ አትሞትም፤ ከሞተችም አታፈራም። እንደዚሁ ለበቀለኛ ከነሊናው በቀል ባትሞት /ካልሞተች/ የሠራት ኃጢአት አትሞትም። በልቡ ውስጥ ያለችውን በቀል በየዋህነት ካልገደላት እንደ ተሰፈቀ መከበቢያ ያዞሩትና ይከቡት ዘንድ ኃጢአቶቹን ትጠራቸዋለች። በእርሱ ላይም መቅሰፍትን ታመጣለች። ከዚህ በኋላ ምሕረትን ይጠራታል፤ አትመልስለትም። ለሚለማመጠው ምሕረትን ካላደረገም ይቅርታን ይፈልጋታል፤ አያገኛትም፤ ለቆሰሉት ምሕረት አላሰበምና።

እናንተም አባቶቻችንና ወንድሞቻችን፥ በቤተ ክርስቲያን ሥርዐት ካህን እግራችሁን ቢያጥባችሁ /ካጠባችሁ/ እናንተ ደግሞ ሥጋችሁን በእንባ ምንጭ እጠቡ። ዳግመኛም ልባችሁን በየዋህነት፥ እጆቻችሁን ምጽዋት በመስጠት እጠቡ። ለክርስቶስ ሕማማት መታሰቢያ የተዘጋጀችሁ ትሆኑ ዘንድ ሥጋችሁንና ነፍሳችሁን አንጹ። ለእርሱ ለዘላለም ምስጋና ይገባል። አሜን።

20. ማቴ. ፮፥፲፬-፲፭::



www.ethiopianorthodox.org

# [ምዕራፍ ፲፫]

## የስቅለት ዓርብ የነግህ ምንባብ

በአንድነት የሚሰበክ፣ በአንድነት ወደ እርሱ የሚጸለይ፥ በአንድነት የሚመሰገን፣ በአኗኗሩ በአናዎሩ [አንዱ በአንዱ ተገናዝቦ በመኖሩ] የማይጉድልና የማይጨመርበት፥ ከሚነዋወጡ [ከሚነሡ] ሞገዶች የተነሣ የማይታወክ የብልጽግናችን መርከብ፣ ከነፋሳት ኀይል የተነሣ የማይንገዳገድ የማይማናታችን ምሰሶ፥ የሥስትነቱ ፈትል በማይበጠስ በብሩክ አምላክ በእግዚአብሔር ስም /እንጀምራለን/:: ለእርሱ አንደበት ሁሉ ይገዛል:: ለእርሱ ጉልበት ሁሉ ይሰግዳል:: በመጽሐፍም ሆነ በቁጥር መጀመሪያ መስመር በእርሱ ስምና በመስቀሉ ምልክት መጀመር [ማማተብ][1] ይገባል:: ለዘላለም አሜን

«የክርስቶስ ሥጋ እንደ እኛ ሥጋ ታሞ አልደከመም» የሚል፥ የከሐዲው የአውጣኪን[2] ዘለፋ እንናገራለን:: ከሐዲው አውጣኪ ሆይ! እንዴት የመለኮትን ሥጋዊ አልደከመም ትለዋለህ? ስለ እርሱ ወንጌላዊው፦ «በሰማርያም ሊያልፍ ግድ ሆነበት:: ስለዚህ ያዕቆብ ለልጁ ለዮሴፍ በሰጠው ስፍራ አጠገብ ወደ ምትሆን ስሟ ሲካር ወደ ምትባል የሰማርያ ከተማ መጣ:: በዚያም የያዕቆብ ጉድጓድ ነበረ:: ኢየሱስም መንገድ ከመሔድ ደክሞ በጉድጓዱ አጠገብ በዚያ ተቀመጠ አለ::»[3]

እነሆ! ንጹሕ የሆነው ወንጌላዊ ስለ እኛ ድኅነት የሆነችውን የአምላክ ልጅ ሥጋ ድካም ዜናን ግልጽ አደረገ:: በደረቱ ላይ የተቀመጠ ወዳጁ ዮሐንስ ግን የክርስቶስን የሥጋውን ድካም ለመናገር ካላፈረ በኢየሱስ ክርስቶስ የፊቱ መስተዋት ያልታየህ [ያልተወለወልክ] ጣቶችህ ያልዳሰሱትና በጣቶቹ ያልዳሰስህ አንተ እንዴት ታፍራለህ? እርሱ ግን እንዲህ ብሎ ተናገረ፦ «ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን

1 ዐቃቤ የሚለውን ዐቃቤ በሚል የሚጽፉ ትጂዎች አሉ:: ይህ ቢሆንም የመጻሕፍት ሁሉ ሕይወትና ጠባቂነት የሚታወቀው በእርሱ ስም መሆኑን ያመለክታል::

2 አውጣኪ /አፍቲክስ/ በቁስጥንጥንያ የአንድ ገዳም አበምኔት የነበረ ግሪካዊ መነኩሴ ነው:: የንስጥሮስን ትምህርት ሲቃወምና ሲከራከርም የኖረ ነው:: ነገር ግን በኋላ ከንስጥሮስ የሁለት ባሕርይ ትምህርት የራቀ ትምህርት ሲቃወምና ሲከራከርም የኖረ ነው:: መለኮት ሁለቱ ባሕርያት ሥጋና መለኮት ተቀላቅለዋል፤ ተጣፍተዋል በማለት የአርስቶትልን የቅመማ ሕግ መሠረት አድርጐ ያስተምር ነበር:: በዚህም የምሥራቅም የምዕራብም አብያተ ክርስቲያናት አውግዘውታል:: አባ ጎርጎርዮስ፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፤ ገጽ ፻፶፰::

3 ዮሐ. ፬፥፮::





ጌታችን ኢየሱስ በሥጋ ድካም ተጠምቶ ሳምራዊትን ውሃ ታጠጣው ዘንድ ለመናት:: የማይደክም ቢሆን ግን አይጠማም፥ ለጉሮሮውም ውሃ አይፈልግም /ነበር/:: እነሆ! የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋው ድካም ከሐዋርያት የሥጋ ድካም ጋር ትክክል ሆነ:: በሥጋ ድካም ራሱን ያስተካከለው ከሐዋርያት ጋር ብቻ አይደለም:: ከሁላችንም ጋር እንጂ:: ከኃጢአት ብቻ በቀር ግዕዘ ጠባይዕ አልጉደለውም /አላፋለሰም/:: ድንቃድንቅ ተአምራትን ከማድረግ በስተቀር ከሰው ልጅ ጠባይዕ አልበዛም [አልበለጠም]::

ሰይጣን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ መሰልጠን አይሆንለትምና መለኮቱ ይተጋለታልና እግዚአብሔር ወደ እኛ ሰይጣንን አያሠለጥነውም:: ከማይበላው ዕፅ እንዳንበላ የመከረንን የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ምክር ትተን የሰይጣንን ምክር በሰማን ጊዜ እኛ ራሳችን አሠለጥንነው እንጂ:: የባለጠጋ አዳራሽ ቤቱን በዘጋው መጠን የቤቱ ንብረት ሁሉ ይጠበቃል:: ራሱ ግን በሩን ከፍቶ ቤቱን ለመጠበቅ ካልተጋ ወንበዴና ሌቦች ይተናኮሉታል፤ ራሱ ከብልጽግና ይልቅ ድህነትን መርጧልና:: እግዚአብሔር አባታችን አዳምን «ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፣ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ጊዜ ሞትን ትሞታለህና» ብሎ የምትመጣውን የጥፋት መልእክት አመለከተው::[7] በእግዚአብሔር ዘንድ መቶ ዓመት እንደ አንዲት ቀን ነው:: ስለዚህ አዳም ከሺሕ ዓመቱ ሰብአ /፸/ ዓመት ጐደለው፣ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ሆኖት ሞቷልና::

እነሆ! የተናገረው ቃል እንዳይታበል በእግዚአብሔር ቀን እንተጋ ዘንድ /ምልክት/ ሆነች:: ዳግመኛ ከዕፀ በለስ በልቶ ከገነት በወጣ ጊዜ የልጁ መለኮት ሥጋዊ ምልክትን ሰጠው:: ስለዚህ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ አለ:: ይህ ኀይለ ቃል ስለ ልጁ ሰው መሆን /የተናገረው/ የቅዱስ አብ ቃል ነው፤ ጌታችን በሥጋ ጡቶች ባደገ ጊዜ ከህላዌ መለኮቱ ትንሽ ለመሆን አልተመለሰምና /እንደገናም/ የሕፃናት አካል ወደ መለኮት አካል አልተመለሰም:: በመለኮት አካል ሰው ሆኖ ቢሆን ግን ሰፊው ዓለም ባልበቃው ነበር:: ድንግልም እናት ለመሆን ባልተገባችው:: ከአኗኗሯ /ከህላዌዋ/ ሳትለወጥ ባለችበት ሆና እናት ሆነችው:: እርሱም ሰው ሆኖ በሥጋዋ ወደ አርያም ሰማይ ከፍ ሳያደርጋት፣ እርሷም ከአጽናፍ አጽናፍ ሳትሞላ ልጅ ሆናት:: ለእናቱ ከእስራኤል

7. ዘፍ. ፪፥፲፯::



www.ethiopianorthodox.org

በዐይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፡ ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክራለን።» ስለ እውነት ምስክር ዮሐንስ ይህን አለ።[4] ምስክር የሚሆን ሰው ባልተጠየቀበት ባልሰማበትና፣ ባላየበት መመስከር አይገባውምና።

ስለ እግዚአብሔር ልጅ የምስክርነቱ ቃል ዮሐንስ «የሰማነውን» ብሎ ምስክር ሆነ። ስለ መመልከቱም «በዐይኖቻችንም ያየነውን» አለ። በሰውነቱ ተመልክተውት ወዳጅ ስለ ሆኑላቸው የተመለከትነውንም አለ። በመንፈስ ጥላ የሚመላለስና በምትሐት የታያቸው እንዳናስመስለው «እጆቻችንም የዳሰሱትን» አለ። ስለዚህም የሚዳሰስ ሥጋንና የማይዳሰስ ነፍስን ነሣ። የደሟን ምንጭ ያደርቅላት ዘንድ ለዐሥራ ኹለት ዓመትም ይፈሳት የነበረችው ሴት የልብሱን ጫፍ በመዳሰስ፤ ዘማዊቷ ሴት [ማርያም እንተ እፍረት] ኃጢአቷ ይሠረይላት ዘንድ ከቅንድቦቿ [ከዐይኖቿ] በፈሰሰው በእንባ ምንጭ እግሮቹን አጥባ በፀጉሮቿ በዳሰሰችው ጊዜ፤ እርሱም የበርጤሜዎስ ልጅ የጤሜዎስን ዐይኖች ይከፍት ዘንድ ጭቃ በመለወስ ምራቁን በመቀባት በዳሰሰው ጊዜ፣ ዳግመኛም ብዙዎች ሕሙማንን ያድናቸው ዘንድ በእጆቹ በዳሰሳቸው ጊዜ ወንጌላዊው እንደ ተናገረው፦ «ብዙ ሕመምተኞችን ይዳስሳቸው ዘንድ እየጣሩ ተጠግተው ከእግሩ በታች ይወድቁ ነበር፡» እንደዳሰሳቸውም ይድናሉ።[5] እርሱ ግን የማይደክም ኀይል ነው። የሚደክም ሥጋን ተዋሐደ። በዚህ በሚደክም ሥጋ ተገለጠ፤ አልጋውን ተሸክም ባለ ጊዜ ለመጻጉዕ ኀይልን ሰጠው። እጁ የደረቀውን /የሰለለውን/ እጅህን ዘርጋ ባለው ጊዜ እጁን ዘረጋ እንደሊላቸው ዳነች።

አስቀድመን ወደተውነው ነገር እንመለስ። ወንጌላዊው፦ ጊዜውም ስድስት ሰዓት ያህል ነበር። ከሰማርያ አንዲት ሴት ውሃ ልትቀዳ መጣች። ኢየሱስም፦ ውሃ አጠጪኝ አላት፡ ደቀ መዛሙርቱም ምግብ ሊገዙ ወደ ከተማ ሔደው ነበርና። ያቺም ሳምራዊቲቱ ሴት አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ? አለችው፤ አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና።» አለ።[6] ደቀ መዛሙርቱ በሥጋ ደክም ተርበው ለምግባቸው እንጀራ ይገዙ ዘንድ ወደ ከተማ ሔዱ። ሥጋ ባይደክም ግን ስለ ሆዱ ምግብ አይራብም አያዝንም ነበር።

4. ፩ኛ ዮሐ. ፩፥፩።
5. ማር. ፲፥፵፮፤ ሉቃ. ፬፥፵።
6. ዮሐ. ፬፥፯።





ሴቶች የሚበልጥ አካል እንዳልፈጠረላት፥ ለራሱም ከገሊላ ሕፃናት የሚበልጥ አካለ ሥጋ አልፈጠረም። ያለ ሩካቤ በመፀነሱ ሕፃናትን በለጣቸው። በሕፃናት መልክ ሥዕል /በመልክ/ አልበለጣቸውም። በልደት ከድንግል ስለ ተወለደ በለጣቸው፤ በእናት ክንድ በመታቀፍ አልበለጣቸውም። ወንድ ከማታውቅ ሴት /ድንግል ማርያም/ ጡቶች ወተት በማፍለቁ ሕፃናትን በለጣቸው፤ ጡት በመጥባት አልበለጣቸውም፤ እንደ እነርሱ ጡት ለመጥባት አፉን ከፍቷልና ጡት ለማጥባት ባዘገየችው ጊዜ ሕፃናት እንደሚያለቅሱት ያለቅሳልና። ከሰብአ ሰገል እጅ መንሻ በመቀበል ሕፃናትን በለጣቸው፤ በሚዳ ላይ /በመስክ ላይ/ በመዳህ አልበለጣቸውም።

ከዛሬ ጀምሮ ግን ወደ ወጣትነቱ ሥርዐት እንመለስ። በደልን ባለማወቅና ኃጢአትን ባለመሥራት ወጣቶችን በለጣቸው፤ ባለመድከምና ባለመውዛት አልበለጣቸውም። ተአምራት በማድረግ ወጣቶችን በለጣቸው፤ ቤቶችን፣ እርሻን፣ አዝርእት፣ በገንዘብ በመግዛት አልበለጣቸውም፤ እርሱ ከእርሱ ራሱን ገቶ አድርጓልና። «ለወፎች መሥፈሪያ ለቀበሮዎች ጉድጓድ አላቸው። የሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያሳርፍበት የለውም።» እንዳለ።[8]

በኹለት ዓመና በጥቂት እንጀራ ብዙ ሰዎችን በማጥገብ ወጣቶችን በለጣቸው፤ በመራብ አልበለጣቸውም። ወንጌላዊው በሰንበት፦ «ጌታችን ኢየሱስም ወደ እርሻ ሔደ፤ ተርቧልና።» ይላልና።[9] ደቀ መዛሙርቱም እሸት ቀጥፈው ይበሉ ጀመር። ውሃውን ወይን እንዲሆን በመለወጥ ወጣቶችን በለጣቸው፤ ባለመጠማት አልበለጣቸውም። ሳምራዊትን ውሃ ታጠጣው ዘንድ ለምኗታልና። እርሷም እንዲህ ስትል ዘለፈችው፦ «አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ? አለችው። አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና ይህን አለች።»[10] አይሁድ ሳምራውያንን ይንቋቸዋልና። አይሁድ በሙሴ የኦሪት ሕግ ተጠብቀው ይጸናሉና። ሳምራውያን ግን የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ላቆመላቸው የጥጃ ምስል በዓል አደረጉ። አንዲቱን በዳን ተራራ ሌላውን በቤቴል ተራራ አቆመ። ስለዚህ አይሁድ ከሳምራውያን ጋር ትብብር የላቸውም። ስለዚህም ሳምራዊቲቱ ሕዝቧ ከሕዝቡ እንደማይተባበር ስታመለክተው፦ «አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ? አለችው።» እርሱ ግን ስለ

8. ማቴ. ፰፥፳።
9. ማቴ. ፳፩፥፲፰፤ ማር. ፲፩፥፲፪።
10. ዮሐ. ፬፥፱።



www.ethiopianorthodox.org

ሥጋው ድካም ለጥማቱ ውሃ ለመነ። እርሱም እንዲህ ሲል በመለኮት ቃሉ ገሥጻት፡- «የእግዚአብሔርን ስጦታና ውሃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑንስ ብታውቂ አንቺ ትለምኚው ነበርሽ፥ የሕይወትንም ውሃ ይሰጥሽ ነበር።» አላት።[11] ከምድራዊ ትስብእት አፍ ሰማያዊ የመለኮት ንባብ ወጣ። በዚህም ከሚታየው የሰው ልጅ ህልውና [ከትስብእት] የማይታየው የአምላክ ህልውና ኀይል ለዘላለም እንደማይለይ ዐወቅን።

ስለ ሥጋው ድካም ግን ወንጌላዊው እንዲህ ሲል ይናገራል፡- «ሰገደ [እየወደቀ እየተነሣ ማለት ነው።] መላልሶም ጸለየ፥ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ። የሚያበረታው መልአክ መጣ።»[12] ሐኪሙ ወንጌላዊው ሉቃስ ሆይ! የልቤን ቍስል ፈውስ። «የሚያበረታው መልአክ መጣ» ስለ ሚለው ቃል ልቤ ተከፍሏልና። የሊቃነ መላእክትና የመላእክትን ጌታ የሚያበረታው ምን ዓይነት መልአክ ነው? ይህ ምስጢር ታላቅ ነው። ስለ ትስብእቱም፥ ገብርኤል መወለዱ ያለ ሩካቤ መፀነሷም ያለ ዘር መሆኑን ይነግራት ዘንድ ወደ ማርያም ተላከ። እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ገብርኤል ሳያበሥራት ከድንግል ሰው ይሆን ዘንድ በቻለ፥ ባደረገውም ነበር። ነገር ግን ስለ ዕንሷ እንዳትደነግጥ ጌታን እናቱ ዕንሷ ቀስ በቀስ ባደገ ጊዜ ጤና ከማጣት ነውን? ወይንስ ሰውን ከሚቃረኑት መናፍስት ይህ ነገር የሆነው ብላ እንዳትደነግጥ ቀድሞ አሰበላት። ስለዚህም ብርሃናዊውን መልአክ «ሰላም ለአንቺ ይሁን፤ ደስ ይበልሽ፥ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ! እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ። ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ ይላት ዘንድ ላከ። ማርያምም መልአኩን፡- ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው። መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኀይል ይጸልልሻል። ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።»[13] ኀይል የለ ኀይል አይወለድምና፡- ስለዚህ የልዑል ኀይል የልጁ እናት እንድትሆን ያጸናት ዘንድ ጸለላት [ጋረዳት]።

የፍጡራን ህልውና /አኗኗር/ ያለ መንፈስ ቅዱስ መምጣት አይቀደስ

11. ዮሐ. ፬፥፲።
12. ሉቃ. ፳፪፥፵፬።
13. ሉቃ. ፩፥፴፭።

www.ethiopianorthodox.org





ምና [አይለይምና] ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ለመለኮት ማደሪያነት ይቀድሳት [ይለያት] ዘንድ ወደ እርሷ መምጣትን አስቀደመ። «እንደ ቃልህ ይሁንልኝ»[14] ባለች ጊዜ እንደ አበሠራት ሆናት [ሆነላት]። ያን ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ ከእርሷ ሥጋን ተዋሐደ [ሰው ሆነ]። ትስብእቱ ከመለኮቱ የተለየ ነውን? እንዳንል በመለኮቱ ግን ዓለም ሳይፈጠር ከአብ ተወልዷልና በትስብእቱ /በሰውነቱ/ ግን ከእርሷ በስተቀር ከዚህ አስቀድሞ አልተወለደም። መልአኩ ንግግሩን በብሥራት ቃሉ ፍጻሜ «ከአንቺ የሚወለደው የልዑል ልጅም ይባላል። እግዚአብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል።» ዳዊት ለዐሥራ ኹለቱ ነገደ እስራኤል አለቃ እንደ ሆናቸው እንዲሁም ክርስቶስም ለዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያቱ አለቃ ሆናቸው። ስለዚህ እነርሱ በዲድስቅልያ ትምህርት፡- ከድንግል በሥጋ ከዘሩ በተወለደ በክርስቶስ ልደት በመካከላችን የዳዊትን መንበር ከፍ አደረግኸ። ኢየሩሳሌምን ይቅር አልካት። ጽዮንን ማርኸት ይላሉ።

«የሚያበረታታው መልአክ መጣ» ማለት የገብርኤልን የመላኩን ዜና ሲያሳስበን [ሊያስታውሰን] እንጂ የመልአክ ማጽናናቱስ እጁን በመስጠት [በእጁ በማዳን] ወይስ በሕማማቱ ጊዜ ለመርዳት ነውን? እንደዚያስ ከሆነ የመልአኩን ርዳታ የሚሻ ከሆነ መለኮቱ ከሕማማቱ መስቀል የተከፈለ በሆነበት ነበር። ከመልአኩ ብርታት የመለኮቱ ብርታት ያይላልና [ይበልጣልና]፤ እርሱ ለኪሩቤል ብርታትን ለሱራፌል ኀይልን ሰጥቷቸዋልና፤ እርሱ የሰማያትና የምድር ብርታት በእጁ ሳለ የትስብእትን /የሰውነትን/ ሕግ ይፈጽም ዘንድ ደክሞ እንደ ወዛ። ራሱም የትስብእቱ ጠባይ ከእኛ ጠባይ ጋር ጉድለት እንዳይኖረው የሰው ልጅን ሕግ ይፈጽም ዘንድ በኀሊናው ውስጥ ሕማማትን መውደድ ሳለ «ነፍሴ እስከ ሞት ደርሳ አዘነች» አለ።[15] ስለዚህ መንፈስ ይፈቅዳል ሥጋ ግን ይደክማል አለ። ይህን ስለመለኮትና ትስብእት ተናገረ። ሰማዕታትም የአረማውያን ነገሥታት የሚቀጹላቸውን የምስክርነት ጽዋ የሚጠጡት ጣዑዖ ሆኖ አይደለም። ኢየንዳንዱን የሥቃይ ጻዕር መንግሥተ ሰማያትን ተስፋ አድርገው ታገሡ እንጂ። ጌታችንም በተያዘባት ሌሊት የአይሁድ ጭፍሮች ሳይደርሱበት፡- «አባት ሆይ! ይህችን ሰዓት ከእኔ ውሰድ አለ። ነገር ግን ስለዚህ መጥቼ ደርሼባታለሁ። በዚያ ሰዓት ነፍሴ እስከ ሞት

14. ሉቃ. ፩፥፴፰።
15. ማቴ. ፳፮፥፴፰።

ደርሳ አዘነች» ያለው «የአንተ ፈቃድ ይሁን፡ የእኔ ፈቃድ አይደለም» አለ።[16] ለሥጋው ሕማማት የርሱና የአባቱ ፈቃድ ነውና። የሥጋ እንደ በት ግን ጠባይዋን ትገልጥ ዘንድ አባት ሆይ! ይችን ጽዋ ከኔ አሳልፉት አለች። ነገር ግን ፈቃደ እግዚአብሔር ታስታጉል ዘንድ አይደለም። ስለዚህ መጥቼ ደረስኩ ትላለች። እነሆ! የመለኮትና የትስብእት አንድነት በአንዲት ቃል መውጣት ተገለጠ። ይችን ሰዓት ከኔ አሳልፉት ባለ ጊዜና ነገር ግን ስለዚህ መጥቼ ደረስኩ ባለ ጊዜ ተገለጠ። ነፍስ. እስከ ሞት ድረስ ተከዘች። ባለበት ሰዓትም የኔ ፈቃድ አይደለም የንተ ፈቃድ ይሁን አለ።

እንግዲህ ግን «እነሆ ንጉሥ የሚያበረታው መልአክ መጣ» ወደ ሚለው ቃል ትርጉም እንግባ። ንጉሥ ወደ ጦርነት በሚገባ ጊዜ በጦሩ ፊት እንዳይሸሽ መዘምራን በፊቱ እየመሰገኑት ይመላለሳሉ። በጦርነቱ ፊት በጨኸት ቃል የንጉሡን ልብ ለውጊያ ያደፋፍራሉ። እንደዚሁ ሕማመ ሥጋን እንዲቀበለው በምስጋና ቃል የመለኮትን ትስብእት [ሰውነት] የሚያበረታ መልአክ መጣ። መላእክት በተያዘም ጊዜ ምስጋናቸውን አላቋረጡም። መንግሥቱን እየቀደሱ ትዕግሥቱን ያደንቃሉ።

የእሾህ አክሊል ሲቀዳጅም በላዩ ላይ በክንፋቸው ብርሃን ይጋርዱለ። ሲቀዩቱ በፊቱ እየተሳለቁበት «የአይሁድ ንጉሥ ሆይ! ሰላም ለአንተ ይሁን»[17] እያሉ በሰገዱ ጊዜ እነርሱም «ሰውን ለወደደ ለእግዚአብሔር ክብር በሰማይ ይሁን፡ ሰላምም በምድር» እያሉ ከአምልኮት ምስጋና ጋር ይሰግዱለ። ይህም ማለት በአርያም ለሚያርፍ በሰማይት ላለው ለመለኮትህ ክብር ይገባል ማለት ነው። ጌታችን ከፍ ካለ ሥፍራ ባሉት /መላእክት/ ይቀደሳል፡ ይመሰገናል። የመስቀል ኀፍረትን [መከራ] ይቀበላል። በሰው አካል ይታያል። በሥጋ መጉናጸፊያ ይጠቀለላል። በሴት ማሕፀን የተወሰነ፡ የሰውን ልጅ ለወደደ፡ ለማይታይ ህልውና [አኗኗርህ] በምድር ላይ ሰላም ይሁን። የተመሰገነ አኗኗሩንና ትዕግሥቱን እያደነቁ ይህን ይላሉ።

እነሆ! «የሚያበረታው መልአክ መጣ»[18] የሚለውን ተረጉምንላችሁ። ንጉሥ ሆይ! በደካማ ሥጋውና በሕማማቱ አትፈርበት። እርሱ ራሱ፦ «ስለዚህ መጣሁ፡ ደረስኩባትም» ብሏልና። ዳግመኛም «ስለዚህ ስለ እውነት

16. ማቴ. ፳፮ ፥ ፴፱።
17. ማቴ. ፳፮ ፥ ፵፱።
18. ሉቃ. ፳፪ ፥ ፵፫።





ምስክር እሆን ዘንድ መጣሁ። ከእውነት የሆነ ሁሉ ቃሌን ይሰማል» አለ። ጴጥሮስንም «ሰይፍህን ወደ ሰገባው ክተተው። አባቴ የሰጠኝን ጽዋ ልጠጣ አልተዋትም።»[19] አለው። ኢሳይያስም «እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፤ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁ በሕማሙ አፉን አልከፈተም።»[20] ዳግመኛ «ደዌያችንን ተቀበለ፥ ሕመ ማችንንም ተሸክሞአል፤»[21] የሰላማችን ምልክት ነው።» አለ። ኤርምያስም፦ «ጻድቁን ኑ እን ሻረው ይላሉ። ሥጋውን በእንጨት እናጠፋ ዘንድ እርሱ ለእኛ ከባድና ዕፁብ ነውና።» ጳውሎስም እንዲህ ያለ ሕማማችንን መታመም የሚችል ሊቀ ካህናት ይገባናል [ያስፈልገናል]» አለ። ዳግመኛም እርሱን እንደ ፈተኑት የሚፈተኑትን መርዳት ችሏል። ስለ ሕማማቱ ብዙ ጥቅስ አለኝ። ነገር ግን ለሚሰሙት ማዘናጋት እንዳይሆን ከመናገር እቆጠባለሁ።

የአምላካችንን የሕማሙን ሰዓት እንናገር። በምሴተ ኀሙስ በያዙት ዕለት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በግዐ ፋሲካን በላ። ከእራት በኋላ በመጀመሪያው ሰዓተ ሌሊት የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ። በኹለተኛው ሰዓተ ሌሊት ሥጋውና ደሙን ሰጣቸው። በሦስተኛ ሰዓተ ሌሊት ለደቀ መዛሙርቱ የመንፈስ ቅዱስን መምጣት እየነገራቸውና እየመከራቸው ነገርን አስረዘመ። በዐራተኛው ሰዓተ ሌሊት ስለ ደቀ መዛሙርቱ እርሱ ከአባቱ ጋር አንድ እንደ ሆነ ከራሱ ጋር አንድ ያደርጋቸው ዘንድ ዐይኖቹን ወደ ሰማይ አንሥቶ ወደ አባቱ ልመናን አስረዘመ። በአምስተኛው ሰዓተ ሌሊት ከእነርሱ ርቆ ለብቻው ይጸልይ ጀመር። ወዙም በምድር ላይ እንደ ሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበር። ወደ ደቀ መዛሙርቱ በተመለሰ ጊዜ ተኝተውም አገኛቸው። ጴጥሮስንም «አንዲት ሰዓት ስንኳን ከእኔ ጋር ልትተጉ አልቻላችሁም? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉ፡ ጸልዩም።» አላቸው።

በስድስተኛው ሰዓተ ሌሊት ይሁዳ ከወታደሮችና ከጭፍሮች ጋር መጣ። ጌታ ኢየሱስን ያዙት፥ አስረውም ወሰዱት። በሰባተኛው ሰዓተ ሌሊት በሊቀ ካህናቱ ሐና ፊት አቆሙት። በዚያም ጴጥሮስ የበር ዘጊው ልጅ በጠየቀችው ጊዜ ካደ። በስምንተኛው ሰዓተ ሌሊት ሐና አስሮ ወደ ቀያፋ ላከው። በዘጠነኛው ሰዓተ ሌሊት ጴጥሮስ ለኹለተኛና

19. ዮሐ. ፲፰ ፥ ፲፩።
20. ኢሳ. ፶፫ ፥ ፯።
21. ኢሳ. ፶፫ ፥ ፬።



www.ethiopianorthodox.org

ለሦስተኛ ጊዜ ካደ:: ያን ጊዜም ዶሮ ጮኸ ጴጥሮስም ኢየሱስ፦ «ዶሮ ኹለት ጊዜ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ» ያለውን [አሰበ] ቃል ትዝ አለው፤ ነገሩንም አስቦ ወደ ውጭ ወጥቶ መራራ ልቅሶ አለቀሰ::

በዚያም እስከሚነጋ ድረስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፦ «በእጅ የሠራውን ቤተ መቅደስ አፈርሰዋለሁ:: በሦስት ቀን እጅ ያልሠራውን እሠራዋለሁ::»[22] ሲል ሰምተነዋል እያሉ የሐሰት ምስክሮችን እየቆጠሩበት፣ እየነቀፉትና እያሾሚጠጡት አደረ:: በነጋ ጊዜም ከጲላጦስ ዘንድ ወሰዱት፤ መስፍናቸው ፋሲካን ማድረግ የማይገባው ሮማዊ ነውና:: በግዓ ፋሲካን እስኪበሉ ድረስ እንዳይረክሱ ወደ ዐጸድ አልገቡም:: ስለዚህ ወደ ዐጸዱ ከመግባት ፈቀቅ አሉ:: ራሱ ጲላጦስ ወደ እነ እርሱ ወደ ውጭ ወጥቶ «የዚህ ሰው በደል ምንድን ነው?» አላቸው:: ሊቃነ ካህናቱ ግን «ክፉ አድራጊ ባይሆን ወደ አንተ አሳልፈን ባላመጣነው ነበር» አሉት:: ጲላጦስም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይጠይቀው ዘንድ ወደ ግቢው ገባ:: በእርሱ ላይ ያገኘው በደል አልነበረም:: ወደ ውጭ ከአይሁድ ዘንድ ወጥቶ «በከሰሳችሁት ሰው ላይ ያገኘሁት በደል የለም» አላቸው:: አይሁድም መለሰው፦ «እኛ ሕግ አለን፥ እንደ ሕጋችንም ሊሞት ይገባዋል፥ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎአልና» አሉት::[23]

እኛ ሕግ አለን፤ እንደ ሕጋችንም ሊሞት ይገባዋል፤ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጓልና» ስለምን ይላሉ? ይህን ቃል ለማለት ምክንያት አላቸው:: የጸናች አሪት «ከዳን ሕዝብ ወገን የሆነች ስሟ ሰሎሚት የምትባል እስራኤላዊት የዳቤር ልጅ የሴት ልጅ ወጣ ትላለች:: አባቱ ግን ግብጻዊ ነው:: ራሱን እግዚአብሔር ብሎ ጠራ፤ ሕዝቡ ይህን ሰው አምጥተው ከሙሴ ፊት አቆሙት፤ ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል ጠየቀ፤ በግቆዖ ውስጥ አቆዩት:: እንደ ሚያደርጉት የፈረዱት የለም:: እግዚአብሔርም ሙሴን ተናገረው፤ የረገመውን ከከተማ ወደ ውጭ አውጣው:: ሕዝቡም እጃቸውን ይጫኑበት፥ በድንጋይም ይደብድቡት፥ አለው:: በዚህም ምክንያት ጳውሎስ እስራኤልን «አሪታቸውን ሲከተሏት» መጽደቅ ተሳናቸው» አለ::[24]

ጲላጦስ ሊያስተዋቸው ባልቻለ /በተሳነው/ ጊዜ ገርፈው ይሰቅሉት

22. ማቴ. ፳፮፥፷፩::
23. ማቴ. ፳፯፥፳፫::
24. ሮሜ. ፲፥፫-፬::





ዘንድ አሳልፎ ሰጣቸው:: በሦስት ሰዓት ቀራንዮ ደርሰው በመስቀል ቸነከሩት፤ በግራና በቀኝ የኹለቱን ወንበዴዎች መስቀል፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል በመካከላቸው ተከሉ:: በስደስት ሰዓት በእንጨት መስቀል ላይ አወጡት:: እጆቹንና እግሮቹን በችንካሮች ቸነከሩት:: ፊቱን ሲመለከቱ፥ የመስቀሉ ፊት ወደ ሰሜን ነበር:: ነቢዩ ኤርያምስ እንደ ተናገው፦ «እግዚአብሔር ተናገረኝ፤ ኤርምያስ ምን ታያለህ አለኝ፤ የሎሚ ዘንግና የለውዝ በትር አልኩ:: እግዚአብሔርም መልካም ዐየህ አለኝ:: እኔ የተናገርኩትን አደርግ ዘንድ እተጋለሁና::[25] ለዓለም ሁሉ እንደ መብራት እንዲያበራ ከተተከለው ከወልድ ዕፀ መስቀል በስተቀር የሎሚ ዘንግ ምንድን ነው? አስቀድሞም በምስክሩ ድንኳን የሎሚ ዘንግ ለክህነት በትር በድንኳኑ አዳራሽ ውስጥ ባስቀመጡት ጊዜ ተመርጧልና:: የሚጣፍጥ አበባ አበበ:: የበሰለ የሎሚ ፍሬ አፈራ፤ በዕጣው ለአሮን ደረሰ:: ዳግመኛም ከለውዝ ዕንጨት የተገኘው በትር ምንድን ነው? የለውዝ ዕንጨት ግን በመስቀል ክንፍ ይመሰላል:: ጌታችን በወንጌል እንደ ተናገረው «ሙሴም በምድረ በዳ የነሐስ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል:: ወንጌላዊው ዮሐንስ ጌታችን ኢየሱ ስን ይዘው ወሰዱት፤ «መስቀሉን ተሸክሞ ቀራንዮ ወደ ተባለው ሥፍራ ወሰዱት::» አለ::[26] ሉቃስ ከሌሎች ወንጌላውያን ጋር «ስምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው [የአሌክስንድሮስና የሩፎስ አባትን] ከገጠር ሲመጣ የክርስቶስን መስቀል ይሸከም ዘንድ አስገደዱት:: ዮሐንስም ከጲላጦስ አደባባይ እስከ ቀራንዮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀሉን እንደ ተሸከመ ተናገረ:: ሦስቱ ወንጌላውያን፦ ከገረፉበት ቦታ እስከ ሰቀሉበት ቦታ ቀሬናዊው ስምዖን መስቀሉን እንደ ተሸከመ ይናገራሉ::[27]

ከእነሱ ማንን ታስዋሻላችሁ? ለመምህራን ውሸት እንደ ማይሆንላቸው ከደቀ መዛሙርቱ አፍ ሐሰት እንደ ሌለ አምናለሁ:: የመስቀል ግንዶች ኹለት ናቸውና:: ለጌታችን ኢየሱስ ሸክም በቁመቱ ልክ ወደ ምድር ውስጥ ተከሉት:: ለስምዖን ሸክም ግማሹን አማትበው [አመሳቅለው] አደረጉት:: እንዳይነዋወጥ ስሙ ሳዶር በተባለ የብረት ችንካር መስል ብረት ወይም ገመድ ካርባይደል ድንጋይ ቸነከሩት:: ሌላ አንደኛ ማለት

25. ኤር. ፩፥፲፩-፲፪::
26. ዮሐ. ፫፥፲፬፤ ዮሐ. ፲፱፥፲፯::
27. ማቴ. ፳፯፥፴2፤ ማር. ፲፭፥፳፩ ፳፫፥፳፮::



www.ethiopianorthodox.org

ነው። እንደገናም የጌታችን የኢየሱስ መሃል እጁን በመስቀሉ ክንፍ ሜዲፍ ላይ ስሙ አላዶር በተባለ የብረት ችንካሮች ቸነከሩት። ትርጓሜውም ኹለተኛ ማለት ነው። ዳግመኛም ኹለተኛ መሃል እጁን በኹለተኛው የመስቀል ክንፍ ዳር ላይ ስሙ ዳናት በተባለ የብረት ችንካር ቸነከሩት። ትርጓሜውም ሦስተኛ ማለት ነው። እንደገናም ኹለት እግሮቹን አንዱን ወደ አንዱ በማጠጋጋት በመስቀሉ ግንድ ላይ ስሙ አዴራ በተባለ የብረት ችንካሮች ቸነከሩት ትርጓሜውም ዐራት ማለት ነው። እግሮቹን በማጣበቅ እጆቹን በመዘርጋት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው በተዘረጋ ጊዜ ከዚህ በኋላ ጲላጦስ አንድ የብረት ችንካር አንሥቶ ከጌታችን ኢየሱስ ራስ በላይ በመስቀሉ ላይ ተከለ። በእንጨት ሰሌዳ ጽሕፈት ጻፈ፤ ጽሕፈቱም «የአይሁድ ንጉሣቸው የና ዝሬቱ ኢየሱስ» የሚል ነበር።[28] ጽሕፈቱ ግን በዕብራይስጥ፣ በሮማይስጥና በግሪክም ተጽፎ ነበር። ስሙ ራዶስ በተባለ የብረት ቀኖት ኢየሱስን ቸንክሮ በራሱ ላይ አኖረ። ትርጓሜ ውም አምስተኛ ማለት ነው።

«የለውዝ ዕንጨት፣ በትርና የሎሚ ዘንግ እመለከታለሁ» ወዳለው የኤርምያስን ትንቢት ትርጉም እንመለስ። የለውዝ ትርጉሙ የመስቀል ዘንግ ማቆም ነው። ዕፀ መስቀል ግን የሎሚ እንጨት ወይም የለውዝ እንጨት አይደለምና፤ የዘይት እንጨት ነው እንጂ። ነቢዩ ስለ መዓዛው ሎሚ፤ ስለ ጣዕሙ የለውዝ እንጨት አለው። ለሚያሸቱት መዓዛው ያማረ ለሚበሉት የሚጣፍጥ የመስቀሉ ፍሬ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እንዲሁም በአፈፈሩ ላምና በጠባዩ በግ ሳይሆን ስለ ሥጋው መታረድ ላም፤ ስለ የዋህነቱ በግ ተባለ። በሰውነቱ የሰው ልጅና በመለኮቱ እግዚአብሔር ነው እንጂ። እንደዚሁም በክዋኔው ዕፀ ዘይት ሲሆን የለውዝ እንጨትና የሎሚ እንጨት ትርጉሙ ወደ ዕፀ መስቀል ይመለሳል።

ዳግመኛ ኤርምያስ «እግዚአብሔር ተናገረኝ» አለ። ዳግመኛ «ምን ታያለህ?» አለኝ። ፊቱ ወደ ሰሜን የሆነ እንስራ ይነዳል አልሁ። እግዚአብሔርም ከሰሜን ፊት /አቅጣጫ/ በምድር በሚኖሩት ላይ ክፉት ትነጻለች።» አለኝ።[29] «ፊቱ ወደ ሰሜን የሆነ እንስራ ይነዳል» ያለው እርሱ ግን ወደ ሰሜን ግልጽ ሁኖ ሳለ በክርስቶስ ላይ የአይሁድ ትምክህት ነው። «እንስራ

28. ዮሐ. ፲፱፥፲፱።
29. ኤር. ፩፥፲፫፥፲፬።





ይነዳል» ማለት ሲያሸሚጥጡት መቆሚያቸውን ወደ ሰሜን ፊታቸው ወደ ደቡብ በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ፊት የተሰቀለውን ይነቅፉታል ማለት ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን፦ «ሰሜን ተነሥ ደቡብ ና» ትላለች። ሰቃልያንን ከመስቀሉ ፊት ስታርቃቸው ከግራ መንገድ ወደ ሰሜን ዝርዋን [የተበተኑ] ይሆኑ ዘንድ «ሰሜን ተነሥ» ትላለች። የሚታመኑበትን ከመስቀሉ በኋላ በመጠጋት ወደ መስቀሉ ይጠጉ ዘንድ ስትጠራቸው «ደቡብ ና» ትላለች።

የአምላክ ልጅ የሰቀላቱ ሰዓት ግን በዘጠኝ ሰዓት ነው። ፀሐይ በሰማይ መሐል [መካከል] በሚኖር ጊዜ፤ መታየቱ /ብርሃኑ/ በሚታጉል ጊዜ ወደ ሰው ተረክዞ ጥላ [ጨለማ] ይገባል። ከዘጠኝም ሰዓት ጀምሮ እንግዲህ ቀስ በቀስ የሚያድግ ጨለማ ሆነ። በዘጠኝ ሰዓት ፀሐይ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አዘቀዘቀ [ተዘቀዘቀ]። እንግዲህ የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ጥላ ለፈያታዊ ዘየማን ደረሰው። እርሱም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ነበር። ያን ጊዜ «አቤቱ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ» አለ።[30] ፈያታዊ ዘፀጋም ግን የመስቀሉ ጥላ አልደረሰውም፤ ስቅለታቸው ግን ጥላ ባልነበረበት ጊዜ በስድስት ሰዓት ሆኗልና። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት እንግዲህ ፀሐይ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ስታዘነብል ጥላውም ወደ ምሥራቅ የሚረዝም ሆነ። ስለዚህ ለፈያታዊ ዘየማን የእግዚአብሔር ምሕረት ታድለዋለችና የመስቀሉ ጥላ ደረሰው መድኃኒታችንን በ፫ /ሦስት/ ሰዓት በሰቀሉት ጊዜ ግን ፈያታዊ ዘፀጋም የመስቀል ጥላ በደረ ሰው ነበር። ጥላ ከፀሐይ ፊት ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ረዝሞ ይሸሻልና [ይፈጥናልና]፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ምሕረት አልታደለውም [አልደረሰውም]።

«አንተስ ክርስቶስ አይደለህምን? ራስህንም እኛንም አድን» ብሎ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ስድቡን ተናግሯልና። ፈያታዊ ዘየማን ግን መለሰ፦ «አንተ እንደዚህ ባለ ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔር አምላክህን ከቶ አትፈራውምን? ስለ አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለን። በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው። ይህ ግን ምንም ክፉት አላደረገም» ብሎ ገሠጸው። ወደ ጌታችን ኢየሱስ ተመለሰ፦ አቤቱ፣ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ አለው። ጌታችን ኢየሱስም፦ ፍጹም እመን፤ እውነት እልሃለሁ፤

30. ሉቃ. ፳፫፥፴፱–፵፪።



www.ethiopianorthodox.org

ባሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው::»[31] ለኃጢአተኛው ይህች መታመኑ ወደ መንግሥት ሰማያት ለመግባት ጠቀመችው:: እግዚአብሔር ከቀደሙ ብፁዓን ነቢያትና ከቀደምት አበው አስቀድሞ ፈያታይን በገነት ማደርን [መኖ ርን] ሳደለው ምሕረቱ፣ ባሕር ለሆነ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል:: በሃይማኖት ኃጢአተኛን ለሚያጸድቅ ለእርሱ ለዘላለም ምስጋና ይገባል:: አሜን::

ክርስቶስን «ሥጋው እንደ ሰው ልጅ በሥጋ ደካማ አይደለም» የሚል፣ እንደ ሙጫ ከርከሮ ጠማማ የሆነ፣ ያለ ዕውቀት የሚቸኩል የሚፈስ የጥፋት ውሃ፣ የተበተነ የምድጃ አመድ፣ የጠወለገ የውጥ ቅጠል፣ ሥር የሌለው የሐሰት ተክል፣ የከሐዲው የአውጣኪን ዘለፋ ተፈጸመ:: በሥላሴ ሃይማኖት የተሸለመ፣ በምግባሩ ግን ከወንድሞች የሚበድል [በደለኛ] የአባቶች ትምህርት ልጅ ጊዮርጊስ አለ [ተናገረ]:: በሥነ አምልኮ የምትሳ ተፋት በጸሎታችሁ አስቡት:: ለዘላለም አሜን::

31 ሉቃ ፳፫፥፴፱-፵፫::





[ምዕራፍ -፲፮]

# የስቅለት ዓርብ የሦስት ሰዓት ምንባብ

በቅድስና መንግሥቱ ንጹሕ የሆነ፣ በልዕልና ባሕርዩ ምጡቅ የሆነ፣ በልቡና የማይታወቅ፣ በኀሊና የማይገኝ፣ ያለ ጥፋት ለዘላለም ጸንቶ የሚ ኖር፣ የመለኮት ባሕሪዩ የተካከለ[1] በአኗኗር የሰለጠነ በሥሉስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ስም እንጀምራለን:: በሰማያት ፣በምድር፣ በባሕርና በቀለ ያት ለእርሱ ለዘላለም ምስጋና ይገባል አሜን::

የእግዚአብሔር ልጅ ታሞ ያለ ፈቃዱ ሞተ የሚሉ የዘንገዓን የህንድኪዩ ጳጳስ ሳዊሮስ እና የእስክንድርያ ታውዶስዮስን[2] ዘለፋ እንጀምራለን:: እንዴት የእግዚአብሔር ልጅ ታሞ ያለ ፈቃዱ ሞተ ያሉታል? እንደዚህ ያለውን ክፋት ምን ሲኦል አወጣችው? እንደዚህ ያለ ስንፍና ምን ገሐ ነም ተፋው::?

ሳዊሮስ እና ታውዶስዮስ ሃይማኖትን አክፋፍተው [አርክሰው] በኢ የሱስ ክርስቶስ ሕማማት ላይ የሰድብን ቃል ተናገሩ:: በአንደበታቸው ቃል ጽጽስናቸውን አርክሰው በረከሰ ትምህርታቸው ክሕነታቸውን አረ ከሱ:: ከወንጌል ቃል መድኃኒታችን ዓርብ ሌሊት ስለ ሕማሙ «አባቴ ቢቻልስ፣ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ» ያለውን ምክንያት አደረጉ:: ከዚህ ቃል በማ ስከተል «ነገር ግን ስለዚህ መጥቻለሁ ፈጽምኪትም» የሚለውን አሳስ ታወሱም»[3] በዚህም ይታመም ዘንድ ቢመጣም እነሆ! በፍጹም ፈቃዱ ታሞ ሞተ፣ «አባቴ ቢቻልስ ይህችን ጽዋ ከእኔ ትለፍ» ስላለው ዝንጉ ዎች ሆይ! ስሙ እንነግራችኋለን! እንግዲህ ሰይጣን፣ አይሁድ በእግዚአብሔር ልጅ ይከፉ ዘንድ ልቦናቻውን አወከ:: ነገር ግን ክርስቶስ የኢያኢሮስን ልጅ ከሞተች በኋላ «ጣቢታ ተነሺ» ብሎ እንዳሥነሣት ተአምራቶቹን ሲያስታውሱ በልቡናቸው ውስጥ ግን ትዝብት አለ:: ዳግመኛ በናይን አገር ወልደ መበለትን (የመበለቲቱን ልጅ) ወገቡን በዳሰሰ ጊዜ ከሞተ በኋላ በሕይወት አነሣው:: ዳግመኛ በሀገረ ቢታንያ «ከተቀበረ አራት

1. ወልድ በመለኮቱ ወይም በእምላክነቱ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ የማይነጣጠልና የማይበልጥ ነው:: ሊቁ ዕሩይ፣ /እኩል፣ ትክክል/ መሆኑን ለመግለጽ «መለኮት ዘውግ [ወገን]» አለው:: የመለኮት ወገን መሆን ከሥላሴ በስተቀር የሚችለው የለምና::
2. «ክርስቶስ ያለ ፈቃዱ ታሞ ሞተ» የሚሉ መናፍቃን
3. ማቴ. ፳፮፥፴፱



www.ethiopianorthodox.org

ቀን በሆነው ጊዜ አልዓዛር አልዓዛር ወደ ውጭና ብሎ ጠራው፤ የሞተውም እጆቹና እግሮቹ በመ ግነዝ እንደ ተገነዙ ወጣ። ፊቱም በጨርቅ እንደተጠመጠመ ነበር» እንደገና በአንካሶች እና በዓይነ ሥውራን ላይ ያደረገውን ተአምራት አስታወሱ። መሔድ በተሳናቸው በእጅ ልምሾዎች በተቀጠቀጡ፤ በወረሐዎች (እግረ ወንካሮች) እርኩሳን መናፍስት በሚያ ሰቃዩአቸው፤ በለምጻሞች፤ እና አካላቸው ባደፈባቸው ላይ።[4] እንግዲህ ሰይጣን ይህንን ከጌታ ተአምራት የተነሣ ፈርቶ ለክፋት ተግቶ አሰበ። ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር ልጅ በሽንገላ ቃል፤ «አባት ሆይ! ቢቻልስ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ ባለ ጊዜ አበረታው። ሰይጣንም ሊቃነ ካህናትን መደንገኒዓለምን ይይዙት ዘንድ ጭፍሮችን ከሰይፍና ጉመድ ጋር ይልኩ ዘንድ አበረታቻቸው።[5] በኀጥአን እጅ ተላልፎ ተሰጥቶ የርኩሳንን ምራቅ ተቀበለ። እንደክፉ አድራጊ መከራ እንዲቀበለ አደረጉት እንደ ሌባ አሰሩት።

በጠዋት ወደ ፍርድ አደባባይ ወስደው በጲላጦስ ፊት አቆሙት፤ ይሰቅለው ዘንድ አሳልፈው ሰጡት፤ ይገድለው ዘንድ ከሰሱት። ጲላጦስም «ንጉሣችሁን፤ ልስቀለውን? አላቸው።» የካህናት አለቆችም «ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም፤ ራሱን የሚያነግሥ ሁሉ ንጉሥን የሚተላለፍ (የሚበድል ነው)።» ብለው መለሱለት።[6] የዳዊትን ልጅ ከደው የሮምን መንግሥት አመስገኑላቸው። የይሁዳን ወገን መንግሥት አስተዳንገለው በአፋቸው ራሳቸውን ለአሕዛብ መንግሥት አስገዙ። በእስራኤል ቅዱስ ለይ እርኩስ ምራቃቸውን ተፉ። በአሮን ካህናትና የእስራኤል ነገሥታት የሚቀቡት የጵዮን ቀንድ ቅባት ቅድስናንም አስወገዱ። ሊቀ ካህናቱ ልብሱን ቀደደ። የአሮን ልጆች ክህነት ተወገደ /ጠፋ/። ሙሴ፤ አሮንና ልጆቹን ናዳብና አብዩድ በሞቱ ጊዜ ራሳቸሁን (ፀጉራችሁን) አትቁረጡ፤ ልብሳችሁንም አትቅደዱ፤ የእግዚአብሔር የቅብዓቱ ዘይት በላያችሁ ላይ አለና። ብሎ እንደነገራቸው በአራት ዘሌዋውያን ተጽፏልና።[7] «የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከታች ድረስ ተቀዶ የቤተ መቅደስ የአራት ክብሯ ተሻረ።»[8] «በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፤ የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ» ያለው የያዕቆብ ቃል በእነርሱ ላይ

4 ማር. ፩፥፴፩፤ ማር. ፪፥፲፯፤ ማር. ፩፥፳፫፤ ዮሐ. ፲፩፥፵፱::
5 ማር. ፲፬፥፵፫::
6 ማቴ. ፳፯፥፳፩-፳፬፤ ዮሐ. ፲፱፥፲፭::
7 ዘሌ. ፲፥፮-፯::
8 ማቴ. ፳፯፥፶፩::
9 ዘፍ. ፵፱፥፲::





ተፈጸመ። በአይሁድ እጅ ዕፀ መስቀል ተተክላ በኢየሱስ ክርስቶስ እጅ ቤተክርስቲያን ታንጻለች። የእግዚአብሔር በግ በዕፀ መስቀል ላይ በሰቃልያን እጅ ተሠውቶ ለምእመናን የበረከት ማዕድ ተሠራ [ተዘጋጀ] የመድኃኒታችን ጉኑ ተወግቶ የቤተ ክርስቲያን ቅጽር ደጆቿ በሙሽራዋ ደም ተቀባ።

የእግዚአብሔር ልጅ ያለ ፈቃዱ ታሞ ሞተ፤ ወደ ሚሉ የሳዊሮስና የታውዶስዮስ ዘለፋ እንግባ። እንደ ገና መድኃኒታችን «ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ» ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ ያለው ምክንያት አላቸው። ኀሊና ልምሾዎች ሆይ! በዚህስ አትሳቱ። ሰይጣንን እንደ ሸነገለው ተላልፎ በመስጠቱ አባት ሆይ! ይህች ሰዓት [ጽዋ] ከእኔ አሳልፋት የሚል ቃል አሰማው።[10] እንደዚሁ መልአከ ሞትንም መቅረብን እንዳይፈራ በሽንገላ ቃል አሰማው፤ አስቀድመን ያስታወስናችሁን የጌታን ተአምራት ይፈራ ዘንድ አስቧልና። ከዚህም በኋላ ጌታችን «አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውኸኝ ብሎ በታላቅ ቃል [ድምፅ] ጮኸ።» ከዚህም በኋላ የጥፋት መልአክ ሞትን ከመፍራት የተነሣ እንደሚጮኽ አስቦ ወደ ጉንደ መስቀሉ ቀርቦ አፉን ከፍቶ መሞጥ እንደለመደው ለዘላለም ሕያው ሆኖ የሚኖረውን ነፍሱን ይቀበለው ዘንድ [ይነጥቀው ዘንድ] ጨከነ። ሆዱ ስስታሙ የትስብእትን ምግብ በጉረሳት ጊዜ እንቆ የሚበላውን የመለኮት መረብ [ወጥመድ] አገኘ፤ ባኘከት ጊዜ ጥርሱን የሚሰብር ዐለት አገኘ በዋጣትም ጊዜ ሆዱን የሚቆርጥ ሰይፍ አገኘ፤ ሞት በመሸነፍ ባሕር ሰጠመ። ብሎ የተናገረው የኢሳይያስ ቃል ተፈጸመ። ሞት ሆይ! ድል መንሳትህ ወዴት አለ፤ ይህ ማስቀረትህስ ወዴት አለ?።[11]

እንግዲህ ልበ ደንዞዎች ሆይ! ስምታችሁ ዕወቁ። ሞትንና ሰይጣንን ስለ መሸንገል እነዚህን ቃላት ተናገረ። ሕማምንና ሞትን በመፍራት አይደለም። ያለፈቃዱ እንዳልታመመና ያለ ፈቃዱ እንዳልሞተ አስተውሉ። የእግዚአብሔርን ልጅ አምላክ መሆን ትከለክሉታላችሁ? አምልኮቱን [እሱን ማምለክን] ከልቦቻችሁ ታስታግሉ ዘንድ ትፈቅዳላችሁን? እሱ ግን አምላክ ከሆነ ይታመም ዘንድ ማን ያስገድደዋል? ይሞትስ ዘንድ ማን ያዘዋል? ስለ እኛና ስለ ሰው ልጅ ፍቅር ይታመምም ዘንድ ቸርነቱ አገበረችው [አስገደደችው]። ስለ ኃጢአታችንም የሞትን ጽዋ ይጠጣ ዘንድ ሳበችው።

10. ማቴ. ፳፮፥፴፱::
11. ኢሳ. ፳፭፥፰፤ ፩ኛ ቆሮ. ፲፭፥፶፭-፶፯::



www.ethiopianorthodox.org

«ለደቀ መዛሙርቱ የሰውን ልጅ ይይዙታል፥ ይገድሉትማል፥ በሦስተኛው ቀን ይነሣል» ያላቸውን የእግዚአብሔርን ልጅ፥ ያለፈቃዱ ሞተ እንዴት ትሉታላችሁ? ጴጥሮስም «ይህ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ አቤቱ ባንተ አይሁን ብሀ [አይደርስብህም]» አለው። እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን ወደ ኋላዬ ሒድ አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና» አለው።[12]

ልበ ሰነፎች ሆይ! ስለ እርሱ ሕማምና ሞትን ያልፈቀደውን ጴጥሮስን እንደ ተቆጣው [እንደ ገሠጸው] አትሰሙምን? ዳግመኛም «ጴጥሮስን ሰይፍህን ወደ ሰገባው መልስ አባቴ የሰጠኝን ጽዋ ሳልጠጣ አልተውም» ብሎታል።[13] ደግምኛ «ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር» የለም ብሎአቸዋል። ዳግመኛም አይሁድን፣ «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀን አነሣዋለሁ» ብሎአቸዋል። … እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር። እነሆ! ለአይሁድ ሥጋውን ለማፈረስ ሥልጣን እንዳለው ገለጠላቸው። በፈቃዱ ባይሞት ኑሮ ይገድሉት ዘንድ ተላላፎ ባልተሰጣቸው ባላሠለጠናቸው ነበር። ዳግመኛም፡ «ስለ ዚህ ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ እኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ እኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ፣ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁት» አለ።[14] እንግዲህ በራሱ ፈቃድ አስቃዩት፣ [ለሕማም ለመከራ ተላልፎ ተሰጠ] በራሱ ፈቃድ ገደሉት፣ በራሱ ፈቃድ በቅንዋተ መስቀል ቸነከሩት በራሱ ፈቃድ በሥጋ የሞትን ጽዋ፣ ተቀበለ በራሱ ፈቃድ ከሕሞት ጋር መራራ የተጨመረበትን አጠጡት።

በራሱ ፈቃድ ነፍሱን ከአባቱ ዘንድ አማፀነ። በራሱ ፈቃድ በወታደር [ሌንጊኖስ] ጦር ተወጋ። በራሱ ፈቃድ ከጐኑ ደምና ውሃ ፈሰሰ። በራሱ ፈቃድ በመቃብር ውስጥ ሦስት ሌሊትና ሦስት መዓልት ያለ መንቀሳቀስ አደረ [ኖረ]። በራሱ ፈቃድ ነፍሱን ወደ ሥጋው መልሶ በመለኮቱ ኀይል ተነሣ።

የክብር መብረቅ ከመቃብር ውስጥ አንፀባርቆ መቃብሩን ይጠብቁ የነበሩትን አስደነገጣቸው። በመካነ ጎልጎታ ስድስቱ ከዋክብት በየሥርዐታቸው ኹለት ኹለት ሆነው ተዘጋጅተው ታዩ። ሰባተኛው ግን በቅዱሳን ላይ ዘወትር የሚያበራ የጽድቅ ፀሐይ ነው።

12 ማቴ. ፲፮፥፳፪-፳፫::
13 ዮሐ. ፲፰፥፲፩፤ ዮሐ. ፪፥፲፱-፳፩::
14 ዮሐ. ፲፥፲፰::





ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ሥጋውን ንጹሕ በሆነች ከፈን ጠቅለሉት [ከፈኑት] ዳግመኛ ሚካኤልና ገብርኤል ነጫጭ ልብስ ለብሰው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ባረፈበት አንዱ በግርጌ አንዱ በራስጌው ሆነው ለሴቶች ታዩአቸው።[15] የመቃብሩ በር በቤተክርስቲያንን ተመሰለች። ዮሴፍና ኒቆዲሞስ አንድኛው በተልዕኮ አንደኛው በክህነት መስዋዕት ለማሳረግ በተዘጋጁ በኹለት አገልጋዮች አምሣል ተመሰሉ፤ ሚካኤልና ገብርኤል ለሥርዐተ ምስጢር አንዱ በጽዋዓ መድኃኒት አንደኛው ቁርባን መብራት በማብራት በሚሳጡ ዲያቆናት ተመሰሉ። ዳግመኛ ጴጥሮስና ዮሐንስ በፓትርያሪክና በመጤሮቢሊጥ[16] [በሊቀ ጳጳስ] ተመሰሉ። እነርሱም ጳጳስና ኢጲስ ቆጶሳት ናቸው። እነርሱም በቤተ ክርስቲያን ሹመት ላይ የሠለጡኑ ናቸው። እንደገናም ማርያም መግደላዊት በዲያቆናዊት ተመሰለች። ከእርሷ ጋር የነበሩ ሴቶች በምእመናን ተመሰሉ። የምስጢሩ ጽዋ እና የቁርባኑ ኅብስት ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በተግባር እንጂ በምሣሌ አይደለም። ሥጋው የተከፈነበት የመግነዝ ጨርቅ [ከፈን] በቁርባን ሥርዐት ኅብስቱ በሚጠቀለል ልበት ማንደር (መሸፈኛ) ይመሰላል። ለብቻዋ ተጠቅልላ የተገኘችው የመከፈኛ ሰበን የመለኮት ደም ጽዋ በሚከደንበት ሰበን (መሸፈኛ) ይመሰላል። ዕፀ መስቀሉም የቤተ ክርስቲያንን ብርሃን በሚሸከም የብርሃን መቅረዝ ተመሰለ (ይመስላል)። ቀራንዮስ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ተቀደሰች። ጎለጎታ ነውር በሌለባት ንጽሕት በሆነች ነፍስ በተለየት ሥጋው ተቀደሰች። በቀራንዮ የሕማሙ ድንኳን ተተክሎ ጎልጎታ የማረፊያው ቦታ ሆነች። ቀራንዮ የሙሽራው ዐጸድ ጎለጎታም ደጃፍ ሆነች። ቤተ ክርስቲያን ስለ ቀራንዮ ማለት ወንድሜ ልጅ ሆይ! በቀትር ጊዜ የት ትተኛለህ ወደ የትስ ታያለህ ትላለች።[17] ስለ ጎለጎታም እነሆ! የሰሎሞን አልጋ ኀያላን ስድሳ ኀያላን በዙሪያው ናቸው ይላል።[18]

ዳዊት ስለ ቀራንዮ ምስጢር፣ «እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ፥ አጥንቶቼን ሁሉ ቆጠሩ፤ ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።»[19] አለ። ስለ ጎለጎታም፣ «እኔ ተኛሁ አንቀላፋሁም እግዚአብሔርም ደግፎኛል ነቃሁ»[20] አለ።

15. ዮሐ. ፲፱፥፴፰-፵፩፤ ዮሐ. ፳፥፲፪::
16. መጤሮቢሊጥ Metro politan በግሪክኛ የአንድ አገረ ስብከት ጳጳስ ማለት ነው። ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ ይመጡ የነበሩ ጳጳሳት መጤሮቢሊጥ ይባሉ ነበር።
17. መኃል. ፩፥፯::
18. መኃል. ፫፥፯::
19. መዝ. ፳፩፥፲፮-፲፰::
20. መዝ. ፫፥፭::

www.ethiopianorthodox.org

ከዛሬ ጀምሮ ግን በፈቃዱ ታሞ ለሞተ በፈቃዱ በመለኮቱ ኀይል ለተነሣ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል። እንዲህ እናምናለን እንደዚህም እንታመናለን። እንግዲህ ከእግዚአብሔር ወንጌል መንገድ እግራቸውን ያሸሹ ለአርዮ መንጋና ለውሾች ማኅበር መምህራን የሆኑ እና ዝንጉዎን የሆኑ የሀን ድኩይ ጳጳስ ሳዊሮስንና የእስክንድርያ ታውዶስዮስን ዘለፋ ፈጸምን።

ስለ እነርሱ ቤተ ክርስቲያን «ወይናችን አብቧልና የወይናችንን ቦታ የሚጠፉትን ቀበሮች ጥቃቅኑን ቀበሮች አጥምዳችሁ ያዙልን» ትላለች።[21] እነርሱም ወደ ገሃነም እሳት የሚያስገቡ የሲኦል በሮች ናቸው። እነርሱም ውሃቸውን በሬት ደም የጨመሩ [የደባለቁ] የሐሰት ምንጮች ናቸው። እነርሱም በአፋቸው ውስጥ የእግዚአብሔር የሥርዐቱና የሕጉ ፈሳሽ የማይገኝባቸው ደረቆች ወንዞች ናቸው። እነርሱም የልቡን መርከብ በመጻሕፍት ባሕር መዋኘት የማይችለውን፤ በነቢያትና በኦሪት መቅዘፊያ፤ በሐዋርያትና በወንጌል መቅዘፊያ የማይቀዝፈውን የሚያሰጥሙ ጽኑዓን ሞገዶችና ጸሊማን የጥፋት ባሕሮች ናቸው። እነዚህ ልል ብትሮችና የተቀጠቀጡ መቃዎች ናቸው። በላያቸው ላይ የተደገፈውን በእጁ ውስጥ ስንጣሬ ይገባበታል። ከፍሊጋቸው [ከጎዳናቸው] አርቆን በወንጌል ሃይማኖት ላጸናን ለእግዚአብሔር ለዘላለም ምስጋና ይገባል አሜን።

በማርያም ልጅ ሕማማት [መከራ] ላይ የስድብን ቃል የተናገሩ የሀን ድኩይ ጳጳስ የሳዊሮስና የእስክንድርያ ታውዶስዮስን የዘለፋቸው መጽሐፍ ተፈጸመ። የሃይማኖት ነገር ለሚያከፋፋት የመከራ አክሊሊ ነች። ለሚያሳምራት (ለሚያከብራት) የዕንቍ አክሊል ናት፡ ለሚገዛት ዕንቍ ናት፤ ለሚያስባት የጥበብ መብራት ናት። የኢትዮጵያ ምስኪን እኔ ጊዮርጊስ አሳለሁ። በክርስቶስ ያላችሁ በጸሎታችሁ አስቡኝ ለዘላለም አሜን።

21. መኃል ፪፥፲፭::



www.ethiopianorthodox.org



## [ምራፍ ፲፯]

# የስቅለት ዓርብ የስድስት ሰዓት ምንባብ

በኀይሉ ጽኑዕ ሆኖ የማይደክም፥ ሥጋችንንና ነፍሳችን በመጠበቅ የማይተኛ፥ በአንድ ባሕርይ ሦስትነቱ ፍጹም የሆነ፥ ያለ ወሰን ምሕረቱ ባሕር የሆነ፥ ያለ ክረምቶች ረጅም ዘመናትን የኖረ፥ ያለ ዘመን በዘመናት የኖረ፥ ያለ ነገ ኋለኛ የሆነና ያለ ዛሬ መካከለኛ የሆነ፥ ያለ ትላትን ቀዳማዊ በሆነ በእግዚአብሔር ስም እንጀምራለን። ለእርሱ ለዘላለም ምስጋና ይሁን። አሜን።

ሃይማኖቱ የጠፋና ደረቱ የጠበበ የክሕደት መምህርና ኀሊናው የተከፈለ ይኸውም አቡርዮስ ሲሆን የእርሱን ዘለፋ እናፋጥናለን። አቡርዮስ ሆይ! የኃጢአት ያር በአንተ ላይ ከብዶ [አይሎ] የበደል ማዕበል አሥጠመህ። መነሣት ወደ ሌለበት ጉድጓድ [ገደል] ውስጥ ወደቅኸ። የተራሮችና የኮረብቶች መሠረቶች በአንተ ላይ ተናዱ።

ሃይማኖቱ ከሙተላለፍ በቀር ገደል ምንድን ነው? ለመውረድ [ለመውደቅ] ራሱ ተወርውሮ ወደ ገደል እግሮቹን ያዳጠው ሰው ወደ ህልውናው መመለስ አይችልምና ሃይማኖቱን የተላለፈ ወደ ቀናበት አይመለስም፡ ሰይጣን ልቡን ያጸናዋልና፤ ሃይማኖትን ለማጠራጠር የሚተካከለው ሌላ በደልን የሚያገኝለት የለምና። ጌታችን በወንጌል እንደ ተናገረው፦ «በሰው ልጅ ላይ የስድብን ቃል የሚናገር ይሰረይለታል። በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የስድብን ቃል የሚናገር በዚህም ዓለም በሚመጣውም ዓለም አይሠረይለትም።»[1] በአንተ ላይ ተራሮችና ኮረብቶች ተናዱ። ስንልም የነቢያትንና የሐዋርያትን የትምህርታቸውን መሠረት አፈረስክ፥ በአንተ ላይም የመርገማቸው ቃል ተናደ።[2] ሙሴ፦ «በዚህ የሕግ መጽሐፍ የተጻፈውን ተግባር [ሥራ] የማይፈጽም የተረገመ ይሁን» እንዳለ።[3] ጳውሎስ ደግሞ «የሕገ ኦሪት ፍጻሜው በክርስቶስ ማመን ነው» ብሎ ተረጐመ።[4]

አቡርዮስ ሆይ! አንተ ግን ራስህን ወደ ረግረግ ጭቃ ውስጥ ጨመርኸ

1. ማቴ. ፲፪፥፴፩::
2. ኦሪትን መፈጸሟን የዘመን ሥቃይ ማብቃቱን ጌታ ይወርዳል ይወለዳል የተባለው ትንቢት መፈጸሙን ኦሪት በወንጌል መተካቷን እና የመከራው ትንቢት፤ መርገም በእርሱ እንደተሻረ ያመለክታል።
3. ዘዳ. ፳፯፥፳፮::
4. ሮሜ. ፲፥፬፤ ገላ. ፫፥፳፫-፳፬::

ነፍስህንም ለገሃነም ጠባቂዎች ሰጠህ:: እንዴት የእግዚአብሔርን ልጅ፥ «ነፍስና ልብ የለውም:: መለኮቱ እንደ ነፍስና ልብ ሆነው» ትላለህ? እኔ ግን እልሃለሁ ጠባአይዊ ልብና ሰብአዊ ነፍስ የለህም:: የሰይጣንም የአፉ እስትንፋስ እንደ ነፍስና ልብ ሆነህ::[5] በመጀመሪያው ክሕደትህ መለኮትን ከፍለህ ሥላሴን ሦስትነትን በተንክ:: የእግዚአብሔር ካህናት [አገልጋዮች] ሙሴና አሮን እንደ ቡሩክት የምድጃ አመድ ተበተንክ! በግብጽ ሰዎችም ላይ የሚፈላ ቁስል እንደ ሆነ እንዲሁ ትምህርትህ በክፋት ሃይማኖትህ ለሚያምኑ ይሁንባቸው:: ዳግመኛም «የክርስቶስ ትስብእት [ሰውነት] ልብና ነፍስ የለውም» እያልክ ሃይማኖትን ማክፋት ጨመርክ::

እግዚአብሔር በሥቃይህ ላይ ሥቃይን ይጨምርብህ:: ዳዊት፡- «በቁስሌ ላይ ቁስልን ጨመሩብኝ:: በበደላቸው ላይ በደልን ጨምርባቸው:: ከጻድቃን ጋር አይጻፉ:: ከሕያዋን መጽሐፍ ይደምሰሱ፥ በጽድቅህም አይግቡ» እንዳለ::[6] ነቢዩ ስለ ስቃዩቱ ይህን አለ:: ጲላጦስ ገርፎት ይሰቅሉት ዘንድ አሳልፎ ሰጥቶአቸዋልና እነርሱም በእንጨት መስቀል ላይ ሰቀሉት:: ዳዊት ስለ እግዚአብሔር ልጅ እንደ ራሱ [አድርጎ] ይናገራል፡ ከእርሱ ዘር ሰው ሆኗልና::

አቡርዮስ ሆይ! አንተም በመጀመሪያ በጥርጥርህ «አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ለየራሳቸው ናቸው::» ብለህ ከአባቱ የተለየ አልክው:: ዛሬም «ለክርስቶስ ትስብእት [ሰውነት] ነፍስና ልብ የለውም፥ መለኮቱም እንደ ነፍስና ልብ ሆነው» ትላለህ:: «ራሱ ነፍሴን በፈቃዴ እሰጣለሁ::» እያለ እንደዚህ ነፍስ የለውም እንዴት ይባላል?[7] ዳግመኛም «ነፍሱን ስለ በጎቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም» አለ::[8] ዳግመኛም ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ ተከዘች:: አባት ሆይ! ቢቻልህ እቺን ጽዋ ከኔ አሳልፋት አለ:: እንደገናም «ነፍሴን በእጅህ እሰጣለሁ» አለ:: እንደገና ወንጌላዊው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆምጣጤውን ጠጥቶ «ሁሉ ተፈጸመ» አለ:: «ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ» አለ::[9] ነፍስ ባይኖረው ግን አሟሟቱ እንዴት በሆነ! ከሥጋ ነፍስ ሳትለይ ሞት የለምና::

5. መናፍቁ ከንዐዘ ሰብእ ወቀቶ በስይጣን መንፈስ መምላቱን እና ክሕደቱ የበዛ መሆኑን ያመለክታል::
6. መዝ. ፻፳፰፥፫-፬::
7. ዮሐ. ፲፥፲፯::
8. ዮሐ. ፲፥፲፰::
9. ዮሐ. ፲፱፥፴::





ስለ ሰው ልጅ የትስብእቱ [የሰውነቱ] ጉዳና እንናገር:: የሰው ልጅ ኹለት ነፍስ አለች አንድ የማይሞት፡ ይህ የሚሞተው:: በመታረድና በመወጋት በምድር ላይ የሚፈስ ደም ነው:: በደዌ ሥጋ ቢያልፍም በእርሱ ማለፍም ነፍስ ከሥጋ ይለያል:: ያንኛው ግን ለዘላለም የማይሞት የሕይወት ነፍስ ነው:: ስለ እሳት ጠባይ ከንፈሮችን በመክፈት ያልባል /ያወዛል/:: ስለ ነፋስ ጠባይ ከንፈሮችን በማጥበብ ይቀዘቅዛል:: አወጣጣቸው ግን ከአንድ ሥጋ ማደሪያ ነው:: የጸናች ኦሪት ስለ ደመ ነፍስም «ከደም ጋር አትብሉ፡ ደመ ነፍሳችሁ ነውና» ትላለች:: ዳግመኛ ዘሌዋውያን መጽሐፍ «ለሰው ልጅ ደሙ ነፍሱ ነውና» ትላለች::[10] ስለዚህ መጽሐፍ «ነፍስን አትግደል» አለ::[11] እነሆ፡- ደመ ነፍስ እንደምትሞት ያሳውቃል::

ጌታችን በወንጌል ስለ ሕያዊት ነፍስ «ሥጋችሁን የሚገድሉትን አትፍሯቸው፡ ነፍሳችሁን[12] መግደል አይቻላቸውምና» አለ::[13] በዚህም ነፍስ እንደማትሞት ዐሳወቀ:: የነፍስ፣ የሥጋና የደም ጠባይም እንደ መብራት፣ ዘይትና ፈትል ጠባይ ነው:: ደመ ነፍስም በቀባት ዘይት፣ የሕይወት ነፍስ በመብራት ትመሰላለች:: ከቀንዲል ውስጥ የቀባት ዘይት ቢያልቅ በፈትሉ ውስጥ የመብራት ብርሃን አይኖርም:: እንዲሁም ከሰው አካልና ከሴት አካል ደመ ነፍስ ካለቀ በሥጋ ውስጥ የነፍስ ሕይወት አይኖርም:: ለጌታችንም ግን የሰው ልጅ ጠባይ አለው:: የሚዳሰስ ሥጋና የማትዳሰስ ነፍስ፣ የምትፈስ ደም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ሰው የሚያስብ ልብ አለው:: ሳንታክትም ልብ እንዳለው እንናገር፡ ራሱ «ነፍሴ እስከ ሞት ድርሳ አዘነች» ይላልና::[14] ያለ ልብ የሚተከዝ አለን? መለኮቱ ግን እንደ ነፍስና ልብ ሁኖት ቢሆን ስለ ሕማምና ሞት መተከዝ ባልሆነው [ባላስፈለገው ነበር:: ራሱ፡- «ነፍስ ይወዳል ሥጋ ይደክማልና» እንዳለ::[15] ስለ መለኮቱ «መንፈስ [ነፍስ] ይወዳል» አለ::[16] ስለ ትስብእቱ [ሰውነቱ] «ሥጋ ይደክማል» አለ:: ለሥጋ ሕማማት [በሥጋ ለመታመም] መለኮቱ ቢጨነቅ ግን እንግዲህ እንደ ልብ ስለ ሕማም በተከዘበት ቦታ እንዴት እንደ ልብ ይሆነዋል?

10. ዘሌ. ፲፯፥፲፬::
11. ዘጸ. ፳፥፲፫ ::
12. የሰው የእንስሳ ደም ከዕፀዋት ደም የተለየ ነው:: ኪዳነ ወልድ ክፍሌ. ገጽ ፫፻፶::
13. ማቴ. ፲፥፳፰::
14. ማቴ. ፳፮፥፴፰::
15. ነፍስ ሰውን ለማዳን ጽዋን ለመቀበል ትፈትዳለች፤ ሥጋ ግን ይደክማል፡ ሲል ትስብእትን መናገሩ ነው:: ነፍስን በመለኮቱ መስሏታልና::
16. ማቴ. ፳፮፥፵፩::



www.ethiopianorthodox.org

ዳግመኛም፦ «አባት ሆይ! ቢቻልስ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ ነገር ግን የአንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የኔ ፈቃድ አይደለም።» አለ።[17] ስለ መለኮቱ «መንፈስ [ነፍስ] ይወዳልና» አለ። ስለ አባቱ «የአንተ ፈቃድ ይሁን» አለ፤ የወልድና የአብ ህልውና፣ መለኮት፣ ፈቃድ አንድ ነውና። ስለ ድኅነተ ዓለም ስለሥጋ ሕማማት [በሥጋ ለመታመም] ይጨነቃልና የሰው ልጅ ልብ የትስብእት [የሰውነት] ጉዳና «ነፍሴ እስከ ሞት ደርሳ አዘነች» አለ። በዳዊት አፍም «ልቤ በሆዴ መካከል እንደሚቀልጥ ሰም ሆነ» አለ።[18] ይህን ስለ ክርስቶስ መለኮት ትስብእት [ሰውነት] አለ [ተናገረ]። ይህን የመዝሙር ቃል ዳዊት ስለ ራሱ የተናገረ ቢሆን [ያስዋሽታል] ጥቂት አልፎ [አልፍ ብሎ] «እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ፤ አጥንቶቼንም ሁሉ ተቆጠሩ፤ ልብሶቼን ለያንዳንዳቸው ተከፋፈሉ፤ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።» ባለ ጊዜ ያስዋሽታል።[19] የዳዊትን እጆችና እግሮች ማን ቸነከረ? ማንስ ልብሶቹን ተከፋፈሉ በቀሚሱ ላይ ዕጣ ተጣጣለ? ነገር ግን ወልድ በእርሱ አፍ ተናገረ፤ ከእርሱ ዘር ሰው ይሆን ዘንድ አለውና።

ዳግመኛ አብ በኢሳይያስ አፍ፦ «ግርማዬ ያስተውላል ክብሮም ከፍ ይላል። ስለ እርሱ አሕዛብ ይደነቃሉ» አለ።[20] እነሆ! የአምላክ ልጅ ህልውና ጠባይ የትስብእት ጉዳና ፍጹም ነው። እንደ አይሁድ ሕግ ወደ መከር በጎላቸው ወጣ። እንደ ተዘጋጀም ፋሲካን በላ። መንገድ በመሄድ ደክሞ ሲከር ወደምትባል የወይን ዐጸድ በሰማርያ ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ።[21] ተጠምቶ ሳምራዊትን ውሃ ታጠጣው ዘንድ ለመናት። በመንፈሱ ተደስቶ፦ የሰማያትና የምድር ጌታ «አባት ሆይ፤ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥኸው አመሰግንሃለሁ። አዎን አባት ሆይ! ፈቃድህ በፊትህ እንዲህ ሆኖአልና» አለ።[22]

«በመጾም በተራበ ጊዜ ፈታኝም ቀርቦ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው። እርሱም መልሶ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል።» አለው።[23] እንደገና ተርቦ በወስጧ ፍሬ ቢያገኝ ያይ ዘንድ ወደ ዕፀ በለስ ሒዶ በውስጧ

17. ማቴ. ፳፮፥፴፱::
18. መዝ. ፳፩፥፲፬::
19. መዝ. ፳፩፥፲፯-፲፰::
20. ኢሳ. ፵፱፥፭::
21. ዮሐ. ፬፥፮::
22. ሉቃ. ፲፥፳፩::
23. ማቴ. ፬፥፬::



www.ethiopianorthodox.org



ፍሬ ባላገኘባት ጊዜ ረግሟት ደረቀች።[24] ስለ ሕማሙ አዝኖ «ነፍሴ እስከ ሞት ደርሳ አዘነች» አለ። ዳግመኛ ስለ አልዓዛር አለቀሰ። እንደ ገናም «ጌታችን ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲቀርብ ከተማይቱን አይቶ በእርሷ ላይ አለቀሰ።» ተብሎ በወንጌል እንደ ተነገረ።[25] እነሆ! የትስብእት ጉዳና ፍጹም ነው፤ መራብ፣ መጠማት፣ መድከምና መቀጥቀጥ የሥጋ ክፍል [ድርሻ] ነውና መተከዝ፣ መታወክና መዋለል የነፍስ ክፍል ነውና። ለቅሶ፣ ኀዘንና ደስታ የልብ ክፍል ነው። ሕማም ግን የማኅበራቸው የአንድነታቸው ክፍል ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋው ታመመ፤ በመንፈስ [በነፍስም] ታመመ። ስለ ሥጋው ሕመም ሰሎሞን ጻድቁን እንሻረው [እናስናብተው]፤ እርሱ ለእኛ አስደናቂና ከባድ ነውና። «ሥጋውን በእንጨት እናጥፋ» አለ። በሌላ በኩልም «በእንጀራው ውስጥ እንጨት እንጨምር» ይላል።[26] የክርስቶስ እንጀራው ያለ ሥጋውና ደሙ ምንድን ነው? «ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል» ብሎ በወንጌል እንደ ተናገረ ዳግመኛም «እንካችሁ፤ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው» አለ።

«ስለ እናንተ ለብዙዎች ቢዛ ይሰጣል» አለ።[27] ዳግመኛም እንጨት ምንድን ነው? በላዩ ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው የተቸነከረበት ዕፀ መስቀል እንጂ። ጴጥሮስም፦ «ክርስቶስ ግን በሥጋው ቢሰቀል እናንተም በዚህ ኀሊና ተከላከሉ፤ በሥጋው የታመመ ከኃጢአት ድኖአልና።»[28] ጳውሎስም «በዐዋጅ የተነገሩትን የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳ በሥጋ አፈረሰ ይህም ከሁለታቸው አንድ አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ፤ ጥልንም በመስቀሉ ገደለበት»[29] ስለ ሕማመ ነፍሱም ኢሳይያስ የሚያሳምማትን ነፍሱን አመሰገኗት አለ። ዳግመኛም ዳዊት «በሆዴ መካከል ልቤ እንደሚቀልጥ ሰም ሆነ ኀይሌም እንደ ገል ደረቀ» አለ።[30] እነሆ! የነቢያት ቃል በሕማማቱ ውስጥ ተሰብስቧል። ሥጋም ከነፍስ ጋር ሳለች ትታመማለች፤ ከእርሷ ከወጣች በኋላ ግን ያለ መተንፈስ ትተኛለች

24. ማቴ. ፳፩፥፲፰-፲፱::
25. ማቴ. ፳፮፥፴፰፤ ዮሐ.፲፩፥፴፭ ሉቃ. ፲፱፥፵፩::
26. ጥበብ. ፪፥፲፪-፲፭::
27. ዮሐ. ፮፥፶፩፤ ማቴ.፳፮፥፳፮::
28. ፩ኛ ጴጥ. ፬፥፩::
29. ኤፌ. ፪፥፲፮::
30. መዝ. ፳፩፥፲፬::

እንጂ አትታመም። ነፍስ ግን ከሥጋ ጋር ከወጣች በኋላም ያለ ሥጋዋ ትታመማለች፤ የማትሞት ናትና። ነቢዩ ዕዝራ የሞትን ነገር ከልዑል ዘንድ አገሌ ይሙት ነፍሱ [መንፈሱ ከእርሱ ላይ ከሥጋው ትውጣ የሚል የትእዛዝ ቃል ከወጣ ወደ ሰጠው ትገባ ዘንድ ለልዑል የምስጋና]። ስግደትን ታስተድማለች አለ።[31] መፈራቱን የሚያስቡ፣ የልዑልን ሕግን አቃል ለው የልዑልን መንገድ ከማይጠብቁ ከከሐድያን ግን እነርሱ ቤት ይዞሯ ታል እንጂ አይገቡም። ከዚህ በኋላ ተቀሥፈው ይሞኻሉ፤ ያዝናሉ። ሰባት መንገድን ያሳዩአቸዋል።

እንድ ሥጋ የሌላቸው መላእክትም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ቢተላለፉ ይታመማሉ። ሐዋርያው፦ «መላእክትም በድለው ሥቃይ ጻዕር ባለበት ቦታ ታስረው ለታላቋ ዕለት አኖራቸው እንጂ አልራራላቸውም» እንዳለ።[32] በሲኖዶስ ሕግም «ዘወትር ፊትህን ታማትብ ዘንድ ተጨነቅ፤ በሰይጣን ላይ የትጣት ምልክት ነውና።» አለ። ወንድሞች ሆይ፥ ሰይጣንም በጠባዩ እንደ መልአክ ነው። በራሱ ትዕቢት ሰይጣን ተባለ። ሰይጣን ማለት ተቃራኒ ማለት ነውና።

በመጽሐፈ ነገሥት ውስጥ «እግዚአብሔር ከኤዶምያስ ነገሥታት ዘር የኢዶምያስን ሰው ሃዳድን ከረሚማቴር ወገን የሆነውን የኢያዶሄ ልጅ ኢሲርማንና የሳባ ንጉሥ ጌታው አድርማዘርን ጠላት አድርጐ በሰሎሞን ላይ አስነሣው። ሰዎችን ሰብስቦ የጭፍራ አለቃ ሆነ፤ ወደ ደማስቆም ሔደ። በሰሎሞን ዘመን ሁሉ የእስራኤል ጠላት ነበር።» ተብሎ እንደተጻፈ።[33] በዚህ ቃል ሰይጣን ማለት ትርጉሙ ተቃራኒ እንደ ሆነ ታወቀ። መላእክትም ሕግን ካልጠበቁ /ካልያዙበቁ/ ቅጣት እንዳለባቸው እመኑ፤ ሥርዐታቸውን ከጠበቁ ግን ቅጣት የለባቸውም። በሚያስቀጣቸው ገንዘብ የሚያስቀጣቸውን አሳደረጉ ምና።

ስለ መድኀን የትስብእቱ [ሰውነቱ] ጠባይ ግን ከብቻዋ ኃጢአት ማድረግ በስተቀር ከሰው ልጅ እንደማይጕድል እነሆ! ተናገርን። ገቢረ ተአምራትን ብቻ ከማድረግ በስተቀር እርሱ አይበልጥም። ከሞተ በኋላ በወጉት ጊዜ ከጐኑ ደምና ውሃ ስለ መፍሰሱ [በመፍሰሱ] ግን የመለኮት ምልክት ነው፤ ከዚህ አስቀድሞም ሆነ ከዚህ በኋላ ከበድን ሥጋ የደም መውጣት

31. ዕዝ. ፩-፲ ይመልከቱ።
32. ይሁዳ. ፩፥፯።
33. ፩ኛ ነገ. ፲፩፥፲፬።





[መፍሰስ] ያልተለመደ ነውና። የደም መውጣት [መፍሰስ] ግን ከሕያው ሥጋም ከሙታን ሥጋም አይሆንም የጥምቀትን አርአያ ሲያመለክት እንጂ። ደም ግን ለምስጢር ሥርዐት፥ ውሃም ለጥምቀት መጠመቂያ ኹለቱም ከሥጋው ቤት ፈሰሱ። ስለዚህ ለምስጢር ሥርዐት ወይንና ውሃን ጨመረ።

ወልድን «ነፍስና ልብ የለውም። መለኮቱ እንደ ነፍስና ልብ ሆነው» የምትል አቡርዮስ ሆይ! ታፍራለህ [እፈር]። እኛ ግን ሰብአዊ ልብን፣ የምትፈስ ደምን፣ የሥጋ ማሰሪያ ጅማቶችንና ሥሮችን፣ የሥጋን ቤት የሚያስር አጥንትን በቅንድብና በጭንቅላት ላይ የበቀለ ፀጉርን በእጆችና በእግሮች ጣቶች የበቀሉ ጥፍሮችን፣ ጠባያዊ ነፍስን ይዞ ምድራዊ ሥጋን እንደተዋሐደ እናምናለን። መንክራትን [ተአምራትን] በማድረግ ግን እግዚአብሔርነቱ እንዳለ እናምናለን። ጳውሎስ «በሥጋ ከዳዊት ዘር መጥቶ በኀይሉና በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ዐሳየ።» እንዳለ።[34]

አቡርዮስ ሆይ! ከወንጌል ቃል፦ «የም ቃል ሥጋ ሆነ» የሚለውን" እንዴት ምክንያት አደረግኸ? በስሕተት ቃልህ «ወንጌላዊው ቃል ሥጋ ሆነ አለ፤ ሰው ሆነ አላለም።»[35] ትላለህ። ስለ ነፍሱ ህላዌ፣ ስለ ሥጋውና ስለ ሰብአዊ ልቡናው፥ ስለ መለኮቱ እግዚአብሔራዊነት ምስክር ባቀረብን ጊዜ እነሆ! የስሕተትህ ቃል ተሻረ [ፈረሰ]። ዛሬም ዘለፋህን አድርሰን። በቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዲህ እንላለን፦ «ከዓለም አስቀድሞ በነበረና ዓለምን አሳልፎ በሚኖር በአንድ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን። እንደ አባቱ ጥንተ አኗኗሩ በማይገኝ በኋለኛው ዘመን ከቅድስት ድንግል ማርያም ፍጹም ሥጋን በነሣ [በተዋሐደ] በአንዱ እግዚአብሔር ወልድ እናምናለን። ከአብና ከወልድ ጋር በመለኮቱ እኩል /ትክክል/ በሚሆን በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እናምናለን። ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሠሯት በአንዲት ክብርት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን። ዳግም ልደት በሚገኝባት በጥምቀት እናምናለን። የሙታንን መነሣት እየተመኘን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት በክርስቲያን ክብር መቆምን ተስፋ እናደርጋለን። ለዘላለሙ አሜን።»

ክርስቶስን እንደ ሰው «ነፍስና ልብ የለውም» የሚል፥ ከጠባይ ጉድለትን

34. ሮሜ. ፩፥፬።
35. ዮሐ. ፩፥፩-፲፬።



www.ethiopianorthodox.org

አስተምሮ የሃይማኖቱ ጠባይ ግን በእግዚአብሔር ዘንድና በሰው ዘንድ የተጠላ ዝንጉ የሆነ የአቡርዮስ ኹለተኛ ዘለፋ ተፈጸመ:: በአምላኩ በመታመን የጸና፥ በሃይማኖቱ ቀጥተኛ የሆነ፥ በበለሳን ቅባት [ቅብዐ ሜሮን] የተቀባ፥ በሥላሴ ስም የተጠመቀ፥ ተደብቆ ከሚዘልፈው በገሀድ ከሚጣላው ያድነው ዘንድ በመሠዊያው አደባባይ ያደጋችሁ፣ የእርያም ካህናትና የምስክሩ ድንኳን የምስጢር ካህናት ለምኑለት:: ከጌታ በጎች መንጋ ዝልጉስ? የሆነ ኀጢአተኛው ጊዮርጊስ አለ:: ለዘላለም አሜን::





## [ምዕራፍ ፲፰]

# የስቅለት ዓርብ የዘጠኝ ሰዓት ምንባብ

ፍጥረት ሁሉ ያመሰግኑታል፣ የመላእክት ማኅበር ይገዙለታል፣ የእሳት ልሳናት [እንደበቶች] ይዘምሩለታል፣ የመብረቆች ምሰሶዎች ይሰግዱለታል፣ ደመናት፣ ነጐድጓድና ብልጭታ ይላኩለታል፣ የነፋሳት ግልብጥ ብጦሽ፣ ይሮጡለታል፣ የባሕር ሞገዶች እልል ይሉለታል፣ የገዳም ዛፎች፣ ሁሉም አትክልትና የገነት ዛፎች በቅርንጫፎቻቸው ያጨበጭቡለታል:: በእግዚአብሔር ስም እንጀምራለን::

«የክርስቶስ ሥጋ ከሰማይ ወረደች» የሚሉ አፍቲክስና[1] የሚመስሉትን ስለ ዘለፋቸው መናገር ተጨንቀን አንታክትም:: እንዴት «የክርስቶስ ሥጋ ከሰማይ ወረደች» ይባላል? ሥጋ በሰማያት ከኖረ ከእርሷ ሰው ይሆን ዘንድ በድንግል ማሕፀን ለምን አደረ? በድንግል ማሕፀን ከሥጋው ጋር አደረ /ከመወለዱ በፊት ሥጋን ነሥቶ ከነበረ/ ብትሉ የሥጋ በሥጋ ውስጥ ማደር ግን የጥንት ሥጋው በበቃው ከድንግልም ሰው መሆን [ሥጋ መኾን] ባላስፈለገው ነበር::

ሰነፎችና ልበ ልባችሁ ከማሰብ የዘገየ ሆይ! «አስቀድሞ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆኑ» ብሎ እንደ ተናገረ ከአዳም ዘር ሥጋ እንደ ተዋሐደ ዕወቁ::[2] መድኃኒታችን የተዋሐደው ሥጋ የአዳም ሥጋ ካልሆነ የአዳም እንደ እግዚአብሔር መሆኑ ምንድን ነው? በዚህች ሥጋ በምድር ላይ መከራን [ጉዳትን] ለበሰ፣ ይህችንም ሥጋ በሰማያት ክብርን አለበሳት::

ስለ ትሕትና ጉዳና መናገርን እናስቀድም፣ ኀይል ወደ ሴት ማሕፀን ተመልሶ እሳት በሥጋና ደም መጐናጸፊያ ተጠቀለለ:: ሕፃናትን የሚሥል በሕፃናት መልክ ተሣለ:: የሔዋን አባቷ ከሔዋን ልጅ ተወለደ:: በኪሩቤል ላይ የሚኖር በክንድ ታቀፈ:: በአርባዕቱ እንስሳት ላይ የሚቀመጥ የእሳት ሥዕል በአህያና በላም መካከል ተኛ:: ሥጋ የለበሰውን ሁሉ የሚመግብ የጡት ውተት ተመገበ:: ዘመን የማይቆጠርለት የጥንቱ ቀስ በቀስ አደገ:: ሕፃናትን በልጅነታቸው ጊዜ የሚያስጠብቃቸው በመስክ ላይ ዳኸ:: የዘመናቱ ቁጥር ጥንት [መነሻ] የሌለው በሰው መጠን ጐለመሰ::

1. አፍቲክስ የተባለው አውጣኪ ነው:: አባ ጎርጎርዮስ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ ገጽ፻፹፫::
2. ዘፍ.፫፥፳፪::



www.ethiopianorthodox.org

ተራፊዎችን ኃይልን የሚያስታጥቃቸው ደክሞት አላበው:: ኪሩቤል ይነኩት ዘንድ ስራፌል ይዳስሱት ዘንድ የማይቻላቸው እግሮቹን በዘማዊቷ ሴት፤ ልብሶቹን ደግሞ በሚፈሳት ሴት ተዳሰሰ::

ከኮሬብ ዐለት ውሃን ያፈለቀ ለጥሙ ከሳምራዊት ውሃ ለመነ፤ ከሲና በረሓ እስከ ቃዴስ በረሓ መናን ያወረደ እንጀራ በማጣት ተርቦ በውስጧ ፍሬ ባጣበት በለሱ ወደ ዕፀ በለስ ሔደ:: ለሰማይ ሰራዊት ንጽሕናን ያለበስ እንደ አደፈ [ሰው] በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ:: ዓለምን በክንዱ የሚደግፍ በሊቀ ካህናት አሽከሮች ተያዘ:: እስራኤልን በደመና ዓምድ የመራቸው በጲላጦስ ፊት ቆመ:: የግብፅ ሰዎችን በሚፈላ ቁስል የገረፋቸው በመኑንን ጅራፍ ተገረፈ:: ሰማይን እንደ ቀመር ቱስል የገረፋቸው... 

ቁስል የገረፋቸው በመኰንን ጅራፍ ተገረፈ:: ሰማይን እንደ ቀመር የስተለው በዕፀ መስቀል ላይ ተሰቀለ:: በኪሩቤል ራስ ላይ አክሊልን ያስተመጠ የእሾኽ አክሊልን ተቀዳጀ:: ለሶምሶን ከአህያ መንጋጋ ፈሳሽ ውሃንና ከአንበሳ አፍ የሚጣፍጥ ማር ያመነጨ ከሐሞት ጋር ሆምጣጤን ጠጣ:: አዳምን «ከእርሱ በበላህ ቀን ሞት ትሞታለህ»[3] ያለው በሥጋ ሞትን ተመሰ::

ይህ ሁሉ መከራ በሥጋው የመለኮት ኃይልን አገኘው፤ በሥጋው ላይ የተደረገው ወደ መለኮቱ ይታሰባልና:: ንጉሥ ሐር ወይም ነጭ ለብሶ ከክፉ አድራጊዎች አንዱን በላዩ ላይ ባለ ልብስ ቢመታ «ንጉሡን መታው» ከሚሉ የንጉሡን ልብስ መታ እንደማይባል ኤጲፋንዮስ ስለ መለኮትና ትስብእት እንደዚህም መሰለ:: ያደፈ ልብስን እንደ ለበሰ ሰው እድፉ በሚለብሰበት ቦታ ይታሰባል:: እንዲሁም መለኮት ግን በሕማም ሳይነካ የትስብእት ሕማም ወደ መለኮት ይታሰባል::

እንግዲህ ስለ መለኮት ከስቃልያን ዘንድ ተሰደበ እንላለን:: «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ራስህን አድን፤ አሁን ከመስቀል ውረድ፤ አይተን እንመንበህ::» ዳግመኛም «ሌሎችን አዳነ ራሱን ያድን» ይሉታልና:: «እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነ ግን ያድነው» ይሉታልና::[3] ይህ የመለኮት መሰደብ ነው፤ የትስብእት መሰደብ አይደለም:: የትስብእትን መሰደብ ግን ጲላጦስ «ንጉሣችሁን ልስቀለውን» ባላቸው ጊዜ «ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም፤ ራሱን የሚያነግሥ ሁሉ ንጉሥን የሚገለብጥ [የሚለውጥ] ነው» ብለው በሳወቁ:: ጲላጦስ ግን «ንጉሣችሁን ልስቀለውን?» ያለው የመንግሥትን ደግሞ በማስፈራት ይቅር ያስብለው

3. ዘፍ. ፪፥፲፯::





ዘንድ ልደቱ ከዳዊት ዘር እንደ ሆነ ሲያመለክታቸው ነው:: እነርሱ ግን ከዳዊት ዘር የሆነውን መንግሥቱን ክደው ሊገድሉት ጨከኑ፤ «ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም» አሉ:: ይህ ስድብ ወደ ትስብእት ይቆጠራል::[4]

ዳግመኛም «ሕግ አለን፤ እንደ ሕጋችንም ሊሞት ይገባዋል፤ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጓልና» አሉ::[5] ይህ ቃል በመለኮቱ ላይ መስደብንና ከአብ ስለ ተወለደው ልደቱ የክሕደት ጕዳናን ያመለክታል:: ስለዚህ በመዝሙር «አፋቸውን በሰማይ አኖሩ አንደበታቸውም በምድር ውስጥ አመላለሰ::» አለ::[6] «አፋቸውን ወደ ሰማይ አስቀመጡ» ያለው ስለ መለኮቱ መሰደብ ነው:: አይሁድ «አባቱንና እናቱን የምናውቃቸው ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን? ከሰማይ ወርጃለሁ እንዴት ይላል?» የሚሉት ናቸው::[7]

«አንደበታቸውን ወደ ምድር አመላለሰ» የሚለው ስለ ትስብእት መሰደብ ነው:: አይሁድ «እንደ ሳምራዊ አንተ ጋኔን እንዳለብህ እናው ቃለን» የሚሉት ናቸው::[8] «አብርሃም ፈጽሞ ሞተ፣ ነቢያትም ሞቱ፤ እንግዲህ ራስህን ማንን ታደርጋለህ?» አሉ::[9] እነሆ! ይህ በአንድ አካል ውስጥ ወደ እግዚአብሔርና ሰው የስድብ መንገድ ነውና::

መለኮት ግን ተገርፎ አልታመመም፤ ተቸንክሮ አልተበሳም፤ ተወግቶ አልቆሰለም:: በሰቃልያን ዘንድ ተነቀፈ፤ በአርያም የመንግሥቱ ክብር [ምስጋና] አልታጐለበትም:: ቄርሎስም ስለ መለኮትና ትስብእት መሰለ:: በመድኃኒት እንደ ተነከረ ፀምር [ግምጃ] እንዲሁም የመለኮትና ትስ ብእት ህልውና አንድ ከሆነ በኋላ ይለያይ ዘንድ አይቻልም:: አለ:: አስ ቀድ መንግን መለኮት የትስብእትን መከራ እንደ ተሳተፈ ተናገርን:: ከዛሬ ጀምሮም ትስብእት የመለኮትን ክብር እንደ ተሳተፈ እንናገራ ለን:: በደብረ ዘይት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሲበላ በደቀ መዛሙርቱ ላይ እጁን አስቀምጦ እያንዳንዱን ባረካቸው:: ከዚህ በኋላ የእሳት

4. ማቴ. ፳፯፥፵-፵፪::
5. ዮሐ. ፲፱፥፯::
6. መዝ. ፸፪፥፱::
7. ዮሐ. ፮፥፵፪::
8. ዮሐ. ፰፥፵፰::
9. ዮሐ. ፰፥፶፫::



www.ethiopianorthodox.org

ደመና ነጥቆት ተሰወረቻቸው:: ይህ በጨርቅ የጠቀለሉት ሥጋው ቃል በኪሩቤል ክንፎች ተጋረደ:: ይህ በክንድ የታቀፉት ሥጋው ቃል በእሳት ሠረገላ ላይ ተቀመጠ:: ይህ በዚህ ዓለም ተርቦ የተጠማ [ሥጋው ቃል] እኽል መብላት ውሃ እና ወይን መጠጣት ወደማይፈቀድበት ወደ ረጅሙ አርያም ዐረገ:: ይህ ከሊቀ ካህናት አሽከሮችና ከጲላጦስ ወታደሮች የተነጠቀ [ሥጋው ቃል] ከኪሩቤልና ሱራፌል አፍ ተመሰገነ:: ይህ በጲላጦስ አደባባይ ፊት ጉንጮቹን በጥፊ የተመታ [ሥጋው ቃል] የሰማይ ሰራዊት የእሳት ክንፎች ተከፍተውለት በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ:: ይህ እጆቹን በመስቀል ላይ የዘረጋ [ሥጋው ቃል] በላይና በታች በግራና በቀኝ የተጋረደ ነው::

ወደ ሰማያት ባረገ ጊዜ የመንግሥት ክብር ከምሥራቅ የፀሐይ መውጫ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን ጫፍ እስከ ደቡብ ጫፍ ሰፋ:: ይህ ከሐዋርያት ጋር ሆምጣጤ መልተው ያጠጡት [ሥጋው ቃል] ለደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ዘንድ ተነሥቶ ከአብ የወጣ የእሳት ፈሳሽ አጠጣቸው:: ይኸውም የጽድቅ መንፈስ የሥላሴ የሦስትነቱ ምልክት ነው:: ይህ ሞትን የቀመሰ ሥጋ [ሥጋው ቃል] መላእክት ይጉበኙት ዘንድ ወደሚመኙበት የሞት ሥልጣን ወደ ሌለበት ቦታ ደረሰ:: ይህ በመቃብር ውስጥ ሦስት ሌሊትና ሦስት መዓልት ያደረ ሥጋ[ሥጋው ቃል] ለዘላለም መሠረቷ ወደ ማይፈርስበት፣ ግንቧ ወደ ማይናድበት፣ የብርሃን ሠረገላ ወደ ተተከለበት፣ የእሳት ድንኳን ወደ ተተከለበት፣ አራት የእሳት ሥዕል [መልክ] ገጽ ያላቸው አርባዕቱ እንስሳት ወደ ሚያመሰግኑበት፣ ሰማያውያን የሚሆኑ ኻያ አራቱ ካህናት የብል ሃተኛ እጅ ባልሠራው በወርቅ ጽንሐሕ መዓዛው ያማረ የተወደደ ዕጣን ወደ ሚያቀርቡበት በአርያም አዳራሽ ውስጥ ተቀመጠ::

እነሆ! የትስብእት [ክብር] ከመለኮት ጋር ታወቀ:: ያለ መለ ወጥ እና ያለ መለየት፣ ያለ ልዩነትና ያለ መጨመር በባሕርይ ጥምረት [ተዋሕዶ] እንጂ በፍጥረታዊ ጠባይ አይደለም:: ሥጋ መለኮትን የትስ ብእት መከራን እንዳ ሳተፈው እንዲሁ መለኮት ትስብእትን የመልክም አምላክ ባሕርይ ክብርን አሳተፈው:: እነሆ! ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ህላዌ [ባሕርይ] አምላክም ሰውም ነው:: እነሆ በግና እረኛ በአንድ





ጽምረት:: እነሆ ካህንና ቁርባን በአንድ ምስጢር:: እርሱም በባሕርዩ የአምላክ ልጅ በሥጋው የዳዊት ልጅ ነው:: በልዩ ልዩ መልክ ለነቢያት የታያቸው ነው:: አምላክ ባልነው ጊዜ በሰማያዊ አባቱ ዘንድ ይገኛል:: ሰው ባልነው ጊዜ በገሊላዊት እናቱ ዘንድ ይገኛል:: ዕፀ ገነት ባልነው ጊዜ በአዳም ዘንድ ይገኛል:: የተወደደ መሥዋዕት ባልነው ጊዜ በአቤል ዘንድ ይገኛል:: ያማረ መዓዛ ባልነው ጊዜ በኖኅ ዘንድ ይገኛል:: ኅብስትና ወይን ባልነው ጊዜ በመልከ ጼዴቅ ዘንድ ይገኛል:: ወዳጅ ባልነው ጊዜ በአብርሃም ዘንድ ይገኛል:: በግ ባልነው ጊዜ በይስሐቅ ዘንድ ይገኛል:: ጉልማሳ ባልነው ጊዜ በያዕቆብ ዘንድ ይገኛል::

እሳት ባልነው ጊዜ በሙሴ ዕፀ ጳጦስ ዘንድ ይገኛል:: መና ባልነው ጊዜ በወርቅ ቅጠል በተሸፈነ ጎሞር [መስፈሪያ] ይገኛል:: የኮሬብ ዐለት የተኣምር ውሃ ባልነው ጊዜ በአሮን የወርቅ እንስራ ዘንድ ይገኛል:: የትእዛዝ ሕግ ባልነው ጊዜ በወርቅ በተለበጠ ታቦት ውስጥ ይገኛል:: ሹቱ ባልነው ጊዜ በጽዮን ቅባት ቀርን [ቀንድ] ዘንድ ይገኛል:: ልምላሜ ባልነው ጊዜ በዳዊት ዘንድ ይገኛል:: ንጉሥ ባልነው ጊዜ በሰሎሞን ዘንድ ይገኛል:: ሕፃን ባልነው ጊዜ በኢሳይያስ ዘንድ ይገኛል:: የሎሚ ዘንግ ባልነው ጊዜ በኤርምያስ ዘንድ ይገኛል:: ቀጭን ፉጨት ባልነው ጊዜ በኤልያስ ዘንድ ይገኛል:: ፈረስ የጫነ ባልነው ጊዜ በዘካርያስ ዘንድ ይገኛል::

የክብር ልብስ ባልነው ጊዜ በሕዝቅኤል ዘንድ ይገኛል:: ከተራራ ላይ ተወርውሮ [ከትልቅ ተራራ] ትልቅ ተራራ የሆነ ባልነው ጊዜ በዳንኤል ዘንድ ይገኛል:: የምስጋና [የክብር] ጽዋ ባልነው ጊዜ በዕዝራ ሱቱኤል ዘንድ ይገኛል:: የማር ወለላ ባልነው ጊዜ በአስተኒ[10] ዘንድ ይገኛል:: ይህን የትንቢት ፍሬ ለነቢያት በሚኖር ምሳሌና በሚኖር ተግባር ያሳያቸው ነው:: በነቢያት ዘንድ ነቢይ ይባላል:: ሙሴ «ከወንድሞቻችሁ መካከል እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣላችኋል:: ይህን ነቢይ የማይሰማው ሁሉ ይቺ ነፍስ ከሕዝቧ ትደምሰስ» እንዳለ::[11] ዳግመኛም በሐዋርያት ዘንድ ሐዋርያ ይባላል:: ጳውሎስ «ኢየሱስ ክርስ ቶስ ከፊታችን ያለ ሐዋርያችን ነው» እንዳለ::[12] ዳግመኛም ጳውሎስ ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀ ካህናት ሆኖ

10. አስኔት ከቅዱሳን የአንዱ ስም ነው::
11. ዘዳ. ፲፰፥፲፭::
12. ዕብ. ፫፥፩::



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር በተከላት በምስክሩ ድንኳን ውስጥ እንዳለ በየወገኑ በሚገባው ቦታ በነዚህ ሁሉ ስሞች ይጠራል።

ስለ ህላዌው [ባሕርዩ] አምላክ፥ ስለ ሥጋዌው ሰው ይባላል። ስለ የዋህነቱ በግ፣ ስለ መታረዱ የሥጋ ላም ይባላል። ስለ መንግሥቱ መሲሕ [የተቀባ]፣ ስለ አሸናፊነቱ አንበሳ ይባላል። ስለ ደሙ ወይን፥ ስለ ሥጋው ኅብስት ይባላል። ስለ ብርሃኑ ፀሐይ፣ ስለ ጽንዑ ደንጋይ ይባላል። ስለ መሥዋዕቱ ካህን፣ ስለ መሥዋዕቱ ቊርባን [መሥዋዕት] ይባላል። ስለ መዓዛ ትምህርቱ ሽቱ፣ ስለ ፍሬው ወንጌል ይባላል። ይኸውም የመለኮት ወንጌል ነው። «እውነተኛ የበጐች በር እኔ ነኝ» ስላለ በር ነው። «የጽድቅና የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ» ስላለ መንገድ ይባላል።[13] ይህን ሁሉ መባሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ይገባዋል። የዓለም ሁሉ ጥቅም በእጁ ውስጥ ነውና።

ከዛሬ ጀምሮ ግን «የክርስቶስ ሥጋው ከሰማይ ወረደች» የሚሉ ዝንጉዓንን እንዘልፋቸው /እንተቻቸው/ ዘንድ እንመለስ። እንዴት «ከሰማይ ሥጋውን አወረደ» ይባላል? የጸናች አሪት ስለ እርሱ «እግዚአብሔር አብርሃምን በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል አለው» ትላለች።[14] ከኢየሱስ ክርስቶስ ትስብእት በስተቀር ዘሩ ማን ነው? ጳውሎስ «ለአንተና ለዘሮችህ» ሳይለው እንደ ብዙኀን «ለአንተና ለዘርችህ እንደ አንድ አለው እንጂ» ብሎ እንደ ተረጐመ።[15] ይህን ተርጕሞ በክርስቶስ ዘንድ አቆመ። ማቴዎስ፦ «የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ አለ።[16]

ልበ ጠማማው ሆይ! ክርስቶስን «የዳዊት ልጅ» እንዳለው ዳግመኛ ዳዊትን የአብርሃም ልጅ እንዳለው ስማ እስኪ! የአብርሃም ልጅ ከዳዊት ዘር ከተወለደ እንዴት «የክርስቶስ ሥጋው ከሰማይ ወረደች» ትላላችሁ? የአብርሃምና የዳዊት ሥጋ ግን ከቶ ወደ ሰማይ አልወጣም። የአብርሃምም የትውልድ አገሩ በሶርያ ወንዞች መካከል ምድረ ከነዓን ነው። መቃብሩም በኬጢያዊ በሰዓር ልጅ በኤፍሮን እርሻ ላይ ባለ ደብር ነው። የዳዊትም የትውልድ አገሩ ቤተ ልሔም ነው። በዚያም በሳሙኤል እጅ ተቀባ። የመጀመሪያ መንግሥቱ በኬብሮን እስከ ሰባት ዓመት ሆነ። ሠላሳ ሦስት ዓመት በኢየሩሳሌም ነገሠ። ዘንግቶ በዚያ በትውልድ አገሩ በቤተልሔም ውስጥ ሞቶ ተቀበረ። ጳውሎስ፦ «የአብርሃምን ዘር

13. ዮሐ. ፲፬፥፮፤ ዮሐ. ፲፭፥፩።
14. ዘፍ. ፳፩፥፲፪።
15. ገላ. ፫፥፲፮።
16. ማቴ. ፩፥፩።



www.ethiopianorthodox.org



ከፍ አደረገ እንጂ መላእክትን የተቀበለ አይደለም» አለ።[17] በመዝሙርም «እግዚአብሔር ለዳዊት በእውነት ማለ፤ አይጸጸትምም። እንዲህ ብሎ፦ ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ።» ዳግመኛ «እኔ ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ። ሥልጣን እሰጣለሁ ለመሲሑም መብራትን አዘጋጃለሁ። ጠላቶቹን ኀፍረትን አለብሳቸዋለሁ። በእርሱ ቅድሳቴ ያፈራል።» አለ።[18]

በዳዊት ሥጋ ውስጥ ያፈራ የእግዚአብሔር የክብሩ ፍሬ ከክርስቶስ መለኮት ትስብእት በስተቀር ምንድነው? ለቅዱሳን የሚሰጥ የክብር ምንጭ የቅድሳት ምስጢሩ ይህ ነው። ሐዋርያት በዲዲስቅልያ ትምህርትም፦ «በሥጋ ከዘሩ በተወለደ በክርስቶስ ልደት በመካከላችን የዳዊትን መንበር ከፍ አደረገኸ» ይላሉ።

ዳግመኛም ሰነፎቹ ሆይ! በሰማያት የእንስሳትም ሆነ የሰው ሥጋ እንደ ሌለ ዕወቁ። የጸናች አሪት «እግዚአብሔርም አለ፦ ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ፣ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ ታውጣ።» ትላለች።[19] ዳግመኛ ስለ ሰው ልጅ ሥጋም የጸናች አሪት፦ «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት።» ትላለች።[20] እነሆ! ይስማያውያን አኗኗር በሰማይና የሥጋውያን አኗኗር በምድር ላይ ታወቀ። ከሥጋውያን በሰማያት የሚመላለሱ የሉም።

ዳግመኛም ቅዱሳንን ለመርዳት ከተላኩ [ከሚላኩ] በስተቀር በምድር ላይ የሚታዩ መንፈሳውያን የሉም። የመላእክት አለመታየታቸውም ግን ሥጋ ስለሌላቸው ነው። ለእኛም እንደ ጠባያቸው የማይዳሰስ የማይታይ ጠባይ አለን። መንፈስ [ነፍስ] ከሥጋ ከወጣች መላእክት እንደ ማይዳሰሱና እንደማይታዩ አትታይም፥ አትዳሰስምና። የእግዚአብሔር መላእክት እንደማይሞቱ፣ መሞትም ለሰው ልጅ መንፈስ [ነፍስ] የለውም። ነገር ግን ሰይጣን ለእግዚአብሔር ክብር አልተገዛምና በፍርድ ሥቃይ ሥጋ ሳይኖረው እንደሚሠቃይ በፍርድ ሥቃይ መከራ አለበት። ስለዚህ በሰማያት ሥጋ የሌለው የእግዚአብሔር ልጅ ከአዳም ሥጋን ይነሣ

17. ዕብ. ፪፥፲፮።
18. መዝ. ፻፴፩፥፲፩፤ ፻፴፩፥፲፯-፲፰።
19. ዘፍ. ፩፥፳፬።
20. ዘፍ. ፪፥፯።

ዘንድ ወረደ:: ይህንም ከአዳም ልጅ የነሣውን ሥጋ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ አስቀመጠው:: ከመለኮቱ ጋር በመጣበቅ በመንታነት አይደለም:: ያለ መመለስ በአንድ መልክ ያለ መጨመር በአንድ አካል እንጂ፣ በየመልኩ ከሀላዌው የተለየ አይደለም:: የእኛን ሥጋ ነሥቶ በራሱ ህላዌ [ባሕርይ] ውስጥ አንድ ካደረገ ከእግዚአብሔር ልጅ በስተቀር በሰማያት ሥጋ ለባሽ የለም:: ራሱ በወንጌል «ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም:: እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው::» እንዳለ::[21] ሄኖክና ኤልያስ ወደ ሰማያት እንዳረጉ የሚናገሩም አሉ::[22] በላይዋ ላይ እኛ ከምንኖርባት ምድር ተነጠቁ እንጂ:: እግዚአብሔር በእርሱ ጥበብ ተሰውሯ የሞት ሥልጣን በላይዋ ላይ በሌለ በተሰወረች ምድር ውስጥ ሰወራቸው::

ስለ ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፣ እግዚአብሔር ወስዶታልና አለ::[23] ስለ ኤልያስም የእሳት ሠረገላ መጥቶ በመካከሉና በደቀ መዝሙሩ መካከል ቆሞ አራራቃቸው::[24] የሚገባውን ወደሚገባው ቦታ ከሞት ይሸሽግ ዘንድ ነጠቀው አለ:: መነጠቅ ማረግ ለማይገባው ግን ከመምህሩ እጥፍ ድርብ የሚሆን የትንቢት ጸጋ ተተወለት [ተሰጠው]:: ከኤልያስ በኤልሳዕ ላይ የወረደው የመንፈስ ቅዱስ እጥፍ ድርብ ምንድነው? ኤልያስ የመበለቲቱ ልጅ ከሞተ በኋላ በላዩ ላይ በጸለየ ጊዜ የመበለቲቱን ልጅ አነሣው [አስነሣው]::[25] ኤልሳዕም በሞተ ጊዜ በድኑን የጥንት በድን ዐፅሞች ባሉበት መቃብር ውስጥ በድኑን ጨመሩ:: የኤልሳዕ በድን ያን ዐፅም በነካው ጊዜ [ያበድን] ፍጹም ሰው ሆነ:: እነሆ! በሕይወቱ ካስነሣው በሞቱ በበድኑ ያስነሣው የጸጋው ክብር በዛ::[26]

እንደዚህ የሚመስል ሌላ የነገር መንገድ አለኝ:: ጌታችን በወንጌል «በእኔ የሚያምንብኝ ሁሉ እኔ የምሠራውን ሥራ ይሠራል፤ እኔ ከምሠራውም የሚበልጥ ይሠራል::» አለ::[27] ጌታችን ካደረገው ተአምራት ማድረግ ምንድን ነው? ስለ ጌታችን ኢየሱስ በወንጌል «ብዙ ድውያንን ይዳስሳቸው

21. ዮሐ. ፫፥፲፫::
22. ሄኖክና ኤልያስ ወደ ብሔረ ሕያዋን እንጂ ወደ ሰማያት አለማረጋቸውን ለማመልከት ነው::
23. ዘፍ. ፬፥፳፭::
24. ፪ኛ ነገሥ. ፪፥፲፩::
25. ፪ኛ. ፲፫፥፲፬-፳፩
26. ዮሐ. ፲፬፥፲፪::
27. ማቴ. ፳፥፫፥ ማር. ፮፥፶፮::





ዘንድ አመጡአቸው:: እንደ ዳሰሳቸውም ይድናሉ::» አለ::[28] ስለ ጴጥሮስም በግብረ ሐዋርያት፡- ወንዶችና ሴቶችም ብዙ ነበሩ:: ስለዚህ ጴጥሮስ ሲያልፍ ጥላውም ቢሆን ከእነርሱ አንዱን ይጋርድ ዘንድ ድውያንን ወደ አደባባይ አውጥተው ያኖሩአቸው ነበር:: ጥላው እንዳረፈባቸው ይድናሉ» አለ::[29] ዳግመኛም ስለ ጌታችን ኢየሱስ ደም የሚፈሳት ሴት የልብሱን ጫፍ ዳስሳ ወዲያው እንደ ዳነች ይናገራል::[30] ስለ ጳውሎስም በግብረ ሐዋርያት፡- «ከጳውሎስ የልብሱን ጫፍ ወስደው በድውያን ላይ ያኖራሉ:: ወዲያውኑ ይድናሉ::»[31] ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ወደ ደቀ መዛሙርቱ በዛ:: እርሱን ግን የዳሰሱት ሲድኑ የጴጥሮ ስም ጥላ ያረፈባቸው ድነዋል:: ዳግመኛ እርሱ ግን ልብስ ለብሶ የልብሱን ጫፍ በመዳሰስ ጳውሎስ ግን እርሱ በሌለበት በድውያን ላይ የልብሶቹን ጫፍ በማኖር ነው:: ነገር ግን ሁሉንም የሚረዳቸው ኃይል ግን ካሥለጠናቸው ከእርሱ [ከኢየሱስ ክርስቶስ] ነው::

ስለ ኤልያስና ሄኖክ ወደ ተናገርነው ወደ ነቢያት የዕርገት ዜና እንግባ:: የዜናው መጽሐፍ «እንደ እነርሱ ወዳለ አገር ወሰዱት» ብሎ እንደ ተናገረ ስለ ዕዝራም እንናገራለን::[32] እነሆ ያቺን ቦታ አገር ባላት ጊዜ ምድር እንደ ሆነ/ች/ በፍጹም ዐሳወቀ:: እንደ እነሱ ወዳለ አገር ባለኝ ጊዜ እንደ ሄኖክና ኤልያስ እነርሱ አስቀድመው የሚኖሩ መሆናቸውን ዐሳወቀ::

«ዔደንም ገነትም በሰማያት ውስጥ ናት:: በምድር ውስጥ አይደለችም» የሚሉ አሉ:: በሰማያት ከሆነች ግን የጻናች አራት« ወንዝም ገነትን ያጠጣ ዘንድ ከዔዴን ይወጣ ነበር:: ከዚያም ለአራት ክፍል ይከፈል ነበር:: የአንደኛው ወንዝ ስም ኤፌሶን ነው፡ እርሱም ወርቅ የሚገኝበት የኢውላጓ ምድርን ይከብባል:: የዚያም ምድር ወርቅ ጥሩ ነው:: ከዚያም ሉልና የከበረ ድንጋይ ይገኛል:: የኹለተኛው ወንዝ ስም ግዮን ነው፡ እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል:: የሦስተኛው ወንዝ ስም ጤግሮስ ነው:: እርሱም በአሦር ምሥራቅ የሚሔድ ነው:: አራተኛውም ወንዝ ኤፍራጥስ ነው::» ለምን አለች?[33] «እነሆ! ገነትን ያጠጣት

28. የሐዋ. ፭፥፲፭-፲፮::
29. የሐዋ. ፭፥፲፭-፲፮::
30. ማር. ፭፥፳፱::
31. የሐዋ. ፲፱፥፲፪::
32. ዕዝ. ፩-፲ ይመልከቱ::
33. ዘፍ. ፪፥፲::



www.ethiopianorthodox.org

ዘንድ ይወጣል። ከዚያም ለአራት የዓለም ማእዘን ይከፍላል» አለ። የወንዞቹን መውጣት ከገነት መለያየቸውም በአራት አቅጣጫና የሚከበቡትም በሁሉም ዓለም አህጉር መሆኑን በተናገረ ጊዜ በምድር ውስጥ እንደ ሆነ አሳወቀ። ገነት በሰማይት ብትሆን ግን «ከላይ ይወርዳል» ካለ «ምድርን ያጠጣት ዘንድ ከገነት ይወጣል» ባላለ ነበር፤ ከገነት ምድርን ያጠጣት ዘንድ ነው። እነሆ! ከምድር እንደሆነ ከላይ ወደታች እንዳይደለ አሳየ። ዳግመኛ የጸናች አሪት፡- እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከዔዴን ገነት። የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ አዳምን አስወጣው። ወደ ሕይወት የሚወስደውን መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልና ሱራፌልን የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔዴን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ።» በዚህም ግን «በፊትህ ወዝ እንጀራህን ትበላለህ» ስላለው ከምድረ ገነት ወጥቶ ወደ ተግባር ምድር እንዳደረ በፍጹም ዐሳወቀ።[34] አዳምና ልጆቹ በውስጧ የሚኖሩባት ምድር ግን ከገነት አጠገብ በምሥራቅ አንጻር ናት። የጸናች አሪት፡- «ቃየንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፤ ከዔዴንም ወደ ምሥራቅ በኖድ ምድር ተቀመጠ» እንዳለች።[35]

የቃየን ከእግዚአብሔር ፊት መውጣት እግዚአብሔር አዳምን ሔዋንን ካስተመጣቸው በታ ከመሬት በስተቀር ምንድን ነው? ከእናትና አባቱ ስለ ምን ሸሸ? አቤልን ስለ ገደለ ያደረገውን ኃጢአት ስለ ማፈር ወላጆቹን ማየት አልቻለምና፤ ወንድሙን ስለ ገደለው ከእናትና አባቱ ፊት ሸሸ። የእግዚአብሔር ጸጋ ከእርሱ ርቆ ከአቤል በኋላ በተወለደ በሴት ዘንድ ወረደ። የአቤል በረከት ወደ ሴት ልጆች ዘንድ ገባ።

እግዚአብሔርም ሱራፌልና ኪሩቤልን የዕፀ ሕይወትን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ የሾማቸው ግን አዳም ተመልሶ ወደ ውስጥ እንዳይገባ ነው። የገነት መኖሪያዋ በሰማይት ቢሆን ግን አዳም እንዳይገባ በበሮቿ ውስጥ ጠባቂዎች ባልተደመሩ ነበር። ከምድር አፈር የተፈጠረ ወደ ሰማይ ማረግ የሚችል የለምና ወደ ገነት ይመለስ ዘንድ በአዳም ላይ ትዝብት ባልሆነችም ነበር። ከአዳም እስከ ኖኅ የአዳም ልጆች በገነት አጠገብ ኖሩ። የሰው ልጆች የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፍ መንገዳቸውን ባበላሹ ጊዜ የሰማይ ትጉሃን የእግዚአብሔር ልጆች ወርደው ከሰው ልጆች ጋር በተደመሩ ጊዜ ሥራ ሥር መበጠስን፣ መድኃኒት ማድረግንና

34. ዘፍ. ፫፥፳፫።
35. ዘፍ. ፬፥፲፮።





ኮከብ ማምለክን አስተማሩ። ምድር ዐመፃን፣ ንጥቂያን፣ ግፍን፣ ዝሙትን፣ ግድያንና ደም ማፍሰስን ተመላች። እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ።[36]

እግዚአብሔርም ኖኅን «አንተ ከሚስትህ፣ ከልጆችህና ከሦስት ሴት ልጆችህ ጋር የምትድንበትን ከእንጨት መርከብን ለአንተ ሥራ አለው። ኖኅም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ። የመርከቢቱን ሥራ በፈጸመ ጊዜ የመርከቢቱ ርዝመቷ ሦስት መቶ ክንድ፣ ወርዷ ኀምሳ ክንድ፣ ከፍታዋ ሠላሳ ክንድ ሆነ። ዳግመኛም አንድ ለራሱና ለሚስቱ፣ ለልጆቹና ለልጆቹ ሚስቶች፣ አንድ ለእንስሳት ወገን፣ አንድ ለወፎች ወገን ሦስት ክፍል ቤትን ይሠራ ዘንድ አዘዘው። ለቁመቷ ፍጻሜ አንድ ክንድ ሲተርፍ በርዋን ይሠራ ዘንድ አዘዘው።

ዳግመኛም በውስጥም በውጭም በቅርጣን [ሙጫ] ይለቀልቃት ዘንድ አዘዘው። ኖኅም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ። ይህችንም መርከብ ከውጭና ከውስጥም በቅርጣን ለቀለቃት። ኖኅም ወደ መርከቢቱ ከን ጹሕ እንስሳ ሁሉ ሰባት ሰባት ተባትንና እንስት፣ ንጹሕ ካልሆነ እንስሳም ኹለት ኹለት ተባትና እንስት፣ ከሰማይ ወፍ ደግሞ ሰባት ሰባት ተባትና እንስትን አስገባ። ከዛሬ በፊት የሰማይ ወፎችና የምድር አራዊት ፍርሃት አልነበረባቸውም። ንጹሕ የሆኑ የፍየል፣ የበግ፣ የከብት፣ የግመሎች፣ የፈረሶች እና የአህዮች መንጋ እንደ ሚጠበቁ፣ ወፎችም ቤት ውስጥ እንደሚያድሩ የዶሮ መንጋ ፍርሀት አልነበረባቸውም። ከዛሬ አስቀድሞ የሰማይ ወፎችና የምድር አራዊት ከሰው ፊት ፍርሀት ቢኖርባቸው ኖኅ ወደ መርከብ ያስገባቸው ዘንድ ባልተቻለው ነበር።[37]

አስቀድሞ ግን አዳምን በእነርሱ ላይ ወደ ራሱ አምጥቶአቸው ይጠብቃቸው ዘንድና ይሰይማቸው ዘንድ አሠለጠነው። አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ በስሙ እንደ ጠራው ስሙ ሕያው ሆነ። አስቀድሞ ግን ንግግር [ቋንቋ] ነበራቸው። የነገሩ ምንጭ ከየት እንደ ሆነ በመጽሐፈ አሪት ተጽፏል። አራዊት ንግግር [ቋንቋ] ከሌላቸው ለምን እባብ፣ «ሴቲቱንም በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት። ሴትቱም ለእባቡ አለችው፡- በገነት ካለው ከዛፍ

36. ዘፍ. ፮፥፳።
37. ዘፍ. ፯፥፩-፱።



www.ethiopianorthodox.org

ፍሬ እንበላለን ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፍ ፍሬ እግዚአብሔር አለ፡- እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም። እባብም ለሴቲቱ አላት፡- ሞትን አትሞቱም፤ ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዐይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔር መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ።»[38]

ገረድ እመቤቷን እንደ ምትመክር እንደተጨነቀችላት አማከረቻት፤ እንደ አሳሳተቻት የልጆቿን እግር ለመንከስ የምትጠብቅ ጠላት ሆነቻት፤ እግዚአብሔርም ሴቲቱንና እባቡን ረገማቸው። ያሳሳታትን እርግማን አበዛበት። የተሳሳተችውን እርግማኗን አሳነሰላት እንጂ እርግማኑ እኩል አይደለም። «እባቡን አለው፡- ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት ከምድርም አራዊት ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ፤ በሆድህም ትሔዳለህ፤ አፈርንም በሕይወትህ ዘመን ትበላለህ። በአንተና በሴቲቱ መካከል፤ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።»[39] መጀመሪያ የግመል ልጅ ትመስል ነበር። ከዚያን ዕለት ጀምሮ ከበስተኋላዋ እግሮቿን ከፊት ለፊቷም ክንዶቿን አስቀረ። በድንቁርና ጆሮዋን ዘጋ።

የሔዋንን ልጆች በምትበቀላቸው ገንዘብ ከዐይን፣ ከጥርስና አፍ በስተቀር መልኳን አላስቀረላትም። እርሷ በኃጢአተኛ ነፍስ [ሰው] የምትመሰል ናት። ዳዊት «እንደ እባብ ጆሮዋ የተደፈነው ዐዋቂ ሲደግምባት የአስማተኛውን ቃል እንደማትሰማ» አለ።[40] በዐይኖቹ እያየ የሚመጣውን ድምፅ ከማይሰማና ለኀደኛ ቂምን ከሚሰበስብ ሰው በስተቀር እንደ እባብ ጆሮው የተዘጋ ማን ነው? ዳግመኛ ሊበቀለው የሚፈልገውን ሰው እንደ እባብ በሃይማኖት ኀይል አሸንፎ በጸሎት ከሚደግመው በስተቀር አስማተኛ ዐዋቂ ማን ነው?

«እግዚአብሔር ለሴቲቱም በጸነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛዋለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤ እርሱም ገዥሽ ይሆናል።» አላት።[41] ከድንግል ማርያም በስተቀር ለወንድ ያልታጨች በጋብቻ ያልተሳሰሩ ይገዙአቸው ዘንድ ባል የሌላቸው ከዚህ መርገም ያመለጠች ሴት የለችም። ጳውሎስ «የሴት ራስ [የበላይዋ]

38 ዘፍ. ፫፥፭።
39 ዘፍ. ፫፥፲፬።
40 መዝ. ፶፯፥፬-፭።
41 ዘፍ. ፫፥፲፮።





ወንድ [ባሏ] ነው» እንዳለ። ማርያም ግን ለዮሴፍ ቤት በሥርዐተ ጋብቻ በሕግ ትገዛና ትገለገል ዘንድ ታጨች። ሳይቀርባት ከመንፈስ ቅዱስ በማሕፀኗ ፅንስ ኖሮ ተገኘች። የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይቀርባት ከለከለው ፅንሷ ቀስ በቀስ ባደገ ጊዜ አረጋዊ አደነቀ። «የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም ታየው። እንዲህም አለ፡- የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ! ከእርሷ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ።»[42] ሕፃኑን በወለደችውም ጊዜ እንደ እመቤት አክብሮ እንደ ባሪያ አገለገላት። ወደ ግብፅ ምድርም በወረዱ ጊዜ ያልወለደውን ሕፃን ተሸክሞ ተገዛላት። እነሆ! የሴት መገዛት ወደ ወንድ ተመለሰ። አለቃው ሆና የሔዋን መርገም ከእርሷ ተወገደ። የተሰጣት የእግዚአብሔር ጸጋ እንዲህ ያለ ሀብት ለአዳምና ለዘሩ እስከ ዘላለም ለባዕድ አልተሰጠም። የሴፍም ስላገለገላት ክብሩ [ጸጋው] ዐይኖቻቸው ብዙ ከሆኑ ከኪሩቤል በለጠ፤ ኪሩቤል በሠረገላ የሚሸከሙትን፣ ሱራፌል ፍሕሙን ለመንካት ያለ ጉጠት የማይደፍሩትን በትከሻው ተሸክሞአልና።

ኖኅ አራዊትንና እንስሳትን ወደ መርከብ እንዳስገባቸው ወደ መርከብ ነገር ዜና እንግባ። ከእንስሳት በየወገናቸው ወፎችንም ሁሉ በየወገናቸው ከሰበሰበ በኋላ እርሱ እና ሚስቱ [አምዛራ]፣ ልጆቹ ሴም እና ሚስቱ (ሲዴቀቴልባብ)፣ ካምና ሚስቱ፣ (ነኢለማዱክ)፤ ያፌት እና ሚስቱ (አደተኒሶስ)። እነዚህ ሁሉ ወደ መርከብ ውስጥ ገቡ። በሁለተኛው ወር /ጨረቃ/ ከምሽቱ ዐሥራ ኹለት ሰዓት በሆነ ጊዜ እግዚአብሔርም የመርከቡን መስኮት በስተኋላው ዘጋ። እግዚአብሔርም ሰባቱን የሰማይ መስኮቶችና ሰባቱን የቀላይ ምንጮች ከፈተ። የሰማይ ፈሳሾች ፈሰው የቀላይ ምንጮች ከፍ ብለው በምድር ላይ ሥጋ ያለው የሚንቀሳቀሰው ሁሉ ወፍም፣ እንስሳውም አራዊቱም በምድር ላይ የሚርመሰመሰውም ተንቀሳቃሹም ሁሉ ሰውም ሁሉ ጠፉ። ኖኅ የሰራትም ያቺ መርከብ በባሕር ሞገድ እየተነዳች በአጽናፈ ዓለም ውስጥ ዞራ አባቶቹ በሚኖሩበት በገነት አጠገብ ተጸለለች።[43]

ምድር በደረቀች ጊዜ፤ በተጠናቀቀም ጊዜ፤ መርከቢቱም በአራራት ተራሮች ላይ ተቀመጠች። ከዚህ በኋላ ጥፋቱ ከምድር ገጽ አልቆ የኀለም ማእዝን ሁሉ በደረቀ ጊዜ ኖኅ ልጆቹና ሚስቱ የልጆቹ ሚስቶች የዱር

42. ማቴ. ፩፥፳።
43. ዘፍ. ፯፥፳።



www.ethiopianorthodox.org

አራዊት፣ የሰማይ ወፎች ወጡ:: እግዚአብሔርም ለኖኅ ምድርን ዳግመኛ እንደ ማይረግማትና በጥፋት ውሃም እንደ ማያጠፋ ማለ:: «እግዚአብሔርም ኖኅንና ልጆቹን ባረካቸው፤ ብዙ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት:: አስፈሪነታችሁና አስደንጋጭነታችሁ በምድር አራዊት፥ በሰማይም ወፎች፥ ይሁን::» አላቸው::[44] ከዚህ በኋላ በሰው ልጆች ፊት በሰማይ ወፎችና በምድር አራዊት ልብ ውስጥ ፍርሃት ድንጋጤ ሆነ:: በምድር ገጽ ሁሉ ተበተኑ፤ እንግዲህም ከፊአቸው የሚሸሹ ሆኑ:: በሰው ልጅ ቋንቋ መናገርም ከአራዊትና ከእንስሳት አፍ ታጉለ፤ የአዳም የስሕተቱ ምክንያት በእባብ ቃል ሆኗልና:: ለሰው ልጅም ለማገርና ለሥራ አገልግሎት ይሆነው ዘንድ ከእንስሳት ንጹሕና ርኩስ ክፍል ቀረለት:: ከጥፋት ውሃ አስቀድሞ ለዱር አራዊት ሁሉ ፍጹም እንደ ሰው ልጅ ቋንቋ እንደ ነበራቸውም በመጽሐፈ ኩፋሌ ተጽፎ ይገኛል::[45]

ኖኅ ከመርከብ በወጣ ጊዜ የዱር እንስሳት ሳይበተኑ ከንጹሕም እንስሳ በሉባር ተራራ ለእግዚአብሔር መልካም መዓዛን ሠዋ:: እግዚአብሔርም መልካሙን መዓዛ አሸተተ::[46] ከዚህ በኋላ ገንዘብና ጽድቅን በመፈለግ ከገዳም ወደ ገዳም፣ ከአገር ወደ አገር በሚዞሩ በፈላስያን ቃልና በተጓዦች ዜና የገነት የመንገድዋ አሰር አልተገኘም:: የገነት መንገድ መጥፋት [መታጣት] ስለምን ሆነ? የኖኅ መርከብ በጥፋት ውሃ ላይ ተንሳፋ ከባድ በሆነ የውሃ ሞገድ እየተነዳች ርቀት ተጉዛ ኖኅንና ልጆቹ ወደ ማያውቁት ቦታ አድርሳቸዋለችና:: የጥፋት ውሃም ባለቀ ጊዜ በአራራት ተራራ ላይ ተቀመጠች:: በዚያም እግዚአብሔር ኖኅ ልጆቹ ከመርከቢቱ ውስጥ እንዲወጡ አዘዛቸው:: ወጥተውም የገነትን መኖርያዋን አጡ::

የእግዚአብሔር ጥበብ ከዚህ በኋላ መድረስ ወደ ማይችሉበት ቦታ በመርከብ ውስጥ አርቆ አፍልሶአቸዋልና:: በመጀመሪያ አዳምና ሔዋን ከማይበላው ዕፅ ስለበሉ ከገነት ዐጸዶች ወጥተው በኀሮዋ እስከመቻቸው ድረስ ተቀመጡ:: ልጆቻቸውም ከእነርሱ በኋላ እስከ ጥፋት ውሃ ድረስ ተቀመጡ:: እግዚአብሔር የጥፋት ውሃ ባወረደ ጊዜ በገነት አጠገብ ይኖሩ የነበሩትን ደመሰሳቸው:: በኃጢአታቸው ፈጽመው አሳዝነውታልና ከጥቂት ስምንት ነፍሳት [ሰዎች] በስተቀር አላስተረፈም::

44. ዘፍ. ፱፥፪::
45. መጽሐፈ ኩፋሌን ይመልከቱ::
46. ዘፍ. ፰፥፳፩::





እነርሱንም ራሳቸው በሠሩአት በጥበቡ መርከብ አፈለሳቸው:: ዳግመኛ ወደ ገነት አጠገብ መድረስ ወደ ማይችሉበት ሩቅ ቦታ አስቀመጣቸው፤ እርሱ አስቀድሞ ከእነርሱ ኃጥአን እንደሚወለዱ አውቆአልና:: ወንድሞች ሆይ! ያለ ምድር አፈርና ያለ ፈሳሽ ውሃ ለአትክልት ዕድገትና ልምላሜ እንደሌለ ዕወቁ::

ዳግመኛም መሬት በሰማያት እንደ ሌለ ዕወቁ፤ ገነት ማለት የአትክልት ቦታ ማለት ነውና:: ወንጌል በተሰቀለበትም ስፍራ አትክልት ነበረ፣ በአትክልቱም ማንም ገና ያልተቀበረበት አዲስ መቃብር ነበረ::[47] ጌታችን ኢየሱስን በዚያ ቀበሩት:: በሌላ ቦታም «ለእርሷ ግን የአትክልት ጠባቂ መሰላት::» አለ::[48] በነቢዩ በዳንኤል መጽሐፍ ስለ ሶስናም «አልፏታልና በገነት ውስጥ ትታጠብ ዘንድ ወደደች:: ተሰውረው ከሚጠብቋት ከሁለቱ መምህራን በቀር በዚያ ማንም አልነበረም:: ዘይት አምጥተው ያጥቧት ዘንድ ልትታጠብ የገነትንም ደጃፍ በር ይዘጉ ዘንድ ደንገጡሮቿን አዘዘቻቸው:: እነርሱም እንዳዘዘቻቸው አደረጉ:: የገነት ደጃፍ ዘግተው ያዘዘቻቸውን ያመጡ ዘንድ በሥርጥ ጎዳና ወጡ::» አለ::[49] መጻሕፍት ሰው የሚያርሳቸውን የአትክልት ፍሬዎችን ገነት እንደሚል ተመልከቱ::

ዔዶም ገነት ግን እግዚአብሔር የተከላት የአትክልት ማፍሪያ ናት:: እርሷም ለቅዱሳን ርስት ተዘጋጅታ ትኖራለች:: አበባዋ አይረግፍም፤ ፍሬዋም አይደርቅም፤ ቅጠሏም አይጠወልግም፤ እግዚአብሔር ተክሏታልና:: የጸናች ኦሪት፡- «እግዚአብሔር አምላክ በምሥራቅ በዔዶን ገነትን ተከለ:: የፈጠረውንም ሰው ከዚያው አኖረው» እንዳለች[50] እነሆ! የእግዚአብሔር ገነት መኖሪያዋ ምድር ውስጥ እንደ ሆነ በጉልበት [በኀያልነት] የሚገባበት እንደሌለ አመለከትናችሁ፤ የእግዚአብሔር ግምብ ይከባታልና:: ስለዚህ ዳዊት «ወደ ጽኑ ከተማ ማን ይወስደኛል? ማንስ እስከ ኤዶምያስ ይመራኛል» አለ::[51]

«ሲኦልም በሰማያት ናት»፤ የሚሉም አሉ፤ ወደ ጥልቅ ምድር ናት እንጂ ይህ እንደዚህ አይደለም:: የጸናች ኦሪት ስለ ዳታንና አቤሮን ሙሴም፡- «ይህን

47. ዮሐ. ፲፱፥፵፩::
48. ዮሐ. ፳፥፲፭::
49. ሶስና. ፩፥፲፭–፲፰::
50. ዘፍ. ፪፥፰–፱::
51. መዝ. ፶፱፥፲::



www.ethiopianorthodox.org

ሥራ ሁሉ አደርግ ዘንድ እግዚአብሔር እንደ ላከኝ እንጂ ከልቤ እን
ይደለ በዚህ ታውቃላችሁ:: እነዚህ ሰዎች ሰው እንደ ሚሞት ቢሞቱ
ወይም እንደ ሰው ሁሉ ቢቀሥፉ እግዚአብሔር አልላከኝም:: እግዚአ
ብሔር ግን አዲስ ቢፈጥር፣ ምድርም አፍዋን ከፍታ እነርሱን ለእነ
ሱም ያለውን ሁሉ ብትውጣቸው በሕይወታቸውም ወደ ሲኦል ቢወርዱ
ያን ጊዜ እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን እንደ ናቁ ታውቃላችሁ:: እ
ዲህም ሆነ፣ ይህን ቃል ሁሉ መናገር በፈጸመ ጊዜ ከበታቻቸው ያለው
መሬት ተሰነጠቀ:: ምድራቱም አፍዋን ከፍታ እነርሱን ቤተሰቦቻቸውን
ለቆሬም የነበሩትን ሰዎች ሁሉ ዕቃዎቻቸውንም ሁሉ ዋጠቻቸው:: እነርሱም
ለእነርሱም የነበሩ ሁሉ በሕይወታቸው ወደ ሲኦል ወረዱ:: ምድራቱም
ተዘጋችባቸው ከጉባኤውም መካከል ጠፉ::» ትላለች::[52]

ዳግመኛ እግዚአብሔር በሕግ መጽሐፍ እሳት ከቁጣዬ ትነድዳለችና
እስከ ሲኦል ድረስ ታቃጥላለች፡ አለ::[53] ሁሉም ነቢያት ሲኦል ከምድር
በታች እንደ ሆነች አመለከቱ:: ዳዊትም «ነፍሴን ከታችኛዪቱ ሲኦል
ከመውረድም አዳንከኝ:: እንደገና ሞት ይምጣባቸው በሕይወታቸውም
ወደ ሲኦል ይውረዱ::» አለ::[54] ኢሳይያስም «ሲኦል ከምድር በታች
ናት::» አለ::[55] ሲኦል ከታች በስተቀር ከላይ እንደ አለች የሚናገርላት
የለም:: በሰዶምና በገሞራ ላይ የሆነው ከሰማይ ስለ እሳት መውረድ
ግን ከሲኦል ወደ እነርሱ ዘንድ እንደ ተላከ እንዳይመስላችሁ:: ይህ
ድንገተኛ የእግዚአብሔር መቅሠፍት ግን የናቁትን ተቆጥቶ በተበቀላ
ቸው ጊዜ ዘወትር ይታያል::

ወደ ምስክሩ ድንኳን ከጕረቤት እሳት ስላመጡ ከናዳብና ከአብዩድ
ማዕጠንት እሳት ወጥታ አቃጠለቻቸው:: ይህች ከማዕጠንታቸው የወጣች
የእግዚአብሔር የቅናቱ እሳት እንጂ የሲኦል እሳት አይደለችም:: «እሳ
ትም ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥታ ያጥኑ የነበሩትን ኹለት መቶ ኀምሳ
ሰዎች በላች::»[56] ይህቺም ከድንኳኑ ክፍል አዳራሽ የወጣች የእግዚአብሔር
የመዓቱ እሳት እንጂ የሲኦል እሳት አይደለችም:: በየወገናቸው ሲጓዙ
በመንገድ ላይ እሳት ነዳ በአንድነት የተሰበሰቡትን አቃጠለች:: ይህቺም

52. ዘኍ. ፳፰ ፥ ፴፱::
53. ዘዳ. ፴፪ ፥ ፳፪::
54. መዝ. ፲፭ ፥ ፱::
55. ኢሳ. ፲፫ ፥ ፳፪::
56. ዘኍ. ፲፯ ፥ ፴፩፣ ዘሌ. ፲ ፥ ፪::





በእግዚአብሔር ላይ የሚያጉረመርሙትን የምትበቀላቸው የበቀል እሳት
እንጂ የሲኦል እሳት አይደለችም:: እግዚአብሔር ግን ስለ ሰው ልጆች በደል
በተቆጣ ጊዜ ሥጋ የለበሰውን ሁሉ ይደመስስ ዘንድ በምድር ገጽ ላይ
ጥፋትን አዘነመ::

ዳግመኛም ቸር በሆነ ጊዜ ለእስራኤል በገዳም እንጀራ [መና] አዘነ
መላቸው:: እንደገና በግብፅ ሰዎች ላይ የምድራቸውን ፍሬ ሁሉ እስኪ
ያጠፋ ድረስ እሳትና በረዶ አዘነመ:: ዳግመኛም ሥጋን በመፈለግ [በመ
ወደድ] መጉረምረማቸውን ያስተር ዘንድ እንደ አፈርና እንደ ባሕር አሸዋ የሚ
በሩ ወፎች ለእስራኤል ልጆች ሥጋን አዘነመላቸው:: እንደ ገና ለኤል
ያስ ኹለቱን የኀምሳ አለቆች ከሕዝባቸው ጋር ያቃጥላቸው ዘንድ
ተበቃይ እሳትን አወረደለት:: ዳግመኛም ቀዝቃዛ ውሃን የሚልስ፣ እርጥብ
እንጨትን የሚበላ፣ የሚቃጠለውን መሥዋዕት የሚቀበልና መሥዋዕቱን
የሚቀድስ የምሕረት እሳት ወረደለት::

እንደገና እግዚአብሔር በሰዶምና በገሞራ ላይ እሳት አናዳን
አወረደ በእግዚአብሔር የመዓት /የቁጣ/ ጽዋ ተቀድቶ በላያቸው ላይ
የፈሰሰ የጥፋት እሳት እንጂ የሲኦል እሳት አይደለም:: የኃጢአታቸው
ሽታ በእግዚአብሔር ዘንድ እንዳረገች ከልዑል ዘንድ የጥፋት እሳት
ተላከ:: ዳግመኛ በንጹሐን ሐዋርያቱ ላይ ራሱን የሚመስል ከጽድቅ
መንፈስ ከጰራቅሊጦስና ከአባቱ ጋር የሚተካከል ማሕየዊ እሳትን
መለኮታዊ እሳትን አወረደ:: እግዚአብሔር በጥፋት ውሃ ዓለምን ሁሉ
እንደ ደመሰሰ እንዲሁ በጥምቀት ውሃ ምእመናንን የዕዳ መጽሐፍ
ደመሰሰ:: እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን በጥፋት ውሃ እንዳቃጠለ
እንዲሁ በሐዋርያት ላይ በተላከ በእሳት መንፈስ የናዝራውያንን የኃጢ
አት እሾኽ አቃጠለ:: «ራሱ ዮሐንስ በውሃ አጠመቀ፡ እናንተ
በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ታጠምቃላችሁ» ብሏልና::[57] ስለዚህ ዳዊት
«መቅሠፍት ከመዓቱ ሕይ ወት ከፈቃዱ ነው» ብሏልና፡[58] ሐዋርያውም
«እርሱ ማዳንም ማጥፋትም ይችላል::» አለ::[59]

እነሆ! በሰማይት በምድር ላይ የሚመላለሱ የሰው ልጅ ሥጋ፡ በባሕር
ውስጥ የሚጠልቁ ዓሳዎች ሥጋ፡ የሚበሩ አዕዋፍ ሥጋ፡ ወይም የእን
ስሳት ሥጋ፡ የፍርድ ቦታ የለም፡ የሰማይት ሰማይ ለእግዚአብሔር ነው

57. ማቴ. ፫ ፥ ፲፩::
58. መዝ. ፵፱ ፥ ፫::
59. ዕብ. ፲፪ ፥ ፳፱::



www.ethiopianorthodox.org

ምድርን ግን ለሰው ልጆች ሰጣት ተብሎ እንደ ተጻፈ::[60] በነይልህም ከንደ ጠላቶችህን በተንሃቸው እንዳለ:: ዳግመኛ ሰማይት የአንተ ናቸው፡ ምድርም የአንተ ናት ዓለምን ሞላውም አንተ መሠረትህ አለ::[61] ለሰማ ያውያን የምድር ግዛትም ለአዳምና ለዘሩም እስከ ዘላለም ተሰጠ:: የእግዚ አብሔር መንግሥት ዘወትር ትስፋናለች ትገዛለች:: በነፋሶችም መነ ቀወጥ በደመናዎች መብረር ሥልጣን አለለት:: ለእርሱ ከመብረ ቆችና ከነጐድጓድ ከብልጭታ አፍ ከሰውና ከእንስሳት ዘንድ በባሕር፣ በሰማ ይትና በምድር ምስጋና ይገባል:: ለዘላለም አሜን::

60. መዝ. ፻፲፫ ፥ ፳፬::
61. መዝ. ፹፰ ፥ ፲፩::





# [ምዕራፍ ፲፱]

## የስቅስተ ዓርብ የሠርክ ምንባብ

በመሐስባን ልብ ውስጥ የሚታሰብ፣ የዓመታትን ልዩነት በሚለይ፡ ክፍለ ዘመኖችን የመጀመሪያውን ከሁለተኛው ጋር ሦስተኛውን ከአራተ ኛው ጋር በማስተካከል የሠራ፣ መፀውን በጸደይ ክረምትን በበጋ የሚያፈ ራርቅ፣ የፀሐይን ብርሃን ሸፍኖ በሰማይ ገጽ ላይ የሚዘረጋው፣ ከጥልቅ /ከባሕር/ የሚወጣውን ውሃ በደመና ውስጥ የሚያቁር፣ በትርጓሜው ሁሉን ቻይ ጌታ በሚባል በአዶናይ እግዚአብሔር ስም እንጀምራለን::

ሥልጣንና ገናናነት የባሕርዩ ለሆነ ለእርሱ ለዘላለም ክብርና ምስጋና ይገባል:: አሜን::

የክርስቶስ ሥጋ የሰው ልጅ ሥጋ አይደለም:: «ምትሐት ነው፡» የሚል የመንክዮስን[1] ዘለፋ እንናገር:: መንክዮስ ሆይ! ስንፍናህን [አለማስተዋ ልክን] አደንቃለሁ:: ከአዳምና ከሔዋን ልጅ ሰው ሆነ፡ ከምትለው ምትሐት ትለው ዘንድ እንዴት ወደድክ? እርሱ ግን ከዕብራውያን ልጅ /ከዕብራዊት/ ሥጋን ባይዋሐድ፣ እርሱ ከእርሷ ባይወለድ በጡቶቿ ወተት ባላደገ ነበር:: በጡቶቿ ወተት ባያድግ በክንዶቿም ባልታቀፈ ነበር:: በክንዶቿ ባይታቀፍ በጣቶቿ ባልተነካ ነበር:: እንደ ሕገዪ ሥርዐትም ባልተገዘረ ነበር:: እንደ ሕገዪ ሥርዐት ባይገዝር በዮርዳኖስ ወንዝ ራሱን እየተዳሰሰ በዘካርያስ ልጅ በዮሐንስ ዘንድ ባልተጠመቀ ነበር:: በዮርዳኖስ ወንዝ ካልተጠመቀ በቅንዋተ መስቀል ባልተቸነከረ ነበር፡ ለቤዛ ብዙኃን ሲባል ባልሞተ ነበር:: ስለ ብዙኃን ቤዛ ሲባል ካልሞተ መንክዮስ÷ አንተ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት አልዳንክም::

በመጽሐፈ ኦሪት ስለ እርሱ «አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ»[2] የተባ ለው ምትሐት ነውን? ዳግመኛ ስለ እርሱ በመዝሙር «ከሆድህ ፍሬ በመንበርህ ላይ አስቀምጣለሁ ብሎ እግዚአብሔር ማለ፡ አይጸጸትም» የተባለው ምትሐት ነውን?[3] ስለ እርሱ በኢሳይያስ አፍ «ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፣ ከሥሩም ቁጥቋጦ ያፈራል» የተባለው ምትሐት ነውን?[4] ዳግመኛ «እነሆ! ባሪያዬ ያስተውላል፡ ክብሩ ከፍ ይላል፡ ስለ እርሱ አሕዛብ

1. መንክዮን /መንክዮስ/ የክርስቶስ ሥጋ ምትሐት እንጂ የሰው ሥጋ አይደለም በማለት የኑፋቄ ትምህርት ያስተማረ ነው:: ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ግን የሐጸ÷ጸን በመጥቀስ ረትተውታል::
2. ዘፍ. ፫ ፥ ፳፪::
3. መዝ. ፻፴፩ ፥ ፲፩::
4. ኢሳ. ፲፩ ፥ ፩::



www.ethiopianorthodox.org

ያደንቃሉ፡፡» የተባለው ምትሐት ነውን? እንደገና ስለ እርሱ «ለዳዊት ቀንድ አበቅላለሁ [ሥልጣን እሰጣለሁ] ለመሲሐየም መብራትን አዘጋጃለሁ፡፡» የተባለለት ምትሐት ነውን?[5]

ስለ እርሱ «እነሆ! ድንግል ትፀንሳለች፡ [ወልድን] ትወልዳለች፡ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች፡፡» የተባለለት ምትሐት ነውን? እንደገና ስለ እርሱ ወንጌላዊው ማቴዎስ «የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ» ያለው ምትሐት ነውን? ዳግመኛ ስለ እርሱ ወንጌላዊው ዮሐንስ «ቃል ሥጋ ሆነ፡ በእኛ አደረ» አለ፡ ምትሐት ነውን? እንደገና ስለ እርሱ ጳውሎስ ከዳዊት ዘር በሥጋ መጣ አለ፡ ምትሐት ነውን? እንደገና ራሱ «እውነትን ስለ ነገርኳችሁ ትገድሉኝ ዘንድ ትወዳላችሁ» ያለው ምትሐት ነውን? «ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፡ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ ሞትን አይቀምሰውም» ያለው ምትሐት ነውን? ዳግመኛም «ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና» ያለው ምትሐት ነውን? እንደገና «የወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም» ያለው ምትሐት ነውን? ዳግመኛም «ይህ የምሰጣችሁ ኅብስት ሥጋዬ ነው፡ ይህም የምሰጣችሁ ጽዋ ደሜ ነው» ያለው ምትሐት ነውን? እንደ ገና «አብ ሕያው እንደ ሆነ እኔም ስለ አብ ሕያው ነኝ፡ ሥጋዬን የበላ ስለ እኔ ሕያው ይሆናል፡፡» ያለው ምትሐት ነውን? ዳግመኛ «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፡፡ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው፡፡» እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ያላቸው ምትሐት ነውን? «እንካችሁ ብሉ ፡ይህ ስለእናንተ የሚቆረስ ለብዙዎች ቤዛ [ለቤዛ ብዙኃን] የሚሰጥ ነው» ያለው ምትሐት ነውን? «ይህ ጽዋ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው ወስዳችሁ ጠጡ» ያለው ምትሐት ነውን? «አባቴ ቢቻልስ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ ነገር ግን አንተ እንደ ምትወድ ይሁን» ያለው ምትሐት ነውን? «መንፈስ ይወዳል [ይፈቅዳል] ሥጋም ይደክማል» ያለው ምትሐት ነውን?[7]

ሰሚ ናዝሬት በሚባል አገር ወንድ ከማያውቅ ከንጽሕት ድንግል በተበርኤል ብሥራት ሰው የሆነው ምትሐት ነውን? በቤተልሔም የተወለደው በስሎሚ እጅ የተዳሰሰው ምትሐት ነውን? በጨርቅ የተጠቀለለው

5. የሐ. ፲፱ ፡ ፴፡፡
6. መዝ. ፻፴፩ ፡ ፲፯፡፡
7. ኢሳ. ፯ ፡ ፲፬፡ ማቴ. ፩ ፡ ፩፡ ዮሐ. ፩ ፡ ፲፬፡ ሮሜ. ፩ ፡ ፬፡ ዮሐ. ፰ ፡ ፵፩፡ ዮሐ. ፮ ፡ ፶፩፡ ዮሐ. ፮ ፡ ፶፯-፶፰፡





በግርግም የተኛው ምትሐት ነውን? እንደ ሕፃናት ሥርዐት ጡት ለመጥባት አፉን የከፈተው፡ በስምንተኛው ቀን ለግዝረት የወሰዱት ምትሐት ነውን? በሕፃናት ሥርዐት እየተከላተፈ ቀስ በቀስ ያደገውና ባደገ ጊዜ በዕብራይስጥ ቋንቋ እንደ እናቱ ሕዝብ ነገድ አፉን የፈታው ምትሐት ነውን? ከቀራጮች ጋር ተቀምጦ ከኃጢአተኞች ጋር የበላው [የተመገበው] ምትሐት ነውን? የኢያኢሮስን ልጅ እጇን ይዞ «ጣቢታ ተነሺ» ያላት የመበለቲቱን ልጅ የአልጋውን ሸንኮር በዳሰሰ ጊዜ ከሞት ያስነሣው ምትሐት ነውን? በደንቆሮው ጆሮ ውስጥ እፍ በማለት «ተፈታ» [ተከፈት] ያለው ምትሐት ነውን?[8]

ዳግመኛ ምራቁን ከጭቃ ጋር በመቀባት ለበርጤሜዎስ ልጅ ለጤሜዎስ አስቀድሞ ዐይን ሳይፈጠርለት ዐይኖችን የፈጠረለት ምትሐት ነውን? ዘማዊቷ ሴት እግሮቹን በእንባዋ ያጠበችለትና ያበሰችለት የአልዓዛር እኅት በራሱ ላይ የቢልቃጥ ሽቱ የቀባችው ምትሐት ነውን? ስለ አልዓዛር ያለቀሰ «ወዴት አኖራችሁት?» ያለው ከዚህ በኋላ ጠርቶ እንዳ ልሞተ በሕይወት ያስነሣው ምትሐት ነውን? በሰው መጠን ደክሞት ያለበው፡ እንደ ነዳይ ተርቦ የተጠማው ምትሐት ነውን? በሊቀ ካህናቱ አሽከሮች ተይዞ እጆቹን እንደ ሌባ ያሠሩት ምትሐት ነውን? በሰቃልያን አደባባይ በዘንግ ራሱን የተመታውና ፊቱን ጉንጩን በጥፊ የተመታው ምትሐት ነውን? የእሾህ አክሊል ተቀዳጅቶ በመኩንን ጅራፍ የተገረፈው ምትሐት ነውን? ጭፍሮች ይዘው መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ መካን የወሰዱት ምትሐት ነውን? በብረት ቅንዋት እጆቹንና እግሮቹን ተቸንክሮ በመስቀል ግንድ የተቸነከረው ምትሐት ነውን? ወደ አባቱ፣ «አባት ሆይ! ነፍሴን ወደ አንተ አማፅናለሁ» ብሎ ነፍሱን የሰጠው ምትሐት ነውን? ነፍሱን ወደ ሥጋው መልሶ በመለኮቱ ኀይል የተነሣው ምትሐት ነውን? ይህን ሁሉ ማድረግ ይችላል[9]

ሰነፉ ሆይ! ከነቢያትና ከሐዋርያት መጻሕፍት የለተምንልህ ምስክር አይበቃህምን? ተጨማሪ ብትፈልግም ወንጌላዊው ማቴዎስ የተናገረው የእውነት ምስክር አለኝ፡፡ «ከሌሊቱም በአራተኛው ክፍል በባሕር ላይ

8. ሉቃ. ፩ ፡ ፳፮-፳፰፡ ሉቃ. ፪ ፡ ፯፡ ሉቃ. ፪ ፡ ፵፩፡ ሉቃ. ፲፱ ፡ ፩፡ ማር. ፩ ፡ ፵፩፡ ማር. ፯ ፡ ፲፡፡
9. ዮሐ. ፱ ፡ ፯፡ ሉቃ. ፯ ፡ ፴፱፡ ዮሐ. ፲፩ ፡ ፴፱ ፵፡ ዮሐ. ፱ ፡ ፯፡ ማቴ. ፳፩ ፡ ፲፡ ዮሐ. ፲፱ ፡ ፲፱፡ ዮሐ. ፲፱ ፡ ፳፡
ሉቃ. ፳፫ ፡ ፳፮፡ ሉቃ. ፳፫ ፡ ፵፯፡፡



www.ethiopianorthodox.org

እየሔደ ወደ እነርሱ መጣ፡፡ ደቀ መዛሙርቱ በባሕር ላይ ሲሔድ ባዩት ጊዜ ምትሐት ነው ብለው ታወኩ፡፡ የታያቸው መንፈስ መስላቸው፡፡ ከፍርሃትም ማስፈራት የተነሣ ጮኹ፡፡ ወዲያውም ኢየሱስ ተናገራቸውና እመኑ አይዞአችሁ፣ እኔ ነኝ አትፍሩ አላቸው፡፡»[10] ወንጌላዊው የክርስቶስ ሥጋ ምትሐት ቢሆን የታያቸው ጋኔን መስላቸው ባላለ ነበር፡፡ ስለምን ምትሐት መሰላቸው? የሌሊቱ ግርማ የሚያስፈራ ስለሆነና በባሕር መንገድ ላይ መራመድ ለሰው ልጅ የማይገባው ነውና የምትን ቀሳቀስ ሥጋ በባሕር ላይ በተመለከቱ ጊዜ ፈሩ፡፡ እርሱ ጌታ ኢየሱስ እንደ ሆነ አላወቁምና እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ በውቀውት ፈሩ፡፡

ምትሐት ማለት በየራሳቸው አምሳል መታየት ማለት ነውና፡፡ ሥጋ ሳይኖራቸው ሥጋ ያላቸው መስለው ይታያሉ፡፡ እንዴ ይታያሉ፥ እንዴም ይሰወራሉ፡፡ መታየታቸውም እንደ ደመና ጥላ የማይዳሰስ ነው፡፡ የብርሃን መላእክትም ግዘፍ ነስተው ሕፃናት ሳይሆኑ በሕፃናት አምሳል ይታያሉ፡፡ ሽማግሌ ሳይሆኑ በሽማግሌ አምሳል ይታያሉ፡ የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንደ ደረሳቸው በተላኩበት ቦታ ለሰው ይታያሉ፡፡ የምስጋና መላእክት ናቸውና የብርሃን ማዕተብ አላቸው፡፡ በራእይም ሆነ በሕልም የሚያዩቸው በልቡ በደስታ ይዘላል፡፡ የስሕተት መናፍስት ግን ጥላቸው በሰው ላይ ባረፈ ጊዜ ሰውን ለሕመም ይዳርጋል፡፡ በራእይም ሆነ በሕልም ሰው ቢያያቸው የሰው ልብ ይደነግጣል፡፡ ነፍስ ጠላቷን ስለ ምታውቅ ትፈራዋለች፡ የጥፋት መላእክት ናቸውና፡፡

ጌታችን ከቅድስት ድንግል የነሳው ንጽሕት ሥጋ ግን ከአዳም ሥር የተገኘች የአበው ሥጋ ነች፡፡ ከአዳም ጠባይ [ሥጋ] በስተቀር የመለኮት ትስብእት ጭማሪ የለበትም፡፡ ዳግመኛም ከኃጢአት ጉዳና በስተቀር ከአዳም ጠባይ ጉድለት የለውም፡፡ እንደገና ጌታችን ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ታያቸው ከሁሉ የሚበልጥ ምስክር አለኝ፡፡ ወንጌላዊው ሉቃስ፡- «ይህንም ሲነጋገር ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸው ቆሞ፣ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው፡፡ ነገር ግን ደነገጡና ፈሩ፡፡ መንፈስ ያዩ መስላቸው፡፡ እርሱም፡- ስለምን ትደነግጣላችሁ? ስለምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፡ በእኔ እንደ ምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው፡፡

10. ማቴ. ፲፬፥፳፮-፳፯፡፡



www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፈ ምስጢር

ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው፡፡»[11] የዚህን ቃል ንባቡን በመከተል ትርጉሙ እንደሚታወቅህ አጠናቅቃለሁ [አረጋግጣለሁ]፡፡

ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ «መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እንደ ምታዩኝ አለሁ» አለ፡፡ ይህም ማለት በምትሐት የታየኋችሁ በጽላሎተ መንፈስ የምናገራችሁ አይምሰላችሁ ማለት ነው፡፡ ምትሐት ይታያል እንጂ አይዳሰስምና፡፡ «መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና በእኔ የሚዳሰስ ሥጋና የሚዳሰስ ዓፅም» እንዳለ ዳሳችሁ ዕወቁ፡፡ ከዚህ በኋላ በቅንዋተ መስቀል የተቸነከሩ እጆቹንና እግሮቹን በወታደር ጦር የተወጋውን ጐኑን አሳየቸው፡፡

«የክርስቶስን ትስብእት የምትሐት መድኃኒት ነው» የምትል መንክዮስ ሆይ! አፈርክ [ታፍራለህ]፡፡ እነሆ! እርሱ ራሱ ሥጋና አጥንት አለኝ ብሎ ሃይማኖትህን አጉደለ፡፡ እኛ ግን ክርስቶስ ፍጹም እንደ አባቱ እግዚአብሔር እንደ ሆነና እንደ እኛ ፍጹም ሰው እንደ ሆነ እናምነዋለን፡ ለእኛም ሃይማኖታችን፣ ጥምቀታችን፣ ቤተ ክርስቲያናችን ፍጽምት ናት፡፡

እመቤታችን በሩካቤ እንዳልተወለደች የሚናገሩ አሉ፡፡ መልአኩ «እነሆ ትፀንሻለሽ፥ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ» ብሎ ባበሠራት ጊዜ ራሷ የደነቀችውን እንዴት በሩካቤ አልተወለደችም ይሏታል? ድንግልም መልአኩን «ወንድ ሳላውቅ እንዴት ይሆንልኛል?» አለችው፡፡ እናቷ ያለ ሩካቤ ፀንሳት ቢሆን ግን «ወንድ ሳላውቅ እንደ ምን ይሆንልኛል ባላች ነበር፡፡[12] የዳዊት ሴት ልጅ [ድንግል] ያልተለመደ የፅንስ ዜና ሰምታ አደነቀች፡፡ ከዚህም በኋላ መልአኩ እንዲህ አላት፡- «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኀይል ይጸልልሻል፡ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል አላት፡፡ ያንጊዜ ድንግል እነሆኝ የጌታ ባሪያ፥ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች፡፡»[13] ይህን ቃል ከማለት ጋር እንደ ተናገራት ሆነላት፡፡ ከገብርኤል ቃል ጋር የማይታይ ኀይል በጆሮዋ መስኮት ገብቶ የዚህ ዓለም ኃጢአት ያልነካው በማሕፀኗ አደረ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል፣ [ተዋሐደ] ንጹሕ ቃል ወደ ንጽሕት ሥጋ አደረ፡፡ የማይዳሰስ እሳት በሥጋ መጐናጸፊያ ተጠቀለለ፡፡ ራሱ በመወለጃ ማሕፀን ተሣለ፡፡ ስለ እርሱ መሣልን የሚፈቅድ የለም፡፡

መላእክትን በእሳትና በነፋስ ጠባይ፥ የሰውን ልጅ በሥጋና በደም ጠባይ

11. ሉቃ. ፳፬፥፴፯-፴፱፡፡
12. ሉቃ. ፩፥፳፩፡፡
13. ሉቃ. ፩፥፴፭፥ ፴፰፡፡

የሚያሥል ለራሱ ከድንግል ማሕፀን ሥጋን ሠራ [ሸመነ] እንግዲህ ድንግል ከእናቷ ያለ አባት ሰው መሆን በየት ቻለች? ሰውን ፈጣሪ አይደለችምና:: እርሱ ግን የሰው ልጅ ፈጣሪ ነውና ከድንግል ማሕፀን ለራሱ ሥጋ ሥራ[14] እንደ ፈቀደ ተጠበበ:: ያሰበውን ለማድረግ የሚከለክለው የለም:: «ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፣ ከሥሩም ቁጥቋጥ ያፈራል::»[15] ተብሎ እንደ ተጻፈ ከኢያቄም ዘንድ በሐና ማሕፀን ውስጥ የሆነች ያለ መውለጃ ዘር ከቅድስት ድንግል በስተቀር ከግንድ በትር መውጣት ምንድነው? የማርያም አባት ኢያቄም የእሴይ ዘር ነውና:: ዳግመኛ ከግንድ የአበባ መውጣት ከልጅ የመለኮት ሥጋዌ በስተቀር ምንድን ነው? ያለ ሩካቤ ትውልደው ዘንድ በድንግል ማሕፀን ልጅን ለላከ ለአብ ምስጋና ይገባል:: በሩካቤ ከተወለደች ያለ ሩካቤ ለተወለደ ለወልድ ስግደት ይገባል:: ያለ ሩካቤ ትወልድ ዘንድ ለይቶ ላጸናት ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል:: ምሕረትና ሰላም ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን:: ለዘላለም አሜን:: የመድኅንን ትስብእት ምትሐት ብሎ የተናገረ የመንክዮስ ዘለፋ ተፈጸመ:: የቤተ ክርስቲያንን ቅጽር ከሚጠብቁ ይልቅ ደካማ አገልጋይ የምሆን፣ ምእመናን ያገኙትን የጥምቀት ልጅነት የተጐናጸፍኩ፣ የንጹሐን ሐዋርያት ትምህርት ልጅ የምሆን፣ የናዘራውያን ሃይማኖት ተሳታፊ የሆንኩ እኔ ምስኪኑ ጊዮርጊስ አጻፍኩት::

14. ሥጋን በማሕፀኗ ፈጥሮ ተዋሐደ እንጂ ለ/ሃይማኖተ አበው ዘኢሬቅሊስ/
15. ኢሳ. ፲፩፥፩::





# [ምዕራፍ ፳]

## የስቅለተ ዓርብ የንዋም ምንባብ

ከውጭ ያለውን ወደ ውስጥ የሚያስገባ፣ ሸንበቆውን አጽንቶ ጠንካራውን እንጨት የሚያፈርስ፣ የፀሐይንና የጨረቃን ጉዞ ወደ ሰሜንና ምሥራቅ መካከል የሚመልስ፣ የማትታየውን የሰውን ልጅ ነፍስ በእጅ የሚነጥቅ፣ ዳግመኛ በትንሣኤ ሙታን ጊዜ ወደ ሥጋ ማደሪያዋ የሚመልስ፣ በሁሉ ላይ ለዘላለም የሠለጠነ ነውና በሦስትነቱ በማይለያይ በእግዚአብሔር ስም እንጀምራለን::

«በነፍስና በሥጋ ወደ ሲኦል ወረደ» የሚሉ የመናፍቃን የአሲስን[1] ዘለፋቸውን እንናገር ዘንድ ከክፋት እንቅልፍ ራሳችንን እናንቃ:: ምክርንና ማስተዋልን ያጣችሁ ሰነፎች ሆይ! ስለዚህም የስሕተታችሁ ስንፍና የመጻሕፍት ምስክርነት ይፈቅዳልን? የእግዚአብሔርን ልጅ ሞተ ትሉታላችሁ ወይስ አልሞተም ትሉታላችሁ? አስቀድማችሁ ንገሩን፤ ሞተ ካላችሁት ግን እንዴት በሥጋና በነፍስ ወደ ሲኦል ወረደ ትላላችሁ?

በነፍስና በሥጋ ሕያው ሆነው ወደ ሲኦል የወረዱ ግን ዳታንና አቤሮን ናቸው::[2] የወረዱትን ምድር አፏን ከፍታ ዋጠቻቸው አልሞተም ብትሉ ትንሣኤን ካዳችሁ:: ሞት ከሌለ ትንሣኤ የለም:: ትንሣኤ ከሌለ ዕርገትም የለም:: ዕርገት ከሌለ በአብ ቀኝ መቀመጥም የለም፤ ለምእመናንም ተስፋ የለም፤ የነቢያትን ትንቢት አሳበላችሁ፤ የሐዋርያትንም ትምህርት ሻራችሁ [አፈረሳችሁ]:: ሥጋው ወደ ሲኦል ከወረደ የኀኔ አውርዶ ይቀብረው ዘንድ ወደ ጲላጦስ ስለ ማን ሥጋ ለመነ? ኒቆዲሞስ የማንን በድን በበፍታ ጠቅልሎ ወደ መቃብር ጨመረው? «ነፍሱ ከሥጋው አልተለየም» ብትል ግን ወንጌላዊው «ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ <ተፈጸመ> አለ:: ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ::» ያለውን ካድክ::[3] ኹለተኛው ወንጌላዊም- «ወደ አባቱ ነፍሱን አማፀነ:- አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ ብሎ ሞተ::» አለ::[4] ማቴዎስ «ኢየሱስ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ነፍሱን ተወ::

1. ክርስቶስን በነፍስና በሥጋ ወደ መቃብር ወረደ የሚሉ መናፍቃን::
2. ዘኍ. ፲፮ ፥ ፩–፴፫ ዘዳ.፲፩ ፥ ፮::
3. ሉቃ. ፳፫ ፥ ፵፮::
4. ማቴ. ፳፯ ፥ ፶::



www.ethiopianorthodox.org

ወዲያውም መንፈሱ [ነፍሱ] ወጣች::» ዮሐንስም «ራሱን አዘንብሎ ነፍ ሱን አሳልፎ ሰጠ» አለ።[5] እነሆ! በአራቱ ወንጌላውያን እጅ የነፍሱ መውጣት ተጻፈ:: የነፍሱን ከሥጋው መውጣት ትክድ ዘንድ እንዴት ይቻልሃል::

ነፍሱ ግን ከሥጋው ወጥታ ከመለኮቱ ኀይል ጋር ወደ ሲኦል ወረደች:: በዘጠኝ ሰዓት የጻድቃን ነፍሳት ወጥተው በዕፀ መስቀል ላይ «ፈጽመህ እመን፡ ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትኖራለህ::» ብሎ ቃል ኪዳን ከሰጠው ከፈያታዊ ዘየማን ነፍስ ጋር ወደ ተድላ ገነት ገብተዋል።[6] በመዝሙሩ ቃል፦ «ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውምና የሕይወትን መንገድ ዐሳየኸኝ፡ ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገበኸኝ፡ በቀኝህም የዘላለም ፍሥሐ አለ» ያለውን ሐዋርያት እንደ ተረጐሙት አበውነቢያት ግን በነፍሳቸው በሲኦል ነበሩ:: በሲኦል በነበሩም ጊዜ ነፍሳቸው ከሥጋቸው ጋር አይደለም:: ከተቀበላችሁን ቀዳሚው አባት ዳዊት ሞቶ እንደ ተቀበረ፡ መቃብሩም በእኛ ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ እንዳለ እንነግራችኋለን::

እንግዲህ ሰነፎቹ ሆይ! ሐዋርያት «የዳዊት መቃብር እስከ ዛሬ ድረስ በእኛ ዘንድ አለ፡»[7] እንዳሉ ስሙ፡ አድምጡ:: ስለ ዳዊት መቃብር ሐዋርያት ምክንያት ከሰጡት እኛም እንደ እርሱ በምድረ ከነዓን በኬጥያዊው ኤፌን እርሻ በተሰወረ ቦታ የተቀበሩ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብን እናምጣልህ? የዮሴፍም አጥንቶች በዚያ ተጨመሩ:: ሙሴም በሞ ኣብ በናባው ተራራ በብዔል ፌጎር ቤት አጠገብ ሞቶ ተቀበረ:: አሮንም በሆር ተራራ በዔዶም ምድር አጠገብ፣ ዳዊትም በቤተ ልሔም፣ ኢሳይያስና ኤርምያስ በይሁዳ ምድር፣ ዳንኤልና ሕዝቅኤል በምድረ ባቢሎን፡ ሠለስቱ ደቂቅ በከለዳውያን ምድር በናቡከደነጾር መቃብር አጠገብ፡ ኤልሳዕም በሰማርያ ተራራ፡ ሌሎችም ነቢያት የእግዚአብሔር ፈቃድ በለየላቸው ቦታዎች የተቀበሩ አሉ:: ስለ እነርሱ የሚነግረኝ አጣህ:: የሁላችን አባት አዳምም በኢልዳ ምድር ተቀብሯል:: ይኸችውም የፍጥረቱ ቦታ ናት:: በእግዚአብሔር ፈቃድ በመቃብሩ ላይ ዕፀ መስቀል ተተክሎ፣ የአብ መሲሕ ደምና ከተወጋ ጐኑ የወጣ ውሃ በላዩ ላይ ፈሰሰ:: ከእግዚአብሔር መሲሕ ጐን የፈሰሰው ውሃ ግን ወደ ዐቢይ ክርስቲያንነት ያስገባው ዘንድ በአዳም ላይ ፈስሶ አጠመቀው:: ወደ መቃብሩ የተመለሰው የመለኮቱ ደም ለሐዲስ ኪዳን የቍርባን ምስጢር ሥርዐት ሆነ:: በድን ካህን [ነፍስ የተለየችው ሥጋ] በወታደር ጦር ጐኑን ተወጋ::

ከጐኑ በፈሰሰው ውሃ የጥንት በድኖችን አጠመቃቸው:: የምእመናን በድኖች ከመቃብር ወጥተው ሰቃልያንን ዘለፏቸው:: በድኑ ካህን [ነፍስ የተለየችው ሥጋ] በመለኮቱ ደም በድኖቻችንን አሳተፋቸው:: የምእመናን በድኖች በተቀደሰ ምስጢሩ በድኑ ካህን [ነፍስ የተለየችው ሥጋ] የካህኑ በድን በመስቀሉ ጥላ አማተባቸው:: የምእመናን በድኖች የጸጋ ማዕተብ ተቀብለው [ይዘው] ወደ ቅድስት አገር ገቡ:: በኢየሱስ ክርስቶስ የምስጢር ሥርዐት በቀራንዮ ተደረገ:: ራሱ መሥዋዕት [ቁርባን]፥ መስቀሉ መሠዊያ ነው:: ራሱ ካህን ሲሆን ሥጋው የሕይወት እንጀራ ነው:: ራሱ በግ ሲሆን ደሙ ወይን ነው:: ራሱ በድን [ነፍስ የተለየው ሥጋ] ሲሆን መለኮቱ ሕያው ነው:: እርሱ የተገረፈ ሲሆን መለኮቱ አልተነካም፡ በመቃብር ውስጥ ሳለ ከበድን ሥጋው [ነፍስ ከተለየው ሥጋ] በፈሰሰ ደሙና ውሃ ሕይወት አደረጋቸው:: በሲኦል ውስጥ ላሉት በነፍሱ ነጻነትን ሰበከላቸው:: በጦር የወጓት ቅድስት ሥጋው ግን በአዲስ ከፈን ሲገንዟት ተንቀሳቅሳ አልተነፈሰችም፡ ከነፍሱ ህላዌ ተራቁታለችና [የተራቆተች] ሆናለችና:: ነፍሱ ከሥጋው ጋር ወደ መቃብር እንዳልገባች እንደዚሁ ሥጋው ወደ ሲኦል አልወረደችም::

ሥጋው ከነፍሱም ጋር ወደ ሲኦል ወረደች፡ ወደ መቃብርም ያለ ነፍስ ገባች» ብትል እኔም ለሥጋዌ /ለሥጋው ቃል/ በኹለት ገጸ መኾን [በኹለት የመገለጫ ሥፍራ፡ ሁኔታ] አንድ ጊዜ ነፍስ የተለየችው ሥጋ በመሆን አንድ ጊዜም [ሌላ ጊዜ] በሕይወት መንፈስ [በነፍስ] ይታይ ዘንድ መንታነት አለውን? እልሃለሁ::

ዘንጋው ሆይ! ለክርስቶስ አንዱ የሚሞት አንዱ የማይሞት ሥጋ እንደ ሌለው እመን:: እስኪ ጴጥሮስ «በአዳም አካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወረደ» አለ::[9] ሰነፉ ሆይ! በሥጋው ነፍስ [አካለ ነፍስ] እንጂ በሥጋው እንዳላለ አስተውል:: በሥጋው ነፍስ [አካለ ነፍስ] ማለት ግን በአዳም ሥጋ ዘንድ በነበረች ነፍስ ማለት ነው:: «የአዳም ሥጋ ግን ከአዳም

5. ዮሐ ፲፱፥፴::
6. ሉቃ ፳፫፥፵፫::
7. መዝ ፲፮፥፲::
8. ዘፍ ፳፭፥፰ ፲::

9. ፩ኛ ጴጥ. ፫፥፲፰–፲፱:: ሊቁ ጳውሎስ ብሎ የጠቀሰው የጴጥሮስ መልእክት በመሆኑ ጥቅሱ ለቅዱስ ጴጥሮስ ተሰጥቶ ተተርጉሟል::

www.ethiopianorthodox.org

ልጅ የነገው የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ነው:: ጌታ «በሥጋ» በወረደ ጊዜ አሩቅ ብእሲ መስሎት መዋቅ እንደ ለመደ ቀረበው በሚለው በመጽሐፈ ኪዳን በተጻፈው ቃል የሳቱ ብዙዎች ናቸውና::

መልአከ ሞት በእርሱ ላይ የመለኮቱን ኀይል በተመለከተ ጊዜ ጮኸ:: ሥጋን ተዋሕዶ ከሥልጣኔ ያሸነፈኝ ይህ ማን ነው? ሥጋን የተዋሐደ ይህ ማነው? እርሱስ ሰማያዊ ነው::[10]

ልባቸው የጠፋ በሥጋ ወደ ሲኦል ስለ መውረድ ይህን ተረጐሙ:: ትርጉሙ ግን እንደዚህ አይደለም፡ አስቀድሞ ስለ መለኮቱ «እኔና አብ አንድ ነን» ብሏልና::[11] ዳግመኛ ስለ ትስብእቱ «አባቴ ቢቻልስ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ» አለ::[12] እነሆ ከመለኮት ክብር ወደ ትሕትና ትስብእት የቃልን መውረድ «አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ» ብሎ ደገመ::[13] ዳግመኛም «አብ ሕያው እንደ ሆነ እኔም ስለ አብ ሕያው ነኝ::»[14] ይህን ያለው ራሱን ከአባቱ ጋር ስለ መለኮቱ ክብር ሲያስተካክል ነው:: በትሕትና ቃል በትስብእት ጉዳና «አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውኸኝ?» አለ::[15] መልአከ ሞት ይህን በሰማ ጊዜ መዋቅ እንደ ለመደው ቀረበው:: መዋቅ የለመደው ለሲኦል ከሰጣቸው ከጻድቃን ነፍስ በስተቀር ምንድን ነው? ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በጅራፍ ተገርፎ ቆስሎ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በተመለከተው ጊዜ መዋቅ እንደ ለመደው ቀረበው:: «አባቴ ቢቻልስ ይህቺ ጽዋ ከእኔ ትለፍ» ባለ ጊዜ «እኔና አብ አንድ ነን» ያለውን ቃል ረሳ::

ዕሩቅ ብእሲ መስሎት መዋቅ እንደለመደ ቀርቦ ተመለከተው:: «አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውኸኝ?» ሲል በሰማው ጊዜ «አብ ሕያው እንደ ሆነ እኔም ስለ አብ ሕያው ነኝ» የሚለውን ቃል ረሳ:: ዕሩቅ ብእሲ መስሎት መዋቅ እንደለመደ ቀረበው:: መከራውን በመስቀል ላይ በተመለከተ ጊዜ በድውያን ላይ ያደረገውን ተአምራቱን ረሳ:: መዋቅ እንደ ለመደው ቀረበው:: በዚህ ቀጣው:: የመለኮት ክብር ወደ ሥጋ ትሕትና ተዋርዶ በተመለከተ ጊዜ መዋቅ እንደ ለመደው ቀረበው:: ነፍሳትን

10. ትምህርተ ኅቡአት
11. ዮሐ. ፲ ፥ ፴::
12. ማቴ. ፳፮ ፥ ፴፱::
13. ማቴ. ፲፯ ፥ ፭::
14. ዮሐ. ፮ ፥ ፶፯::
15. ማቴ. ፳፯ ፥ ፵፮::



www.ethiopianorthodox.org



መዋጥ የለመደው የጻድቁን ነፍስ ለመዋጥ አፉን ከፍቶ ሳለ የእሳት ፍን ጣሪ ከመለኮቱ የፍላፃ ቤት ወጥቶ መዋጥ ከለመደው ጉሮሮ ውስጥ ገባ:: ከዚህ በኋላ መልአከ ሞት፡- «ሥጋን ተዋሕዶ እኔን ከሹመቴ የሻረኝ ይህ ማን ነው? «ሥጋን የለበሰ፥ [የተዋሐደ] ይህ ማን ነው?» ብሎ ጮኸ:: እነሆ! አሸናፊ ተሸነፈ፥ አሥጋቸው የሚቀበል እርሱ [ኢየሱስ ክርስቶስ] ሆኗልና:: የመለኮት ኀይል [ገንዘቧ ከሆነ] ከኢየሱስ ክርስቶስ ነፍስ ብስተቀር በዚያ ካሉት ነፍሳት አንዷት እንኳ [መልአከ ሞትን] ያሳመመችው ነፍስ አልነበረችም:: ስለዚህ መልአከ ሞት «እርሱስ ሰማያዊ ነው» ብሎ ጮኸ:: የቀደምት ነቢያትንም ነፍሳቸውን ይቀበላል:: በድኖቻቸው ግን ለመቃብር መታሰቢያ ይቀራሉ::

አዳኙ ታደነ፣ አሥጋሪው ተሠገረ:: የጻድቃንን ነፍሳቸውን ከጌታንም ወደ ዐጸደ ዲይን ነፍሱን ይጨምራት ዘንድ በመለኮቱ ኀይል በሚያቃጥል ቅጣትም አሳመመው:: በዚያ የነበሩ የጻድቃንን ነፍስ በረበረ:: ከዚያም አውጥቶ ወደ ገነት በምሽት አስገባቸው:: አዳም በዕለተ ዓርብ በስባተኛው ዓመት እንደ ወጣ እንደዚሁ በምሽት በዕለተ ዓርብ ሩሲክ ወደ ገነት ገባ:: ከገነት ስለ መውጣቱ የጸናች አሪት፡- «ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፥ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር አምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ:: እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ ወዴት ነህ? አለው:: እርሱም አለ፡- በገነት ድምፅህን ሰማሁ፥ ዕራቁቴንም ስለሆንሁ ፈራሁ፥ ተሸሸግሁም:: እግዚአብሔርም አለው:: ዕራቁትህን እንደ ሆንህ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን? አዳምም አለ፡- ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ:: እግዚአብሔር አምላክ ሴቲቱን ይህ ያደረግሽው ምንድን ነው? አላት:: ሴቲቱም አለች፡- እባብ አሳተኝና በላሁ:: እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ:: በሆድህም ትሔዳለህ፣ አፈርንም በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ትበላለህ፥ በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ:: እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል:: አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ::[16] እግዚአብሔር አምላክም አዳምና ሔዋንን ከገነት ተድላ አወጣቸው::

16. ዘፍ. ፫ ፥ ፲፰::

በዚህም አዳም በምሽት ከገነት እንደ ወጣ ዐወቅን። በዘጠኝ ሰዓት ጌታችን ፈያታዊ ዘየማንን «ፈጽመህ እመን ከእኔ ጋር በገነት ትኖራለህ።» አለው።[17] በዚያች ሰዓት የጌታችን ኢየሱስ፣ ነፍሱ ወጣች። በዮሐንስ ወንጌል እንደ ተጻፈ የፈያታዊ ዘየማን ጉልበቱን በሰበሩ ጊዜ በዐሥራ አንድ ሰዓት ነፍሱ ወጣች። በዘጠኝ ሰዓት የመድኀኒታችን ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዳ የአዳምንና የልጆቹን ነፍስ አውጥቶ በዐሥራ አንድ ሰዓት በመስቀል ላይ ኪዳን በሰጠው ከፈያታዊ ነፍስ ጋር ወደ ገነት አስገባቸው።

የእግዚአብሔር የምሕረቱ በር ተከፈተች። ከኪሩቤል እጅ የእሳት ሰይፍ ከሱራፌል እጅ የእሳት ጦር ቀረ የገነት ደጅ [በር] ተከፍቶ መንጋዎች ወደ መሰማሪያቸው ገቡ። ነቢያት ዓይነቱ የየራሱ የሆነ፣ መልኩ የየራሱ የሆነ አበባ፣ ሽታው የየራሱ ፍሬው የየራሱ የሆነ የዕፀዋት መዓዛን በተመለከቱ ጊዜ በደስታ ዘለሉ። እንደ ወተት ንጹሕ የሆነው የገነት ውሃም ከማር ወለላ ፈጽሞ ይጣፍጣል። አንዱ ወዲህ አንዱ ወዲያ ሲፈስ አንዱ በሌላው ላይ ሲመለስ ዐዩ። የሚያጽደለድል የሚያንጸባርቅ ውበትና የብርሃን ጉርፍ ዐዩ። በገነት ዕፀዋት መዓዛን በተመለከቱ ጊዜ የሐሴት ወንዞች በደስታ ሲጉርፉ [ሲፈሱ] ዐዩ። ሳይበሉ ጠገቡ፣ ሳይጠጡም ረኩ። የእግዚአብሔርን ክብር በማየት ሰከሩ፣ ወይን ከመጠጣት አይደለም። በጥበብና በማስተዋል ሰከሩ፣ ባለማስተዋል በመዘናጋት አይደለም።

አዳምና ነቢያት በሲኦል እንዳልነበሩ የሚናገሩ አሉ። ነቢያትን በሲኦል እንዴት አልነበሩም ይሉአቸዋል። ዳዊት ስለምን «ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውምና» አለ? «ነፍሴን በሲኦል አትተዋትም» አለ እንጂ «ነፍሴን ወደ ሲኦል አታውርዳት» እንዳላለ ዕወቁ።[18] ነቢዩ በመንፈስ ትንቢት ጌታችን በሲኦል ያሉ የነቢያትን ነፍስ ነጻ ያወጣ ዘንድ እንደሚወርድ ዐውቆ በመታመን ይህን ተናገረ። ስለዚህ ነፍሴን በሲኦል በዚያ ከታሰሩ፣ ከሚበዙ በጣዖት አምልኮ ከበደሉ ከአሕዛብ ነፍሳት ጋር በሲኦል ውስጥ አትተዋትም አለ። ስለዚህ ነቢዩ ከነቢያት ነፍሳት ጋር ከሲኦል መውጣትን ተስፋ አድርጎ ተደሰተ።

17. ሉቃ. ፳፫፥፵፫።
18. መዝ. ፲፭፥፲።



www.ethiopianorthodox.org



ከኃጥአን ነፍሳት ጋር በሲኦል እንደማይቀር ተናገረ። ጳውሎስም «ኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋው ከኃጢአትና ከፍትወት ጋር ሰቀሉት።» አለ።[19] ይህ የሐዋርያው ቃል ምንድን ነው? በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ፍትወት አለን? ኃጢአትስ በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ አለን? አባቴ ጳውሎስ ሆይ! ይህን የምሥጢር ቃልህን ተርጉምልኝ፣ ካልሆነ ግን በአንተ ላይ ያለው የጸጋ መንፈስ ይረዳኝ ዘንድ በላዬ ላይ ባርክ [በረከትህን አኑር]። «ኢየሱስ ክርስቶስን ከኃጢአትና ከፍትወት ጋር ሰቀሉት» ያለው ግን አዳምና ሔዋን አምላክ መሆን በመፈለግ ካደረጉት የተከለከለውን ዕፀ ከመብላት በስተቀር ፍትወቱ ምንድን ነው? ዳግመኛ ከገነት መውጣት እስከ ክርስቶስ ስቅለት ካደረጉት ከልጆቻቸው ኃጢአት በስተቀር ኃጢአቱ ምንድን ነው? ስለዚህ የአዳም ፍትወትና የልጆቹን ኃጢአት ተሸክሞ ወደ ዕፀ መስቀል ላይ ወጣ።

ያዕቆብ የሁለት ጠቦቶችን ለምድ በእጆቹ አድርጎ በላዩ ላይ ሽታ ያለው የዔሳውን ልብስ እንደ ለበሰ፣ የጠቦቶችን ለምድ በእጆቹ ያጠለቀው አባቱ በዳሰሰው ጊዜ ዔሳውን እንዲመስል እናቱ እንደ ተጠበበች፣ እንደዚሁ ጌታችን የዓለምን ኃጢአት በትከሻው አጥልቆ ወደ ዕፀ መስቀል ላይ በወጣ፣ ጊዜ በሥጋው ሕማማት አቃጠላት፣ ያንጊዜ «በአንተ የተነሣ ምድር እሾህና አሜከላ ታብቅል»[20] ብሎ እግዚአብሔር አዳምን በረገመው ጊዜ በአዳም ሥጋ ውስጥ የበቀለውን የኃጢአት እሾኽ ተቃጠለ። ያዕቆብ ፀጉር እንዳልነበረው ኢየሱስ ክርስቶስም ኃጢአት የለበትም። ያዕቆብ የጠቦቶችን ለምድ በእጆቹ እንዳጠለቀ እንደዚሁ የእግዚአብሔር ልጅም የራሱ ያልሆኑችውን የዓለም ኃጢአት ተሸከመ። ያዕቆብ መዓዛ ያለውን የዔሳውን ልብስ እንደ ለበሰ እንደዚሁ ጌታችን ኃጢአታቸውን በሚያስተሰርይበት ቦታ የነቢያትን መዓዛ ሽታ እግዚአብሔርን በሚያስባስብበት ቦታ የቅዱሳንን የጽድቃቸውን መዓዛ ለበሰ። ያዕቆብ ለአባቱ የወደደውን ምግብ እንደ አቀረበ እንደዚሁ ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱን መሥዋዕት ለአባቱ መዓዛው ያማረ የተወደደ ቍርባን አቀረበ። አባቱም «ያዕቆብን ለወንድምህ ጌታ ሾምኩት» እንዳለው[21] እንደዚሁ ክርስቶስም ለሐዋርያት አለቃ ሆናቸው። ያዕቆብ የእናቱን ወንድም የላባን ሴት ልጆች ይወስድ ዘንድ ብቻውን ወደ ሶርያ ምድር ወረደ። ሲመለስ ግን የኹለት ክፍል ሰራዊት እንደ ሆነ፣ እንደዚሁ ጌታችን የእናቱ ነገድ ሕዝብ የሆኑትን

19. ገላ. ፭፥፳፬።
20. ዘፍ. ፫፥፲፯።
21. ዘፍ. ፳፯፥፴፯።

አበውን ብቻውን ከሲኦል ያወጣቸው ዘንድ ወደ ሲኦል ወርዶ ሲመለስ ግን የኹለት ክፍል ሰራዊት ሆነ። አንዱ የሰራዊት ክፍል ከሙሴ ኦሪት እስከ ክርስቶስ ስቅለት የነበሩ ናቸው።

ቀደምት አበው ከአዳም እስከ ሙሴ ወደ ሲኦል ለምን ወረዱ? እግዚአብሔር አዳምን «የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝኩህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ።» «እሾህንና አሜኬላን ታበቅልብሃለች» ብሎ ረግሞታልና[22] ከመሬት ተወልዷልና በአዳም ኃጢአት ምድር ተረገመች። ይህ ግን በእናቱ ላይ በወጣ በይሁዳ መርገም ይመስላል። በመዝሙር «የአባቶቹ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ትታሰብ፤ የእናቱ ኃጢአት አትደምሰስ» ይላልና።[23] የአምላክ ደም ካልፈሰሰ በቀር በአዳም ኃጢአት ምክንያት የመጣው የምድር እርግማን አይሻርም። ከአዳም ልጅ የተወለደው ባሳመማት አዳናት፤ በረገማት ነፃ አዋጣት፤ ነጻ መውጣትን አደረገ።

ዳግመኛ ሙሴም በምድረ በዳ እባብን [የነሐስ እባብ] እስከ ሰቀለበት ጊዜ ድረስና ክርስቶስ በዕፀ መስቀል እስከ ተሰቀለበት ጊዜ ድረስ ለኦሪት ሕግ የተገዙ የእግዚአብሔር ነቢያት ወደ ሲኦል ለምን ወረዱ? ሙሴ በሕግ መጽሐፍ «በዚህ የሕግ መጽሐፍ ያለውን ቃል ያደርግ ዘንድ የማይቆም ሰው ሁሉ የተረገመ ይሁን» ይላልና ሕዝቡ ለዘላለም አሜን ፈጽሞ ይደረግ ይላሉ።[24] ስለ ዚህ በኦሪት ሕግ መጽደቅ የቻለ የለም፤ የታዘዘውን አልፈጸሙምና። ስለ ዚህ ጳውሎስ «መጽሐፍ ሁሉንም በኃጢአት ውስጥ ዘግቷልና» አለ።[25]

በአዳም ኃጢአት የተኰነኑትን የኃጢአታቸውን እሾኽና የክፉ ምግባራቸውን አሜኬላ በሥጋው ሕማም አቃጠለ። እነሱም ትእዛዙን አልፈጸሙምና በሙሴ የኦሪት ሕግ መጽደቅ አልቻሉም። ሙሴም ራሱ የተቀበለውን ትእዛዝ ተላልፎ ኢትዮጵያዊ ሚስትን አገባ። እግዚአብሔር የእስራኤል ልጆች የአሕዛብን ልጆች እንዳያገቡ፤ ልጆቻቸውንም ለአሕዛብ ልጆች እንዳይሰጡ፤ ሕዝቡን ከአባቶቻቸው አምላክ ኋላ እንዳያስከትሉአቸው አዟልና፤ በዚህ ኃጢአት የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ስቷል። ከአባቶቻቸው አምላክ በኋላ እስከ ሚያስከትሉት ድረስ ከአሕዛብ ነገሥታት ሁሉ ሴቶችን አግብቷል።

22. ዘፍ. ፫፥፲፯።
23. መዝ. ፻፰፥፲፬።
24. ዘዳ. ፳፯፥፳።
25. ገላ. ፫፥፳፪።



www.ethiopianorthodox.org



በሙሴ ላይ ግን ኢትዮጵያዊት ሴት ከማግባት በስተቀር አምልኮተ ጣዖት አልተገኘበትም። ስለዚህ ኃጢአቱ እንደ ሰሎሞን ኃጢአት ፍጹም አልሆነችም። ሊቀ ካህናቱ አሮንም የጥጃ ምስል ሠርቶ «እስራኤል ሆይ! እነሆ! አማልክቶቻችሁ» አለ።[26] የአሮንና የሰሎሞን ኃጢአት ከሙሴ ኃጢአት ይልቅ ጸናች። ሐዋርያው ዮሐንስ እንደ ተናገረው፦ «ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ። ስለዚያ [ይለምኑ] ይጠይቁ ዘንድ የምናገር አይደለም። ዐመፃ ሁሉ ኃጢአት ነውና። ሞትም የማይገባው ኃጢአት አለ። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን እንዳያደርግ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወለደው ራሱን እንዲጠብቅ ክፉውም እንዳይነካው ዕናውቃለን።»[27] እነሆ! ወንጌላዊው «ሞት የሚገባው ኃጢአት እንዳለ» ተናገረ። ስለ እርሱም ይጸልዩ ዘንድ አላዘዘ። ሞት ስለሚገባው ኃጢአት ግን መጸለይን አላስተማረም።

ጣዖት ከማምለክ በስተቀር ሞት የሚገባው ኃጢአት ምንድን ነው? ስለዚህ በመልእክቱ ፍጻሜ «ከአማልክት ተጠበቁ» አለ።[28] ስለዚህ የጸናች ኦሪት «በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ የሆነውን ምስልና ጣዖት የሚሠራ ሰው የተረገመ ይሁን።» ትላለች።[29] ዳዊትም በኦርዮ ሚስት በደለ። በጦር አለቃ በኢዮአብ ዘንድ የምታስገድል የጽሑፍ መልእክት ልኮ ኦርዮ በጠላት ጦር ሞተ። በዚህም ላይ የምትከብድ በደልን ጨመረ። በዚህም በነቢዩ አፍ «አንተ ይህን በስውር አድርገኸዋል። እኔ ግን ይህን በእስራኤል ሁሉ ፊትና በፀሐይ ፊት አደርገዋለሁ። ብሎ በዳዊት ላይ ፈጽሞ ተቆጣ። ዳዊትም «እግዚአብሔርን በድያለሁ» አለ።[30] እግዚአብሔር ስለ ኪጥያዊው ኦርዮ ሞት ቤርሳቤሕ ከወለደችው ከሰሎሞን በሚልቅ ልጅ ሞት ዳዊትን ገሥጾ አሳዝኖታል። ዳግመኛም እግዚአብሔር ወደ ዐሥሩ የአባቱ ቁባቶች ገብቶ በተራራ ላይ ድንኳን ተክሎ ከመንግሥቱ አዳራሽ ባሳደደው በልጁ በአቤሴሎም ወንጀል ዳዊትን ገሥጾታል። ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ልጁ አቤሴሎም ከሞተ በኋላ ዳዊትን ወደ ቤተ መንግሥቱ መልሶታል።

የኃጢአት ምክንያት በላዩ ላይ የሌለበት ከነቢያት ወገን አንድ ስንኳ የሚገኝ

26. ዘጸ. [illegible]
27. [illegible]
28. [illegible]
29. [illegible]
30. [illegible]

የለም። ስለዚህ ሁሉም በአሪት መርገም ውስጥ ሠጠሙ። የጸናች ኦሪት «በዚህ የሕግ መጽሐፍ የተጻፈውን የማይፈጽም የተረገመ ይሁን» ትላለችና። መጥምቁ ዮሐንስ «እነሆ! የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» ብሎ[31] እንደ ተናገረ በሲኦል ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ኃጢአት በትከሻው ተሸከመ። ኢሳይያስ «በእውነት ደዌያችንን ተቀብሎ ሕማማችንንም ተሸክሞአል።» አለ።[32] ጳውሎስም «ሕማማችንን የሚታመም እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ያስፈልገናል። መከራ በደረሰበት ቦታ ሕሙማንን ሊረዳ ናቸው ይችላል።» አለ።[33] ዳግመኛ ጳውሎስ ሰውን ሞት እንደሚጠብቀውና ከዚያም ፍርድ እንደሚጠብቀው ይናገራል። እንደዚሁ ክርስቶስ የብዙዎችን ኃጢአት ይቅር ይል ዘንድ አንድ ጊዜ ራሱን ሠዋ።

ስነፍ ሆይ! የጥበብ መፍለቂያ ጳውሎስ እንደ ተናገረ ስማ። ስለ ነፍስ ከሥጋ መለየት ለሰው አንድ ጊዜ መሞት እንደሚገባው እንደ ተጻፈ ስለ ነፍስ ከሥጋ መለየት ይህን አስቀደመ። ከዚህ በኋላ ፍርድ በማለት አስከተለ። እነሆ! የአበው ነፍሳትን ወደ ሲኦል መውረድ አመለከትህ። ከዚህም በኋላ ከሲኦል ስለ መውጣታቸው አስከትሎ ተናገረ። እንደዚሁ ክርስቶስም የብዙኃንን ኃጢአት ይቅር ይል ዘንድ አንድ ጊዜ ራሱን ሠዋ። በዚህም የቀደምት አበው ኃጢአታቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማት ይቅር እንደ ተባለ ዐሳወቀ።

እግዚአብሔር ሰውን ከመፍጠሩ አስቀድሞ የሰውን ልጅ ወዶታልና ለማደሪያውም ገነትን ተክሎ ያበራለት ዘንድ በሰማይ ጠፈር ውስጥ ፀሐይን ሾመ። ለሕፃን ልጅ ዐይኖቹን የሚያስደስቱትን ሽልማት እንደሚያሳዩት በአንጋጠጠ ጊዜ በሰማይ ሽልማት በሚያደርስበት ቦታ በረጅሙ ሌሊት ጨረቃንና ከዋክብትን አፈራረቀ። በፈጠረውም ጊዜ የሕይወትን እስትንፋስ በፊቱ እፍ ብሎ ተናጋሪና በልቡ አስተዋይ አደረገው እንጂ እንደ እንስሳትና አዕዋፍ ጠባይ አልተወውም። እግዚአብሔር የሕይወትን እስትንፋስ በሚያመሰግኑ መላእክት ወይም በመላእክት ፊት ላይ እፍ እንዳለባቸው በመጻሕፍት ገጽ ውስጥ የተገኘ ዜና የለም። «ይሁን [ለይኩን]» ባለ ጊዜ በአፉ ንግግር ተፈጥረዋልና[34] እግዚአብሔርንም ከሰማያት አመስግኑት፣ በአርያም አመስግኑት፣ መላእክቱ



31. ዮሐ. ፩፥፳፱።
32. ኢሳ. ፶፫፥፬።
33. ዕብ. ፱፥፳፯።
34. ዘፍ. ፩÷፫።



ሁሉ ያመሰግኑታል፤ ሰራዊቱ ሁሉ ያመሰግኑታል፤ ፀሐይ እና ጨረቃ ያመሰግኑታል፤ ከዋክብት እና ብርሃን ሁሉ ያመሰግኑታል፤ ሰማየ ሰማያት ያመሰግኑታል፤ በላይ በሰማያት ያለ ክፍልም ያመሰግኑታል። እርሱ ብሎአልና ሆኑ በእርሱም ትዕዛዝ ተፈጠሩ ለዘላለም አቆማቸው።

«ትእዛዝን ሰጣቸው አላለፉም»»[35] ብሎ በመዝሙር እንደተናገረ ዳግመኛ «መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል።» አለ።[36] የጸናች ኦሪት ስለ አዳም ግን «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፥ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት። ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። እግዚአብሔር አምላክም በምሥራቅ የዔደን ገነትን ተከለ። የፈጠረውንም ሰው ከዚያው አኖረው።» ትላለች።[37] እግዚአብሔር ግን አዳምን ሕያው [የማይሞት] አድርጎ ፈጠረው። እርሱ ግን በመበደሉ [በማመፁ] ሞትን ገዛ። የጸናች ኦሪት እንደ ምትናገረው፣ እግዚአብሔር ግን በሁሉ ፍጥረት ላይ ንጉሥ አደረገው። «በምን ስም እንደሚጠራቸው ያይ ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው። አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ በስሙ እንደ ጠራው ስሙ ሕያው ሆነ።» ዳዊትም «በእጆችህም ሥራ ሁሉ ላይ ሾምከው፤ ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት፣ በጐችንም ላሞችንም ሁሉ፤ ደግሞም የምድረ በዳውን እንስሶች፣ የሰማይንም ወፎች የባሕርንም ዓሦች፣ በባሕር መንገድ የሚሔደውንም ሁሉ።» አለ።[38] ስለዚህ ዳዊት «ሰው ክቡር ሆኖ ሳለ ዐላወቀም።» አለ።[39] ይህ ግን አዳም በገነት ውስጥ ሲኖር እንስሳት ሁሉ ሲታዘዙለት በእርሱ ላይ ያለውን ክብር ዐላወቀም በሚለው ይተረጐማል።

አምላክ መሆንን በመፈለግ የጠላትንም ምክር ሰምቶ ከተከለው ዕፀ በላ። ከዚህም አስከትሎ ሰው አዋቂ ሲሆን አላዋቂ ሆነ። አዕምሮ እንደሌላቸው እንደ እንስሳት ሆነ አለ።[40] በእርሱ ላይ የነበረ የብርሃን ልብስ በተገፈፈ ጊዜ በገነት ዕፅዋት መካከል ዕርቃኑን ከመጋለጥ በስተቀር እንስሳ መምሰል ምንድን ነው? የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በተላለፈ ጊዜ የብርሃን ልብሱን ተወው። የሕይወት እስትንፋሱ [የነፍሱ] ማስተዋል

35. መዝ. ፻፵፰፥፮።
36. መዝ. ፻፫፥፬።
37. ዘፍ. ፪፥፯።
38. መዝ. ፰፥፮።
39. መዝ. ፵፰፥፲፪።
40. መዝ. ፵፰፥፳።



www.ethiopianorthodox.org

አልተወ ውም። ዕርቃኑ ስለ ተገለጠ አፈረ። የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው እርስም ሚስቱም አገለደሙ።

ከዚህም በኋላ በመዝሙር ቃል «ደህች መንገዳቸው መስናክላቸው ናት።» አለ።[41] በእግዚአብሔር በመቅደሱ ዐጸድ ከፈጸሟት የኃጢአት መንገድ በስተቀር የአዳምና ሔዋን መሰናክላቸው ምንድን ነው? ሔዋን በእባብ ቃል ተሰናከላለች፣ አዳም በሚስቱ በሔዋን ተሰናከሏል። ከዚህ በኋላ ከተድላ ገነት ወጡ። ከገነትም ከወጡ በኋላ አዳምና ሔዋን ወደ ማደሪያቸው እንዳይመለሱ በምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍ የገነትን ቅጽር ይጠብቁ ዘንድ ከኪሩቤልና ከሱራፌል ጠባቂዎች ተሾሙ።

ኤርምያስና ሕዝቅኤል፦ «አባቶች ጨርቋ በሉ፣ የልጆቻቸው ጥርሶች ጠረሱ [ተበላሹ]።» እንዳሉ[42] የኃጢአታቸው ስሕተት በልጆቻቸውም ላይ ታሰበ። ጳውሎስም «በአዳም መተላለፍ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፣ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ።» አለ።[43] ስለ ነቢያትም ሕይወት ያለው «ሁሉ የኦሪትን ሕግ በመፈጸም አይጸድቅምና ከሙሴ እስከ ክርስቶስ ከኦሪት ሕግ በታች የተጠመዱ ናቸው።» አለ።[44] ስለምን? ሕግዋ የፈጸሙአትንም ሳይቀር ሳለማጽደቅ መርገም አለባትና። እንግዲህ እንደ በጐች «በሲኦል ሞት ይጠብቃቸዋል» ወደ ሚለው የመዝሙር ቃል ንባብ በማስከተል እንግባ። እነሆ፣ በሲኦል ውስጥ ሞት እንደ ሚጠብቃቸው ወደ አዳምና ልጆቹ ነፍሳት መኖሪያ የመዝሙሩ ቃል አደረሰን። ከዚህም በኋላ በጠዋት እውነተኞች ይገዙአቸዋል። ምስኪኑን [ድኻውን] ስለ ድህነቱ ካልበደለ አያቦዝኑትም። ንጉሡን ስለ ክብሩ ከበደለ አይራሩለትም። ፊትን ዐይቶ ማድላት የሌለባቸው ገሃነምን ከሚጠብቁ በስተቀር እውነተኞች እነማን ናቸው? «በሲኦል ሞት እንደ በጐች ይጠብቃቸዋል» የሚለው[45] ግን «እውነተኞች በጠዋት ይገዙአቸዋል።» በሚለው ይተረጐማል። ኃጥአን ለሞት ፍርድ ዛሬ ይሰጣሉ። በጠዋትም የፍርድ ቅጣት ከሲኦል ጠባቂዎች ዘንድ ትከተላቸዋለች። ከዚህም በኋላ ነቢዩ «ነገር ግን ባነሣኝ ጊዜ እግዚአብሔር ነፍሴን ከሲኦል እጅ ያድናታል።» አለ።[46]

41. መዝ. ፻፫፥፲፱።
42. ሕዝ. ፲፰፥፪።
43. ሮሜ. ፭፥፲፬።
44. ገላ. ፫፥፲-፲፫።
45. መዝ. ፵፰፥፲፬።
46. መዝ. ፵፰፥፲፭።





ነቢዩ እግዚአብሔር በአንድ ልጁ ሕማም እንደሚያድነው ተናገረ። ለአንድ ወልድ ወደ የፍርድ ቦታ በመውሰዱ የጻድቃን ነፍስ መውጣት ቻሉ። ስለዚህም ነቢዩ «በአማላጅም አይደለም፣ በመልእክተኛም አይደለም፣ ራሱ መጥቶ ያድናቸዋል እንጂ።» አለ። ዳግመኛም በመዝሙር፦ «ዐይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ፣ ረዳቴ ከወዴት ይምጣ?» አለ።[47] ነቢያትን አድባር [ተራሮች] ይላቸዋል። ከእነርሱም ረዳት ፈልጉ ያገኘው የለም። ከዚህም በትንቢት መንፈስ ከክርስቶስ በስተቀር ረዳት እንደ ሌለ ዐወቀ። ስለዚህም «ረዳቴ ግን ሰማይና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።» አለ።

ኢሳይያስም ወደ ሲኦል እንደሚወርድ ተናገረ። «ሀንሳ ወደ ወለደች ነቢዩት ሴት ሔድኩ።» አለ። እግዚአብሔር «ስሙን ፈጥነህ ስደመው፣ ፋጠህ ፈጽመህ ማርከው።» አለኝ።[48] ሀንሳ ልጅን የወለደች ነቢዩት ሴት መድኃኒታችንን ከወለደች ከእመቤታችን ማርያም በስተቀር ማን ናት? ከሲኦል ውስጥ ከማረካቸው ከአበው ነፍሳት በስተቀር ማረኪ ማን ነው? ዳግመኛ መድኃኒታችን ከፍርድ ቦታ ካወጣቸው ከነቢያት ነፍሳት በስተቀር ምርኮው ምንድን ነው? ዳዊትም «ምርኮን ተካፍዬ እደሰታለሁ።» አለ።[49] ለራሱ የተናገረው ለእግዚአብሔር ልጅ እንደ ተናገረ ነው። ከዳዊት ሥር ሥጋ ለብሷልና፣ አስቀድመን እንደ ተናገርነው «ምርኮን እካፈላለሁ» ያለው ግን የአበው ነፍሳትን ነው። ከዚህም አስከትሎ «በሞቃትም ቦታዎች እሰፍራለሁ። ይህንም በርስትነት እንዳለ ስለ ምርቃት ፍርድ ይላል [ይናገራል]። ከእናቱ ወገን አባቶቹን ይመስላቸው ዘንድ ፈቅዷልና በፍርድ ቅጣት ሙቀት ውስጥ ወደ ሚኖሩት ዘንድ ተስተናገደ። ያወጣቸውም ዘንድ ወረደ፣ ከእነርሱ ጋር ይሠቃይ ዘንድ አይደለም። ሙሴ ከሕዝቦቹ ጋር አዳም ከልጆቹ ጋር ይወጡ ዘንድ የሲኦልን ቁልፍ ከፈተላቸው።

ከገሃነም ባሕር ውስጥ ያሠጠመቻቸውን የኦሪትን መርገም ሻራት። ኦሪት ግን ቅድስት ነች። ትእዛዟም ቅዱስ ነው። ነገር ግን አለመፈጸማቸው መርገዝ ሆነባቸው። እግዚአብሔር የኦሪትን ትእዛዝ ለመፈጸም የሚችል እንደ ሌለና ሁሉም በኦሪት መርገም ውስጥ እንደ ሠጠመ በተመለከተ ጊዜ የእስራት መርገምን በውስጧ ካስቀመጠ ከእርሱ ብቻ በስተቀር መታሰሪያዋን መፍታት የሚችል እንደ ሌለ አሰበ። ዳግመኛም እርሱ የዘጋውን

47. መዝ. ፶፬፥፮።
48. ኢሳ. ፴፰፥፲።
49. መዝ. ፸፯፥፪።



www.ethiopianorthodox.org

ከእርሱ ብቻ በቀር ሌላ የገነትን በር ሊከፍት የሚችል እንደሌለ አስበ:: ስለዚህም የአዳምን መርገም ይሽር ዘንድ ከአዳም ልጅ ተወለደ:: የአራትን መርገም ይሽር ዘንድ ከአይሁድ ልጅ ተወለደ:: በእርሱ ላይ የአብርሃም ምልክት ይታወቅ ዘንድ እንደ ዕብራውያን ሥርዐት በስምንተኛውም ቀን ተገዘረ:: ነቢያትን ከሞት ጥላ ውስጥ ያወጣቸው ዘንድ ወደ መጸለት በዓላቸው ወጣ:: ምእመናንንም ለአዲሷ ፋሲካ ያዘጋጃቸው ዘንድ አሮጌውን ሥርዐት ይፈጽም ዘንድ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ፋሲካን አደረገ:: ከግብጽ ምድር የእስራኤል ልጆች በወጡ ጊዜ የተሠራውን ሕግ ይፈጽም ዘንድ በምሴተ ኀሙስ [ኀሙስ ማታ] የፋሲካን በግ አረደ:: በማግሥቱም በስቅልያን እጅ ታርዶ ራሱ የፋሲካ በግ ሆነ:: በእርሾ ያልተለወሰ የአይሁድ ቂጣን በላ:: ከእራት በኋላ ይኸውም የመዋለጃ ዘር በሚሆን በሰው እርሾ ያልተለወሰች ብቻዋን ድንግል ከምትሆን የነሣውን አዲስ ቂጣ የሥጋውን ኅብስት [ሥጋውን] ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው:: ስለዚህም ጳውሎስ «እናንተ ግን ለአዲስ ቂጣ ተለዩ::» አለ:: ከእራት የፋሲካ በግ ጋር መንታ አደረገ እንጅ ሥጋ ወና ደሙን ከዚህ አስተድሞ ወይም ከዚህ በኋላ ለምን አልሰጠም? በፋሲካ የመሥዋዕት በግ ደም የምኩራብን የፍችዋን መጽሐፍ አደረገ ሳት:: በሥጋውና ደሙ ቊርባን [መሥዋዕትነት] ቤተ ክርስቲያንን አጫት:: ነገር ግን ሳልተጠመቀ ቊርባን መቀበል አይገባውምና በጥም ቀት አምሳል አድርጐ የደቀ መዛሙርቱን እግራቸውን በማጠብ በወን ጌል መሥዋዕት መካከልና በእራት መሥዋዕት መካከል ልዩነትን አደ ረገ:: ዮሐንስ ባጠመቀው ጊዜ እጁን በራሱ ላይ አኖረ:: ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ባጠባቸው ጊዜ እግራቸውን በማበሻ ጨርቅ አሸቶ በቅድ ስት እጁ የተረከባቸውን ቆሻሻ [እድፍ] አነጻ:: በዮሐንስ ዘንድ የክህነት ክብር በጌታ ኢየሱስም ዘንድ የተልእኮ ትሕትና ታየ፡ የእግሮች መኖሪያ ከሁሉ በታች ሲሆን የራስ መኖሪያ ከሁሉ በላይ ነውና:: በዮርዳኖስ ወንዝ አብ፦ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው:: እርሱን ስሙት» ብሎ ምስክር ሆነ:: ይህ የእውነት ምስክርነት ስለ ተጠመቀው [ስለ ተጠ ማቂው] እንጂ ስለ አጠመቀው [ስለ አጥማቂው] አይደለም:: ሰማይ ተከ ፍቶ በነጭ ርግብ አምሳል መንፈስ ቅዱስ ወርዶ በራሱ ላይ ተቀመጠ::

50. ሉቃ ቁር ፳፪፥፯-፰::
51. ማቴ. ፫፥፲፯::





በኢየሱስ ዘንድ እንጂ በዮሐንስ ዘንድ አይደለም:: የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበ በ፶ኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት ወረደ:: በታጠቡት ዘንድ እንጂ በአጠባቸው ዘንድ አይደለም:: ሰው ከሆነበት ዕለት አንሥቶ እስከ ዐረገበት ዕለት ድረስ በጽርሐ አርያም የወልድ የህልውናው ክብር [ምኲናን]እንዳልታጐለ እንዲሁ የመንፈስ ቅዱስ የህልውና ክብር [ምስጋና] በጽርሐ አርያም በሐዋርያት ላይ በጽርሐ ጽዮን ውስጥ በወረደ ጊዜ አልታጐለም::

አምላካችን ግን በዚያ ሦስት በዚህም የማይለያይ ነው:: በዚያ ምሉዕ በዚህም የማይጐድል ነው:: በዚያ በአርባዕቱ እንስሳት አፍ የተመሰገነ ነው:: በዚህም በአርባዕቱ ወንጌላውያን አፍ የተመሰገነ ነው:: በዚያ የማይታይ ኀይል ነው:: በዚህም የማይዳሰስ እሳት ነው:: አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በሦስትነት ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ተብሎ ተመሰገነ:: ምስጋናው በሰማያት፣ በምድር፣ በተራራዎች፣ በኮረብቶች፣ በባሕር፣ በወንዞች በሁሉም አጽናፍ በሚታየውም በማይታየውም የተመላ ነው:: እናታችሁና እናታችን በዕፀ መስቀል ተመርከዛ የመለኮት ወንጌልን የያዘች፡ ጐኖቿን በወርቅ አመልማሎ የተሸለመች፡ የርግብ ክንፍ ብብር ያጌጠች፡ ይህችውም ንጽሕት የሆነች እናታችሁና እናታችን ቤተ ክርስ ቲያን እንደዚህ ተምራ እንደዚህ ታስተምራለች:: ለሚከተሏትም በዮር ዳኖስ ወንዝ የገዛኋት የጥምቀቴ ዓጽፍ ይህች ናት:: ሐዋርያት የሰጡኝ የመድኅኒቴ አክሊል ይህ ነው:: የሥላሴ ስሞች የተጐናጐኑ የሃይማኖት አክሊል ይህ ነው ትላቸዋለች::

ከዚህም በኋላ የተረገመ ሳይሆን ወደ አራት መርገም አንዱ ወልድ እንደ ገባ ወደ ሚናገር ዜና እንመለስ:: ሕግጋቱን ባለመፈጸም የሥጋው ሕግ ኃጢያት እንደ ዐየለባቸው እርሱ ግን ከሙሴ ትእዛዝ ምንም አልተላለፈም:: ለምጻ ሙን ራሱ አንጽቶ በእነርሱ ላይ ምስክር ይሆን ዘንድ «ሙሴ እንደ አዘዘው ስለ ነጻህ መብዓህን አቅርብ:: ሔደህ ራስህን ለካህን ዐሳይ» እንዳለው እንግዲህ ከኃጢአት ንጹሕ ሁኖ ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር የአራትን ትእዛዝ ጠብቆ የተሸከማት የለም:: በመለኮቱ ለሙሴ አራትን የሰጠው በሰውነቱ ለአራት ትእዛዝም ተገዛ፡ ነገር ግን እርግማንንም ይሽር ዘንድ ወደ መስቀል ግንድ ቀረበ:: የጸናች አራት፦ «ማንም ሰው ለሞት የሚያበቃውን ኃጢአት ቢሠራ፣ እንዲሞትም ቢፈርድበት በእንጨትም ላይ ብትሰቅለው፣ በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረ

52. ማቴ. ፳፯፥፴፱::



www.ethiopianorthodox.org

ገመ ነውና ራሳው በእንጨት ላይ አይደር።» ትላለች።[53] በመስቀል ወደ መር
ግሚ ገባ። በበደል አይደለም። ስለዚህም የመርገሚ ማሰሪያ ሁሉ ተፈታ።
ጳውሎስም፦ «ክርስቶስ ከኦሪት እርግማን ዋጀን» እንዳለ።[54] ዳግመኛም
ኃጢአትን የማያውቅ የኃጢአተኛን ልጅ ሥጋን ተዋሕዶ በሥጋው ያቺን
ኃጢአት ፈረደባት።

ከኃጢአተኞች ልጅ ኃጢአተኛ ሥጋን እንደተዋሐደ ይችውም በነ
ፍሷ ቅድስት በሥጋዋ ንጽሕት ናት። የአባቷ ኃጢአት ልጇን አልነካ
ውም። እንዲሁም ወደ ኦሪት መርገም ገብቶ እርግማኗ አልደረሰ
በትም፤ ነገር ግን ማሰሪያዋ ሁሉ ተፈታ። ሐዋርያት፦ «መድኃኒታችን
ኦሪትንና ነቢያትን ለመሻር አልመጣም። በዳግም ሕግ ውስጥ ማሰሪያ
ውን ይፈታና ይፈጽማቸው ዘንድ ነው» እንዳለ። በዕፀ መስቀል ላይ ሳለ
የታሰሩትን ከእስራታቸው መፍታትን አስቀደመ፤ እነርሱ ታስረው ሳሉ
በእግራቸው መመላለስ አይችሉምና። ሐዋርያው እንደ ተናገረው ከነፍሱ
መውጣት በኋላ ከጥፋት ቦታ ያወጣቸው ዘንድ ወደ ሲኦል ወረደ።
ነፍሳቸውም በእስራት ወዳለችበት ቦታ ሔደ፤ አስቀድመው ለካዱትም
ሰበከላቸው።

ዳግመኛም ሐዋርያት በቅዳሴ መጽሐፍ[55] በአኰቴተ ቍርባን፦ ሕሙ
ማንን ያድን ዘንድ የሰይጣንን ማሰሪያ ይበጥስ ዘንድ ሲኦልን ይረግጥ
ዘንድ ቅዱሳንን ይመራ ዘንድ ሥርዐትን ይተክል ዘንድ ትንሣኤውን
ያሳውቅ ዘንድ እጆቹን ለሕማም ዘረጋ።» አለ። በሕማሙ በጥፋት ቦታ
ያሉትን ሕማማቸውን ይፈታ ዘንድ በዕፀ መስቀል ላይ እጆቹን ስለ
ዘረጋ፦ «እጆቹን ለሕማም ዘረጋ» የሚለውን አስቀደሙ። ከዚህም
በማስ ከተል «የሰይጣንን ማሰሪያ ይበጥስ ዘንድ» አለ። የሰይጣን
ማሰሪያ በአበው ዘንድ ከነበረ ኃጢአትን ከማሠራት በስተቀር ምንድን
ነው? ሲኦልንም መርገጥ ምንድነው? ሲኦልን መርገጥ ዕፀ በለስን ስለ
መብላታቸው በተቆጣው ጊዜ አዳምና ሔዋንን ያስወጣቸው ዘንድ
በዘወትር ጉዳና ወደ ገነት የተመላለሰ ነው። እንዲሁ በዓርብ ወደ
ፍርድ ቦታዎች ተመላልሶ መከራ በተቀበለ ጊዜ አዳምንና ሔዋንን
ሁሉንም የእስራኤል ነቢያትን ማሕየዊ በሆነ ሞቱ አዳናቸው።

53 ዘዳ ፳፩ ፥ ፳፫።
54 ገላ ፫ ፥ ፲፫።
55 ቅዳሴ እግዚእ። ይህ ጥቅስ ከአባ ጊዮርጊስ በፊት የተወሰኑ ቅዳሴዎች በኢትዮጵያ እንደነበሩ ያመለክታል።





እንደገናም ከኪዳን ቃል[56] «ለጥፋት የተሰጠ የቀደመ ሰው አዳምን ያዳ
ንክ በልጅህ መስቀል በማይጠፋ መንፈስ ቅዱስ አደስከው» የሚል የእውነት
ምስክር አለ።» ዳግመኛም ወደ ሲኦል ስለ መውረዱ ከኪዳኑ ቃል ምስክር
አለ፦ «ከታመመ በኋላ ወደ ሲኦልም ወርዶ የሙታንን ነፍስ ለሕይወት የማረከ
ነው።» አለ። ከአባታቸው ከአዳም፣ ከእናታቸውና ሔዋን ከመስቀል ላይ ከተተ
ጠቀ ከፈያታዊ ዘየማን ነፍስ ጋር ወደ ተድላ ገነት አስገባቸው። የገነት የበር፰
ጠባቂዎች ራቁ። እነሆ ነቢያት በሲኦል እንደ ነበሩና እንደዚሁም ጌታችን
በሞቱ ወደ ተሻለ ገነትም እንዳስገባቸው ምስክር አቀረብንላችሁ።

በፍርድ ቦታ [በዐጸደ ደይን] ስለ ነበሩ አበውም እንናገር። የእግዚ
አብሔር የምሕረቱ ጠል ሠለስቱ ደቂቅን ከባቢሎን ከእቶን እሳት መካ
ከል እንደ ጠበቃቸው፣ ዮናስን ከዓሣ አንበሪ ሆድ እንደጠበቀው ዳንኤልን
ከተራቡ አንበሶች ጉድጓድ እንደ ጠበቀው። እግዚአብሔር አናንያን፣
አዛርያንና ሚሳኤልን በእሳት ውስጥ ከተወረወሩ በኋላ ከሚያስፈራው የእ
ሳት ነበልባል አዳናቸው እንጂ ከንጉሡ ከናቡከደነፆር እጅ አላዳናቸውም።
ፍላቱ እንደ ክረምት ነጐድጓድ ከሚሬሙሽ እቶን እሳት መካከል ሳይገቡ
አስቀድሞ አድኖአቸው ቢሆን ግን የእግዚአብሔር የማዳኑ ኃይል ባልተ
መሰገነ፥ ንጉሡም ባልተገዛላቸው ነበር። በነበልባሉ መካከል ተደስተው፤ ከእ
ቶኑ መካከል ድነው በተመለከታቸውም ጊዜ ለእግዚአብሔር ተገዝቶ ስለ
አራተኛው መልክ አደነቀ። «የአራተኛው መልኩ የእግዚአብሔር ልጅ
ይመስላል» አለ።[57] ወደ እቶን እሳቱ መግቢቱ ያልታየ፤ በሥላሴ ሞገስ
ከተከለሉ ከሠለስቱ ደቂቅ ጋር በእቶን እሳቱ መካከል ሲመላለስ ታየ።
ስለዚህም ንጉሡ የሠለስቱ ደቂቅ አምላክ የእሳት ጌታ እንደሆነ ዐውቆ
«ለሲድራቅ፣ ለአብደናጎና ለሚሳቅ አምላክ ያልሰገደ ሁሉ ሞትን ይሙት
እያለ ዐዋጅ ነጋሪ እንዲዞር አዘዘ።[58]

ስለ ዮናስም እንናገር። እግዚአብሔር ዮናስን የባሕር ሞገድ እንዲ
ይዘው በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ ጠበቀው እንጂ ባሕር ውስጥ ከመጣል
አላዳነውም። በመርከቧ ሆድ ድኖ ቢሆን ግን የእግዚአብሔር የማዳኑ
ኃይል ባልተመሰገነ ነበር። በጀልባዎችም ልማድ የሚጠፉና የሚድኑም አሉ።
በዓሣ አንበሪ ሆድ ግን ከመጥፋት በስተቀር መጠበቅ [መዳን] የተለመደ

56. መጽሐፈ ኪዳን።
57. ዳን. ፫ ፥ ፳፭።
58. ዳን. ፫ ፥ ፳፱።

አይደለም። የአንበሪው ሆድ ለዮናስ እንደ ጎልጎታ መቃብር ሆድ ሆነው።

የዮናስ ወደ ዓሣ አንበሪ ሆድ መግባት እሱ ሕያው ሆኖ ሳለ ከባሕር በወረወሩት ዘንድ እንደሞተ ይታሰባል፤ እንደዚሁ ነፍስ የተለየው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ መለኮቱ ሕያው ሆኖ ሳለ ወደ መቃብር ገባ [ወረደ]። ስለዚህም ጌታችን በወንጌል «ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፤ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም፤ ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበር እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል።» አለ። ዮናስ በመርከብ ልብ ቢደን ኖሮ ግን ከእግዚአብሔር ፊት ወደ ተርሴስ አገር ይኮበልል ዘንድ ባልሔደ ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር ለጥልቅ ባሕር ሰጠው። ጥልቁ ባሕርም ለዓሣ አንበሪ ሆድ ሰጠችው። ዓሣ አንበሪው እንደ ለመደው ዋጠው። እግዚአብሔርም ከጥፋት አዳነው። ዓሣ አንበሪውም በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ተጉዞ ወደ ነነዌ አገር አድርሶ መልሶ አወጣው። ዮናስም አገራቱን በተመለከተ ጊዜ እግዚአብሔር በባሕር ላይ ንጉሥ እንደ ሆነና ሥልጣኑም በጥልቅ ባሕር ውስጥ እንዳለ በውቆ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረበ።

ስለ ዳንኤልም፤ እግዚአብሔር ከፋርስ ከሜዶን ሰዎች ውዴታና [ጉድጓድ ውስጥ ከጣሉት] ከንጉሡ ከዳርዮስ እንዳዳነው ስለ ዳንኤልም እንናገር። ነገር ግን የጉድጓዱ በር በላያቸው ላይ ተዘግቶ ሳለ ከተራቡ አንበሶች አፍ አዳነው፤ ጾማቸውን ከእርሱ ጋር ተቀመጠ እንጂ በጥርሶቻቸውም አልነኩትም /አልሜኑትም/ በጥፍሮቻቸው አልነኩትም። አልጎዱትም። እግዚአብሔር ከንጉሣቸው ከዳርዮስ እጅና ከሜዶንና ከፋርስ ሰዎች ውዴታ ቢያድነው ግን የእግዚአብሔር የማዳኑ ኃይል ባልተመሰገነ ነበር፤ ከንጉሡ ቁጣና ከጓደኞቻቸው ውዴታ ክርክርና በፍርዳቸው ውሳኔ የሚድኑ ብዙዎች ናቸውና። በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ከአንበሶች ጋር መቀመጥ ግን እንደ ጤቅላ እና፤ ከእርሷ ጋር ምስክር የሆኑ እንደ ዳንኤል ሕይወታቸው በአምልኮተ እግዚአብሔር የሆነ እንጂ ለሁሉ የሚገባ አይደለም።

ንጉሡ የጉድጓዱን በር ይከፍቱ ዘንድ ባዘዘ ጊዜ አንበሶቹን ከነቢዩ ከዳንኤል እግር ሥር ሰግደው አገኛቸው። ንጉሡም ተደንቆ የዳንኤል አምላክ የአንበሶች ጌታ እንደ ሆነ ዐወቀ። ንጉሡም ዳንኤልን የከሰሱትን

59. ማቴ. ፲፪ ፥ ፴፱።
60. ጤቅላ የሰው ስም ነው።

www.ethiopianorthodox.org



እነዚያን ሰዎች ወደ አንበሶች ጉድጓድ ይጥሉአቸው ዘንድ አዘዘ። ወደ ጉድጓዱም መጨረሻ ሳይደርሱ አንበሶች ያዙአቸው፤ አጥንታቸውንም ሁሉ ሰባበሩ። የባቢሎን እቶን በውስጧ ያሉትን ያለ ጥፋት ጠበቀቻቸው። ከውጭ ያሉትን ግን ከሩቅ አቃጠለቻቸው። የንጉሡ የዳርዮስ አንበሶች በጉድጓድ ውስጥ ከነቢዩ ጋር ተስማምተው ተቀመጡ። ዳንኤልን ይበሉት ዘንድ የወረወሩትን ከሳሾቹን ሰዎች ከጉድጓዱ አፍ ነጠቁአቸው።

ነቢዩ፣ «ጻድቅ ግን ከእገታ ያመልጣል፣ ስለ እርሱም በዛ ኃጥእ ይሰጣል» ያለው እውነት ነው።[61] ሦስቱ ደቂቅን የነበልባሉ እቶን እንዳላቃጠላቸው እንዲሁ ቅዱሳን አበውን የሲኦል ነበልባል አያቃጥላቸውም፤ የእግዚአብሔር የምሕረቱ ጠል ጠብቋቸዋልና ነቢዩ እንደ ተናገረው ከአንተ ዘንድ ያለው ጠል ሕይወታቸው ነውና። አንበሶቹ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ከዳንኤል ጋር ሳሉ በዳንኤል ላይ እንዳልከፉ እንዲሁ የገሃነም ጠባቂዎች ንጹሐን ነቢያት ከእነርሱ ጋር ሲኖሩ አልከፉባቸውም። እስከ ክርስቶስ ምጽአት [ልደት] ድረስ በሲኦል ውስጥ ስለ ነቢያት ህልውና ግን ዳዊት «ሰው ሆኖ ሞትን ሳያይ በሕይወት የሚኖር ማነው? ነፍሱን ከሲኦል እጅ የሚያድናት ማነው? አለ።[62] በዚህም በኦሪትና በነቢያት ዘመናት ከሲኦል መዳን እንደ ሌለ በግልጽ ተናግሮ ዐሳወቀ።

ዳግመኛም ስለ ነፍሳቸው ወደ ሲኦል መውረድ «አቤቱ፥ ጥልህ አፈረስከኝ፣ ቀጥተህም ይቅር አልከኝ።» አለ።[63] ይህ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ከሲኦል ስለ መውጣታቸው ነው። «ምድርን አናወጥካት፤ አወከት» አለ።[64] ይህም ነፍሱ ከሥጋው በተለየች ጊዜ ስለ ምድር መናወጥ የተነገረ ነው። ቁስሏን ፈወስከ፤ ተናውጣለችና። ይህም እንዳትናወጥ መሠረቶቿን ስለ ማጽናትና ቁስሏን ለመፈወስ ስለ ደሙ መፍሰስ የተነገረ ነው። ሕዝቡን ድንቅ አሳየኻቸው። ይህም በዘጠኝ ሰዓት ስለ ፀሐይ መጨለም፤ ስለ ዐለት መሰነጣጠቅም ስለ ምድር መናወጥና በዘጠኝ ሰዓት ስለ ምኩራብ መጋረጃ መቀደድ የተነገረ ነው።

«አስደንጋጭ ወይንን አጠጣኸን፦ የወታደር ጦር በወጋው ጊዜ ከጐኑ ከፈሰሰው ከኢየሱስ ክርስቶስ ደም በስተቀር አስደንጋጭ ወይን ምንድን

61. ዳን. ፫ ፥ ፳፯።
62. መዝ. ፹፰ ፥ ፵፰።
63. መዝ. ፳፱ ፥ ፩።
64. መዝ. ፳፱ ፥ ፭።

ነው? ከሕያው ጐን አይደለም። ከበድን [ነፍስ ከተለየው] ጐን የፈሰሰው አስደንጋጭ ወይን መሆኑ እውነት ነው፤ ከሕያው በድን አይደለም የመለኮት ሕይወት በውስጥ አለና። በዓርብ ፋሲካ ከበድን ጐን የመነጨው በእውነት አስደንጋጭ ወይን ነው፤ በድኖችንም ከጥንት ከእንቅልፍ ሞታቸው አንቀሳቀሳቸዋል። በነዶሉና በነበልባሉ ሰይጣንን የሚያየውን ዐይኑን የሚያፈዝ፤ የሚያንጸበርቅ መብረቅን እንደ ተመለከተ ሰይጣንን የሚያስደነግጥ በእውነት አስደንጋጭ ወይን ነው። የጥንት በድኖች ከበድን ጐን የመነጨውን የዓርብ ፋሲካ አርጥብ ወይን ጠጡ። ከሞቱ እስከ መወጋቱ ያለው የሰዓት መጠን ግን ሦስት ሰዓት ነው፤ በዘጠኝ ሰዓት ነፍሱ ከሥጋው ወጥታለችና። በዐሥራ አንድ ሰዓት ጐኑን ተወጋ። በዐሥራ ሁለት ሰዓት ከመቃብር ውስጥ ጨመሩት። ስለ ነቢያት ንብረታቸው ግን በፍርድ ቦታ የእግዚአብሔር የምሕረቱ ጠል እየጠበቃቸው በፍጹም እርደታ ይኖራሉ።

የምስክርነቱ ቃል በሉቃስ ወንጌል እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ልጅ መታመኛዬና ምስክሬ ነው። ቀይ ልብስ ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ። ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር። አልዓዛርም የሚባል አንድ ድኻ በቁስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር። ከባለጠጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር። ውሾች እንኳ መጥተው ቁስሉን ይልሱ ነበር። ድኻውም ሞተ፤ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት ባለጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ። በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ ዐየ፤ አልዓዛርንም በእቅፉ። እርሱም እየጮኸ፤ አብርሃም አባት ሆይ! ማረኝ፤ በዚህ ነበልባል እሠቃያለሁና የጣቱን ጫፍ በውሃ ነክሮ ምላሴን እንዲያረጥብልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ። አብርሃም ግን፡- ልጄ ሆይ! አንተ በሕይወት ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ፤ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል፤ አንተም ትሠቃያለህ። ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ ወዲያ ያሉት ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጓል። አለ።[65]

ልብህ የታወረው ሆይ! ጌታችን በወንጌል ባለጠጋው በሲኦል ዐይኖቹን እንሥቶ አልዓዛርን በአብርሃም እቅፍ ተቀምጦ ዐይቶ ያለውን ስማ። በፍርድ ቦታ እንጂ በገነት ዐጸድ ውስጥ አይደለም። ይቺ የገነት ዐጸድ

፷፭ ሉቃ ፲፮፥፳፮።





ባትሆን ግን ባለጠጋው ባልተመለከታት ነበር። ገነት ግን ከምሥራቅ አቅጣጫ ነችና ሲኦልም በስተምዕራብ ነች።

ስለዚህም ሐዋርያት የምእመናን ጸሎት ወደ ምሥራቅ ይሆን ዘንድ አዘዙ። ፀሐይን ለሚያመጣው እንጂ የምሥራቅን ፀሐይ አይደለም። ወደ ፀሐይ መገለጫ መጸለይ ፀሐይ ሲገባ ተደንግጎ ቢሆን ግን ፀሐይ አምላኪዎች ፋርሳውያን እንደሚያደርጉት ጸሎታችን በጠዋት በምሥራቅ በምሽት በምዕራብ አቅጣጫ በሆነ ነበር። እኛን ግን በነግህ፤ በሠርክ፤ በመዓልትና በሌሊት ወደ ምሥራቅ እየተመለከትን እንድንጸልይ አዘዙን።

«የጻናች ኦሪት እግዚአብሔር አምላክ በምሥራቅ በዔደን ገነትን ተከለ» የምትል ነች።[66] ስለዚህም ሐዋርያት ጸሎታችን ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ይሆን ዘንድ አዘዙን። የኃጥአን ማደሪያ የፍርድ ቦታ ከሆነው ከምዕራብ አቅጣጫ ፊታችንን እንመልስ። የቅዱሳን ማደሪያ የገነት ተድላ ወዳለበት ቦታ ወደ ምሥራቅም አቅጣጫ እንመልስ። መዝገባችን ባለበት ልባችን አለ። የገነት አበባ በየራሱ መልክ ባለው በዚያ የልቡናችን ዐይኖች ያያሉ። የየራሱ መዓዛ ያለው ያማረ ሽቱ ባለበት ቦታ በዚያ አፍንጫችን ያሸታል። ብዙ ሺሕ የሚቆጠሩ የተወደዱ የበረከት ፍሬዎች ባሉበት ቦታ በዚያ ቅንድቦቻችን ያንጋጥጣሉ፤ ተስፋ ወደ ምናደርገው ቦታ እንገባ ዘንድ በሩን እናንኳኳለን። መንዝ ወደ ምንፈልግበት ቦታ በዚያ የጸሎት ስንቃችንን እናዘጋጅ። ማደር ወደ ምንፈልግበት ቦታ በዚያ በእግረ ልቡናችን እንመላለስ። መኖርያዋ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ወደ ሆነችው ወደ ገነት ተድላ ጸሎታችን ይሆን ዘንድ ስለዚህም ተሠርቷልና።

ዳንኤልም እንደዚህ ዓይነት አርአያ አደረገ። ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ የሚታየውን የአዳራሹን መስኮቶች ከፍቶ ይጸልይ ዘንድ የቤቱን በር ዘጋ። በምርኮ አገር ሳለ የኅሊናውን ተስፋ ወደ ሀገረ እግዚአብሔር አድርጓልና። እኛም ስለ አዳም ለቅዱሳን ርስት እግዚአብሔር አዘጋጅቶ ወደ ተከላት ወደ ገነት አቅጣጫ አድርገን በጸለይን ጊዜ ፊታችንን ወደ ምሥራቅ እንመልስ ዘንድ ይገባናል። «ስለ ሲኦልም በምዕራብ አቅጣጫ እንደሆነች ዳዊት እንዲህ ብሎ ይናገራል። «ስሙ እግዚአብሔር ለሚባል ወደ ዓረብ ለወጣም መንገድ አድርጉ።»

ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ማረግ መኖሪያዋ ወደ ምዕራብ ፀሐይ ከሆን

66. ዘፍ. ፪፥፰።



www.ethiopianorthodox.org

ከፍርድ ባሕር ከመውጣት በስተቀር ምንድን ነው?[67] ከምርኮኞች እንደ አንዱ ብትሕትና ወደ እርሷ ወረደ፡፡ ከሁሉም ቅዱሳን ነፍሳት ጋር በልዕልና ከእርሷ ዘንድ ዐረገ፡፡ ስለዚህም ወደ ዓረብ ለወጣም መንገድ አድርጉ አለ፡፡ እነርሱን ግን ከፍርድ ባሕር አወጣቸው፤ ወደ ተድላ ገነት አስገባቸው እንጂ ወደ ሰማይት አላሳረጋቸውም፡፡ ወደ ሲኦል በመውረዱ እንደ መሰላቸው እንዲሁ ወደ ገነት በመግባቱ በየወገናቸው ርስትን አካፈለ፡፡

በእሑድ ሌሊት ነፍሱን ወደ ሥጋው መልሷታል፡፡ በመለኮቱ ኀይል ተነሣ፡፡ ራሱ «ነፍሴን በፈቃዴ ፈጽሞ እሰጣለሁ፤ እንሣት ዘንድም አኖራትም ዘንድ ይገባኛል፡፡ ይህን ትእዛዝ ከአባቴ ዘንድ ተቀበልሁ» ብሎ እንደ ተናገረ፡፡[68] በጠዋትም ለመግደላዊት ማርያም ተገለጸላት፡፡ ትሳለመው ዘንድ በፈለገች ጊዜ ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ አላት፡፡ በዚህም ሥጋው ከአሁን አስቀድሞ በአብ ቀኝ እንዳልተቀመጠ ዐወቅን፡፡ ከዘጠኝ ሰዓት እስከ ምሽት ድረስ በአካለ ነፍስ ነፍሳትን አወጣቸው፡፡ በሥጋው ያስገባቸው አይደለም ወደ ተድላ ገነት ከዓርብ ምሽት እስከ እሑድ ሌሊት ነፍሱ በገነት ውስጥ ከሚኖሩ ከጻድቃን ነፍሳት ጋር የሚያለቅሱትን እያረጋጋች ያዘኑትን እያስደሰተች ተቀመጠች፡፡ ሥጋው ግን ነፍሱ ከወጣች በኋላ ከሦስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ከዘጠኝ ሰዓት እስከ ምሽት በዕፀ መስቀል ላይ ነበረች፡፡ ከዓርብ ምሽት እስከ እሑድ ሌሊት በመቃብር ውስጥ ተቀመጠች፡፡

አይሁድን «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፤ ከሦስት ቀን በኋላ አስነሣዋለሁ» እንዳላቸው[69] በእሑድ ሌሊት ነፍሱን ወደ ማደሪያው ሥጋ አስገባት፡፡ ከትንሣኤ በኋላ ግን የመለኮትን ትስብእት መከራ አላገኛትም፡፡ ወደማትገኝበት ሥፍራ ከፍ አለች፤ ወደ ማትዳሰስበት ተነጠቀች፤ የእሳት መጋረጃ ተጋርዶላት በብርሃን ድንኳኖች ተሰወረች፡፡ የመላእክትና የሰው ኀሊና ወደ ማይደርስበት በኪሩቤል ሠረገላ ተቀመጠች፡፡ የአምላክን ልጅ ስለ ሰውነቱ የምናመልከው አምልኮት እንደ መጀመሪያው አኗኗሩ ነው፤ አልተለወጠም፤ «ለትስብእቱ እንገዛለን፤ ለመለኮቱ እንሰግዳለን» አንበል፡፡ ሥጋ ለለበሰ ለመለኮቱ እንሰግዳለን፤ አምላክ ለሆነ ትስብእቱ እንገዛለን፤ ያለ ቍመራ፤ ያለ መጠመርና ያለ መለየት በአንድነት እናምናለን፡፡

67. መዝ. ፷፯፥፲፰፡፡
68. ዮሐ. ፲፥፲፰፡፡
69. ማቴ. ፳፮፥፷፩፡፡





ይኸውም አንድ እግዚአብሔር አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው፡፡ ለእርሱ ከሰ ውና ከመላእክት ዘንድ ከተፈጠሩ ከሁሉ ፍጥረት ዘንድ ለዘላለም ምስጋና ይገባል፡፡ አሜን፡፡

ከሰማይ ዋልታዎች የወደቁ፣ በውሾች ጠጉር ያደጉ፣ ሐሰትን የሚያጸድቁ፣ የሲኦልን በር የተጠጉ፣ ክርስቶስን «በሥጋውና በነፍሱ ወደ ፍርድ ቦታ ወረደ» የሚሉት የአርሲስና የመናፍቃን ዘለፋቸው ተፈጸመች፡፡

የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጅ ጊዮርጊስ ተናገረ /አለ/፡፡ ሕያዋንና ሙታንን ለሚገዛ ለእግዚአብሔር ለዘላለም ምስጋና ይሁን፡፡ አሜን፡፡



www.ethiopianorthodox.org

# [ምዕራፍ ፳፩]

## የፋሲካ ምንባብ

በልዕልናው የልዑላን ልዑል፣ በቅድስናው የቅዱሳን ቅዱስ፣ በንጽሕናው የንጹሐን ንጹሕ፣ በግርማው ግሩማንን የሚያስፈራ፣ በግዛቱ የገዥ ገዥ፣ በሐሳቡ የጥበበኞች ጥበበኛ፣ ስለ እርሱ ከዚህ እስከዚህ የማይባል፣ መጠኑ ይህን ያህላል፣ ስፋቱ ይህን ያህላል የማይባል፣ የእግሩ መረገጫ በዚህ፣ ራሱ በዚህ ነው የማይባል፣ መድረሻው እስከዚህ ነው የማይባል፣ በየዕለቱ በሁሉ ቦታ ምሉዕ ሆኖ ተአምራትን በሚያደርግ በእግዚአብሔር ስም እንጀምራለን። ለዘላለም አሜን።

የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት የሆነውን የልዮንን[1] ዘለፋ እንናገር ዘንድ በደል የመዘመዘን [የነተነተን] ከስካር መፍዘዝ፣ ከክፋት እንቅልፍ ራሳችንን እናንቃ። የአገር ሁሉ እናት ቁስጥንጥንያ ስሕተት በተሞላ ጉድጓድ ውስጥ ወድ ቃለችና የሮሚ አብያተ ክርስቲያናት በቁጥንጥንያ ላይ አልቅሱ። በወርቅ ምሰሶዎች ያጸናት የመንግሥት አገር፣ ዛሬ ግን በሽንበቆ ወደቀች። የቤተ ክርስቲያን ሹማምንት በልዮን ላይ አልቅሱ፤ የጴጥሮስን ሃይማኖት ሰይፍ ያለ አንጥረኛ እሳት አቅልጦ ጽጽስናውን አርክሷልና። የምስጢር ካህናት በቤተ መቅደስ ላይ አልቅሱ፤ የጴጥሮስ መንበር ተነዋውጧልና። እንግዲህ ውሾች በመሠዊያው አደባባይ የሚመላለሱ ሆኑ። የምድር ነገሥታት ምእመናን በመርቅያን ላይ አልቅሱ፤ ያለ አባቱ ነግሦአልና። የንጉሥ ልጅ ወደዋለችና የመንግሥቱን ዘመን አረከሰ። ይኸውም የእግዚአብሔር መንግሥት ነው፤ በልዮን ሃይማኖት ተባብሯልና። ጠቢቡ በመጽሐፈ ጥበብ «በእነዚህ በሦስቱ አገር ትነዋወጣለች። ባሪያ ሲነግሥ፤ ሴት እመቤቷን ስታቃልል እና ሴት ደግ ሰውን ስትገፋ» ሲል የተናገረው እውነት ነው።[2] መንበር በማይገባው የጉስቆለ ባሪያ በሆነ በመርቅያን መንግሥት [ዘመን] በእውነት አገር ተነዋወጠች።

1 ልዮን በሬቿው ምዕት ዓመት ለተከሰተው የቤተ ክርስቲያን ክፍፍል ምክንያት ለሆነው ጉባኤ ኬልቄዶን መግር አዘጋጅቶ የላከ ነው። በዚህም መግር ውስጥ በኤፌሶን የተወገዘውን የንስጥሮስን ትምህርት በማደስ ደግሞ ለተፋት ያተረበ የሮም ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ነበር። የኑፋቄ ትምህርቱ ዋና ሐሳብም ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ አለት የሚል ሲሆን ዛሬ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የምትከተለው የስሕተት ትምህርት መነሻ ነው። ጊዮርጊስ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ያለው የመንግሥቱ መቀመጫ ቁስጥንጥንያ በመሆንዋ በዚያ ሲጠራው ነው እንጂ የልዮን መንበሩ ሮም ነው።

2 ምሳ. ፴፥፳፩።





የአንጾኪያ ንጉሥ ልጅ አስቀድማ ያገባችውን ግብጻዊ የፈረሰች አረኛ አግሪጳን በአባቷ መንግሥት ላይ አስቀመጠችው። እርሱ ለሰይጣን እያጠነ ለአጋንንት እየሠዋ በአምልኮተ ጣዖት ዓለምን አረከሳት። አብያተ ክርስቲያናትን አፍርሶ አብያተ ጣዖታትን ከፈተ። ዳግመኛም የቁስጥንጥንያ ንጉሥ ልጅ መርቅያንን አግብታ በአባቷ መንበር ላይ አስቀመጠችው። እርሱም አስቀድሞ በንስጥሮስ ሃይማኖት በኋላም በልዮን ሃይማኖት ተባብሯልና አብያተ ክርስቲያናትን አረከሰ። ለንስጥሮስና ለልዮን ከአካላቸው አለመገረዝ ይልቅ የልባቸው አለመገረዝ ይከፋል። ነቢዩ ኤርምያስ «የአባላችሁን ሸለፈት ከምትገዙ ይልቅ የልባችሁን ሸለፈት ግረዙ።» እንዳለ።[3]

ዛሬ ሊቀ ጳጳሳት ልዮን የተሳሳቱ ሰዎች አለቃ ሆነ። በማይገባው የመንግሥት ወንበር ላይ የተቀመጠ ንጉሥ መርቅያንም አደባራትን፤ ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን አርክሶ፤ ትስብእት ገቶ አድርጉ በሁለት መንገድ ለክረስቶስ መገዛትን የምታገዘ ጠማር በመጻፍ ለምእመናን የማይገባ ሃይማኖትን ገዛ። ከወንጌል ቃል «መንፈስ ያድናል፤ ሥጋ ግን የሚጠቅመው የለም።» የሚለውን ምክንያት አድርገው። ይህን ቃል «መንፈስ ያድናል» ስለ መለኮት [የተነገረ ነው]፤ «ሥጋ ግን የሚጠቅመው የለም።» የሚለውን ስለ ትስብእት [የተናገረ] ብለው ተረጐሙት።[4]

የእፉኝት ልጆች መለካውያን [ንጉሣውያን] ሆይ! እንዴህ ትላላችሁን? መለኮት ግን ለብቻው የሚያድን ከሆነ ለምን የእግዚአብሔር ልጅ ከማርያም ሰው ሆነ። መለኮት ያለ ሥጋ ብቻውን የሚያድን ከሆነ «ስለ እናንተ የሚፈተት፣ ለብዙኀን ቤዛ የሚሰጥ ሥጋ ይህ ነው። እንካችሁ ብሉ» ለምን አለ? መለኮት ያለ ሥጋ ብቻውን የሚያድን ከሆነ «ሥጋዬን የበላ ስለ እኔ ሕያው ይሆናል፤ ደሚንም የጠጣ ሞትን አይቀምስም» ለምን አለ? መለኮት ብቻውን ያለ ሥጋ የሚያድን ከሆነ «ሥጋዬ እውነተኛ መብል ነው፤ ደሚም እውነተኛ መጠጥ ነውና» ለምን አለ?[5] መለኮት ብቻውን ያለ ሥጋ የሚያድን ከሆነ «አብ ሕያው እንደ ሆነ እኔም ስለ አብ ሕያው ነኝ፤ ሥጋዬን የሚበላ ስለ እኔ በሕይወት ይኖራል» ለምን አለ?[6] መለኮት ብቻውን ያለ ሥጋ የሚያድን ከሆነ «እኔና አብ አንድን» ስለምን አለ?[7] መለኮት ብቻውን

3. ኤር. ፬፥፬።
4. ማቴ. ፳፮፥፵፩።
5. ዮሐ. ፮፥፶፯።
6. ዮሐ. ፮፥፶፭።
7. ዮሐ. ፲፥፴።



www.ethiopianorthodox.org

ያለ ሥጋ የሚያድን ከሆነ ኦሪት ያገለገሏትን ነቢያት ለምን አላዳናቸውም? ኦሪት ግን እግዚአብሔር ሰው ሳይሆን የተነገረች የመለኮት ንባብ ናት። ስለዚህም ጳውሎስ በሙሴ ሕግ ኦሪት መጽደቅ በተሳነ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ልኮ ከሴት ተወለደ። ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ አለ።[8] እግዚአብሔር በመለኮቱ ባለ መድኃኒት ነው። በሰውነቱ [በትስብእቱ] የድውያን ፈውስ ነው። ባለ መድኃኒት ከእርሱ ጋር ፈውስ ከሌለ ምን ያደርጋል?

ድውያን በሚድኑበት ገንዘብ ባለመድኃኒት የፈውስ ዕፅንም ካላዘጋጀ ምን ይጠቅማል? ባለ መድኃኒቱ በታመሙ ሰዎች ልጅ ዘንድ አደረ። ለድውያን ፈውስ በሚሆንበት ገንዘብ ከእርሷ ምድራዊ ሥጋን ነሥቶ ከመለኮቱ ጋር አንድ አደረገው። ባለመድኃኒት ከሰማየ ሰማያት መጥቶ [ወርዶ] የፈውስ ዕፅ በዳዊት ቤት ተገኘ። ባለመድኃኒቱ ያለ መለኮትና ትስብእት መዋሐድ ፈውስ እንደ ማይሆን ዐወቀ። ስለዚህም ራሱን ሰው ለመሆን አሳልፎ ሰጠ። ድውይ ግን ለራሱ ፈውስን ያደርግ ዘንድ አይችልም። ነገር ግን ባለመድኃኒቱን ፈውስን በሚያገኝበት ገንዘብ [ሁኔታ] መድኃኒት ያደርግለት ዘንድ ይለምነዋል። ዳዊት፣ «ድውይ ነኝና አቤቱ ይቅር በለኝ፤ አጥንቶቼ ታውከዋልና ፈውሰኝ» ብሎ ለመነ።[9]

ነቢዩ በኦርዮ ሚስት ውበት በዲያብሎስ ጦር ተነድፎ እንደ ቆሰለና አጥንቶቹም ሰይጣን በተስተሰው የዝሙት ጾር ዝሙትን በመጐምጀት እንደ ታወኩ ዐወቀ። ባለመድኃኒቱ ልመናውን ተቀበለ። ከዱር ዕፅዋት ወይም ከገነት ዕፅዋት ፈውስን አልፈለገለትም። በሚድንበት ገንዘብ መድኃኒትን በእንስሳትና ወይም በዱር አራዊት ደም አላደረገለትም። በመዋለጃ ዘር ከወገቡ በወጣች፣ በዝሙት ጾር በነደፈችው በኦርዮ ሚስት በቤርሳቤሕ ማሕፀን ተወስና ፈውስን አደረገለት እንጂ። ዳግመኛም ይህች የመዋለጃ ዘር ከኃጥአን ወገብ ወጥታ በኃጥአን ማሕፀን ውስጥ ተቀምጣለች። ከኦርዮ ሚስት ከዳዊት ልጅ ከሰሎሞን ዘር ጀምሮ እስከ ኢያቄምና ሐና ልጅ ማርያም ድረስ እንግዲህ ከልጅ ልጆች /ከትውልድ ትውልድ/ የምትወጣ ሆነች። ይህች ግን በወንድና ሴት ፈቃድ በመዋለጃ ዘር ተወለደች። እርሷ ግን በፍጹም እንዳትረክስ መንፈስ ቅዱስ ጠበቃት፤ የእግዚአብሔር እናት ትሆን ዘንድ አላትና። ንጉሡ ከመግባቱ አስቀድሞ ደስተኛ ይሆን ዘንድ ሳይገባ አዳራሹን እንደ ሚያስጌጡት።

8. ገላ. ፬፥፬።
9. መዝ. ፮፥፪።





እግዚአብሔር ሙሴን፡- «ከማይነቅዝ እንጨት ታቦትን ለራስህ ሥራ። በውስጥና በውጭ ወርቅ ትለብጠዋለህ፤ በውስጧም የምሰጥህን ሕግ ታኖራለህ።» አለው።[10] እግዚአብሔር ለሙሴ በሰማይ ጽላት ኦሪትን ከመስጠቱ አስቀድሞ ለመቀመጫዋ ታቦትን ያዘጋጅላት ዘንድ አዘዘው። እንዲሁ ድንግል ማርያም በቅድስናና በንጽሕና ትሸለም ዘንድ አዘጋጃት። ውስጧን ያለው፡- በይውህናና በሐሳብ፤ ውጭዋን ያለው፣ በጾም በጸሎትና በንጽሐ ሥጋ መንፈስ ቅዱስን የሚያስደስተውን ነው፤ በንጽሐ ሥጋ መኖሯን የሚያመለክት ነው፤ የምሰጥህ አለ በውስጧ ታኖራለህ ያለው የሚያስደስተውን ይህም የእግዚአብሔር ትእዛዝ በሰማይ ጽላት ላይ እንደተጻፈ እንዲሁም የአባቱ ትእዛዝ በወልድ ኀሊና ውስጥ የተሳለ ነው።

ባለመድኃኒት በኃጢአት ጦር ወደ ታመመ ወደ ዳዊት ቤት መጣ። በልጁ ማሕፀን አድሮ መድኃኒትን አደረገለት። ከእርሷ በነሣው ሥጋ ቁስሉን ፈወሰው፤ ባለመድኃኒቱ ከአብ ዘንድ ከጽርሐ አርያም መጣ። ስሟ ጽዮን በተባለ በዳዊት አገር መድኃኒት ተገኘች። «ከጽዮን መድኃኒት ለእስራኤል ማን ይሰጣል?።» የተባለው ትንቢት ተፈጸመ።[11] «የሚያድን መንፈስ ነው። ሥጋ ግን የሚጠቅመው የለም።» ያለው ቃል ትርጉም ግን የአዳም ሥጋ ለልጆቹ ድኅነት [አልጠቀመም]። በእርሱ ላይ የመለኮት ተዋሕዶ [መዋሐድ] የለምና ከመሬት ወጥቶ ወደ መሬት ገብቶአልና። እንዲሁ የልጆቹም ሥጋ ለራሳቸው ወይም ለባዕድ ጠቃሚ አልሆነም፤ ሕያውና ማኅየዊ በሚሆን በመለኮት ኀይል አልተደመረምና [አልተዋሐደምና]። የእግዚአብሔር ልጅ ሥጋ ግን በመለኮቱ ጠቃሚ ነው። መለኮቱም በሥጋዊው ጠቃሚ ነው። በሥራ ሌላውን እንደ ሚረዳው አይደለም። በማትለያይ በአንድ ጽምረት [ተዋሕዶ]፤ በማትዋዋስ በአንዲት ህላዌ፣ በማይናወጥ በአንዲት ባሕርይ፣ በማይጐድል በአንዲት ዕሪና ያለ ነው እንጂ። ሰው ግን በፈቃዱ እግዚአብሔርን መሆን አይችልም፤ እግዚአብሔር ግን በፈቃዱ ሰው መሆን ይችላል። እግዚአብሔር በተዋርዶ ሰው መሆን ቢችልም ዳግመኛ ሰው መሆኑን በልዕልና እግዚአብሔር ወደ መሆን ይመልሰው ዘንድ ይችላል።

ክዋኔው ግን ወደ መለኮት ግዕዝ በጠባይ መመለስ አይደለም። በባሕርይም ወደ ሰው ልጅ ግዕዝ ጠባይ በመለወጥ አይደለም። መለኮትም ከመውጣት፤

10. ዘጸ. ፳፭፥፲፩።
11. መዝ. ፲፫፥፯።



www.ethiopianorthodox.org

ከድካም፣ ከረኃብና ጥም፣ ሕማምና ሞት ከመቀበል ሳይነካ፣ ትስብእ ትም የሰው ልጅን ሥርዐት ከኃጢአት በስተቀር በአንድ አካልና በአንድ ባሕርይ ሳይለይ [ሳይደመስስ] ነው። ከትስብእቱ መለኮቱ አልተለየም፤ ከመለኮቱ ተዋሕዶ ትስብእቱ አልተለየም፤ እግዚአብሔር ሰው ሆነ፤ ሰው ግን እግዚአብሔርን መሆን አልቻለም፤ ከኩነት በኋላ በሰማይት ካለው ከአባቱ ዘንድ ክብሩዐን አልተውም። ከመለኮቱ ጋር ሲያባምዳት ከእናቱ ዘንድ ሥጋዊን አልተወም።

የልዮን ሰው ሆይ! ትስብእት ከመለኮት ያንሣል ትላለህ? ከመለኮቱ ትስብእቱን አሳንሳችሁ አምልኮት ካደረጋችሁ እነሆ! እናንተ ባለ አራት ትባላላችሁ። ባለ ሦስት አይደላችሁም። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በሦስትነት ትክክል ናቸው። «የወልድ ትስብእት ግን ከመለኮቱ ጋር ትክክል አይደለም» ብትሉም «ከመለኮቱ ጋር ትክክል፤ አንድ አልሆነም» ብትሉ እነሆ! ወደ ሁለት አካል ከፈላችሁት። አንዱን ለማሳነስ አንዱን ለማብዛት አደረጋችሁ። እነሆ! እናንተ ካልተጠመቁ ከንዑሳን ክርስቲያን አንሳችሁ የሰይጣን መክፈልት ሆናችሁ። ከክርስቶስ መንጋ በጐች ተከፈላችሁ። አዳምም «ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» የሚለውን የአራት ቃል አፈረሳችሁ።[12] እንደ ኪሩቤልና እንደ ሱራፌል አላለም፤ እነርሱም ግን ፍጡራን ናቸውና። «ከእኛ እንደ አንዱ አለ» እንጂ። ከአዳም ልጅ ሥጋን ከነሣው ከወልድ ዋሕድ በስተቀር ከሥላሴ አንዱ ማነው? እነሆ የትስብእት ዕሪና [ትክክልነት] ከመለኮት ጋር ተገኘ።

ዳግመኛም በወንጌል «ፊልጶስ፦ ጌታ ሆይ! አብን አሳየንና ይበቃናል» ባለው ጊዜ እርሱም ፊልጶስ፤ ይህን ያህል ዘመን ከእኔ ጋር ስትኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን ዐይቶአል።» አለ።[13] «እነሆ! እኔን ያየ አብን ዐየ» ባለ ጊዜ ወልድ ትስብእቱን ከአባቱ መለኮት ጋር ያስተካክለዋል። ከትስብእቱ በስተቀር ወልድን ያየው ማን ነው? የአብ መለኮት እንዳልታየ መለኮቱ ግን ዐልታየም፤ የአብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ህልውና ግዕዝ [የባሕርይ ሥራ] አንድ ነውና። ትስብእቱን ስለ ዐየ የአባቱን መለኮት እንዳየ [የአባቱን መለኮት ከማየት ጋር] አተካከለው። መለኮቱ

12. ዘፍ. ፫፥፳፪።
13. ዮሐ. ፲፬፥፱።





ግን እስከ መቼም የሚታይ አይደለም። ዳግመኛም «ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ።» አለ።[14] ያለ ሥጋው በስተቀር [ሥጋው እንጂ] መለኮት ኅብስት ይባ ላልን? «ሥጋዬም እውነተኛ መብል ነው» ብሏልና።[15]

«ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በስተቀር ወደ ሰማይ የወጣ የለም።» ብሏልና።[16] የሰው ልጅ ግን ከሰማይ እንደ ማይወርድ ዕናውቃለን። ኀይልን ከሥጋዊ፥ ሥጋዊን ከኀይል እንዳንለይ የመለኮትን ወደ ትስብእት ኀይልን ከሥጋዊ፥ ሥጋዊን ከኀይል እንዳንለይ የመለኮትን ወደ ትስብእት መውረድ ቆጠረው እንጂ። እነሆ! ወደዚህም የትስብእት ዕሪና ከመለኮት ጋር አልተለየም። ጳውሎስም «ይኸውም የእግዚአብሔር መልክ ነው፤ ቀምቶ እግዚአብሔር የሆነ አይደለም እራሱን ገዥ አድርጐ የአዳምን ባሕርይ ገንዘብ አደረገ እንጂ፤ ሰውንም መስለ ሰው ሆነ ሰማ፤ ለሞት እስከመድረስም ታዘዘ ሞቱም በመስቀል የተፈጸመ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ ከፍ አደረገው ከስም ሁሉ የሚበልጥ ስምንም ሰጠው። በሰማይና በምድር በቀላይት ከምድር በታች ያለ ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይሰግድ ዘንድ።» አለ።[17] እነሆ! ጳውሎስ፦ «እኔን ያየ አብን አየ»[18] ያለውን አንድ ወልድ ቃል ሥጋዊውን ማየት የአብን መለኮት እንደ ማየት እንደሚቆጠር ደገመ። ጳውሎስም፦ «የወልድን የሥጋዊ መልክ ወደ አብ መልክ አርኣያ አየሳየ እርሱ «በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደ ሚገባ ነገር አልቆጠረውም፤ ነገር ግን የባሪያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ገዥ አደረገ፤ ለሞትም ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።» ብሏልና።

«ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም» ያለው ስለ ሰውነቱ እንደ ሆነ ዕወቅ። መለኮቱ ግን ከዓለም አስቀድሞ እግዚአብሔር ነው። ዓለምንም በፈጠረ ጊዜ እግዚአብሔር ነው። በነቢያት እግዚአብሔር ነው በሥጋዊው ከባሕርዩ ሳይለወጥ እግዚአብሔር ነው። ስለ ትስብእቱ «እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም።» አለ። የትስብእትን እግዚአብሔር ወደ መሆን መንጠቅን

14. ዮሐ. ፮፥፵፩።
15. ዮሐ. ፮፥፶፭።
16. ዮሐ. ፫፥፲፫።
17. ፊልጵ. ፪፥፮-፲።
18. ዮሐ. ፲፬፥፱።



www.ethiopianorthodox.org

ይናገራል። የእግዚአብሔር ሰው ለመሆን መዋረድ በአምልኮት ትክክል
ይሆን ዘንድ ነው። የሚጠፋ ሥጋን ተዋሐደ። ይህን የሚጠፋውን ሥጋ
የማይጠፋ አደረገው። ይህን የሚሞተውን ሥጋ ከማይሞት ህልውና ጋር
ይተካከል ዘንድ የማይሞት አደረገው። ምድራዊ ሥጋን ተዋሐደ፤ ይህ
ምድራዊ ሥጋ ከእርሱ ልዕልና ጋር ትክክል ይሆን ዘንድ ሰማያዊ
አደረገው። የተዋረደ ሥጋን ተዋሐደ። ይህን የመከራ ሥጋ ደካማው
ከእርሱ ኃይል ጋር ትክክል ይሆን ዘንድ ለክብር አደረገው። የሚታ
መም ሥጋን ተዋሐደ። ይህ ምድራዊ ሥጋ ከእርሱ ልዕልና ጋር ትክ
ክል ይሆን ዘንድ ሰማያዊ አደረገው። የሚታመም ሥጋን ተዋሐደ።
ይህን የሚታመመውን ሥጋ ከማይታመም ባሕርዩ [ህላዌው] ጋር ትክ
ክል ይሆን ዘንድ የማይታመም አደረገው። እንዳይለያይ በጽምረት
[በአንድነት] አዋሐደው፤ እንዳይጨምርም በመጠበቅ [በተዐቅቦ] አኖረው።
የተደመረው [የተዋሐደው] ጠባዩን በማስወገድ አይደለም። ሰው የሆነውም
በመለኮት መለወጥ አይደለም። በትንሣኤው ጊዜ እንደ ኢያኢሮስ ልጅ
ጣቢታ ተነሺ ብሎ የሥጋውን በድን [ነፍስ የተለየውን ሥጋ] አልጠራም።
እንደ ወልደ መበለትም [እንደ መበለቲቱ ልጅም] የአልጋውን ሸንኮር
አልዳሰሰም።

ዳግመኛም እንደ አልዓዛር ተነሥ፤ ወደ ውጭ ውጣ ብሎ አልተጣራም። ከፊ
ጣራ ዘንድ የጥሪት ሥራ አገልጋይ እንዳይሆን። «አንዱ ፍጡር አንዱ ፈጣሪ፣
አንዱም ይበልጣል አንዱም ያንሳል» እንደ ሚሉ እንደ መለካውያን
አምላካችንን እንዳናከፋ።

ስነርች የሮሜ ታላላቆች ሆይ! እግዚአብሔር ከጎስቋላች ሥጋችን
ጋር መሳተፍን ካላፈረ ሥጋዊን ከመዋረድ ከፍ ማድረግና ከመለኮቱ
ጋር መስተካከልን እንዴት ያፍራል? ትስብእቱንም በመለኮቱ ክብር
ያሳተፈው ዘንድ ካልፈቀደ መለኮቱን በትስብእቱ ነገር [መዋረድ]
ቢያሳትፈው ከበሩን መከራ መሸከሙ ያስደንቀዋል። ለጎስቋለው ክብርና
ምስጋና መሸከም አይደንቅለትም። ዳግመኛም ሕያውን ሕማምና ድካም
በመሸከሙ ያስደንቀዋል። ሕመምተኛው የዘላለም ሕይወትን መሸከሙ
አይደንቅለትም። እግዚአብሔር የመለኮቱን ክብር ወደ ሥጋዌ ነገር
[መከራ] ማውረዱ ካላ ስደንቀው ሥጋዊውን ወደ መለኮቱ ክብር ከፍ
ማድረጉ እንዴት ያስደንቀዋል።?





የሮሜ ሰዎች ሆይ! የተደሰታችሁትን ያህል ትተክዛላችሁን? እግዚ
አብሔር የሰውን ልጅ ወድዶ የእኛን ሥጋ ከመለኮቱ ጋር ትክክል አደረ
ገው። ሥጋዊውን ከመለኮቱ ጋር ስለ አደረገው ለእግዚአብሔር ትተክ
ዙለታላችሁ።? ሰማያትን ዝቅ አድርጐ ወደ ምድር በወረደ ጊዜ «አቤቱ፤
ወደ ደካሞች መከራ ለምን ትወርዳለህ?» አላላችሁም? የእኛን መከራ
እንዳትሸከም ወደ ሴት [ድንግል] ማሕፀን ለምን ትመለሳለህ አላላችሁም?
የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድከም ከቻላችሁ «ለምን ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ
በመሬታዊ ሰው ትጠመቅ ዘንድ አትወረድ» አትሉትም? የእግዚአብሔርን
ትሕትናውን ማስተንጎል ከተቻላችሁ ዳግመኛ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መከ
ልከል ብትችሉ «በጲላጦስ አደባባይ ላይ አትቁም፤ የመስቀል ኀፍረትን
አትቀበል» ለምን አትሉትም?

እንደገናም «በፍርድ ቦታ መሠቃየት ይሻለናልና፤ ስለ እኛ ከሞት
ሞት በፍርድ ቦታ መሠቃየት ይሻለናል፤ የሞትን ጽዋ ስለ እኛ አትጠጣ»
ለምን አትሉትም?

እኔ ግን ስለ እናንተ እላለሁ፦ በእርሱ ሞት የሕይወትን ተስፋ ከምታ
ገኙ ይልቅ በፍርድ ቦታ መቆመጥ ይሻላችኋል? እንደ ልባችሁ ፍላጐት
አግኙ። መለኮቱን መከራ ከመቀበል መከለከል ከተቻላችሁ ሥጋዊውን
በመለኮት ዕሪና ክብርና ድካም ከመቀበል መከልከል እንዴት ትችላ
ላችሁ? እኔ ግን ማርያም ለእርሷ መድኀኒትና የእኔ መድኀኒት ትወልድ
ዘንድ ሔዋን እንኳን ከተከለከለችው ዕፅ በላች እላለሁ።

ሔዋን በትእዛዝ እግዚአብሔር ተጠብቃ ብትኖር ብቻዋን ከባለቤቷ
ጋር በገነት ፍሬዎች እየተደሰተች በተቀመጠች ነበር። የኃጢአቷን
ፍዳ ለማስቀረት ከዘሮቿ ዘር ድንግል ማርያምም ባልተወለደች፤ የሴት
ልጇ ልጅ በመለኮት ጨው አልጫ ያደረገቻት የእባብ መርዝ አልጫ
ባልሆን ነበር። ዳግመኛም አዳም ከገነት ይሰደድ ዘንድ ከተከለከ
ለው ዕፅ ለመብላት እንኳን እጁን ዘረጋ እላለሁ። አዳም ከገነት ባይሰ
ደድ የእግዚአብሔር ልጅ አዳምን ወደ ገነት ይመልሰው ዘንድ በዕፀ
መስቀል ላይ እጆቹን ባልዘረጋ። አዳም በገነት ቢቀመጥ ግን መድኀኒ
ታችን ከማርያም ባልተወለደ፤ በተድላ ገነት ውስጥም የመዋለጃ ዘር
ባልሆነም፤ በውስጧ የሚያድሩ በሰማይ ሥርዐት ያኖራልና በገነት ዐጸድ
የወንድና ሴት ግንኙነት [ሩካቤ] የሚገባ ቢሆን አዳም ሔዋንን ባወቃት



www.ethiopianorthodox.org

ነበር፡ በዚያ ለሰባት ዓመት ያህል ተቀምጠዋልና። የኋት ዐጸድ ግን የቅዳሴ ቦታ ነውና በውስጧ የሥጋና ደም ሕግ ያደርግ ዘንድ አይቻልም [አይገባም]።

በገነት ውስጥ ግን ለሰባት ዓመታት ያህል እንደ ተቀመጡ ለሙሴ በአምሳለ መልአክ እንደ ነገረው በመጽሐፈ ኩፋሌ ይገኛል።[19] አዳም ከሔዋን ጋር ከገነት ከወጡ በኋላም [ሩካቤ ሥጋ] ግንኙነትን አላደረጉም። እኛም በሥጋ የእግዚአብሔር ዘመድ ባልሆንን። ሰነፉ ሆይ! እግዚአብሔር አዳምን ሳይፈጥረው አስቀድሞ ትእዛዙን ተላልፎ የተከለከለውን ዕፅ እንደሚበላ የማያውቅ ይመስልሃልን? እግዚአብሔር ከአዳም ጎንአን እንደሚወለዱ ካላወቀ፡ ለምን ፈቃዱን ለማያደርጉት ማደሪያ ይሆናቸው ዘንድ ገነትንም አዘጋጀት? ጻድቃን ከአዳም እንደ ሚወለዱ ካላወቀ ለምን ትእዛዙን ለጠበቁ ርስት ትሆናቸው ዘንድ ተድላ ገነትን አዘጋጀት?

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከመፍጠሩ አስቀድሞ ትእዛዙን በመተላለፍ እንደሚበድል ዐውቋል። ስለዚህ «ሰው ከታናሽነቱ ጊዜ ጀምሮ በልቡ ውስጥ ተንኰል ተሸሽጓልና» አለ።[20] ዳግመኛ እግዚአብሔር ከአዳም ልጅ ተወለደ፡ ከእርሷ የነሣውን ሥጋ ከመለኮቱ ጋር ትክክል እንደሚያደርገው ዐወቀ። ስለዚህ «አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» «አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ ሕያው ሆኖ እንዳይኖር» አለ። እነሆ! ትስብእት ከመለኮት ጋር ትክክል እንደ ሆነ ታወቀ። አስቀድመን እንደ ተናገርን ጳውሎስ፦ «ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደ ሚገባ ነገር አልቆጠረውም። ነገር ግን የባሪያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ። እንደ ባሪያ ሆኖ እንደ ሰው ታዛዥ ሆኖ ራሱን አዋረደ። ለሞትም ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ ብሎ ምስክር ሆነ።»

ሰነፉ ሆይ! መለኮት ለሞት ሥልጣን እንዳልተያዘ ዕወቅ። ስለ ትስብእቱ ሐዋርያው ይህን አለ። ከዚህም በማስከተል «በዚህም ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፣ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፡ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር

19. ኩፋ. ፬፥፲፱።
20. ኤር. ፲፯፥፱።
21. ዘፍ. ፫፥፳፪።



www.ethiopianorthodox.org



ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።» አለ። የወልድ ትስብእቱ ከመለኮቱ ጋር ትክክል ካልሆነ ግን ጳውሎስ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ የክብር ጌታ እንደ ሆነ ይል ዘንድ እንዴት አለ? እነሆ! የወልድን ሰውነት ከፈጣሪ መለኮቱ ጋር አስተካከለው።

ገብርኤልም «ወልድን ትወልጃለሽ» ብሎ ባበሠራት ጊዜ «መለኮትን ትወልጃለሽ» አላለም። ዳግመኛም ትስብእትን ትወልጃለሽ አላለም። የትስብእትና መለኮት ጉዳናን በአንድ መልክ ሲያሳይ «ወልድን ትወልጃለሽ» አለ እንጂ። ድንግልም በወለደችው ጊዜ እንደ ትንሽ ልጅ፥ እንደ ሕፃናት ሥርዐት እንዳይጮኽ በሁለት ወገን በማሕፀኗ የተቀመጠ አይደለም። መለኮቱ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍም በሁሉ ቦታ ምሉዕ ሆኖ የተለመደው የክብር ኀይል እንዳይጓደል እርሱ የሚሸከማት ሲሆን እናት ለመሆን ተገባችው፡ እርሱ ዓለምን ካለ መኖር ወደ መኖር ያመጣና የዓለም አባት ሲሆን ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ ተወለደ። በዚህም ከእርሷ የተወለደው እግዚአብሔር እንደ ሆነ ዐወቅን። በመለኮት [ተዋሕዶ] ካልሆነ በስተቀር ሰው ግን በተዘጋ በር መውጣት አይችልምና በክንዶቿ ታቅፎ [እቅፍ ውስጥ ሆኖ] በእጆቿ ተዳሰሰ። በዚህም በእቅፍ የተቀመጠው እርሱ የሰው ልጅ እንደ ሆነ ዐወቅን። በዚህም የሕፃናትን ሥርዐት እንደ ሰው ልጅ የፈጸመ እርሱ እንደ ሆነ ዐወቅን። ከትስብእት ጽምረት [ያለ ተዋሕዶ] እሳተ መለኮትን መዳሰስ የሚችል የለምና ወንድ ከማታውቀው ከድንግል ጡቶች ወተት መነፈ። ከዚህም ከእርሷ የተወለደው አምላክ እንደ ሆነ ዐወቅን፡ ኪሩቤል ዐለት ውሃን ካፈለቀው በስተቀር ከድንግል ጡቶች ወተትን ማመንጨት የሚችል የለምና። ዳግመኛም ብቻውን በድንግል ማሕፀን ካደረ ከእግዚአብሔር በስተቀር በድንግልና ወተት ያደገ የለም። እነሆም በአንድ መንገድ አምላክም ሰውም ነው።

ዳግመኛም ትስብእት በዮርዳኖስ ወንዝ በትስብእት ሕግ [በሰው ሕግ] ለመጠመቅ አኍንብሶ [ራሱን ዝቅ አድርጐ] የመለኮት እና የተስብእትን ተዋሕዶ ዐሳየ። «አብም የምወደው ልጄ ይህ ነው፡ እርሱን ስሙት» ብሎ ምስክር ሆነ።[22] ስለ መለኮቱ ሳይለይ ስለ አንዱ ምስክር ሆነ። ስለ ትስብእቱም ሳይለይ በአንድ ጥሪ «የምወደው ልጄ ይህ ነው» አለ እንጂ። ድንግል ከእርሷ ሥጋ ነሥቶ በተዋሕዶ ያለ መለኮት ብቻዋን ሥጋዊን

www.ethiopianorthodox.org

ከእራሷ ሥጋ [ብቻ] እንዳልወለደች እንደዚሁም አብም ስለ ልጁ በመ ስክረ ጊዜ ስለ ነደል [መለኮቱ] ሥጋዊን አልለየም፡ በማዋሐድ «የምወደው ልጄ ይህ ነው» አለ እንጂ።

ለአባቱ አንድ ቢሆንም መለኮቱ ከሥጋዊው አልተለየም። ለእናቱም አንድ ቢሆንም ትስብእቱ እና መለኮቱ አልተለያየም። መለኮቱ ከትስብእቱ፣ ትስብእቱም ከመለኮቱ የዐይን ቅንድቦች ጥቅሻ ያህልና የዐይኖች ጥቅሻ መጠን ያህል ከተዋሕዶ በኋላ አልተለየም። ስለ ሥጋ ዊውም ዳዊት «እግዚአብሔር አለኝ፡ አንተ ልጄ ነህ፡ እኔ ዛሬ ወለድ ሁህ፡ ለምነኝ፡ አሕዛብን ለርስትህ የምድርን ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥ ሃለሁ።»[23] እንግዲህ ዳዊት እስከ ምድር ዳርቻ ነግሦ ነበርን? የአሕዛብን ግዛት ርስት አድርጐ ሰጠውን? ግዛቱ ከይሁዳ ግዛት፡ መስፍንነቱም ከኢየሩሳሌም አውራጃ አላለፈችም። ይህን ስለ ወልድ ተናገረ። የወልድ ሥጋው ከዳዊት ዘር ነውና «ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ፡ ለመሲሐዬም [ለተቀባው] መብራትን አዘጋጀለሁ።» እንደ ተባለ።[24] በሌላም በኩል እግዚአብሔር ለዳዊት ማለ፡ አይጸጸትም፡ ከሆድህ ፍሬ በመንበርህ ላይ አስቀምጣለሁ።» ይላል።[25] ገብርኤልም ማርያምን «እግዚአብሔር አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል።» አላት።[26] እንግዲህ ክርስቶስ በአባቱ በዳዊት መንበር ላይ መቼ ተቀመጠ? ከይሁዳ ንጉሥ ሄሮድስ ፍርሀት የተነሣ እናቱ ከቦታ ቦታ እያሸሸችው በችግር ያደገ አይደለምን?

«የጥበብ ሰዎች ሰብአ ሰገል፣ የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ ዐይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። ንጉሡ ሄሮድስም ሰምቶ ደነገጠ፡ ኢየሩ ሳሌምም ሁሉ ከእርሱ ጋር። የካህናትንም አለቆች የሕዝቡንም ጸፎች ሁሉ ሰብስቦ ክርስቶስ ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው። አንቺ ቤተ ልሔም የይሁዳ ምድር ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሽም። ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና ተብሎ በነቢይ ተጽፏልና በይ ሁዳ ቤተ ልሔም አሉት።[27]

ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገልን በስውር ጠርቶ ኮከቡ የታየበትን

23. መዝ. ፪፥፯።
24. ማቴ. ፻፴፩፥፲፯።
25. መዝ. ፻፴፩፥፲፩።
26. ሉቃ. ፩፥፴፪-፴፫።
27. ሚክ. ፭፥፪።





ዘመን ከእነርሱ በጥንቃቄ መርምሩ፣ ባገኛችሁትም ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ አላቸው። እነርሱም ንጉሡን ሰምተው ሔዱ። እነሆም በምሥራቅ ያዩት ኮከብ ሕፃኑ ባለበት ላይ መጥቶ እስኪ ቆም ድረስ ይመራቸው ነበር። ኮከቡንም ባዩ ጊዜ በታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው። ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፤ ወድቀውም ሰገዱለት፤ ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤም አቀረቡለት።[28]

እነሆ! አሕዛብ የአምላክን ልጅ ለመቀበል ለመንግሥቱ እጅ መንሻ በመስጠት ቀደሙ። «የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመ ጣሉ፣ የዐረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻ ያቀርባሉ» የሚል ጽሑፍ እንደ ተጻፈ።[29] ዳግመኛም «እርሱ ይኖራል፥ ከዐረብም ወርቅ ይሰጡታል፣ ሁልጊዜም ወደ እርሱ ይጸልያሉ፣ ዘወትርም ያመሰግኑታል።»[30] የሚል ጽሑፍ ተጽፏል። ከዚህ በኋላ ወደ ሄሮድስም እንዳይመለሱ የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም ለሰብአ ሰገል ታያቸው። እንዳዘዛቸው አድርገው በሌላ መንገድ ወደ አገራቸው ሔዱ። «ሄሮድስ ሰብአ ሰገል እንደ ተሳለ ቂበት ዐውቆ እጅግ ተቆጣና ልኮ ከሰብአ ሰገል እንደ ተረዳው ዘመን በቤተልሔምና በአውራጃዋ የነበሩትን ኹለት ዓመት የሆናቸውንና ከዚ ያም የሚያንሱትን ሕፃናትን ሁሉ ይገድሉ ዘንድ አዘዘ።»[31] በንጹሐን ሕፃናት ላይ የሞት ፍርድ ከገሊላ ንጉሥ ከሄሮድስ አፍም ወጣ።

የአሕዛብ ነገሥታት በዕጣን ሀብት ለክህነቱ፣ በወርቅ ሀብት ለመንግ ሥቱና በከርቤ ሀብት ለሥጋው መገነዣ ይሆን ዘንድ እጅ መንሻ አገቡለት። ከእናቱ ሕዝብ ነገድ የሆነው የገሊላ ንጉሥም [ሄሮድስም] የሞትና የሕይወት ሥልጣን በእጁ ያለውን [ኢየሱስ ክርስቶስን] በሞት ፍረድ መታሰቢያውን ሽሮ በሰይፍ እጅ ይነሣው ዘንድ [በሰይፍ ይቀ ላው ዘንድ] ወደደ። «ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታይቶ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ። ሕፃኑ ንና እናቱን ያዝና ወደ ግብፅ ሒድ አለው። ዮሴፍም ተነሥቶ ሕፃኑንና እና ቱን ይዞ ወደ ግብፅ አገር ሔደ።[32] እነሆ! እግዚአብሔር በፈጣን ደመና

28. ማቴ. ፪፥፱-፲፩።
29 መዝ. ፸፩፥፲።
30. መዝ. ፸፩፥፲፭።
31. ማቴ. ፪፥፲፮-፲፰።
32. ማቴ. ፪፥፲፫-፲፭።

www.ethiopianorthodox.org

ተተምጦ ወደ ግብጽ ይመጣል የግብጽ ሰዎች በእጃቸው የሰሩት ጣኦትም በፊቱ ይደቃል።» ተብሎ በነቢዩ ኢሳይያስ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ወደ ግብጽ ሔደ።[33]

ሄሮድስም የሕፃኑን መኖሪያ ቦታ ባጣ ጊዜ በእርሷ ላይ ከፈሰሰው የሕፃናት ደም የተነሣ የገሊላ ምድር እስክትቀላ ድረስ ሕፃናትን ይገድል ዘንድ ጀመረ። ልጆቻቸው ከተገደሉባቸው ሴቶች [እናቶች] ጡቶች ከተን ጠባጠበው [ከፈሰሰው] ወተት የተነሣ ኩሬ የሆነ ቦታም አለ። ከቅንድቦቻቸው [ከዐይኖቻቸው] ከፈሰሰው እንባ የተነሣ የራብ ቦታም አለ፤ በገሊላ የእንባ ዝናም ፈስሶ የልቅሶው ጩኸት እስከ ረጅሙ ሰማይ ወጣ። ስለዚህ እግዚአብሔር የሄሮድስን ሞቱን አፋጠነው። ለእንደዚህ ዓይነት አውሬ ምን ያህል የሥቃይ ቅጣት ይገባዋል? ለእንደዚህ ዓይነት ክፉ ምን ያህል የገሃነም ሥቃይ ይገባዋል? የልቡ ክፋት እንደ ሰው ልጅ የልብ ክፋት አይደለም፤ የእባብ ልብም በክፋት ይከፋል። ሕፃን እባብን በእጁ እንደ ያዘው ቢጫወትበትም በላዩ ላይ [በእርሱ ላይ] መተናኮል አይችልም። በጥርሶቹም አይነክሰውም። የሕፃኑ የየዋህነቱ ኀይል የእባቡን የልብ ክፋት ያሸንፈዋልና። ሄሮድስ ግን ጡት የሚጠቡ ሕፃናትን የእናታቸውን ጡቶች መከልከል አያሳዝነው።

ወታደሮች አንገታቸውን ለማስተላት አሳልፈው ሲሰጡአቸው እነርሱ ግን ለግድያ እንደሚሰጡአቸው ሳያውቁ በየዋህነት ይሥቁላቸው ነበር። ኹለተኛው ሄሮድስ ከነቢያት ሁሉ በሚበልጠው በዮሐንስ ደም በደልን ጀመረ። በኋላም በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከሰቃልያን ጋር ተሳተፈ። ወንጌላዊው እንደ ተናገረው ጲላጦስ ግን ገሊላ ሲሉ በሰማ ጊዜ «የገሊላ ሰው ነውን? ብሎ ጠየቀ። ከሄሮድስ ግዛት እንደ ሆነ ባወቀ ጊዜ ወደ ሄሮድስ ሰደደው፤ እርሱ ደግሞ በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም ነበርና። ሄሮድስም ኢየሱስን ባየው ጊዜ እጅግ ደስ አለው፤ ስለ እርሱ ስለ ሰማ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሊያየው ይመኝ ነበርና። ምልክትም ሲያደርግ ሊያይ ተስፋ ያደርግ ነበር። በብዙ ቃልም ጠየቀው። እርሱ ግን አንድ ስንኳ አልመለሰለትም። የካህናት አለቆችም ጻፎችም አጽንተው ሊከሱት ቆመው ነበር።

33. ኢሳ. ፶፫፥፯።



www.ethiopianorthodox.org



ሄሮድስም ከሰራዊቱ ጋር ናቀው፤ ዘበተበትም፤ የጌጥ ልብስም አልብሶ ወደ ጲላጦስ መልሶ ሰደደው። ሄሮድስና ጲላጦስም በዚያን ቀን እርስ በርሳቸው ወዳጆች ሆኑ፤ ቀድሞ በመካከላቸው ጥል ነበርና።»[34]

በእውነት የገሊላው ንጉሥ ከኢየሩሳሌሙ መስፍን ጋር የቀደመ ጠባቸውን በንጹሕ ደም ትተው ከሰቃልያን ጋር በእግዚአብሔር መሲሕ ላይ አጉረመረሙ። ሐዋርያት በመዝሙር ኹለት ትርጓሜ እንደ ተናገሩት፦ «አሕዛብ ለምን ያጉረመርማሉ? ወገኖችስ ለምን ከንቱን ይናገራሉ? የምድር ነገሥታት ተነሡ፤ አለቆችም በእግዚአብሔርና በመሲሑ ላይ ሄሮድስና ጲላጦስ በእግዚአብሔር መሲሕ ላይ በእውነት አጉረመረሙ።[35] ስለዚህም የገሊላ ነገሥታት መንግሥት ተወገደ። ከሳኦል እስከ ፍልሰተ ባቢሎን በጽዮን ቅባት ቀንድ ይሾሙ ነበር። ከፍልሰተ ባቢሎን እስከ ጽዮን ምርኮ መመለስ ድረስ ያለ ንጉሥ፤ ያለ አለቃ፤ ያለ ካህን እና ያለ ልብሰ ተክህኖ ሰባ አምስት ዓመት ተቀመጡ። ከጽዮን ምርኮ መመለስ በፋርስ ንጉሥ በዳርዮስ ዘመን በዘሩባቤል እጅ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በታነጸ ጊዜ የገሊላም መንግሥት ወደ ዳዊት ዘር ገባች። የአሕዛብ ነገሥታት ይገዙአቸዋል እንጂ ሹመታቸው እንደ ቀድሞው በጽዮን ቅባት ቀንድ አይደለም። ከለዳውያን የገዙአቸው ጊዜ አለ፤ ሚደናውያን የገዙአቸው ጊዜ አለ፤ ሮማውያንም የገዙአቸው ጊዜ አለ። እንግዲህ በምርኮ እስከ ገበብት ጊዜ ድረስ መሲሐውያን አልተሾሙም።

በዝሙት ፍትወትና በደልን በማምጣት ሳይሆን የሰውን ልጅ ጠባይ የሚገዛ መራራ የሞት ጽዋን በመጠጣት ለሥጋ ሕግ ተገዛ። የሚያጠፉትን በማጥፋት አልተገዛላትም። ጴጥሮስን «ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይሞታሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ እንዳለው። ወይስ አባቴን እንድለምን እርሱ አሁን ከዐሥራ ኹለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይችል ይመስላችኋልን? እንዲህስ ከሆነ እንደዚህ ሊሆን ይገባል።» የሚሉ መጻሕፍት እንዴት ይፈጸማሉ?»[36] ለጠባይ በሚገዛ ገንዘብ ለሥጋ ሕግ ተገዛ። ለቅዱሳን በማይገባ ገንዘብ እግዚአብሔርን በማያስቆጣ ገንዘብ አልተገዛለትም። ሁሉም ኃጢአት ከሥጋ አይደሉምና

34. ሉቃ. ፳፫፥፯-፲፪።
35 መዝ. ፪፥፩-፪።
36. ማቴ. ፳፮፥፶፪-፶፫፤ ዮሐ. ፲፰፥፲፩።

የሥጋን ድካም ከሚገዛ ከሰይጣን እንጂ:: የኢየሱስ ድካም በሕገ ሥጋ የሥጋን ድካም ከሚገዛ ከሰይጣን እንጂ:: የኢየሱስ ድካም በሕገ ሥጋ እግዚአብሔርን በሚያሳዝነው ገንዘብ አይደለም:: ሥጋውም ኃጢአትን ለመሥራት አይደለምና የሰይጣን ሥልጣን አይቀርበውምና:: ስለዚህ ጳውሎስ «ኃጢአተኛ ሥጋን ለብሶ ይህችን ኃጢአት ገዛት [ፈረደባት]::» አለ::[37]

እግዚአብሔር ሰውነታችንን በመለኮቱ ያስተካክል ዘንድ ከእኛ ለእርሱ አደረገ:: የእርሱንም ኃይል ወደ እኛ ሥጋ መለሰው:: ከእኛ ያለ ሩካቤ ሰው ሆኖ በንጽሕና ተዋሐደን:: ወንጌላዊው ዮሐንስ፦ «ቃል ሥጋ ሆነ፡ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ» ብሎ እንደ ተናገረ::[38] የዚህች ቃል ትርጉም ምንድን ነው? ዐይኖቻችሁ የጨለሙ፣ ጆሮዎቻችሁ የደነቆሩ፣ ልባችሁ የጠፋ ሆይ! በዚህም ትስታላችሁ ልብ አላችሁ [እያላችሁ] ከአዳም ልጅ ሰው የሆነውን አታስበሉትም፡ ጆሮ አላችሁ ለሥጋዌ ነቢያት የተናገሩትን ቃል አታደምጡም፡ ዓይን አላችሁ ስለ እርሱ የተጻፈውን የመጽሐፍት ገጽን አትመለከቱም፣ ቃል ሥጋ ሆኖ በማርያም ዘንድ እንደ አደረ ትላላችሁ? አስቀድሞ ሥጋ ከሆነ ከማርያም ሥጋዌን [ሥጋ መልበስን] ለምን ወደደ? አንዱ የሚቀድም አንዱ የሚከተል ኹለት ሥጋዌ ለወልድ አለውን? ሐሰት ነው፡ እግዚአብሔር ከማርያም በስተቀር ሰው አልሆነም::[39]

«ቃል ሥጋ ሆነ በእኛ አደረ» የሚለውን ነገር ትርጉም ስሙ፤ [ልንገራችሁ]:: «ቃል ሥጋ ሆነ» ከቅድስት ድንግል ማርያም ቃል ሥጋ በመሆኑ [በመዋሐዱ] ይተረጎማል:: «በእኛም አደረ» የሚለው የክርስቶስ ጸጋ በሐዋርያት ላይ ወደ ማደሩ ይተረጎማል:: ራሱ በወንጌል «እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ::» እንዳለ::[40] ክርስቶስ የሚኖረው ከሐዋርያት ጋር ብቻ አይደለም፡ በቃላቸው ካመኑበት ሁሉ ጋር እንጂ:: «የሚወደኝን አባቴ ይወደዋል፡ ከእርሱ ጋር መጥተን በእርሱ ዘንድ ማረፊያ እናደርጋለን» ብሎ ራሱ እንደ ተናገረ::[41]

ስነሮቹ ሆይ! ክርስቶስ በድንግል ማሕፀን ሳያድር ሥጋ እንዳልተዋሐደ ዕወቁ:: ነገር ግን አስቀድሞ ሥጋ ሳይሆን በሥጋውያን ልጅ ማሕፀን ውስጥ አድሮ ሥጋ ሆነ:: ያለ ወንድና ሴት ዘር ልማድ እናቱ ያለ

37. ሮሜ. ፰፥፫-፬::
38. ዮሐ. ፩፥፲፬::
39. ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው ሆነ::
40. ማቴ. ፳፰፥፳::
41. ዮሐ. ፲፬፥፳፫::





ወንድ ዘርና ያለ ዕንስ ልማድ ትፀንስ ዘንድ አደረጋት:: ያለም ምድራዊ አባት ከእርሷ ይወለድ ዘንድ አደረገ:: ወልድ ለአባቱ ብቸኛ ነው:: ወንድምና እኅት የለውም:: ስለ ልደቱም አኗኗር ከዚህ እስከዚህ የሚባል ነው:: በአባቱ ህላዌ ጸዳልና በአባቱ መልክ አርአያ የተገለጠ ነው:: በመንግሥት [ግዛት] በክብር በመለኮት እኩል ትክክል ነው:: በኋለኛው ዘመን በራሱ ፈቃድ፣ በአባቱ ፈቃድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የተወለደ ነው::[42]

ብቻው ቃል ከብቻዋ ድንግል፡ ብቻው ኃይል ከብቻዋ ምድራዊት፡ የማ ይዳሰስ እሳት፣ ብቻውን የማይታይ መንፈስ፣ ብቻውን ከብቻዋ ሴት ሰው የሆነ ነው:: አርዮስ ፍጡር ሊያደርገው ያሰበው እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የአርዮስን ትምህርት የተከተሉ አርዮሳውያን ይባላሉ:: ንስጥሮስ ከነቢያት እንደ አንዱ ያሰበው እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የእርሱን ትምህርት የተከተሉ ንስጥሮሳውያን ተባሉ:: አርጌንስ ከአባቱ ማነሱን ያስተማረበት እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የእርሱን ትምህርቱንም የተከተሉ አርጌንሳውያን ተባሉ፡ መንክዮስ ሥጋዌውን ምትሐት ያለው እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የእርሱን ትምህርት የተከተሉ መንኪዮሳውያን ተባሉ:: አቡርዮስ «በኩር ያለ ፈቃዱ ታሞ ሞተ» ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ትምህርቱን የተከተሉ አቡርዮሳውያን ተባሉ:: አፍቲክስ «ሥጋውን ከሰማይ አወረደ» ያለው እርሱ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የአፍቲክስን ትምህርት የተከተሉት አፍቲክሳውያን [አወጣኪውያን] ተባሉ:: አርሰሲና መናፍቃን «በሥጋና በነፍስ ወደ ሲኦል ወረደ» ያሉት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የእርሱን ትምህርት የተከተሉትም አርሲሳውያን ተባሉ:: አርሲስ [አርሲሳውያን] ማለት ከሐድያን ማለት ነውና አስቀድመን ከዘከርናቸው [ከጠራናቸው] እንደ አንዱ የሰው ስም አይደለም ልዩኑ– «ትስብእቱ ከመለኮቱ ያንሳል» ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የእር ሱንም ትምህርት የተከተሉ ልዮናውያን ተባሉ:: የኬልቄዶን ማኅበር «የመለኮት ሥራ ለመለኮት ይገባል፡ የትስብእት ሥራ ለትስብእት ይገባል» ብለው ለኹለት ባሕርይና ለኹለት ሥርዐት የከፈሉት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ዳግመኛም «አንዱ ተአምር ያደርጋል፡ አንዱም ሕማም ይቀበላል::» ይላሉ:: ትምህርታቸውን የተከተሉት «መለካውያን» ተባሉ፡ የሃይማኖታቸው ፍላጐት በንጉሥ ዘንድ ሆኗልና:: ንጉሡ መርቅያን የልዮንን ሃይማኖት

42. እስመ በፈቃዱ ወበሥምረተ አቡሁ መንፈስ ቅዱስ መጽአ ወአድኅነነ፡
በእሱ ፈቃድ በአባቱ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ መጥቶ አዳነን:: የማክሰኞ ውዳሴ ማርያም::



www.ethiopianorthodox.org

ወዷልና:: ስለዚህ በኒቅያ ከተሰበሰቡት ከ፫፻፲፰ ማኅበር የበለጠች ትሆን ዘንድ ለረከሰች ሃይማኖቱ ክብር ፈልጎ ፲፻፴፯ ኢጲስ ቆጶሳትን ሰበሰበ ዘንድ ለረከሰች ሃይማኖቱ ክብር ፈልጎ ... ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በእነርሱ ይመከብቸዋልና የክሕደት መምህር በስሙ ያሳሳታቸው ሁሉም ከሐድያን ይባላሉ::

እኛ ግን ከእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ዐጸድ የሚያስወጡ መምህራንን አንፈልግም:: ዳግመኛም በስማቸው መጠራትን አንፈልግም:: መምህራችን ክርስቶስ:- «ለራሳችሁ መምህር አትሹሙ፤ መምህራችሁ አንዱ ክርስቶስ ነው::» ይለናልና::[43] ስለዚህም ክርስቶስ ተብሎ እንደ ተጠራ እኛም ክርስቲያን እንባላለን:: መሲሕ እንደ ተባለ መሲሐውያን እንባላለን:: ናዝራዊ እንደ ተባለ ናዝራውያን እንባላለን:: የእነዚህ የሦስቱ መጠሪያዎች ትርጉም በአንድ [በአንድነት] «የተቀባና የተቀቡ» ተብሎ ይተረጐማል::

ከእነዚህም መናፍቃን «የወልድ ሥጋ በአብ ቀኝ አልተቀመጠም» የሚሉ አሉ:: ሰነፎች ምክር ያጣችሁ ሆይ! «ሥጋው በአብ ቀኝ አልተቀመጠም» ትላላችሁን? ስለምን ዳዊት «እግዚአብሔር ጌታዬን ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስከአደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው..?[44] አብ «በቀኜ ተቀመጥ» ያለው ስለ ወልድ መለኮት ነው ትላላችሁን? የወልድ መለኮት በአባቱ ቀኝ ለመቀመጥ መቼ ተስማማ? የሰው ልጅ ለመሆን ቢፈልግም እግዚአብሔርነቱን አልተወም:: በድንግል ማሕፀን ሕፃን በሆነም ጊዜ በጽርሐ አርያም ከአባቱ ጋር ሸማግሌ [ዘመናትን የሚያስረጅ] ነው:: ገሊላዊት እናቱም በክንዶቿ በታቀፈችው ጊዜ በመለኮቱ ክብር ከሰማያዊ አባቱ ጋር በኪሩቤል ሠረገላ ላይ ነበር:: በሕፃናት ሥርዐት የጡቶቿን ወተት በጠባም ጊዜ በአምላክ ሕግ ከአባቱ ጋር ህልው ነው:: በዮርዳኖስ ውስጥ ለመጠመቅ እርቃኑን ሲገለጥ በላዩ ላይም በብርሃን ድንኳኖችና በመብረቅ ክብር የተጨመረበት በደመና መጋረጃዎች ይሰወራል:: አብ በዮርዳኖስ ወንዝ ምስክር ሲሆን መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል[45] ያን ጊዜ ያለ ሥጋው ከእነርሱ ጋር በመገለጣቸው በታ [በሉዐላዊ መንበራቸው ጽርሐ አርያም] እየተሰለሰ [እየተመሰገነ] በጭፍሮች ተገርፎ በጲላጦስ አደባባይ ፊት በቆመም ጊዜ በሰማያ

43. ማቴ. ፳፫:፰::
44. መዝ. ፻፱:፩::
45. የመጀመሪያው ጥናቱ ቅጅ ወመንፈስ ቅዱስሂ እንዘ ይሔውጽ በርእየተ ርግብ ይላል:: M, EMML I-ጽ, EMML IX ይረውጽ ይላል:: የተረቡት ቃላት ሐሳቡን በሚገባ ስለሚያገልጡት በምስክር ሲታይ የሚለው ቃል ተመራጭ ሆኗል::





ሰማያት የሚካኤል ሰራዊት በፍርሀትና የገብርኤል ሰራዊት በመንቀጥቀጥ ከፊቱ ቆመው በሰማያዊ አባቱ ቀኝ [ያለ፣ የሚኖር] ነው:: የካህናት አለቆች የሕዝብ ጻፎች በመንገድ የሚተላለፉ መንገደኞች ሲሰድቡትና ሲያንቋጥጡት ከላይ ኪሩቤል እያመሰገኑት ሱራፌል እየቀደሱት ህልው ነው:: በቅንዋተ መስቀል ተቸንክሮ በመስቀል ላይ እጆቹንም በዘረጋ ጊዜ መለኮቱ ሳይነካ እንደ አብና መንፈስ ቅዱስ ህልውና [አኗኗር] ያለ የሚኖር ነው:: በሥጋ ሞትን በተቀበለ ጊዜ መለኮቱ በመቃብር ውስጥ ነፍስ ከተለየው ሥጋ ጋር፤ ያለ ነፍስ፤ በሲኦል ውስጥም ከነፍሱ ጋር ያለ ሥጋ፤ በአባቱም ቀኝ ያለ ነፍሱና ሥጋው ህልው ነው:: በትንሣኤውም ጊዜ ነፍሱን ወደ ሥጋው ማኅደር በመለሳት ጊዜ አስቀድሞ ለአይሁድ:- «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፤ ከሦስት ቀን በኋላ አነሣዋለሁ::» እንዳላቸው አይሁድ ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፣ አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት:: እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር:: ስለዚህ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ አሰቡና መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ::»[46]

ዳግመኛ «ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም:: ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ:: ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ::»[47] አለ:: ዳዊትም «አቤቱ፥ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ፤ አንተና የመቅደስህ ታቦት» አለ::[48] ነቢዩ ስለምን «አቤቱ፥ አንተና የመቅደስህ ታቦት ተነሥ» አለ? ይህችውም የመቅደሱ ታቦት ከሆነች ከዳዊት ዘር ከነሳው ሥጋ ጋር በመለኮቱ ኀይል ከእንቅልፍ ሞት ከመነሣት በስተቀር የእግዚአብሔር መነሣቱ ምንድን ነው? ምድራዊ ድካም፥ ወዝ፥ ረኀብ፥ መጠማት፣ ደዌና ሕማም ከሌለባት ከጽርሐ አርያም በስተቀር ዕረፍት ምንድን ነው? «አቤቱ! ወደ ዕረፍትህ ተነሥ» የሚለው ቃል የሞት ሥልጣን አይቀርብህም፥ ሲቃልያን አይደርሱብህም ወደሚለው ይተረጐማል:: «አንተ እና የመቅደስህ ታቦት» የሚለው ቃል ለመለኮትህ ኀይል ማደሪያ የሆነች ሥጋዊህና «አንተ» እግዚአብሔር ወደሚለው ይተረጐማል::

እነሆ የመዝሙሩ ቃል ትስብእትን ስጊት ከመለኮቱ ጋር እስከ

46. ዮሐ. ፪:፲፱-፳፪::
47. ዮሐ. ፲:፲፯-፲፰::
48. መዝ. ፻፴፩:፰::



www.ethiopianorthodox.org

ጽርሐ አርያም ከፍ ያደርጋታል። መለኮት ትስብእት [ተዋሕዶ] ግን በመዘምራን ዘንድ በታቦት ተመስለች፡ አቤቱ፥ አንተና የመቅደስህ ታቦት ተነሡ» ይላሉና። በሰሎሞን ዘንድም መሸከሚያ ነው፡ ንጉሥ ሰሎሞን «መሸከሚያ ምሰሶዋን ከሊባኖስ እንጨት ለራሱ አሠራ» ይላልና።[49] የመድኃኒታችን የትስብእቱ ምሰሶዎች አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብና የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት ናቸው። የቤት ማእዘን በአራት ማእዘን እንደሚጸና የእግዚአብሔር የኪዳኑ ትስብእት በአብርሃም እምነት፣ በይስሐቅ ጽንዓት፣ በያዕቆብ ምስጋናና በዳዊት የአምልኮት መልክ በአራቱ የማእዘን ምሰሶዎች ጸንቶአል።

ስለዚህም ወንጌላዊው፦ «የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ» አለ።[50] «የእግዚአብሔር ኪዳን ባለበት ጀምሮ የባዕዳን ትውልድን አስከተሎ ይህን ቃል በመከተል መቀመጫውን ሐምራዊ ማምጃ ንጹሕ አደረገ» አለ፡ የድንግል ማርያም የሥጋዋ ጽዳት እንደ ሐምራዊ ማምጃ ንጹሕ ነውና። የሔዋን የበደሏ አሚከላና የአዳም የኃጢአት እሾኽ በውስጧ አልበቀለምና። ከዚህም በኋላ ውስጡ በሰንፔር ድንጋይ የተነጠፈ ነው» አለ። የሰንፔር ድንጋይ በፍሕም ብዛት ይቀላልና ይህም የመለኮቱ አርአያ [ምሳሌ] ነው።

ሕዝቅኤል እንዳለው፦ «በእነዚህ የሰማይ እንስሳት በራሳቸው ላይ፣ በላዩ ላይም እንደ ሰንፔር ዕንቍ ያለ የበረድ ኅብር የተዘረጋ ነው።»[51] የጸናች አራት የእስራኤል ልጆች ከእግሩ በታች ከጡብ እንደተሠራ ሰንፔር ያለ ነገር ተመለከቱ፡ ቤተ መቅደስም ትስብእት ትባላለች። «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱ፡ በሦስት ቀን አነሣዋለሁ፡ ይላልና። ወንጌላው፦ እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይነግራቸው ነበር።» አለ።[52] መጋረጃም ትስብእት ትባላለች። ጳውሎስ፣ «በሥጋው መጋረጃነት በድንገት የሕይወትንና የጽድቅ መንገድን አድሶልናልና።» ይላል።[53] ታቦት ትስብእት ትባላለች። በመዘምራን አፍ የመለኮት ሙዳይ ስለሆነች፥ በክብር ከእርሱ ሳታንስ በአብ ቀኝ ተቀምጣለችና። በተዋሕዶ እንጂ በመንታነት አይደለም። በሥጋ እግሮች በዓለም ውስጥ እግዚአብሔር ስለ ተመላለሰ ትስብእት መሸከሚያ ትባላለች። በኪሩቤል ሠረገላ ስለ

49. መኃ. ፫፥፱።
50. ማቴ. ፩፥፩
51. ሕዝ. ፲፥፩።
52. ዮሐ. ፪፥፳፩።
53. ዕብ. ፲፥፲፱-፳።





ተቀመጠች ከእርሱ በክብር አታንስም። የኀይል ቤት ስለሆነች ከእርሱ በብርሃንና በጸዳል ስላልጕደለች ትስብእት ቤተ መቅደስ ትባላለች፡ በደመና እሳት ከፍ ብላ የሰውና የመላእክት አእምሮ ወደ ማይደርስበት ወደ ጽርሐ አርያም ገብታለችና። ለማይታይ ኀይል መሰወሪያ ስለሆነች በአምልኮት መልክ [ክብር] ከእርሱ ስለማታንስ ትስብእትም መጋረጃ ትባላለች፡ በሰማየ ሰማያት ሲያዩት የሚያስፈራ የእሳት መጋረጃ ተዘርግቶላታልና።

«ጌታ ጌታዬን ጠላቶችን የእግርህ መረገጫ እስከ ማደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ» ወዳለው ወደ ዳዊት የቃሉ ትርጉም እንግባ። አስቀድሞ በሰማያት መንበር ያልነበረ የወልድ ትስብእት በመንበሩ አስቀድሞ ይቀመጥ ዘንድ ስለ ወልድ ትስብእት አብ ይህን አለ። አስቀድሞ የተቀመጠውን ግን በኋላ ተቀመጥ አይለውምና፡ የእግዚአብሔር ልጅ የመለኮቱ ህልውና የነበረ ነውና። ከአባቱ ህልውና መቼም አልተለየም፤ በወላጁ ቀኝ ለዘላለም ይኖራል። ስለ መለኮቱም ትስብእት ግን ከልደቱ ዕለት እስከ ዕድገቱ ፍጻሜ ድረስ የሕፃናትን ሥርዐት [ሕግ ጠባዓያዊ] ፈጸመ። ከዕድገቱ ፍጻሜም እስከ ስቅለቱ ዕለት የጉልምስና ሕግን ከኃጢአት ብቻ በስተቀር ሳያተርፍ ፈጸመ። በስቅለቱም ዕለት የአባቱን ትእዛዝ ፈጸመ። ለምእመናን ክብር ይሰጥ ዘንድ መከራን ለበሰ [መዋረድን]። መከራን፣ ጻዕርን፣ ሥቃይን፣ ኀፍረትን ለሚታገሡ ሰማዕታት ፍሊጋውን [አርያኑን] ይተው ዘንድ ለብዙኃንም ቤዛ ይሆን ዘንድ የመስቀልን ኀፍረት ታገሡ። ኢያፍሳሊም የቀዳችለትን የሞት ጽዋ ጠጣ። በሰው ሕግ ላይ ሠልጥኖ በመለኮቱ ኀይል ተነሣ። በተነሣበት በእሑድ ንጋትም አስቀድሞ ለመግደላዊት ማርያም ታየ። እርሱ ጌታ ኢየሱስ እንደሆነ ባወቀችው ጊዜ እግሩን ትስመው ዘንድ ወደደች። በመንገድ ባገኘችው ጊዜ «ወደ አባቴ ገና ዐላረግሁምና አትንኪኝ።» አላት።[54] ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ እርሱን መንካት እንዴት ይቻላል? ከሰው ልጅ ወደ ሰማይ ማረግ የሚችል የለምና።

ስለምን አትንኪኝ አላት? ዘማዊቷ ሴት፥ በፀጉሮቿ የዳሰሰችው፡ በእንባዋ እግሮቹን ያጠበችው፣ እግሮቹን የዳሰሰችው እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን? ደምስ ይፈሳት የነበረችው ሴት የዳሰሰችው በመለኮቱ ኀይል ደሟን ያደረቀላት እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን?

54. ዮሐ. ፳፥፲፯።



www.ethiopianorthodox.org

ጸሐፍት ፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርቱን፡- «መምህራችሁ ለምን ከኃጢአተኞችና ከቀራጮች ጋር ይቀመጣል፡፡» ብለው እስከ ሚያንጉራጉሩ ድረስ ዘወትር ከኀጢአተኞች ጋር የሚቀመጥ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን?[55] በምራቁ ወደ ምድር ትፍ ብሎ ዐይኖቹን ቀብቶ አስቀድሞ ዐይን ሳልነበረው ሰው ዐይን የፈጠረ እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን? በብረት ዘንግ ራሱን መትተው በፊቱ ላይ ርኩስ ምራቅን የተፉበት እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን? ከእርሷ ስባት አጋንንትን ያስወጣላትን ማርያም መግደላዊትን ዘወትር የሚወዳት እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን?

ከትንሣኤው በኋላ ስለምን አርቋት «አትንኪኝ» አላት? ትርጉሙን እንናገር፡ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ በትስብእቱ መከራ የአባቱን ፈቃድ ፈጸመ፡፡ ወንጌላዊው እንደ ተናገረው ሐሞቱን ጠጥቶ «ሁሉ ተፈጸመ» አለ፡፡[56] በትንሣኤውም ባለፈው የትስብእት መከራ እና በጌትነቱ በሚመጣበት የክብር ኃይል [ትንሣኤ ዘጉባኤ] መካከል ያለውን ልዩነት ዐሳየ፡፡

እንደ ንጉሥ ልጅ በመንግሥት መንበር ከመቀመጡ በፊት የአባቱ አሽከሮች እንደ ወንድምና ጓደኛ ይቀልዱበታል፡፡ እርሱም ራሱን ከእነርሱ እንደ አንዱ አድርጐ በፍቅርና በትሕትና ይቀበላቸዋል፡፡ በአባቱ መንበር እንደ ተቀመጠም በፊቱ ይሰግዳሉ፡፡ ማንም እንዳይቀርበው የሚያስገቡ ጠባቂዎች በፊቱ ቆመው እንዳይነኩት በፊቱ ይሰግዳሉ፡፡ ከእርሱ ጋር ከሚጠጉ፡ ንጉሥም ከሚቀመጥባቸው [ከሚቀርባቸው] በስተቀር እርሱን መንካት የሚችል የለም፡፡ በመሐልየ መሐልይ «ባለ ብር ዝንጉርጉር ግንብ የሆነ የወርቅ ጠልሰም እናደርግልሻለን፡ ንጉሡ በማዕዱ ሳለ፡፡» እንደ ተባለው፡፡[57] ይህም ማለት በአባቱ ህልውና በራሱ ህልውና ከዓለም አስቀድሞ የነበረ ንጉሥ በሥጋዌው ከንጉሥ ዳዊት ዘር ኢየሱስ ክርስቶስ በማዕዱ እስከሚቀመጥ ድረስ ቀሳውስትንና ኢጲስ ቆጶሳትን ለአንቺ ይሾማሉ ማለት ነው፡ የንጉሥ ሠራዊት መቅረብ እንደ ማይችሉ በእርሱ ዘንድ ቀርበው ሥልጣንን አይቀበሉምና፡፡ እንዲሁ ሕዝባውያን ወደ ጽንሐው ምስጢር ቀርበው ሥጋ ወደሙን ለመዳሰስ አይችሉም፡፡ ስለዚህም መግደላዊት ማርያምን «አትንኪኝ» አላት፡፡ ሥጋውን ካለፈው የትስብእት መከራ ሥጋውን ከልክሏልና በተንሥኦም ጊዜ ከመለኮቱ ክብር አሳተፋት፡፡

55. ማቴ. ፱፥፲-፲፩::
56. ዮሐ. ፲፱፥፴::
57. መኃ. ፩፥፲፩::





የንጉሡ ቤት ጠባቂዎች ንጉሡን ይቀርቡትና ይነኩት ዘንድ እንደ ሚገባቸው እንዲሁ ኢጲስ ቆጶሳትም [ካህናትም] የክርስቶስን ቍርባን ሥጋውን ይነኩ ዘንድና ጣቶቻቸውን ወደ መለኮቱ ደም ውስጥ ይነክሩ ዘንድ ይገባቸዋል፡ በተነሣባት በዕለተ እሑድ ሐዋርያቱን አስቀድሞ አሠልጥኖአቸዋልና፡፡ [ሥልጣን ሠጥቶአቸዋል] «ለምን ልባችሁ ውስጥ ሐሳብ ይገባል፡ ምንስ ያስደነግጣችኋል? እኔ እንደ ሆንኩ እግሮቼንና እጆቼን ዳሳችሁ ዕዩኝ፡፡» አላቸው፡፡[58] መግደላዊት ማርያምን በትንሣኤው ጊጋት «አትንኪኝ» አላት፡፡ ሐዋርያቱንም በትንሣኤው ማግሥት «ዳሱኝ» አላቸው፡፡ መግደላዊት ማርያምን ትታቀብ ዘንድ በምእመናንና በምእመናት ሥርዐት ጠቀሳት፡፡ ሐዋርያትን ለምስጢር ክህነት አርአያ ይሆኑ ዘንድ ሥጋውን ይዳስሱት ዘንድ አሠለጠናቸው፡፡

በዚህም ከትንሣኤው አስቀድሞ መለኮት የትስብእትን መከራ እንደ ተሳፈተ ዝንጉው ሆይ! አስተውለህ ዕወቅ፡፡ ከትንሣኤውም በኋላ ግን ትስብእት የመለኮትን ክብር እንደ ተሳተፈ ዕወቅ፡፡ በዕሪና ሳይከፈል በተዋሕዶ ሳይለወጥ ነግሦ ታየ፡፡ ለመጀመሪያው ሄሮድስና ለኹለተኛው ሄሮድስ ምድራዊ መንግሥታቸው እርሱ እንደ ሚወስድ መሰላቸው፡፡ ቀዳማዊው ሄሮድስም ከተገደለት መካከል ያገኘው ዘንድ እርሱን ፈልጎ ሕፃናትን ገደላቸው፡፡ ኹለተኛው ሄሮድስ በተሰቀለበት ዕለት አክፋፍቶ ወደ ጲላጦስ ዘንድ እርሱ መንግሥቱን እንደ ሚፈልግ ታዝቦት በእርሱ ላይ ሲሳለቅ ይቅር ያለውን ቀይ ከለሜዳ አልብሶ ላከው፡፡ ስለዚህ ጲላጦስ ጌታ ኢየሱስን «አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን? ብሎ ጠየቀው፡፡ እርሱም መልሶ አንተ የምትለው ከልብህ ነውን ወይስ ሌላ ሰው የነገረህን? አለው፡፡ ጲላጦስም መልሶ እኔ አይሁዳዊ ነኝን? ሕዝብህና የካህናት አለቆች ወደ እኔ አሳልፈው የሰጡህ አይደለምን? አለው፡፡ ጌታ ኢየሱስም፡- መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፡፡ መንግሥቴ ከዚህ ዓለም ቢሆን ግን አሽከሮቼ አይሁድ ከአንተ ዘንድ አሳልፈው እንዳይሰጡኝ በተዋጉልኝ ነበር፡፡» አለው፡፡[59]

የእግዚአብሔር ልጅ የአባቱን የዳዊት መንግሥትን ንቆት እስከ ትንሣኤው ድረስ በችግር [በሕማም] ተቀመጠ፡፡ ከትንሣኤው በኋላ በመለኮት ክብር ከልሏት በአባቱ ቀኝ አስቀመጣት፡፡ ከዚህም በኋላ ከዳዊት ዘር የገሊላ

58. ሉቃ. ፳፬፥፴፱ ዮሐ. ፳፥፳-፳፯::
59. ዮሐ. ፲፰፥፴፫-፴፮::



www.ethiopianorthodox.org

መንግሥት ተወገደች። ያዕቆብ «በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፡ የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፡ ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ የአሕዛብ ተስፋቸው ነው።» እንዳለ።[60] «ከይሁዳ ገዥ አይጠፋም» የተባለው ከልጁ ከተወለደው ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር ምንድን ነው? በሐዋርያት እጅ ለአሕዛብ ከተሰጠ ከእግዚአብሔር ልጅ ጸጋ ከወንጌል በስተቀር የአሕዛብ ተስፋ ምንድን ነው?

እኛ ግን ሐዋርያት ስለ ሰበሰቧት ስለ አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላም ዳግመኛ እንማልዳለን እንላለን። እነርሱም የአሕዛብ የሆነችው ያቺ ቤተ ክርስቲያን የተባረከች ናት ይሏታል። ሃይማኖታችንን በሃይማኖታቸው ላስማማ ላዋሐደ ለእግዚአብሔር ለዘላለም ምስጋና ይሁን። አሜን።

የሮማውያንን ትምህርት ያጠፋና እንደ ሰይጣን ለማሳት የሚጨነቅ እንደ ሌጌዎን አጋንንት ለማጣደፍ የሚተጋ ከግዮን [ወንዝ] ዳርቻ አሸዋ የሚበዛ የመርቅያን የስንፍና መምህር የልዮን ዘለፋ ተፈጸመ።

ከተተራረቡ ተራሮች መሠረትና ከማይንቀሳቀሱ ተራሮች ሚዛን የኃጢአት ክብደት የሚበልጥ ጊዮርጊስ አለ [ተናገረ]። ለእግዚአብሔር ለዘላለም ምስጋና ይሁን። አሜን።

60 ዘፍ. ፵፱፡ ፲





# ዋቢ መጻሕፍት


1. ሃይማኖተ አበው፣ ተስፋ ገብረሥላሴ፣ ማተሚያ ቤት፡ ፲፱፻፹፪ ዓ.ም፡ አዲስ አበባ።
2. መዝሙረ ዳዊት፡ ንባቡና ትርጓሜው፡ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ ፲፱፻፹፪ ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
3. መጽሐፈ አርጋኖን፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
4. መድሎተ አሚን፡ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፡ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት፡ ፲፱፻፺፬ ዓ.ም፡ አዲስ አበባ።
5. መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፡ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡ ፲፱፻፵፰ ዓ.ም፡ አዲስ አበባ።
6. ርቱዕ ሃይማኖት፡ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ምርምር መጽሔት፣ ቅጽ ፩፣ ፲፱፻፺፫ ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
7. ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡ ፲፱፻፵፪ ዓ.ም፡ አዲስ አበባ።
8. ሺሕ ዓመትና ሐሳዊ መሲህ፡ ስቡሕ አዳምጤ፡ ጥቁር አባይ ማተሚያ ቤት፡ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም፡ አዲስ አበባ።
9. ባሕረ ሐሳብ፣ ጌታቸው ኃይሌ፡ ፲፱፻፺፫ ዓ.ም፡ ኮሌጅቪል /ሚኒሶታ/።
10. ተአምረ ማርያም፣ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም፡ አዲስ አበባ።
11. ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት፣ ሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ፣ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
12. ወንጌል ቅዱስ ንባብና ትርጓሜው፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡ ፲፱፺፰ ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
13. ዐማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት፡ ሥርግው ሀብለ ሥላሴ፡ /ያልታተመ/
14. የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ፡ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት፡ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም፡ አዲስ አበባ።




www.ethiopianorthodox.org

15. የትዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባብ ከነትርጓሜው፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት፣ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

16. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊትና መንፈሳዊ ሕይወት መግቢያ /ትርጉም/፣ መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሳሁን፣ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

17. የአባ ባሕርይ ድርሰቶች፣ ጌታቸው ኃይሌ፣ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

18. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ አባ ጎርጎርዮስ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት፣ ፲፱፻፸፫ ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

19. የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች፣ ዲ/ን ዳንኤል ክብረት፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

20. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ አባ ጎርጎርዮስ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት ፲፱፻፺፩ ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

21. ደቂቀ እስጢፋኖስ /ትርጉም/፣ ጌታቸው ኃይሌ፣ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም፣ ኮሌጅቪል /ሚኒሶታ/።

22. ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ከሐይቅ እስጢፋኖስ የተገለበጠ።

23. Amsalu Aklilu, Survey of Ethiopian literature 1974 (Unpublished)

24. Cerulli, Il Libro Ethiopica dei Mircoll dl Maria (Rome 1943).

25. Conti Rossini "Due capital del 17 brodel mistern dierly- orgis da sagla" raveyna distudi Ethiopici Vol. VII /1999/.

24. Conti Rossni, Il Libro dellu lice del Negus Zaraya' Cob uscos,, Aeth, t, 51 (Louvain, 1955).

25. Getachew Haile; Fekkare Haymanot or the Faith of Abba Giyorgis saglawl, in LEMUSE ON: REVUE D E TUDES ORIENTALES. 1981

26. Sergew Hable Sellassie, Giyorgis Zegasitcha, Teacher and Author, The Jornal of education Vol (1975).

27. Taddesse Tamirt; Church and State; Oxford University press. 1972

28. Young blood, Ronald F. Bible Concordance, THOMAS NELSON Publishers; Nashville,1993.


www.ethiopianorthodox.org